አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና

በ

ሰይድ ይማም

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ሰኔ፣2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሰይድ ይማም

አማካሪዎች

አቶ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ሙሐመድ አሊ (ዶ/ር)

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)

ሰኔ፣ 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

«የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና» በሚል ርዕስ በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በሰይድ ይማም በሰኔ ወር 2018 ዓ.ም. የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪዎች፡- ሙሐመድ አሊ (ዶ/ር) **ፊርማ** .....

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር) **ፊርማ** .....

የውጪ ፈታኝ፡- ጌቱ ገላዬ (ዶ/ር) **ፊርማ** .....

የውስጥ ፈታኝ፡- መሥፍን ፈቃዴ (ዶ/ር) **ፊርማ** .....

ማረጋገጫ

የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብከኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ፣ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም …….. ፊርማ …….. ቀን ……..

ምስጋና

በቅድሚያ በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች በመስክ በቆየሁባቸው ጊዜያት አስፈላጊ የኾኑ መረጃዎችን በመስጠት ቀና ትብብር ላደረጋችሁልኝ የቃለ መጠይቁና የቡድን ተኮር ውይይቱ ተሣታፊዎች በሙሉ አመሰግናችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ያለ እናንተ ድጋፍ ይህ ጥናት ከፍጻሜ ላይ አይደርስም ነበርና ነው፡፡

በሕይወት በነበሩበት ወቅት ካለባቸው የማስተማር ሥራና ከልዩ ልዩ ኃላፊነቶች በተጨማሪ ይህንን ጥናት ሳይታክቱ በተደጋጋሚ በማረምና በማስተካከል ክፍ ያለ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ ጽሑፌ እዚህ ደረጃ ላይ እንድደርስ ላደረጉት አስተዋፅኦ ለዶክተር ሙሐመድ አሊና ለዶክተር የወንድወሰን አውላቸው ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ የእነርሱ የዕለት ተዕለት ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ባይኖር ኖሮ ጥናቱ የመጨረሻው ደረጃ ላይ አይደርስም ነበር፡፡

የትምህርት ዕድል የሰጡኝና የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉልኝ የአዲስ አበባና የወሎ ዩኒቨርሲቲዎች በያሉበት ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህራንም ለዚህ ጥናት የነበራቸው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ስለኾነ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በትልመ ጥናቱ ተቋቁሞ ወቅት ፈታኞቼ የነበራችሁ ዶክተር ዓለሙ ካሳዬና ዶክተር ስለሺ አባተ ፈታኝ ብቻ ሳትኾኑ በቀጣይ ለማከናውናቸው የጥናቱ ተግባራት ትክክለኛ የኾኑ አቅጣጫዎችን እንዲከተል ስላደረጋችሁኝ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡ በደረጃ ተቋቁሞ ወቅትም ቢኾን ረጅም ጊዜ ወስዳችሁ በእያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ የኾኑ አስተያየቶችን ለሰጣችሁኝ ዶክተር ዓለሙ ካሳዬና ዶክተር የወንድወሰን አውላቸው ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ የዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፌን ያለመታከት አንብበው እጅግ በጣም አስተማሪ የሆኑ አስተያየቶችን ለሰጡኝ፣ በተቋቁሞ ዕለትም ቢሆን ተዝናኖትን በተላበሰ ሁኔታ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና አስተያየቶችን በመስጠት ለወደፊት ሕይወቴ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ላስተማሩኝ ለዶክተር ጌቱ ገላዬ (የውጭ ፈታኝ) እና ለዶክተር መሥፍን ፈቃዴ (የውስጥ ፈታኝ) ፈጣሪ ከእነቤተሰቦቻቸው ዕድሜ ይስጣቸው እላለሁ፡፡

ለጥናቴ የሚኾኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ ቦረና ሄጄ በየወረዳዎቹ በተዘዋወርኩበት ወቅት ለሥራዬ ከሚረዱኝ ሰዎች ጋር በማገናኘትና ሌሎች አስፈላጊ የኾኑ ሰነዶችን ሁሉ በማሟላት ትብብር ላደረጋችሁልኝ ለአቶ ሰይድ ጎቸል የቦረና ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ ለወ/ሮ ዓይናለም በጸና የወግዲ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊና ለወ/ሮ ከረን ሐሰን እንድሪስ የከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከልቤ አመሰግናችኋለሁ፡፡ በተለይ የወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የባህል ልማት ተጠሪ የኾኑት አቶ ይማም አብዱ አንድም ሳይሠሥቱ በወረቀትም ኾነ በSoft copy ላይ ያሉትን መረጃዎች ስለሰጡኝ በሕይወት ዘመኔ በሙሉ ሳመሰግናቸው እኖራለሁ፡፡

ማውጫ

ርእስ ገጽ

ምስጋና I

ማውጫ ----------II

የፎቶግራፎች ማውጫ ----------VI

መዳዬ ቃላት ----------VII

አጠቃሎ x

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ----------1

1.1. የጥናቱ ዳራ ----------1
1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች ----------4
1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ----------5
1.4. የምርምሩ ጥያቄዎች ----------5
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች ----------6
1.6. የጥናቱ ወሰን ----------7
1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ----------7
1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ----------10
1.9. አጥኚው የተከተላቸው የሥነ ምግባር መርሆዎች ----------11

ምዕራፍ ኹለት፡- የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ የጥናቱ አዋሳኝ ወረዳዎች መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችና ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች ----------13

2.1. የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን መልክዓ ምድራዊ ገጽታና ማኅበረ ባህላዊ ዳራ በአጭሩ 14

2.1.1. የቦረና፣ የወግዲና የከለላ ወረዳዎች መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች ----------15

2.1.2. የቦረና፣ የወግዲና የከለላ ወረዳዎች ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች ----------20

ምዕራፍ ሦስት፡- ክለሳ ድርሳን ----------35

3.1. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ----------35

3.2. ጽንሰ ሐሳባዊ ቅኝት ----------52

3.2.1. ቃል ግጥም----------52

3.2.1.1. የቃል ግጥም ባሕርያት ----------55

3.2.1.2. የቃል ግጥም ማቅረቢያ ስልቶች ----------56

3.2.1.3. የቃል ግጥም ዓይነቶች ----------58
3.2.1.4. የክዋኔ ዐውድ----------61
3.2.1.5. የቃል ግጥሞች ፋይዳ ----------65
3.2.1.6. የቃል ግጥሞችና የክዋኔ አጋጣሚዎች ለውጥና ቀጣይነት ----------67
3.2.1.6.1. ክዋኔ ----------67
3.2.1.6.2. ለውጥና ቀጣይነት ----------70
3.2.1.6.2.1. ለውጥ ----------70
3.2.1.6.2.2 ቀጣይነት ----------72
3.3. የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፎች ----------72
3.3.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ ----------73
3.3.2. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ----------74
3.3.3. ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ----------75
ምዕራፍ አራት፡- የጥናቱ ዘዴ ----------77
4.1. የጥናቱ ዓይነት ----------77
4.2. የጥናቱ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ----------77
4.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ----------79
4.3.1. ካልኣይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ----------80
4.3.2. ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ----------81
4.3.2.1. ምልከታ ----------81
4.3.2.2. ቃለ መጠይቅ ----------85
4.3.2.3. ቡድን ተኮር ውይይት ----------87
4.4. የመረጀ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ----------88
4.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዐውዶች ----------89
መረጃ ትንተና ----------95
ምዕራፍ አምስት፡- የቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች ----------95
5.1. ምርታማነትን ለማሳደግ የሚውሉ ግብዓቶች ----------95
5.1.1. የኬሚካል ማዳበሪያ ----------96
5.1.2. ብስባሽ (Compost) ----------99
5.1.3. ፀረ ዐረም ----------102
5.1.4. ዕርከን ሥራ ----------105
5.2. የግብርና የሥራ ዓይነቶች ----------109

5.2.1. የእርሻ ወቅት ----------109
5.2.2. የዐረም ወቅት ----------114
5.2.3. የአጨዳ ወቅት ----------120
5.2.4. የውቂያ ወቅት ----------123
5.3. የማኅበረሰቡ የሕይወት ሽግግር ሂደቶች ----------127
5.3.1. የኩርድና (የልጃገረድነት) ዕድሜ ----------128
5.3.1.1. ተበቺሳ ----------128
5.3.1.2. የተለያዩ የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች ----------132
5.3.1.3. ክብረ በዓላት ----------137
5.3.1.4. **በሰብል መጠበቂያ ቦታ የምልልስ ግጥሞች**----------141
5.3.2. በሰርግ ዕለት የሚኖረው ሥርዓት ----------145
5.3.2.1. ሙሽራውና ዐጃበዎቹ በወላጆቹ ቤት ባለው ሥርዓትና በጉዞ ወቅት ------145
5.3.2.2. ሙሽራዋ በሰርጓ ዕለትና ከቤተሰቦቿ የስንብት ጊዜ ----------150
5.3.3. የቀብር ሥርዓት----------166
5.3.3.1. የእናት ለቅሶ ----------167
5.3.3.2 የአባት ለቅሶ ----------168
5.3.3.3. የልጅ ለቅሶ ----------169
5.3.3.4. የወንድም ለቅሶ ----------170
5.3.3.5. የእኅት ለቅሶ ----------171
ምዕራፍ ስድስት፡- የቃል ግጥሞች የዘውግ ምደባ ----------173
6.1. የግብርና ሥራ ቃል ግጥሞች ----------173
6.2. የሰርግ ቃል ግጥሞች ----------181
6.3. የሙሾ ቃል ግጥሞች ----------189
6.4. የሆታ ቃል ግጥሞች ----------194
6.5. የቀረርቶ ቃል ግጥሞች ----------199
6.6. የፉከራ ቃል ግጥሞች ----------203
ምዕራፍ ሰባት፡- የቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና ----------209
7.1. የሥራ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና ----------209
7.1.1. የሙገሳና የእርካታ ቃል ግጥሞች ----------209
7.1.2. የትችት ቃል ግጥሞች ----------216
7.1.3. **ፈጣሪን እና ባለሥልጣንን መማጸን የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞች** ----------223

7.1.4. **ጠንክሮ የመሥራትን** ተገቢነት የሚያመላክቱ ቃል ግጥሞች ----------226
7.2. የሕይወት ሽግግር **ሥርዓትን የሚያመለክቱ** ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና----------230
7.2.1. **በጉርምስና ዕድሜ** ውበትን ስለማድነቅ ----------231
7.2.2. የጠይም ሰው ፍቅር ኃያል ስለመኾኑ ----------236
7.2.3. በልጅነት ወቅት በተከሠተ ፍቅር ስለመጎዳት ----------238
7.2.4. የከንፈር ወዳጅን ቤተሰቦች ስለማወደስ ----------240
7.2.5. ጀግናን ማሞገስና ማድነቅ ----------243
7.2.6. በፍቅር አቻ ስላለመኾን ----------248
7.2.7. **ተፋቅሮ የመለያየት አስከፊነት** ----------250
7.2.8. ፈሪን ስለመተቸት ----------254
7.2.9. ነገረኛን ስለመተቸት ----------257
7.2.10. የጦር መሣሪያ አስፈላጊነት ----------259
7.2.11. **በሕይወት** ዘመን ስለሚያጋጥም ብሶት ----------261
ምዕራፍ ስምንት፡- የቃል ግጥሞቹ ፋይዳ ----------264
8.1. ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ ፋይዳ ----------264
8.2. የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን የማስተማር ፋይዳ ----------268
8.3. **የታታሪነትን** ጥቅም የማሳወቅ ፋይዳ ----------272
8.4. እኩይ የኾኑ ባሕርያትን የመግታት ፋይዳ ----------274
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ለውጥና ቀጣይነት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች አንጻር ----------287
9.1. የባህል ለውጥ በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች-------287
9.2. ቀጣይነት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች ----------294
ምዕራፍ ዐሥር፡- ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች ----------300
10.1. ማጠቃለያ ----------300
10.2. የይሁንታ ሐሳቦች ----------304
ማጣቀሻ ጽሑፎች ----------307
አባሪዎች
አባሪ አንድ፡- የመረጃ ሰጪዎች አጭር ግለታሪክ ----------318
አባሪ ሁለት፡- ከመስክ ተሰብስበው ያልተተነተኑ ቃል ግጥሞች ----------320
አባሪ ሦስት፡- ቃለ መጠይቅ ----------414
አባሪ አራት፡- ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች ----------417

የፎቶግራፎች ማውጫ

ፎቶግራፍ አንድ፡- በ09/01/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ የተካኼደውን ቡድን ተኮር ውይይት የሚያመለክት ----------27

ፎቶግራፍ ኹለት፡- በ20/05/2012 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ቀያፈር (35) በተባለው ቀበሌ ከዐውድማ ላይ ምርቱ እየተሰፈረ ወደጎተራ ከመግባቱ በፊት የቀረበውን አግማስ በጋራ በመመገብ ላይ እያለሁ----------86

ፎቶግራፍ ሦስት፡- በ05/01/2013 ዓ.ም በከለላ ወረዳ የተካኼደውን ቡድን ተኮር ውይይት የሚያመለክት ----------116

ፎቶግራፍ አራት፡- ልጃገረዶቹና ጎረምሳዎቹ በየጾታቸው ተለያይተው ሲጨፍሩ----------134

ፎቶግራፍ አምስት፡- በቦረና ወረዳ፣ ቀያፈር ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች የአንዱን የማሳ ላይ ዕርከን ሥራ ጨርሰው ወደሌላው ሲሸጋገሩ በነበሩበት ወቅት--------219

ፎቶግራፍ ስድስት፡- እኔና በደቦ ጤፍ ሲያጭዱ የነበሩ ወጣቶች ለምሳ የተዘጋጀውን ዳቦ በመመገብ ላይ በነበርንበት ወቅት----------220

ፎቶግራፍ ሰባት፡- መስከረም 07/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ሰቀ ሽንብራ ቀበሌ ወንድና ሴት ወጣቶች ወንፈል በተባለው የመረዳጃ ተግባር በጋራ ዐረም በሚያርሙበት ወቅት እኔም ለተወሰነ ጊዜ ተሳታፊ ነበርኩ----------222

ፎቶግራፍ ስምንት፡- አቶ አማን ሁሴን በ04/11/2012 ዓ.ም እርሻውን እያረሰ ባለበት ወቅት ሌሎች ኹለት ሰዎች ማረሻ ሰንጥቆ በኼደበት መስመር ላይ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በማንጠባጠብ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ሲያደርጉ----------224

ፎቶግራፍ ዘጠኝ፡- በቦረና ወረዳ ከአቶ ምትኩ አገኘሁ ጋር ጤፍ እያጨድኩ ባለኹበት ወቅት----------227

ፎቶግራፍ ዐሥር፡- በ04/11/2012 ዓ.ም በከለላ ወረዳ የማረስ ተግባር በማከናወን ላይ በነበርኩበት ወቅት----------229

ፎቶግራፍ ዐሥራ አንድ፡- በቦረና ወረዳ፣ ከቶ በተባለው ቀበሌ፣ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ በምታገባ ዕለት ሙሽራይቱ በበቅሎ፣ሙሽራውም በፈረስ ላይ ኾነው መንገድ በጀመሩበት ወቅት ነው----------246

ፎቶግራፍ ዐሥራ ሁለት፡- በ07/01/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ቡድን ተኮር ውይይት ሲካኼድ-------294

ሙዳዬ ቃላት

ዘውግ	ዘርፍ
ዱር ቤቴ	መኖሪያው ከመንደርና ከአምባ የራቀ፣ የተለየ ስፍራ፣ ዱር የኾነ
ዘየረ	ሰላም አለ፤ ሰላምታ ሰጠ፤ ቅዱስ የኾኑ ቦታዎችን ተሳለመ
ቤጋ	በጎኑ በኩል ሰፊ የኾነ ቀሚስ ሲኾን በሌሊት ወቅትም በድራብነት የሚያገለግል
ድንብል	ክብ ቅርጽ ያለው ሲኾን ከውስጥ በኩል ልሙጥ፣ ከውጭ ያለው
አካሉ	ደግሞ ኹለት ማዕዘን እንዲኖረው ተደርጎ ከብር ወይም ከኒኬል የሚሠራ የአንገት ጌጥ
አሸንክታብ	በረኻም ማተብ ላይ ከብርና ከሌሎችም ማዕድናት የተሠሩ ትናንሽ ጌጦች የተሰኩበት በአንገትና በአንድ ትከሻ ላይ ብቻ የሚጠለቅ፣ በኹለተኛው ትከሻ በኩል ከብብት ሥር እስከ ዳሌ የሚደርስ የሴቶች ጌጥ
ጋሜ	መኻሉ ተላጭቶ ዙሪያው የሚቀር የሴት ልጅ ጸጉር
ኮልኮሎ	ጎንና ጎኑ (ዙሪያውን) ተላጭቶ ከላይ የሚቀረው ክፍል የተሠራ የልጃገረዶች ባህላዊ የጸጉር አሠራር
አማጭ ረማጭ	ለሴት ባል ወይም ለወንድ ሚስት የሚያመጣ፣ የሚያገናኝና አማላጅ የኾነ ሰው
ምልኪ	አንድን ድርጊት ወይም አጋጣሚ የመጥፎ ወይም የጥሩ ምልክት አድርጎ የመውሰድ እምነት
ርክክብ	ሴት ልጅን ለሚስትነት ሕጋዊ በኾነ መንገድ በሽማግሌዎች የመቀበልና የመስጠት ክንውን
ፍጥጥም	የጋብቻ ውል የሚታሰርበት ወይም ፊርማ የሚፈረምበት ሥርዓት
ቀሪቦ	ጌሾ የሌለበት፣ ከገብስና ከብቅል ብቻ የሚዘጋጅ አልኮልነት የሌለው መጠጥ
ማጫ	ለሚስትነት ለተመረጠችዋ ልጅ የሚሰጥ ገንዘብ፣ ከብት፣ …..

ጀንዲ (ገርንዲ)	በቀድሞው ጊዜ ለመኝታ ምንጣፍ የሚያገለግል የተለፋ የበራ ወይም የላም ቆዳ
በሌ	በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በዳይና ተበዳይ መሃላ የሚገቡበት ሥርዓት
ርጥባንን	ርዳታ (የገንዘብ፣ የዕቃ)፣ የጠፋ ምትክ
አዝማች	ቢያንስ ሰማኒያ ሰዎችን ሊያስተናግድ የሚችል የድግስ ድጋፍ
ቆንጆ	ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ
ሚጊራጉራና ጭንቁርሳ	የስንደዶና የአክርማ ቀጨታ ወቅቶች
ቪዛ	አንድ ሰው ወደሌላ ሐገር እንድገባ፣ እንድተላለፍ ለመግለጽ በሚመለከተው ሐገር ባለሥልጣን የሚሰጥ ፈቃድ
መደንከል	በጭብጥ በጭብጥ የተቀመጠውን እኽል በአንድ ላይ በማድረግ በዕቅፍ ለመያዝ በሚያስችል ኹኔታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ
ነዶ	ከነብርዑ (ከነአገዳው) እየታጨደና ኹለት ኹለት ወይም ሦስት ሦስት ጭብጥ በአንድነት እየተደረገ የታሰረ እንደ ገብስ፣ ስንዴ፣ ..
ፌጦ	አብዛኛውን ጊዜ በጤፍ ሰብል ውስጥ ሊለማ የሚችል በትንሽ መጠን በገበያ ላይ የሚቀርብ ሲቀምሱት የሚሰነፍጥና ሰዎች ለመድኀኒትነት የሚገለገሉበት የቅመም ዓይነት
ግራምጣ	ጠንካራ የሆነ የሣር ዓይነት ሲሆን ተነቅሎ ከደረቀ በኋላ ሴቶች እየሰነጠቁ የተለያዩ የስፌት ዓይነቶችን የሚሰፉበት
የነገር አባት	ባልና ሚስት በሚጋቡበት ጊዜ ከእያንዳንዳቸው በኩል የሚቀርብና በውለታው ላይ የሚገኝ፣ አለመግባባት በሚፈጠርበት ወቅት ለቆመለት ወገን የሚከራከር ሰው
ዋጫ	የግራር ወገን የሆነ፣ እሾህ ያለው የቆላ ዛፍ
አማሞቶች	ሰርገኞች
ቀንጃ	አጣማጅ የሆነ ሌላው በራ
ተሀራዊይ	በረመዳን ጾም ወቅት ከ2፡30 እስከ 4፡00 በሚደርስ ጊዜ የሚከናወን ስግደት ነው፡፡
ሪጋ	የጥርስ ማጽጃ፣ መሚጫ እንጨት
ጨሌ	ነጭ፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ብጫና አረንጓዴ ቀለም ያለው ባለ ቀዳዳ ጌጥ

ጨሌ ጣይ	በእነዚህ የጌጥ ዓይነቶች የሚጠነቀል
ሞራ ገላጭ	በጨንራ ላይ የሚገኘውን ሥብ የሆነ አካል በመዘርጋት የሚጠነቀል ጠንቋይ
ሃራም	ክልክል፣ ግዝት፣ዕርም የኾነ ነገር፡፡
ግራምጣ	ጠንካራ የኾነ የሣር ዓይነት ሲኾን ሴቶች እየሰነጠቁ የተለያዩ የስፌት ዓይነቶችን የሚሰፉበት
ላይዳ	እንደአካፋ ኾኖ ከእንጨት የተሠራና በዐወድማ ላይ በነፋስ አማካይነት ፍሬን ከእብቅና ከገለባ ለመለየት የሚያገለግል የግብርና መሣሪያ

አጠቃሉ

ይህን ጥናት ለማካሄድ ካስቻሉኝ አነሣሽ ምክንያቶች መካከል አንደኛው የሕይወት ልምዴ ሲሆን፣ ይኼውም ጥናቱ በተካሔደባቸው ወረዳዎች የሚከወኑት ቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየሩና እየተለወጡ በመምጣታቸው የተነሣ በጊዜ ሒደት እየተረሱ ከመጥፋታቸው በፊት ተሰብስበው መጠናት አለባቸው የሚለው እምነት በውስጤ በማደሩ ነው። ኹለተኛው ደግሞ "አካዳሚያዊ" ጉዳይ ሲሆን፣ ጥናቱ ባተኮረባቸው ወረዳዎች በማኅበረሰቡ አንደበት ሲቀነቀኑ የነበሩት ቃል ግጥሞች በባችለር ዲግሪ ብቻ እንጂ ከዚያ በላይ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ከመስክ ተሰብስበውና በዘውግ ተከፋፍለው የተጠናከረ ምርምር የቀረበባቸው አይደሉም። የተሠሩት ጥናቶችም ቢሆኑ የቃል ግጥሞቹን እና የመከወኛ አጋጣሚዎቹን የለውጥና የቀጣይነት ኹኔታ አልተመለከቱም። በዚህ መሠረት ይኼንን ክፍተት ለመሙላት ባለኝ ውስጣዊ ፍላጎት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ጥናቴን ለማካሄድ ተነሣሥቻለሁ። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች በወረዳዎቹ በሚኖረው አርሶ አደር ማኅበረሰብ የሚዜሙት ቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎች መለየት፣ ቃል ግጥሞቹን በዘውግ መከፋፈል፣ በቃል ግጥሞቹ ላይ ዐውዳዊ ትንተና ማድረግ፣ ከመስክ የተሰበሰቡት የቃል ግጥም ዘውጎች የባህሉ ባለቤት ለኾነው ማኅበረሰብ ያላቸውን አገልግሎት በጥልቀት መመርመር፣ የቃል ግጥሞቹን እና የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውን ለውጥና ቀጣይነት መግለጽ የሚሉ ናቸው። ጥናቱ ዓይነታዊ ዘዴ ሲኾን፣ ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በትንተና እና በገለጻ ለማቅረብም ገላጭ የምርምር ዓይነትን በተግባር ላይ አውሏል። ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎችም ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይቶችና በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰቡ በኋላ በፈርጅ በፈርጅ ተመድበው በክዋኔያዊ፣ በተግባራዊና በዐውዳዊ ንድፈ ሐሳቦች ተተንትነዋል። በዚህ መሠረት በየወረዳዎቹ የሚገኙት አርሶ አደሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች በአጠቃላይ ሲታዩ የማኅበረሰቡን ሥነ-ልቦና፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኹኔታ እንደሚያንጸባርቁ ለመረዳት ተችሏል። ይህ በመሆኑም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረውን የኅብረተሰብ ክፍል የድካም ስሜቱን እንደሚያስወግዱለት፣ ለሥራ እንደሚያነሣሱትና እንደሚያበረታቱት ለመገንዘብ ተችሏል። በልጃገረዶች የሚከወኑት የቃል ግጥሞችም ማለፊያ የመዝናኛና የማስተማሪያ አጋጣሚዎች መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። የሙሽ ቃል ግጥሞችም እናት ለልጇ ያላትን የጠበቀ ቁርኝት፣ አባት ለልጆቹ ያለውን መመኪያነትና አለኝታነት፣ በወንድም ሞት

የተነሣ የተሟላ ሕይወትን መምራት እንደማይቻል፣ አኅትም ብትሆን የእናት አምሳያ መሆኗን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል። በተለይ በግብርና ሥራ ወቅት የተዜሙት ቃል ግጥሞች በሙገሳ፣ በትችት፣ በብሶት፣ በቁጭት፣ በመማጸን፣ ጠንክሮ በመሥራት ተገቢነት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ቃል ግጥሞቹ ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ፣ እኩይ የሆኑ ባሕርያትን የመግታት፣ የማኅበረሰቡን መልካም ዕሴቶች ለተከታዩ ትውልድ የማስተማር እና የማስተላለፍ ፋይዳ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ ወጣቶች በቃል ግጥሞች ላይ ያላቸው አመለካከት አናሳ መኾን፣ በመንግሥታት የፖለቲካ ሥርዓት መለዋወጥ፣ ዘመናዊ የመዝሙ መሣሪያዎች በአካባቢው በብዛት መሰራጨት፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ወጣቶች እምነታቸውን አጠንክረው መያዛቸው፣ በዘመናዊነት መስፋፋት የተነሣ በቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ ለውጦች የተከሠቱ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። በመጨረሻም የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ማንነት፣ ባህል፣ ወዘተ. ማጥናት የሚፈልጉ የታሪክ፣ የሥነ ማኅበረሰብ፣ የሥነ ልቡና፣ የሥነ ሰብእ ተመራማሪዎች ቃል ግጥሞቹን በመረጃ ምንጭነት ቢጠቀሙባቸው የሚል የይሁንታ ሐሳብ ቀርቧል። ምክንያቱም ቃል ግጥሞች ያለፈውን ለማጥናት፣ ለማወቅ፣ የወደፊቱንም ለማቃናት ያገለግላሉና ነው።

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ በቃል የሚከወን እና በቃል የሚተላለፍ ነው እየተባለ ቢነገርም በተጻፉ ሥራዎችም ውስጥ ሊገኝ እንደሚችልና ዐብሮ እንደሚኖርም Finnegan (1974:58) ገልጸዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ቃል ግጥም ህልውናው ከዘፈን፣ ከሙሾ፣ ከእንጉርጉሮና ከዜማ ጋር መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በዜማ ሳይታጀብ የሚደረስና የሚከወን ቃል ግጥም እስካሁን ድረስ በሀገራችን እንዳላጋጠመ ፈቃደ (1991፣84) አስረድተዋል፡፡

በዓለም ላይ በተለያዩ ከዋኞች የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች ልዩ ልዩ ፋይዳዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ለፈጣሪ ምስጋናን ለማቅረብ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚታዩት ፍርሃቶች፣ ከግጭቶች፣ ወዘተ. ራስን ለመጠበቅ ያገለግላሉ (Alembi, 2002፡49)፡፡ ታሪክን ለመመዝገብ ወይም ሰንዶ ለማስቀመጥና ፖለቲካዊ ሚናን ለመጫወትም ይውላሉ (Finnegan, 1970:83)፡፡ Kabira እና Mutahi (1988:50) በበኩላቸው ቃል ግጥሞች ተማሪዎችን የማስተማር፣ ማኅበረሰብን የማስጠንቀቅ፣ መረጃዎችን የማቀበል፣ የማዝናናት፣ ባህልን የማሳደግና ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ፣ የመምከርና የማሰልጠን አገልግሎት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

የቃል ግጥምም ኾነ አጠቃላይ የሥነ ቃል ጥናት በምሥራቅ አፍሪካ የተጀመረው በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ነው (Peek እና Yankah,2004:209)፣ (ፈቃደ፣1991፡42) እና (Finnegan, 2012:30)፡፡ በዚህ ወቅት የአውሮፓውያን ተጓዦች፣ የወንጌል ሰባኪዎችና የቋንቋና የሥነ ሰብ ምሁራን ትረካዎችን፣ ዘፈኖችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እና ሌሎች ዘውጎችን ሰብስበዋል (Finnegan,1974፡53)፡፡ እነዚህ የሥነ ቃል ሰብሳቢዎች የየራሳቸው የኾኑ ዓላማዎች ነበሯቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ባላቸው ፍላጎት እንደኾነ ይታወቃል፡፡ በተለይ የምሥራቅ አፍሪካን ቋንቋዎችን እና ባህሎችን ለመረዳት ሲሉ ንጽጽራዊ ጥናት ለማካኼድም ችለዋል (Peek እና Yankah, 2004: 209)፡፡ ከአውሮፓውያኑ በተጨማሪ አፍሪካውያኑ ራሳቸው በሥነ ቃል ላይ መጻሕፍት ያሳተሙ መኾኑን በዘርፉ ላይ ጥናት ያካኼዱት Peek እና Yankah (2004:374) ገልጸዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ የሚጠቀሱት ሥራዎችም

የNketia “Funeral Dirges of the Akan People”› (1955), የBabalola “The Content and Form of Yoruba Ijala” እና የMbiti “Akamba Stories” (1966) ናቸው። ከእነዚህ መካከል የመጨረሻዎቹ ሹለት ሥራዎች “The Oxford Library of African Literature Series”[1] በሚለው ውስጥ ተካትተው በ1966 ታትመዋል (Peek እና Yankah, 2004: 374-375)።

ከዛሬ ኃምሳ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የFinnegan (1970) “Oral Literature in Africa” እና (1977) “Oral Poetry: Its Nature, Significance and Social Context” የሚሉት በአፍሪካ ጎልተው የሚታዩ ሥራዎች ናቸው። የOkpewho (1992) “African Oral Literature” የተባለው ሥራም በርእሰ ጉዳዩ ላይ ስለተደረገው ጥናት አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ችሏል (Peek እና Yankah, 2004:375)። Seifu Metaferia እ.ኤ.አ በ1982 በኢትዮጵያ ሥነ ቃል ላይ ጥናት አካሂደዋል። የእሳቸው ጥናት ዓላማም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሥነ ቃሎችን ለልጆችና ለወጣቶች ጥቅም ላይ ለማዋል፣ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የበለጸጉ የሥነ ቃል ሐብቶችን ለመጠበቅና ለሚቀጥሉት ትውልዶች ለማስተላለፍ፣በመማሪያ መጻሕፍት አማካይነት የሞራል ጽንሰ ሐሳቦች ያሏቸውን ሥነ ቃሎች ለልጆች ለማስተማር ያለመ ነው። Getie Gelaye (2002) ባካሄዱት ጥናት በአማርኛ በልጆች የተገጠሙ ቃል ግጥሞችና ዘፈኖች ላይ በማተኮር ትንተና አድርገዋል። በትንተናቸውም ስለታታሪና ሰነፍ ገበሬዎች፣ ስለባልና ሚስት ግንኙነት፣ እንዲሁም ባካባቢያቸው ስለሚከሰቱ ወቅታዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማየት ችለዋል። በዚህ መሠረት በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው አፍሪካውያን በየራሳቸው ቋንቋዎች የሥነ ቃል ጥናት ማካኼዳቸው ወጥ የኾኑ የምርምር ሥራዎች እንዲታዩ አድርገዋል ማለት ነው።

Alembi (2002፡26-31) በአፍሪካ ውስጥ ያሉትን የሥነ ቃል ጥናት ኺደቶች በሦስት ምዕራፎች ከፍለዋቸዋል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ያለው ሲኾን፣ ይህም የሃይማኖት ሰባኪዎች ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በዚህን ወቅት የሃይማኖት ሰባኪዎቹ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች ለወንጌል ስብከት አገልግሎት የተጠቀሙባቸው መኾኑን Finneganም (1970፡28) ገልጸዋል። ከ1960ዎቹ እስከ 1980ዎቹ ያሉት ዓመታት ደግሞ በአፍሪካ የሥነ ቃል ጥናት ኹለተኛው ምዕራፍ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ይህ ምዕራፍ

[1] እንደ Dorson (1972፡ 125) አገላለጽ የቃል ግጥምን እና ዝርው ሥራዎችን በጣም ብዛት ባላቸው ቅጾች ያሳትም የነበረ ተቋም ነው።

በአፍሪካ ውስጥ የነበረውን የብሔርተኝነትን ስሜት የሚያመላክት ነበር። ምክንያቱም አፍሪካውያን በራሳቸው ሥነ ቃል ላይ ጥናት ለማካሄድ ያላቸው ፍላጎት የመጨመር ዝንባታ የጀመሩበት ወቅት ነበር። ሦስተኛው ምዕራፍ የሚባለው ደግሞ ከ1980ዎቹ በኋላ ያለው ሲሆን፣ ይህም ዘመናዊ ወይም የቅርብ በመባል ሊጠራ ይችላል። ይህ ደግሞ ቃላዊ የሆኑትን መረጃዎች ለመረዳት በሚደረገው ጥረት የመስክ ሥራ ወሳኝ መሆኑን የሚያሳውቅ ነው።

ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በራሳቸው ፍላጎት ተነሣሥተው የባህል ቅርስን ለወጣቱ ትውልድ ለማስተላለፍ ባላቸው ዓላማ ልዩ ልዩ የሥነ ቃል ዘውጎችን ሰብስበው አሳትመዋል (ፈቃደ፣1991፡42-43)። ከእነዚህ ቀጥሎ ደግሞ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ በኋላ ላይም በፎክሎር በባችለር፣ በማስተርስና በፒኤች. ዲ. ዲግሪ የተመረቁ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፎቻቸውን በሥነ ቃል ላይ ሠርተዋል። አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ምሁራን ለየደረጃዎቹ የሚያበቃቸውን ዲግሪ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ጥናቶቻቸው ባካለሏቸው አካባቢዎች ያሉትን ሥነ ቃሎች ሰብስበው ለመተንተን ባላቸው ዓላማ ነው።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑትና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ሥር በሚገኙት በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች በቃል ግጥም ላይ ሦስት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ተሠርተዋል። እነዚህም በጎበና (1986) “በወሎ /ቦረና/ ‘የቆንጆ‘ ዘፈን ግጥሞች”፣ በካሳው (1997) “የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና“ እና በእንድሪስ (1997) “የዛር ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በወግዲ ወረዳ” የሚሉት ናቸው። እነዚህ የመመረቂያ ጽሑፎች የተጠቀሱት በቃል ግጥም ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ነው።

ኾኖም አጥኚዎቹ አንደኛ፣ በየግላቸው ተናጠላዊ የኾነውን የቃል ግጥም ዘውጎችን ብቻ እንጂ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ዕምቅ የቃል ግጥም ሀብት በስፋት አልዳሰሱም። ኹለተኛ፣ በቃል ግጥሞቹ ላይ ዐውዳዊ ትንተና አላካሄዱም። የቃል ግጥሞቹንም ፋይዳ፣ የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውን ለውጥና ቀጣይነትን አልተመለከቱም። ከዚህ በተጨማሪ ለጥናቱ በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ እስካሁን ድረስ በማኅበረሰቡ በሚከወኑ ቃል ግጥሞች ላይ በማስተርስና በፒኤች. ዲ ዲግሪ ደረጃ የተሠሩ ጥናቶች አላገኘሁም። በዚህ መሠረት ይህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ይሞላል ተብሎ ታስቧል።

1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች

አንድን ምርምር ለማካኼድ አነሣሽ ምክንያቶች ሊኖሩ ይገባል። Moutonም (1988፡ 24) በምርምር ሥራ ወቅት አስፈላጊዎች ናቸው ብለው ከዘረዘሯቸው ጉዳዮች መካከል አንደኛው አነሣሽ ምክንያት የሚባለው ነው። በመኾኑም Kothari (2004፡12) ማንኛውም ተመራማሪ ሊያጠና በፈለገው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ለምርምሩ ሊያነሣሡ የሚችሉ ምክንያቶችን ለይቶ ማውጣት አለበት ብለዋል። እኔም ከላይ የተዘረዘሩትን ቁም ነገሮች መሠረት በማድረግ የጥናቴን አነሣሽ ምክንያቶች በኹለት ዐበይት ዘርፎች ከፍያቼዋለሁ።

የመጀመሪያው የሕይወት ልምዴ ነው። ይኼውም ጥናቱ በሚካኼድበት አካባቢ የተወለድኩ በመኾኑና የማኅበረሰቡ ሀብት በኾነው ቃላዊ ግጥም ክዋኔ ላይም እየተሳተፍኩ ስላደግሁ ይህንኑ ጉዳይ በትኩረት መመርመር አለብኝ በሚል እምነት የተነሣ ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት ባለው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኹኔታ ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው ማኅበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች እየተቀየሩና እየተለወጡ መምጣታቸው እየተስተዋለ ነው። ይህንንም ኹኔታ በተለያዩ ጊዜያት ወደየወረዳዎቹ ስመላለስ በነበረበት ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ። በዚህ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በማኅበረሰቡ የተፈጠሩት ቃል ግጥሞች በጊዜ ኺደት እየተረሱ ከመጥፋታቸው በፊት ተሰብስበው መጠናት አለባቸው የሚለው እምነት በውስጤ በማደሩ ነው።

ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ “አካዳሚያዊ” ነው። ይኼውም ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች በማኅበረሰቡ አንደበት የሚነገሩት ቃል ግጥሞች ለባችለር ዲግሪ ማሟያነት እንጂ ከዚያ በላይ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ከመስክ ተሰብስበውና በዘውግ ተከፋፍለው የተጠናከረ ምርምር የቀረበባቸው አይደሉም። በተለይ በቅርቡ ምርታማነትን ለማሳደግ በሚያገለግሉ ግብኣቶች (በሰው ሠራሽ ማዳበሪያ፣ በብስባሽ፣ በፀረ ዐረምና በእርከን ሥራ) ላይ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች ካላቸው ከፍተኛ ፋይዳ አንጻር ተሰብስበው አልተጠኑም። ከእነዚህ በተጨማሪ የቃል ግጥሞቹን እና የመከወኛ አጋጣሚዎቹን የለውጥና የቀጣይነት ኹኔታ ለማወቅ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ ኾኖ ተገኝቷል። በዚህ መሠረት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ለመመርመር ባለኝ ውስጣዊ ፍላጎት በርእሰ ጉዳዩ ላይ ጥናቴን ለማካኼድ ተነሣሥቻለሁ።

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ምርምር ጽሑፍ ዐቢይ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጡ በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች በሚኖረው ማኅበረሰብ ዘንድ የሚነገሩትን ቃል ግጥሞች ከመስክ ሰብስቦ በፈርጅ በፈርጅ መመደብና ትንተና ማካኼድ ነው።

ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

1. ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎች መለየትና ማጥናት፣
2. ቃል ግጥሞቹን በፈርጅ በፈርጅ መመደብ፣
3. በቃል ግጥሞቹ ላይ ዐውዳዊ ትንተና ማድረግ፣
4. ከመስክ የተሰበሰቡትን የቃል ግጥም ዘውጎች የባህሉ ባለቤት ለኾነው ማኅበረሰብ ያላቸውን አገልግሎት መመርመር፣
5. የቃል ግጥሞቹን እና የመከወኛ አጋጣሚዎችን የለውጥና ቀጣይነት መንስኤዎችን መመርመር፣

1.4 የምርምሩ ጥያቄዎች

ይህ ርእሰ ጉዳይ ከመስክ መረጃዎችን በማሰባሰብ በምርምሩ ሊመለሱ የታቀዱትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚያካትት ነው። እነ Carol እና Ember (2009፡27) ጥሩ የሚባሉ የምርምር ጥያቄዎች የምርምሩን ዓላማ በግልጽ በማሳየት ተግባራዊ የሚደረጉ መኾን አለባቸው በማለት ይገልጻሉ። በአጭር አገላለጽ የምርምር ጥያቄዎችን በጥንቃቄ ማዘጋጀት ለሚሠራው ምርምር አቅጣጫንና ቅርጽን ለማስተካከል ይረዳል።

እንደ Flick (2006:106) አገላለጽ የምርምር ጥያቄዎች ከየትም የሚመጡ አይደሉም። በመኾኑም ከተመራማሪዎች ግላዊ የሕይወት ታሪካቸውና በአካባቢያቸው ካለው ማኅበራዊ ዐውድ ጥያቄዎች ሊገኙ ይችላሉ በማለት አብራርተዋል። በመኾኑም ከላይ የቀረቡትን ሐሳቦች መነሻ በማድረግ በሚከተለው ኹኔታ የተዘጋጁት ዋና ዋና ጥያቄዎች በምርምሩ ምላሽ አግኝተዋል ተብሎ ይታሰባል።

1. ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?
2. ቃል ግጥሞቹ በምን በምን ዘውጎች ላይ ያተኩሩ ናቸው?
3. ቃል ግጥሞቹ በዐውድ ሲተነተኑ የሚያስተላልፉት ይዘት ምንድን ነው?
4. ቃል ግጥሞቹ ለማኅበረሰቡ ያሏቸው አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?
5. በማኅበረሰቡ የአኗኗር ለውጥ የተነሣ የቃል ግጥሞቹና የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ለውጥና ቀጣይነት መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ቃል ግጥም ለአንድ ማኅበረሰብ ከፍተኛ የኾነ ጠቀሜታ ያለው መኾኑ የሚታወቅ ነው። በአብዛኛው በአፍሪካ ሀገራት ያሉ ሕዝቦች ለፈጣሪ ምስጋናን ለማቅረብ፣ ቅድመ አያቶቻቸው በአዝመራ አሰባሰብ ወቅት "ተመስገን ጌታዬ ከሞላ ጎተራዬ" ለማለት፣ ልጆችን እና የቤት እንስሳትን ለመመረቅና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን ቃል ግጥሞችን እንደሚጠቀሙ Alembi (2002:49) አስረድተዋል። ይህ ጥናት በሚካሔድበት አካባቢ ባለው ማኅበረሰብ አንደበት የሚዜሙት ቃል ግጥሞችም ከሥራ ጋር ተቀላቅለው ሲቀርቡ ስሜትን ለማነሣሣትና ለማበረታታት የሚጠቅሙ መሆኑን ከመረጃ ትንተናው ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ ውጭ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች በዓላትን ለማድመቅ፣ ለማዝናናት፣ የማኅበረሰቡን የእርስ በርስ ፍቅር፣ ሐዘን፣ ደስታና ብሶት፣ ወዘተ. ለመግለጽ እንደሚጠቅሙ በተለያዩ ዘዴዎች ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች አመልክተዋል። እነዚህና ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎች ባሏቸው ቃል ግጥሞች ላይ ተመሥርቶ የተሠራው ይህ ጥናትም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ታስቧል።

1. በየወረዳዎቹ የሚገኘው አርሶ አደር ማኅበረሰብ የጋራ ሀብቱ በኾኑት ቃል ግጥሞች ሥነ ልቦናውን እና ፍላጎቱን ሊያንጸባርቅ ስለሚችል፣ በኺደት አካባቢዎቹን ለማልማት እንቅስቃሴ ለሚያደርግ አካል ጥናቱ መረጃ ሊሰጥ ይችላል።
2. የየወረዳዎቹ አርሶ አደሮች ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶቻቸው በቃል ግጥሞቻቸው ሊንጸባረቁ ስለሚችሉ አጠቃላይ ማኅበረሰቡም ቢሆን ለእነዚህ አንጡራ ሀብቶቹ ትኩረት እንድሰጥ ጥናቱ ሊጠቅመው ይችላል።
3. ለባህል ፖሊሲ አውጪዎች የመረጃ ምንጭና ግብዓት ሆኖ ያገለግላል።
4. የሥነ ጽሑፍ ምሁራን፣ የፊልም ደራሲያን እና የሙዚቃ አቀናባሪዎች ቃል ግጥሞቹን እና ዜማዎቹን በየሥራዎቻቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያስችላል። በዚህም የፈጠራ ሥራዎቻቸው በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ሊያተርፉላቸው ይችላሉ።
5. በቃላዊ ግጥሞች አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ይቻል ዘንድ የሥርዓተ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፣ እንደዚሁም በክፍል ውስጥ ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ቃል ግጥሞችን በይዘትነት እንዲያካትቱ በማድረግ ረገድ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።
6. የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ማንነት፣ ባህል፣ ወዘተ. ማጥናት ለሚፈልጉ ለከፍተኛ ትምህርት ምሁራን (ለታሪክ፣ ለሥነ ማኅበረሰብ፣ ለሥነ ልቡና፣ ለሥነ ሰብእና ለፎክሎር ተመራማሪዎች) የመረጃ ምንጭ በመኾን ያገለግላል።

7. ጥናቱ ከዘመን ዘመን እየተሸጋገሩ የመጡትን ቃል ግጥሞች በጽሑፍ መዝግቦ የያዘ በመኾኑ ለመጪው ትውልድ በሰነድነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ሥር በሚገኙትና በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ በተመረጡት በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች ላይ ብቻ የተገደበ ሆኗል፡፡ ለዚህም አንደኛው ምክንያት ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በውስጡ 22 ወረዳዎች ያሉት ሲሆን፣ ከወረዳዎቹ ብዛትና ከመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ለትራንስፖርት አስቸጋሪ ከመሆን፣ ከወጪ፣ ከጊዜና አጥኚው ካለው የወረዳዎች ዕውቂያ ውስንነት አንጻር ጥናቱ ከላይ በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ በተመረጡት ወረዳዎች ላይ ብቻ እንድወሰን ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ከመስክ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ አንደበት የተነገሩበትን ወቅት የሚያሳዩ ባለመሆናቸው ጥናቱን በጊዜ መወሰን አልተቻለም፡፡

ከርእሰ ጉዳይ አንጻር ጥናቱ የግብርና ግብኣቶች በኾኑት በማዳበሪያ፣ በብስባሽ፣ በፀረ ዐረም፣ በዕርከን ሥራ፣ እንደዚሁም የግብርና የሥራ ዓይነቶች በኾኑት በእርሻ፣ በዐረም፣ በዐጨዳ፣ በውቂያ ወቅት በሚዜሙ፣ የሕይወት የሽግግር ሥርዓት በኾኑት በሰርግ፣ በለቅሶና በልጃገረዶች በሚከወኑት የቃል ግጥሞች ላይ የተወሰነ ኾኗል፡፡ በእስልምናም ኾነ በክርስትና ሃይማኖታዊ ሥርዓተ ከበራዎች የሚከወኑት ቃል ግጥሞች ግን በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች የሚያካትት ከሆነ በጣም ስለሚሰፋ ቃል ግጥሞቹ በሌሎች ምሁራን ምርምር ቢካሄድባቸው የሚል ጥቁምታ መስጠቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

አንድ አጥኚ በምርምር ሥራው ወቅት ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሊኾንለት አይችልም፡፡ ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ መሠረት እኔም ይኽንን ጥናት ስሠራ በሚከተለው ኹኔታ ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ለችግሮቹ የወሰድኳቸውንም መፍትሔዎች ከተጠቀሱት ችግሮች ጋር አያይዤ አቅርቤያቸዋለሁ፡፡

የመጀመሪያው ችግር በዕርከን ሥራ፣ በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅቶች በዐውድ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በተለያዩ ጊዜያት በመኾኑ በየወረዳዎቹ ስንቀሳቀስ ለተለያዩ ወጪዎችና እንግልቶች ተዳርጌያለሁ፡፡ ኾኖም ግን ችግሮቹን በመቋቋም የግብርና ሥራዎቹ

በሚከወኑባቸው ወቅቶች በናሙናነት በተመረጡት ቀበሌዎች በመዘዋወር ቃል ግጥሞቹን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ሌላው ችግር ደግሞ ለ18 ረዳት የመረጃ ሰብሳቢዎች የሚሾኑ መቅረጸ ድምፆችን እና ፎቶ ካሜራዎችን ማሟላት አለመቻል ነው። ለዚህ ችግር የተወሰደው መፍትሔ ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎቹ ማስታወሻ ደብተር እንድጠቀሙ፣ በተጨማሪ የየራሳቸውን ተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቅመው በቃል የተነገሯቸውን መረጃዎች እና ምስሎች እንዲቀርጹ ማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ በእኔም ሆነ በእነሱ አማካይነት በማስታወሻ የተያዙት መረጃዎች በኮምፒዩተር ተጠናቅረው ተቀምጠዋል። ምስሎቹንም ቢሾን "Bluetooth"ን በመጠቀምና ወደኮምፒውተር በማሸጋገር በጥንቃቄ ለመያዝ ተችሏል። በረዳት መረጃ ሰብሳቢዎች አማካይነት ከተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች መካከልም አንዳንዶቹ ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ነበሩ። ቃል ግጥሞቹን በሙሉ ወደኮምፒውተር ከገለበጥኩ በኋላ ግንኙነት የሌላቸውን ከዝርዝር ውስጥ በማውጣት ለማስተካከል ችያለሁ።

በከለላና በወግዲ ወረዳዎች በጠቋሚ የናሙና ዘዴ አማካይነት ለቡድን ተኮር ወይይቱ የመረጥኳቸውን ሰዎች በተመሳሳይ ሰዓት በአንድ ቦታ ላይ ለማግኘት አለመቻሉ ሌላው ችግር ነበር። ለእዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሔ አድርጌ የወሰድኩት መረጃ ሰጪዎቹ ለሚኖሩባቸው ቀበሌዎች አማካይ ወደሾኑ ትምህርት ቤቶች በመኼድ ላውቃቸው የምችላቸውን መምህራን ማፈላለግ ነበር። በዚህ መሠረት በከለላ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል (ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል) እና በሰቀ ሸንብራ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመኼድ በወሎ ዩኒቨርሲቲ በማኅበራዊና ሰብኣዊ ሳይንስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል በክረምቱ መርሓ ግብር ያስተማርኳቸውን እና እያስተማርኳቸው ያሉ መምህራንን ለማግኘት ቻልኩ። ከዚያም በቦታው ላይ የተገኘሁበትን ዓላማና ያጋጠመኝን ችግር ገለጽኩላቸው። እነሱም ችግሩ ቀላል መኾኑን ካስረዱኝ በኋላ ቀደም ሲል ለቡድን ተኮር ውይይቱ የተመረጡትን ሰዎች በሚቀጥለው ቀን ትምህርት ቤቶቹ ቅጥር ግቢ ድረስ በማምጣት ስለተባበሩኝ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ። በተመሳሳይ ኹኔታ በቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት አማካይነት በቡድን ተኮር ውይይቱ እንዲሳተፉ የተነገሩኝ ሰዎች ፈቃደኛ ባለመኾናቸው በታሰበው ዕለት ውይይቱን ማካኼድ አልተቻለም ነበር። ነገር ግን የሥጋ ዘመዶቼ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ብለው ያመኑባቸውን ሰዎች በጥቆማ የናሙና ዘዴ ("ከእገሌ እገሌ ይሻላል" ብለው የመረጡልኝን ሰዎች) በመረጃ ሰጪነት እንዲሳተፉ ተደርገዋል።

ሌላው ችግር ደግሞ እኔም ኾንኩ ረዳቶቼ ለመረጃ ሰጪዎቻችን ባቀረብነው ቃለ መጠይቅ አማካይነት ቃል ግጥሞችን እንዲነግሩን ስንጠይቃቸው አንዳንዶቹ የሚያውቁትን አስታውሰው ለመናገር ያለመቻል ኹኔታ የመከሠቱ ጉዳይ ነበር። ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት "ከየት እናመጣዋለን፤ ረስተነዋል እኮ።" እንደዚሁም በየመካከሉ "ጠፋን" የሚሉም ነበሩ። ለዚህ ችግር እንደ አንድ መፍትሔ አድርገን የወሰድነው ከተለያዩ ሰዎች የሰማናቸውን የቃል ግጥሞች እንደ አዲስ ስናዜምላቸው እነሱም በመነቃቃት የቻሉትን ያክል እንዲነግሩን አድርገናል። ከዚህ በተጨማሪ መረጃ ሰጪዎቹ ቃል ግጥሞችን አስታውሰው ለመናገር ያልቻሉት የዐውድ አለመኖር[2] ነው የሚለው ግምት በውስጤ አድሮ ስለነበር የግብርና ሥራዎችና የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች በሚከወኑበት ወቅት በአካል ተገኝቼ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት ችያለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከመስከረም 05 እስከ 09/2013 ዓ.ም ድረስ በዐረም ወቅት በተካኼደው የመረጃ አሰባሰብ ኺደት ልጃገረዶች የፍቅርንም ኾነ የዐረም ሥራ ቃል ግጥሞችን እንድያዜሙልኝ ስጠይቃቸው እየተሸኮረመሙ ስላስቸገሩኝ መረጃዎችን በበቂ ኹኔታ ለማግኘት አልቻልኩም ነበር። ነገር ግን በዐረሙ ሥራ አብረዋቸው እየተሳተፉ የነበሩ ጎረምሳዎች በሌሎች ልጃገረዶች ሲዜሙ የሰሙትን ቃል ግጥሞች በቡድን ካንጎራጎሩላቸው በኋላ እነሱም በኹኔታው ተነሣሥተው የቻሉትን ያክል ሊያዜሙልኝ ችለዋል።

ከላይ በተከታታይ ከቀረቡት ችግሮች የበለጠ ገዝፎ የነበረው በሀገራችን የCOVID - 19 ወረርሽኝ ከመጋቢት 04/2012 ዓ.ም ጀምሮ መከሠቱ ነበር። ከዚህን ዕለት ጀምሮ እስከ መስከረም 2013 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ መስክ ወጥቶ መረጃዎችን በወቅቱ መሰብሰብ አልተቻለም ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከመጋቢት 7/2012 ዓ.ም ጀምሮ ከቤት መውጣትና ከቦታ ቦታ በሕዝብ ትራንስፖርት እንደልብ መንቀሳቀስ እንደማይቻል በመንግሥት ተደንግጎ ነበር። በዚህ የተነሣ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ካሉ መረጃ ሰጪዎቼ ጋር በአካል ተገናኝቼ መረጃዎችን በወቅቱ መሰብሰብ አልቻልኩም። በዚህም አጠቃላይ የምርምር ሥራዬ ሊጓተት ችሏል። ሆኖም ግን የCOVID - 19 ወረርሽኝን በተመለከተ በመንግሥት ተጥሎ የነበረው ገደብ እንደተነሣ ከመስከረም 04/2013 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ዐውዶች በየወረዳዎቹ በመገኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል።

[2] ሁሉንም ቃል ግጥሞች ከመጀመሪያውኑ በዐውድ ለመሰብሰብ ያልቻልኩት ለጥናቱ የተሟላ መረጃ ማግኘት ስለማይቻል ነው።

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ዐሥር ምዕራፎችን የያዘ ነው። በእያንዳንዱ ምእራፍ የቀረቡት ርእሰ ጉዳዮች በሚከተለው ኹኔታ በቅደም ተከተል ቀርበዋል። ምዕራፍ አንድ አጠቃላይ የጥናቱ መግቢያ የቀረበበት ነው። በዚህ ሥርም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓቢይና ንኡስ ዓላማዎች፣ በጥናቱ የሚመለሱ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎችና የጥናቱ ወሰን ቀርበዋል። ጥናቱ በሚከናወንበት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎችም የመግቢያው አካል ኾነዋል።

ምዕራፍ ኹለት ስለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ ስለጥናቱ አዋሳኝ ወረዳዎች መልክአ ምድራዊ ገጽታና ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች መግለጫ የተሰጠበት ነው። በዚህ ክፍል ስለመስተዳድር ዞኑም ኾነ ስለወረዳዎቹ የመገኛ ቦታ፣ ስለአየር ንብረታቸው፣ ስለሕዝቡ ብዛት፣ ስለሃይማኖታቸው፣ ስለቋንቋቸው፣ ወዘተ. በቅድሚያ ዳሰሳ ተካኺዷል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረተሰቡ በወሎዬነት ስሜትና እምነት ተፈቃቅዶና ተፈቃቅሮ ያለ አንዳች ችግር ዐብሮ እንደሚኖር ተገልጿል። በተለይ በገጠር የሚኖረው የቦረና፣ የወግዲና የከለላ ወረዳዎች ሕዝብ አለባበሱና በኹለቱም ጾታዎች የሚገኙ ወጣቶች ማንነታቸውን የሚገልጹበት አጊያጊያጥ በዝርዝር ተዳስሷል። በየወረዳዎቹ ከመተጫጨት ጀምሮ እስከ ሰርጉ ዕለት ድረስ ያለው ኺደትም በስፋት ቀርቧል። የክርስትናም ኾነ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በኾነው ማኅበረሰብ ዘንድ የአንድ የቤተሰብ አባል በሞት ሲለይ ቤተሰቡ መሪር ሐዘኑን የሚገልጽባቸው የተለያዩ መንገዶች በምዕራፉ ቀርበዋል። በግለሰብም ኾነ በቡድን ደረጃ የሚከሠቱ ግጭቶች በሚኖሩበት ወቅት በአካባቢው ተሰሚነት ባላቸው የሀገር ሽማግሌዎች እየታየ ፍትሕ የሚሰጥ መኾኑም ተገልጿል። በመጨረሻም ማኅበረሰቡ በርካታ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ስለሚያጠናክርባቸው ዕሴቶች ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ምዕራፍ ሦስት ክለሳ ድርሳን የተካኼደበት ሲኾን፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ቃል ግጥምን የጥናታቸው ርእሰ ጉዳይ አድርገው የተሠሩ ጥናቶች በቅደም ተከተል ተቃኝተዋል። ቀጥሎ የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ቀርቧል። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር ስለቃል ግጥም፣ የቃል ግጥሞች ዐውድ፣ ፋይዳ፣ የመከሠቻ አጋጣሚዎች ለውጥና ቀጣይነት በሚሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ተደርጓል። በተለይም ድረሳ፣ ተስተላልፎና ክዋኔ ቃል ግጥምን ለመበየን የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮች መኾናቸውን ለማየት ተችሏል። ከዚያም የቃል ግጥም መሠረታዊ ባሕርያት፣ የማቅረቢያ ስልቶች፣ የቃል ግጥም ዓይነቶች በዝርዝር ተዳስሰዋል።

በምእራፉ መጨረሻ ላይም በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡት ጥሬ መረጃዎች በክዋኔያዊ፣ በተግባራዊና በዐውዳዊ ንድፈ ሐሳቦች ተተንትነው ቀርበዋል።

በምዕራፍ አራት ደግሞ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን እንደተከተለና ገላጭ የምርምር ዓይነትንም በተግባር ላይ እንዳዋለ ተገልጿል። ከጥናቱ ዓላማ አንጻርም በዓላማ ተኮርና በጠቋሚ የናሙና ዘዴዎች መረጃዎቹ መሰብሰባቸውን ለማስረዳት ተችሏል። ጽሑፋዊ ሰነዶች፣ ቃለ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና ምልከታ ዓይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደኾኑም በምዕራፉ ተጠቅሷል። ማስታወሻ ደብተር፣ ብዕር፣ መቅረጸ ድምፅ፣ ፎቶና ቪዲዮ ካሜራ ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መኾናቸውም ተገልጿል። ለዚህ ጥናት ከሌሎቹ መቼቶች ይልቅ ተፈጥሯዊ መቼት የተሻለ ኾኖ በመገኘቱ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተግባራዊ ተደርጓል።

ከአምስት እስከ ዘጠኝ ባሉት ምዕራፎች ከመስክ የተሰበሰቡትን የቃል ግጥሞች መሠረት በማድረግ የመረጃ ትንተና ተካኺዷል። በዚህ መሠረት በምዕራፍ አምስት ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች ተተንትነዋል። በምዕራፍ ስድስት ደግሞ በቃል ግጥሞቹ ላይ የዘውግ ምደባ በማካኼድ በአስረጂነት በቀረቡት ቃል ግጥሞች ላይ ትንተና ተደርጓል። በምዕራፍ ሰባት በግብርና ሥራዎችና በማኅበረሰቡ የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ወቅት ከዐውድ በተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ላይ ትንተና ተካኺዷል። በምዕራፍ ስምንት በአስረጂነት በተመረጡት ቃል ግጥሞች ላይ ትንተና በማድረግ የባህሉ ባለቤት ለኾነው ማኅበረሰብ ያሏቸውን ፋይዳዎች በጥልቀት በመመርመር ላይ ትኩረት ተደርጓል። በእነዚህ ምዕራፎችም በሰነድ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ከተሰበሰቡት 1,524 የቃል ግጥሞች መካከል 228ቱ ተተንትነዋል። በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ በጊዜ ኺደት በቃል ግጥሞቹና በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ላይ በታዩ ለውጦች፣ እንደዚሁም በቀጣይነታቸው ላይ ማብራሪያ ተሰጥቷል። በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶችና እነዚህንም መሠረት በማድረግ የቀረቡ የይሁንታ ሐሳቦች በምዕራፍ ዐሥር ቀርበዋል።

1.9 አጥኚው የተከተላቸው የሥነ ምግባር መርሆዎች

- በቅድሚያ ከሦስቱም ወረዳዎችና ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች መካከል የሥራ መደባቸው የባህል ልማት ተጠሪ ለሆኑት፣ እንደዚሁም መረጃ እንድሰጡ ለተመረጡ አርሶ አደሮች በጽሑፍም ሆነ በንግግር የጥናቱን ዓላማ ለማስረዳት ትችሏል።

- የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸው መረጃዎች ከምርምር ውጭ ለሌላ አገልግሎት እንደማይውሉ ትሕትና በተሞላበት ኹኔታ ተገልጸላቸዋል፡፡
- በዓላማ ተኮር ናሙና ከተመረጡት ሰዎች መካከል በመረጃ ሰጪነት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆኑ ከጥናቱ ተሳታፊነት መውጣት እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል፡፡
- ቃለመጠይቁ በሚካሄድበት ወቅት በቴፕ ምላሻቸው እንደሚቀረፅ፣ ፎቶግራፍም እንደሚነሱ ከተገለጸላቸው በኋላ ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸውን ተጠይቀው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው ሴቶች መካከል የእስልምና ሃይማኖታዊ ህግ (shariah) ስለማይፈቅድ ፎቶግራፍ አንነሳም ያሉ ስለነበሩ እነሱን ማስገደድ አልተቻለም፡፡
- በመረጃ አቀባይነት የተሳተፉት ሰዎች ለቃለ መጠይቁ ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት መረጃውን የሰጡኝ በፈቃደኛነት እንደሆነ የሚገልጽ ደብዳቤ ጠይቄ ነበር፡፡ ሆኖም ፈቃደኛነታቸውን በደብዳቤ ለመግለጽ ስላልቻሉ ከራሴ ስሜትና ፍላጐት አንፃር ተፅዕኖ አላሳደርኩባቸውም፡፡

ምዕራፍ ኹለት፡- የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን እና የጥናቱ አዋሳኝ ወረዳዎች መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችና ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች

በቅድሚያ በዚህ ምዕራፍ ሥር የጥናቱ አካላይ ወረዳዎች ስለሚገኙበት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን መልክዓ ምድራዊ ገጽታን እና ማኅበረ ባህላዊ ዳራን በተመለከተ ቅኝት ተካሂዷል፡፡ ቀጥሎም ጥናቱ ባተኮረባቸው ወረዳዎች ስላለው መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ እንደዚሁም ስለማኅበረሰቡ አኗኗርና ባህል በተናጠል ተዳስሶበታል፡፡



ካርታ አንድ፡- ወረዳዎችን ያካተተ የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ሲሾን፣ መረጃውም የተገኘው ከማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ደሴ ቅርንጫፍ ነው፡፡

ጥናቱ የተካሄደባቸው ወረዳዎች

2.1. የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን መልክዓ ምድራዊ ገጽታና ማኅበረ

ባህላዊ ዳራ በአጭሩ

የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ስያሜውን ያገኘው ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፣ ከዚያ በፊት ግን በመጀመሪያ ወሎ ጠቅላይ ግዛት፣ በኋላ ላይ ደግሞ ወሎ ክፍለ ሀገር እየተባለ የሚጠራ ሰፊ ግዛት ነበር። ከላይ በተገለጸው ዓመተ ምሕረት ክፍለ ሀገሩ ደቡብና ሰሜን ተብሎ ሊከፈል ችሏል። የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ከሚገኙ ዐሥራ አምስት ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ኻያ ኹለት ወረዳዎችን እና ዐራት የከተማ አስተዳደሮችን ይዟል። የዞኑ ርእሰ ከተማ ደሴ ስትሆን፣ ከአዲስ አበባ በ401 ኪሎ ሜትርና ከክልሉ ርእሰ ከተማ ከባሕር ዳር ደግሞ በ480 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ይህ የአስተዳደር ዞን በሰሜን ከሰሜን ወሎ፣ በደቡብ ከሰሜን ሸዋና ከኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር፣ በምዕራብ ከምሥራቅ ጎጃምና ከደቡብ ጎንደር፣ በምሥራቅ ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና ከኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር፣ በሰሜናዊ ምዕራብ ከደቡብ ጎንደር ዞኖች ጋር ይዋሰናል። የዞኑ ሕዝብ ብዛትም ሦስት ሚሊዮን ዘጠና አምስት ሺህ አራት መቶ ኃምሳ ሰባት መኾኑን ለማወቅ ተችሏል (ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፣ 2012)።

ዞኑ ቆላ (9.2%)፣ ወይና ደጋ (54.4%)፣ ደጋ (35.2%) እና ውርጭ (1.2%) በሚባሉ የአየር ንብረቶች የተከፋፈለ ነው። በተፈጥሮ መልክዓ - ምድራዊ አቀማመጡም የተለያዩ የመሬት ገጽታዎችን ይዟል። ማለቂያ የሌለው የተራሮች ሰንሰለት፣ ኮረብታዎች፣ ሸንተረሮች፣ ሜዳዎች፣ ሸለቆዎች፣ ወንዞችና ሐይቆች የደቡብ ወሎን ምድር ልዩ ውበት ሰጥተውታል (ጌታቸው፣ 1984፡13)። እነዚህ መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች ለተለያዩ ከያኒያን ለሙዚቃ ግጥሞቻቸው ምንጭ እንደኾኗቸው አጥኚው የሚያረጋግጠው ጉዳይ ነው።

የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ብሔረሰቦች በወሎዬነት ስሜትና እምነት ተፈቃቅደውና ተፈቃቅረው ያለ አንዳች ችግር በዞኑ ውስጥ በሰላም ይኖራሉ። በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ውስጥ በዋናነት የእስልምና እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖች ተከታይ ሕዝቦችም አሉ። በመስጊዶችና በአብያተ ቤተክርስቲያናትም የሃይማኖት ትምህርቶች በአረብኛና በግእዝ ቋንቋዎች መሰጠታቸው የረጅም ዘመን ታሪክ ነው። ሌላው በአርኣያነት የሚጠቀሰው ጉዳይ ደግሞ በሃይማኖት ምክንያት ምንም ዓይነት የጋብቻ ድንበር አለመኖሩና ያለ መግባባት ስሜት አለመታየቱ ነው።

የደቡብ ወሎ ዞን ማኅበረሰብ አባላት ስሜቶቻቸውን፣ ስለ ሕይወት ያላቸውን አተያይ፣ እምነታቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ወዘተ. እስካሁን ድረስ በሥነ ቃሎቻቸው ማለትም በዘፈኖች፣ በግጥሞች፣ በእንቆቅልሾች፣ በዝርው ትረካዎች፣ ወዘተ. አማካይነት በመግለጽ ላይ ይገኛሉ። እንደ ጌታቸው (1984፣52) አገላለጽ በእስልምና ሃይማኖት ጥልቅ ስሜትና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚዘጋጀውና ሃይማኖታዊ አጋጣሚዎች ላይ ብቻ የሚቀርበው "መንዙማ" በወሎ ጉልሕ ቦታን ይዟል። እንደሚታወቀው ትዝታ፣ አንቺ ሆዬ፣ ባቲና አምባሰል በመባል የሚጠሩት አራቱ መሠረታዊ የሙዚቃ ቅኝቶች የሚገኙት ወሎ ውስጥ ነው (አስቴር ሙሉ፣ 2007፡174)።

ስለ ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን መልክዓ ምድራዊ ገጽታና ማኅበረ ባህላዊ ዳራ በአጭሩ ቅኝት የተደረገው ያለ ምክንያት አይደለም። ባንድ በኩል መልክዓ ምድራዊ ገጽታውን እና ማኅበረ ባህላዊ ዳራውን ጥናቱ የሚካኼድባቸው ወረዳዎችም ስለሚጋሩት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጥናቱ ከሚያተኩርባቸው የቃል ግጥም ዘርፎች ጋር ጥብቅ ትሥሥር ሊኖር ይችላል ብዬ ስላመንኩኝ ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ጥናቱ የተካኼድባቸው ወረዳዎች መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችና ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች በቅደም ተከተል ተቃኝተዋል።

2.1.1. የቦረና፣ የወግዲና የከለላ ወረዳዎች መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች

ቦረና የአሁኑን የወረዳ ገጽታ ከመያዙ በፊት የወግዲ ወረዳን ጨምሮ ደብረሲና ወረዳ እየተባለ ሲጠራ የቆየና በአውራጃ ደረጃም በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት (ከ1923 — 1966) ቦረና ሳይንት፣ ከ1967 ዓ.ም እስከ 1985 ዓ. ም ድረስ በነበረው የደርግ አስተዳደር ወቅት ደግሞ ቦረና አውራጃ ተብሎ ይጠራ ነበር። የቦረና ወረዳ በምሥራቅ ከለጋምቦ፣ በሰሜን ከሳይንትና ከመሐል ሳይንት፣ በደቡብ ከወግዲ ወረዳና በምዕራብ ደግሞ ከምሥራቅ ጎጃም ዞን ጋር ይዋሰናል።

የቆዳ ስፋቱም 100,088 ስኩዌር ኪ.ሜ. ሲኾን፣ ከዚህ ውስጥ 41,421.26ቱ ለእርሻ ሥራ የዋለ ነው። መልክዓ ምድሩም ወጣ ገባ ያለ፣ ቆላ (32%)፣ ወይና ደጋ (47%)፣ ደጋ (20%) እና ውርጭ 1% የሚባሉ የአየር ንብረቶች ያሉት ስለመኾኑ የቦረና ወረዳ አስተዳደርና የመካነ ሰላም ሚሊኒየም የልማት ባዛር አዘጋጅተውት የነበረው መጽሔት (2000)፣ እንደዚሁም ከወረዳው የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት (2012) የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ። በወረዳው ውስጥ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ በቆሎ፤ ምስር፣ ባቄላ፣ አተር፣ ገብስ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ሰብሎች ይመረታሉ። የተለያዩ የዕፅዋት ዝርያዎችና እንስሳትም ይገኛሉ። በተለይ ደግሞ እንደ ቀይ ቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ የምኒልክ ድኩላ የተባሉ ብርቅዬ የዱር አራዊት

ቀደም ሲል “ደንቆሮ” ጫካ ተብሎ በሚጠራው፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በቦረና፣ በሳይንትና በወረሂመኖ (ቦ.ሳ.ወ.) ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ እንደሚገኙ ከHussien (2014:58,101-168) እና ከቦረና ሳይንት ብሔራዊ ፓርክ ጽሕፈት ቤት[3] በተገኙት መረጃዎች ተገልጿል።

በወረዳው ውስጥ ያለው አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ አምስት መቶ ዐሥራ አምስት ሲኾን፣ ከዚህ ቁጥር መካከል ወንድ ዘጠና አንድ ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት፣ ሴት ደግሞ ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ኃምሳ ኾለት ነው። የወረዳው ሕዝብ ሙሉ በሙሉ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲኾን፣ በእምነት[4] ረገድም የእስልምና እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖቶች ተከታይ ነው። አብዛኛው ሕዝብ በገጠር የሚኖር በመኾኑ መተዳደሪያውም የግብርና ሥራ ነው። ይህ በመኾኑም የተፈጥሮ ሀብትን ጠብቆ ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ለጥናቱ በተመረጡት ቀበሌዎች በየካቲት ወር 2012 ዓ.ም በዕርከን ሥራ ላይ በጋራ ተሰማርቶ እንደነበር በምልከታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ።

የቦረና ወረዳ ዋና ከተማ መካነ ሰላም ስትኾን ከደሴ ከተማ በአንድ መቶ ሰማንያና በመርጡለ ማርያም በኩል ከባሕር ዳር ከተማ በኾለት መቶ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ከተማዋ የተቆረቆረችውም በ1942 ዓ.ም እንደኾነ ይነገራል። በዚያን ጊዜ የአውራጃውን ከተማ የአውሮፕላን ማረፊያ ተሠርቶ በነበረበት የተንጣለለ ሜዳ (ጉሮ ዶባ) አካባቢና ኋላም “ሶዬ” በሚባል ቦታ ላይ ለመመሥረት ተሞክሮ ነበር። በወቅቱ መሬትን በግል ሀብትነት የያዙ ሰዎች ”እንቢ አሻፈረኝ“ ስላሉ በጊዜው የነበሩት ደጃዝማች ጎበና መካነ ሰላምን ቆረቆሩና በዚያው የአውራጃ ከተማ ኾነች። ከተማዋ “መካነ ሰላም” የተባለችበት ምክንያትም በፊት በፊት የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ከአልጋቸው ሥር መዝዘው ትከሻቸው ላይ በማድረግ “ዱር ቤቴ” ባሉ ሽፍቶች የምትታመስ አካባቢ ነበረች። ታዲያ በዛሬዋ መካነ ሰላም ዙሪያ የነበሩ መንደሮች በዐማፂዎች እሳት ሲጋዩ እሷ ግን ሳትነድና ሳትከስል በመቅረቷ “መካነ ሰላም” የሚለውን ስያሜ አገኘች (ክፍሌ ሙላት፣ 1980፡4)።

የወግዲ ወረዳ ደግሞ የደርግ የአገዛዝ ሥርዓት እስከሚወድቅበት እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በቦረና አውራጃ፣ በደብረሲና ወረዳ ሥር ይተዳደር እንደነበር ቀደም ሲል ተገልጿል። የወረዳዋ ስያሜ ወግዲ ከሚለው የከተማዋ መጠሪያ የተወሰደ ሲኾን፣ ለዚህ ቃል ትርጉም የሚኾን የጽሑፍ ማስረጃ አልተገኘም። ኾኖም ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት ከተማዋ በተቆረቆረችበት ቦታ

[3] በቦረና ሳይንት ወረዳ ብሔራዊ ፓርክ ጽሕፈት ቤት በቪዲዮ ተቀርጾ በdiretube.com ላይ የተጫነ።

[4] በእምነት ረገድ የባለቤትነት ሽሚያ ስላለ የኹለቱንም ሃይማኖቶች ተከታዮች ትክክለኛ ቁጥር መግለጽ አለመቻሉን ሰይድ ጎቸል ገልጸዋል (ቃለ መጠይቅ፣ ሰይድ ጎቸል፣ የካቲት 2፣2012 ዓ.ም፣ ቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ውስጥ)።

“ወግዴ” የሚባል ሰው ይኖር እንደነበር የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። ይህንን መነሻ በማድረግ ምናልባትም ጥንት ቦታዎችን በሰው ስም መጥራት የተለመደ በመኾኑ “ወግዴ” ከተባለው የቦታው ነዋሪ ሰው ስም የተወሰደ ሊኾን ይችላል የሚል ግምት አለ (ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ እና ወይዘሮ ዓይናለም በፀና፣ ጥር 22፣ 2012 ዓ.ም ወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት)። በ1909 ዓ.ም ግን ንጉሥ ሚካኤል ወግዲ እየተባለ የሚጠራውን ቦታ ወረገን (ከብቶች የሚቀለቡበት ጠፍ መሬት፣ የከብት ማርቢያ) ይኾን ዘንድ በተወሰኑ ባላባቶች እንዲመራ አድርገዋል። ከዚያም በ1912 ዓ.ም ራስ ካሣ ኃይሉ የወግዲን ከተማ በግምት በአንድ ጋሻ ስፋት ከከለሉ በኋላ ቀኝ አዝማች አልዩን እና አባተ ባዬን አስተዳዳሪ አድርገው በመሾማቸው አካባቢው በሥርዓት መመራት መጀመሩን የወረዳው ኮሚዩኒኬሽን በ2011 ዓ.ም የሰነደው መረጃ ያመላክታል።

የወግዲን ወረዳ በሰሜን የቦረና፣ በሰሜን ምሥራቅ የለጋምቦ፣ በምሥራቅ የከለላ ወረዳ፣ በምዕራብ የምሥራቅ ጎጃም ዞን፣ በደቡብ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ሸዋ ዞን ሥር የሚገኘው የደራ ወረዳ ያዋስኑታል። ከዚህ በተጨማሪ ወረዳው የዐባይ ወንዝ፣ ወለቃና የሹም በተባሉ ወንዞች መካከል የሚገኝ ነው። የወግዲ ወረዳ አንድ መቶ አሥራ ኾለት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ስኩዌር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አለው። ከዚህ መካከል ከሠላሳ ኾለት ሺህ በላይ የኾነው የሚታረስ ለም መሬት ያለው በመኾኑ በክልሉ ስድስተኛ፣ በዞኑ ደግሞ አንደኛ ደረጃ ከፍተኛ አምራች ወረዳ ነው። ወረዳው ቆላ (39.7%)፣ ወይና ደጋና (59.5%) ደጋ (0.8%) የሚባሉ የአየር ንብረቶች እንዳሉት የ2011 ዓ.ም የወረዳው የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ሰነድ ያመለክታል። በወረዳው ውስጥ ባለው ደጋማ ክፍል ገብስ፣ ባቄላ፣ ተልባ፣ ስንዴ፣ በወይና ደጋው አካባቢ ጤፍ፣ ሽምብራ፣ ጓያ፣ ስንዴ፣ በቆላማው ክፍል ደግሞ ማሽላ፣ በቆሎ፣ አደንጓሬ፣ አተር፣ ጤፍ በዋናነት እንደሚመረቱ ሰነዱ አክሎ ገልጿል።

የወግዲ ወረዳ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ሰንዶ ባስቀመጠው መረጃ መሠረት የ2011 ዓ.ም ጠቅላላ የሕዝቡ ብዛት አንድ መቶ ኀምሳ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስድስት ሲኾን፣ ከዚህ ውስጥ ሰባ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ሰማንያ አራት ወንዶች፣ ሰባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ኾለት ሴቶች ናቸው። የወረዳው ሕዝብ በአብዛኛው የአማርኛና ውስን በኾነ መልኩ ደግሞ የኦሮምኛ ቋንቋዎች ተናጋሪ ነው። በሃይማኖት ረገድ ሕዝቡን በቁጥር ማስቀመጥ ባይቻልም የክርስትና እና የእስልምና እምነቶች ተከታይ መኾኑን ለማወቅ ተችሏል። የእነዚህ እምነት ተከታዮች በሥርዓተ አምልኮ ብቻ እንጂ በተለያዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ልዩነት የሌላቸው በመኾኑ የአንደኛቸው መኖር ለሌሎቹ ህላዌ ናቸው።

የወግዲን ከተማ አመሠራረት በተመለከተ በ1948 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በወሎ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ የወሰን ማስተካከያ ሲያደርጉ የአሁኖቹ ከለላና ወግዲ ራሳቸውን የቻሉ የየወረዳዎቹ ዋና ከተማዎች ኾነው ቀጠሉ። የደርግ አስተዳደር በ1967 ዓ.ም ሥልጣን እንደያዘ አዲስ አወቃቀር በመፈጠሩ የተነሣ ወግዲ ከተማ የደብረሲና ወረዳ ዋና ከተማ በመኾን አስተዳደራዊ አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች። ከ1987 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ለሚና ጫቀታ የተባሉትን ሰፋፊ አካባቢዎች በማካተት ወግዲ የተባለ መስተዳድር በመመሥረቱ የደብረሲና ወረዳ ዋና ከተማ መኾኗ ሙሉ በሙሉ ቀርቶ የወግዲ ወረዳ ርእሰ ከተማ ኾና ቀጥላለች። ከተማዋ ከዞኑ ዋና ከተማ ከደሴ በአንድ መቶ ሰማንያ ኹለት ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ርእሰ መዲና ከኾነው ከባሕርዳር በደሴ በኩል በስድስት መቶ ስድሳ ኹለት ኪሎ ሜትር፣ ከአዲስ አበባ በአምስት መቶ ሰማንያ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።

የከለላ ወረዳ ደግሞ በ1903 ዓ.ም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተመሠረተ ሲኾን፣ የቀድሞ ስሙም "ገፈርሳ"[5] ነበር። በአሁኑ ወቅት ከለላ የሚለው የወረዳው ስያሜ እስከ ደርግ የአገዛዝ ሥርዓት መጨረሻ ድረስ ከላላ ይባል ነበር። ከላላ የሚለው ቃል ደግሞ ከኦሮምኛ ቋንቋ የተወሰደ ነው። አሁን ግን ከላላ የሚለው ስያሜ ቀርቶ በምትኩ "ከለላ" የተባለበት ምክንያት በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው ዓሊ ሙሐመድ በተባለ የሚመራና ከወረሂመኖ የመጣ ተስፋፊ ዓሊ ወዳጀ ቦሩ በመባል ከሚጠሩትና የመንገሥ ፍላጎት ካላቸው ጋር በዚሁ አካባቢ ጦርነት ይገጥማሉ። ከተማዋ በምሥራቅና በምዕራብ አቅጣጫዎች በተራራ የተከበበች ስለኾነች የዓሊ ወዳጀ ቦሩ ጦር ይህችን አካባቢ ስትራቴጂክ (ለጦርነት ምቹ) አድርጎ በመጠቀሙ የተነሣ በዓሊ ሙሐመድ የሚመራው ጦር ድል ተደረገ። በዚህን ጊዜ ዓሊ ወዳጀ ቦሮ "አካባቢው መከታ ኾነን፤ ከዚህ በኋላ እኛን የሚነካን እና የሚነቀንቀን የለም" በማለት ድል ማድረጋቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነግሠው አካባቢውን መግዛት ጀመሩ። ይህንን ታሪካዊ ኹነት ለመዘከር ወረዳው "ከለላ" ተባለ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ አራጋው ሐሰን፣ መጋቢት 4፣2012 ዓ.ም፣ ከለላ ወረዳ)።

ከለላ በመባል የምትጠራው ዋና ከተማም ከአዲስ አበባ በደሴ በኩል በ565 ኪሎ ሜትር፣ ከክልሉ ርእሰ ከተማ ከባሕር ዳር በ644 ኪሎ ሜትር፣ የደቡብ ወሎ ዞን ርእሰ ከተማ ከኾነችው ከደሴ ደግሞ በ164 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ወረዳው በደቡብ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ባለው በሰሜን ሸዋ ዞን ከደራና ሚዳ ወረዳዎች፣ በሰሜን ከለጋምቦ፣

[5] ጥንት በአካባቢው ሰፍረው የነበሩት ሰዎች በኦሮምኛ ቋንቋ "ኑ ገፈርሳ ሴኒ" ይሉ ነበር። ትርጉሙም ለካ ድርብ ኾንን፤ ተስፋፋን፤ ባለ ብዙ ዘርፍ ኾንን ለማለት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ አራጋው ሐሰን፣ መጋቢት 4፣2012 ዓ.ም፣ ከለላ ወረዳ)።

በምሥራቅ ከጃማና ከለገሂዳ፣ በምዕራብ ከወግዲ ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል፡፡ በከለላ ወረዳ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት በ2012 ዓ.ም በቀረበው ሪፖርት መሠረት የከለላ ወረዳ የቆዳ ስፋት አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሄክታር ሲኾን፣ ከእዚህ መካከል ለእርሻ ሥራ የዋለው ሠላሳ አምስት ሺህ ዐሥራ አምስት ሄክታር ነው፡፡ የአየር ንብረቱ ደግሞ 35%ቱ ወይና ደጋ፣ 65%ቱ ቆላማ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በእርሻው ዘርፍ በብዛት የሚመረቱት የሰብል ዓይነቶች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ማሽላ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሽንብራ፣ ምስር፣ ጓያ፣ ቦሎቄ፣ ወዘተ. ናቸው፡፡

ጽሕፈት ቤቱ በ2012 ዓ.ም ከሥነ ሕዝብና ፕላን ኮሚሽን አገኘሁት ባለው መረጃ መሠረት የወረዳው አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ አንድ ሲኾን፣ ከእዚህ አሓዝ መካከል ወንዶች ሰማንያ አራት ሺህ አምስት መቶ ዐሥራ ስድስት፣ ሴቶች ሰማንያ ሺህ ስምንት መቶ ኃምሳ አምስት መኾናቸውን አረጋግጧል፡፡ ሃይማኖትን በተመለከተ 89%ቱ የእስልምና፣ 10%ቱ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ሲኾኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ 95%ቱ ሕዝብ የአማርኛ፣ በቆላማው አካባቢ የሚኖረው 5%ቱ ደግሞ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነው፡፡ 90%ቱ የወረዳው ሕዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሲኾን፣ 10%ቱ የሚኾነው በንግድና በመንግሥት ሥራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡

የከለላ ወረዳ በበቶና በወለቃ ወንዞች የተከበበ ሲኾን፣ በቱሪዝም መስሕብነት የሚያገለግሉ የደገር ጌታው ሼህዬ መስጅድና የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳምም ይገኙበታል፡፡ በተለይ የደገር ጌታው ሼህዬ መስጅድ በሼህ ሸረፈዲን ኢብራሂም በ1860 ዓ.ም የተመሠረተ ሲኾን፣ በአካባቢው የሚገኘውን ጎብረተሰብ ጨምሮ ከአራቱም የሀገሪቱ ማእዘናት፣ እንደዚሁም ከውጭ ሀገራት የሚመጡ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታዮች በቡድንም ኾነ በተናጠል በነቢዩ ሙሐመድና በሸረፈዲን የመወሊድ በዓላት በዓመት ኹለት ጊዜ በቦታው ላይ በመገኘት ይዘይራሉ በእነዚህ በዓላት ዘያሪዎቹ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ፍየሎች፣ በጎችና ኮርማ በሬዎች ያመጣሉ፡፡ ከዚያም እንስሳቱ ከታረዱ በኋላ ሥጋው በመቀቀልና በመጠበስ በነጻ ለታዳሚው ይታደላል (ቃለ መጠይቅ፣ ከረን ሐሰን እንድሪስ፣ መጋቢት 4/ 2012 ዓ.ም፣ ከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት)፡፡ ከእነዚህ ዓመታዊ ክብረ በዓላት በተጨማሪ የአካባቢው ማኅበረሰብና ከሩቅ አካባቢዎች የሚመጡ አማኞች በየሳምንቱ ኀሙስ ሌሊትና ዕለተ ዓርብ በቦታው በመገኘት በምሥጋና እና በዱዓ እንደሚያሳልፉ በመጋቢት 3 እና 4/ 2012 ዓ.ም በቦታው ላይ ተገኝቼ ባካኼድኩት የመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

2.1.2. የቦረና፣ የወግዲና የከለላ ወረዳዎች ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች

ከሦስቱም ወረዳዎች የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤቶች የተገኙት መረጃዎች እንዳመለከቱት በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ባህላዊ አለባበስን በተመለከተ ወንዶቹ በአብዛኛው ሰፊ የኾነ ቁምጣ ሱሪ፣ እጁ ጠባብ፣ ሸሚዝ፣ ጋቢ፣ ኩታና የራስ ጥምጣም ይለብሱ ነበር። እንዲሁም በዋናነት ተለይተው የሚታወቁበትን በትር (ዱላ) ከእጃቸው አይነጥሉም። በትሩንም ጥቃትን ለመከላከልና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ይጠቀሙበታል። ለአብነትም በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ካገኘኋቸው የፉከራ ግጥሞች መካከል የሚከተሉት ይህንኑ እውነታ ያረጋግጣሉ።

ቃል ግጥም 1፡- አጅሬ አጅሬ በዚህ ወረደ
ትለሙ እንደ እሳት እየነደደ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሰሚራ ጌቶ፣ 19/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥም 2፡- የያዘው ሰፋ እጁን የሞቀው
መች ይመለሳል ሳይደባልቀው።
(ቃለ መጠይቅ፣ በለጠ አደላ፣ 19//05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በኹለቱም መንቶ የቃል ግጥሞች “ትለም” እና “ሰፋ” የሚሉትን ቃላት የርእሰ ጉዳዩን ማንጸሪያ ወይም ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። በዚህ መሠረት ትለምና ሰፋ በበረሓ አካባቢ የሚበቅሉ ቀጥና መለል ያሉ የዛፍ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ የዛፍ ዓይነቶች በጣም ጠንካራ በመኾናቸው የተነሣ ለዱላ፣ ለእርፍ፣ ወዘተ. ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ይውላሉ። በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ከእነዚህ የዛፍ ዓይነቶች ለዱላ የሚኾነውን መርጠው ከቆረጡ በኋላ አርቀውና በእሳት ለብልበው ለገበያ ያቀርባሉ። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የሚገኙት ወጣቶችም የሚፈልጉትን ዱላ ከእነዚህ ሰዎች በመግዛት በቤታቸው ውስጥ ጭስ ባለበት የቤት ጣሪያ ላይ ለወራት ያኽል ሰቅለው ያስቀምጣሉ። ይህ የሚኾነውም ዱላው ጥንካሬ ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። በመቀጠልም ወጣቶቹ በሦስት ክንድ ለክተው ካስተካከሉ በኋላ በዱላው ዐናት፣ መካከልና ግርጌ ላይ ከፍየል ቅልጥም የተገኘ ርጥብ ቆዳና ጅንፎ (ጥምዝ የብረት ቀለበት) ያስገቡበታል። ይህ ተግባር ዱላውን ከጭሱ በተጨማሪ ጥንካሬ እንዲኖረው ስለሚያደርገው ነው። ከዚህ ባሻገር በእጅ መያዣው በኩል ያለውን ጫፍ በስተው በተተለተለ ቆዳ ዛጎል ያንጠለጥሉበታል። ይህም ዱላውን ውበት ስለሚያላብሰው በሩቁ እንዲያብረቀርቅ ያደርገዋል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተዘጋጅቶ ከወጣቶች እጅ የማይለየው ዱላ በብርሃን እና በጨለማ ወቅት ለምርኩዝ ያገለግላል። የሚተናኮሉ የዱር አራዊትንም ለመከላከል ይረዳል። ከዚህ በላይ ደግሞ በተበቺሳና በሌሎች አጋጣሚዎች በሚከሠቱ ግጭቶች ወጣቶቹ ከተቃራኒ ወገን የሚሰነዘረውን ምት ይመክቱበታል፤ መልሰውም ያጠቁበታል። መክቶም ራስን መጠበቅና ማጥቃት የሚቻለው የትለም ወይም የሰፋ ዱላ የያዘው ወጣት ሐሞታም (ኃይለኛ ጀግና) ከሾነ ነው እንጂ ፍርሃት ካለበት በተቃራኒ ወገን ተቀምቶ በራሱ ዱላ በመደብደብ ሊጎዳ እንደሚችል ከመስከረም 05 — 09/2013 ዓ.ም የተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት አመላክቷል።

ሴቶቹ ደግሞ ያገቡ ከሾነ ከሸማ ምርት የሚገኙትን፣ በዓይነታቸውና በቅርጻቸው ቤጋ፣ ሐበሻ ጥልፍ ቀሚስ፣ ነጠላ ኩታ፣ መቀነት፣ የጸጉር ማሰሪያ ሻሽ የሚባሉትን የሀገረሰብ ልብሶች ይለብሱ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የፋብሪካ ውጤት የሾኑትን ብትን ጨርቆችን ከሱቅ በመግዛት በአካባቢያቸው ባሉ ልብስ ሰፊዎች አሰፍተው በመልበስ ላይ ይገኛሉ። በአንገት ላይ በሚንጠለጠሉ በድንብልና በመስቀል፣ በአምባር፣ በአሸንክታብ እና በሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ጌጣጌጦችም ይዋባሉ። በአልባሳቱና በጌጣጌጦቹም ማንነታቸውን ይገልጻሉ። በጸጉር አሠራር በኩልም ልጃገረዶቹ ጋሜና ኮልኮሎ፣ ባል ያገቡት ደግሞ ሹርባ ዋነኛ መገለጫዎቻቸው ነበሩ።

በከለላ ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያመለክተው የማኅበረሰቡ አባላት ለወንድ ልጃቸው ሚስት ሲያፈላልጉም ሾነ ሴት ልጃቸውን ለባል ሲሰጡ ጥንቃቄ በተሞላበት ኹኔታ ነው። ይሄውም የኹለቱም ወላጆች ከነልጆቻቸው በጥሩ ሥነ ምግባር የታነጹ መኾናቸውን ያረጋግጣሉ። “እናቷን አይተህ ልጅቷን አግባ” የሚለው አነጋገር በማኅበረሰቡ ዘንድ ባለው የወንድ ወገን በተግባር ላይ ሲውል ይታያል። ይህ ሳይኾን ቀርቶ በልጆቹ ትዳር ላይ ሳካ ቢፈጠር በኹለቱም ወገኖች መካከል ድልድይ ኾኖ ያቀራረበው ሰው “የአማጭ ረማጭ” ተብሎ ሲረገም ይኖራል። ከዚህ በተጨማሪ፦

ክፉ አማጪን በጦር
ደግ አማጭን መጦር።
(ቡድን ተኮር ውይይት፣ 05/01/2013፣ ከለላ ወረዳ)

የሚሉ ብሂሎች በማኅበረሰቡ አንደበት እንደሚነገሩ በቡድን ተኮር ውይይቱ ወቅት ከአቶ ተስፋዬ ጌታቸው ለማረጋገጥ ተችሏል። ምንም እንኳን የሰውን ባሕርይ እንደ ጨው ቀምሶ ማወቅ ባይቻልም መጥፎ ግብር የተላበሰውን ወጣት ውብ ባሕርይ ላላት ኮረዳ፣ ባንጻሩ ደግም ጠባይዋ ብልሹ የኾነችዋን ሴት ልጅ መልካም ነገር ከሚያደርግ ወጣት ጋር ለጋብቻ የሚያገናኘውን አማጪ መጥፎ ነገር እንዲደርስበት ማኅበረሰቡ የተመኘ መኾኑን ከመጀመሪያው

አባባል መረዳት ይቻላል። ይኸውም እንደዚህ ያለ ሰው ስለታም ኾኖ ጫፉ ድረስ ሹል በኾነ ብረት ወይም ጦር መውጋት ነበር በማለት ማኅበረሰቡ ሲያወግዝ እንመለከተዋለን። በተቃራኒው ደግሞ በግብራቸው ወይም በጠባያቸው ጥሩ የኾነ ሥነ ምግባር ያላቸውን እና ከአጸያፊ ተግባራት የራቁትን ተቃራኒ ጸታዎች ለጋብቻ ያማለደ ሽማግሌ ደግሞ ልክ እንደ አረጀና አካሉ እንደ ደከመ ሰው ምግቡን፣ ልብሱን፣ መጠለያውን እና ሌላውንም ነገር በማሟላት መንከባከብ እንደሚያስፈልግ ማኅበረሰቡ በብዛሉ አስረግጦ ተናግሯል።

በቦረና ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያመለክተው ደግሞ የወንድ ወላጆች ከላይ የተጠቀሰውን ባህላዊ መመዘኛ የምታሟላ ሴት ልጅ በአማጭ ካገኙ ሽማግሌዎችን ለልመና ወደ ሴቷ ወላጆች ቤት ይልካሉ። በዚህን ወቅት ለጥየቃ የሚኼዱት ሽማግሌዎች በመንገዳቸው ላይ ለሚያጋጥሟቸው ምልኪዎች ሁሉ ትርጉም ይሰጣሉ። ይሄውም ኮርማ በሬ ካጋጠማቸው ልጆቹ እንደሚጋቡና ወንድ ልጅም እንደሚወልዱ ይገምታሉ። ዝንጀሮ ካገኙም ልጆቹ ከተጋቡ በኋላ ሀብታሞች፣ ረድኤታሞችና ሲሳያም ይኾናሉ ብለው ያምናሉ። በማንኛውም ሚስት የመለመን ሒደት ከሴቷ ቤተሰቦች ቤት ሽማግሌዎች ሲገቡ ምጣድ ተጥዶ እንጀራ እየተጋገረ ከደረሱ የሚጋቡት ልጆች እንጀራ ያላቸው ሀብታሞች እንደሚኾኑ ይገመታል። የሽማ ውጤቶችንም ለማሠራት ድር እየተደራ (ጠንካራ ፈትል ወይም ዝላ በረኾሙ እየተዘረጋ) ካጋጠማቸው ተጣማሪዎቹ ረጅም ዕድሜ ያላቸው ባለትዳሮች ይኾናሉ ተብሎ ይታሰባል። በተቃራኒው ደግሞ በመንገድ ላይ ቀበሮ፣ እንደዚሁም ወደ ለቅሶ የሚኼዱ ሰዎች ካገኙ ጋብቻው መሰናክል ያጋጥመዋል ተብሎ ይታመናል። ሚስት የማጨት ጉዟቸውንም አቋርጠው ይመለሱና በሌላ ወቅት ሌላ ሚስት ለመለመን ይወስናሉ (ቡድን ተኮር ውይይት፣ 09/01/2013፣ ቦረና ወረዳ)።

ሚልኪዎቹ አንድምታቸው ካማረ ሽማግሌዎቹ መመዘኛውን ወደ አሟላችው ሴት ልጅ ወላጆች ቤት በመኼድ "ልጃችሁን ወይዘሪት እገሊትን ለልጃችን ለእገልዬ ለሚስትነት[6] ትሰጡን ብለን ነው የመጣነው።" የሚል ጥያቄ በአክብሮት ያቀርባሉ። ኾኖም የልጂቷ ቤተሰቦች ለቀረበላቸው ጥያቄ ወዲያውኑ ፈቃደኝነታቸውን አይገልጹም። ይኸ ደግሞ ልጃቸው የወደፊቱ ሕይወቷ የማይኾን ቦታ ላይ እንዳይወድቅ በማሰብ ጉዳዩን በሰከነ አኳኋን የማየት ብቃት እንዳላቸው ያመለክታል። ከቀናት በኋላ በሚደረግ የመረጃ ልውውጥም ከስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ርክክብ፣ ፍጥጥም እና ሰርግ ተብለው በሚታወቁ ሦስት ተከታታይ ኺደቶች ጋብቻው የሚፈጸም ሲኾን፣ በእያንዳንዱ ኺደትም ደረጃቸው የተለያየ የድግስ ሥርዓቶች ይኖራሉ።

[6] ወይዘሪት እገሊትን ለልጃችን ለእገልዬ የሚለው አነጋገር የወንዱም ኾነ የሴቷ ወላጆች ከአንድ በላይ ልጆች ካሏቸው የትኛይቱን ለየትኛው እንደጠየቁ ለማመላከት ነው።

ይኸውም በርክክብ ወቅት ከሴቷ ቤት ፍየል ወይም በግ ይታረዳል፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ጠጅ፣ ሙስሊሞች ከኾኑ ቀሪቦ፣ አሁን አሁን ደግሞ ቢራና ሌሎችም አልኮልነት ያላቸው የፋብሪካ ውጤቶች ለእንግዶች ይቀርባሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ከወንድ ቤት የተላኩት ሽማግሌዎች በባህሉ አስገዳጅነት ከተቀመጡበት ተነሥተው ይቆማሉ፡፡ በሴት በኩል የተጠሩትም ሽማግሌዎች በተቀመጡበት ኾነው “ምን ነው ቆማችሁሳ?” ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ የወንዱ ሽማግሌዎችም “አባት ኹኑን፤ ልጅ እንኾናችኋለን ብለን ነው” ብለው ይመልሳሉ፡፡ ይህ ማለት ልጃቸውን የሚያገባው ወጣት ወደ ፊት እንደ ልጅ ኾኖ እንደሚያገለግል ቃል የመግባት ኺደት ነው፡፡ የሴት ወገንም “ልጅ ከኾናችሁን አባት እንኾናችኋለን” በማለት ይመልሱላቸዋል፡፡ ይህ ምላሽም ሴት ልጃችን ለልጃችሁ የትዳር ጓደኛ እንድትኾን ፈቅደን ሰጥተናል ማለት እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቀጥሎም ከወንድ ቤተሰብ የመጡት ሽማግሌዎች እስከ አምስት መቶ፣ አሁን አሁን ደግሞ እስከ አምስት ሺህ ብርና አንድ ኪሎ ቡና ከቅጠል ጋር ከፊት ለፊታቸው በርከት ያለ እንጀራ ይዞ ከተቀመጠው መሶብ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ በሴት ወገን ከተቀመጡት ሽማግሌዎች መካከል አንደኛው ብሩን ቆጥሮ ይረከባል፡፡ ቡናውም ወዲያው እንዲፈላ ለታጨቺው ሴት ልጅ እናት ያስረክባል፡፡ በዚህ ወቅት የሚጣለው ብር ማጫ ማሠሪያ ይባላል፡፡ ይህ ኺደትም ከዚህ ዕለት ጀምሮ ልጅቷ ለጋብቻ ታጭታለች፤ ውል ታሥሯል ለማለት ነው፡፡ በኾነ አጋጣሚ ውሉ ካልፈረሰ በስተቀር ማንም ሰው ተደርቦ ልጅቷን ለሚስትነት መለመን ክልክል ነው የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባህል መሠረት ቡና አፍልቶ ተመራርቆ መጠጣት ለወደፊቱ ለልጆቹ ጋብቻ መቃናት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው የሚል እምነት በማኅበረሰቡ አእምሮ ውስጥ ያለ ሲኾን፣ ቅጠሉ ደግሞ የልጆቹ ትዳር እንዲሠምር፣ በሀብት እንዲደረጅ፣ በርካታ ልጆችን ወልደው እንዲያሳደጉ ለመመኘት ነው፡፡ በመጨረሻም በሴቷ ቤተሰቦች የተዘጋጀው ምግብ ይበላል፤ይጠጣል፡፡ እንግዶቹ መጥገባቸውን ለማመልከት እጃቸውን ሲያቆሙ እንደ የእምነታቸው “በማርያም፣ በጊዮርጊስ፣ በሼህዬ፣ በአላህ...” እያሉ አስተናጋጆቹ ይጋብዟቸዋል፡፡ “በሞቴ፣ በሞቴ” እያሉም በአፍ በአፋቸው ያጎርሷቸዋል፤ መጠጡንም ከተቀመጠበት እያነሡ በእጃቸው ይሰጧቸዋል፡፡ ከዚያም ሐሜት በተሞላበት ኹኔታ ተቀላልደውና ተሣሥቀው ይለያያሉ (ከመስከረም 05 - 09/2013 ዓ.ም በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው ጭምቃ ሐሳብ)፡፡

በክዋኔ ረገድ የፍጥጥም ሥነ ሥርዓት ከርክክቡ ብዙም የሚለይ አይደለም፡፡ ልዩነቱ በፍጥጥም ወቅት የድግሱ መጠን ከፍተኛ መኾኑና በርካታ ሰዎች መሳተፋቸው ነው፡፡ በልጆቹ ትዳር ላይ እንከን ያጋጥማል ተብሎ ስለሚታመን ወደሴቷ ቤት የሚኼዱት ሰዎች ቁጥራቸው ነጠላ

መኾን የለበትም። በአሁኑ ወቅት እነዚህ ሰዎች ቢራ፣ ለስላሳ፣ አረቄ፣ የመሳሰሉትን የመጠጥ ዓይነቶች ይዘው የመኼድ ግዴታ አለባቸው። በዚህን ወቅት ለሴቷ የሚሰጠው ጥሎሽ ግማሽ በልብስ ብቻ፣ ግማሽ ደግሞ በልብስና በጥሬ ገንዘብ፣ አለበለዚያም ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ሊኾን ይችላል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጠው ጥሎሽ ከዐሥር ሺህ እስከ ዐሥራ አምስት ሺህ ብር እያደገ ስለመጣ ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ መምጣቱን በቦረና ወረዳ በ09/01/2013 ዓ.ም በተካኼደው የቡድን ተኮር ውይይት ወቅት የተሳተፉት አምስቱም አባላት ገልጸዋል።

ይህንኑ ሐቅ ለማስገንዘብም ትዳር የፈለገ ወንድ ልጅ፡-

> ቃል ግጥም 3፡- ፍቅር ተወደደ አወጣ ሚሊዮን[7]
> እንደ እኔ ያለ ድሃ እንዴት ይኾነው ይኾን?
> (ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የሚለውን የቃል ግጥም በማዜም ላይ እንደሚገኝ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ነግሮኛል። የግጥሙ ባለቤት ዕጦተኛ፣ ችግረኛ፣ በቂ የኾነ መተዳደሪያ የሌለው ወዘተ. መኾኑን በቋጠራቸው ስንኞች አንጸባርቋል። ምንም እንኳን ከሚፈልጋት ኮረዳ ጋር ፍቅር ይዞት ትዳር ለመመሥረት ቢፈልግም ያን ያኽል ገንዘብ አውጥቶ ጥሎሽ ለመጣል ዐቅሙ አልፈቀደለትም - "ድኻ ይበላው እንጂ ይከፍለው አያጣም" ካልተባለ በስተቀር። ባለ ታሪኩ ለእሱ ብቻ አይደለም ያሰበው፤ ለእሱ መሰልና ቢጤዎቹም ጭምር ነው።

የመጨረሻው የጋብቻ (የሰርግ) ሥርዓት ከመድረሱ ከዐሥራ አምስት ቀናት በፊት ጀምሮ እስከ ሰርጉ ዋዜማ ድረስ በኹለቱም ተጋቢዎች ቤት ከየአካባቢው በሚመጡ ጎረምሳዎችና ኮረዳዎች ደማቅና ማራኪ የኾነ ባህላዊ ጨዋታ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማታ ማታ ይከወን ነበር። ይህም በአካባቢው አጠራር "ተበቺሳ" ወይም "ለፍጆሌ" በመባል ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ግን ብዛት ባላቸው አካባቢዎች ይህ ዓይነቱ የወጣቶች ጨዋታ ከኤች.አይ. ቪ. ኤድስና ከሰላም መደፍረስ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች እየቀረ መምጣቱን ከ05 — 09/01/2013 ዓ.ም በሦስቱም ወረዳዎች በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎቹ ገልጸዋል።

ወረዳዎቹን ከሌሎች አካባቢዎች ለየት የሚያደርጋቸው በተበቺሳና በተለያዩ ክብረ በዓላት ወቅት ወጣቶቹ በከንፈር ወዳጅነት[8] ላይ የተመሠረተ የተቃራኒ ጾታ ፍቅር መመሥረታቸው ነበር።

---

[7] በቃለ መጠይቅ መረጃውን በ22/05/2012 ዓ.ም ከመስክ አግኝቼ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ኃይለየሱስ ፈይሳ የተባለ የባህል ሙዚቃ ተጫዋች በሚያዝያ ወር 2012 ዓ.ም በክሊፕ ባወጣው ሙዚቃ ላይ ቃል ግጥሙን በአዝማችነት እንደተጠቀመበት ለማወቅ ችያለሁ። እሱም ቢኾን ክሊፑ ላይ ቃል ግጥሙን የሕዝብ ነው በማለት ዕውቅና ሰጥቷል።

[8] የከንፈር ወዳጅ የሚኾኑት የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ወጣቶች ናቸው። የከንፈር ወዳጅ ለመኾንም ኹለቱም ጾታዎች ያላገቡ መኾን ይጠበቅባቸዋል። በአሁኑ ዘመን ግን የከንፈር ወዳጅነቱን የመሠረቱት ወጣቶች እንደ

በዚህ ኺደትም ቆንጆ ሴት ልጅ ለከንፈር ወዳጅነት በጎረምሳዎች የመመረጥ ዕድሏ ከፍተኛ ነው። የሴቷ ምርጫ ግን በወንዶች ተጽዕኖ ሥር የወደቀ በመኾኑ በዘፈቀደ ነው እንጂ ሌላ መስፈርት የለውም። የከንፈር ወዳጅነት ክዋኔው በአካባቢው ባህል መሠረት ከንፈር ለከንፈር ከመሳሳም ያለፈ ወደሌላ ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽሞ የሚያመራ አልነበረም። ይህ ደግሞ ያን ጊዜ ማኅበረሰቡ በሥነ ምግባር የታነጸ መኾኑን ያመለክታል። ይህ ኹኔታ ግን በአሁኑ ወቅት የተቀየረ መኾኑን በ09/01/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ለመረዳት ተችሏል። ከውይይቱ ተጨምቆ የቀረበውንም ሐሳብ ቀጥለን እንመልከት።

በፊት ጊዜ ሴቶቹም ኾኑ ወንዶቹ አባትና እናቶቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ ወዘተ. ይፈሩ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን አንደኛ ቤተሰብ ሳይጠየቅ ወንዱ የሚያፈቅራትን የከንፈር ወዳጁን በመጥለፍ አንድ ቦታ ወስዶ ያስቀምጣታል። ኹለተኛ አንዲት ሴት ልጅ ጧት ተነሥታ ምንም ገበያ ሳይኖራት ገበያ አለኝ በማለት ወደ ከተማ ትኼዳለች። ከዚያም ከምትፈልገው ወጣት ጋር የምትሠራውን ሠርታ ነውር[9] ነገር ታመጣለች።

ትልቁ ነገር ትምህርትን መማር ዕውቀትን ለማግኘት ስለኾነ ጥሩ ነገር ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በትምህርት ሰበብ ጎረምሳው በመንገድ ላይ ሴቷን "እያንባባ"[10] ትምህርት ቤት ይደርሳል። ከትምህርት ቤት ሲወጣም እንደዚሁ እያንባባ ከቤት ይደርሳል። ትምህርት ለብልግና እየዋለ በመኾኑ ተቸግረናል። ስለዚህ ከባህሉና ከቤተሰብ ፈቃድ ውጭ ሴቶቹ ሳያገቡ ብልግና ይፈጽማሉ። በዚህን ጊዜ ሴቶቹ አርግዘው ተንቀፍደው ይመጣሉ። ከጋብቻ በፊት ያልተፈለገ እርግዝና ይመጣል። በመኾኑም ቤተሰብ በማፈር ላይ ይገኛል። "ከባል በፊት ልጅ ይስጥሽ" እንደሚባለው የእርግማን ዓይነት ማለት ነው። ወጣቶቹ ለአንድ ሰሞን ብቻ የሥጋ ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ በፈጸሙት መጥፎ ድርጊት ሴቷ አርግዛ ከወለደች በኋላ ሕፃኑን አባትና እናቷ ላይ በመጣል ወደፈለገችበት ትኼዳለች። ልጁም በጥሩ ኹኔታ የማደግ ዕድል የለውም። አለበለዚያም ሴቷ አርግዛ ስትመጣ በተለያዩ የሕክምና ተቋማት ወይም በሐበሻ መድኃኒት ጽንሱን ታስወርዳለች። በዚህም ለሞት አደጋ ልትጋለጥ ትችላለች በማለት ሐዘን በተሞላበት ስሜት ተወያዮቹ ገልጸውልኛል።

ድሮው ባህልን አክብረው በመሳሳም ብቻ ሳይወሰኑ ወደወሲብም እየተሸጋገሩ እንደኾነ በቡድን ተኮር ውይይቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

[9] የቡድን ተወያዮቹ "ነውር ነገር" ያሉት ዲቃላ ለማለት ፈልገው ነው። ይህም ቃሉ በማኅበረሰቡ ዘንድ አይነኬ መኾኑን ያመለክታል። ምክንያቱም ልጁ በአመንዝራ የተገኘ፣ በሕግ፣ በሥርዓት ከሚስት ያልተወለደ፣ በስርቆሽ የመጣ በመኾኑ ነው። ይህንኑ ሐሳብ ለማጠናከርም "ከልጅ ክፉ ዲቃላ፤ ከልብስ መጥፎ ነጠላ" የሚባል ምሳሌያዊ አነጋገር ሲነገር ይደመጣል።

[10] ተወያዮቹ "እያንባባ" የሚለውን ቃል በመጠቀም ጎረምሳውን ለማጥቃት ወይም ለመስረር የደረሰን የፍየል ወይም የበግ ወጠጤን ባሕርይ አላብሰወታል።



ፎቶግራፍ አንድ፡- በ09/01/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ የተካኼደውን ቡድን ተኮር ውይይት የሚያመለክት

ከመስከረም 05 — 09/2013 ዓ.ም ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ተጨምቆ ከቀረበው ሐሳብ መገንዘብ እንደተቻለው በሦስቱም ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ ወንድ ልጅ የሚያገባ ከኾነ ከሰርጉ ዕለት ሦስት ቀናት ቀደም ብሎም ሙሽራውና ቤተሰቦቹ በጋራ ኾነው በመመካከር ለሚዜ የሚኾን ሰው ይመርጣሉ፡፡ የዚህ ዓላማም ከአሁን ቀደም ከነበራቸው የሥጋ ዘመድ ላይ ሌላ ዘመድ ፍለጋ ስለኾነ ለሚዜነት የሚመረጠው ሰው ባዕድ የኾነ፣ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ በሕይወት ዘመኑ ለወንዱም ኾነ ለሴቷ ሙሽራ እንደ ወንድምና እኅት ኾኖ የሚያገለግል፣ ታታሪ፣ በችግር ወቅት ዐብሮ ተረዳድቶና ተደጋግፎ ለመኖር ይችላል ተብሎ የሚታመንበት መኾን አለበት፡፡ በሚከተለው ቃል ግጥም የተንጸባረቀው ሐሳብም የሚዜ የመምረጫ መስፈርት መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቃል ግጥም 4፡- እርሻ እረሱ አትፍቱ በጊዜ
እርሻ ያረሰ ነው የሚኾነው ሚዜ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ጦይባ ገለታ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

መንቶ ስንኞቹ አርሶ አደሮቹ ያላቸውን የሥራ ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ይመክራሉ፡፡ ስለዚህ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራ አንድ ግለሰብ ጠንክሮ በማረስ በሚያገኘው ምርት ቤተሰቡን በአግባቡ በማስተዳደር ለሌላውም ሰው በችግሩ ወቅት ስለሚደርስለት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው ደረጃ ላቅ ያለ ይኾናል፡፡ በዚህም ሰዎች ሚዜ ለተባለውና ሥጋዊ ላልኾነው ዝምድና ጭምር ይፈልጉታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ኹኔታ የሚመሠረተው የሚዜ ዝምድና ፋይዳ ደግሞ

ጥናቱ ባካለላቸው አካባቢዎች ያለውን ጎብረተሰብ ከሥጋ ዝምድና ባልተናነሰ መልኩ ያለውን ማኅበራዊ ግንኙነት የበለጠ እንዲያጠናክር ያደርገዋል።

የሰርጉ ድግስ በኹለቱም ወገኖች እንደተጠናቀቀ ሙሽራው ዐጃቢ የሚኾኑትን የቅርብ ጓደኞቹን ያዘጋጃል። ዐጃቢዎቹም በተቻለ መጠን ሆታ፣ ጭፈራ፣ ቀረርቶ፣ ፉከራና እስክስታ የሚችሉ፣ በአጋጣሚ የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጅ ጥል ቢያነሣ፣ እንዲሁም በመንገድ ላይ ከሌላ ሰርገኛ ጋር ቢገናኙና ግጭት ቢነሣ ያንን ለመመከትና ለማሸነፍ እንዲችሉ የዱላ ልምድና ብቃት ያላቸውን ወጣቶች ይመርጣል። የሙሽራው አባትም ዐጃቢዎቹ እንዳይሰክሩ የሚቆጡ፣ ሙሽራይቱን ተንከባክበው ለሙሽራው ቤተሰቦች የሚያስረክቡ፣ የሚሰጣቸውን የሙሽራ ዕቃ በጥንቃቄ የሚይዙና በአካባቢው የታወቁ ሽማግሌዎችን ይመርጣል። ሽማግሌዎቹም ከአባትዮው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመቀበል ወደሴቷ ቤት ሙሽራውን እና ዐጃቢዎችን እየመሩ ይኼዳሉ። እዚያም እንደደረሱ በባህሉ መሠረት ከቤቱ አቅራቢያ ባለ ዛፍ ሥር ይቀመጣሉ። ቀጥሎም፣ ከሴቷ አባት ቤት የተላኩ ወጣቶች ሽማግሌዎችን እና ሙሽራውን ከነዐጃቢዎቹ ወደ ቤት ያስገቧቸዋል። እንግዶቹም በተዘጋጀላቸው የክብር ቦታ ማኅበራዊ ደረጃን በጠበቀ መልኩ ይቀመጣሉ።

ወዲያውኑም እንግዶቹ ሃይማኖታቸውና ፍላጎታቸው እየተጠየቀ ጠላ፤ አረቄ፣ ጠጅ፣ ቀሪቦና ሌሎችም የመጠጥ ዓይነቶች ይሰጧቸዋል። ከአፍታ ቆይታ በኋላም በደንብ የተዘጋጀ የቀይ ወጥ፣ የአልጫ፣ የዶሮ ወጥ ምግብ ይቀርባል። ምግቡ ተበልቶ እንደተጠናቀቀ ቡና ተፈልቶ እስከሚጠጣ ድረስ ከሙሽራው ዐጃቢዎች መካከል የማቅራራት ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች በየተራ ሙሽራውን እና የሰርጉን ታዳሚዎች ለማዝናናት ሲባል ራሳቸው የሚያውቋቸውን እና በሌሎች ሰዎች የሚነገሩትን የቀረርቶ ቃል ግጥሞች በሰርገኛው መኻል ለመኻል እየተንጎራደዱ ያቀነቅናሉ (ያቅራራሉ)። በመስክ ቆይታዬ ወቅት ካገኘኋቸው የቀረርቶ ግጥሞች መካከልም የሚከተለውን በምሳሌነት እንመልከት።

ቃል ግጥም 5፡- ኧረ እናንተ ሆዬ እባብ ጥርስ አለው ወይ
ሰውን የሚጥለው ምላስ አይደለም ወይ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ትዕግስት ክብረት፣ 21/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ግጥሙ በነገረኛ ሰው የተነሣ በከፋ አደጋ ላይ ሊወድቁ የሚችሉ ሰዎች መኖራቸውን ያመለክታል። ለዚህም ገጣሚው በትይዩ ማረጋገጫን በማቅረብ መልእክቱን ሊያስተላልፍ ችሏል። ይኸውም እንበለ ጥርስ የሾነው እባብ እግር ሳይኖረው በደረቱ እየተሳበ በመኼድ በምላሱ ሰውን ከነደፈ በኋላ በመርዙ እንደሚገድል ይታወቃል። ተንኮለኛ ሰውም ቢኾን ምላሱን

ለምግብ መፍጫና በአንደበትነቱ ለመልእክት ማስተላለፊያነት ማዋል ሲገባው መርዝ በሽነው ንግግሩ ሰውን የከፋ ችግር ላይ ይጥላል በማለት አግራሞትን በተላበሰ ኹኔታ ገጣሚው ውስጣዊ ስሜቱን ገልጿል።

ከመሸራው ዐጃቢዎች መካከል በቀረርቶው ስሜታቸው የተነቃቃ ሰዎች ካሉ በተናጠልም ሽነ በጥንድ በመሽን ይፎክራሉ። የአፎካከሩ ኺደትም ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ዓይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ፣ እየተንበረከኩ፣ ደረታቸውን ወደ ፊት ገልበጥ እያደረጉ፣ ወዘተ. ዱላቸውን በመስበቅና መሬቱንም በአነስተኛ መጠን በመደብደብ፣ እንደዚሁም ጠብመንጃ ካላቸውም ቃታ ስበው የተኮሱ በመምሰል ፉከራውን ይከውናሉ። ለአብነት ያኽል የሚከተለውን የፉከራ ግጥም ማየቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

ቃል ግጥም 6፡- ከላይ ሲፈጥረን ከምሰሷችን
አልተፈጠረም ፈሪ ቤታችን።
(ምልከታ፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

የፉከራው ቃል ግጥም ማንነትን የሚያመለክት መሽኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። በመሽኑም በግጥሙ ውስጥ "ምሰሶ" የተጠቀሰው በሰው አምሳል የተፈጠሩት ገጸሰቦች የቤተሰቦቻቸው ዋነኛ መሠረት ምን እንደሽነ አጉልቶ ለማሳየት ነው። በተጨማሪም "ቤታችን" የሚለው ደግሞ የዘር ሐረጋቸውና የዝምድና ደረጃቸው የላቀ መሽኑን ያመለክታል። ይሄውም ቀድሞውንም ቢሽን ፈጣሪያችን ፈሪና ድፍረት የሌለውን ሰው በውስጣችን አልፈጠረብንም። በትውልዳችን ጀግንነትን በሚጠይቅ ኹኔታ ላይ ሁሉ ጀብዱ መሥራት፣ ብርታትና ጥንካሬ በሚያስፈልግ ሥራም ችግርን መቋቋም ስለሽነ አፈጣጠራችን ለውጤት የምንበቃ ጎበዞች ነን በማለት ነው ገጣሚው በልበ ሙሉነት ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው።

በመጨረሻም ከተፈላው ቡና አቦሉ ተቀድቶ ከተጠጣ በኋላ ሽማግሌዎቹ፣ መሸራው፣ መሸሪትና ዐጃቢዎቹ ከቤት ይወጣሉ። በባህሉ መሠረት ከቤት በሚወጡበት ወቅት ሁል ጊዜ መሸራይቱ ከመሸራው ፊት ፊት ነው የምትኼደው። በመካከላቸውም ሌላ ሰው ጣልቃ አይገባም። ምክንያቱም ወንድ የሴቷ ጠባቂ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ቀጥሎም ከቤቱ በር ፊት ለፊት ባለው ቦታ መሸራውና መሸራይቱ ቀደም ባለው ወቅት በጀንዲ[11] ላይ ይቀመጡ ነበር። ሌላው ሰው ደግሞ እነሱን ዐጅቧቸው ይቆማል። የሴቷ ወገኖችም የመሸራውን ውጫዊ ውበት ለማየት ያሰፈስፋሉ። በዚህን ጊዜ የመሸራይቱ ቤተሰቦች ከቤታቸውም ሽነ ከገበያ

[11] በአሁኑ ወቅት በማኅበረሰቡ የኑሮ ለውጥ የተነሣ ተጋቢዎቹ በጀንዲው ምትክ ከገበያ ላይ የስፖንጂ ፍራሽ እየገዙ ይጠቀማሉ።

ገዘተው ያዘጋጁላትን አልባሳትና ቁሳቁሶች ሙሽራውን ዐጅበውት ለመጡት ሽማግሌዎች እየቆጠሩ ያስረክባሉ።

ከዚህ ጎን ለጎን የሙሽራይቱ የከንፈር ወዳጅና ጓደኞቹ ዱላቸውን ወደ ላይ ይዘው ሙሽራውና ሙሽሪት በተቀመጡበት ቦታ እየዞሩ ሆታቸውን ያቀልጡታል። የዚህ ዓላማም ሙሽራይቱን ቀምቶ ለራስ ለማድረግ በማሰብ ነበር። በሆታው ወቅት ከሚያቀነቅኗቸው ቃል ግጥሞች መካከልም የሚከተለውን እንመልከት።

ቃል ግጥም፡ 7- አንቺ ዓለም ዓለም] ሹለት ጊዜ
የማይልሽ የለም የማይልሽ የለም።
ሽመሉ ረጅም ሰማይ ይጠቅሳል
ወዳጂን ቀሙኝ ብሎ ያለቅሳል።
ወዳጂን ቀሙኝ ብሎ ከማልቀስ
በሰፋ ዱላ ወርዶ መከስከስ።

(በ22/05/2012 ዓ.ም ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ)

ከአዝማቹ ውጭ ያሉት ስንኞች ትችት አዘል ናቸው። ምክንያቱም በጋብቻ የተነሣ የከንፈር ወዳጁን የተቀማው ጎረምሳ ቁመቱ በጣም ረዥም የኾነ በትር ቢሸከምም አስፈራርቶበት እንደኾነ እንጂ ምንም ነገር አልሠራበትም። እንዳውም በኃይል ወይም በጉልበት ፍቅረኛዬን ነጠቁኝ እያለ ይነፋረቃል። የከንፈር ወዳጂን ወሰዱብኝ እያለ በሐዘን ወይም በብስጭት ስሜቱ ተነክቶ ሮሮ እያሰማ ከማልቀስ ይልቅ በዐምባንሮ ወቅት ጠላትን ለመደብደቢያ ባዘጋጀው የሰፋ ዱላ እየተከታተለ ጠላቱን መነረት ወይም መደብደብ ይገባው ነበር በማለት ገጣሚው የነቀፌታ አስተያዬቱን ሰንዝሯል። ይህ በግጥሙ የቀረበው አስተያዬትም በጋብቻ አማካይነት የምትለየዋን የከንፈር ወዳጁን ቀምቶ ለማስቀረት በማሰብ በሙሽራውና በዐጃቢዎቹ ላይ ዐምባንሮ ቀድሞ እንዲያነሣ የሚገፋፋ ይመስላል። ይህንን ሲያደርግም "ያለ ወንድማማች ዐምባንሮ አያምርም" እንደሚባለው ጓደኞቹን በመከታነት ስለያዘ ሊደፋፈር ይችላል ተብሎ መታሰቡ አይቀሬ ነው።

ሽማግሌዎቹ የሙሽራዋን አልባሳትና ቁሳቁሶች ተረክበው ጉዞ ሲጀምሩ ሙሽራውና ዐጃቢዎቹም በበኩላቸው ዱላቸውን አቁመው እርስ በርሱ እያማቱ በደመቀ ኹኔታ "ሆ" ይላሉ። የሚከተሉት ስንኞችም በሆታ ውስጥ እየተካተቱ የሚዜሙ መኾናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

የሆታ ግጥም 8፡- የሼግዬን ከንፈር ወልምጠህ ወልምጠህ[12]
ወዴት ትሸሻለህ ወገብክን ለምጠህ?!

[12] ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) «ወለመጠ» የሚለው ቃል በስድብ መልክ ለማጣ፣ ቀጥተኛ የሆነ አቋም የሌለው፣ ጠንከር ብሎ መሥራት የማይወድ፣ ዋልጌ የሚል ትርጉም ቢኖረውም በቃል ግጥሙ ዐውድ መሠረት ግን ከአንገቱ ደፋ፣ ጎንበስ ብሎ የልጃገረዷን ከንፈር መሳም ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል።

እኔ እናቱ አይደለሁ ሲሸሽ የምወደው

በተራዘም ሰፋ ሳላንጎራድደው።።

(በ22/05/2012 ዓ.ም ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ)

መሽራው፣ ዐጅቦት በመጣው በሆታ አውራጁ አማካይነት ሼጋ የኾነችዋን የትዳር ጓደኛውን በከንፈር ወዳጅነት የያዘበትን ጎረምሳ "ሚስቴን ስመሃታል፤ ና እንግጠም፤ ከፍርሃትህ የተነሣ ወደኋላ ተመልሰህ ወዴት ትሮጣለህ። ጭንቅላትህ እንዳይፈነክት ከወገብህ ጎበጥ ብለህ ብትሸሽም አንላቀቅም፤ መሸሺህን የምፈልገው የምትወልድህ እናትህ አይደለሁም። ሰፋ በተባለው ረዥም ዱላ እያሯሯጥኩ ሳላንጎራድድህ አልተውህም።" በማለት ቃል ግጥሙ ሴዜም በዓይነ ኅሊናችን እናዳምጣለን። የመሽራው ዐጃቢዎች ደግሞ በተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች አምባጓሮ ፈላጊነታቸውን ያውጃሉ። ለፍልሚያ ዝግጁ መኾናቸውንም ይናገራሉ። የአካባቢው ሽማግሌዎች ግን በኹለቱ ወገኖች መካከል ግጭት እንዳይነሣ የልጅቷ የከንፈር ወዳጅና ጓደኞቹ ሆታውን አቋርጠው ወደዳስ እንዲገቡ ያደርጋሉ። ነገሩ ጠንከር ካለም በዱላ የሚማታ ሽማግሌ ይኖራል። በባህሉ መሠረት መከባበር ስላለ ተመታሁ ብሎ መልሶ ሽማግሌን የሚማታ ጎረምሳ አይኖርም። ይህ በመኾኑም ራሱን እንደ ተሸናፊ አድርጎ አይቆጥርም።

የመሽራይቱ ቤተሰቦች ልጃቸው አደጋ ላይ እንዳትወድቅ የምትጋልበውን በቅሎ ሞክረው ሻል ካለችው ላይ እንድትወጣ ያደርጓታል። ከመሽራው ጋር የመጡት ሽማግሌዎች ከፊት ከፊት፣ ዐጃቢዎቹ ደግሞ ከመሽራውና መሽሪት ጎን እና ኋላ ኾነው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ። በአካባቢው ባህል መሠረት መሽራይቱ በቅሎ ላይ ወጥታ ትንሽ መንዝ እንደጀመረች ኹለት ጊዜ በግራ እና በቀኝ ወደ ኋላ እየዞረች የአባቷን ቤትና ግቢ ማየት ይኖርባታል። ይህ የሚኾነው የራሷን ትዳር ልትመሠርት በመኾኑ የአባቷን ሀብት ወይም ሲሳይ ይዛ ወደ ባሏ ቤት እንዳትኼድ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። በዚህ ጊዜ መሽራው መሽራይቱ ወደ ኋላ እንዳትዞር በቅሎውን እያሰገረ ይከተላታል። ወደ ኋላ ከዞረችም በያዘው ዐለንጋ[13] ይገርፋታል። በዚህ ወቅት ድርጊቱን በርቀት የሚመለከቱ የመሽራይቱ ቤተሰቦች ይናደዳሉ። እነሱንም ኾነ ባህሉን ባለማክበሩ "ጋጠ ወጥ፣ ባለጌ" ወዘተ. እያሉ ይሰድቡታል። ይሁን እንጂ ደንብ ነውና መሽራው ምንም ያልሰማ መስሎ ሚስቱን ይዞ ወደ ፊት ይኼዳል።

ሰርገኞቹ ሲኼዱም ኾነ ሲመለሱ በምንም መንገድ ቢኾን መለያየት የለባቸውም። በመንገዳቸውም ላይ ለሚያጋጥሟቸው ምልኪዎች ሁሉ ትርጉም ስለሚሰጡ በመካከላቸው

[13] ከቀንድ ከብት ወይም ከጉማሬ ቆዳ የሚዘጋጅ መግረፊያ ሲኾን ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለ መሽራ የጫጉላ ቤቱን ጨርሶ እስከሚወጣ ድረስ አለንጋው ከእጁ አይነጠለውም። ይህ የሚኾነውም ሰይጣንን ይከላከልለታል ተብሎ በማኅበረሰቡ ዘንድ ስለሚታመን ነው።

ምንም አይነት ሰውም ኾነ እንስሳት አቋርጧቸው ሊያልፍ አይገባም። ይሁን እንጂ በየአካባቢው ያሉ እረኞች ሰርገኞቹ ሲመለሱ ካዩ ቅጠል በመንገዱ ላይ ከጎዘጎዙ በኋላ ራቅ ብለው ጫካ ውስጥ ወይም በድንጋይና በትልቅ ዛፍ ተከልለው ይደበቃሉ። ተምሳሌቱም "በሙሽራይቱ አገልግል ከተያዘው ዳቦ ወይም ፍትፍት ጣሉልን" ማለት ነው። በዚህ መሠረት አገልግሉን የያዘው ሰው ፈትቶ ቁራሽ ዳቦ ወይም ፍትፍት በቅጠሉ ላይ ጥሎላቸው ያልፋል። ልጆቹም ሰርገኞቹ ራቅ ብለው ከኼዱ በኋላ ከየተደበቁበት ወጥተው የተሰጣቸውን ነገር በጋራ ኾነው ይበላሉ። ሰርገኞቹ ከሙሽራው አባት ቤት ሲደርሱም ተቀባይ የኾኑ ልጃገረዶች የሙሽራውን በሰላም መመለስ ለማንጸባረቅ የተለያዩ ግጥሞችን በደስታ ይዘፍናሉ። ዘፈኖቹንም በተመለከተ ወደፊት በይዘት ትንተና ላይ በስፋት ለማቅረብ ይሞክራል።

በሦስቱም ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ የአንድ የቤተሰብ አባል በሞት ሲለይ ቤተሰቡ መሪር ኀዘኑን የሚገልጽባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው። ይሄውም እንደሚቹ ቀረቤታ፣ የዕድሜ ደረጃ፣ የአሟሟትና ሌሎች ኹኔታዎች ጋር ተያይዞ የሚቹ ወገኖች በመሪር ለቅሶ፣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ከኾኑ ደግሞ ሙሾ በመደርደር፣ ጸጉር በመላጨት፣ ለረጅም ጊዜ ጥቁር ልብስ በመልበስ፣ የፊትን ቆዳ በመንጨት፣ በአንገት ላይ ነጭ ክር በማሠር... ሐዘናቸውን ይገልጻሉ። ምንም እንኳን በመስክ ቆይታዬ ወቅት በርካታ ርእሰ ጉዳዮችን የሚያነሡ ቃል ግጥሞች በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ቢኾንም፣ ከቤተሰብ አባላት መካከል ልጅ ሲሞት ወላጆቹ ለመንፈስ ስብራትና ለመሪር ሐዘን እንደሚዳረጉ የሚያመለክተውን ቃል ግጥም ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 9፦ አባት ይሞትና ሐዘን ይታዘናል
እናት ትሞትና ሐዘን ይታዘናል
ተሁሉ ተሁሉ የልጅ ሞት ይበልጣል
ያለ ካራ መትሮ ያለ እሳት ይጠብሳል።
(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽ አብዱ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ሙሾ ደርዳሪው(ዋ) አባትና እናት ቢሞቱ በለቅሶ አማካይነት እንባን በመርጨት ሐዘኑ ይወጣል። ከእዚህ ሐዘን ሁሉ የላቀው ግን የልጅ ሞት ነው ብሏል (ብላለች)። እዚህ ላይ አንዱን ከሌላው ጋር አነጻጽሮ የማየት ነገር ይታያል። ልጅ ሲባል በዕድሜ ያልገፋውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ዐራሱን፣ ሕፃኑን፣ ትንሹንም ትልቁንም፣ ወንዱንም ሴቱንም፣ ተወልዶ ለዐቅመ አዳምና ሔዋን እስከሚደርስበት ደረጃ ድረስ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ ይመለከታል። በእነዚህ ደረጃዎች ያለ የልጅ ሞት ታላቅ አደጋ በመኾኑ የተነሣ ሐዘኑ አባትን

እና እናትን ይጎዳል። ቢላዋ በሌለበት ኩርምትምት በማድረግ ከሰውነት ውጭ ያደርጋል። እሳት አልባ በሾነ መንገድም ሐዘኑ በነዲድ ላንቃ፣ በፍም ውስጥን ጠባብሶና ለብልቦ ይጥላል የሚለውን መልእክት ከቃል ግጥሙ ልንረዳ እንችላለን። በእርግጥ ዋናዎቹ የአደጋው ተቋዳሾች እናትና አባት ቢሾኑም ተወላጆቹም የሐዘኑ ሰለባ ሊሾኑ እንደሚችሉ ማጤን ይገባል።

በየወረዳዎቹ ካሉ መረጃ ሰጪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የእስልምናም ሾነ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የአኗኗር ዘይቤ ልዩነትን ሳይሾን አንድነትን፣ ጥላቻን ሳይሾን ፍቅርን እና በሰላም ዐብሮ የመኖር መርሕን መሠረት ያደረገ ነው። ለዚህም ዕድርን ማስረጃ አድርገን ብንወስድ በአንድ የክርስትናም ሾነ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በሾነ ቤተሰብ ውስጥ ሞት ቢያጋጥም የዕድሩ አባላት የሾኑ የሹለቱም ሃይማኖት ተከታዮች በጎበረት ቀብር ከመፈጸም፣ እንግዳ ከማስተናገድና ከመሸኘት፣ እንደዚሁም ከማጽናናት በተጨማሪ ተጎጂውን ቤተሰብ በጉልበት፣ በገንዘብና በሥነ ልቡና የማገዝ ኹኔታ ይታያል። ይህ ደግሞ የየሃይማኖቶቹ ተከታዮች መደጋገፍን እና መረዳዳትን የሕይወታቸው መመሪያ ማድረጋቸውን መገንዘብ ይቻላል።

የጎበረተሰቡ አስተሳሰብ “ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው።” በሚለው ሕዝባዊ ፍልስፍና የሚገለጽ መሾኑን ተወልጀ ባደግሁበት አቅራቢያ ሲተገበር የነበረውን ሰናይ ገጠመኝ ለአብነት በመውሰድም ማረጋገጥ ይቻላል። ይሄውም በቦረና ወረዳ ምርጋጅ፣ ቀያፈር፣ ማጎሌ፣ ላይ ከቶ፣ ታች ከቶ በሚባሉት ቀበሌዎች የሚኖሩት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ሲሾን፣ ባንጻሩ የክርስቲያኖቹ ቁጥር ደግሞ እጅግ በጣም አነስተኛ ነበር። ቤተክርስቲያናቸው የሚገኘው ደግሞ ላይ ከቶ በተባለ ቀበሌ መጨረሻ ላይ በመሾኑ ርቀቱ የውሎ ገብ መንገድ ያኽል ነው። ታዲያ ሰው ሲሞት እነዚያው በቁጥር አነስተኛ የሾኑት ክርስቲያኖች ኀዘንተኛ ስለሚሾኑ አስከሬን ተሸክሞ በመኼድ የቀብር ሥርዓቱን የሚያስፈጽሙት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን ግን ለዚህ ችግር መፍትሔ ለማፈላለግ በቀያፈር ቀበሌ የሚኖሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮቹ በአካባቢያቸው ካሉ ክርስቲያኖች ጋር ተሰባስበው ተወያዩ። በውይይታቸው መጨረሻ ላይም ካላቸው የወል መሬት ላይ ቆርሰው በመስጠት የማርያም ቤተክርስቲያንን አሠሩ። ገንዘባቸውን አዋጥተው፣ ጉልበታቸውንም አስተባብረው ይህንን በማድረጋቸው ረጅም መንገድ ተጉዘው የቀብር ሥርዓቱን ያስፈጽሙ የነበሩት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የእነሱንም ሾነ የክርስቲያኖቹን ችግር ቀርፈዋል።

በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያመለክተው የኹለቱም ሃይማኖት ተከታዮች በየበኩላቸው በዓላቸውን በሚያከብሩበት ወቅት እንደ የእምነታቸው የተለያዩ ሃይማኖታዊና ሀገረሰባዊ ልብሶችን ይለብሳሉ፤ያጌጣሉም። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ዐቅማቸው በየቤታቸው በመደገስ ከወዳጅ፣ ከዘመድ፣ ከጎረቤት ጋር አብረው በመብላትና በመጠጣት ያሳልፋሉ። ሃይማኖታዊ በዓላቱ በሚከበሩበት ወቅት ጎረምሳዎቹና ኮረዳዎቹ ተሰባስበው የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ለወጣቶቹ ለወደፊት የትዳር ጓደኛ የመምረጫ ዋነኛ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል።

ባህላዊ የግጭት አፈታትን በተመለከተ በወረዳዎቹ ውስጥ ባለው ጎብረተሰብ መካከል በግለሰብም ኾነ በቡድን ደረጃ የሚከሠቱ ግጭቶች ካሉ በአካባቢው ተሰሚነት ባላቸው የሀገር ሽማግሌዎች የሽምግልና (የግልግል) ዳኝነት ታይቶ ፍትሕ ይሰጥበታል። የተሰየሙት ሽማግሌዎችም ቅራኔውን ከምንጩ በማድረቅ ጎሚ /ቅሬታ/ እንዲወርድ ያደርጋሉ። ይህ ኹኔታ ደግሞ በጎ ጎኑ አመዝኖ ይታያል። ምክንያቱም የተጋጩት ሰዎች ፍርድ ቤት በየቀጠሯቸው እየተመላለሱ ጊዜያቸውንም ኾነ ገንዘባቸውን አያባክኑም። "በሌ" ገብተው ስለኾነ የሚታረቁት ዳኝነቱ ከቂም የጸዳ ነው።

በተለይ በከለላ ወረዳ የአማሬ ቁና[14] በተባለ የዕርቅ ሥነ ሥርዓት ዘዴ ጎብረተሰቡ ሚዛናዊ ፍትሕ እያገኘ ነው። የአማሬ ቁና ሽማግሌዎችም የጠበቀ ማኅበራዊ የኾነና ያልተጻፈ መተዳደሪያ ደንብ ስላላቸው ከአነስተኛና ጥቃቅን ግጭቶች አንሥቶ እስከ ሕይወት ማጥፋት ድረስ ያለውን ወንጀል በመመርመር በአጥፊዎች ላይ ቅጣት ይጥላሉ። በዚህ ኺደትም አንዱን ወግነው ሌለኛውን አይበድሉም፣ ሲሸመግሉ አጥርተው ነው። በደልን የሚመዝኑት ባስቀመጡት ደንብ ላይ ብቻ ተመሥርተው ነው። ደንቦቹም መጀመሪያውኑ በጎብረተሰቡ ይኹንታን አግኝተው በመመሪያነት የተቀመጡ በመኾናቸው ተቃውሞን እንደማያስነሱ በከለላ

[14] በከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት በባህልና እሴቶች ተቋማት ጥናት ልማት አጠቃቀም የትግበራ ቡድን (ጎዳር 17፣2007 ዓ.ም) የተዘጋጀው ሰነድ እንደሚያስረዳው "የአማሬ ቁና" ዘመናዊ የሕግ ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት ከዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ወዲህ የአማራ ማኅበረሰብ በኾነው በሰሜን ሸዋ፣ በከለላ እና በጃማ ወረዳዎች በአገልግሎት ላይ ያለ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሲኾን፣ በአሁኑ ወቅት በየደረጃው እንዳሉት የሕግ አካላት ሕግ አውጭና ሕግ አሰፈጻሚ የሚባሉ ወገኖች አሉት። ሕግ አውጭው "ቁና ሰፊ" ሲባል ሕግ አስፈጻሚው ደግሞ "ቁና ሰጪ" በመባል ይጠራል። ኹለቱም አካላት በየዓመቱ ጎዳር ወር ላይ ለሁሉም አማካይ በኾነው "በቶ" በተባለ ወንዝ ላይ እየተገናኙ የቀደምት ውሳኔዎች መፈጸም አለመፈጸማቸውን ያረጋግጣሉ። አዳዲስ አቤቱታዎችንም ያዳምጣሉ፤ ውሳኔም ያስተላልፋሉ። ውሳኔዎቻቸውም ከወቅቱ ጋር ተገቢነት እንዲኖራቸው ባህላዊ የኾነውን ሕግ በየዓመቱ ይከልሳሉ። የተሻሻለ ካለም ለማኅበረሰቡ ያሰራጫሉ። በሕግ አውጭነትም ኾነ በሕግ አስተርጓሚነት ሽማግሌዎቹ የሚመረጡት በማኅበረሰቡ ሲኾን፤ ለነገሮች ትኩረት ሰጥተው ጉዳዮቹን በትክክል የሚመዝኑ፣ ተሰሚነት ያላቸው መኾን አለባቸው።

ወረዳ ከተካሄደው ቡድን ተኮር ውይይትና ከወረዳው የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል።

እንደሚታወቀው የሰው ልጅ በማኅበር እንጂ በተናጠል የሚኖር ፍጡር ባለመኾኑ በየወረዳዎቹ ያለው ማኅበረሰብም በርካታ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን የሚፈጽምባቸው ዕሴቶች አሉት። ከእነዚህ መካከል ደቦ፣ ርጥባን፣ ወንፈል፣ ወዘተ. በመባል የሚታወቁት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከእነዚህ ማኅበራዊ ዕሴቶች አንዱ የኾነው ደቦ አንድ ሰው ብቻውን መሥራት የማይችላቸውን የግብርና ሥራዎች (የእርሻ፣ የአረም፣ የአጨዳ፣ ወዘተ.) በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ዋነኛ የመደጋገፊያና የመረዳጃ ሰናይ ተግባር ነው። ርዳታ የሚደረግለት ሰውም ቢኾን ሥራውን ሲያሠራ በዋለበት ቀን የሚበላና የሚጠጣ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ግለሰቡ ይህንን የሚያደርገው ግንኙነቱን ለማጠናከር ብቻ ሳይኾን አንዳች መጥፎ ወይም ክፉ ነገር ይድረስብህ ተብዬ እረገማለሁ ብሎ በማሰብ ነው። አንድ ግለሰብ ሰው ሠራሽም ኾነ የተፈጥሮ አደጋ ከደረሰበትም ዘመድ ወዳጅን ርጥባን[15] ይጠይቃል። የተጠየቁትም ሰዎች ዐቅማቸው የፈቀደውን ያኽል ይረዱታል። ወንፈል በተባለው የመረዳጃ ባህልም ሰዎች በየተራ ሥራዎቻቸውን ያከናውኑበታል።

ሌላው የማኅበራዊ ግንኙነት መገለጫው ደግሞ በሰርግ ሥርዓት ወቅት ለሚከናወነው ድግስ ድጋፍ የሚኾን አዝማች ከሰርጉ ባለቤት ጋር ከፍተኛ ቀረቤታ ያላቸው ሰዎች ደግሰው ያበላሉ፤ ያጠጣሉም። እነዚህ ከላይ በዝርዝር የቀረቡት መልካም ተግባራት ማኅበራዊነት ህልው እንዲሆን ከፍተኛ የኾነ አስተዋፅኦ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በየወረዳዎቹ ያሉት መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎችና ማኅበረ ባህላዊ ዳራዎች የተዳሰሱት በማኅበረሰቡ አንደበት ለሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች መሠረት ይኾናሉ ተብሎ በመገመታቸው ነው።

15 ርጥባን የሚደረግለት ሰው ከራሱና ከቤተሰቡ ዐቅም በላይ የኾነ ጉዳት ከደረሰበት ማለትም መኖሪያ ቤቱ ቢቃጠል፣ የእርሻ በሬው ቢሞት፣ ሰብሉ በተለያዩ ምክንያቶች ቢወድም፣ የሰው ሕይወት ቢያጠፋና በሀገር ሽማግሌዎች ካሳ እንዲከፍል ቢደረግ ሰዎች እጃቸውን እንዲዘረጉለት የሚያደርግበት የልመና ዓይነት ነው።

ምዕራፍ ሦስት፡- ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ በመጀመሪያ የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ፣ ቀጥሎም የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ተካኺዷል። በመጨረሻም ለጥናቱ በተመረጡ የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፎች ላይ ትንታኔ ተሰጥቷል።

3.1. የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ

በአንድ የምርምር ኺደት በቀደምት ጥናቶች ላይ ዳሰሳ ማድረግ የአጥኚውን ዕውቀት ለማበልጸግና ሐሳቡንም ለማጎልበት እንደሚረዳ የታወቀ ነው። እንደዚሁም የተጠናውን እና ያልተጠናውን ርእሰ ጉዳይ ለይቶ ለማወቅ ያስችላል። ይህም ተደጋጋሚና ተመሳሳይ የኾኑ ምርምሮች እንዳይካኼዱ ስለሚረዳ አዲሱ ጥናት ይዞት በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲያነጣጥር ያደርጋል። በዚህ ጥናትም የተደረገው የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች መነሻ በማድረግ ነው።

በዚህ መሠረት ቃል ግጥምን በተመለከተ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂደማኒቲስ፣ በቋንቋዎች ጥናት፣ በጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ በባችለር፣ በማስተርስና በፒኤች. ዲ. ዲግሪ ደረጃ በተለያዩ ክልሎች በርካታ የመመረቂያ ጽሑፎች ተሠርተዋል። እነዚህን ሥራዎች በሙሉ በዚህ ጥናት መቃኘት የማይቻል መኾኑን አምኜበታለሁ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ጥናቱ ሙሉ በሙሉ በቅኝት ላይ ብቻ የሚታጨቅ መስሎ ስለታየኝ ነው። በመኾኑም ከተጠኑበት ርእሰ ጉዳይ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ አምስት የባችለር ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፎች ተዳስሰዋል። ቃል ግጥምን የጥናታቸው ርእሰ ጉዳይ አድርገው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማኅበረሰቦች ላይ ብቻ የተሠሩ ዐሥራ አንድ የማስተርስና ሦስት የፒኤች ዲ. ዲግሪ፣ በድምሩ ዐሥራ ዐራት ጥናቶችም ተቃኝተዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች በተጨማሪ በ16ኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ የኢትዮጵያ ጥናት ቅፅ 4 ላይ የታተመውና በታሪክ ላይ የተመሠረቱ የፉከራ ቃል ግጥሞችን ያካተተው ምርምር፣ እንደዚሁም ረኃብን መሠረት በማድረግ ትንተና የተደረገባቸውን የቃል ግጥሞች የያዘው መጽሐፍም ተቃኝቷል። በመኾኑም ከእነዚህ ሥራዎች መካከል የባችለር ዲግሪ ማሚያ የኾኑት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በሚከተለው ኹኔታ ተዳስሰዋል። ሌሎቹም ቢኾኑ በየተሠሩበት ዓመተ ምሕረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ተቃኝተዋል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚቻለው ቅኝት የሚካኼድባቸውን ጥናቶች በየጭብጣቸው በማቧደን በጋራ የሚታዩባቸውን ጥንካሬዎችና

ድክመቶች በንጽጽር ለመተንተን አልተቻለም። ምክንያቱም የየጥናቶቹ ጭብጦች በጣም የተለያዩ በመሆናቸው የተነሣ ነው።

ጥናቱ ከተሠራበት ዓመተ ምሕረት አንጻር በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከትኩት ደስታ ካሳ በ1985 ዓ.ም ‹‹በደርግ ዘመነ መንግሥት ላይ የተገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና›› በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችውን ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የደስታ ጥናት ዋና ዓላማ በግጥሞች አማካይነት ሕዝቡ በመንግሥት ላይ ምን አይነት አመለካከት እንደነበረው መመርመር ነው። መረጃዎችን ከመስክ የሰበሰበችው በልዩ ልዩ የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራንና ከተማሪዎች፣ ከመጻሕፍትና ከጋዜጦችም ጭምር እንደሆነ ገልጻለች:: ቃል ግጥሞቹም አስተዳደራዊ ጉድለቶችን፣ በሥልጣን መባለግን፣ ጉቦን እና ምዝበራን፣ ቀይ ሽብርን፣ ውትድርናን፣ ስደትን፣ ሰፈራን፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀትን፣ ለትግል መነሣሣትን፣ ወዘተ. የሚያመለክቱ ናቸው:: በዚህ መሠረት ይህ ጥናት ከደስታ ጥናት ርእሰ ጉዳዮች ጋር በጣም የተለየ ነው። አጥኚዋ ከመስክ የሰበሰበቻቸውን መረጃዎች የተነተነችባቸውን ንድፈ ሐሳቦች ባለማመላከቷ ጥናቷ ክፍተት ታይቶበታል ማለት ይቻላል።

ቀጥሎም ቅኝት የተካኼደው ሞላ መኮንን በ1986 ዓ.ም “በቆቦ ወረዳ የተነገሩ ፖለቲካ ቀመስ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና” በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። አጥኚው ከ1966 እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ የተገጠሙትን ቃል ግጥሞች ይዘት በትንተናው ተመልክቷል:: መረጃዎችንም በአብዛኛው የሰበሰበው በሰፈራ ምክንያት ሌላ አካባቢ ቆይተው ከተመለሱ ግለሰቦች ሲሆን፣ ከመረጃ ሰጪዎቹ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞችም ሰፋሪዎቹ የሰፈሩባቸውን አካባቢዎች የህይወት ውጣ ውረዶች የሚያንጸባርቁ እንደነበሩ በጥናቱ ተገልጿል:: የሞላ ጥናት ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ፣ ንድፈ ሐሳቦችን ካለመጠቀሙ፣ ካተኮረባቸው ርእሰ ጉዳዮች አንጻር ሙሉ በሙሉ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል።

ጎበና ጌታነህም በ1986 ዓ.ም “በወሎ /ቦረና/ ‘የቆንጆ’ ዘፈን ግጥሞች” በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል። የጎበና ጥናት ዋና ዓላማ “የቆንጆ” ዘፈን ግጥሞች የሥነ ቃል ዘርፍ በመኾናቸውና በጊዜ ብዛት ሊረሱ ስለሚችሉ “በቃል ያለ ይረሳል፤ በጽሑፍ ያለ ይወረሳል” የሚባለውን ሐቅ በመገንዘብ በጽሑፍ ተመዝግበው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩበትን መንገድ ለማመቻቸት እንደኾነ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ እስከዛሬ ድረስ

ቃል ግጥሞችን በተመለከተ ከተሠሩት አንዳንድ ጥናታዊ ጽሑፎች የቦረና የቆንጆ ዘፈን ግጥሞች በቅርጽ ረገድ ለየት ያሉ ባሕርያትን የሚያሳዩ መስለው ስለታዩት ይህንንም ለማስተዋወቅ እንደኾነ አመላክቷል።

አጥኚው በተለያዩ አጋጣሚዎች ዘጠና ዘጠኝ የቃል ግጥሞችን የሰበሰበ ሲኾን፣ አሰባሰበቡም በአካባቢው በአካል በመገኘት ልጃገረዶችን እና አረጋዊያንን በቃል ጠይቆ ያገኘውን ምላሽ በማስታወሻ በመያዝ ነው። ሌላው ዘዴው ደግሞ በቀጥታ ትምህርት ቤት በመኼድ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በቤት ሥራ መልክ አዝዘው ካሰባሰቧቸው የቃል ግጥሞች ውስጥ ለጥናቱ የሚኾኑትን መርጦ በማጠናቀር ነው። ከእነዚህም ሌላ በዘፈን መከወኛ አጋጣሚዎች በመገኘት ዜማውን በካሴት በመቅረጽ፣ እንዲሁም ቀደም ሲል አንዳንድ ግለሰቦች ከቀረጹዋቸው ካሴቶች ላይ የድጋሜ ቀረጻ በማካኼድ ነው።

ጎበና በዘመኑ የተሻለ ጥናት ማቅረብ ችሏል የሚል አስተያየት አለኝ። ምክንያቱም የቆንጆ ዘፈን መከወኛ አጋጣሚዎች ተበቺሳ፣ ማገዶ የመልቀሚያ ቦታዎች (የኩበት፣ የእንጨት)፣ የውሃ መቅጃ ወንዝ ወይም ምንጭ፣ የእረኝነት ቦታ፣ የዐረም ወቅት፣ ክብረ በዓላት (ቅዱስ ዮሐንስ ወይም የዓመት መለወጫ)፣ የመስቀል ዋዜማ፣ ሚጊራጉራና ጭንቁርሳ[16]፣ የገና ዋዜማ፣ ጥምቀት፣ ወዘተ. መኾናቸውን በመዘርዘር በእነዚህ አጋጣሚዎች የሰበሰባቸውን ሁሉንም የቃል ግጥሞች ተንትኗል።

አጥኚው በዋናነት የተመለከታቸው የቆንጆ ዘፈን ግጥሞች በአብዛኛው ይዘታቸው የውዳሴ ግጥሞች ሲኾኑ፣ እነዚህም የከንፈር ወዳጅን፣ የከንፈር ወዳጅን እናት፣ የከንፈር ወዳጅን እኅትና ወንድሞቹን፣ መልክን በተለይ ጠይምነትን፣ ሴት ጓደኛን፣ ቤተሰብን፣ ባለሥልጣናትን የሚያሞግሱ ናቸው። ስለፍቅር ምንነት፣ በፍቅር ላይ ስለሚነሡ ነገረኛነትና ስለምቀኝነት፣ ከከንፈር ወዳጅ ጋር ስለመቃቃር፣ ስለመለያየት፣ ይቅርታ ስለማድረግ፣ ስለስድብ (የከንፈር ወዳጅን ስለነጠቀች ልጃገረድ)፣ ያላቻ ስለኾነ የከንፈር ወዳጅነት በትንታኔው አመላክቷል።

በስልት ረገድ ደግሞ ግጥሞቹ በዘይቤዎች፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮችና በፈሊጦች የተገነቡና በአብዛኛው የወል ቤት መኾናቸውን አጥኚው በትንተናው አመላክቷል። የአዝማች መደጋገም፣ የመነሻ ስንኞች ከቀጣዩ ወይም ከቀጣዮቹ ስንኞች ጋር የሐሳብ አንድነት አለመኖር፣ በልጆች አንደበት በቀላሉ እንዲታወሱ ለማድረግ ከየስንኞቹ አንድን ቃል ወይም ሐረግ በመውሰድ በተከታታይ ባሉት ስንኞች ውስጥ መድገም፣ የቅብብል ወይም የምልልስ ግጥሞች መሰናሰል፣ ግጥሞቹ መደጋገማቸውና መሰናሰላቸው ደግሞ ታዋሺነት እንዲኖራቸው መድረጉ፣ አንድ

[16] ሚጊራጉራና ጭንቁርሳ የስንደዶና የአክርማ ቀጨታ ወቅቶች ማለት ነው።

ዓይነት ይዘት ያላቸው ግጥሞች እስከ ኻያ ስንኞች ድረስ የመርዘም ኹኔታ እንደሚታይባቸው ጎበና አስረድቷል።

የጎበና ጥናት በቆንጆ ዘፈን የመከወኛ አጋጣሚዎችና በአጋጣሚዎቹም በሚዘፈኑት ግጥሞች ይዘት ላይ በማተኮሩና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። በሌላ በኩል ግን ቅርጽን እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ በመመልከቱ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ በሚያገለግሉ ግብዓቶችና በግብርና ሥራዎች በተነገሩ ቃል ግጥሞች ላይ ባለማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር እንዲለይ ያደርገዋል። ስለዚህ ይህ ሥራ የጎበና የጥናት ርእሰ ጉዳይ ባልሆኑት ላይ ጥልቅ ፍተሻ በማካኼድ ክፍተትን ይሞላል ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ በተጨማሪ ጎበና በተለያዩ ዘዴዎች የሰበሰባቸውን ቃል ግጥሞች ለመተንተን የተጠቀመው ንድፈ ሐሳብ ስላልነበረ ይዤንን ጉድለት ጥናቱ ይሞላል ተብሎ ይገመታል።

በመቀጠልም ካሳው ደሳለው በ1997 ዓ.ም “የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና” በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበውን ጥናት ለመመልከት ተችሏል። አጥኚው የጥናቱን ዋና ዓላማ ባያሰፍርም ንኡሳን ዓላማዎቹ ግን ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ሰው ሲሞት የሚከናወነውን የለቅሶ ሥርዓት ማሳየት፣ አስለቃሾች የሚያሰሟቸውን የሙሾ ግጥሞች ይዘት መተንተን፣ በክርስትና (በኦርቶዶክስ) እና በእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን የለቅሶ ሥርዓት ልዩነት ማስረዳት የሚሉት ናቸው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ደግሞ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው። የካሳው ጥናት በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። አጥኚው በተፈጥሯዊ መቼት በአካል ተገኝቶ የለቅሶውን ሥርዓት ለመመልከትና ግጥሞቹንም በማስታወሻ ደብተር ለመያዝ ችሏል። በዚህ አካኼድም ኹለት መቶ ኃምሳ የቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በኃምሳ አንዱ ላይ የይዘት ትንተና አካኺዷል። ሌሎቹን ደግሞ በኣባሪነት አያይዟል።

የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተናንም በተመለከተ አባት ሲሞት፣ እናት ስትሞት፣ ወንድም ሲሞት፣ እኅት ስትሞት፣ መካን ሴት ስትሞት፣ አራስ የኾነች ስትሞት፣ ጀግና ሲሞት የሚደረደሩ ግጥሞችን በየዘውጋቸው በመከፋፈል ተንትኗል። የእኔ ጥናት ግን ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን፣ የግብርና ሥራዎችን በተመለከተ በተነገሩ፣ እንደዚሁም በልጃገረዶች በተቀነቀኑ ቃል ግጥሞች ላይ በማተኮሩ ከካሳው ጥናት ይለያል። በኹለቱ ጥናቶች መካከል ያለው ተመሳስሎ ደግሞ የለቅሶ ቃል ግጥምን መመልከታቸው ነው።

በመጨረሻ ላይ የተመለከትኩት እንድሪስ ይማም በ1997 ዓ.ም “የዛር ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በወግዲ ወረዳ” በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበውን ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የጥናቱ ዓላማ ለዛር የሚዘፈኑና የሚዜሙ ግጥሞች የማኅበረሰቡን ስሜትና አመለካከት ስለሚገልጹ የወረዳው ነዋሪ ለዛር ያለውን እምነት መግለጽ፣ የዛር ዘፈን ግጥሞቹ ከዛር መንፈስ ልመና ክዋኔ ጋር ያላቸውን ግንኙነት መተንተን የሚሉት ናቸው። አጥኚው አንድ መቶ አርባ ስድስት የቃል ግጥሞችን የሰበሰበው ከዐሥራ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ ታዋቂ ባለዛሮችን እና ዛር አስታራቂዎችን መርጦ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውን እና ጎረቤቶቻቸውን በመጠየቅ የቃል ግጥሞችን በጽሑፍ እንዲሰጡት አድርጓል። ሰነድ ፍተሻንም ለመጠቀም ችሏል። በእነዚህ ዘዴዎች ከሰበሰባቸው የቃል ግጥሞች መካከል በዐሥራ ዘጠኙ ላይ ትንተና አካኺዷል። የእንድሪስ ጥናት ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ በማተኮሩና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም ቃል ግጥሞቹ ግን ለዛር የሚዘፈኑና የሚዜሙ በመኾናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ሙሉ በሙሉ ልዩነት አላቸው።

ከባችለር ዲግሪ የማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀጥሎ ቅኝት የተካኼደባቸው ለማስተርስ ዲግሪ መርሓ ግብር የቀረቡት ጥናቶች ናቸው። ከእነዚህ መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል አምስት፣ ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ እንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል ስድስት በድምሩ ዐሥራ አንድ ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን የሚያነሡ በመኾናቸው ከይዘት አንጻር በፈርጅ በፈርጅ ከፋፍሎ ለማቅረብ ባይቻልም በየቀረቡበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል በሚከተለው ኹኔታ ተቃኝተዋል።

ሞገስ ሚካኤል በ2002 ዓ.ም “በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካኼድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው” በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት መርሓ ግብር ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማሟያ ጽሑፉን አቅርቧል። የጥናቱ ዓቢይ ዓላማም በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረገውን የጀግና የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅረጽ፣ በቴፕ በመቅዳትና ፎቶግራፍ በማንሣት እንዲቀረስ ማድረግ ነው። እኔ ግን በዚህ የትምህርት ደረጃ ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ ከመቅረስ በዘለለ ላቅ ያለ ዓላማ መቀረጽ ነበረበት የሚል አስተያየት አለኝ።

ሞገስ ኹለት መቶ የቃል ግጥሞችን ቢሰበስብም በቀብር ሥነ ሥርዓት ወቅት ስለሚደረጉት ክዋኔዎች ሰፊ ትኩረት በመስጠት አራቱን ብቻ ተንትኗል። አጠቃላይ መረጃዎቹን ከመስክ

የሰበሰበውም በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሲሆን፣ መሣሪያዎቹ ደግሞ ድምፀ መቅረጽ፣ ቪዲዮ ካሜራና ፎቶ ካሜራ ናቸው። እኔ ግን በሦራሁት ጥናታዊ ጽሑፍ ቡድን ተኮር ውይይትን በመጠቀሜ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴያችን ልዩነት ኖሯል። በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ግን የኹለታችንም ሥራዎች ተመሳሳይነት አላቸው። የአጠናን ዘዴውን በተመለከተ ደግሞ ገላጭ ዘዴን ከመጠቀሙ ውጭ ዓይነታዊ የሚባለውን የምርምር ዓይነት ስለመጠቀሙ አልገለጸም። ስለቀብር ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም በቂ ዕውቀትና ልምድ አላቸው የተባሉትን የሃይማኖት ሰዎችን፣ አዛውንቶችን፣ ፎካሪዎችን እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በታላሚ ሁነኛ ናሙና በመምረጡ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን ሞገስ የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፉ አልተጠቀሰም።

ማሞ ተፈራ በ2002 ዓ.ም "በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር የመመረቂያ ጽሑፉን አቅርቧል። የጥናቱን ዋና ዓላማ በተመለከተም በዳንግላ ወረዳና አካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች በመኸር ወቅት የሚከውኗቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መግለጽ፣ ከሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ዓቢይ የሆኑ ጭብጦች ላይ ትንተና ማድረግ የሚል ነው። ከዓላማ አንጻር ቃል ግጥሞችን ከመተንተን ውጭ ሀገረሰባዊ እምነቶች ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ የእኔ ጥናት ስለማይመለከት በኹለቱ ጥናቶች መካከል ልዩነት ታይቷል።

የአጠናን ዘዴውን በተመለከተም ጥናቱ ዐውድ ተኮር በኾነ ገላጭ ምርምርና የጭብጥ ትንተና ላይ የተመሠረተ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹም ምልከታና ያልተዋቀሩ ቃለ መጠይቆች ናቸው። አጥኚው በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንድ መቶ ኃምሳ ኹለት ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በአርባ ስድስቱ ላይ ትንተና አካኺዷል። ማሞ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ሊኖረው ቢችልም የትኛውን የጥናት ዘዴና የናሙና ዓይነት እንደተጠቀመ ባለመግለጹ፣ በየትኛው የንድፈ ሐሳብ ማእቀፍ መረጃውን እንደተነተነ ባለማሳየቱ ደግሞ ልዩነት ተስተውሏል።

ጋሻው አሻግሬ በ2005 ዓ.ም "በእብናት ወረዳ ከባህላዊ ወፍጮ ዐውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ያቀረበውን ጥናት ተመልክቻለሁ። የጽሑፉ ዐቢይ ዓላማ ጥናቱ በሚካኼድበት ወረዳ በባህላዊ የወፍጮ ዐውድ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ላይ ትንተና በማካኼድ የሴቶቹን

ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቡናዊ መልኮችን ማሳየት ነው። በዚህ ዓላማ አማካይነት አጥኚው ከሰበሰባቸው ስድስት መቶ ዐሥራ ኹለት የባህላዊ የወፍጮ ቃል ግጥሞች መካከል ከዐውዳቸው አንጻር ኃምሳ አምስቱን ብቻ በመተንተን መልእክታቸውን ገልጿል። የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች መቼ፣ ለማን እና ለምን እንደሚከወኑ በመለየትና በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ያሉ ትእምርቶችን እና የመባያ ጉዳዮችን ዘርዝሮ በማውጣት መተንተንም ችሏል። የአጥኚው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። ከዚሁ ጋር መቅረጸ ድምፅ፣ ፎቶ ካሜራና የማስታወሻ ደብተር በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ተግባር ላይ ውለዋል።

በደቡብ ጎንደር በእብናት ወረዳ የተከናወነው ይህ ጥናት በአንድ የቃል ግጥም ዘውግ ላይ ብቻ በማተኮሩ ከእኔ ሥራ ጋር ሊለይ ችሏል። ከዚህ ውጭ ግን የቃል ግጥሞቹን ከዐውዳቸው ሰብስቦ በመተንተን፣ ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን እና የቡድን ተኮር ውይይትን በመጠቀም፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መቅረጸ ድምፅን፣ ፎቶ ካሜራን እና የማስታወሻ ደብተርን አገልግሎት ላይ በማዋል ረገድ ኹለቱም ጥናቶች ተመሳሳይነት ታይቶባቸዋል። ምንም እንኳን የእኔ ጥናት የሥራ ቃል ግጥሞችን የሚመለከት ቢኾንም ከባህላዊ ወፍጮ ዐውድ ላይ የሚሰበሰቡትን የቃል ግጥሞች ሙሉ በሙሉ ስለማይመለከት ልዩነት ይኖራል።

ሀብታም ግዛትም በ2006 ዓ.ም “የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የሥራ ግጥሞች ክዋኔና ማኅበራዊ ሕይወታቸው” በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ለጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር የመመረቂያ ጽሑፏን አቅርባለች። የአጥኚዋ ዓላማ የዳባት ወረዳ ገበሬዎች በተለያዩ የሥራ ዓይነቶች (አጋጣሚዎች) ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን የቃል ግጥሞች በዐውዳቸው በመሰብሰብ የሚያነሟቸውን ርእሰ ጉዳዮች መተንተን፣ የግጥሞቹን ማኅበራዊ ፋይዳ መግለጽና ገበሬዎች ያላቸውን ማኅበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ኑሮ ማሳየት የሚል ነው።

ይህንን ዓላማ መሠረት በማድረግ አጥኚዋ ገበሬዎቹ ግጥሞችን ከሚደረድሩባቸው የሥራ ዓይነቶች መካከል ከአውድማ፣ ከአጨዳ፣ ከእርሻ፣ ከጉልጓሎና ከአረም ዐውዶች ላይ አምስት መቶ የቃል ግጥሞችን ሰብስባ በኃምሳ አራቱ ላይ ገለጻና የይዘት ትንተና አካኺዳለች። እነዚህ አጋጣሚዎች የተመረጡበት ምክንያት የሥራ ዓይነቶቹ ሲከወኑ ገበሬዎቹ ራሳቸውን ለማነቃቃትና ሥራቸውን ለማፋጠን በርካታ ቃል ግጥሞችን የሚያቀነቅኑባቸው በመኾኑ ነው። ገበሬዎቹ እያንዳንዱን የሥራ ዓይነት ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸው ግጥሞች ርእሰ ጉዳዮችም

ተተንትነዋል። አርሶ አደሮቹ እርስ በርሳቸው ያላቸው ማኅበራዊ ግንኙነትና የዕለት ተዕለት ውሎ ምን እንደሚመስል አጥኚዋ ገልጻለች። የቃል ግጥሞቹን አደራረስ፣ ተስተላልፎና በማን፣ ለማን፣ ለምን፣ እንዴት፣ እንደሚከወኑ አብራርታለች። የሥራ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ወቅት ከዋኝና ተሳታፊዎች ያላቸውን ሚናም አስረድታለች።

ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው። ምንም እንኳን በምልከታ መረጃ ሲሰበሰብ ተሳትፏዊ፣ ጥሞናዊና ኅቡእ የተባሉ የምልከታ ዓይነቶች ቢኖሩም አጥኚዋ ተሳትፏዊና «ጥሞናዊ» የተባሉትን ዘዴዎች ብቻ በጥናቷ ተጠቅማለች። ይህንን በምታደርግበት ወቅት መረጃዎችን በማስታወሻ ደብተርና በመቅረጸ ድምፅ ለመያዝ ችላለች። በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ስትሰበሰብ ከዋኞቹን እና ታዳሚዎቹን የጾታ፣ የዕድሜና የሙያ ስብጥር በማድረግ ነው። ለመረጃ ሰጭዎች የቀረቡት የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ክፍትና ዝግ ናቸው። የናሙና አመራረጥን በተመለከተ በዳባት ወረዳ ከሚገኙ ቀበሌዎች መካከል ሰባቱ በርካታ የቃል ግጥም ደርዳሪ ገበሬዎች የሚገኙባቸው በመኾኑ በዓላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል። በመረጃ ትንተና ወቅትም ክዋኔ ተኮርና ተግባራዊ የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፍን ተጠቅማለች።

ሀብታም ግዛት ጥናቷ በአንድ የቃል ግጥም ዘርፍ ላይ ብቻ በማተኮሩና በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎችን መሰብሰብ ባለመቻሉ እኔ ካካኼድኩት ጥናት የተለየ ያደርገዋል። ኾኖም ግን በግብርና ሥራ ላይ የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን ከየሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ማለትም ከዐውድማ፣ ከዐጨዳ፣ ከእርሻ፣ ከጉልጓሎና ከዐረም ዐውዶች በመሰብሰቧና ትንተና በማካሄዷ፣ እንደዚሁም ገበሬዎቹ ሥራዎቻቸውን ሲያከናውኑ የቃል ግጥሞቹ የማነቃቃትና ሥራን የማፋጠን ፋይዳ እንዳላቸው በመግለጿ፣ ክዋኔ ተኮርና ተግባራዊ የተባሉትን ንድፈ ሐሳቦች በመጠቀሟ የእሷ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

በትምህርት ክፍሉ በማስተርስ ዲግሪ ደረጃ ከቀረቡት ጥናቶች መካከል በመጨረሻ ላይ ቅኝት የተካኼደው መኰንን አስማማው በ2007 ዓ.ም “በደላንታ ወረዳ የአበሹቱ እና የኧኸይቦሌ[17] ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና” በሚል ርእስ የሠራው ጥናት ነው። ይህም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የቀረበ ነው። የጥናቱ ዓላማ በደላንታ ወረዳ የአበሹቱና የኧኸይቦሌ ቃል

[17] የአበሹቱ እና የኧኸይቦሌ ሴቶች በሃይማኖት ክብረ በዓላት ቀን ከሚያዜሟቸውና ከሚከውኗቸውና ዓለማዊ ይዘት ካላቸው የቃል ግጥሞች የሚመደቡ ናቸው።

ግጥሞችን ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ክዋኔያቸውና ይዘታቸው ምን እንደሚመስል ተንትኖ ማሳየት ነው። በዚህ መሠረት አጥኚው ወጣት ሴቶች ቃል ግጥሞቹን መቼ፣ የትና እንዴት እንደሚያዜሟቸውና እንደሚከውኗቸው አሳይቷል። የቃል ግጥሞቹን ማኅበራዊም ኾነ ባህላዊ ፋይዳቸውንም ጠቁሟል።

መኮንን ለጥናቱ የሚኾኑ ኹለት መቶ ኃምሳ ስምንት የቃል ግጥሞችን ከመስክ የሰበሰበ ሲኾን፣ ለዚህም ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን እና ቡድን ተኮር ውይይትን ተጠቅሟል። በተፈጥሯዊ መቼትም የቃል ግጥሞቹን የአከዋወን ኺደት አጥኚው ለመረዳት ችሏል። አጥኚው ዘጠና አራቱን የቃል ግጥሞች ለመተንተን ጥቅም ላይ ያዋላቸው የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎች ክዋኔ ተኮርና ተግባራዊ የተባሉትን ነው። የናሙና አመራረጥ ዘዴው ደግሞ ዓላማ ተኮር ሲኾን፣ በወረዳው ውስጥ ካሉት ሠላሳ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ አራቱን ብቻ ተተኳሪ አድርጓል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በጥር ወር ቀበሌዎቹ የራሳቸው የኾነ የታቦት ንግሥ ስለሚከበርባቸው ነው። ምንም እንኳን ጨዋታው የወጣት ሴቶች ቢኾንም በመረጃ ሰጭነት ግን የተመረጡት መካከለኛ ዕድሜ ላይ የሚገኙና በዕድሜ የገፉ ሴቶች ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ መካከለኛ ዕድሜ ላይ የሚገኙና በዕድሜ የገፉ ሴቶች ወጣት በነበሩበት ወቅት በጨዋታው ሲሳተፉ ስለነበር በቂ የኾነ መረጃዎችን ይሰጣሉ ብሎ አጥኚው በማሰቡ የተነሣ ነው።

የመኮንን ጥናት ቃላዊ ግጥሞቹን ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ይዘታቸውን በመተንተኑ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳቸውን በመግለጹ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ፣ እንደዚሁም በመረጃዎቹ ትንተና ወቅት ክዋኔ ተኮር እና ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የተባሉትን ማዕቀፎች በመጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በሌላ በኩል ግን ጥናቱ በአንድ የቃል ግጥም ዘውግ ላይ ብቻ በማተኮሩና የእኔ ጥናት በሚያካልላቸው ወረዳዎች የአበሹቴ እና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ባለመከወናቸው በኹለቱ ጥናቶች መካከል ከፍተኛ የኾነ ልዩነት ተስተውሏል።

በትምህርት ክፍሉ በአማርኛ ቋንቋ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡት ጥናቶች በተጨማሪ ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ እንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል ቃል ግጥምን ርእሰ ጉዳያቸው አድርገው የተሠሩ ጥናቶች ተዳስሰዋል። እነዚህም ቢኾኑ የሚያነሧቸው ርእሰ ነገሮች የተለያዩ በመኾናቸው ከይዘት አንጻር በፈርጅ በፈርጅ ከፋፍሎ ለማቅረብ ባይቻልም በየቀረቡበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል በሚከተለው ኹኔታ ተቃኝተዋል።

ሺበሺ ለማ በ1986 ”A Thematic Approach to Famine-Inspired Amharic Oral Poetry.›› በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት መርሓ ግብር

ለመመረቂያ የሚሆነውን ጥናታዊ ጽሑፉን አቅርቧል። የዚህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በድርቅ አማካይነት በተከሠተው ረኃብ ሰዎች የገጠሟቸውን ችግሮች የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞችን ከመስክ ሰብስቦ መተንተን ነው። የጥናቱ ዓላማም የግጥሞቹን ጭብጥ በመተንተን በረኃብ የተጠቁትን ሰዎች ሥነ ልቦና፣ ስሜት፣ ተስፋ፣ ወዘተ. መለየት እንደሚቻል ማሳየት ነው። አጥኚው ለጥናቱ የሚሆኑትን ቃል ግጥሞች የሰበሰበው በወሎና በሸዋ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመላው ሀገሪቱ ለእርዳታ ተግባር በተሰማራባቸው አካባቢዎች ሲዘዋወር የሰማቸው ነው። ሺበሺ የሰበሰባቸውን ቃል ግጥሞችም በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የመደባቸው ሲሆን፣ እነሱንም፡- ጭንቀትን እና ስቃይን፣ አለመረጋጋትን፣ ከቅገጮት መንቃትን፣ ቅሬታን እና ብስጭትን፣ ምስጋናን እና ጥንካሬን የሚያመላክቱ ናቸው በማለት ይዘታቸውን ተንትኖ ጥናቱን ደምድሟል። አጥኚው በድርቅ አማካይነት በተከሠተ ረኃብ የተገጠሙትን ቃል ግጥሞች ሰብስቦ የተነተነ በመሆኑ ፈቃደ በ1996 ዓ.ም <u>ሰሚ ያጡ ድምፆች</u> በሚል ርእስ ካቀረበው ሥራ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የእኔ ጥናት ግን ከዓላማ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ ከጥናቱ አካባቢ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ሙሉ በሙሉ ይለያያል።

ብርሃኑ ገበየሁ በ1998 “Islamic Oral Poetry in Wollo፡ A Preliminary Descriptive Analysis” በሚል ርእስ የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፉን አቅርቧል። የጥናቱ ዋና ዓላማ የእስልምና የመንዙማ ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎችን፣ አጠቃላይ የሥርዓተ ክበራ ኺደቶችን፣ የአድማጮችን ዓይነትና ሚናቸውን፣ የመንዙማ ግጥሞችን ዓላማና ለአድማጮች ያላቸውን ጠቀሜታ በጥልቀት መግለጽ የሚል ነው። አጥኚው በዚህ ዓላማ መነሻነት የቃል ግጥሞቹ የመከወኛ አጋጣሚዎች Eid-al-adha, Eid-al-Fatir, Rammadan, Mäwlid & Wädajja መኾናቸውን አመልክቷል። የመንዙማን የቃል ግጥሞች በየዘውጋቸው ለይቶ በመከፋፈል ባህላዊና ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታዎቻቸውን ገልጿል። የመንዙማ ግጥሞች ሚና የተለየ መኾኑን እና የድረሳ፣ የክዋኔ፣ የተስተላልፎ ባሕርይን እንደተላበሱ አሳይቷል። የተለያዩ የመንዙማ ግጥሞችን ይዘትም አብራርቷል።

ለጥናቱ የሚኾኑት መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡት በወሎ ውስጥ ከሚገኙ ከአምባሰል፣ ከደሴ ዙሪያ፣ ከየጁ፣ ከቃሉ፣ ከቦረና እና ከወረኢሉ ወረዳዎች ነው። አጥኚው በመረጃ አሰባሰብ ወቅት የተጠቀማቸው ዘዴዎች ተሳትፏዊ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው። በእነዚህ ዘዴዎች ሠላሳ አንድ ረጃጅም ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በሁሉም ላይ ትንተና አካኺዷል። በዚህ ኺደት በወሎ ውስጥ የሚገኙትን የመንዙማ የቃል ግጥም ዘውጎች በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው፣ በይዘታቸው፣ በፋይዳቸው፣ በክዋኔያቸውና በመዋቅራቸው ላይ ትንተና አካኺዷል።

ከእነዚህ ጉዳዮች ውጭ ብርሃኑ በሥራው ውስጥ የተጠቀመውን የጥናት ዘዴና ንድፈ ሐሳብ ባለመግለጹ በአሁኑ ውቅት እንደሚሠሩት የምርምር ሥራዎች አቀራረብ የተሟላ አይደለም። ምክንያቱም ጥናቱ ከተሠራበት ዓመተ ምሕረት አንጻር እነዚህ ነገሮች ተሟልተው ይገኛሉ ተብሎ ሊጠበቅ ባለመቻሉ ሊኾን ይችላል። ጥናቱ በመንዙማ የቃል ግጥሞች ፋይዳና በከፊልም ቢኾን በተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከእኔ ጥናት ጋር ሊመሳሰል ችሏል። በእኔ ጥናት ላይ የመንዙማ ቃል ግጥሞችን ስለማልመለከት በኹለቱ ጥናቶች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ታይቷል።

ዳንኤል ለገሰ ደግሞ በ1998 ‹‹A Thematic Approach To Amharic Oral Poems Associted With the Derg Red Terror in Gonder and Gojam.›› በሚል ርእስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ለመመረቂያ የሚሆነውን ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል። የዳንኤል ጥናት በደርግ ጊዜ በጎጃምና በጎንደር ሀገራት በተፈጸመው የቀይ ሽብር እርምጃ ምክንያት በማኅበረሰቡ አንደበት የተነገሩትን ቃል ግጥሞች ከጭብጥ አንጻር የመረመረ ነው:: የጥናቱ አላማ በቀይ ሽብር አጋጣሚዎች የተነገሩትን ግጥሞች ከማኅበረሰቡ በመሰብሰብ ዐውዳዊ ትንተና ማድረግ ነው:: ዳንኤል መረጃውን ለመሰብሰብ የተጠቀመው ዘዴ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውሮ መረጃ አቀባዮችን በማነጋገር፣ የቡድን ተኮር ውይይት በማካሄድ፣ በቃል ግጥሞቹ ይዘትና ጭብጥ ላይ የጥናቱ ተሳታፉዎች አስተያየት እንድሰጡ በማድረግ ነው:: አጥኚው የግጥሞቹን ጭብጥ አካላዊና ስሜታዊ ጉዳቶች፣ እንደዚሁም አልሸነፍም ባይነት በሚሉ ምድቦች ከፋፍሏቸዋል። በእነዚህ ምድቦች መሠረትነት ቃል ግጥሞቹ ግርፋት፣ ትልተላ፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ነጻ እርምጃ፣ ጥልቅ ኀዘን፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ስደትና ድንገተኛ ጥቃት የሚያመለክቱ እንደሆኑ አሳይቷል:: ይህ ጥናት በርእሰ ጉዳይ ከመለያየቱም በተጨማሪ ንድፈ ሐሳብ ባለመጠቀሙ ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰልም::

ከዚህ በመቀጠል በማስተርስ ዲግሪ ደረጃ የተቃኘው መስፍን መሰለ በ2000 “Abba Wudde Oral Peorty in South Wollo: A Descriptive Analysis” በሚል ርእስ ያቀረበው ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን የአባውዴ ቃል ግጥሞች መተንተን የሚል ነው። በዓላማው መሠረት አጥኚው ኃምሳ ዘጠኝ የቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በሁሉም ላይ ትንተና በማካኼድ የአባውዴዎችን የልመና ትውፊት ዋናና መሠረታዊ ምክንያቶችን እና አባውዴዎችን በተመለከተ የሌላው ሰው አመለካከት ምን እንደኾነ ለመመርመር ችሏል። የቃል ግጥሞቹን የክዋኔ ዐውዶችንም ለይቶ አመልክቷል።

አባውዴዎቹ በቃል ግጥሞቻቸው አማካይነት ሰውን የሚያሳምኑበትን መንገድና ቃል ግጥሞቹም በአድማጮች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ገልጿል። የቃል ግጥሞቹ የተስተላልፎና የክዋኔ ኺደቶች እንዴት እንደሾኑም አመልክቷል። የአባውዴ የቃል ግጥሞችን ይዘትና ተግባራቸውንም አብራርቷል። ይህ ጥናት ቃል ግጥምን መሠረት አድርጎ በመሠራቱ አነስተኛ ቅኝት ተደረገበት እንጂ ከእኔ ሥራ ጋር ሙሉ በሙሉ ልዩነት ተስተውሎበታል። ምክንያቱም በእኔ ጥናት ውስጥ የአባውዴ ቃል ግጥሞች ባለመካተታቸው የተነሣ ነው።

አብርሃም መልኬ በ2007 “Thematic and Technical Analysis of Oral Poetry in and around Debre Tabor በሚል ርእስ ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናትም በሚከተለው ኹኔታ ቅኝት ተካኺዶበታል። የአብርሃም ጥናት ዋና ዓላማ በደብረ ታቦርና አካባቢው በመጥፋት ላይ ያሉትን ቃል ግጥሞች ለመጠበቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር፣ የዕድሜ ጠገብ ሰዎችን የሕይወት ገጠመኝ፣ እምነት፣ ታሪክ፣ የጥናቱ ታላሚ በኾነው አካባቢ ያለውን ሕዝብ የዓለም አመለካከት ለሌላው የጎበረተሰብ ክፍል ለማስተዋወቅ የሚል ነው።

አጥኚው በቃል ግጥሞች ላይ የተሻለ ዕውቀት ካላቸው፣ በዕድሜ ከገፉ ሰዎችና ከገጣሚዎች ስድስት መቶ የቃል ግጥሞችን በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ተኮር ውይይት የሰበሰበ ሲኾን፣ ከእነዚህ መካከል ስልሳ የቃል ግጥሞችን በኹለት ምዕራፎችና በአምስት ርእሰ ጉዳዮች ከፋፍሎ ተንትኗል። ሌሎቹን ግን በአማርኛ፣ ከሥር ላይ ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በመተርጎም በአባሪነት አስቀምጧል። በትንተናው ላይ የቃል ግጥሞቹ ታታሪነትን (ጠንክሮ መሥራትን) የሚመክሩ፣ ጀግንነትን የሚያበረታቱ፣ ሞት የጥልቅ ኀዘን መግለጫ መኾኑን የሚያመላክቱ፣ እንደዚሁም ማኅበራዊ ሂስን የሚሰነዝሩና ግብረ ገብነትን የሚያስተምሩ መኾናቸውን ገልጿል።

ይህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹና ትኩረት ባደረገባቸው አንዳንድ ርእሰ ጉዳዮች ከእኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም የተጠቀመውን የጥናት ዘዴ፣ የጥናት ዓይነት፣ ለትንተናው በተግባር ላይ ያዋለውን የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ፣ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀማቸውን መሣሪያዎች ባለመግለጹ ደግሞ ልዩነት ታይቶበታል።

በመቀጠልም በአካል ንጉሤ በ2010 ”THE SOCIAL FUNCTION OF AMHARIC FOLK POETRY WITH REFERENCE TO SHÄNÄA IN RAYYA QOBBO“ በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ባቀረበው የመመረቂያ ጽሑፍ ላይ ቅኝት

ተካኺዷል። የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በራያ ቆቦ የሚነገሩትን የቃል ግጥሞች መመዝገብ፣ መሰነድ፣ ዋና ዋና ጭብጦቻቸውን መለየትና ግጥሞቹ ካላቸው ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ከፋፍሎ ማሳየት የሚል ነው።

በአካል ጥናቱን ለማከናወን በተግባር ላይ ያዋለው ዘዴ ዓይነታዊ ሲኾን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹም ተሳትፏዊ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው። በእነዚህ ዘዴዎችም በቆቦ ወረዳና ከተማ ከሚገኙ ሽማግሌዎች ከሰባ በላይ ቃል ግጥሞችን ከሰበሰበ በኋላ ግጥሞቹ ካላቸው ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ዐርባዎቹን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ በመተርጎም ተንትኗቸዋል። ሌሎቹን ግን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በመከፋፈል በአባሪነት አስፍሯቸዋል። በአካል ቃል ግጥሞቹን በተለያዩ ፈርጆች ከፋፍሎ ለመተንተን የተጠቀመው ተግባራዊና ዐውዳዊ በመባል የሚታወቁትን የንድፈ ሐሳብ ማእቀፎች ነው። በትንተናው ወቅት የቃል ግጥሞቹ በምረቃ፣ በርግማን፣ በምስጋና፣ በማኅበረ - ፖለቲካዊ ትችት፣ ወዘተ. ላይ ያተኮሩ መኾናቸውን አሳይቷል።

የበአካል ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀሙ፣ ተሳትፏዊ ምልከታን እና ቃለ መጠይቅ የተባሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ እንደዚሁም ለመረጃ ትንተናው ተግባራዊና ዐውዳዊ የተባሉትን የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎች ተግባራዊ በማድረጉ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ታይቶበታል። ቡድን ተኮር ውይይትን እና ክዋኔያዊ የተባለውን ንድፈ ሐሳብ ባለመጠቀሙ፣ እንደዚሁም የመረጃ ትንተናው በምረቃ፣ በእርግማን፣ በምስጋና፣ ወዘተ. ላይ በማተኮሩ ደግሞ በኹለቱ ጥናቶች መካከል ልዩነት ተስተውሏል።

በመጨረሻ ላይ የተዳሰሰው በዘላለም ዘውዴ በ2010 ”THEMATIC ANALYSIS OF AMHARIC ORAL LYRIC POETRY OF WEST GOJJAM ZONE“ በሚል ርእስ የቀረበው ጥናት ነው። የዘላለም ጥናት ዓቢይ ዓላማ የአማርኛ ቃላዊ የሊሪክ ግጥሞችን ዋና ጭብጥ መመርመር ነው። በዚህ ዓላማ መሠረት አጥኚው በዐውድ ሊሪክ ግጥሞቹን በመለየት ያላቸውን ማእከላዊ ሐሳብ ተንትኗል። የሊሪክ ግጥሞቹን የድረሳ እና የክወናቸውን ባሕርይም መግለጽ ችሏል። ጥናቱ በተካኼአበት አካባቢ ያሉ የሊሪክ ግጥሞች በአድማጭ ዘንድ የሚያሳድሩትን ስሜትና ጥበባዊ ምላሾች በመመርመር አብራርቷል።

የዚህ ጥናት የምርምር ዘዴ ዓይነታዊ ሲኾን፣ ዘዴው የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው መረጃዎቹን በተሳትፏዊ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ለመሰብሰብ በመቻሉ ነው። እንደዚሁም መረጃዎቹን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት መሣሪያዎች ደግሞ ድምፀ መቅረጽ፣ ማስታወሻ ደብተርና ፎቶ ካሜራ ናቸው። አጥኚው ዐሥራ አምስት የመረጃ ሰጭዎችን ከሦስት ወረዳዎች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ እንደመረጣቸው አመላክቷል።

ትምህርታቸውን ጨርሰው በየወረዳዎቹ ለበርካታ ዓመታት ለኖሩ ዘጠኝ መረጃ ሰብሳቢዎች ስልጠና በመስጠት መረጃዎችን አሰባስቧል። በቡድን ተኮር ውይይቱም ከየወረዳዎቹ በሚገባ የተጠኑ አምስት አምስት በድምሩ ዐሥራ አምስት ወንድና ሴት ተወያዮችን በመምረጥ መረጃ አሰባስቧል። ዘላለም ከላይ በዝርዝር በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምን ያክል የቃል ግጥሞችን እንደሰበሰበ ባይገልጽም በሰባ ስድስት ግጥሞች ላይ ትንተና ማካሄዱን ማረጋገጥ ተችሏል።

ይህ ጥናት በዘዴው፣ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹና በናሙና አመራረጡ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ታይቶበታል። የእኔ ትኩረት ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚከወኑ የቃል ግጥም ዘውጎች ላይ እንጂ ስሜት ነኪ (lyric) የተባለውን የግጥም ዓይነት ስለማይመለከት በኹለቱ ጥናቶች መካከል ልዩነት ታይቷል።

የፒኤች. ዲ. ዲግሪ ማሚያ ጥናቶችም ቢኾኑ በቀረቡባቸው ዓመታት ቅደም ተከተል በሚከተለው ኹኔታ ተቃኝተዋል። በዚህ መሠረት ለማ ንጋቱ በ2006 ዓ.ም "የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ጥናታዊ ጽሑፉን አቅርቧል። የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ጎንደር ዞን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ማኅበረሰብ አባላት ሞት ሲከሠት በቡድን የሚከውኗቸውን የለቅሶ ሥርዓቶችን እና የቃል ግጥሞችን ክወና መግለጽ ነው። በዓላማው መሠረት ሦስት መቶ ዘጠና አንድ ረጃጅም የቃል ግጥሞችን ከመስክ ከሰበሰበ በኋላ በሰማንያ አራቱ ላይ የለቅሶ ሥርዓቶቹን እና የቃል ግጥሞቹን ክወናዎች መርምሯል፤ ትእምርቶችንም ለመፈከር ችሏል። የመታሰቢያ ሥርዓቶቹን ምንነት በመተንተን እና ትእምርታዊ ትርጉማቸውንም በመፈከር ማኅበራዊ ፋይዳቸውን ገልጿል።

አጥኚው የአጠናን ዘዴው ዓይነታዊ ምርምር እንደኾነና ኢትኖግራፊያዊ የምርምር ዘዴንም እንደተከተለ ገልጿል። ጥናቱ ከተካሄደባቸው ወረዳዎች ስለባህሉ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች በታላሚ የናሙና ዘዴ፣ በተጨማሪም ታዋቂ ግለሰቦችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን እና የለቅሶ ቃል ግጥም ከዋኞችን በጥቆማ (snowball sampling) በመምረጥ መረጃዎችን ሰብስቧል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡትም ክዋኔዎቹ በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ መቼት በግንባር በመገኘት በተሳትፏዊ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በሰነድ ምርመራ

ነው። ለመረጃ ትንተናውና ፍከራውም የመሠረት ባህል ሞዴል (Infracultural Model) የተባለውን ዘዴና የክወና ንድፈ ሐሳብን (Perforemance Theoryን) ተጠቅሟል።

ይህ ጥናት በአጠናን ዘዴው፣ በናሙና አመራረጡ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹና መሣሪያዎቹ፣ በተጠቀመው የክወና ንድፈ ሐሳብ ከእኔ ጥናት ጋር ሊመሳሰል ችሏል። ልዩነቱ ደግሞ ለማ ኢትኖግራፊያዊ ዘዴን ቢጠቀምም ይህ ዘዴ በእኔ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ አልኾነም። ከዚህ በተጨማሪ አጥኚው በለቅሶ ሥርዓቶቹና በቃል ግጥሞቹ ክወና ላይ ብቻ ትኩረት ሲያደርግ እኔ ግን በቃለ መጠይቅ በተሰበሰቡት የሙሾ ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው ትንተና ለማካሄድ የቻልኩት።

በኹለተኛ ደረጃ ቅኝት የተደረገው ስለሺ አባተ በ2008 ዓ.ም "የምንጃር ሸንኮራ ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ክዋኔ እና ማኅበራዊ ፋይዳ" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ የምንጃር ሸንኮራ ማኅበረሰብ ቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎችን እና ዐውዶችን መለየት፣ የቃል ግጥሞቹን ማኅበራዊ ፋይዳ መተንተን እና መፈከር የሚል ነው። ስለሺ በጥናቱ ውስጥ የምንጃር ሸንኮራን ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውን በመለየት ዐውዳዊ ክዋኔያቸውን አብራርቷል። የቃል ግጥሞቹን ማኅበራዊ ፋይዳዎችንም በመመርመር ተንትኗል።

አጥኚው ገላጭ በመባል የሚታወቀውን የምርምር ዓይነት በተግባር ላይ አውሏል። ምልከታን፣ የመስክ ማስታወሻዎችን፣ ቃለ መጠይቆችን፣ የፎቶ ካሜራዎችን፣ የድምፅ መቅረጫዎችን፣ የግል ማስታወሻዎችን ተጠቅሞ መረጃዎችን መሰብሰብ በመቻሉም የጥናቱ ዘዴ ዓይነታዊ ምርምር መኾኑን ገልጿል። የመረጃ አቀባዮች አመራረጥን በተመለከተ በአንደኛ ደረጃ "ጥቁምታ" የተባለውን የናሙና ዘዴ ተጠቅሟል። ኹለተኛው መንገድ ደግሞ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚከወኑ በሰርግ፣ በሥራ እንዲሁም በበዓላት አከባበር ወቅት በከዋኝነት የተሳተፉትን ሰዎች በዐውዱ ላይ ተገኝቶ በመመልከት መረጃ ሰጪ የሚኾኑ ሰዎችን ለመምረጥ ችሏል። አጥኚው መረጃውን ለመተንተን የተጠቀመበት ሥልት የጽሑፍ ትንተና መኾኑን አብራርቷል። ሥነ ማኅበረሰባዊ የትንተና ሞዴልንም ተጠቅሟል።

አጥኚው የቃል ግጥሞችን የመከወኛ አጋጣሚዎች በመለየቱ፣ ፋይዳቸውን በመተንተኑ፣ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀሙ፣ ከመስክ ላይ መረጃዎችን በቀዳማይ ምንጭ በመሰብሰቡና በናሙና አመራረጡ ጥናቱ ከእኔ ሥራ ጋር ሊመሳሰል ችሏል። ነገር ግን ስለሺ የቃል ግጥሞቹን የመከወኛ አጋጣሚዎች ለውጥና ተከታታይነት ባለመመልከቱ ኹለቱ ጥናቶች በመካከላቸው ልዩነት ታይቶባቸዋል።

በመጨረሻ ላይ የተቃኘው አማረ ሞላ በ2009 ዓ.ም “የአማርኛ ቃል ግጥሞች ምደባ፣ ዐውዳዊ ትንተና እና ማኅበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ” በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ያቀረበው ጥናት ነው። የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጡ አካባቢዎች የተነገሩትን ቃል ግጥሞች በብዛትና በዓይነት መሰብሰብ፣ መመደብና ትንተና ማድረግ ነው።

አጥኚው ስድስት መቶ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በአራት መቶዎቹ ላይ የሙገሳና የውደሳ፣ የትችት፣ የጀግንነትና የፍርሃት፣ የቁንጅና እና የፍቅር፣ የማንኳሰስና የቁጭት፣ የፖለቲካና የጦርነት፣ የድርቅና የርኃብ ጉዳዮች በማለት ምደባ አካኺዷል። ቃል ግጥሞቹ የሚያንጸባርቁትንም ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ እውነታዎችንም አሳይቷል። ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ስልቶች ለይቶ በማሳየት በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ላሉት ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና አካሂዷል። በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም በትንተናው ውስጥ በማካተት ዓላማቸውን እና ፋይዳቸውን ለመግለጽ ችሏል።

አማረ የጥናቱን ዓይነት በተመለከተ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል። የናሙና ዓይነቱ ደግሞ ዓላማ ተኮር ሲኾን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ሰነዶች ናቸው። መሣሪያዎቹም ቀረጻና ማስታወሻ ደብተር ናቸው። የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎቹ የተግባራዊያን፣ የሥነ ልቦና - ተግባራዊን እና የታሪካዊ ጠቀሜታ የሚሉት ናቸው። በሰዎች ወይም በቡድኖች ዘንድ የተመለከተውን ነገር ለመግለጽ ኢትኖግራፊክ፤ ከመስክ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ለመተንተን ደግሞ ተንታኝ የሚባሉትን ዘዴዎች ተጠቅሟል። ይህ ጥናት ዓይነታዊ ምርምርን በመከተሉ፣ ዓላማ ተኮርን በመጠቀሙ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹና ተግባራዊ የተባለውን ንድፈ ሐሳብ አገልግሎት ላይ በማዋሉ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ታይቶበታል። ነገር ግን የአማረ ጥናት የቋንቋ አጠቃቀምን በመመልከቱ፣ የውቂያን እና የዐጨዳ ቃል ግጥሞችን፣ እንደዚሁም የልጃገረድ ዘፈኖችን ባለመመርመሩ ልዩነት ተስተውሎበታል።

Getie Gelaye, (2009) Amharic Praise Poems Related to Emperors Tewodros II and Yohannes V በሚል ርእስ በ16ኛው የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም አቀፍ ጉባዔ ቅፅ 4 ላይ ለጎትመት አብቅቷል። Getie በምርምር ጽሑፉ በታሪክ የፉከራ ግጥሞች የሚደረሱት፣ ተደጋግመው የሚቀነቀኑት፣ በተፈለገው ጊዜ ተዘጋጅተው የሚቀርቡትና የሚከወኑት በታላላቅ ድሎች፣ በጦርነት፣ በአደን ዘመቻ፣ በሰርግ ሥነ ሥርዓቶች፣ በንጉሣዊ ታላላቅ ግብዣዎች፣ የታወቀና ዝነኛ በኾነ ሰው የቀብር ሥርዓት በሚፈጸምበት ወቅት እንደኾነ አብራርቷል።

በተደጋጋሚ የሚያቀነቅኑትም ተዋጊዎች፣ አርበኞች፣ ጀግኖች፣ ፈረሰኛ ወታደሮች መኾናቸውን አመላክቷል። የፉከራ ግጥም ግለሰቦችን በማሞገሱና የተደበቀውን ስሜት በማውጣቱ ረገድ ከቃል ግጥም ዘውጎች የተለየ እንደሚያደርገውም ገልጿል። የእኔ ሥራ በአሁኑ ወቅት ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች ከአርሶ አደሮቹ ሕይወት ጋር ተቆራኝተው በሚቀነቀኑ የሥራ፣ የልጃገረዶች የዘፈን፣ የሙሾ፣ ወዘተ. ቃላዊ ግጥሞች ላይ በማተኮሩ ከGetie ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያል።

ፈቃደ አዘዘ በ1996 ዓ.ም ሰሚ ያጡ ድምፆች በሚል ርእስ ባሳተመው መጽሐፍ በረጎብ የቃል ግጥሞች ላይ ትንተና አካኺዷል። የተወሰኑትን ቃል ግጥሞችም ራሱ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን በሚገኘው በደብረሲና አካባቢ እየተዘዋወረ ከአርሶ አደሮች የሰበሰባቸው መኾኑን ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ በ1986 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዓመቱን ትምህርት ካጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል ወደ ወሎ የሚኼዱትን በረዳት መረጃ ሰብሳቢነት በማሰማራት ከየተወለዱባቸው አውራጃዎች ማለትም ከየጁ፣ ከአምባሰል፣ ከወረሂመኖና ከላስታ፣ እንዲሁም ከዋድላ ደላንታ የረጎብ ቃል ግጥሞችን ለማሰብሰብ ችሏል። በፈቃደም ኾነ በተማሪዎቹ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ከአንድ ሺህ በላይ ሲኾኑ፣ ከእነዚህ መካከል ሰማኒያ ሰባቱ ትንተና ተካኺዶባቸዋል። የፈቃደ ዓላማ በ1977 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በደረሰው ድርቅና ረጎብ የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በዘውግ በዘውግ በመከፋፈል ይዘታቸውን መተንተን ነው። ቃል ግጥሞቹም “የዘመነ መጣሁብህ፣ የዘመነ ዐጸባ፣ የዘመነ እፎይታ፣ የረጎብ ከተል ስንኞች” የሚሉ ርእሰ ጉዳዮችን ያካተቱ ናቸው። የፈቃደ ሥራ በተወሰነ መልኩ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹና መሣሪያዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ቢኖረውም፣ ከድርቅ፣ ከረጎብ፣ ወዘተ. ጋር ተያይዘው የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን ግን የእኔ ጥናት አይመለከትም።

በአጠቃላይ ከላይ የተዳሰሱት ቀደምት ጥናቶች በሰርግ ሥርዓት፣ በልጃገረዶች ዘፈን፣ በዛር ዘፈን፣ በለቅሶና በቀብር ሥርዓት፣ በመኸር ወቅት፣ በወፍጮ ዐውድ፣ በሊሪክ፣ በፉከራ፣ በረጎብ ወዘተ. የቃል ግጥሞች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ምንም እንኳን ከእነዚህ መካከል በተወሰኑት ርእሰ

ጉዳዮች ላይ የእኔ ጥናት የሚያተኩር ቢኾንም አጥኚዎቹ በማዳበሪያ፣ በብስባሽ (Compost)፣ በፀረ ዐረምና በዕርከን ሥራ ላይ የተነገሩ የቃል ግጥሞችን፣ እንደዚሁም የቃል ግጥሞቹን የመከወኛ አጋጣሚዎች ለውጥና ቀጣይነት ሙሉ በሙሉ አልተመለከቱም። ስለዚህ በእነሱ ጥናቶች ላይ የተስተዋለውን ክፍተት ለመሙላት ይህን ምርምር ለማካኼድ ተችሏል።

የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ - በሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ላይ ብቻ የታጠረ እንዳይኾን በሚል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። ይኼውም በዋናው ግቢ ውስጥ በተለያዩ ኮሌጆች በሚገኙ ቤተ መጻሕፍት በአካል እየተዘዋወርኩ ከእኔ የጥናት ርእሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኙ የሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ የሶሲዮሎጂ፣ የሶሻል ወርክ የመመረቂያ ጽሑፎችንም ኾነ ሌሎች ሥራዎችን ብፈልግ ላገኝ አልቻልኩም። ከዚህ በተጨማሪ እስከ መጋቢት 28/2018 ዓመተ ምሕረት ድረስ በዲጂታል ቤተ መጻሕፍት ውስጥ http://etd.aau.edu.et/ በሚለው ድረ ገጽ ላይ upload የተደረጉ መረጃዎችንም አላገኘሁም።

3.2. የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር ቃል ግጥም፣ የቃል ግጥም ባሕርያት፣ የቃል ግጥም ማቅረቢያ ስልቶች፣ ዓይነቶች፣ የቃል ግጥሞች ዐውድ፣ ፋይዳ፣ የቃል ግጥሞች ክዋኔ፣ ለውጥና ቀጣይነት የሚሉት ነጥቦች ትኩረት የተሰጣቸው ሲኾን፣ እነዚህን ጽንሰ ሐሳቦች በሚያስተነትን መልኩ የተካኼደው ተግባርም በሚከተለው ኹኔታ ቀርቧል።

3.2.1. ቃል ግጥም

ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ ሊቀናበርና ሊተላለፍ የሚችለው ያለ ምንም የጽሕፈት አገልግሎት ነው እየተባለ ሲገለጽ የነበረው ብያኔ ዘውጉን ሙሉ በሙሉ ሊገልጽ አይችልም። ምክንያቱም የተለያዩ የቃል ግጥም ዘውጎች ከጽሕፈት ጋር እየተቀናበሩ ሊቀርቡ እንደሚችሉ በዚሁ ጥናት መነሻ ገጽ "1" ላይ ተገልጿል። የቃል ግጥም አደራረሱም ኾነ ክዋኔው በማንኛውም ቡድን ወይም ኹነት የተገደበ አይደለም (Peek እና Yankah, 2004:991)። ምክንያቱም በተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግባራትም ኾነ በሕይወት ሽግግር ወቅት ሳይቀር አገልግሎት ላይ እየዋለ ይገኛል። በዚህ መሠረት እንደ ውልደት፣ ጋብቻና የቀብር ሥርዓት ያሉ አጋጣሚዎች ለቃል ግጥም ማቅረቢያ ምቹ የኾኑ አነሣሾች ናቸው (Peek እና Yankah,2004:991)።

ቃል ግጥም በቦታና በጊዜ ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር የተቆራኘ በመኾኑ እስካሁንም ድረስ የሕይወታችን አካል ኾኖ ይኖራል፤ ያለፈውንም ይዘክራል። በአሁኑ ወቅት ያለውንም ኹኔታ

ያስገነዝበናል፤ የወደፊቱንም እንዲንተነብይ ያደርገናል (Morris እና Breeze, 2004፡8)። በሀገራችንም ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት አንሥቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እየተፈራረቁ ሀገሪቷን በገዙት መሪዎች ላይ በማኅበረሰቡ አንደበት የተዜሙት የቃል ግጥሞች ብንመረምራቸው ይኸንኑ ሐሳብ የሚያስረግጡ እውነታ አላቸው የሚለው እምነት በአጥኚው አዕምሮ ውስጥ አድሯል።

በቃል ግጥሞች ላይ ፈር ቀዳጅ የኾኑ ምርምሮች በFinnegan (1970,1977)፤ በNandwa (1976)፤ በMutswairo (1978) እና በOkpewho (1992) የተሠሩ ሲኾን፤ በአፍሪካ ጠቃሚ የሆነ የቃል ግጥም ጥናት አለ ወይ? (Does Africa have Oral Poetry worth Studying?) በማለት በአውሮፓውያኑ የተነሡ ሙግቶች አሉ (Alembi, 2002፡33)። ለምሁራኑ ሙግት መነሻ የኾነው ዋናው ምክንያት ቃል ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰና የተሻሻለ ባህል ወይም ሥልጣኔ መግለጫ በመኾኑ ነው። አውሮፓውያኑ ግን የአፍሪካን ሕዝቦች ልማዳዊ (traditional) በመኾናቸውና እስካሁን ድረስም በችግሮች ውስጥ ተተብትበውና በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ፍጡራን አድርገው በመቁጠራቸው የተነሣ ቋንቋዎቻቸውም ቢኾኑ ውስብስብ የኾነውን የቃል ግጥም አገላለጽ ቴክኒኮችን አርኪ በኾነ መንገድ ለመግለጽ ብቁ ኾነው አላደጉም ብለዋል (Okpewho, 1985:3)። ነገር ግን በአፍሪካ በመስክ ላይ የሥነ ቃል ጥናት ያደረጉ ምሁራን በአህጉሩ በጣም የዳበረና በማኅበረሰቡ ውስጥ የተትረፈረፈ ቃል ግጥም መኖሩን በምርምሮቻቸው አማካይነት ስላረጋገጡ ከላይ የቀረበውን አመለካከት አልተቀበሉትም።

የቃል ግጥምን ለመበየን ድረሳ፣ ዐውድ፣ ተስተላልፎ እና ክዋኔ የሚባሉትን መሠረታዊ ባሕርያት በሚገባ መገንዘብ አስፈላጊ መኾኑን Finnegan (1970፡17-20) ገልጸዋል። Finnegan ለእነዚህ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች የሰጧቸውን ማብራሪያዎች በሚከተለው መልኩ ጨምቆ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል።

1. **ድረሳ፡-** በቃል ብቻ የተቀነባበረውን የድረሳ ዓይነት የሚመለከት ነው። የድረሳው ኺደት ከክዋኔው ድርጊት ቀዳሚና በስፋት የተለየ ሊኾን ይችላል። ስለዚህ ቃላዊ ድረሳ ከክዋኔ በፊትና በክዋኔ ወቅት ያለውንም ኺደት ያካትታል (Finnegan,1970፡18)። እዚህ ላይ እንዴት ነው ቃል ግጥም የሚደረሰው? የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይችላል።

በዚህ መነሻነት ከዋኙ የተሰጠውን አሐድ በቃሉ አጥንቶ በማስታወስ ነው? ወይስ ኹኔታው በተሟሟቀበት ጊዜ ወዲያውኑ አዘጋጅቶ ነው የሚያቀርበው? ወይም አንድ ወጥ የኾነ የድረሳ ስልት አለ ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ሊቀርቡ ይችላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች እየሠሩ፣ እየጠጡ፣ የሞተን እየቀበሩ፣ እየጸለዩና የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት እየተዝናኑ ባሉበት

ወቅት የደረሷቸውን የቃል ግጥሞች ሌላው ሰው የቅርብ ተሳታፊ ኾኖ ሊያዳምጣቸው ይችላል። በእነዚህ አጋጣሚዎች የሚቀርቡ ዘፈኖች፣ ዜማዎች፣ ዝማሬዎች፣ የጋለ ስሜት ንግግሮች፣ ወዘተ. ኢ- መደበኛ ለኾነው ሥልጠና ምቹ ኹኔታን ስለሚፈጥሩ ለክወና ብቁ የኾነ ሰው በቃሉ አጥንቶ በማስታወስ ሌላ ጊዜ ሊከውናቸው ይችላል በማለት Alembi (2002፡37) በFinnegan ሐሳብ ይስማማሉ።

Finnegan (1970: 83-110) የአፍሪካን የቃል ግጥም ደራሲዎች የቤተ መንግሥት ገጣሚዎች (Court Poets)፣ የሃይማኖት ገጣሚዎች (Religious Poets)፣ በሙያቸው የሚሠሩ መደበኛ ያልኾኑ ወይም ተዘዋዋሪ ገጣሚዎች (Professional Freelance or Roving Poets)፣ የትርፍ ሰዓት ገጣሚዎች (Part-time poets) እና አጠቃላይ ገጣሚዎች (General Poets) ብለው በአምስት ደረጃዎች ከፈረጁ በኋላ ለእያንዳንዳቸው ሰፊ የኾነ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት የሚመለከተው በአጠቃላይ ገጣሚዎች (General Poets) የሚደረሱትን ቃል ግጥሞች ነው። ምክንያቱም እነዚህ ዓይነቶቹ የቃል ግጥም ገጣሚዎች በሚጫወቱበት፣ በሚሠሩበት፣ በሥርዓተ ቀብር፣ በመጠጥ ግብዣ፣ ልጅ በሚወለድበት፣ በሚጸለይበትና በልዩ ልዩ ዐውዶች የቃል ግጥሞችን የሚደርሱና የሚከውኑ ሴቶችና ወንዶች፣ ወጣቶችና ልጃገረዶች በመኾናቸው የተነሣ ነው (Alembi, 2002፡48)።

2. **ተስተላልፎ**፡- ቃል ግጥም አፋዊ በኾነ መንገድ ከትውልድ ትውልድ የመተላለፍ ባሕርይ እንደነበረው በተለያዩ ምሁራን ለረጅም ዘመናት ሲገለጽ ቢቆይም በቅርብ ወቅት ግን በአቀንቃኝ አማካይነት በቃል የተፈጠረው ቃል ግጥም ተስተላልፎው በታተሙ መጻሕፍት ወይም በዘመናዊ የትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎች ሊኾን እንደሚችል Finnegan (1970፡19) ገልጸዋል። አሁን አሁን ላይ ደግሞ በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴዎች ሳይቀር የቃል ግጥም የሽግግር ተግባር በመከናወን ላይ መኾኑን የዚህ ጥናት አንባቢ የሚገነዘበው ጉዳይ ነው።

በሀገራችንም የጀግናን መንፈስ በሚጠሩ ጽሑፋዊ ግጥሞችና ሀገራዊ ዜማዎች ውስጥ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፉ የነበሩ የቃል ግጥሞችን በንባብ ኺደታችን ልናገኛቸው፣ በእዝነ ልቡናችንም ልናዳምጣቸው እንችላለን። ገጣሚያኑ ይህንን የሚያደርጉት ለግጥሞቻቸው ማካኼጃ ብቻ ሳይኾን ለአንባቢ ሊነግሩት የፈለጉትን ጭብጥ ለማስረገጥ ሲሉ እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ፎክሎራዊ ርእሰ ጉዳዮችን ተላብሰው በሚደረሱ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ቃል ግጥሞችን እና ዘፈኖችን ማግኘት የተለመደ ነው።

3. **ክዋኔ፡-** ቃል ግጥም ተከዋኝ ነው፡፡ አንድን አጋጣሚ ሰበብ በማድረግ ነው በአቀንቃኙና በተቀባዩ የሚከወነው፡፡ ይህ ማለት ያለ ምክንያት ስለማይከወን በዋናነት የመከሠቻ አጋጣሚን ይፈልጋል ማለት ነው (Finnegan, 1970:21)፡፡ በክዋኔው ወቅት እንደ ቃል ግጥሙ ዓይነት ቃል አልባ የሆኑ አሐዶች በአጃቢነት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለአብነትም እንደ አልባሳት፣ ዱላ፣ ቃጭል፣ ታምቡር፣ ከበሮ፣ በገና፣ መለከት፣ ጥሩንባ፣ ክራር፣ ደወል፣ የእጅ ጭብጨባ፣ ወዘተ. ያሉት አጃቢ ሽነው ይቀርባሉ (Alembi, 2002,35:)፡፡ የክዋኔውና የአጃቢዎቹ ቅንጅት በታዳሚውም ሽነ በከያኒው ላይ ከፍተኛ የሽነ ተጽዕኖ ያሳድራሉ (Olajubu, 1978:24-25)፣ (Okpewho, 1985:9) እና (Miruka, 1994:8)፡፡

3.2.1.1. የቃል ግጥም ባሕርያት

ሰዎች በቀላሉ ማስታወስ እንዲችሉ ቃል ግጥሞች በአብዛኛው የሚፈጠሩት ወይም የሚዋቀሩት በአጫጭር ቅርጾች ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል አብዛኛዎቹ ይህንኑ ሐሳብ ያረጋግጣሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥም የመታጀብ ባሕርይ አለው፡፡ Finnegan (1970:265) እንደገለጹት በአንድ የባህል ዐውድ ውስጥ የሚቀርብ የቃል ግጥም ዘፈን በእጅ በማጨብጨብ፣ በአካላዊ፣ በተለያዩ የሙዚቃ *መሣሪያዎች*፣ ወዘተ. ሊታጀብ ይችላል፡፡ Okpewhoም (1992:46-47) በተመሳሳይ *መ*ልኩ በክወና ወቅት የፊት፣ የእጆች፣ ወይም የሌሎች የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች በአጃቢነት ያገለግላሉ በማለት የFinneganን ሐሳብ አጠናክሯል፡፡ ስለዚህ ቃላቱ ወይም ስንኞቹ ሌጣቸውን ወይም ብቻቸውን ሊቀርቡ አይችሉም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ማጀቢያዎች ክዋኔውን ውብ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ የሽነ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለቃል ግጥም ዋና እና *መ*ሠረታዊ ባሕርያት ተደርገው የሚወሰዱት ክዋኔና ተለዋዋጭነት ናቸው፡፡ ክዋኔ ለቃል ግጥም ዋና ገጽታ ነው (Morris እና Breeze,2004:19):: ምክንያቱም ክዋኔ በወቅቱ ላለው ትክክለኛ ኹኔታ፣ ለተስተላልፎ እና ለድረሳ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ የተነሣ ነው፡፡ በአብዛኛው በቃል ግጥም ክዋኔ ወቅት አድማጩና ከዋኙ፣ በተለይ ደግሞ የአቀንቃኙ ተቀባዮች ገደብ በሌለበት ኹኔታ የእርስ በርስ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ በክዋኔውም ወቅት የተወሰነ የጊዜ ርዝማኔ (has no fixed length of performance) የለውም፡፡ ምክንያቱም የማንኛውም የቃል ግጥም የክዋኔ ርዝማኔ የሚወሰነው በአድማጩና በክዋኙ መካከል ባሉ አንዳንድ ጉዳዮች የተነሣ ነው፡፡ ለምሳሌ አድማጩ ከተደሰተና ለማዳመጥ ጉጉት ካለው፣ እንደዚሁም በአንድ በተወሰነ ዘፈን ላይ ለመደነስ ከፈለገ ከዋኙ ያለማቋረጥ

በመደጋገም ዘፈኑን ሊያስረዝመው ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ አድማጩ ከተሰላቸና ፍላጎት ከሌለው ክዋኔውን ሊያሳጥረው ይችላል (Alembi, 1995: 95)።

Finnegan (2012፡ 135) ቃል ግጥሞች ከሚነበቡ ይልቅ ቢከወኑ እንደሚመረጥ ገልጸዋል። ለዚህም በምክንያትነት ካቀረቧቸው ሐሳቦች መካከል ጥቂቶቹ ቃል ግጥሙን ተከትለው የተለያዩ ድራማዊ የአካል እንቅስቃሴዎች ይታያሉ። አድማጮችም ቢኾኑ የድርሻቸውን ለመወጣት የተለያዩ ተግባራትን አብረው ያከናውናሉ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። Finnegan (1977:215) እና Okpewho (1992:107) የብቻ ከዋኝ ባለበት ወቅት (solitary performer) ወይም ጭር ባለ ጊዜ በሚከወን ክዋኔ ግን አድማጭ አይኖርም በማለት ገልጸዋል። በሀገራችንም ለብቻ በሚደረግ የመንገድ ላይ ጉዞ፣ በባህላዊ ወፍጮ እኽል በሚፈጭበት፣ በእርሻ፣ በከብት እረኝነትና በተናጠል በሚሠሩ ሥራዎች ወቅት የሚቀነቀኑት ስሜት ገላጭ ቃል ግጥሞች ለዚህ ማሳያዎች ይኾናሉ።

ሌላው የቃል ግጥም ዋና እና መሠረታዊ ባሕርይ ተለዋዋጭነት (Variability) ነው (Finnegan, 1970፡10)። ይህ ማለት አንድ የቃል ግጥም አሐድ በጊዜ ኺደት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ በተለያዩ ከዋኞች ሊለዋወጥ ይችላል (Alembi, 2002፡31)። ቃል ግጥም ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፈው፣ ከቦታ ቦታ፣ ወዘተ. የሚሰራጨው በቃል በማዜም፣ በማንሳራሳር እና በመሳሰሉት ስለኾነ በቅርጹም ኾነ በይዘቱ ላይ ወጥነት የለውም (Finnegan, 1970፡11)። ይኼ ኹኔታ የሚከሠተው ደግሞ እንደከዋኙና እንደክዋኔው ባሕርይ ለውጥ ስለሚያሳይ ነው። እንደከዋኙ ባሕርይ የተባለበት ምክንያት አቀንቃኙ በአንድ በኾነ አጋጣሚ የሰማውን ቃል ግጥም በሌላ አጋጣሚ፣ ቦታና ጊዜ ሲከውነው ቀድሞ በሰማበት ኹኔታ ቃል በቃል አስታውሶ እንዳለ ማቅረብ ያዳግተዋል። በዚህን ጊዜ ካለው ኹኔታ ጋር ለማስማማት ሲል አንዳንድ ነገሮችን ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ስለሚችል ቃል ግጥሙ ለውጥ ይከሠትበታል። የመለዋወጥ ገጽታውንም በተመለከተ ዘሪሁን (1992፣25) የቃላት፣ የሐረጋት፣ የአረፍተ ነገሮችና ሌሎች የሐሳብ መግለጫ ዘዴዎች ሊኾኑ እንደሚችሉ ገልጸዋል። በአከዋወን ስልቱ ደግሞ በአቀንቃኙና በተሳታፊዎቹ ዕድሜ፣ ጸታ፣ ማኅበራዊ ደረጃና ቃል ግጥሙ በሚነገርበት ምክንያት የሚወሰን በመኾኑ የተነሣ ነው።

3.2.1.2. የቃል ግጥም ማቅረቢያ ስልቶች

ቃል ግጥሞችን ሳቢና ቀላል የሚያደርጉ ስልቶች እንዳሉ Finnegan (1970)፣ Okpewho (1985 & 1992) እና Miruka (1994) ያስረዳሉ። እነዚህም ስልቶች ድግግሞሽ፣ ትይዩነት

(parallelism)፣ የድምፅ ቃና፣ ዘይቤዎች፣ መዝሙራዊ ምት (ዜማዊነት)፣ የድምፅ ቅንብር (alliteration) እና በጥንቃቄ የተመረጡ ቃላት ናቸው።

ድግግሞሽ፡- Finnegan (1970፡90) በአብዛኛው የቃል ግጥም ጉልህ ገጽታው ድግግሞሽ ነው ይላሉ። ምንም እንኳን ድግግሞሽ የሁሉም ግጥም አካል ቢኾንም ቃል ግጥሞች ግን በሐረጋት፣ በስንኞች ወይም በአዝማቾች ድግግሞሽ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። Miruka (1994:90) እና Okpewho (1985:9) እንደገለጹት በአፍሪካ ቃል ግጥም ውስጥ ድግግሞሽ፡-

- ክዋኔውን ለማስረዘም፣
- የግጥሙን ርእሰ ጉዳዮች ለማጠንከርና ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት ለመስጠት፣
- ለክዋኔው የመዝሙራዊውን (የግጥሙን) ምት ለመጨመር፣
- ለግጥሙ መዋቅር አስተዋጽኦ ለማድረግ ያገለግላል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ድግግሞሽ የመርሳትን ወይም የመዘንጋትን ችግር እንደሚከላከል Vansina (1985፡40) አስረድተዋል። በአውራጅና በተቀባይ መካከል ባለው ምልልሳዊ ቅርጽ የሚቀርቡ የቃል ግጥሞች በድግግሞሽ አካኼድ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ትይዩነት (parallelism)፡- ቃላዊ ከዋኙ የሐሳብ ግንኙነቶችን እና ምስሎችን ራሳቸውን በቻለ ኹኔታ ማቅረብ ሲችል ነው። የተለያዩ የትይዩነት ዓይነቶች እንዳሉ Okpewho (1992,78) ገልጸዋል:: ከእነዚህም መካከል አንደኛው የቃላት ትይዩነት (Lexical parallelism) ነው። ይህ ዓይነቱ ትይዩነት የተወሰነ የመዝሙራዊውን እና የግጥሙን ሚዛናዊነት ለመጠበቅ ሲባል ተመሳሳይ የኾኑ ቃላት በስንኞች ውስጥ ተደጋግመው እንዲገኙ ይደረጋል። ኹለተኛው ደግሞ የፍቺ ትይዩነት (Semantic parallelism) ነው። ይህ ዓይነቱ ስልት በዘፈኖችና በመዝሙሮች የተለመደ ሲኾን፣ ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በተከታታይነት በቃል ግጥም ውስጥ መጠቀም ሲቻል እንደኾነ Okpewho (1992,79) አስረድተዋል::

የድምፅ ቃና (Tonality)፡- የቃል ግጥም ከዋኙ ድምፅ በቂ የኾነ ጥንካሬ ከሌለው በሰዎች ዘንድም ታዋቂነትና ተወዳጅነት አይኖረውም (Okpewho,1992: 88-93)። በእርግጥ በዘፈኖችና በመዝሙሮች ውስጥ የድምፅ ቃናው ወጥነት ስለማይኖረው ሊለዋወጥ ይችላል። ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ በጣም ከፍ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ሊል ይችላል። በዚህ ጊዜ በቃል ግጥሙ አማካይነት የሚተላለፈው ይዘት ይጨምራል ማለት ነው።

ዘይቤ፡- እንደ ጽሑፋዊ ግጥም ሁሉ ቃል ግጥምም ዘይቤን ማዕከል የሚያደርግ መኾኑ የታወቀ ነው። ምክንያቱም ግጥሙ አንድነቱን እንዲጠብቅ፣ ጥልቀት ያለው ትርጉም እንዲሰጥ

ለማድረግና ውበትን የተላበሰ እንዲሆን ሲባል ነው (Finnegan,1970፡113)። ለምሳሌ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ንጋት፣ ኮከብ፣ አንበሳ፣ ወዘተ. በቃል ግጥም ውስጥ የዘይቤዎች መንገሪያ በመሆን ያገለግላሉ። ስለዚህ ለዋጭ፣ ሰውኛ፣ አነጻጻሪና ግነት ዘይቤዎች በአብዛኛው በቃል ግጥም ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውላሉ:: ተምሳሌታዊ ዘይቤም በተለያዩ ባህሎች ልዩ ልዩ ትርጉሞች ቢኖሩትም በቃል ግጥም ውስጥ ጠቃሚ ነገር መሆኑ ይታመናል። ያለ ዘይቤያዊ ቋንቋና ገለጻ፣ ውበትና ማዝናናት የቃል ግጥሞች ውጤት አይኖራቸውም (Finnegan,1977:113-118)።

3.2.1.3. የቃል ግጥም ዓይነቶች

Okpewho (1992፡127) በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የቃል ግጥም ዓይነቶችን ለይቶ ለመመደብ ችግሮች መኖራቸውን ከገለጹ በኋላ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከወኑትን የተለያዩ የዘፈን እና የዝማሬ ዓይነቶችን ለመከፋፈል ልዩ ልዩ መስፈርቶችን መጠቀም እንደሚቻል አስረድተዋል። በዚህ መሠረት የቃል ግጥሞቹ በሚያነሡት ርእሰ ጉዳይ፣ ከዋኞቹ በሚጠቀሟቸው መሣሪያዎች፣ በአዘፋፈን ስልት (style of vocalization)፣ ከዋኞቹ አባል በሆኑበት ማኅበረሰብ (by the association to which the performers belong)፣ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ወቅትና በሌሎችም መስፈርቶች ሊመደቡ እንደሚችሉ ተገልጿል። ከዚህ በመቀጠል በተለያዩ ወገኖች የተደረገውን የቃል ግጥም ዓይነቶች ምደባ እንደሚከተለው እንመልከት።

በUNESCO (1998፡21) አመዳደብ መሠረት ሕዝባዊ ቃል ግጥሞች በሦስት ሰፋፊ ፈርጆች ተከፋፍለዋል። ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያዎቹ ወቅታዊ ዘፈኖች /Occasionai Songs/ የሚባሉት ሲሆኑ፣ እነዚህም በሕይወት ዑደት ወቅት የሚቀርቡ ዘፈኖች (በልደት፣ በልጅ ስም አወጣጥ፣ በጉልምስና ወይም በኩርድና፣ በሰርግና በሞት ወቅት)፤ የሥራ ዘፈኖች (በተወሰኑ ሥራዎች ማለትም በአደን፣ በዓሳ ማስገር፣ በሸማ ሥራ ወቅት የሚቀርቡ)፣ በሃይማኖት ሰገዳና በአምልኮ ወቅት የሚቀርቡ ግጥሞች፣ በቤተ መንግሥት የሚቀርቡ፣ የጦርነትና፣ የትችት ዘፈኖች ናቸው።

በሹለተኛ ደረጃ የተፈረጁት ደግሞ በመዝናኛ ወቅት የሚቀርቡ ዘፈኖች /Recreational Songs/ ሲሆኑ፣ በአብዛኛው በዕረፍት ጊዜና በተለየ ወቅት የሚከወኑ ናቸው። ለዚህም የልጃገረድ የፍቅር ዘፈኖች በአብነት ይጠቀሳሉ። በሦስተኛነት የተቀመጡት የልዩ አጋጣሚ ዘፈኖች /Incidental Songs/ የሚባሉት ናቸው። እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የሚቀርቡ ሲሆኑ፣ ልጅን ለማስተኛት ወይም ሲያለቅስ ዝም ለማሰኘትና ለማባበል የሚከወኑ ዘፈኖች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

Finnegan ደግሞ (2012፡111 - 291) የቃል ግጥም ዓይነቶችን የሙገሳ (Panegyric)፣ የሐዘን ወይም የእንጉርጉሮ (Elegiac፣ ሃይማኖታዊ (religious)፣ የሥራ (Working Song)፣ ወቅታዊና ፖለቲካዊ ዘፈኖች (Topical and Political Songs)፣ ስሜት ነኪ (Lyric-Song)፣ ለሕፃናት የሚዜሙ ዘፈኖች በማለት ከፈረጁ በኋላ እያንዳንዳቸውን በሰፊው አብራርተዋል። እነዚህንም ጠቅለል ባለ ኹኔታ በቅደም ተከተል ቀጥሎ እንመልከት።

1. **የሙገሳ ቃል ግጥም** (Panegyric)፡- በአፍሪካ ከፍተኛ የኾነ ጥንቃቄ የሚደረግለትና በጣም የዳበረ የቃል ግጥም ዘውግ ነው። በዚህ መሠረት ሕጋዊ በኾነ መንገድ ለነገሥታት፣ ለሹሞች፣ ለመሪዎች፣ ወዘተ. በአደባባይ ወይም በሕዝብ ዘንድ የሚቀርብ ነው። የሙገሳ ቃል ግጥም አብዛኛውን ጊዜ በሕይወት ሽግግር ወቅት ዋና ሚና ይጫወታል። ይሄውም በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ አንድ ግለሰብ ከአንድ የሕይወት ዕርከን ወደሌላው ሲሸጋገር ለአዲሱ ደረጃ መነሻ፣ ለአሮጌው ደግሞ መታሰቢያ ይኾን ዘንድ ሽግግሩ በምስጋና ይከበራል።

2. **የሐዘን ወይም የእንጉርጉሮ ቃል ግጥም** (Elegiac poetry)፡- በአፍሪካ በጣም የታወቀና የተለመደ፣ ስሜት ነኪ ቅርጽ ያለው ሲኾን፣ አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞች በቀብር ወይም በመታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚከወኑ ናቸው። በእስልምና የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ግን የሐዘን ወይም የእንጉርጉሮ ቃል ግጥሞች የተገደቡ መኾናቸውን Finnegan ገልጸዋል። የቃል ግጥሞቹ ከመጀመሪያውኑ በሌላ የለቅሶ አጋጣሚ ተደርሰውና ተቀናብረው ከቆዩ በኋላ በጊዜው ባለው የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ሊቀርቡ እንደሚችሉ Finnegan (2012፡147) አስረድተዋል። የሐዘን ወይም የእንጉርጉሮ ቃል ግጥሞች የመክፈቻ፣ ሊተላለፍ የሚፈለገውን እና ሟቹን ወይም ባለቤቱን የሚመለከተውን ዋናውን ርእሰ ጉዳይ በመካከል ላይ የሚያንጸባርቁ፣ ወደ ግብዓተ መሬት፣ የመደምደሚያ ወይም የማጠናቀቂያና ተጨማሪ በሚባሉ ደረጃዎች ይከፋፈላሉ።

3. **ሃይማኖታዊ ቃል ግጥም** (religious oral poetry)፡- በዚህ ሥር የሚካተቱት መንፈሳዊ መዝሙሮች፣ የጸሎት ግጥሞች፣ ለፈጣሪ የሚቀርቡ የምስጋና ግጥሞች፣ የነቢይ ግጥሞች ሲኾኑ፣ እነዚህም በተለያዩ ባህሎች በይዘታቸውና በተግባሮቻቸው አንዱ ከሌላው ይለያያሉ። ይህን ዓይነቱን ግጥም ሃይማኖታዊ ነው ብሎ ለመፈረጅ ሦስት ዓይነት መንገዶች እንዳሉ Finnegan (2012፡165-166) ገልጸዋል። የመጀመሪያው ይዘቱ ሃይማኖታዊ መኾኑ፣ ኹለተኛው ግጥሙ በሚመለከታቸው የሃይማኖቱ ሙያተኛ ሰዎች በተደጋጋሚ በቃል መባሉ፣ ሦስተኛው ደግሞ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ በተስማማባቸው ሃይማኖታዊ አጋጣሚዎች መከወኑ ነው።

4. **የሥራ ቃል ግጥም**፡- አሰልቺነት ያላቸውን ሁሉንም የሥራ ዐውዶች የሚያካትቱ ቃላዊ ግጥሞች ሲኾኑ፣ ሰብልን ለመኮትኮት፣ እኽልን ለማረም፣ ለማጨድ፣ ጀልባ ለመቅዘፍ፣ እንጨትን በመጋዝ ለመቁረጥ፣ ዓሳን ለማጥመድ፣ በሙቀጫ እኽልን ለመውቀጥ፣ ውሃን ከጥልቅ ጉድጓድ ለማውጣት፣ የንብ ማስፈሪያ ቀፎን በዛፍ ላይ ለመስቀል፣ የእንስሳትን ቆዳ ለማለስለስ በሚደረጉ ተግባራት ላይ በወንዶች የሚቀርቡ ዘፈኖች ናችው። በቤት ውስጥ ሴቶችም ብቻቸውን ኾነው እኽል ሲፈጩ፣ በሙቀጫ ሲወቅጡ፣ ስፌት ሲሰፉ፣ ወዘተ. የሚያዜሟቸው ዘፈኖችም በዚሁ የሚጠቀሱ ናቸው። በቡድን በቡድን ኾነው የሚሠሩ ሠራተኞችም (ለመንገድ ሥራ መኪና በሚጎትቱበት፣ በፋብሪካ ውስጥ በሚሠሩበት እና ማዕድን በሚያወጡበት ወቅት) የራሳቸውን የኾነ ግጥም ይገጥማሉ። እነዚህ መሰል የዘፈን ግጥሞች ሥራን ለማቃለል፣ ለማስተባበር፣ ወዘተ. የሚያስችሉ መኾናቸው የታወቀ ነው። በተለይ በገጠር አካባቢዎች ያሉ የግብርና ሥራዎች ለሥራ ዘፈኖች የመከወኛ አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ (Finnegan, 2012:225)።

5. **ወቅታዊና ፖለቲካዊ ዘፈኖች** (Topical and Political Songs)፡- እነዚህ ዓይነቶቹ የቃል ግጥሞች እንደተማረው ማኅበረሰብ ሁሉ ባልተማረው ማኅበረሰብ ዘንድ ጋዜጣዎችን በመተካት በወቅቱ ያሉትን ጉዳዮች በመተቸትና ሪፖርት በማድረግ ሊጠቅሙ ይችላሉ (Finnegan, 2012:265)። ይኸውም በፖለቲካው ላይ ግፊት ለማድረግ፣ ለቅስቀሳ፣ የሕዝብ አስተያየቶችን ለማንጸባረቅ፣ ምሬትን ለመግለጽ፣ ወዘተ. ሲባል የሚቀርቡ ናቸው። ተገቢነታቸውም በተነገሩበት ወቅት ላለው የፖለቲካ ኹኔታ ብቻ ነው። የፖለቲካ ግጥሞች በባለሥልጣናት ላይ ግፊት ለማድረግ ወይም በአካባቢው ባለው ፖለቲካ ላይ ትችት ለማቅረብ ሊያገለግሉ ይችላሉ። እንደ ተመራማሪዋ አገላለጽ የወቅቱን አስተዳደር ያለ መቀበል ኹኔታ የሚያንጸባርቁና የምፀት ትችቶች የሚቀርቡባቸው የቃል ግጥሞች የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላቸው ናቸው።

6. **ስሜት ነኪ** (Lyric-Song)፡- ይህ የቃል ግጥም ዓይነት ገደብ አልባ በኾኑ በብዙ ዐውዶች አጭር በኾነ ቅርጽ የሚቀርብ ዘፈን ነው (Finnegan, 2012:236)። Finnegan የውስጥ ስሜት ገላጭ ግጥሞችን ሰዎች በዘመቻ ላይ ባለ ውጊያ፣ በሥራ፣ በፍቅር፣ በጥላቻ፣ ሕፃን በሚወለድበት፣ ከፍተኛ የኾነ ጉዳት ባደረሰ ሞት ወቅት ሊያዜሟቸው እንደሚችሉ ገልጸዋል። የሕይወት ሽግግር ወቅቶች የውስጥ ስሜት ገላጭ ለኾኑ የግጥም ዘፈኖች የታወቁና የተለመዱ አጋጣሚዎች ናቸው። ይህ ማለት ከወሊድ፣ ከሕይወት ጅማሮ፣ ከጉርምስና፣ ከመተጫጨት፣ ከጋብቻ፣ ከቀብር ሥነ ሥርዓትና ከመታሰቢያ ጋር በተያያዘ ብዙ ስሜት ገላጭ የኾኑ የግጥም ዘፈኖች ሊቀርቡ ይችላሉ።

7. ለሕፃናት የሚዜሙ ዘፈኖች፡- እንደ Finnegan (2012፡291) ማብራሪያ ለእዚህ የግጥም ዓይነት ጥሩ ምሳሌ ተደርጎ የተወሰደው ሰዎች የታዘለ ወይም በእቅፍ የተያዘ ሕፃን ሲያለቅስ ዝም እንዲል እየተወዛወዙ በዜማ የሚያባብሉበት የእሸሩሩ (Lullaby) ቃል ግጥም ነው፡፡ የእሸሩሩ ግጥሞች የልጆችን ፍላጎት ለመረዳትና ለማድነቅ የሚቀነባበሩ (የሚገጠሙ) ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የእሸሩሩ ግጥም በተለምዶ ሕፃንን ለማዝናናትና የሚያለቅስም ከሆነ ለማባበል የሚከወን ቢሆንም ልጆችን ከማጎበረሰቡ ጋር ለማቀራረብ ያገለግላል (Peek and Yankah,2004:129)፡፡ በFinnegan (2012:292) የቀረበው አንዱና ዋናው ጥያቄ "ማን ነው ሕፃናትን ለመንከባከብ የእሸሩሩ ግጥሞችን የሚያዜመው?" የሚል ነው፡፡ ለዚህ የሚሆነው መልስም እናቶች ወይም ማንኛውም ጎልማሳ፣ ዐዋቂ ሰው፣ ወዘተ. የእሸሩሩ ቃል ግጥሞችን ሊከውናቸው ይችላል፡፡ የእሸሩሩ ቃል ግጥም ከታሰበው ጉዳይ አንጻር ዝግ ያለ፣ ዜማዊ፣ ምት ያለው ወይም እንቅልፍን የሚያስመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ የእሹሩሩ ግጥሞች ልጆችን ከማጎበረሰቡ ጋር የሚያቀራርብ ዘዴ እንደመሆኑ በዋናነት ቋንቋን እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል (Philip M. Peek and Kwesi Yankah.,2004:129)::

Finnegan ከላይ የቀረቡትን የቃል ግጥም ዓይነቶች የከፈሉበትን መስፈርት በውል አልገለጹም፡፡ ይኹን እንጂ አንድም ጥናቱን ያካሄዱበት ማጎበረሰብ ለልዩ ልዩ የቃል ግጥም ዓይነቶች የራሱ ስያሜ ስላለው ያንን በመጠየቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቃል ግጥሞቹ ከሚከወኑበት ምክንያትና ከከዋኙ ጋር በተያያዘ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት በዚህ ጥናት ባለቤት አዕምሮ ውስጥ ተንጸባርቋል፡፡ እዚህ ላይ ሙያው በዳበረባቸው ሀገራት ያሉ የመስኩ ምሁራን ቃል ግጥምን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በጥልቀት የመረመሩት ጉዳይ ስለሆነ የዚህ ጥናት ባለቤትም የእነሱን ዕውቀት ጥናቱ ከሚካሄድበት አካባቢ ልምድ ጋር በማሰናኘት የምርምሩን ተግባር ለማከናወን ተችሏል፡፡

ቃል ግጥሞች የመዛነቅ ኹኔታ ቢስተዋልባቸውም በይዘት መከፋፈል ጠቃሚ መሆኑን ፈቃደ (1991፡88) እና (Getie,1994: 127-129) አመላክተዋል፡፡ በእኔም ጥናት ቃል ግጥሞቹ ከመስክ በሚሰበሰቡበት በአብዛኛው ማጎበረሰብ ውስጥ የጋራ ይዘት አላቸው ከሚባሉት መካከል ዓበይት የኾኑትን መርጬ በእነሱ መሠረት ለመከፋፈል ችያለሁ፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት አንደኛው ዓላማ በሚሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ላይ ዐውዳዊ ትንተና ማካሄድ በመሆኑ ስለክዋኔ ዐውድ ምንነት በሚከተለው ኹኔታ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

3.2.1.4. የክዋኔ ዐውድ

ዐውድ ማለት ቃል ግጥም በሚከወንበት ወቅት የሚፈጠረውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት ተፈጥሯዊ ቦታና ጊዜ ነው ማለት ይቻላል፡፡ Sims and Stephens

(2005፡19) ዐውድን ሁሉንም ነገር ማለት ሲሾን በአሐድ፣ በመቼት፣ በሰዎች፣ በኹኔታዎች፣ ወዘተ. ዙሪያ ያሉትን ማንኛቸውንም ነገሮች የሚያጠቃልል ነው በማለት ገልጸዋል። በተጨማሪም አብረን የምንጋራቸውን የክዋኔ ገለጻዎችን፣ ሐሳቦችን፣ ተጨባጭ ነገሮችን ያካትታል በማለት በይነዋል።

እንደ Hufford (1995፡528) አገላለጽ ምርምሮች ዐውዳዊ የአጠናን ዘዴን መከተል የጀመሩት ከ1960ዎቹ ጀምሮ ነው። ለዚህ አንደኛው ምክንያት በባህል ጥናት ውስጥ ለተጠኚው ማኅበረሰብ አስተሳሰብ ወይም እይታ ቦታ መሰጠት አለበት የሚል እንቅስቃሴ በመጀመሩ የተነሣ ነው። ኹለተኛው ደግሞ ለተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ትኩረት እየተሰጠው መምጣቱ ሲሾን፣ ተግባራዊያንም በዋናነት ማጠንጠኛቸው የፎክሎር ዘርፉን ለሚከውነው ማኅበረሰብ የራሱ የሾነ ፋይዳ እንዳለውና ያንን ፋይዳ ለማሳየት ፎክሎሩ ከማኅበረሰቡ አቅጣጫ ወይም ማኅበራዊ ዐውድ ላይ ተመሥርቶ መጠናት አለበት የሚል ነው።

አንድ ተመራማሪ የፎክሎር ዘውጎችን በመስክ ላይ እንዴትና በምን ዓይነት መንገድ እንደሚከወኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ በዐውድ መተንተን ይኖርበታል (Douglas,2000፡85)። ከዚህ በተጨማሪ የፎክሎር ዘርፉ የተገኘበትን እና አገልግሎት ላይ የዋለበትን መቼት፣ ልማዶቹ ተግባራዊ የሾኑበትን፣ እምነቱ የተገለጸበትን፣ ታሪኩ የተነገረበትን ኹኔታ አጥኚዎች ማሰብ ይኖርባቸዋል በማለት Sims and Stephens (2005:20) መክረዋል። በዚህ መሠረት የሥነ ቃል ዘርፎችን በዐውድ ማጥናት ያልተበረዘውን መረጃ ማግኘት የሚቻል መኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

Sims and Stephens (2005፡137) ዐውድን “ተጨባጭ ዐውድ” እና “ማኅበራዊ ዐውድ” በማለት በኹለት ዓበይት ፈርጆች ከፍለውታል። እንደ እነሱ ማብራሪያ ተጨባጭ ዐውድ ሲባል አንድ የፎክሎር ዘውግ የሚከወንባቸውን (የሚቀርብባቸውን) ተጨባጭ ነገሮችን እና አካባቢን የሚያጠቃልል ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በክዋኔ ወቅት የምናያቸውን ተጨባጭ ነገሮችን ስንመለከት ከዋኙ የሚያሳየውን የፊት፣ የዓይን፣ የእጅ፣ የእግር እንቅስቃሴ፣ የድምፅ አወጣጥንም ስናይ የውፍረት ወይንም የቅጥነት ኹኔታዎች፣ የአድማጮች ስሜት፣ ታዳሚዎች ለክወናው የሚሰጡት ምላሽ፣ በከዋኝና በታዳሚው መካከል ያለው ግንኙነት፣ በክዋኔው ወቅት የተገኙ ሰዎች ያሉበት ሥነ ልቡናዊ ኹኔታና ሌሎችንም ያጠቃልላል። ኹለተኛው የተጨባጭ ዐውድ ዓይነት ተጨባጭ አካባቢ የምንለው ነው። ተጨባጭ አካባቢ የሚባለው የፎክሎር ዐውድ ክዋኔው የሚቀርብበትን ቦታና ጊዜ፣ የከዋኙን፣ የተሳታፊውን፣ የታዳሚውን ማንነት፣ በክዋኔው ወቅት የሚታዩትን እና ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን ጭምር የሚመለከት ነው።

ማኅበራዊ ዐውድ ደግሞ በፎክሎር ዘውጉ ክዋኔ ወቅት የክዋኔው ባለቤት የኾነውን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ማኅበራዊ ደረጃን ይመለከታል። ይህ ሲባል ባህልን፣ ጸታን፣ ዕድሜን፣ የዘር ሐረግን፣ ሃይማኖታዊ ዳራን፣ ሥራን፣ የመተዳደሪያ ኹኔታን የሚመለከት ነው። ከዋኞቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ወይም አስተሳሰብ በአጠቃላይ በከዋኞችና በታዳሚዎች እንዲሁም በቀሪው ማኅበረሰብ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያሳይ ሲኾን፣ ይህ መስተጋብር በፎክሎሩ ክዋኔ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖም ይመለከታል።

ከጥናት ሥነ ዘዴ አንጻር የመስክ ሠራተኛው መረጃውን ሰብስቦ ለማደራጀትና ዐውዳዊ ትንተና ለመስጠት በBauman (1983:367) የቀረቡ ስድስት ነጥቦች አሉ። እነሱም፡-

1. **ፍቻዊ ዐውድ**፡- የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ትርጉም ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የዐወድ ዓይነት ነው።
2. **ተቋማዊ ዐውድ**፡- ፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚከወነው የት ቦታ ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ሲኾን፣ የሚከወነው ጉዳይም ለባህሉ ተስማሚነትና ተገቢነት ያለው መኾኑንም ይመረምራል።
3. **የተግባቦት ስልት (ሥርዓት)**፡- ይህ ደግሞ የሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ከሌላው የፎክሎር ዘርፍ ጋር እንዴት ይዛመዳል በሚለው ላይ ትኩረት ያደርጋል።
4. **ማኅበራዊ መሠረት**፡- የሚጠናው ርእሰ ጉዳይ የሚከወነው ከየትኛው የማኅበረሰብ ክፍል ጋር ግንኙነት እንዳለው ለመረዳትና የተሻለ ዐውዳዊ ትንታኔ ለመስጠት ያስችላል።
5. **ግለሰባዊ ዐውድ**፡- የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰብ ሕይወት ጋር እንዴት ተስማሚነት ይኖረዋል? የሚለውን ለመመርመር ያስችላል።
6. **ኹኔታዊ ዐውድ**፡- የሚከወነው የፎክሎር ዘርፍ በማኅበራዊ ኹነት ውስጥ እንዴት ጠቀሜታ ይኖረዋል? የሚለውን የሚያመላክት ነው።

Ben - Amos (1993:216) የMalinowskiን ሐሳብ በመከተል ዐውድን ባህላዊ ዐውድና ኹኔታዊ ዐውድ በተባሉ ኹለት ዋና ዋና ርእሰ ጉዳዮች ከፍለውታል። ባህላዊ ዐውድ የሰዎችን አስተያየት፣ በክዋኔው ወቅት ለነገሮች የሚሰጡትን ውክልና፣ የከዋኞችን የዕውቀት መጋራትን፣ ልማድን፣ ጠባይን፣ የተሳታፊዎችን የእምነት ሥርዓትን፣ የዘይቤያዊ ቋንቋ አጠቃቀሞችን፣ የንግግር ስልቶችን፣ የታሪክ ዕውቀትን፣ የሥነ ምግባር መርሕን፣ ወዘተ. የሚባሉትን ያካትታል። ኹኔታዊ ዐውድ ደግሞ የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማኅበራዊ ኹኔታ ይመለከታል። በዚህ ሥር የከዋኙ ዕድሜ፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ ሥርዓተ ጸታ፣ በተግባቦት

ኺደትም የትእምርቶች አስፈላጊነት ይካተታሉ። በተመሳሳይ ኹኔታም ከቋንቋ ክዋኔዎች ማለትም ከኮድ፣ ከቃል አወጣጥ፣ ወዘተ. ጋር ይገናኛል።

ከዚህ በላይ ስለዐውድ ምንነትና ዓይነቶች ለማየት ተሞክሯል። ስለኾነም በተለያዩ ምሁራን የቀረቡት እነዚህ የዐውድ ዓይነቶች ለምርምር ሥራ ጠቀሜታ ያላቸው ቢኾንም እኔ ለማጠናው ጥናት በአገልግሎት ላይ የዋሉት ግን Sims and Stephens (2005፡137) ተጨባጭና ማኅበራዊ ዐውዶች ብለው የመደቧቸው ናቸው። ምክንያቱም በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ የምልከታ ዓይነቶች ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች አደራጅቶ ትንተና ለመስጠት አመች ኾነው በመገኘታቸው የተነሣ ነው።

ስለአንድ የፎክሎር ዘውግ ምንነት ሲጠና በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች ገጽታ (Texture)፣ አሐድ (Text) እና ዐውድ (Context) ናቸው በማለት Dundes (1980፡22) አስረድተዋል። እነዚህ ጉዳዮች ለዚህ ጥናት መሠረታዊ ኾነው ተገኝተዋል። በመኾኑም የገጽታን እና የአሐድን ምንነት፣ እንደዚሁም የሦስቱንም የእርስ በርስ ግንኙነት ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

- **ገጽታ (Texture)፡-** አንድ የፎክሎር ዘውግ የቀረበበትን መንገድ ወይንም ስልት፣ እንደዚሁም ታዳሚው ያን አቅርቦት ወይንም ክዋኔ የተረዳበትን እና የተገነዘበበትን መንገድ የሚመለከት ነው። ገጽታ ከመነሻው ከቋንቋ ጋር የተያያዘ ሲኾን፣ ወደ ፎክሎሩም ሲመጣ ብዙውን ጊዜ ቃላዊ ፎክሎሮች ጋር የማያያዙ ኹኔታ የተለመደ ነው (Dundes, 1980፡22)። ገጽታ ሲባል ከዋኙ የሚከውነው ጉዳይ ቃላዊ ከኾነ በሚተረክበት፣ በሚዘፈንበትና በሚቀነቀንበት ጊዜ የሚወጣውን የድምፅ ኹኔታ፣ ከፍታ እና ዝቅታ፣ ቅላጼ፣ እንደዚሁም በማጀቢያነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሶችንና የአካል እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ነው። ታዳሚውም ቢኾን በማጉረምረምና በፉጨት ተቃውሞውን እና ድጋፉን ሊያሳይ ይችላል።
- **አሐድ (Text)፡-** የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የተጻፉ መማሪያ መጻሕፍትን፣ አጫጭርም ይኹኑ ረጅም የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን፣ በተንቀሳቃሽ ወይም በቴሌቪዥን Screen ግርጌ የተጻፉ የመግለጫ ጽሑፎችን (Caption) ያካትታል (Sims and Stephens, 2005:19)። ተመራማሪው ሥርዓተ ከበራ የሚያጠና ከኾነ በሥርዓተ ከበራው ወቅት ተደጋግመው የቀረቡትን የቃላዊ አሐዶችን አስፈላጊነትና ትርጉም መመርመር፣ ከዚያም ማጤን ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ አሐድ ሲባል በቃል የሚነገረውን ብቻ ሳይኾን በድርጊት የሚቀርበውንም ያካትታል (Sims and Stephens,2005:20)።

ለቃል ግጥም ምርምር ጥሬ መረጃዎቹ አሐዶች ናቸው። እነዚህ አሐዶችም ከዋናው ቃላዊ ምንጭ ቃል በቃል መሰብሰብ ይኖርባቸዋል። በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ የፎክሎር ተመራማሪዎች ቴፕና ቪዲዮ መቅረጫዎችን በመጠቀም ከመረጃ ሰጭዎች ትክክለኛውን መረጃ ለመሰብሰብ ይችላሉ። ይህንንም ሲያደርጉ ቃል በቃል ካሉት አሐዶች በተጨማሪ የመረጃ ሰጪዎቹን ዕድሜ፣ ሥራ፣ ዜግነት፣ መኖሪያ፣ ወዘተ. በተመለከተ ያለውን መረጃ ይመዘግባሉ (Brunvand, 1998 in Sims and Stephens. 2005፡26)::

3.2.1.5. የቃል ግጥሞች ፋይዳ

ቃል ግጥም የተለያዩ ፋይዳዎች እንዳሉት በAlembi (2002፡49)፣ በFinnegan (1970:83)፣ በKabira እና Mutahi (1988:50) ተገልጿል። እነDouglas (2000፡ 84) እና Dundes (2007:56) ቃል ግጥም ለአንድ ማኅበረሰብ የማንነት ስሜትን ወይም ትርጉምን ይሰጣል። ሞራልን ያስተምራል፤ ያዝናናል። ትምህርትን ይሰጣል። ሕፃናትን ፈጣሪ አእምሮ እንድኖራቸው ያደርጋቸዋል። በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ቀለል አድርጎ በማቅረብ ረገድ የማስተማሪያ መሣሪያ ኾኖ ያገለግላል። የሰውን ልጅ አእምሮ ያቃናል፤ ያስተካክላል በማለት አስረድተዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች በተጨማሪ ቃል ግጥም አንድ ማኅበረሰብ የተቀረጸባቸውን ዕሴቶች ያመለክታል (Dundes,2007:59)። በዚህ መሠረት ማንኛውም ሰው በገሃዱ ዓለም በሚኖርበት ወቅት በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን በጎ ተግባራት ጸንተው እንዲቆሙ ያደርጋል። በተቃራኒው ደግም እኩይ የተባሉት ባሕርያት እንዳይፈጸምበት ቃል ግጥም ይከላከልለታል። ስለኾነም በአጠገቡ ያለውን ሰው በተለያዩ አነሣሽ ምክንያቶች መጋፋትን አያስበውም። ለምሳሌ የጥናቱ አካላይ በኾኑት ወረዳዎች አንድ ሰው አብሮት የሚኖረው ጎረቤቱ በሌለበት ቦታ ላይ ያለ ጥፋቱ በክፉ ማንሣትና መተት አደረገብኝ ብሎ መውቀስ እንደሌለበት ቀጥሎ ያሉትን የፉከራና የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን እንመልከት።

መንደር ለመንደር ሰው ከማማት
በሰዓቱ አጭዶ ከቤት መግባት።
(ቃለ መጠይቅ፣ ምትኩ አገኘሁ፣ 21/04/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ሲነግዱ አትነግድ ሲያርሱ አትረስና
አሚረቱብኝ በል ተኝተህ ዋልና።
(ቃለ መጠይቅ፣ ፱ አለቃ አድማሱ ከበደ፣ 21/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የሚሉትና በማኅበረሰቡ አንደበት የተነገሩት ቃል ግጥሞች ያመለክታሉ። እነዚህን መሰል ቃል ግጥሞች “በአንተ ላይ እንዲደረግብህ የማትፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አታድርግ” የሚለውን መርሕ እያንዳንዱ የማኅበረሰቡ አባል አምኖ በመቀበል ተግባራዊ እንዲያደርግ ያስችለዋል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በግብርና በሚተዳደር ማኅበረሰብም ኾነ በአሁኑ ወቅት ባሉ የኢንዱስትሪ ሥፍራዎችም ብዙ ጉልበትን የሚጠይቁ ሥራዎች ስላሉ ቃላዊ ዘፈኖች ስሜትን በማነሣሣት፣ በማስተባበር፣ በማበረታታት፣ ሥራውን የበለጠ አስደሳች በማድረግ፣ በማዝናናት፣ ወዘተ. በኩል በጣም በርካታ ፋይዳዎች ይኖራቸዋል (Peek and Yankah, 2004:220)።

Bascom (1954፡333 - 349) “Four Functions of Folklore” በሚል ርእስ የሥነ ቃል ፋይዳዎችን በአራት ዋና ዋና መደቦች በመከፋፈል አቅርበዋል። ከእነዚህም ፋይዳዎች መካከል የመጀመሪያው ማስደሰት ወይም ማዝናናት የሚል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ሰው ከጭንቀት፣ ከማኅበረሰብ ጫና፣ ካለበት መልክዓ ምድራዊ ክልል፣ ከባዮሎጂካል ውስንነት (ከወሲብ፣ አይነኬ ከኾኑ ነገሮች) ለማምለጥ ያገለግላል።

ኹለተኛው የሥነ ቃል ፋይዳ የባህልን ተገቢነት የማረጋገጥ ሚናን ይጫወታል። ይኸውም ሥርዓተ ከበራዎችን ለሚከውኑ ወገኖችና የተቋማቱንም ቀጣይነት ተገቢ መኾኑን በማስረጃ ያረጋግጣል። ለምሳሌ፡- የሚት ፋይዳው ልማድን እና እምነትን ያጠናል፤ ከፍተኛ የኾነ ዕሴትን ያጎናጽፋል፤ ግብረ ገብነትን ይጠብቃል፤ ያጠናክራልም። ከፍተኛና የተሻለ አምልኳዊ ሥርዓትን ለማስቀጠል ያስችላል (Bascom, 1954፡344)።

ሦስተኛው ደግሞ በትምህርት፣ በተለይ ባልተማረው ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የኾነ የማስተማር ሚና ይጫወታል። በአብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት የብዙዎቹ የሥነ ቃል ዘርፎች ፋይዳ እንደ ሥነ ትምህርታዊ ዘዴ ኾኖ ተሰንዷል። ሕፃናት ሥርዓትን እንዲያከብሩ ለማድረግ ይጠቅማል። ሕዝባዊ ተረቶች ግብረ ገብነትን ጨምሮ አጠቃላይ የኾኑ አመለካከቶችን እና መርሖዎችን ሳይከስሙ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። በመኾኑም ትጋትን፣ ሃይማኖት አክባሪነትን ለማስረጽና ከዚያም አልፎ ለማጠንከር ጥቅም ላይ ይውላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በስንፍና ላይ መሳለቅን፣ ዐመፀኝነትን፣ እምቢተኝነትን እና ትእቢተኝነትን ለመንቀፍ ያገለግላሉ። እንቆቅልሾች በትምህርት አዘል መሣሪያነታቸውም የልጆችን አእምሮ ለማጎልበትና ለማስላት ያገለግላሉ (Bascom,1954፡345)።

የመጨረሻው የሥነ ቃል ተግባር ተቀባይነት ያለውን የሰውን ልጅ ባሕርይ ጠብቆ ማቆየት ነው። ይኸውም ሰዎች ከልደታቸው እስከ ዕልፊተ ሕይወታቸው ድረስ የሚያከናውኗቸውን መልካም ተግባራት ሳይከስሙ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ማለት ነው። ይህ ሐሳብ

ከመጨረሻዎቹ ኹለት ፋይዳዎች ጋር ግንኙነት ያለው ነው። ምክንያቱም የተቋማትን፣ የአመለካከቶችን፣ የአስተሳሰቦችን፣ የእምነቶችን ትክክለኛነትና ተገቢነትንም ስለሚያረጋግጡ ነው። የሥነ ቃል ዘርፎቹ የአንድን ማኅበረሰብ ሞራልና ሥነ ምግባር ያንጸሉ፤ የሌሎችን ሰዎች ባሕርይ ለመተቸት ምቹዎችም ናቸው። ይህ ማለት በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈቀደውን እና የማይፈቀደውን ለመግለጽ ያገለግላሉ። በመኾኑም ማኅበረሰቡ የተስማማበትን ሌላውም ተቀብሎ በተግባር ላይ እንዲያውል ያደርጋሉ። አፈንጋጭ የኾነውን ሰው በመሄስ ወይም በእሱ ላይ በመሳለቅ ወደ ብዙኀኑ አስተሳሰብ ይመልሳሉ። ማኅበረሰቡ የተቀበላቸውን ዐበይት ዕሴቶች የሚጥሰውን እና የማያከብረውን እምቢተኛ ለመተቸት፣ በጓደኞቹ ለማስመከርና ከዚያም ካለፈ ለማስጠንቀቅ፣ ብሎም ማኅበራዊ ግጭት የሚያስከትል ከኾነም ታስቦና ተገምቶ በማኅበረሰቡ ርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋሉ። በአጭሩ የሰውን ልጅ ልማድ ለመቆጣጠርና ለመግታት ያስችላሉ ማለት ነው (Bascom, 1954፡346)።

ቀደም ሲል የቃል ግጥም ፋይዳዎችን በአጭር በአጭሩ ለማየት ተችሏል። በዚህ የተነሣም “የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች፣ ዘውጎች፣ ዐውዳዊ ትንተና፣ ማኅበራዊ ፋይዳ፣ የቃል ግጥሞቹና የመከወኛ አጋጣሚዎቹ ለውጥና ቀጣይነት” በሚል ርእስ በተካኼደው ጥናት ዓላማ መሠረት ከመስክ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በተከወኑባቸው ዐውዶችና በታደሙ ተደራሲያን ወይም ተሳታፊዎች ዘንድ የሚኖራቸው የተለያዩ ማኅበራዊ ፋይዳዎች ተመርምረዋል ተብሎ ይታሰባል።

3.2.1.6. የቃል ግጥሞችና የክዋኔ አጋጣሚዎች ለውጥና ቀጣይነት

ቃል ግጥሞች በሚጠኑበት ወቅት ስለክዋኔ፣ የክዋኔዎቹንም ለውጥና ቀጣይነት ማየቱ ተገቢነት ይኖረዋል። በመኾኑም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር ስለክዋኔ ምንነት በመጀመሪያ ደረጃ ለመዳሰስ ተችሏል። ቀጥሎም ለውጥና ቀጣይነት በቃል ግጥሞች ክዋኔ ላይ እንዴት እንደሚንጸባረቁ ለመመልከት ጥረት ተደርጓል።

3.2.1.6.1. ክዋኔ

ክዋኔ የቃል ግጥም ፈጠራ የሚካኼድበት ትክክለኛው ወቅት ሲኾን፣ በታዳሚዎች ፊት በቤት ውስጥ፣ በቡና ቤቶች፣ በአጥር ግቢ፣ በአብዛኛው ደግሞ በክብረ በዓላት ወቅት፣ ወዘተ. ሊካኼድ ይችላል። Finnegan (1970፡200) በትውፊት (Oral tradition) ረገድ ዋናው ጉዳይ ክዋኔ ነው በማለት በአጭር አገላለጽ ምንነቱን አስረድተዋል። Joyner (1975:257) ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረቶች፣ ዘፈኖችም ይኹኑ ሌሎች የሥነ ቃል ዘርፎች በሕይወት ሊኖሩ የሚችሉት ሲከወኑ

ብቻ ነው በማለት ከFinneganን ጋር የሚስማማ ሐሳብ ሰንዝረዋል። ክዋኔም የሚከወነውን የጥበብ ተግባር፣ ከዋኞቹን፣ የክዋኔውን ኹኔታ፣ የጥበብ ቅርጹን፣ ታዳሚውን እና መቼቱን ያካትታል። እነዚህ ሁሉም ለቃላዊ ክዋኔ መዳበር ዋና እና ማእከላዊ ነገሮች ናቸው (Bauman,1975፡290)።

የቃል ግጥም ክዋኔ በቃል የሚተገበረውን ብቻ ሳይሆን ከዋኞቹ የሚገለገሉባቸውን እና አስፈላጊ የሆኑ ቃል አልባ ቴክኒኮችንም ያካትታል። እነዚህም በክዋኔው አማካይነት የታዳሚውን ትኩረት ለመሳብ ሲባል ታቅደው የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የአካል እንቅስቃሴዎች፣ አስመስሎ መቅዳት ወይም በአጠቃላይ ድርጊትን ያለ ንግግር በምልክት ብቻ ማሳየት የሚሉትንም ይጨምራል (Peek and Yankah, 2004:633)። እንደ እነ Peek ማብራሪያ በከዋኞችና በታዳሚዎች መካከል ባለው መስተጋብር በርካታ ቃላዊ ጥበቦች በግልጽ ወይም በይፋ ይከወናሉ።

የክወና አጋጣሚዎች አስፈላጊ የሆነ ሥርዓተ ከበራ ወይም ፌስቲቫል፣ ባልተለመደ ኹኔታ በሚሰባሰቡ ታዳሚዎች አማካይነት የተዘጋጀ ቦታ፣ በታዳሚዎች መካከል ያለው የውድድር ኹኔታና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኛዎቹ የተለመዱት የመከወኛ አጋጣሚዎች የለቅሶ፣ የእርሻ፣ የዐረም፤ የዐጨዳ፣ የውቂያ፣ የሰርግ፣ የደቦ፣ የአደን፣ ወዘተ. ቦታዎችና የልዩ ልዩ የሃይማኖትና የዓመት ክብረ በዓላት፣ እንደዚሁም መጠጥ ቤቶች ናቸው። የቃል ግጥም ክዋኔ ዋና ዋና መንገዶችም ዘፈን፣ ማዜምና ማንሳራጎር ናቸው (Finnegan,1970:118)።

አንድ ከዋኝ በታዳሚ ፊት ለፊት ኾኖ ዘፈኖችን ሊዘፍን፣ ወይም ዘፈኖችን ተራ በተራ ከሌሎች ታዳሚዎች ሊጋራ ይችላል - ልክ እንደ እኛ ሀገር አዝማሪ “ተቀበል” እንደምንለው ዓይነት ማለት ነው። በዚህን ጊዜ ቃላዊ ጥበቡም ኾነ ፈጠራው ደምቆ ሊታይ ይችላል። በዚህ መሠረት ክዋኔ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የዐውድ አካል ነው ማለትም ይቻላል። በዚህ አረዳድ ክዋኔ በከፍተኛ ኹኔታ እውነተኛና ተፈጥሯዊ የኾነ የቃል ግጥም መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል (Finnegan,1992፡87)።

በመሠረቱ ከዋኞች የቃል ጥበቡን የሚማሩት በኹለት ዓይነት መንገድ ነው። እነዚህም መንገዶች መደበኛና ኢ-መደበኛ በመባል ይጠራሉ (Peek and Yankah, 2004፡ 633)። መደበኛ የሚባለው በተደራጀ ተቋም ለከዋኞቹ ሥልጠና የሚሰጥበት ኺደት ነው። ኾኖም የቃል ግጥም ክዋኔ መደበኛ ትምህርት በአፍሪካ ጎብረተሰብ ዘንድ የተለመደ አይደለም (Finnegan,1977፡19)። በሀገራችን ለአብዛኛዎቹ ቃላዊ የክዋኔ ዓይነቶች በይበልጥ የተለመደው ኢ-መደበኛው ነው። በዚህ መሠረት በብዙ አጋጣሚዎች ከሥርዓተ ከበራዎች አንሥቶ እስከ ሀሳታ የበዛበት መጠጥ ቤት ድረስ ለብዙ

ሰዓታት ተደጋግመው የተዘፈኑትን ዘፈኖች ከዋኞቹ በማዳመጥ በቀላሉ ሊማሩ ይችላሉ፡፡ እንዲያውም የተወሰኑ ግለሰቦች የፈጠራ ተሰጥኦ እስካላቸውና መንፈሳቸው እስከተቀሰቀሰ ድረስ ዘፋኞችና የዘፈኖችም ደራሲ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ወቅት የአድማጮች ወይም የታዳሚዎች ግብረ መልስ ከከዋኞች ጋር ጠንካራ የኾነ ቁርኝትን ለመመሥረት ስለሚያስችል ለክዋኔው ቀስቋሽነት ከፍተኛ የኾነ ሚና ይጫወታል (Finnegan,1992፡87)፡፡

በመኾኑም ከዋኙ በክዋኔው አማካይነት የታዳሚዎቹን የተሳታፊነት ስሜት፣ ፍላጎት፣ መንፈስና ትኩረት እንዲነሣሣ ስለሚያደርግ በዚያው መጠን እነሱም ለእሱ ክዋኔ ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ ራሳቸውም ቢኾኑ ተማርከው በክዋኔው ውስጥ ራሳቸውን ያስገባሉ፡፡ እንዲህ ያለው ነገር ሲታይ ከዋኙ አድማጩን በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል፤ ክብርንም ሊጎናጸፍ ይችላል (Bauman,1975፡305)፡፡

በቃላዊ ዘፈኖች አምስት የክዋኔ ደረጃዎች መኖራቸውን Lomax (ውስጠ Hymes, 1971፡46) በዝርዝር አስፍረዋል፡፡ እነዚህም፡- 1. በቡድን፣ በተናጠልና በብዛት የዘፋኞች መጠን፣ 2. በአውራጅ (በአቀንቃኝ)ና በተቀባይ መካከል ያለ ግንኙነት፣ 3. የአውራጅ (የአቀንቃኝ) ልቆ የመታየቱ መጠን፣ 4. በቡድኑ ውስጥ ያለው የቅንጅት ደረጃ፣ 5. በክዋኔውና በታዳሚዎች መካከል ያለው ግንኙነት ናቸው፡፡ እነዚህ በማንኛውም ክዋኔ ወቅት መኖር ያለባቸው ቀዳሚና መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በምርምር ሥራ ወቅትም ቢኾን ክዋኔ ተጨባጭ የኾኑ ኹነቶችን በተከወነበት ጊዜ ለማሳየት ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ጥበባዊ የኾነው ቃላዊ ክዋኔ የቱ ነው? መቼና ለምን ዓላማዎች ሲባል ነው የሚከወነው? ፋይዳውስ ምንድን ነው? የከዋኞቹም ኾነ የአድማጮቹ ስሜት ምንድን ነው የሚመስለው? የተለየ መለዮ ባሕርይ ላለው ሰው ነው የሚከወነው? ወይስ ለማንነት መገለጫ ነው የሚቀርበው ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ የኾኑ መልሶችን ለመሻት ያስችላል (Bauman,1971:40):: በዚህ ጥናትም እነዚህ ጥያቄዎች ለመረጃ ሰጪዎች እየቀረቡ ምላሾችን ለማግኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ ከዋኞቹ በተለያየ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ፣ ጾታቸው፣ ማኅበራዊ ደረጃቸው፣ አሠለጣጠናቸው፣ ዝናቸው፣ ብቃታቸው፣ ወዘተ. የተለያዩ ስለሚኾኑ እነዚህ ሁሉ ለምርምሩ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ በክወናው ወቅት ተራ ነገር የሚመስሉን ግን ደግሞ ለምርምሩ ሥራ ጠቃሚነት ያላቸው ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነገሮችን በጥንቃቄ መመልከት እንዳለብን Finnegan (1992:90) ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ እያንዳንዱ የሥነ ቃል ክዋኔ ዋና ዋና ባሕርያቱ የተናጋሪና የአድማጭ የፊት ለፊት መገናኘት፣ ክክዋኔው የሚጠበቅ ነገር መኖር፣ ባህላዊ ክዋኔው የሚገዛበት ሥርዓት ወይም ቅደም ተከተል ያለው መኾኑ፣ ክዋኔው እንዲፈጸም አነሣሽ ምክንያት መኖር፣ በክዋኔው ወቅት የሚቀርቡ አሐዶች ተሟልተው መገኘት የሚሉት ናቸው። ክዋኔው ሲጠናም ከእነዚህ ጉዳዮች አንጻር መኾን እንዳለበት Bauman (1975፡295) አመላክተዋል። ስለዚህ ከላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን ሐሳቦች በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል።

3.2.1.6.2. ለውጥና ቀጣይነት

የባህል ለውጥና ቀጣይነት በጥልቀት የተቆራኙ መኾናቸውን Ascher and Heffron (2010፡10) ገልጸዋል። በመኾኑም በዚህ ክፍል እነዚህ ርእሰ ጉዳዮች የተካተቱበት ዋናው ምክንያት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ አንደበት በሚዜሙ የቃል ግጥሞችና በሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ላይ ያለውን ለውጥና ቀጣይነት መመርመር የጥናቱ አንደኛው ዓላማ በመኾኑ የተነሣ ነው። እዚህ ላይ አስቴር ሙሉ በ2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር ባቀረበችው የዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ ለመመርመር ችላለች። በዚህ ሥራዋም የወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች ምን ምን እንደሆኑ፣ በአዝማሪዎቹ የዘፈን ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ልምዶች ምን መልክ እንዳላቸው፣ በሙያተኞቹ ኑሮ ውስጥ የተከሠቱ ለውጦችና ምክንያቶቹ ምን ምን እንደሆኑ፣ የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ምን እንደሚመስል ለማየት ችላለች። የእኔ ጥናት ግን በወሎ አዝማሪዎች ላይ ያለውን የኑሮና የዘፈን ልምድ ተከታታይነትና ለውጥ፣ እንደዚሁም ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ርእሰ ጉዳዮች ስለማይመለከት ከአስቴር ሙሉ ጥናት ጋር ሙሉ በሙሉ የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

3.2.1.6.2.1. ለውጥ

ለውጥ የሚለው ቃል ፍች የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ኹኔታ፣ ባሕርይ፣ መልክ፣... በሌላ እንዲቀየር፣ እንዲተካ ማድረግ ማለት ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣1993፡21)። ስለኾነም በማንኛውም የኅብረተሰብ ሥርዓት ለውጥ ተፈጥሯዊ ክሥተት እንደኾነ ነው የሚታመነው (Strasser,1977:19) እና (Ascher and Heffron (2010፡10):: በዚህ መሠረት ለውጥ በየትኛውም የማኅበረሰብ ደረጃ አይቀሬና የተለመደ ነገር መኾኑ ለማንም የተሰወረ ነገር አይደለም። ከዘመናት በላይ በዚያው ባለበት ኾኖ

የሚቆይ ወይም የሚኖር ነገር የለም (Vansina,1985፡130)፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የታየው የማኅበረሰብ ለውጥም በከተሞች ዕድገት፣ በኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና በሰዎች ዝውውር፣ ወዘተ. እንደመጣ የሥነ ሰብና የሥነ ማኅበረሰብ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ (Alemmaya, 2002፡11)፡፡

የፎክሎር ለውጥም በውስጥም ኾነ በውጭ አስገዳጅ ኹኔታዎች ሊመጣ ይችላል፡፡ በውስጥ አስገዳጅነት የሚታየው ለውጥ በኅብረተሰቡ ሥርዓት ውስጥ ባለ የልማድ ጣጣ፣ በኢኮኖሚ ዕድገት የተነሣ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚኖር የኑሮ መሻሻል፣ በፖለቲካ ለውጥ ምክንያት ሊመጣ የሚችል ነው (Ascher and Heffron, 2010:3)፡፡ በአጠቃላይ የአንድ ሀገር ኅብረተሰብ በኺደት ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ማለትም በኢኮኖሚውም ኾነ በማኅበራዊው መስክ ለውጥ ሊያሳይ ይችላል (ሥዩም ተፈራ፣1999፣165)፡፡ በተለይ በልማድ ጣጣና በኅብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል የሚመጣው ለውጥ የፎክሎሩ ባለቤት የኾነው ማኅበረሰብ ጠቃሚነቱን ተረድቶና ተገቢ መኾኑን አምኖበት ሊኾን ስለሚችል ለውጡ ተቃውሞን የማስተናገድ ዐቅም አይኖረውም፡፡ ከውጭ በሚመጣው ተጽዕኖ የሚከሠተው ለውጥ ግን በድንበር ጦርነቶች፣ ኾን ተብለው በሚደረጉ የዘር ማጥፋት ተግባራት፣ በበሽታ፣ በቅኝ ገዥዎች ወዘተ. ሊኾን ይችላል፡፡ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ባህልን በፍጥነትና በአደገኛ ኹኔታ ሊለውጡትና ሊያጠፉት ይችላሉ (Sims and Stephens 2005፡ 74)፡፡ በቴክኖሎጂ ምክንያቶች የሚመጣው የፎክሎር ለውጥ ማንነትን፣ የማኅበረሰቡን ዕሴቶች፣ እምነቶችን፣ አጠቃላይና ተናጠላዊ የኾኑ ምግባራትን ስለሚያሳጣ ማኅበረሰቡን ራቁት ሊያስቀር ይችላል ማለት ነው፡፡

Dundes (1965፡120) በፎክሎር ዘውጎች ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከታትሎ ለመድረስና ማኅበረሰቡ ስለዓለም ያለውን አመለካከትና ዕሴቶቹን፣ ለውጡንም እንዴት ማንጸባረቅ እንደሚችል ለማጥናት “ለምን” የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ፋይዳ እንዳለው አስገንዝበዋል፡፡ በቃል ግጥሞችና በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ላይም ለሚከሠተው ለውጥ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የከተሞችን ዕድገትና የሰዎችን ዝውውር ጨምሮ የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ የመንግሥት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ፣ የኤሌክትሮኒክስ የመዝ‍ሙቃ መሣሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህ ጥናትም በቃል ግጥሞቹም ኾነ በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የመጣውን ለውጥ በመረጃ ትንተና ወቅት ለማወቅ ለምን ዓላማና ምክንያት ነው ለውጥ የተደረገው? ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው ለውጡ የተከሠተው? በለውጡ

አማካይነት የተገኙ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉ ወይ? ማኅበረሰቡ ለውጡን በአዎንታዊ ወይስ በአሉታዊ ነው የተመለከተው? ወዘተ. የሚሉት ጥያቄዎች ተመርምረውበታል።

3.2.1.6.2.2. ቀጣይነት

ቀጣይነት የሚለው ቃል አንድ ነገር በነበረበት ኹኔታ ያለማቋረጥ አንዱ ከሌላው ተከታታይነት ባለው ኺደት መንገዝ ማለት ነው። ይህም የማያቋርጥ ኺደትን ያመለክታል። ምክንያቱም በአንድ ባህል ውስጥ የሚከናወኑ ልማዶች፣ ነገሮች፣ ወዘተ. በማኅበረሰቡ አማካይነት ሳያቋርጡ የሚከናወኑ ከኾነ ነው ቀጣይነት ኖሯቸዋል የምንለው በማለት Friedland እና Mohr (No Year, 71) ገልጸዋል። ይህ ማለት ግን ማንኛውንም ነገር ምንም ሳይለወጥ ማኖር ማለት እንዳልኾነ መገንዘብ ይቻላል።

የሥነ ቃል ዘውጎች ከትውልድ ወደ ትውልድ ቀጣይነት የሚኖራቸው በትምህርት አማካይነት ባላቸው ሚና ነው (Bascom,1954:349)። ይህ ሲባል ተማሪዎች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሥነ ቃሎችን የሚያገኟቸው ከኾነ በእነሱ አማካይነት ቋንቋውን እየተዝናኑ ይማራሉ፤ ሥነ ቃሎቹንም ሳይረሷቸው ለቀጣዩ ትውልድ በቀላሉ ሊያስተላልፏቸው ይችላሉ። ከእዚህ በተጨማሪ በመዝናኛዎች፣ በምናባዊ ፈጠራዎች፣ በእምነቶች ... አማካይነት ሥነ ቃሎችን ከለውጥ ጠብቆ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል (Bascom, 1954፡ 349)። በተለይም በቃል ግጥም የተቀናበሩ ዘፈኖችን በመከወንና ልማዳዊ በኾነ ዘዴ ልጆችን በማስተማር ከአንድ ትውልድ ወደቀጣዩ ትውልድ ማሸጋገር ይቻላል (UNESCO,1998:23)። በተለያዩ ምክንያቶች አማካይነት በሚፈጠሩት የመከወኛ አጋጣሚዎች የሚደርሱትን ለውጦች፣ ለውጦቹን ተቋቁመው በመከወን ላይ ያሉ ቃል ግጥሞች ያላቸውን ቀጣይነት ለይቶ ለማመልከት በዚህ ጥናት ትኩረት ተደርጓል።

3.3. የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፎች

ፎክሎር ያን ያኽልም ንድፈ ሐሳብ አያስፈልገውም ተብሎ በምሁራን ይታሰባል። Oring (1991፡80 በግልጽ አነጋገር “Folklore is liminal precisely because it has no theory or methodology that governs its perspective.” በማለት ገልጸዋል። ሌሎች የፎክሎር ባለሙያዎች ደግሞ የጥናት መስኩ የራሱ የኾኑ የንድፈ ሐሳብ መነሻዎች ባይኖሩትም ከሌሎች ሙያዎች በፈለቁ ንድፈ ሐሳቦች አማካይነት ጥናት ሲደረግበት እንደቆየ ይገልጻሉ:: ከእነዚህ መካክል Ben-Amos (1993፡209-226) የፎክሎር ጥናት ከሥነ ሰብእ፣ ከማኅበራዊ ሥነ ልሳን፣ ከሥነ ማኅበረሰብ፣ ከሳይኮሎጂ፣ ከፍልስፍና እና ከሥነ ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን

ንድፈ ሐሳቦችን እና ዘዴዎችን በማስማማት ወይም አንድ በማድረግ ነው የሚጠቀመው በማለት አብራርተዋል።

Dundesም (2005፣ 387-388) በበኩላቸው በፎክሎር ጥናት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት ንድፈ ሐሳቦች የመጡት ከሌላ ሙያ ነው ይላሉ:: ንድፈ ሐሳቦቹ ከሌሎች ሙያዎች የተወሰዱ ናቸው ቢባልም ለፎክሎር ጥናት አስፈላጊ ናቸው የተባሉትን በማስተርስም ኾነ በፒኤችዲ .ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን የሠሩ ምሁራን እንደተጠቀሙባቸው ከሥራዎቻቸው ለማረጋገጥ ችያለሁ። በዚህ ጥናትም በሰነድ ፍተሻ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በክዋኔያዊ (Performance Theory)፣ በተግባራዊ (Functional Theory) እና በዐውዳዊ (Contextual Theory) ንድፈ ሐሳቦች በመተንተን ጥናቱ የመጨረሻው ውጤት ላይ እንዲደርስ ጥረት ተደርጓል።

3.3.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ

ዐውድን ማእከል አድርጎ አሐዶችን ለመተንተን በሚካሔደው በዚህ ጥናት ጠቃሚ ኾኖ የተመረጠው አንደኛው ንድፈ ሐሳብ ክዋኔያዊ የተባለው ነው። ምክንያቱም ያለ ክዋኔ ማንኛውም የሥነ ቃል ዘርፍ ሊኖር አይችልምና ነው። ስለዚህ ዋና ትኩረቱ የፎክሎር ዘርፉን ማጥናት ያለብን እየተከወነ ባለበት ወቅት ነው የሚል ነው (Dundes,2005:389):: ከዚህ በተጨማሪ ለቃላት ብቻ ሳይኾን ከዋኞቹ እንዴት አድርገው ክዋኔውን እንዳቀረቡት መመርመር ላይ ነው።

ንድፈ ሐሳቡ የተጀመረውና የታወቀ ዘዴ የኾነው በ1970ዎቹ ሲኾን፣ ይህንንም በማዳበር በኩል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት Hymes, Bauman, and Abrahams ናቸው (Peek and Yankah,2004፡ 803)። እነBauman ለክዋኔ ያላቸው ፍላጎት ያደገውም ንድፈ ሐሳቡ ለቃላዊ ተግባቦት የተለየ ስልት በመኾኑ የተነሣ ነው። በተለይ ከዐውድ በተገኙ አሐዶች (text in context) ላይ ትንተና ለማድረግ ጠቃሚው ንድፈ ሐሳብ ክዋኔያዊ እንደኾነ Myrvold (2008:8) ገልጸዋል።

ክዋኔ ዝም ብሎ ጭፈራ ወይንም ሌላ ነገር በዘፈቀደ ማከናወን ማለት አይደለም። ራሱ ሊመራበት የሚችልበት ቅደም ተከተል አለው። ይዜውም እንዴትና መቼ ተጀምሮ መቼና እንዴት መጨረስ እንዳለበት፣ በመካከል ላይ ምን ምን ነገሮች እንደሚከናወኑ በቅደም ተከተል የሚከተለው ሕግ አለው። አንዳንዶቹ ክዋኔዎች የሚከወኑበት ቋሚ የኾኑ ቦታዎችና ቀናት አሏቸው። እነዚህም ክዋኔ በዘፈቀደ መከናወን እንደሌለበትና በሕግ የሚመራ መኾኑን ያመለክቱናል (Bauman,1975፡299)።

በመኾኑም የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የሥነ ቃል ዘውጉ የተከሠተበትን አጋጣሚ በመመርመር ኅብረተሰቡ የሚከተለውን መዋቅር፣ ኺደት፣ በመከወኛ አጋጣሚው ያለውንም ፍች ለመገንዘብ ይረዳል ተብሎ ይታሰባል። እንደ Bauman ማብራሪያ በክዋኔ ንድፈ ሐሳብ መሠረትነት የሚጠናው የሥነ ቃል ዘውግ ሳይነጣጠሉ በሚቀርቡ አላባውያን መሠረት መመርመር አለበት። እነዚህ አላባውያንም ክዋኔውን የሚመራው ሰው /Performer/፣ ከከዋኙ ጋር የፊት ለፊት ግንኙነት ሊያደርግ የሚችል ተመልካች (ክዋኔው የብቻ ካልኾነ)፣ ክዋኔው የሚቀርብበት ጊዜና ቦታ፣ በቃል የሚቀርብ አሐድ፣ ሕግና ደንብ፣ ከአድማጮች የሚቀርብ አሉታዊም ኾነ አዎንታዊ ምላሽ፣ የሚተላለፉ መልእክቶች የሚሉት ናቸው። የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ከእነዚህ አላባውያን በተጨማሪ ክዋኔው ተቀነባብሮ የሚቀርብበትን ዐውድ ይመረምራል (Peek and Yankah, 2004፡ 632)::

በዚህ ጥናትም ክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ የኾነው ጥናቱ ባካለለው ማኅበረሰብ የሚቀነቀኑት የቃል ግጥሞች በየዐውዳቸው እንዴት እንደሚከወኑ ለመመርመር፣ ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎች፣ ለውጥና ቀጣይነታቸውንም ለመግለጽ የሚሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ነው።

3.3.2. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተጀመረና ማንኛውም የፎክሎር ዘውግ ተግባር አለው በሚለው አስተሳሰብ ላይ ያተኮረ ነው። ይኸውም አንድ ተመራማሪ የሚሰበስበው የፎክሎር ዘውግ በባህሉ መሠረት ለግለሰቡም ኾነ ለማኅበረሰቡ ፋይዳ አለው (Green,1997፡386)። የንድፈ ሐሳቡ አራማጆች የነበሩት Radcliffe እና Malinowski ሲኾኑ ብዙውን ጊዜ ፎክሎር የሚጠናው በተገኘበት፣ ባለበት ወቅት ወይም በተቀረጸበት ዘመን ነው የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው (Oring,1976፡67) እና (Green,1997፡386)። እኒሁ ምሁራን ፎክሎር በተለያዩ መንገዶች አገልግሎት ላይ እየዋለ መኾኑን በማሳየታቸው የአፍሪካ ፎክሎር አይረባም፤ አገልግሎት የለውም የሚለውን የቅኝ ገዥዎችን አስተሳሰብ ሽረው ትልቅ ነገር ለማምጣት ችለዋል (Oring,1976፡67)። በመኾኑም በፎክሎር ጥናት እያንዳንዱ የፎክሎር ዘውግ ተግባር ያለው መኾኑ መመርመር አለበት የሚል መርሕ አለ። ለአብነትም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው ማንኛውም ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ተረት፣ ሚት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ዘፈን፣ ወዘተ. ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተግባር አለው (Green,1997:386)::

Bascom (1954፡343-349) በማኅበረሰብ ውስጥ ቋሚነት ወይም ቀጣይነት ያለውን የፎክሎር ኹኔታ ለመግለጽ የሚያገለግሉትን በርካታ ተግባራትን በሐሳብ ደረጃ አቅርበዋል። ኾኖም

ትኩረት የሰጡት ለማምለጫ፣ የአንድን ነገር ተገቢነት ለማጽደቅ፣ ለማስተማር፣ ለመቆጣጠርና ለመግታት ነው የሚለው ሐሳብ ቀደም ሲል በዚሁ የጥናት ጽሑፍ ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል። እነዚህ የባህልን ዘለቄታነት የመጠበቂያ ብቸኛ ተግባራት ናቸው በማለት Bascom ፈርጀዋቸዋል።

በተጨማሪም ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ብቅ ማለቱ በአሁኑ ወቅት ያለውን የማኅበረሰብ ሥርዓት የሚኖረውን ማኅበረ ባህላዊ ቀጣይነት ለመግለጽ አስችሏል (Oring,1976:71)። በማንኛውም ወቅት ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በልማዶች (norms) ቁጥጥር ሥር ናቸው። ምክንያቱም ማኅበረሰቡ ምስጉን እና ድንቅ ናቸው ከሚላቸው ዕሴቶች የሚያፈነግጡ ሰዎች ካሉ ግሣጼ ይደርስባቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸው መልካም ድርጊቶች አስፈላጊነታቸውና ተገቢነታቸው እንዳይከስም ለማድረግ አድናቆትና ሙገሳ ይቸራቸዋል። የፎክሎር ተግባርም እነዚህን ልማዶች ማስጠበቅና ማስቀጠል ነው። በዚህ ረገድ Radcliffe ለተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ለዚህ ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ለመረጃ መተንተኛነት የተመረጠበት ዋናው ምክንያት ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች ከሚገኘው ማኅበረሰብ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ያላቸውን ተግባር ለመመርመር፣ የቃል ግጥሞቹን ለውጥና ቀጣይነት ለመግለጽ ለሚሉት ዝርዝር ዓላማዎች ግብ መምታት ከፍተኛ የኾነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ከሚል ዕሳቤ ነው። የቃል ግጥሞቹን ተግባራትና ትርጉም ለመመልከትም ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ጥቅም ላይ መዋሉን በሚከተለው ኹኔታ ለማየት ተችሏል።

3.3.3. ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ

ከ1960ዎቹ በኋላ የፎክሎርን ዘርፎች በዐውድ ማጥናት እንደሚገባ Ben-Amos (1971, 1993), Bauman (1983) እና Hufford (1995) አመላክተዋል። ንድፈ ሐሳቡም የመነጨው በጎሣ ጥናት ምሁራን (Ethnographers) አማካይነት መኾኑን Hufford (1995፡528) ገልጸዋል። ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር፣ በሥነ ሰብእ፣ በማኅበራዊ ሥነ ልሳን፣ በሥነ ማኅበረሰብ፣ ወዘተ. ካሉት የጥናት ዘርፎች በተገናኘ መልኩ ንድፈ ሐሳብና ዘዴ በመኾን አገልግሏል (Ben-Amos,1993:209)። በመኾኑም አንድ ተመራማሪ ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብን በጥናቱ ውስጥ በተግባር ላይ ማዋሉ የሚያጠናውን ማኅበረሰብ አካባቢና ባህል በትክክል እንዲረዳና እንዲያውቅ ያደርገዋል ማለት ነው።

በተለይ በማኅበረሰቡ አንደበት በሚነገሩት የሥነ ቃል ዘውጎች ላይ ጥናቱን የሚያካኺድ ምሁር ታላሚ የኾነው ርእሰ ጉዳይ ትርጉም ምን ማለት እንደኾነ መገንዘብ የሚችለው በዐውድ ሊኾን እንደሚገባ ማጤን ይቻላል፡፡ ይህ ካልኾነ ግን ማኅበረሰቡ ሥነ ቃሉን በዐውዱ ውስጥ እንዴት እንደሚተረጉመው፣ እንዴት እንደሚረዳው፣ እንዴት ፍቺ እንደሚሰጠው፣ እንዴት እንደሚገለገልበት፣ ወዘተ. ሊያውቅ አይችልም ማለት ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተገለጸው ቁም ነገር የቃል ግጥም ጥናትም ቢኾን እንዴት ሊመራና ለትንታኔውም እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል የሚያመላክት መሠረተ ሐሳብ በመኾኑ እኔም ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብን በምርምር ሥራዬ ውስጥ ለመጠቀም ችያለሁ፡፡

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ በተጨማሪ ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ለክዋኔያዊ ጥናት መሠረታዊ ጉዳይ እንደኾነ Hufford (1995፡531) ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም ያለ ዐውድ ብቻውን የሚኖር ክዋኔ የለምና ነው፡፡ ስለኾነም ጥናቱ ባካለለው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚነገሩ የቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸው ዐውዳዊ ስምምነቶች ወይም ልማዶች አሉ፡፡ እነዚህም የቃል ግጥሞቹ የመከወኛ ቦታዎችና ጊዜያት፣ እንደዚሁም በክወናው ወቅት ዐብረው በማጀቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናትም ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብን በተግባር ላይ ለማዋል በመጀመሪያ ደረጃ የጥናቱ ትኩረት የኾኑት የቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ እየተከወኑ መኾን አለመኾናቸውን በየወረዳዎቹ ካሉት የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች መካከል ከባህል ዕሴት ተጠሪዎች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ በውይይቱም አብዛኛዎቹ የቃል ግጥሞች በመከወን ላይ መኾናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚያም በዐውድ የቃል ግጥሞቹን ይዘት እና ፋይዳ ለመለየት ተችሏል፡፡ ይህ በሚኾንበት ወቅት ዘይቤያዊ አገላለጾች በያሏቸው መልእክቶች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ ባጭሩ ለማጠቃለል ከላይ በቅደም ተከተል ባሉት ገለጻዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ለዚህ ጥናት ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ተገቢ መኾኑን አጥኚው ተረድቷል፡፡

ምዕራፍ አራት፡- የጥናቱ ሥነ ዘዴ

በዚህ ርእስ ሥር በቅድሚያ የጥናቱን ዓይነት፣ የናሙናውን አመራረጥ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ያገለገሉትን ጉዳዮች በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡ ከእነዚህ በመቀጠል የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን እና መቼቶችንም ተራ በተራ እናቀርባለን፡፡

4.1. የጥናቱ ዓይነት

ከ1950ዎቹ ወዲህ ቃላዊ የሾኑ ልዩ ልዩ መረጃዎች በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የይዘት ትንተና እንደሚካኼድባቸው Kothari (2004፡110) ገልጸዋል፡፡ ይህ ምርምርም ከተነሣበት ዓላማ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹና የተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች ከሚተነተኑባቸው ዘዴዎች አንጻር ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ በዚህ የምርምር ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ኾኑ የትንተና ውጤቶቹ በቁጥር የሚገለጹ ወይም የሚወከሉ አይደሉም፡፡ Bestም (1981፡75) ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ያለ ምንም አኃዛዊ መረጃዎች ኹነቶችን፣ ሰዎችን፣ ወዘተ. ሳይንሳዊ በኾነ መንገድ ሊገልጽ ይችላል በማለት ገልጸዋል፡፡ ይኸውም ተመራማሪው ያገኛቸውን መረጃዎች በሙሉ በስታትስቲካዊ ዘዴ አይገልጻቸውም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ላንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለጻዊ መንገድን ተከትሎ በመኾኑ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በዐውድ ላይ ያለውን ነባራዊ ኹኔታ መሠረት አድርጎ የተገኙትንም መረጃዎች በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብና የተለያዩ እውነታዎችን መርምሮ ማግኘትን የሚያካትት በመኾኑ ገላጭ የምርምር ዓይነትን በተግባር ላይ አውሏል፡፡ ገላጭ ምርምር አብዛኛውን ጊዜ በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፎች በሚካኼዱ ጥናቶች የታወቀ ነው፡፡ ዋና ባሕርይውም አጥኚው በሚሰበስባቸው መረጃዎች አማካይነት ምን ምን እንደተከሠተ ወይም ምን እየተከሠተ እንደኾነ ለማብራራት ያስችላል፡፡ ከዚያም በእነዚህ መረጃዎችና እውነታዎች ላይ ተመሥርቶ ጥልቀት ያለው ግምገማ በማካኼድ መተንተን ይኖርበታል (Kothari,,2004:3)፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ ይህ የምርምር ዓይነት የተመረጠው ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በዓይን እንደሚታዩ፣ በጆሮ እንደሚሰሙ አድርጎ በትንተና እና በገለጻ ለማቅረብ ስለሚያስችል ነው፡፡

4.2. የጥናቱ የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በመስክ ጥናት ቆይታዬ ወቅት የምፈልገውን መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎችን ሥርዓታዊና ተጠይቃዊ በኾኑ መንገዶች አማካይነት ውስን የኾኑ አካላትን በናሙናነት በመምረጥ

ለመጠቀም ችያለሁ። በመኾኑም ከየወረዳዎቹ በናሙናነት የተመረጡት አካላት በጥናቱ ክልል ውስጥ ባለው ማኅበረሰብ የሚዜሙትን የቃል ግጥሞች በመንገርና በክዋኔም ላይ በመሳተፍ ብቁ ችሎታ ይኖራቸዋል ተብለው የታሰቡ ግለሰቦች ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ በወረዳም ኾነ በዞን ደረጃ ካሉ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች መካከል ለሚጠናው ርእሰ ጉዳይ መረጃ ይኖራቸዋል የተባሉ ሰዎችም የጥናቱ ተሳታፊዎች ኾነዋል። በመኾኑም ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ከወሳኝ የናሙና ዘዴዎች መካከል የዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል። ምክንያቱም ይህ ዘዴ እነማን በጥናቱ ውስጥ ቢሳተፉ የምፈልገውን መረጃ አግኝቼ ዓላማዬን ለማሳካት እችላለሁ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አስችሎኛልና ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ጠቋሚ የናሙና ዘዴ ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህ የኾነበት ምክንያት ለጥናቱ አስፈላጊ የኾኑ መረጃዎችን አገኝባቸዋለሁ ብዬ ያሰብኳቸውን ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ለማግኘት አስቸጋሪ ኹኔታ አጋጥሞኝ ነበር። በዚህን ጊዜ ጠቋሚ ናሙናን ለመጠቀም ችያለሁ። በዚህ መሠረት በማጠናው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ዕውቀቱ ካለው ሰው መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ ካገኘሁ በኋላ እንደሱ ተመሳሳይ የኾነ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን እንዲጠቁመኝ አድርጌያለሁ። እንዲህ እንዲህ እያደረግሁ የምፈልገውን መረጃ አግኝቼ እስከምጨርስ ድረስ ከአንዱ ጠቋሚ ወደሌላው ተጠቋሚ የመዘዋወር ኺደቱን አከናውኛለሁ። በጥቆማው መሠረት ቀጣዮቹን ሰዎች አግኝቼ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።

በመኾኑም፡-

- ✓ ከደቡብ ወሎ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች መካከል የሥራ መደቡ የባህል ልማት ተጠሪ የኾነ አንድ ባለሙያ፣
- ✓ ከቦረና፣ ከወግዲና ከከለላ ወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች መካከል የሥራ መደባቸው የባህል ልማት ተጠሪ የኾኑና ከሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁለት ሴቶችና አንድ ወንድ በድምሩ ሦስት ባለሙያዎች በጥናቱ ተሳታፊዎች ኾነዋል።
- ✓ ከሦስቱም ወረዳዎች በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ በተመረጡ ሦስት ሦስት፣ በድምሩ በዘጠኝ ቀበሌዎች ውስጥ ከሚኖሩት የቃል ግጥም ከዋኞች ወይም ታዋቂ ዘፋኞች መካከል ዐሥራ ስድስቱ ሴቶችና ኻያ ዘጠኙ ወንዶች በድምሩ ዐርባ አምስት ሰዎች በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል። ከላይ በተከታታይ እንደቀረበው በአጠቃላይ ዐርባ ዘጠኝ

ሰዎች[18] በዓላማ ተኮርና በጥቆማ የናሙና ዘዴዎች ተመርጠው በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል። ከየወረዳዎቹ የተመረጡትን ሰዎች ቁጥር የወሰነው የመረጃዎች ድግግሞሽ በመታየቱ ነው። እነዚህ ተሳታፊዎች ከኹሉቱም ጾታዎች፣ ከተለያዩ የዕድሜ ክልሎችና የሃይማኖት ተከታዮች የተውጣጡ ናቸው። በሙያ ደረጃም በአብዛኛው አርሶ አደሮች ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞችና ጡረተኞች ናቸው። ስብጥሩ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ሰዎቹ በሕይወት ዘመናቸው ቃል ግጥሞችን እየከወኑ የኖሩ ናቸው ተብሎ ስለታሰበ ነው። ከዐርባ ዘጠኙ መረጃ ሰጪ አካላት መካከል ከአንድ ጊዜ በላይ መረጃዎችን የመሰብሰብ አጋጣሚ ተፈጥሯል። ይህም የኾነው የእርሻ፣ የአረም፣ የአጨዳና የውቂያ ተግባራት በተለያዩ ወቅቶች የተከናወኑ በመኾናቸው የተነሣ ነው።

ለዘጠኙ ቀበሌዎችም ኹለት ኹለት፣ በድምሩ ዐሥራ ስምንት ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎች ተሰማርተዋል። እነዚህ ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎች በ2012 ዓ.ም በወሎ ዩኒቨርሲቲ በማኅበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ ኮሌጅ የሦስተኛ ዓመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ይህ የኾነበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት በመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት “Introduction to Folklore” እና “Oral Literature” የተባሉትን ኮርሶች በተከታታይ ስለወሰዱ በመረጃ አሰባሰብ ኺደት ችግር አያጋጥማቸውም በሚል ዕሳቤ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስለመረጃ አሰባሰብ የግማሽ ቀን ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል። የሥልጠናውም ዋና ትኩረት በተለያዩ የግብርና ግብአቶች ውጤታማነት ማለትም በማዳበሪያ፣ በብስባሽ (Compost))፣ በፀረ ዐረም፣ በዕርከን ሥራ ላይ፣ በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በእርሻ፣ በዐረም፣ በዐጨዳ፣ በውቂያ ወቅቶች የሚነገሩትን፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች በልጃገረዶች የሚዘፈኑትን የቃል ግጥሞች ብቻ እንዲሰበስቡ ለማድረግ ነው። መረጃ ለመሰብሰብ የተሰማሩበት ወቅትም ቢኾን የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ዕረፍት በነበሩበት ጥር ወር 2012 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ነው።

4.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በምርምር ሥራ አገልግሎት ላይ የሚውሉ በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መኖራቸውን Kothari (2004፡7) ገልጸዋል። በዚህ ጥናትም ከፎክሎር ባሕርይ ጋር ሊስማሙ የሚችሉ የቤተ መጻሕፍትና የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮችን ለመጠቀም ተችሏል። Best (1981፡254)

[18] በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጡት ሰዎች የየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤቶች መረጃ ይሰጣሉ ብሎ ያስቀመጣቸውን ያካትታል።

በዓይነታዊ ምርምር ጽሑፋዊ ሰነዶች፣ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ዓይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደኾኑ አስረድተዋል። Dorson (1972፡465) ደግሞ አንድ የፎክሎር ሙያተኛ ለምርምሩ የሚያስፈልጉትን ቀዳማይ መረጃዎች ከመስክ፣ ከቤተ መዘክር እንዲሁም ከታተሙ ጽሑፎች ማግኘት እንደሚችል "The folklorist obtains his Primary data in three basic ways through fieldwork, from archieves & by way of printed sources" በማለት ገልጸዋል። በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀምኳቸው ዘዴዎች ካልኣይና ቀዳማይ ናቸው። እነሱንም እንደሚከተለው አብራራለሁ።

4.3.1. ካልኣይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በካልኣይ የመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ የሚችሉት በሀገር ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ባሉ የመንግሥት አካላት በኅትመት ላይ የዋሉ ጽሑፎች፣ በዓለማቀፍ ደረጃ በሚገኙ ድርጅቶች የታተሙ ጽሑፎች፣ ሙያዊ የኾኑ የምርምር ጆርናሎች፣ መጻሕፍት፣ ጋዜጣዎች፣ መጽሔቶች፣ በተለያዩ መስኮች በዩኒቨርሲቲዎችና በታወቁ ምሁራን የተዘጋጁ ዘገባዎች፣ የሕዝብ መዛግብትና ስታትስቲክስ፣ ታሪካዊ ሰነዶች፣ ጥናቱ በሚካኼድበት አካባቢ የተጻፉ ልቦለድ መጻሕፍት ካሉ፣ በሬዲዮም ኾነ በቴሌቪዥን የተላለፉ ፕሮግራሞች፣ በኅትመት ላይ ያልዋሉ ጽሑፎች መኾናቸውን Goldstein (1974፡38) እና Kothari (2004፡111) ገልጸዋል።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት እኔም ወደመስክ ከመውጣቱ በፊት በአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ውስጥ ካሉት ቤተ መጻሕፍት መካከል በኬኔዲ፣ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም እና በዲጂታል አብያተ መጻሕፍት በመገኘት ለሥራው ማካኼጃ የሚኾኑ የጽንሰ ሐሳብ መረጃዎችን ከተለያዩ መጻሕፍትና ከኢንተርኔት ለመሰብሰብ ችያለሁ። ጥናቱ ስለሚካኼድባቸው ወረዳዎች ማኅበረ ባህላዊ ዳራ በተመለከተ ከዞኑና ከየወረዳዎቹ ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል። ከእነዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባሉ በባህል ዕሴቶች ዘርፍ ሠራተኞች አማካይነት በተለያዩ አጋጣሚዎች የተሰበሰቡ የቃል ግጥሞችን በወረቀትና በ"Soft copy" ለማግኘት ችያለሁ።

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በቦረና ወረዳ፣ በቀያፈር ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ትብብር ተማሪዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩትን እና የሚከወኑትን የቃል ግጥሞች ከራሳቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጠይቀው በቤት ሥራ መልክ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ በተደረገው መሠረት የቃል ግጥሞችን ለማግኘት ተችሏል። እነዚህ በባህል ልማት ባለሙያዎችም ኾነ በተማሪዎች ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደ ካልኣይ

የመረጃ ምንጭ የሚቆጠሩ ናቸው። የቃል ግጥሞቹም ከይዘታቸው አኳያ በሌሎች የመረጃ ማሰባሰቢያ ምንጮች ከተገኙት መረጃዎች ጋር እየተዋሐዱ በየምድቡ ውስጥ ተካትተዋል።

አንድ ተመራማሪ ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን ከመጠቀሙ በፊት ታማኝነታቸውን፣ ለምርምር ሥራው ያላቸውን ተስማሚነት፣ ትክክለኛነታቸውን፣ ብቁ መኾናቸውን በማረጋገጡ ረገድ ከፍተኛ የኾነ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት Kothari (2004፡111) አስረድተዋል። በዚህ መሠረት ከላይ ከተዘረዘሩት ምንጮች መካከል ለእኔ ጥናት ይበጁኛል ያልኳቸውን መረጃዎች በመምረጡ በኩል ጥንቃቄ ለማድረግ ሞክሬያለሁ።

4.3.2. ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ከ1960ዎቹ በኋላ እንደ Goldstein (1974)፣ Jackson (1987)፣ Donald (1972) እና Fukuta (1987) ባሉ ምሁራን አስተሳሰብ የሥነ ቃል ዘውጎች ያሏቸውን ተግባራት ለማጥናት ያለ መስክ ሥራ ፈጽሞ ሊኾን አይችልም። በተለይ Fukuta (1987:94) የመስክ ሥራ ለፎክሎር ጥናት አስፈላጊ ብቻ ሳይኾን ግዴታም እንደኾነ ገልጸዋል። ይህም ሲባል ከመስክ ላይ መረጃ መቅደም አለበት ለማለት ነው። መረጃውም ከአንድ አካባቢ ሲሰበሰብ ያንን መረጃ እየተጠቀሙበት የሚገኙት ማኅበረሰቦች ካላቸው ውስጣዊ አመለካከት (Emic Approach) አኳያ መኾን እንዳለበት Green (1997፡215) በአጽንዖት አስረድተዋል። ለዚህ ጥናትም መረጃዎች በተሰበሰቡበት ወቅት የባህሉ ባለቤት የኾነው ማኅበረሰብ ባህሉንና ራሱን ከሚገልጽበት አንጻር ስለነበር ውስጣዊ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል።

ይህ ጥናት መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡበትና ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ በመኾኑ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት የተጠቀምኳቸው ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። እነዚህን የመረጃ ምንጮች በሚከተለው ኹኔታ በቅደም ተከተል ለማብራራት ተችሏል።

4.3.2.1. ምልከታ

ምልከታ መረጃ ሰብሳቢው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በመኾን እነሱ የሚያደርጉትን እና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ኾኖ እያየና እየሰማ፣ ከዚያም በላይ ደግሞ እየተሳተፈ በመመዝገብ መረጃዎችን የሚሰበስብበት ዘዴ እንደኾነ ይታወቃል። በዚህ መሠረት ክዋኔ በሚኖርበት ወቅት ወዲያው በዐውዱ ላይ በመገኘት ምልከታን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባም Bauman (1977:213) ገልጸዋል። ምልከታውም ታቅዶበት የሚሠራ ከኾነ ለአንድ ተመራማሪ ሳይንሳዊ የኾነ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መኾኑ የተረጋገጠ ነው

(Kothari, 2004፡96)፡፡ ምክንያቱም የሚጠናውን ጉዳይ ተጨባጭ በሆነ ኹኔታና በተፈጥሯዊ መልክ አዳምጦና ተመልክቶ ለመመዝገብ ያስችላልና ነው፡፡ ይህ ደግሞ መረጃውን ከአድልዎ የጸዳ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በምልከታ የተጠያቂዎቹን ምላሽ ለማግኘት ደጅ መጥናት ስለማያስፈልግ ከቃለ መጠይቅ የተሻለ ጠቀሜታ እንዳለውም Kothari አስረድተዋል፡፡

በእርግጥ ምልከታ የሚለው ቃል በሚታዩ ነገሮች ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ማዳመጥን፣ መዳሰስን፣ ማሽተትን እና መቅመስን ያካትታል፡፡ እኔም በመስክ ቆይታዬ ወቅት በተፈጥሯዊ ዐውድ መረጃዎችን ስሰበስብ የምፈልጋቸው መረጃ ሰጪዎች የሚያደርጉትን ድርጊትና የሚናገሩትን ነገር በጋራ አከናውኛለሁ፡፡ በቅርበትም እያየሁና እየሰማሁ በማስታወሻ ደብተር መዝግቤያለሁ፡፡ በድምፅና በምስል መቅረጫ መሣሪያዎችም መረጃዎችን ይዣለሁ፡፡

ምልከታ ተሳትፏዊ፣ ኢ-ተሳትፏዊና ድብቅ (Covert) ተብሎ በሦስት ዓይነቶች እንደሚከፈል የሚታወቅ ነው (Flick, 2006:216)፡፡ ከእነዚህ መካከል ድብቅ የተባለው የምልከታ ዘዴ በስውር መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ የሚያገለግል መኾኑ ይታወቃል፡፡ ከሥነ ምግባር መርሕ አንጻር ይህ ዓይነቱ መንገድ የመረጃ ሰጪዎቹ ፈቃደኝነት ስለማይስተዋልበት በእኔ ጥናት ተግባር ላይ አልዋለም፡፡ የተሳትፏዊ ምልከታ ዘዴ ክዋኔን ለመገንዘብ ጠቀሜታ ያለው ቢኾንም ማስታወሻ ለመያዝና በተለያዩ መሣሪያዎች ድርጊቶችን ለመቅረጽ አያስችልም፡፡ ኢ-ተሳትፏዊ ዘዴ ግን ማስታወሻ ለመያዝ፣ በመቅረጸ ድምፅ ለመቅዳትና ፎቶግራፍ ለማንሣት የሚያስችል ዘዴ በመኾኑ ጽሞናዊነት ይኖረዋል፡፡ በመኾኑም በዚህ የምርምር ሥራ ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ የምልከታ ዓይነቶችን እንዳስፈላጊነታቸው ተግባራዊ በማድረግ መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

በተሳትፏዊም ኾነ በኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ የተካኼዱ ተግባራትን በተመለከተ ከ04 — 08/11/2012 ዓ.ም ድረስ በነበረው የእርሻና የሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ብተና ወቅት በከለላ፣ በወግዲና በቦረና ወረዳዎች 8 ጊዜ ምልከታዎች ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ የምልከታ ጊዜያት አርሶ አደሮቹ የሙገሳ፣ የትችት፣ የቁጭት፣ የተማጽኖ፣ የብሶት ቃላዊ ግጥሞችን ሲያዜሙ አዳምጫቸዋለሁ፡፡ በ06/01/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳና በ08/01/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ በነበረው ምልከታ በዐረም የማረም ተግባር ላይ በ4 ማሳዎች የተሰለፉ ወጣቶች ሙገሳን፣ ትችትን፣ የጠንክሮ መሥራትን ተገቢነት የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞችን አቀንቅነዋል፡፡ በ22/04/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳና በ23/04/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ 2 ጊዜ የዐጨዳ ተግባራትን ተመልክቻለሁ፡፡ በእነዚህ የምልከታ ወቅቶችም የሙገሳ ቃል ግጥሞች ተዚመዋል፡፡

በ01 እና በ02/06/2012 ዓ.ም በቦረና ወረዳ 2 የዕርከን ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅትም ምልከታ አካኺጃለሁ፡፡ በዕርከን ሥራዎቹ ወቅትም የሙገሳ ቃል ግጥሞች ሲዜሙ ለማዳመጥ ችያለሁ፡፡ በ19 እና በ20/05/2012 ዓ.ም በቦረና ወረዳ 3 የውቂያ ተግባራትን ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ ወቅት የሙገሳ ቃል ግጥሞች ተቀንቅነዋል፡፡ በ07 እና በ21/06/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ፣ እንደዚሁም በ10 እና በ14/07/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ 4 የሰርግ ሥርዓቶችን በአካል ተገኝቼ ተከታትያለሁ፡፡ ውበትን የሚያደንቁ፣ የጠይም ሰው ፍቅርን ኃያልነት የሚገልጹና ነገረኛ ሰውን የሚተቹ ቃል ግጥሞችን ለማዳመጥ ችያለሁ፡፡ በዝርዝር በቀረቡት የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች በጠቅላላው 22 ምልከታዎችን አካኺጃለሁ፡፡

በዚህ መሠረት ከአርሶ አደሩ ማኅበረሰብ ሕይወት ጋር የተያያዙትን የሥራ ግጥሞች ለመሰብሰብ ወቅቶችን መጠበቅ ስለነበረብኝ በየወረዳዎቹ በአኺዶ (በውቂያ)፣ ዐውድማ ላይ በነፋስ አማካይነት ምርቱ ከገለባ በሚለይበት፣ በእርሻ፣ በዐረም፣ በዐጨዳ፣ በዕርከን ሥራ ዐውዶች፣ እንደዚሁም በሰርግ ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ በመገኘት ተሳትፏዊ ምልከታ አካኺጃለሁ፡፡ በተለይም ውቂያው ሲገባደድ የእኽሉ ባለቤት ያዘጋጀውን አግማስ ተጋብዤ በልቻለሁ፣ ጠጥቻለሁ፡፡ ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ከዐውድማ ላይ ምርቱ እየተሰፈረ ወደጎተራ ከመግባቱ በፊት የቀረበውን አግማስ በመመገብ ተሳትፌያለሁ፡፡ ማኅበረሰቡ አግማስ ብሎ የሚጠራው እኽል በዐውድማ ላይ በሚወቃበትና በመጨረሻም ምርቱ እየተሰፈረ ወደቤት ከመግባቱ በፊት በጉልበት ሥራው ለተሳተፉትና በአቅራቢያ ላሉት ልጆችም ጭምር የሚቀርብ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ነው፡፡ ፋይዳውም በሥራ ተጠምዶ የዋለ ሰው በጋራ መብላትና መጠጣት ከአባት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ስለኾነ ፍቅርን፣ መተሳሰብን ያጎለብታል፤ ምርቱም ይጨምራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አግማሱ በሚበላበትና በሚጠጣበት ወቅትም በዕድሜ ያለውን ማኅበራዊ ደረጃ (ሽማግሌ፣ ወጣት፣ ሕፃን) የተከተለ መኾኑን በምልከታዬ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

በተሳትፏዊ ምልከታ ይህ ሁሉ የኾነው በእኔና በማኅበረሰቡ አባላት መካከል የጋራ የኾነ የመግባቢያ ቋንቋ ስለነበረን ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ኺደቶች የተካኼደው ምልከታም የተሳካ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን እውነታ የበለጠ የሚያጠናክረው ደግሞ ምልከታና ቃለ መጠይቅ አድርጌ ስጨርስ መልካም ምኞትን የሚያንጸባርቁ ምርቃቶችን መመረቄ ነበር፡፡ ለማስረጃም ከላይ በነበረው ዐውድ አቶ ሱለይማን ኢብራሂም የተባሉ መረጃ ሰጪ “ይሄ

የሰጠንህ ግጥም ፈጣሪ መጠቀሚያ ያድርግልህ፤ አላህ ይግጠምህ" በማለት መርቀውኛል። በተለያዩ ቦታዎች ባካኼድኩት ምልከታም የማኅበረሰቡ አባላት የየዕለት ተራክቧቸውን የሚጀምሩትና የሚጨርሱት በምርቃን እንደኾነ ለማረጋገጥ ችያለሁ። በኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ወቅት ደግሞ በዐውዱ ላይ ያለውን የአካል እንቅስቃሴ ዓይነት፣ የድምፅ አወጣጥ ኹኔታ፣ ማጀቢያዎችን፣ ወዘተ. ለመከታተል ጥረት ተደርጓል።



ፎቶግራፍ ኹለት፡- በ20/05/2012 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ቀያፈር (35) በተባለው ቀበሌ ከዐውድማ ላይ ምርቱ እየተሰፈረ ወደጎተራ ከመግባቱ በፊት የቀረበውን አግማስ በጋራ በመመገብ ላይ እያለን።

ቀደም ሲል ምልከታ ወሳኝ የመረጃ ምንጭ እንደኾነ የተገለጸ ቢኾንም በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ካልተደገፉ በስተቀር የተሟላ መረጃዎችን ማግኘት ስለማይቻል ቃለ መጠይቅም በሚከተለው ኹኔታ ተግባር ላይ ውሏል።

4.3.2.2. ቃለ መጠይቅ

በዓይነታዊ ዘዴ ለሚካኼደው ምርምር መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ አንደኛው ዘዴ መኾኑ የታወቀ ነው። ዓለም እሸቱም (1992፡65) ቃለ መጠይቅ በብልሃት ከተያዘና ተግባር ላይ ከዋለ መረጃን ከዋናው ከምንጩ ለመሰብሰብ የሚያስችል አንዱ የጥናት መንገድ እንደኾነ ገልጸዋል። ስለዚህ ቃለ መጠይቅ በመስክ ሥራ ወቅት አስተማማኝነት ያለው መረጃን ሰብስቦ ለማጠናቀር ያስችላል ማለት ነው። በዚህ መሠረት መረጃዎች በምልከታ በሚሰበሰቡበት ወቅት ይስተዋሉ የነበሩትን ክፍተቶች ለመሙላት ወሳኝነት ያላቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅቼ ከደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ ከሦስቱም ወረዳዎችና ከየቀበሌዎቹ በናሙናነት ለተመረጡት 49 መረጃ ሰጭዎች ሦስት ዓይነት የቃለ መጠይቅ መንገዶችን ተጠቅሜ አቅርቤያለሁ።

ከእነዚህ መንገዶች መካከል አንደኛው አስቀድሞ የተወሰነ ቃለ መጠይቅ (Structured Interview) የሚባለው ነው። ይህም ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ጥያቄዎችን አስቀድሞ በማዘጋጀት ለመረጃ ሰጭዎች ለማቅረብ የሚያስችል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተመራማሪው ለመላሾቹ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች የምፈልጋቸውን መረጃዎች ላገኝባቸው እችላለሁ ብሎ የሚያስባቸውና በቅድሚያ ከተጻፉት ውጭ የማይጨመርባቸው ናቸው (Vanderstoep and Johnston, 2009: 225) እና (Fife, 2005፡93):: በምሁራኑ ሐሳብ መሠረት ለዚህ ጥናት ዓላማ ግብ መምታት አስፈላጊ ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ጥያቄዎች አስቀድሜ በማዘጋጀት በናሙናነት ለተመረጡት መረጃ ሰጪዎች በቅደም ተከተል አቅርቤያለሁ። በዚህ መንገድ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች መካከልም የተወሰኑት ዝግ የኾነ የአጠያየቅ ቅርጽን የተከተሉ ናቸው። በዚህም ጥናቱ በሚካኼድባቸው ወረዳዎች ያለው የኅብረተሰብ ክፍል የሚከተለው ሃይማኖት የክርስትና ነው ወይስ የእስልምና? ቃል ግጥሞች በአብዛኛው መቼ መቼ ነው የሚከወኑት? በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በግብርና ሥራ ወቅቶች፣ ወዘተ.፣ በልጃገረዶች የሚዜሙት ዘፈኖች በግል ነው ወይስ በቡድን? የሚሉት ዝግ ጥያቄዎች ለተጠያቂዎች ቀርበው አስፈላጊ የኾኑ መረጃዎች ተገኝተዋል።

በኹለተኛ ደረጃ ደግሞ በከፊል የተቀናበረ (Semi-Structured Interview) የተባለው የቃለ መጠይቅ ዓይነት ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ውሏል። ምክንያቱም የተወሰኑ ጥያቄዎችን ክፍት በኾነ መልኩ አዘጋጅቼ ለመረጃ ሰጭዎቼ ባቀረብኩበት ወቅት ከእነሱ የሚመጡ አዳዲስ ሐሳቦችን እንዳገኝ ረድቶኛል። ከዚህ በመነሣትም ሌሎች አዳዲስና ተጨማሪ ጥያቄዎችን እያነሣሁ በመጠየቅ መረጃዎችን ለማግኘት አስችሎኛል። እንዲህ በሚኾንበት ወቅት በቅደም ተከተል ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄዎች በማዘበራረቅ በሚመቸኝ መንገድ አቅርቤያለሁ። በዚህ

መሠረት “ተበቺሳ” ማለት ምን ማለት ነው? ብዬ በጠየቅሁበት ወቅት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ብያኔውን ከገለጹልኝ በኋላ በዚሁ ጥያቄ መነሻነት እንዴት እንደሚከወንም በዝርዝር አስረድተውኛል። ከዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥሞቹ በሚቀርቡባቸው አጋጣሚዎች፣ እንደዚሁም በግጥሞቹ ላይ የታየውን ለውጥና እንዳለ እስካሁን የቀጠለውን ኹኔታ ቢነግሩኝ የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡

ሦስተኛው ደግሞ ነጻ /Unstructured interview/ የተባለው የቃለ መጠይቅ ዓይነት ሲኾን፣ ግትርነት የማይታይበትና ነጻነትን ለመላሹ የሚሰጥ ዘዴ ነው። ተመራማሪውም ቢኾን በሚያጠናው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ጠቃሚ መረጃ ያስገኙልኛል ያላቸውን ጥያቄዎች ባስፈለገውና ለተጠያቂው ይመቻል ብሎ ባሰበው መንገድ ማቅረብ የሚችልበት፣ ተጠያቂዎች ደግሞ መልስ ይኾናሉ ብለው የሚገምቷቸውን እና ያመኑባቸውን መረጃዎች በነጻነት የሚሰጡበት ነው። ከዚህም ሌላ ተመራማሪው ከተጠያቂዎች ጋር በሚያደርገው ውይይት ጥያቄዎችን እያነሣ ማብራሪያ እየጠየቀ መረጃ ይሰበስባል። ስለዚህ በዚህ ዘዴ ጠያቂም እንደችሎታው ጥያቄዎችን ከአእምሮው እያፈለቀ የመጠየቅ፣ ተጠያቂዎችም ያላቸውን አስተያየት፣ አመለካከትና ዝንባሌ ወዘተ. የመግለጽ ነጻነት አላቸው። በዚህ የተነሣ በርካታና ጥልቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይቻላል (ያለው፣ 1998፡185)። እኔም በናሙናነት ከተመረጡት መረጃ ሰጪዎች ጋር ውይይት ባካኼድኩበት ወቅት የማኅበረሰቡ አባላት ማኅበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው? እስኪ እርስዎ ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ግብዓቶችን፣ የእርሻ ተግባራትን፣ በተበቺሳ ወቅት በልጃገረዶች የሚዜሙትን እና በጎረምሳዎች ሆታ ወቅት የሚቀርቡትን፣ እንደዚሁም በለቅሶ ሥርዓት ጊዜ በሙሾ የሚደረደሩትን ግጥሞች ቢነግሩኝ? የሚሉትን እና ለጥናቱ የሚረዱና ክፍት የኾኑ ጥያቄዎችን እያነሣሁ፤ ተጠያቂዎቹም ቢኾኑ ያለ ምንም ገደብ ምላሻቸውን በነጻነት እየሰጡ አስፈላጊ ናቸው ያልኳቸውን መረጃዎች ሰብስቤያለሁ።

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች የቀረቡት ጥያቄዎች በአብዛኛው ማን? እንዴት? ምን (ምንድን)? ምንን? ከምን? መቼ? የት? ወዘተ. የሚሉትን መጠይቃዊ ቃላት የያዙ ናቸው። ሦስቱም የቃለ መጠይቅ አይነቶች የተካኼዱት ከጥር 19/ 2012 ዓ.ም እስከ መጋቢት 05/2012 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ቢሮዎች፣ መኖሪያ ቤቶችና አካባቢዎች ሲኾን፣ እንደ አስፈላጊነቱም የተለያዩ የግብርና ሥራዎችና የሕይወት ሽግግሮሽ በሚካኼዱበት ወቅት የቃለ መጠይቁ ተግባር የተከናወነ መኾኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ። ከላይ ከተጠቀሱት ጊዜያት በተጨማሪ መረጃዎች በምልከታ

በሚሰበሰቡበትም ወቅት ይስተዋሉ የነበሩትን ክፍተቶች ለመሙላት ወሳኝነት ያላቸው ጥያቄዎች ለመረጃ ሰጪዎች ቀርበዋል።

4.3.2.3. ቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት ሲባል የጥናቱን ርእሰ ጉዳይ አስመልክቶ ለሚነሡት ሐሳቦች በተመራማሪውና በግለሰቦች መካከል የጋራ ውይይት የሚካሄድበት ነው (Perecman and Curran,2006:104)። በመሆኑም በእኔ ጥናት ውስጥ የቡድን ተኮር ውይይቱ ዋና ትኩረት በምልከታና በቃለ መጠይቅ የማይገኙትን መረጃዎች ለማሟላት ነው። በቡድን ተኮር ውይይቱ ወቅት የሚሳተፉ አባላትን ብዛት በተመለከተ Marshal and Rossman (2006:114) በዝቅተኛ ደረጃ አራት እንደሚኾኑ፣ ከፍተኛው ደግሞ ከዐሥራ ኹለት እንደማይበልጡ፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን ከሰባት እስከ ዐሥር እንደሚደርሱ ገልጸዋል። በእዚህ ጥናት በሦስቱም ወረዳዎች በተካሄዱት ውይይቶች አምስት አምስት በድምሩ ዐሥራ አምስት መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮርና በጠቋሚ የናሙና ዘዴዎች ተመርጠው በቡድን ውይይቱ እንዲሳተፉ ተደርገዋል። ምንም እንኳን በቡድን ውይይቱ አባላት መካከል የጾታ ስብጥር መኖር አስፈላጊ መኾኑን ባምንበትም መረጃ አገኝባቸዋለሁ ብዬ ያሰብኳቸው ሴቶች ከወንዶች ጋር አብረው ተቀምጠው ውይይት ለማካሄድ ፈቃደኛ አልኾኑልኝም፤ ለማስገደድም አልቻልኩም።

በቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ሰዎች አብዛኛዎቹ በቃለ መጠይቁ ወቅት መረጃ ያልሰጡ ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በቃለ መጠይቅ ወቅት አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ተቃራኒ የኾነ መረጃ ሲሰጡ የተስተዋለበት አጋጣሚ ስለነበር እንደነዚህ ያሉ ርእሰ ጉዳዮችን አጣርቶ ሚዛናዊ የኾነ መረጃ ለማግኘት ሲባል ቀደም ሲል በተካሄደው ቃለ መጠይቅ መረጃ የሰጡ ሰዎች በቡድን ውይይቱ ወቅት እንዲሳተፉ አልተደረጉም። የተወሰኑት የውይይቱ ተሳታፊዎች ግን በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኙ ናቸው። ይህ መንገድ ደግሞ በቂ የኾኑ መረጃዎችን ለማግኘትና በቡድን ውይይቱ ወቅት ለቀረቡት ጥያቄዎች የሞቀ የሐሳብ ልውውጥ ለማድረግ አስችሏል።

ቡድን ተኮር ውይይቱ በመስከረም 09/ 2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ፣ መካነ ሰላም ከተማ በመቶ አለቃ ሰይድ ሀሰን ቤት 1 ጊዜ፣ በመስከረም 07/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ በሰቀ ሽንብራ አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ ባለ መኖሪያ ቤት 1 ጊዜና በመስከረም 05/2013 ዓ.ም በከለላ ወረዳ ከለላ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት 1 ጊዜ ብቻ በጠቅላላው ለሦስት ጊዜያት ተካሂዷል። በዚህ ኺደትም በሚጠናው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ የኾነ መረጃ ይኖራቸዋል ተብለው ለታሰቡ ሰዎች የተለያዩ የመነሻ ሐሳቦች ለውይይት

ቀርበውላቸዋል። እነሱም በየቡድናቸው እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል። በዚህን ጊዜ የእኔ ተግባር የውይይቱ መሪ (Moderator) ሾኜ ኺደቱን ከመምራትና የመወያያ ሐሳቦችን ከማቅረብ፣ ማስታወሻ ከመያዝና በድምፅ መቅጃ ከመቅዳት ውጭ ሚናዬ የተገደበ ነበር። በመሆኑም በውይይቱ ወቅት ከተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች በናሙናነት የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች ቃላዊ ግጥሞቹ መቼ መቼ እንደሚከወኑና ምን ምን ፋይዳ እንዳላቸው፣ እንደዚሁም በቃላዊ ግጥሞቹ ላይ እየታየ ያለውን ለውጥና ቀጣይነት፣ ወዘተ. እንዲገልጹ ተደርጓል። እዚህ ላይ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎች ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ የተወሰኑትን በየቡድን ውይይቱ ዳግም በማንሣት እውነትነታቸውን ለማጣራት ተችሏል።

4.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተብለው የሚዘረዘሩት ማስታወሻ ደብተር፣ ብዕር፣ ፎቶና ቪዲዮ ካሜራዎች፣ መቅረጸ ድምፆች ናቸው። ለአንድ ጥናት የሚሾኑ መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ መሟላት ያለባቸው አቅርቦቶች (Logistics) ብለው Schensul (1999፡6) የጠቀሷቸው የምስልና የድምፅ መቅረጫ መሣሪያዎች፣ የመስክ የማስታወሻ ደብተር፣ ወዘተ. ናቸው። Best ደግሞ (1981:258) “The preferred method for data collection is to tape record the interview if the respondent is willing.” በማለት ገልጸዋል። በዚህ ጥናትም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎችን ከመስክ ለመሰብሰብ ከላይ የተዘረዘሩት መሣሪያዎች በአገልግሎት ላይ ውለዋል።

በተጨማሪ በካልኣይ የመረጃ ምንጮች፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ እንደዚሁም በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙትን መረጃዎች በማስታወሻ ደብተር ለመጻፍ ተችሏል። በምልከታ ወቅት ደግሞ የአንድን ድርጊት ክዋኔ ወይም ኹነት ከነመቼቱ ለመቅረጽ የድምጽና የምስል መቅረጫ መሣሪያዎች ዋናውን ቦታ ይዘዋል። በቃለ መጠይቅ ወቅትም ከማስታወሻ ደብተር በተጨማሪ መቅረጸ ድምፅ አገልግሎት ላይ ውሏል።

በቃለ መጠይቅም ኾነ በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙት መረጃዎች በመቅረጸ ድምፅ እንደሚያዙ ቀደም ሲል ተገልጿል። እነዚህን መረጃዎች በተገቢው መንገድ ለመተንተን ደግሞ ወደ ጽሑፋዊ ቅንብር መቀየር ግዴታ ነው የሚኾነው። ይህ ተግባር በተለያዩ መንገዶች ሊከናወን ይችላል። አንደኛው ሙሉ በሙሉ የመገልበጥ ተግባር ነው። ይህ ዓይነቱ ጽሑፋዊ ቅንብር ከፍተኛ የኾነ ጉልበትን እና ጊዜን ከማባከኑ በስተቀር ሁሉንም ቃላዊ የኾኑ መረጃዎችን ጥልቀት ባለው ኹኔታ ለመሰነድ ይጠቅማል። በዚህን ወቅት የሰውነት እንቅስቃሴዎችን፣ የፊት ገጽታዎችን እና የመሳሰሉትን ቃል አልባ ድርጊቶች ከፎቶዎች ጋር እያዋደዱ ማቀናበር ያስፈልጋል

(Schensul,1999፡18)። ኹለተኛው ደግሞ ለምርምር ጥያቄዎቹ ተገቢ የኾኑትን ብቻ መርጦ (Transcribing Selected Segments) ወደጽሑፋዊ ቅንብር መለወጥ ማለት ነው። በዚህ መንገድ ግን ሁሉንም መረጃዎች በቀላሉ ለማግኘት አስቸጋሪ ነው የሚኾነው። በመኾኑም በእኔ የምርምር ሥራ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ የመገልበጥ ተግባር ከተካኼደባቸው በኋላ በጭብጥና በዐውድ ተኮር ተተንትነዋል ።

4.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዐውዶች

Goldstein (1974፡80) ከመስክ የምርምር መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ መቼቶችን ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሠራሽና ቅንብር ተፈጥሯዊ በሚባሉ ዘርፎች በመከፋፈል ሰፊ የኾነ ማብራሪያ ሰጥተዋል። እነዚህንም በሚከተለው ኹኔታ በአጭር በአጭሩ ለማብራራት ተችሏል።

ተፈጥሯዊ መቼት፡- ተፈጥሯዊ መቼት የሚባለው የሥነ ቃል ዘርፉ በተለምዶም ኾነ በሀገረሰብ ባህል የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ነው ማለት ነው (ፈቃደ፣1991፡122)። በዚህ ዓይነቱ መቼት ፎክሎራዊ መረጃዎችን ከመሰክ መሰብሰብ መቻል ለተመራማሪው ሥራ ትክክለኛና /Authentic/ የተሟላ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ጥሩ አጋጣሚ እንደኾነ የሚታወቅ ነው። መረጃ ከመስክ ሲሰበሰብ ለአመቺነቱ ሲባል ተፈጥሯዊ መቼት በከፍተኛ ኹኔታ የሚጠበቅ፣ በከፊል የሚጠበቅና በአጋጣሚ የሚከሠት በማለት Goldstein (1974፡81) መድበዋል።

እንደ Goldstein ማብራሪያ በከፍተኛ ኹኔታ የሚጠበቅ ከሚባሉት መካከል አንደኛው በሚገባ የተዘጋጀና የተቀናበረ፣ በባህሉ ባለቤቶች ዘንድ አስፈላጊ የኾነና አንዳንድ ጊዜም የታቀደ መቼት ሲኾን፣ በዚህ ሥር ተካትተው ከሚከናወኑት ተግባራት የመጀመሪያው የሰውን ልጅ የሕይወት ሽግግር የሚመለከቱ እንደወሊድ፣ ክርስትና፣ ጋብቻና ሞት ያሉ ሥርዓቶች ናቸው። እነዚህም የቦታን፣ የኹኔታን፣ የማኅበራዊ ደረጃን እና የዕድሜ ለውጥን ያስከትላሉ።

በኹለተኛው ደረጃ የተቀመጡት ደግሞ Calendar Customs ተብለው በዓመት ውስጥ ጊዜና ቦታ የተወሰነላቸው ናቸው። የአዲስ ዓመት የዘመን መለወጫ፣ መስቀል፣ ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ መውሊድ፣ አረፋና የመሳሰሉት ክዋኔዎች በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። በአጭሩ በባህሉ ውስጥ የተፈጠሩ፣ ቀን የተቆረጠላቸው፣ ቦታው የተለየ፣ አስቀድሞ የታሰበባቸው ናቸው ማለት ነው። በዚህ መሠረት ይህ ዓይነቱ ዐውድ ለክዋኔያዊ ጥናት አስፈላጊ ጽንሰ ሐሳብ መኾኑን Hufford (1995:531) ገልጸዋል።

በከፊል የሚጠበቁ የሚባሉት ያን ያክልም በቋሚነት የሚቀርቡ ላይኾኑ ይችላሉ። ለአብነትም ልጆች ወደመኝታቸው ከመኼዳቸው በፊት ወላጆች የሚተርቱላቸው ተረቶች፣ አዕምሮን

ለማጎልበትና ዓላማ ላለው ትምህርት ሲባል አባት ለልጁ የሚያቀርባቸው እንቆቅልሾች፣ በእርሻ ወይም በከብት ጥበቃ ወቅት ለአራሾችና ለእረኞች ልምድ ለማካፈል የሚቀርቡ ጨዋታዎች፣ ተረኮችና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ (Goldstein,1974፡81)።

በእርግጥ በሚጠናው ማኅበረሰብ ውስጥ ከዋኙ ተረት እንዲተርት፣ እንቆቅልሽ እንዲናገር፣ ቃል ግጥም እንዲገጥም የሚደረገው፣ የሚገፋፋው፣ የሚቀሰቀሰው በምን ዘዴ ነው? የተረት፣ የእንቆቅልሽ ... ማቅረቢያ ጊዜስ አለ ወይ? እነዚህ ነገሮች በሚከወኑበት ወቅት ሌላ ዐብረው የሚደረጉ ነገሮች አሉ? የተለያዩ የክወና ስልቶች (የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች፣ የድምፅ መለዋወጥ) አሉ ወይ? የአድማጮች ሚና ምንድን ነው? የሚሉትን የጥያቄ ዓይነቶች መረጃ ሰብሳቢው ይዞ በተግባር መተርጎም ይኖርበታል (ፈቃደ፣1991፣125 -127)።

ተመራማሪው እንደነዚህ ያሉትን መረጃዎች በሚሰበስብበት ወቅት የከዋኙን፣ የታዳሚውንና የራሱን ስሜት፣ የታዳሚውን ግብረ መልስ፣ የከዋኙንና የታዳሚውን የሰውነት እንቅስቃሴ፣ ስሜታዊ ገለጻ (ሳቅ፣ ለቅሶ፣ እልልታ ጩኸት፣ ወዘተ.) የፊት ገጽታ መቀያየር የመሳሰሉትን ትኩረት ሰጥቶ መከታተል ይኖርበታል። ምክንያቱም እነዚህ ኹነቶች የማኅበረሰቡን የዓለም እይታ፣ ባህል፣ ሕግ፣ ዕሴት፣ ወዘተ. የሚያሳዩ ግብዓቶች ናቸው (ሰሎሞን፣2007፣49)። እነዚህን ማኅበራዊ ኹነቶች በአብዛኛው በመቅረጸ ድምፅ ብቻ ቀድቶ በቀላሉ መረጃ መሰብሰብ አዳጋች ነው። በመኾኑም አጥኚው ኹነቶቹን በንቃት ተከታትሎ በማስታወሻ ደብተሩና በሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችም መረጃውን መመዝገብ ይኖርበታል።

Goldstein (1974፡81) በአጋጣሚ የሚከሠተው ተፈጥሯዊ ዐውድ የፎክሎር ዘርፉ እንዳጋጣሚ ወይም ሳይታሰብበት ድንገት እንዳመጣ የሚከወን ነው ብለውታል። ይህ ማለት እንዲህ ይኾናል፤ ይደረጋል ተብሎ በዕቅድ ያልተያዘ ማለት ነው። ለምሳሌ ሰዎች ለርእሰ ጉዳያቸው ማንጸሪያ በጨዋታቸው መካከል ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ወይም እንደየጸታቸው ሥራዎችን ሲሠሩ ዐብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች ተረት ሊተረትላቸው፣ ቀልድ ሊወራላቸው፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሊነገራቸው ይችላል።

ሰው ሠራሽ መቼት፡- በዚህ የመቼት ዓይነት ሥነ ቃሉ የሚከወነው አጥኚው መረጃ ያስፈልገኛል ብሎ ሲያስብ በራሱ ተነሣሽነት የሚፈጽመው ነው Goldstein (1974፡82)። ፈቃደ (1991፣123) ደግሞ ሰው ሠራሽ መቼት በኹለት ዓይነት መንገዶች ተግባር ላይ መዋል እንዳለበት ያስገነዝባሉ። አንደኛው “ከዚህ በፊት ይከወን የነበረ፣ ዛሬ ግን የሌለን ሥነ ቃል እንዲህ ነበር እያሉ፣ እያስታወሱ በታሪክነት ለመቅረስ የሚከወንበት መቼት ነው።” ኹለተኛው

ደግሞ “አንድን ሥነ ቃል ከዐውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ ሰጪ በተገኘበት ጊዜና ቦታ ተመራማሪው የሥነ ቃል መረጃውን የሚሰበስብበት መቼት ነው።” በማለት ገልጸዋል።

ሰው ሠራሽ መቼቱ በጥንቃቄ ካልተያዘ የሚከወነው የፎክሎር ዓይነት ለይምሰል ሊኾን ይችላል። ምክንያቱም በተፈጥሯዊ መቼት የክዋኔው ተሳታፊዎች ሳይሸማቀቁና ኀፍረት ሳይሰማቸው በድፍረት የሚፈለገውን ነገር መከወን ሲችሉ በሰው ሰራሽ ግን ኀፍረት ሊሰማቸው ይችላል። በተለይ ደግሞ የመረጃ ሰብሳቢው ጣልቃ ገብነት የክዋኔውን ተሳታፊዎች በተወሰነ መልኩ የኀፍረት ስሜት እንዲሰማቸው ሊያደርግ ስለሚችል የፎክሎር ዐውዱን ሊቀይረው ይችላል።

በሰው ሠራሽ መቼት ዋና ዋና የሚባሉ ውስንነቶች መኖራቸውን Goldstein (1974:85) ይገልጻሉ። ይሄውም የተወሰኑ የክዋኔ ዓይነቶች በሰው ሠራሽ ዐውድ በማስመሰል ሲሠሩ የተሳታፊዎች፣ የተራኪዎች፣ የዘፋኞችና የዘማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ በሚኾንበት ወቅት የቤተሰብ አባላትም ኾኑ ሌሎች ሰዎች እንዲካተቱ ሊደረግ ይችላል። በዚህን ጊዜ የተፈለገው መረጃ በበቂ ኹኔታ ሊገኝ አይችልም ተብሎ ይታሰባል።

በሰው ሠራሽ መቼት መረጃውን በምልከታ ለሚሰበስበው ሰው ሌላው ትልቁ ውስንነት የሚፈለገው ነገር ተጋንኖ መከወኑ ብቻ ሳይኾን በማስመሰል ድርጊቱ ሲፈጸም ሰዎች ካላቸው ባሕርይ አንጻር አስመስለው መሥራት አለመቻላቸውም ጭምር ነው። ብዙዎቹ ባህላዊ ከዋኞች በተፈጥሯቸው ከእውነተኛው ወይም ከዋናው ዐውድ ውጭ ለመከወን ፍላጎት አይኖራቸውም። በመረጃ ሰብሳቢው ትእዛዝ ወይም በድንገት በሚኾነው ነገር ሚናቸውን ለመጫወት ፍላጎቱ አይኖራቸውም ማለት ነው። ዋናው ነገር ሁሉም መረጃዎች የሚሰበሰቡትና አብዛኛዎቹ ምልከታዎችም የሚደረጉት በሰው ሠራሽ ብቻ ከኾነ የተመራማሪውን ሥራ ውጤታማ ላያደርጉት ይችላሉ። ስለዚህ ሌላ አማራጭ መፈለግ ግድ ነው የሚኾነው።

ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት፡- በአንድ የፎክሎር ዘውግ ያለውን የክዋኔ ስልት የሚያጠና ተመራማሪ መረጃውን በተፈጥሮ መቼት መሰብሰብ እንዳለበት እሙን ነው። ኾኖም ግን በተፈጥሯዊ መቼት የፎክሎር ዘውጎችን መረጃ መሰብሰብ ሳያመች ወይም በጊዜው ሳይቻል ሲቀር ተመራማሪው ተፈጥሯዊ የሚመስል ዐውድ ያዘጋጃል፤ ያደራጃል፤ ያቀናብራል (Goldstein,1974:87) እና (ፈቃደ፣1991፣23)።

ይህንን ከማድረጉ በፊት ግን የሚፈለገው ፎክሎር የሚከወንበትን ተፈጥሯዊ መቼት መርምሮ ማወቅ ይጠበቅበታል። ተመራማሪው ይህንን ካደረገ በኋላ ጥሩ ችሎታና ዕውቀት ያላቸውን

መረጃ ሰጭዎች ይፈልግና ከጓደኞቻቸው ጋር ኾነው የሚከውኑበትን ዐውድ ይፈጥራል። በዚህ የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ የሚሳተፉት ሰዎች በተቻለ መጠን በፍጹም ነጻነት እንዲሳተፉ ከመካከላቸው መረጃ ሰብሳቢው በተመልካችነት መኖሩ ሊነገራቸው አይገባም (ፈቃደ፣1991፣124)።

እንደ Goldstein (1974:87-88) አገላለጽ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ሦስት የተለያዩ ደረጃዎች መካተት አለባቸው። ከእነዚህ መካከል አንደኛው መረጃ ሰብሳቢው በመስክ ሥራው ወቅት የአንድ የተወሰነ የፎክሎር ዘውግ በማኅበረሰቡ ውስጥ የተፈጥሯዊ ክዋኔ እንደሚያስፈልገውና እንደማያስፈልገው መወሰን ይገባዋል። ለዚህም የሚኾኑ መረጃዎችን በኹለት ዓይነት መንገዶች ማግኘት ይችላል። የመጀመሪያው በተለምዶ ተፈጥሯዊ መቼት ያላቸውን ክዋኔዎች በመመልከት ሲኾን፣ ቀጣዩ ደግሞ በተፈጥሯዊ መቼት ሲሳተፉ ለነበሩት ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ይኾናል። ከተጠያቂዎቹ ምላሽ ማለትም ከቃላዊ ገለጻቸው በመነሣት የትኛው መቼት በቅንብር ሊዘጋጅ እንደሚችል መወሰን ይቻላል።

መረጃ ሰብሳቢው ተፈጥሯዊ መቼቱ በቅንብር እንዲዘጋጅ ከወሰነ በኋላ ወደኹለተኛው ደረጃ መሸጋገር አለበት። በዚህ ደረጃም ተባባሪ ከዋኞችን መፈለግ ይኖርበታል። ኹኔታው ከፈቀደም መረጃ ሰብሳቢው በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱ የሚሳተፉትን ሰዎች ለክዋኔው መገፋፋትና ማነሣሣት አለበት። እንደሚታወቀው ፎክሎር በርካታ ሰዎች በሚሳተፉበት ማኅበራዊ ኹነት ውስጥ የሚገኝ ነው። ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢው ከእነዚህ ሰዎች መካከል በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱ ሊሳተፉ የሚችሉ ተባባሪዎችን መምረጥ ይችላል። የሚመረጡት ሰዎችም መካከለኛ ወይም ዋና ዘፋኝ፣ አቅራሪ፣ ፎካሪ፣ ወዘተ. ነን ብለው ራሳቸውን የሰየሙትም ኾኑ በማኅበረሰቡ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸው ዋና ዘፋኝ፣ አቅራሪ፣ ፎካሪ፣ ወዘተ. መኾን ቢችሉ ተመራጭነት ይኖረዋል። ምክንያቱም በዚህ ምርጫ ወቅት ለማኅበረሰቡ የክዋኔው ውበት መመዘኛ ኾኖ ያገለግላልና ነው (Green,1997:13)።

በተጨማሪም Bauman (1992:38) ፎክሎር ከሚታወቅባቸው ጉዳዮች አንዱ ጥበባዊነቱ እንደኾነ በመግለጽ በተሰኑ ቡድኖች ዘንድ የሚደረግ ጥበባዊ የኾነ የመግባቢያ ዘዴ ነው ብለዋል። ተግባቢዎቹም ፊት ለፊት ስለሚገናኙ ጥበባዊነቱ የጎላ ነው። ጥበባዊ የሚያደርገው ሌላው መንገድ ደግሞ በንግግርና በትግበራ መቅረቡ ነው በማለት አስረድተዋል።

ሦስተኛው ደረጃ ደግሞ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቱ ለመሳተፍ የተመረጡት ተባባሪዎች በዋና ሚናቸው ምን ምን መከወን እንዳለባቸው ዐውድ መፍጠር ነው። ይህ ደግሞ ከእነሱ አልፎ የቅርብ ጓደኞቻቸውን በመጥራት በእንደዚህ ያለ ዐውድ ሊቀርቡ የሚችሉ ተረኮችን፣ ዘፈኖችን፣

መዝሙሮችን፣ እንቆቅልሾችን እና ሌሎችንም የማኅበረሰቡን ጥበቦች ሊከውኑ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ተመራማሪው ለተሳታፊዎች ዓላማውን ሳይናገር አጭር ትዕይንት ቢያዘጋጅ ክዋኔውን በድርጊት ለመመልከት ያስችለዋል።

የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ክዋኔ ሲጀመር መረጃ ሰብሳቢው አንድም እንደተሳታፊ፣ አንድም ከቡድኑ በስተጀርባ፣ ወይም ዳር ላይ ኾኖ ስለሚከወኑት ኹነቶች ማስታወሻ መውሰድ ይኖርበታል። መረጃውን በመቅረጸ ድምፅ ለመያዝ የማይችል ከኾነም ክዋኔውን በምሥጢር ጽሑፍ /Code System/ ወይም መረጃውን በአጭሩ ለማስታወስ በሚያግዝ መሣሪያ /Mnemonic Device/ ማመልከት አለበት። በመጨረሻም በሰው ሠራሽ መቼት ወይም በቃለ መጠይቅ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት እያንዳንዱን ተሳታፊ በግል ፈቃደኝነታቸውን መጠየቅ ይችላል።

ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼትም እንደየኹኔታው ውስንነቶች ይስተዋሉበታል (Goldstein, 1974:87)። Calendar Customs ተብለው በዓመት ውስጥ ጊዜ ተወስኖላቸው የሚከወኑ ሥርዓቶች (እነዚህም የአዲስ ዓመት መለወጫ፣ መስቀል፣ ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ መውሊድ፣ አረፋና የመሳሰሉት)፣ በአንድ በተወሰነ ኹነት ውስጥ የሚከሠቱ እንደወሊድ፣ ጋብቻና ሞት ያሉ የሕይወት ሽግግሮች፣ ወይም ከብቃትና ከችሎታ ማነስ የተነሣ መረጃ ሰብሳቢው የማይሳተፍባቸው ወይም ዳር ኾኖ የማይመለከታቸው ክዋኔዎች በቅንብራዊ ተፈጥሯዊ መቼት ማስመሰል አይቻል ይኾናል።

የፎክሎር መረጃውን ቀርጾ ለመያዝም ኾነ በአግባቡ ተመልክቶ በማስታወሻ ለመመዝገብ ከቅንብር ተፈጥሯዊና ከሰው ሠራሽ ይልቅ ተፈጥሯዊ መቼት ዓይነተኛ እንደሆነ Goldstein (1974) ገልጸዋል። ምክንያቱም መረጃ ሰብሳቢው ተፈጥሯዊ ዐውዱን በትክክል መመልከት ከቻለ እየተከወነ ካለው የፎክሎር ኺደት ብዙ ነገሮችን ሊማር ይችላልና ነው። ይህ ማለት አንደኛ፣ መረጃ ሰብሳቢው ያለ ማንም አስገዳጅነት የሚከወነውን ድርጊትና ኹነት በአንድ ላይ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ሊቀርጽና በማስታወሻ ደብተሩም ሊመዘግብ ይችላል። እንደዚህ ባለው ምልከታ ደግሞ ሰዎቹ ከሚሉት ይልቅ የሚያደርጉትን በደንብ እንዲያውቅ ዕድል ይኖረዋል።

ከላይ በቀረቡት ሐሳቦች መሠረት ሰው ሠራሽና የቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች የየራሳቸው ውስንነቶች እንዳሉባቸው በግልጽ ለማየት ተችሏል። በመኾኑም እኔ ባካኼድኩት ጥናት ተፈጥሯዊ መቼት የተሻለ ኾኖ ስላገኘሁት በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተግባራዊ አድርጌዋለሁ። ይህ መኾኑ ደግሞ ትክክለኛና (Authentic) የተሟላ መረጃን ለማግኘት አስችሎኛል ብዬ አስባለሁ።

ምክንያቱም ወቅትን ጠብቀው ይከወኑ የነበሩትን የሰርግ፣ የእርሻ፣ የዐረም፣ የዐጨዳ፣ የውቂያ፣ እንደዚሁም የዕርከን ሥራዎችን በየወቅታቸው የጥናቱ አካላይ በኾኑ ወረዳዎች እየተዘዋወርኩ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በእርግጥ ይህ ተግባሬ ብዙ ጊዜ ሊወስድብኝ ችሏል፡፡ ብስባሽ (Compost) እና ፀረ ዐረምን በተመለከተ የተነገሩት የቃል ግጥሞች በተለያዩ አጋጣሚዎች እንጂ በዐውድ የሚቀነቀኑ ኾነው ስላላገኘኋቸው በቃለ መጠይቅ ብቻ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ሌላው ደግሞ በ22/12/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ሶዬ ሚሎ በተባለ ቀበሌ በ፱ አለቃ አስፋው ተሰማ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝቼ የቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ኾኖም ተፈጥሯዊ መቼትን በተግባር ላይ በማዋል የሙሾውንና የቀብር ሥርዓቱን ክዋኔ በካሜራ ለመቅረጽ፣ ሰው ሠራሽና ቅንብራዊ ተፈጥሮንም ለመጠቀም ባህላዊና ልማዳዊ ኹኔታዎች አግደውኛል፡፡ በመኾኑም አማራጭ የሆነውን ዘዴ በመጠቀም በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥርዓቱን ሲከታተሉ ከነበሩ ሰዎች በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

መረጃ ትንተና

በዚህ ርእሰ ጉዳይ በጥናቱ ዓላማ ሥር ትኩረት የተደረገባቸው መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች በዝርዝር ተለይተዋል። ቀጥሎም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና መሣሪያዎች የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በዘውግ እየተከፋፈሉ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። ከዚያም በቃል ግጥሞቹ ላይ ዐውዳዊ የይዘት ትንተና ተካሂዷል። ከዚህ በማስከተልም ከመስክ የተሰበሰቡት የቃል ግጥም ዘርፎች የባህሉ ባለቤት ለሆነው ማኅበረሰብ ያላቸው ፋይዳዎች ተመርምረዋል። በመጨረሻም በጊዜ ኺደት በቃል ግጥሞቹና በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ላይ በታዩ ለውጦች፣ እንደዚሁም በቀጣይነታቸው ላይ ትንተና ተደርጓል። እነዚህ ተግባራት የተከናወኑትም ከመስክ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በካልኣይ ከተገኙ ጽንሰ ሐሳቦችና ከመረጃ መተንተኛ ንድፈ ሐሳቦች ጋር በማገናዘብ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

ምዕራፍ አምስት፡- የቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች

በጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ ቃል ግጥም የመከወኛ ዐውድ ፈላጊ መሆኑን ለማየት ተችሏል። ስለሆነም ቃል ግጥም ያለ ምክንያት አይከወንም ማለት ነው። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው ማኅበረሰብም ቃል ግጥምን የሚከውንባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። በዚህ መሠረት ምርታማነትን ለማሳደግ የሚውሉ ግብዓቶች (የኬሚካል ማዳበሪያ፣ ብስባሽ (Compost)፣ ፀረ ዐረምና ዕርከን ሥራ)፣ የእርሻ፣ የዐረም፣ የዐጨዳና የውቂያ ወቅቶች፣ የሰርግና የለቅሶ ሥርዓቶች፣ ልጃገረዶችን የሚያሰባስቡ ጉዳዮች የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች በመሆናቸው እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች ከተለያዩ መረጃዎች ጋር በቅደም ተከተል ቀጥሎ እንመለከታለን።

5.1. ምርታማነትን ለማሳደግ የሚውሉ ግብዓቶች

ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች የሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮው የተመሠረተው በሰብል ምርት ላይ በመሆኑ ምርታማነቱን ለማሳደግ የኬሚካል ማዳበሪያ፣ ብስባሽ (Compost)፣ ፀረ ዐረምና ዕርከን ሥራ የተባሉትን ግብዓቶች ይጠቀማል። እነዚህ ግብዓቶች ለቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች መሆናቸውን በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት በመስክ ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህንን ኹኔታ በሚከተለው መልኩ በቅደም ተከተል እንመልከት።



ሥዕላዊ መግለጫ አንድ፡- ምርታማነትን ለማሳደግ የሚውሉ ግብዓቶችን የሚያመለክት

5.1.1. የኬሚካል ማዳበሪያ

የኬማካል ማዳበሪያ ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋለ ሲኾን፣ በእርሻ ማሳ ላይ እየተጨመረ ለሰብል ዕድገትና ምርታማነት አስፈላጊ የኾነውን ንጥረ ነገር ከፍ በማድረግ ላይ ይገኛል (በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ የ2012/2013 ምርት ዘመን የሰብል አመራረት ፓኬጅ፣ 2012፡ 18)። ይህ የሚኾነውም 100 ኪ.ግ. ኤን. ፒ. ኤስ. የተባለውን እና 200 ኪ.ግ. የዩሪያ ማዳበሪያን በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በትክክለኛው ወቅትና መጠን መጠቀም ከተቻለ ነው። ከላይ በተጠቀሰው ምንጭ እንደተገለጸው እነዚህን የኬሚካል ማዳበሪያዎች በአገልግሎት ላይ ማዋል የሚቻለው ለኹለት መደቦች በመክፈል ነው። ይኸውም፣ ⅓ኛው እርሻ እየታረሰ ዘር በሚዘራበት ወቅት በማሳው ላይ ተበትኖ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል፣ ⅔ኛው ደግሞ ሰብሉ ከበቀለ ከ35 እስከ 40 ባሉት ቀናት ውስጥ እየተረጨ በኹለተኛ ዙር የዐረም ወቅት ዐፈር እንዲለብስ በማድረግ ነው።

በዚህ ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውለው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩት የኅብረተሰብ ክፍሎች የምርት ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ ገልጿል ። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉት አርሶ አደሮችም በተወሰነ የእርሻ መሬት ይዞታቸው ላይ ማዳበሪያን ተጠቅመው ብዙ ምርት ማምረት መቻላቸውን በሦስቱም ወረዳዎች ከመስከረም 05 - 09/2013 ዓ.ም ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ጭምቃ ሐሳብ ለመረዳት ተችሏል። ይህ

ኹኔታ ደግሞ ለቃል ግጥም መከወኛ መልካም አጋጣሚ ኾኖ ተገኝቷል። ለዚህ ማስረጃ ይኾን ዘንድ አርሶ አደሮቹ በአንደበታቸው ያዜሟቸውን ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 10፡- እኽል አልኾን ብሎ መሬቱ አቅቶ
ሕዝቡን አሻሻለው ማዳበሪያ መጥቶ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ላይ የቀረበው የመጀመሪያው ስንኝ እጅግ ስሜት ነኪ ነው። ምክንያቱም በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የአርሶ አደሩ ማሳ የዐፈር ለምነቱ ከሚገባው በላይ ተሟጥጧል። በዚህ የተነሣ ለቀለብ የሚኾን ወይም ለምግብ አገልግሎት የሚውል የአዝርዕት ውጤት ለማግኘት አዳጋች መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል። በመኾኑም ገጣሚው ከማኅበረሰቡ የሕይወት ገጠመኝ በመነሣት ስሜቱን በእዝነ ኅሊናችን እንዲሰማን አድርጓል። በኹለተኛው ስንኝ ላይ ግን በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በማሳቸው ላይ ለሰብላቸው ተስማሚና ጠቀሜታ ያለውን፣ በፋብሪካ ተመርቶ የሚቀርበውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን ማዳበሪያ በመጠቀማቸው ምርታማ ለመኾን በቅተዋል። በዚህም በኑሯቸው ላይ ለውጥን እና መሻሻልን ማምጣት ችለዋል በማለት ገጣሚው ለሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ውዳሴውን አቅርቧል። ይህ ኹነትም ለቃል ግጥም መከወኛ መልካም አጋጣሚ መኾኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ቃል ግጥም 11፡- ተልባ እየዘራሁኝ መሬቴን ሳመክነው
ማዳበሪያ መጣ ስንዴን የሚያዝቀው።

(ከቀያፈር ትምህርት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ ጋር በተመሳሰለ መልኩ በዚህ ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ የአርሶ አደሩ የእርሻ መሬት በጎርፍና በነፋስ በመጠረጉ፣ እንደዚሁም በተደጋጋሚ በመታረሱ የተነሣ የዐፈሩ ለምነት እየቀነሰ ኺዷል። በዚህ ምክንያት አርሶ አደሩ የዘራው እኽል ፍሬ ስላልሰጠ መናውን በመቅረቱ ተቸግሯል። ያን ያኽልም ለም ዐፈር የማይፈልገውን እና ተልባ የተባለውን የሰብል ዓይነት ይሻላል ብሎ ቢዘራውም የፈለገውን ያኽል ውጤት ሊያገኝ ስላልቻለ መሬቱን ሲያመክነው እንደኖረ በምሬት ብሶቱን ገልጿል። የኬሚካል ማዳበሪያውን ተጠቅሞ የተትረፈረፈ የስንዴ ምርት ማምረት በመቻሉ ደግሞ ሐሴት አድርጓል። በዚህ የተነሣ “ማዳበሪያ መጣ ስንዴን የሚያዝቀው” በማለት ስንኝ አዋቅሯል።

ቃል ግጥም 12፡- ከማዳበሪያው ጋር ዘርን እየዘራን
ከምርት አለፈና ገለባም አገኘን፡፡
ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የኬሚካል ማዳበሪያ ያለውን ጠቀሜታ በአወንታዊ መልኩ የተመለከተው አርሶ አደር ከላይ ያለውን ቃል ግጥም አዚሟል፡፡ ይኸውም ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮች ለሰብላቸው ዕድገትና ምርታማነት አስፈላጊ የኾነውን ንጥረ ነገር በውስጡ የያዘውን የኬማካል ማዳበሪያ በእርሻ መሬታቸው ላይ በትክክለኛው ወቅትና መጠን መጠቀም ችለዋል፡፡ ታዲያ ገጣሚው ከማኅበረሰቡ አብራክ የተገኘ በመኾኑ የስሱነትን (በኹነቱ የመኳትን) ባሕርይ በመላበሱ በአጥጋቢ ኹኔታ በሕይወት ለመቆየት የሚያስችል የምግብ ፍጆታ እኽል ባለቤት ለመኾን በቅተናል፡፡ ከዚያም አልፎ ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ጋር የጠበቀ ቁርኝት ላላቸው የቤት እንስሳት ቀለብ የሚኾን ገለባም ለማግኘት ችለናል በማለት ደስታውን በቋጠራቸው ስንኞች ገልጿል፡፡

ቃል ግጥም 13፡- ማዳበሪያው እኮ አይከፋም ነበር
ለሁሉም ሳይደርሰው በጅምር ባይቀር፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ዓይናለም በጸና፣ 22/05/2012/ ወግዲ ወረዳ)

አርሶ አደሮቹ የኬሚካል ማዳበሪያን ተጠቅመው ባገኙት ከፍተኛ ምርት በኑሯቸው ላይ ለውጥ ማምጣት እንደቻሉ ከላይ ከቀረቡት ቃል ግጥሞች ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንጻር ማዳበሪያን በአወንታዊ ጎኑ የተመለከቱት ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ከስርጭት አንጻር በሚታዩ ችግሮች የተነሣ በአሉታዊነት የሚያዩት አካላት መኖራቸውን የሚያንጸባርቀው ግጥም ደግሞ ከላይ መቅረቡን መመልከት እንችላለን፡፡ በመኾኑም ማዳበሪያ በማሳ ላይ ሲጨመር የሰብሉን የምርታማነት ደረጃ ከፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ የኾነ ሚና ስላለው ኬሚካሉን መጠቀሙ መጥፎ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአቅርቦት ማነስ የተነሣ ሁሉም አርሶ አደር ማዳበሪያውን ሳያገኝ ሥርጭቱ በጅምር የቀረ መኾኑን ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ በሥርጭት ዕጥረቱ የተነሣ በሚከሠተው ኢ- ፍትሓዊነት አከፋፈል አርሶ አደሩ ስለሚቆዝም ውጤታማ የመኾን ዕድሉ ዝቅተኛ ሊኾን እንደሚችል ከቃል ግጥሙ ለመገንዘብ አዳጋች አይኾንም፡፡

ቃል ግጥም 14፡- በማዳበሪያ ዕዳ ሀብቴን ተገፍፌ
እኽሉን አቅንቼ ገለባ ነው ትርፌ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አሕመድ ጀማል፣ 02/072012፣ ከለላ ወረዳ)

ይህንን ቃል ግጥም ያዜመው ግለሰብ በማዳበሪያ ዕዳ የተነሣ ለከፋ ችግር መጋለጡን በትካዜ ገልጿል። ምክንያቱም የኬሚካል ማዳበሪያ በመንግሥት አማካይነት በብድር መቅረቡ የተለመደ ተግባርና መርሓ ግብር ቢኾንም ዋጋው ውድ ስለኾነ አርሶ አደሩን ዕዳ በዕዳ አድርጎታል። ይኸውም ከአሁን ቀደም ያፈራውን ሀብትና ንብረት በመቀማት እንዲከፍል ተደርጓል። ዓመት ሙሉ ወጥቶ ወርዶ ያመረተውን እኽልም ቢኾን ገበያ ላይ አውጥቶ በመሸጥ ማዳበሪያ የገዛበትን ገንዘብ መልሷል። ካመረተው ነገር ምንም የተረፈው ነገር ባለመኖሩ የተነሣ ባዶ እጁን አጨብጭቦ ቀርቷል። አስፈጭቶና አስጋግሮ የማይበላው ገለባ ብቻ ነው በእጁ ላይ የቀረው። በመኾኑም በብድር መልክ የሚቀርበው ማዳበሪያ የአርሶ አደሩን የመክፈል ዐቅም ማገናዘብ እንዳለበትና ለዚህም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መኾኑን ሐሰ አዘል ከኾነው ቃል ግጥም መረዳት ይቻላል።

5.1.2.ብስባሽ

ብስባሽ ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋት ቅሪትና የሣር በል እንስሳት ፍግ ከውሃ ጋር ተዋሕዶ በጉድጓድ ውስጥ ከተብላላ በኋላ ከዐፈር ጋር የሚጨመር ግብዓት ሲኾን፣ ለሰብሎች አስፈላጊ የኾኑ ንጥረ ነገሮችን ለመስጠት፣ የዐፈር ለምነትን ለመጠበቅ፣ ውሃ የመያዝ ችሎታን ከፍ ለማድረግ፣ የምግብ እኽልና የፍራፍሬ ምርቶችን ለመጨመር የሚያስችል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ነው (ኃይሉ አርኣያና ሌሎችም፣ 2009፡5)። በወግዲ ወረዳ በመስከረም 07/2013 ዓ.ም በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ከአምስቱም መረጃ ሰጪዎቹ ያገኘሁት ጭምቃ ሐሳብ እንዳመለከተው በእያንዳንዱ ጉድጓድ ውስጥ ያለ ብስባሽ ተብላልቶ ለመጠናቀቅ ኹለት ወራትን የሚፈጅ ሲኾን፣ የዘር ሥራ ከመካኼዱ ከአንድ ወር ቀደም ብሎ ማሳ ላይ እየተበተነ በአርሻ አማካይነት ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ይደረጋል። በዚህ የተነሣ ብስባሹ በውስጡ የያዛቸውን ንጥረ ነገሮች በቀላሉ ለሰብሎች እንዲደርሱ በማድረግ ምርትን እና ምርታማነትን ለማሳደግ ይችላል። ሀገር በቀል በኾነ ዕውቀት የተዘጋጀው ብስባሽ የአርሶ አደሮችን ምርታማነት በማሳደጉ የተነሣ ለቃል ግጥም መከወኛ በጎ አጋጣሚ መኾኑን ከተከታዮቹ ምሳሌዎች እንመልከት።

ቃል ግጥም 15፡- ጥሩ ምርት አግኝቼ ልጆቼ እንዲያድጉልኝ
እበቱን በጥብጬ ኮምፖስት[19] አቀረብኩኝ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አሰፋ ግዛው፣ 08/01/2013፣ ቦረና ወረዳ)

[19] ዘመናዊ ትምህርትን ያልተማሩ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቹ በንበት ችግር ምክንያት ‹‹ኮምፖስት›› የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በትክክል ስለማይጠሩ ‹‹ኮምበስት›› እያሉ ቃል ግጥሙን የነገሩኝ መሆኑን መጠቆም ወድጃለሁ።

ከላይ የቀረበውን ግጥም ያዜመው ግለሰብ ተስፋን ሠንቋል። ምክንያቱም የቀንድ ከብትን ዕዳሪ ወይም ፍግ በውሃ በጥብጦ ያዘጋጀውን ብስባሽ በማሳው ላይ ከበተነ በኋላ የተትረፈረፈ ምርት አግኝቶ የምግብ ዋስትናውን በማረጋገጥ ከአብራኩ የወጡት ልጆች አድገው ለቁም ነገር እንዲበቁለት ተመኝቷል። እዚህ ላይ ገጣሚው "ልጆቼ" ይበል እንጂ ግጥሙ ግን የትዳር ጓደኛን እና አጠቃላይ ቤተሰብን ያሳስባል። ያለ ትዳር ጓደኛ ልጆችን ማፍራት አይቻልምና። ልጅ ሲባልም ትንሹም ትልቁም፣ ወንዱም ሴቱም በአጠቃላይ ተወልደው ለዐቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን እስከሚደርሱ ድረስ በእሱ ትከሻ ሥር የወደቁትን ሁሉ ያጠቃልላል። እዚህ ላይ ገጣሚው ለትዳር ጓደኛውና ያጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ቁራጭ ለኾኑት ልጆቹ ጽኑ የኾነ ቤተሰባዊ ፍቅርና መተሳሰብ ያለው መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ እንችላለን። ብስባሽ ለምርት እድገት ካለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ በምርት ጣዕምና ጥራት ላይ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ኃይሉ አርኣያና ሌሎች (2009፡21) ገልጸዋል። በዚህ መሠረት ገጣሚው "ጥሩ ምርት አግኝቼ ልጆቼ እንዲያድጉልኝ" በማለት ዘለላ ስንኝ ያቀነቀነው በብስባሽ አማካይነት ከተመረተው እኽል ለአካል ግንባታና እድገት የሚበጅ ምግብ ልጆቹ ማግኘት እንደሚችሉ ለማመላከት ሲባል ነው።

ቃል ግጥም 16፡- ኮምፖስቱን አፍስሼ እኽል ብዘራበት
ጭነት በጭነት ላይ አደራረብኩበት።
(ቃለ መጠይቅ፣ ማርቆስ መክብብ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ብስባሽን አዘጋጅቶ በእርሻ መሬት ላይ መበተን በሰብሎች የእድገት ጊዜያት በሙሉ አስፈላጊ እንደኾነ፣ ምርትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማሳደግ እንደሚቻል፣ ዐረምን፣ ተባይን እና በሽታን ለመቆጣጠር እንደሚረዳ በ07/01/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ባካኼደኩት ቡድን ተኮር ውይይት ከተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች መካከል አቶ ሁሴን አደምና አቶ መሐመድ አብዱ አስረድተውኛል። ከዚህ በተጨማሪ ብስባሹ ሲዘጋጅ በመብላላት ኺደት በሚፈጠር መቀት ዐረሞቹ ስለሚቀቀሉ የመብቀል ችሎታቸው እንደሚቀንስ፣ ከኬሚካል ማዳበሪያ በተቃራኒው የዐፈር ለምነትን በዘላቂነት ለማሻሻል እንደሚያግዝ በመስክ ቆይታዬ ወቅት በ08/01/2013 ዓ.ም የጤፍ ዐረም ሲያርሙ ያነጋገርኳቸው አቶ መስጠፋ የሱፍና ደበበ አያሌው በሰፊው አብራርተውልኛል። ከላይ ያለውን ቃል ግጥም የተናገረው ግለሰብም ቀደም ሲል በዝርዝር የቀረቡትን ቁም ነገሮች ተገንዝቦ ደጋግሞ ባረሰው ማሳ ላይ ያዘጋጀውን ብስባሽ በመጠቀም ለምግብ አገልግሎት የሚውል እኽልን መዝራት እንደቻለ ነግሮኛል። ይህንን ማድረግ በመቻሉም የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት በቅቷል። በዚህ የተነሣ ምርቱን በጋማ ከብትም ኾነ

በመኪና ሲያንጉዝ አንዱን በአንዱ ላይ እያነባበረ በመጫኑ የተሰማውን የደስታ ስሜት ገልጿል።

ቃል ግጥም 17፡- “ዩሪያ” ከመግዛት ገንዘብን አውጥቶ
መጠቀም ይሻላል ኮምፖስት አዘጋጅቶ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አብዱ መሐመድ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ይህንን ቃል ግጥም ያዜመው ገጣሚ ብስባሽን በማሳ ላይ መጠቀም የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት ከማስቻሉም በተጨማሪ “ዩሪያ” ለተባለው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ የሚወጣውን የገንዘብ ወጪ ለመቀነስ እንደሚረዳ ምክሩን ለግሷል። እዚህ ላይ “ዩሪያ” እና ብስባሽ በንጽጽር የቀረቡ መኾኑን ከግጥሙ መገንዘብ ይገባል። በመኾኑም ብስባሽ ያለ ምንም የገንዘብ ወጪ በአርሶ አደሩ ጉልበት ብቻ ሊዘጋጅ የሚችል በመኾኑ በገንዘብ ተገዝቶ ከሚቀርብ የኬሚካል ማዳበሪያ የተሻለ እንደኾነ መንቶ ስንኞቹ ያስረዳሉ። በአጭሩ በገንዘብ መልክ በብድር አማካይነት ከሚመጣ ዕዳ ያድናል ማለት ነው። ምንም እንኳን የኬሚካል ማዳበሪያና ብስባሽ ያሏቸው ንጥረ ነገሮች ለሰብል እድገትና ምርታማነት ጠቀሜታ ያላቸው ቢኾንም ብርን ወጪ አድርጎ ማዳበሪያ ከመግዛት ይልቅ ብስባሽን በቀላሉ አሰናድቶ በእርሻ ማሳ ላይ መጠቀሙ ፋይዳው የጎላ እንደኾነ ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል።

ቃል ግጥም 18፡- በዋጋ በዛብን ከማምጣት ሮሮ
እናዘጋጃለን ኮምፖስትን ከጓሮ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙስጠፋ ሙሔ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም የተናገረው ግለሰብ ቀደም ሲል ከቀረበው ማብራሪያ ጋር በተመሳሰለ መልኩ አርሶ በሌ ለኾነው የጎብረተሰብ ክፍል ምክር አዘል አስተያየቱን ሰንዝሯል። እንደሚታወቀው አርሶ አደሩ ብስባሽን ለማዘጋጀት የሚጠቀምበትን ቁሳቁስ የሚያገኘው ከአካባቢው ነው። ይኼውም ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋት ቅሪትን እና የሣር በል እንስሳትን ፍግ ከውሃ ጋር አዋሕዶ በጉድጓድ ውስጥ በማብላላት አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚደረግ በመኾኑ ገንዘቡ በየጊዜው እየጨመረ በመንግሥት አማካይነት ከሚቀርበው የማዳበሪያ ዕዳ ከመነከር ያድናል። የቃል ግጥሙ ገጣሚም ቢኾን የሚነግረን የኬሚካል ማዳበሪያ መግዣ ዋጋ ከልክ ባለፈ ኹኔታ በመቆለሉ የተነሣ ዋይታና ሐዘን ከማሰማት ይልቅ በመኖሪያ ቤት ዙሪያ ባለ ቦታ ላይ ብስባሽን አዘጋጅቶ መጠቀም እንደሚሻል ነው። ገጣሚው ከአርሶ አደሩ ሕይወት አንጻር ይህን ይበል እንጂ ከዚህም ባለፈ መንግሥት ለሰው ሠራሽ ማዳበሪያ የሚያወጣውን የውጭ ምንዛሬ ችግር ሊያቃልልለት እንደሚችል ልብ ማለት ይገባል። ኃይሉ አርኣያና ሌሎች

(2009፡9) እንደገለጹት ደግሞ በአሁኑ ወቅት በዓለም ገበያ ላይ ከ“ኦርጋኒክ” (ያለ ማዳበሪያ ከተመረተ ምርት) የሚገኘው ምግብ ተፈላጊነቱ ከፍተኛ በመኾኑ ብስባሽን ተጠቅመው ሰብልን በማምረት ለገበያ የሚያቀርቡ አርሶ አደሮች የተሻለ ገቢን ያስገኝላቸዋል፡፡

ቃል ግጥም 19፡- ሰነፉ ገበሬ ኮምፖስት ያልቀበረ
ዘሩንም ሳያገኝ መና ኾኖ ቀረ፡፡

ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ሐሰን፣ 05/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በዚህ ጥናት የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ እንደተመለከትነው ቃል ግጥሞች በስንፍና ላይ የመሣለቅ ፋይዳ እንዳላቸው Bascom (1954፡343-349) ገልጸዋል፡፡ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም ያዜመው አርሶ አደርም ሰነፍ በኾነው ገበሬ ላይ ትችቱን ሰንዝሯል፡፡ ይኼውም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው ሥራ ጠል ሰው በሰበብ አስባቡ ተቀምጦ እየዋለ የቀንድ ከብትን ዕዳሪ ወይም ፍግና የዕፅዋትን ቅሪት በውሃ ካዋሐደ በኋላ በጉድጓድ ውስጥ ቀብሮ ብስባሽ በማዘጋጀት በእርሻ መሬቱ ላይ አለመጠቀሙን በመጀመሪያው ስንኝ ላይ አንጸባርቋል፡፡ ታዲያ እንዲህ ያለው ሰው እንደሌሎቹ አርሶ አደሮች የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ ቀርቶ በማሳው ላይ በዘርነት የተጠቀመውን እኽል እንኳ መመለስ ወይም መተካት አልቻለም፡፡ በዚህ የተነሣ ምንም ነገር ሳያገኝ ባዶ እጁን መቅረቱን ገጣሚው በዓይነ ኅሊናችን እንድናየው አድርጓል፡፡

5.1.3. ፀረ ዐረም

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ለማሳደግ ከሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች መካከል አንደኛው የፀረ ዐረም ኬሚካል እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሮቹ ኬሚካሉን በተገቢው ወቅትና መጠን በመርጨት እየተጠቀሙ እንደኾነ በሦስቱም ወረዳዎች ከመስከረም 05 - 09/2013 ዓ.ም ድረስ በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች አስረድተውኛል፡፡ እነሱ ተገቢ የኾነ ወቅት የሚሉት አዝርዕቱ በቅሎ በአብዛኛው ከሦስት እስከ አምስት ቅጠል እስከሚያወጣ ድረስ ያለውን ጊዜ ሲኾን፣ በመጠን ሲባል ደግሞ አንድ ስኒ የሚኾን የፀረ ዐረም ኬሚካሉን ኻያ ሊትር ውሃ በያዘ ጀሪካን ከበጠበጡ በኋላ ተገቢ በኾነ የመርጫ መሣሪያ ከላይ በተጠቀሰው ወቅት በሰብሉ ላይ መርጨት ሲችሉ ነው፡፡

ኬሚካሉ የሚከላከላቸው ቅጠለ ሰፋፊ የኾኑትን እና የሣር ዐረሞችን ሲሆን፣ ቅጠለ ሰፋፊ የሆኑትን ዐረሞች የሚያጠፋውን ፀረ ዐረም ኬሚካል አርሶ አደሮቹ “መርጦ ገዳይ” በማለት ይጠሩታል፡፡ ከኹለቱ አንዱን ወገን ብቻ መርጦ ስለሚያጠፋ ማለት ነው፡፡ ኹለቱንም የዐረም

ዓይነቶች በአንድ ጊዜ የሚገድል ከሾነ ደግሞ “አይመርጤ” ይሉታል። ምንም እንኳን ሰብልን በተቻለ መጠን በእጅ ማረም ጥሩ ቢሾንም የጉልበት ዕጥረት በሚያጋጥምበትና የዐረሙ ክሥተት ከፍተኛ በሚሾንበት ወቅት ፀረ ዐረም ኬሚካልን መርጨት ተገቢ መሾኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ (2012፡85) ገልጿል። በዚህ ዓይነት ኺደት ፀረ ዐረም ኬሚካልን መጠቀም ለቃል ግጥም መከወኛ አንደኛው መንገድ መሾኑን በቃለ መጠይቅ አማካይነት በጥር 19/05/2012 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ከምትኖረው ከገንዘቤ በለጠ ከተገኙትና በተከታታይ ትንተና ከተካኼደባቸው አምስት መንቶ ስንኞች መገንዘብ እንችላለን።

ቃል ግጥም 20፡- ቅጠላ ቅጠሉ ስንዶዬን ሲወርሰው
ፀረ ዐረም መጣልኝ የሚበጣጥሰው።

ቃል ግጥሙን ያንጎራጎረው ግለሰብ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የስንዴ ቡቃያውን አስፈላጊ ያልሾነ፣ ተነቅሎ የሚጣል፣ ብዙ ዓይነት መልክና ባሕርይ ያለው ቅጠለ ሰፋፊ ዐረም ወርሶት ወይም ውጦት ስለነበር ያዘነና የተከዘ ይመስላል። ቅጠለ ሰፋፊ የሾነውን የዐረም ዓይነት የሚያጠፋና “መርጦ ገዳይ” እያሉ አርሶ አደሮቹ የሚጠሩት ፀረ ዐረም ኬሚካል በነፍሱ እንደደረሰለት በኹለተኛው ስንኝ ላይ ገልጿል። በዚህም ዐረሙ ቀስ በቀስ እየቀጨጨና እየኮሰመነ እንደሚኼድ፣ ቀጥሎም ተበጣጥሶና ተቆራርጦ እንደሚወድቅ፣ በመጨረሻም የስንዴ ሰብሉ ዐራሙቻ ተወግዶለት ግለሰቡ ከፍተኛ ምርት ሊያገኝ እንደሚችል ተስፋን ሠንቋል። ይህ በመሾኑም ባለ ውለታው ለሾነው ፀረ ዐረም ኬሚካል ክብርና ምስጋና እንደሚገባው በማመን ምስጋና አቅርቦለታል።

ቃል ግጥም 21፡- ጥቅሙ ከፍተኛ ዋጋው አነስተኛ
ፀረ ዐረም ኬሚካል መጣ ያረም ዳኛ።

የሚፈልገውን ነገር በማግኘቱ እርካታ የተሰማው አርሶ አደር ከላይ በቀረው ቃል ግጥም ውስጥ ያሉትን መንቶ ስንኞች ተናግሯል። ይህ ቃል ግጥም የቀረበው በሰውኛ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት አል - ሰው የሾነውን ፀረ ዐረም ኬሚካል ሰብዓዊ ተግባርን እንዲፈጽም በማድረግ ነው። ይሄውም የፀረ ዐረም ኬሚካሉ አገልግሎት እጅግ በጣም የላቀ መሾኑን ለማሳየት ግኡዝ የሾነውን ነገር ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ የዳኛን ባሕርይ አላብሶ በዓይነ ኅሊናችን እንዲንመለከተው አድርጎናል። ምክንያቱም ዳኛ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ ብያኔ፣ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ... ለመስጠት ሥልጣን ያለው አካል በመሾኑ ነው። አርሶ አደሩ ቃል ግጥሙን እንድያዜም ያስቻለው ደግሞ የጉልበት ዕጥረት እንዳጋጠመውና ሰብሉን በወቅቱ ማረም ስላልቻለ ዐረም እንደወረሰበት፣ በዳኛ በተመሰለውና ዋጋው ዝቅተኛ በሾነው የዐረም መከላከያ

ኬሚካል አማካይነት የነበረበትን የዐረም ተግባር ችግር መቋቋም እንደቻለ የቋጠራቸው ስንኞች እንዲናገሩለት በማድረግ ነው፡፡

ቃል ግጥም 22፡- አዝመራው ቀጭጮ ከመባል የእገሌ
እንዴት ነው ፀረ ዐረም አርሶ አደር ገላግሌ፡፡

ቃል ግጥሙ በባሕርይና በችሎታ አማካይነት ግላዊ ማንነት የተንጸባረቀበት ይመስላል፡፡ ምክንያቱም “የእገሌ” የሚል ማጠንጠኛ ቃል በመጀመሪያው ስንኝ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ በመኾኑም በግጥሙ ውስጥ በምናብ የተሳለው ግለሰብ የሚያደርገው ድርጊት ለራሱ ብቻ እንጂ በሌሎች ሰዎች እንዲታወቅበት ያለ መፈለግ ነገር ይስተዋልበታል፡፡ በዚህ መሠረት ከእኽል ጋር ዐብሮ በሚበቅልና ተፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ተነቅሎ በሚጣል የዕፅዋት ዓይነት ሰብሉ ተወርሶ እያለ ክብሩን ለመጠበቅ ሲል በማሳው አቅራቢያ ባለው መንገድ ወጪ ወራጅ የኾኑ ሰዎች “የእገሌ አዝመራ ዐረም ውጦት ቀረ” እያሉ እንዳይዘባበቱበት ይፈልጋል፡፡ በዚህ የተነሣ ግለሰቡ በራሱ ስንፍናም ይኹን በሌላ ምክንያት ባጋጠመው የጉልበት ዕጥረት ዐረሙን ሊያስወግድ ባለመቻሉ ሰብሉ በሚገባው መጠን ሳያድግና ሳይፋፋ በመቅረቱ ነውሩ ተገልጦበታል፡፡ በግብርና ሥራ ለሚተዳደርና እንደ እሱ ዳተኛ ለኾነ ሰው ገመና ከታች የኾነው ፀረ ዐረም ኬሚካል ደርሶለት ከችግሩ መላቀቁን ግጥሙን ያዜመው ገጣሚ አመላክቷል፡፡

ቃል ግጥም 23፡- ጤፍና ስንዴዬን እንከባከባለሁ
ፀረ ዐረም ስላለ መታከት ትቻለሁ፡፡

ምንም እንኳን ሰብልን በተቻለ መጠን በእጅ ማረም ጥሩ እንደኾነ ቀደም ሲል የተገለጸ ቢኾንም ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር ካለበት የጊዜና የጉልበት ዕጥረት የተነሣ በአዝርዕቱ ውስጥ የሚታየውን ዐረም በወቅቱ ለማስወገድ ሊያቅተው ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ በማኅበረሰቡ አጠራር “መርጦ ገዳይ›› እና ‹‹አይመርጤ” የተባሉትን የፀረ ዐረም ኬሚካሎች የመጠቀም ዕድል አለው፡፡ ለዚህም ነው “ፀረ ዐረም ስላለ መታከት ትቻለሁ” እያለ በመመካት የተናገረው፡፡ ስለኾነም፣ አርሶ አደሩ በዋናነት በዐረም ማረም መውጣትና መውረዱ፣ መልፋት መድከሙ ቀርቶለታል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በኬሚካሉ አማካይነት የጤፍና የስንዴ አዝመራውን ከዐረም ተከላክሎ በመያዝ ለተሻለ ውጤት ሊበቃ እንደሚችል ተስፋ በማድረጉ የተነሣ ነው፡፡

ቃል ግጥም 24፡- የዐረም ማጥፊያ መድኃኒት ከመጣ
ሰው ሥራ ፈታ ከብቱ ምግብ አጣ፡፡

እስካሁን ድረስ ስለፀረ ዐረም ትንተና የተካኼደባቸው የቃል ግጥሞች በአወንታዊ መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ግን አሉታዊ ገጽታን የተላበሰ መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለዚህ ማረጋገጫው ደግሞ ተፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ከአዝርዕት ውስጥ ተነቅሎ የሚጣለው ዐረም (የዕፅዋት ዓይነት) ለቤት እንስሳት በመኖነት ያገለግል ነበር። ዐረምን ለማስወገድ የሚያገለግለው ኬሚካል ከመጣ ወዲህ ግን እንስሳቱ ሥጋዊ ሕይወታቸው የሚጠበቅበትን ቀለብ ሊያገኙ አልቻሉም። ከዚህ በተጨማሪ በግብርና ሥራ የሚተዳደረው ሰብዓዊ ፍጡር ያለ ማቋረጥ ሥራ ሲሠራ ነበር፡ አሁን ላይ ግን የአረም ማረሙ ሥራ ስለተቃለለት ቦዝኗል በማለት ወቅታዊ ኹነቱን የገመገመው የቃል ግጥሙ ባለቤት ከአንደበቱ በወጡ ቃላት አማካይነት መንቶ ስንኞቹን ቋጥሮ አስተያየቱን ሰንዝሯል። ገጣሚው ይህን ይበል እንጂ ጊዜ ሳይወሰድ በኬሚካሉ አማካይነት የቡቃያው ዐረም በተገቢው ወቅት ከተወገደለት ከፍተኛ የኾነ ምርት አርሶ አደሩ ማግኘት እንደሚችልም ማስተዋል ይገባል።

በጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ እንደቀረበው ቃል ግጥምን ማጥናት ያለብን እየተከወነ ባለበት ዐውድ ነው በማለት Dundes (2005:389) ገልጸዋል። ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች የሚገኘው የጎብረተሰብ ክፍል ግን ምርታማነቱን ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት ብስባሽ (Compost) በማሳው ላይ ሲበትን፣ ፀረ- ዐረምን በአገልግሎት ላይ ሲያውል የቃል ግጥሞችን እምብዛም እንደማይከውን ተረድቻለሁ። ከዚህ ይልቅ በእነዚህ ግብዓቶች አማካይነት የሰብሉ ቡቃያ በማሳው ላይ አምሮ ሲያየው፣ በዐጨዳ ወቅት የዳበረውን ብርዕ እንደልብ መጨበጥ ሲችልና የሰብሉ ፍሬም በእጁ ላይ ሲከብደው፣ እንደዚሁም በውቂያ ወቅት በዐውድማ ላይ ምርቱ ሲትረፈረፍና ለእንስሳቱ ቀለብ የሚኾን ገለባም በገፍ ሲያገኝ ቃል ግጥሞችን እንደሚያዜም በቃለ መጠይቅ ወቅት የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎቼ በዝርዝር አስረድተውኛል። በዚህ መሠረት እኔም Compost (ብስባሽ)ን እና ፀረ ዐረምን በተመለከተ የተነገሩትን ቃል ግጥሞች በዐውድ ላይ ለማግኘት ተቸግሬ ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አርሶ አደሩ ማኅበረሰብ እነዚህን ግብዓቶች የሚያከናወንበት አንድ የተወሰነ ወቅት ስላልነበረው ነው። ቢኾንም ይህንን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ በቃለ መጠይቅ፣ በጽሑፍ፣ በsoft copy ቃል ግጥሞችን የሰበሰብኩ መኾኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

5.1.4. ዕርከን ሥራ

የዕርከን ሥራ የዐፈርን ለምነት ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ሲኾን፣ የማሳና የጋራ (የተራራ) ላይ በሚሉ ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል። ይህ ጥናት የዐፈርን ለምነት በመጠበቅ ምርትን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ባለው የማሳ ላይ ዕርከን ትኩረቱን አድርጓል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አርሶ አደሮችም በእርሻ ማሳቸው ላይ የዐፈር ዕጥበትን በመከላከል ምርታቸውን ለማሳደግ በዓመት ውስጥ ከ40 — 60

ያክል ቀናት በጋራ በመረባረብ የማሳ ላይ የዕርከን ሥራን ያከናውናሉ። ይህ ዓይነቱ የዕርከን ሥራ የቃል ግጥሞችን ለመከወን ምቹ አጋጣሚ በመኾኑ ምክርን የሚለግሱ፣ ትችትን የሚሰነዝሩ፣ ጥገኝነትን የሚነቅፉ፣ ታታሪነትን የሚያበረታቱ ቃል ግጥሞችን ከአርሶ አደሮቹ ከጥር 19 - መጋቢት 04/2012 ዓ.ም ድረስ በመጀመሪያው ዙር በነበረኝ የመስክ ቆይታዬ በቃለ መጠይቅ ለማግኘት ችያለሁ። በማስረጃነት የቀረቡት የሚከተሉት ቃል ግጥሞችም ከላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች የሚያንጸባርቁ መኾናቸውን ማጤን ይገባል።

ቃል ግጥም 25፡- ዐፈራችን ታጥቦ እንዳይኼድ በውሃ
ዛሬ ነገ ሳንል ዕርከንን እንሥራ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

አርሶ አደሮቹ የዕርከን ሥራን በጋራ በመረባረብ እንደሚያከናውኑ ቀደም ሲል ተገልጿል። የዚህ ቃል ግጥም ባለቤት የኾነው አርሶ አደርም ለአንድ ኹለት ሰዎች ብቻ አይደለም ምክር አዘል የኾኑ መንቶ ስንኞቹን ያሰናኘው። በጋራ፣ በአንድነት፣ በመደጋገፍ፣ ወዘተ. ዕርከንን ለሚሠሩት የኅብረተሰብ ክፍል አባላትም ጭምር ነው። በመኾኑም ለአዝርዕት እድገትና መዳበር አስፈላጊ የኾነው ለም ዐፈር በዝናብ አማካይነት በሚፈጠር ጎርፍ ተጠራርጎ መወሰድ እንደሌለበት ገጣሚው ምክረ ሐሳቡን ለግሷል። በመቀጠልም የዕርከን ሥራው ጊዜ የማይሰጥ በመኾኑ ዛሬ ነገ እያልን ሳናመነታና ቀጠሮ ሳንይዝ የእርሻ መሬታችን ዐፈር በጎርፍ እየተሸረሸረና እየተጠረገ እንዳይወሰድ ደግፎ በሚይዝ የድንጋይ ካብ በጋራ ተባብረን መሥራት ይገባናል በማለት ገጣሚው አርሶ አደር ለኾኑት ባልንጀሮቹ ጠቀሜታ ያለው ሐሳብ ችሯቸዋል።

ቃል ግጥም 26፡- የኢሕአዲግ [20]መንግሥት ይዘናል በመላ
መሬቱን በዕርከን ሥራ ሴቱን በክኒና።
(ቃለ መጠይቅ፣ ይማም እብሬ፣ 20/05/2012/ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥም የሕግ ቁጥጥርና ምርመራ (ሳንሱር) ስለማይደረግበት ተገዥ የኾነው የኅብረተሰብ ክፍል ገዥው ያሳደረበትን ብሶት በነጻነት የሚገልጽበት መሣሪያ እንደኾነ በምዕራፍ አንድ ላይ ተገልጿል። ለዚህ ጥናት የሚኾኑት መረጃዎች በተሰበሰቡባቸው ወረዳዎች የተገኙት ውስን ቃል ግጥሞችም ይህንኑ ሐቅ አረጋግጠዋል። ከላይ የቀረበው ግጥምም በኢሕአዲግ አገዛዝ ወቅት በመንግሥት መዋቅር ላይ የሚገኙት ባለሥልጣናት ሕዝቡን እንዲያማርር የሚያደርግ ተግባር መሥራታቸውን ገጣሚው በምፀት ተችቱን ሰንዝሯል። እዚህ ላይ ጉዳዩን ማጤን

[20] የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞራሲያዊ ግንባር ማለት ነው።

ያለብን በቃል ግጥሙ ውስጥ ያለውን ሐሳብ በቀጥታ በተባለው መንገድ ሳይሸን ተቃራኒ የሚሸን ፍቺ ወይም ትርጓሜ ለመስጠት በሚያስችል የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ነው።

በዚህ መሠረት በየደረጃው ያሉ የመንግሥት የመስተዳድር አካላት ኅብረተሰቡን የሚያስተዳድሩበት ዘዴ ወይም ብልኀት ተቀባይነት የሌለው መሸኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ምንም እንኳን የዐፈርን ለምነት ለመጠበቅ የዕርከን ሥራ አስፈላጊ ተግባር ቢሸንም ፈጻሚው አካል አምኖበት የሚያከናውነው አለመሸኑን እንረዳለን። በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሳይሸን በውድም በግድም በሚባል ዓይነት ነው የዕርከን ሥራው እንዲሠራ የተፈለገው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቃል ግጥሙ ፓለቲካዊ አንድምታ አለው። ይኸውም በጥናቱ የታቀፉት ወረዳዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ያሉ በመሸናቸው እኩይና መሠሪ በሽነ መንገድ ከፍተኛ የሽነ በጀት በመመደብ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ኅብረተሰቡ ዘሩን እንዳይተካ በየሳምንቱ ገበያ በሚኖር ዕለት ሴቶቹ የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን እንዲውጡ በመደረጉ ቃል ግጥሙ ያመላክታል። በዚህ የተነሣ የሕዝቡ ቁጥር እንዲቀነስ ከመደረጉም በላይ ሴቶቹ ለመካንነት እየተዳረጉ ነው በማለት ገጣሚው ብሶቱን ገልጿል።

ቃል ግጥም 27፡- ማዳበሪያው በሺህ ብር ተገዝቶ
ዘሩም አንድ ሺህ ብር ተገዝቶ ተዘርቶ
አይጥ ለቃቀመው በየካቡ ገብቶ።

(ቀያፈር አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዋጋ መናሩን፣ የዕርከን ሥራውም ቢሸን የዐይጥ ጉድጓድ መሸኑን የሚያንጸባርቀው ሐሳብ በቃል ግጥሙ ቀርቧል። በመሸኑም የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የሽነው የኬሚካል ማዳበሪያ በማሳ ላይ ላለው ሰብል ተስማሚና ጠቃሚ ቢሸንም በመንግሥት አማካይነት በብድር በሚቀርብበት ጊዜ የኩንታሉ ዋጋ አንድ ሺህና ከዚያም በላይ በሆነ ብር የሚገዛ በመሸኑ አርሶ አደሩን ለምሬት አጋልጦታል። የምርጥ ዘሩም ዋጋ ቢሸን ለአርሶ አደሩ "በእንቅርት ላይ ጉሮ ደግፍ" ሸናበታል። ይህ ደግሞ የአርሶ አደሩን የማዳበሪያም ሽነ የምርጥ ዘር ዋጋ የመክፈል ዐቅም ያላገናዘበ መሸኑን ያመለክታል። የዕርከን ሥራውም ቢሸን ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበርና በዐፈር በማስታቀፍ ሊዘጋጅ የሚችል በመሸኑ በማሳ ላይ ያለውን ሰብል በመብላት ጥፋት ለሚያደርሰው ዐይጥ ምቹ መኖሪያ ጉድጓድ ሸኗል። በዚህ የተነሣ አርሶ አደሩ በሜዳ ላይ ያለውን አዝመራ ዐይጥ ጠራርጎ ስለበላበት ምሬቱን በቃል ግጥሙ አማካይነት ለመግለጽ ችሏል።

ቃል ግጥም 28፡- አፋፍ ላይ ውጣና ለሁሉም ንገረው
ነገ ከዕርከን ሥራው እርዳታ አለ በለው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ጀማል፣ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ የዕለት ሞት ሲያጋጥም ለመቅበር፣ መርዶም ካለ ለማላቀስ ሰዎች ተራራ አፋፍ ላይ ወጥተው ጥሪ ያስተላልፋሉ፡፡ ጥሪውም ያለ ማቋረጥ ሰፊ የሾነ መልክኣ ምድርን ሊሸፍን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቀበሌ ስብሰባና የሥራ ዘመቻ ሲኖርም ተራራ ላይ ተወጥቶ ጥሪው ይተላለፋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በቀበሌ የሚካኼደውን ስብሰባ ለመሳተፍም ሾነ የሥራ ዘመቻውን ለማካኼድ ማኅበረሰቡ በጣም ስለሰለቸ ጥቅምን ታላሚ ያደረገ ጥሪ ተራራ ላይ በመውጣት እንደሚተላለፍ ከላይ ካለው ቃል ግጥም መገንዘብ እንችላለን፡፡ ስለሾነም ‹‹ተራራ ላይ ሾነህ ለጠቅላላው የኅብረተሰብ ክፍል በነገው ዕለት የዕርከን ሥራ ከሚሠራበት ቦታ በበጎ አድራጊ ድርጅት አማካይነት የሚቀርብ ርዳታ ይኖራል›› ብለህ መልእክት አስተላልፍ የሚል መልእክት ከግጥሙ ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ርዳታው ኖረም አልኖረም ኅብረተሰቡ ሠርቶ ራሱን እንዳይችል ለጥገኝነት መዳረግ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም የዕርከን ሥራው ለራሱ ለኅብረተሰቡ እንደሚጠቅም ማሳመን እንጂ በሌላ አካል ወይም ጥላ ሥር ሕይወቱን እንዲመራ ለማድረግ ማሳበብ አይገባምና ነው፡፡

ቃል ግጥም 29፡- ዕርከን እሠራለሁ በጪት በማለዳ
ዐፈር ተሸርሽሮ በጎርፍ ሳይነዳ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው ሐሰን፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ደግሞ ታታሪነትን፣ ትጋትን፣ ጥረትን፣ ወዘተ ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም ግጥሙን የተናገረው ግለሰብ የዕርከን ሥራው ያለውን ጠቀሜታ አስቀድሞ የተረዳ በመሾኑ ወኔ በተሞላበት ስሜት በጣም ጧት በሾነ ወቅት ከቤቱ ወጥቶ የዕርከን ሥራውን እንደሚያከናውን በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ተናግሯል፡፡ ግለሰቡ ይህንን የሥራ ዕቅድ የወሰነው ደግሞ በዕርከን ሥራው ዋዜማ ምሽት ላይ መሾኑን “በጪት በማለዳ” የሚለው ሐረግ ይጠቁማል፡፡ ይህንን ሠናይ ተግባር ለማከናወን የተነሣሣውም በኃይለኛ ዝናብ አማካይነት በሚከሠት ጎርፍ የእርሻ መሬቱ ለም ዐፈር ተሸርሽሮ እንዳይወሰድበት ለማድረግ እንደሾነ ኹለተኛው ስንኝ ያስረዳል፡፡

5. 2. የግብርና ሥራ ዓይነቶች

አርሶ አደሩ በቅደም ተከተል የሚያከናውናቸውን የሥራ ዓይነቶች የሚወስነው ሥራዎቹ እንደሚከናወኑበት ወቅት ነው። ምክንያቱም ዋነኛዎቹ ሥራዎች ማረስ፣ ማረም፣ ማጨድ እና መውቃት ስለኾነ ወራቱን ተከትሎ የግብርና ሥራውን ያከናውናል። ሲዘንብ ኹለት ሦስት ጊዜ በማረስ ማሳውን ያለስልሳል፤ በመጨረሻም ዘሩን ይዘራል። ቀጥሎም ቡቃያውን በተደጋጋሚ ያርማል። ሰብሉ ከጎመራ በኋላም ሲደርቅ ያጭዳል። አንጉዞም በዐውድማ ላይ ይወቃል። ዑደትን ተከትለው የሚከናወኑት እነዚህ የሥራ ዓይነቶች ለቃል ግጥም መከወኛ ዓይነተኛ አጋጣሚዎች መኾናቸውን ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በአካል እየተገኘሁ ለማረጋገጥ ችያለሁ። በዚህ መሠረት አርሶ አደሩና ቃል ግጥሞች ጥብቅ ትስስር አላቸው ማለት ነው። ምክንያቱም ግጥሞቹ በእርሻ ሥራ የሚተዳደረውን አርሶ አደር የድካም ስሜቱን ያስወግዱለታል፤ ለሥራ ያነሣሡታል፤ ያበረታቱታል። ከዚያም አልፎ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሥራውን ሲያከናውን ያስተባብሩለታል። ስለኾነም በርካታ ፋይዳ ያላቸውን ቃል ግጥሞች አርሶ አደሮቹ በእርሻ፣ በዐረም፣ በዐጨዳና በውቂያ ወቅት ሲያዜሟቸው በዓይነ ኅሊናችን ቀጥለን እንመልከት።



ሥዕላዊ መግለጫ ኹለት፦ የግብርና የሥራ ዓይነቶችን የሚያመለክት

5.2.1. የእርሻ ወቅት

አርሶ አደሩ በዓመቱ ውስጥ ከሚያከናውናቸው የሥራ ዓይነቶች መካከል የመጀመሪያው በእርሻ አማካይነት ተገቢ የኾነ የማሳ ዝግጅት ማድረግ ነው። የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ግብርና ቢሮ (2012፡18) በገለጸው መሠረት አንድ አርሶ አደር የእርሻ ማሳውን በአማካይ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ማረስ ይኖርበታል። የመጀመሪያው ቀድሞ በማሳው ላይ የነበረው ሰብል እንደተነሣ ዐፈሩ እርጥበቱን ሳይለቅ የሚከናወን ነው። ኹለተኛው በበጋ ወቅት የሚከናወን ሲኾን፣ ሦስተኛው ደግሞ የክረምቱን የዝናብ ኹኔታ መሠረት አድርጎ ዘር በሚዘራበት ጊዜ የሚታረስ ነው። ለሰብል የሚፈለገውን ማሳ በድግግሞሽ ማረስ ያለው ጠቀሜታ ዐረምን ለመከላከል፣ ለዝናብ ውሃ ስርገት ምቹ ኹኔታን ለመፍጠር፣ አየርና ውሃ በውስጡ እንዲዘዋወር ለማድረግ፣ ለሰብሉ ምግብና ውልደት ምቹ ኹኔታን ለመፍጠር እንደኾነ ከላይ የተጠቀሰው ምንጭ በዝርዝር አስረድቷል። አርሶ አደሩ ከመጀመሪያው ዙር አንሥቶ ዘር እስከሚዘራበት ወቅት ድረስ የእርሻ ሥራውን ሲያከናውን የሚያሰማቸውን ትችትና መገሳ አዘል ወዘተ. ቃል ግጥሞች ቀጥለን እናያለን። ታዲያ ቃል ግጥሞቹ በሚዜሙበት ወቅት በሬዎቹ እንደ አድማጭና እንደተሳታፊ ይታሰቡ ይኾናል።

ቃል ግጥም 30፡- በጎምላላ በሬ ወርደው ታላረሱት
አይሞላም ጎተራ አጎንብሰው ቢያዩት።

(ቃለ መጠይቅ፣ ራህመት ማህሙድ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

አርሶ አደሩ ደጋግሞ በማረስና የተለያዩ ግብዓቶችን በመጠቀም ያዘመረውን አዝመራ በዐውድማ ላይ ከወቃ በኋላ በአቁማዳ እየሰፈረ ከእንጨትና ከጭቃ በተሠራ የእኽል ማከማቻ ወይም ጎተራ ሲያስገባም ኾነ ሌላ ወቅት ክዳኑን ከፍቶ የምርቱን መጠን አተኩሮ መመልከቱ የተለመደ ነው። ይህንን ድርጊት በተደጋጋሚ የታዘበ ግለሰብም ከላይ ባለው ቃል ግጥም ምክር አዘል ትችቱን አቅርቧል። በዚህ መሠረት በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ግለሰብ ሞፈርና ቀንበሩን በማዋደድ ሲኼዱ የሚጀነኑ ቅልብ በሮቹን በመጥመድ፣ ወጥቶና ወርዶ የእርሻ መሬቱን በተደጋጋሚ በማረስ የተትረፈረፈ ምርት ካላገኘ በስተቀር የጎተራውን ክዳን እየከፈቱ የእኽሉን መጠን ቢመለከቱት በምትሀት ካልኾነ በስተቀር ጎተራው ከአፍ እስከ ገደፉ ድረስ ጢም ብሎ ሊሞላ እንደማይችል ገጣሚው ምክሩን ለግሷል።

ቃል ግጥም 31፡- ማረስ ነው እንጂ እያሸረጡ
እንደ ሸርሙጣ ሳይለመጡ
እንደ እምቧጮ እንጨት ሳይለመጡ።

(ከቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

ያለ ዘይቤያዊ ቋንቋና ገለጻ፣ውበትና ማዝናናት የቃል ግጥሞች ውጤት ሊኖራቸው እንደማይችል Finnegan (1977:113-118) ገልጸዋል። በዚህ መሠረት የቃል ግጥሙ ገጣሚ በዘወትራዊ እይታ በማይመሳሰሉ ሦስት ነገሮች መካከል አንድ ተመሳሳይ የኾነ ገጽታን ፈልጎ ሐሳቡን ላቅ ባለ ደረጃና ውበት ለመግለጽ አነጻጻሪ ዘይቤን ተጠቅሟል። በመኾኑም በመጀመሪያዎቹ ኹለት ስንኞች አርሶ አደርና ሴተኛ ዐዳሪ “እንደ” በሚል ቃል ጎን በጎን

ተነጻጽረዋል። ምንም እንኳን ኹለቱም ከአንድ ጎራ የመጡ ሰብዓዊ ፍጡራን ቢኾኑም በተለያዩ ተግባራት ውስጥ ተሰልፈው የሚገኙ አካላት ናቸው። በግጥሙ ውስጥ ሴትኛ ዐዳሪዋ የቀረበችው በአመንዝራነቷ ወይም በሴሰኛነቷ አይመስለኝም። በባሕርይዋ አንድ ጊዜ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሌላው ጋር የምትኾን፣ በአንድ አቋም ላይ የማትረጋ መኾኗን ለማሳየት ነው። በዚህ ባሕርይዋ የአርሶ አደሩን ድርጊት አጉልታ ለማሳየት ሲባል አንጻሪ ኾና ቀርባለች። አርሶ አደሩ ደግሞ በእርሻ ሥራ ወቅት ከድካሙ የተነሣ አካሉ እንዳይለመጥ ወይም እንዳይብረከረክ በተነጻሪነት ተቀምጧል። ስለዚህ አርሶ አደሩ ድካም እንዳይሰማው ወገቡን በሽርጥ ደግፎ የሚይዝለትን አገልድሞ በጽናት የእርሻ መሬቱን በተደጋጋሚ ጠንክሮ እያረሰ ውጤታማ መኾን እንዳለበት ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል።

ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩና እምቧጮ የተነጻጸሩ ሲኾን፣ ኹለቱም ከተለያዩ ጎራዎች የመጡ ናቸው። ምክንያቱም አርሶ አደሩ ነፍስና ሥጋ ያለው የሰውን ባሕርይ የነሣ (የያዘ) ፍጡር ሲኾን፣ እምቧጮ ደግሞ የተክል ዓይነት ነው። ከባሕርይ አንጻር ስንመለከታቸው አራሹ ሰውነቱ በመድከሙ የተነሣ ዐቅም አጥቷል። እምቧጮውም ቢኾን ውስጡ ክፍት በመኾኑ ጥንካሬ አይኖረውም። ስለዚህ ከማገዶ በስተቀር ለሌላ አገልግሎት አይውልም ማለት ነው። በዚህ መሠረት ባሕርይው ጎልቶ እንዲወጣ የተፈለገው አርሶ አደር ተነጻሪ ሲኾን፣ እምቧጮው ደግሞ የተነጻሪውን ኹኔታ አግዝፎ የሚያሳይ በመኾኑ አንጻሪ ነው። በመካከላቸው ያለው የጋራ ባሕርይ ደግሞ ጥንካሬ ማጣት ነው። በመኾኑም ግለሰቡ በችግር የማይፈታ ጠንካራ ሰው መኾን አለበት እንጂ እንደ እምቧጮው መልፈስፈስ እንደሌለበት ግጥሙ ያስረዳል።

ቃል ግጥም 32፦ ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ
ሚስቱን አይላትም ቃጤ ተበደሪ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ራህመት ማህሙድ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር በተሰማራበት የእርሻ ተግባር ጠንካራ፣ ታታሪና ትጉህ በመኾኑ በቀረርቶ ስልት ራሱን ሲያሞግስ ይሰማል። ለሙገሳውም ምክንያት የኾነው በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሮቹን ጠምዶ “ሳብ፣ ና ውጣ፤ ና ውረድ” በማለት የማነቃቂያ ድምፅ እያሰማ፣ ጅራፉን ከላያቸው ላይ ሾጥ፣ ሲያስፈልግም ገረፍ እያደረገ ማሳውን ያርሳል። እንደዚሁም ከዚህ በፊት ታርሶ የማያውቀውን ድንግል መሬት ወይም በርከት ላሉ ዓመታት ሳይታረስ የቆየውን ማሳ ያለማል። በተጨማሪም በተለያዩ ውለታዎች ማለትም በኪራይ፤ በእኩል፣ በሚሶ ወይም በእርቦ በመስማማት ሌላ ሰው እንዲያርስለት ያደርጋል። በእነዚህ የተለያዩ መንገዶች ከታረሰው መሬት ታታሪው አርሶ አደር የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ

ችሏል። በዚህ መሠረት የትዳር ጓደኛው ለምግብ ፍጆታ የሚውል እኽል ስለማይቸግራት ከባለ ሀብት ከቁና ባነሰች ለመስፈሪያ ወይም ለመለኪያ በምታገለግል አነስተኛ የስፌት ዕቃ ተጋደሽ ወይም ተበድረሽ ተጠቀሚ ብሎ አይነግራትም ማለት ነው።

ቃል ግጥም 33፡- በሚያዝያ በግንቦት እርሻ ዋዛ ነው ወይ
አቧራው በጥፊ ይማታ የለም ወይ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አማን ሁሴን፤ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ምንም እንኳን ስንፍና ከልዩ ልዩ ተግባራት ጋር የተያያዘ ቢሾንም ጥናቱ በተካኼደባቸው አካባቢዎች በእርሻ ተግባር ላይ ከተሰማሩት አርሶ አደሮች መካከል በስንፍና የሚተች ግለሰብ መኖሩን ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ያመለክታል። እንደሚታወቀው ጠንካራው አርሶ አደር ከጥዋት እስከ ማታ ዝናብና ፀሐይ ሳይፈራ፣ ብርድና ነፋስ ሳይበግረው ያርሳል። በዚህም አጥጋቢ ምርት ያገኛል። ለሰነፉ አርሶ አደር ግን ደረቅና ፀሐያማ በሾነው ሚያዝያ ወር ማረስ ቀላል አለመሾኑን የቃል ግጥሙ ደርዳሪ ተሳልቆበታል። ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ ሰው ፀሐይ ፈርቶ በየጥላው እየዋለ ጊዜውን በአልባሌ ቦታ ያሳልፋልና ነው። ግንቦት ወር ደግሞ ከወራቱ ሁሉ ሐሩሩ የጠነከረበት፣ በኃይል የሚንቀሳቀስ ነፋስ የሚከሠትበት ወቅት ነው። ደስታ ተክለ ወልድም (1962፡281) "አየሩ ተስማሚ ስላልሾነ ጋብቻ በግንቦት ወር ክልክል ነው" ብለዋል። ገጣሚውም ቢሾን በግንቦት ወር የሚከሠተውን ከፍተኛ አቧራ ልክ እንደ ሰው አእምሮን የሚጠይቅ ተግባር እንዲፈጽም አድርጎታል። የሰውን ባሕርይ የተላበሰው አቧራም ሰነፉን ገበሬ በጥፊ (በውስጠ እጅ በትር) የሚያጠናግረው መሾኑን ገልጿል። ስለሾነም ይህ ወር በእርሻ ተግባር ለተሰማራ ሰነፍ ሰው ቧልት ወይም ቀልድ አለመሾኑን ገጣሚው በትችት መልክ አቅርቧል።

በሌላ በኩል ደግሞ በመስከረም 05/2013 ዓ.ም በከለላ ወረዳ ከተካኼደው የቡድን ተኮር ውይይት ተጨምቆ የቀረበው መረጃ የሚያመለክተው የእርሻ ወቅት ለትችት አዘል ቃል ግጥም መነገር ሰበብ መሾኑን ነው። ይህንኑ ሁኔታ ቀጥሎ እንመልከት። እስከ ዐሜ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ አባትና እናት ልጆቻቸውን ሲድሩ ጎጆ መውጫ ብለው ትንሽ የእርሻ መሬት ቆርሰው ይሰጧቸው ነበር። አለበለዚያም ልጆቹ አርሰው ካገኙት ምርት ሦስት እጁን ለወላጆቻቸው ሰጥተው የቀረውን ለራሳቸው እንዲጠቀሙ ይደረጉ ነበር። በደርግ የአስተዳደር ወቅት ደግሞ ልጆች ሲወለዱ የተወሰነ፣ ከዚያም ሲያገቡ ‹‹ለባለትዳር›› በሚል ዝቅተኛውን የመንግሥት መዋቅር በያዙት የቀበሌ አመራሮች መሬት ተከፍሎ ይሰጣቸው ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በመንግሥት በኩል መሬትን የማከፋፈል ሕግ ስለሌለ ትዳር

መሥርቶና ልጅ ወልዶ የሚያርሰው መሬት የሌለውን ወጣት ማየት አዲስ ነገር አይደለም። በዚህ የተነሣም ወጣቱ ቀዬውን ትቶ አንድም ወደ ውጭ ሀገርና ወደከተማ ይሰደዳል። አለበለዚያም የወላጆቹን መሬት አርሶ ከሚያገኘው ምርት አንድ ሦስተኛውን ብቻ ለራሱ አስቀርቶ ሌላውን ለእነሱ በመስጠት ላይ ይገኛል።



ፎቶግራፍ ሦስት፡- በ05/01/2013 ዓ.ም በከለላ ወረዳ የተካኼደውን ቡድን ተኮር ውይይት የሚያመለክት

ይህ ከላይ ያለው መረጃ ለቃል ግጥም የመከወኛ መልካም አጋጣሚ በመኾኑ ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ቀጥሎ ያለውን ቃል ግጥም በመጠቀም በመንግሥት ላይ ምፀታዊ ግጥሙን አቅርቧል።

ቃል ግጥም 34፡- ተሰፈረች አሉ መሬት በቀበቶ
ወጣት ሆድ የለውም የሚል ዳኛ መጥቶ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ጀማል፣ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

እንደሚታወቀው በገጠሩ የኅብረተሰብ ክፍል የእርሻ ማሳ ሲከፋፈል የሚጠቀመው መለኪያ ረዥም ገመድ ነበር። በአሁኑ ወቅት ባለው የሕዝብ ብዛት ግን በቀበቶ የተመሰለችና በጣም አነስተኛ በኾነች መስፈሪያ የተለካች መሬት ናት ለወጣቱ ተከፋፍላ የተሰጠችው። ይህ የሚያመለክተው ደግሞ ወጣቱ እንደማይበላና እንደማይጠጣ ተደርጎ በመቆጠሩ ብያኔ ለመስጠት ሥልጣን ባላቸው የቀበሌ ባለሥልጣናት አማካይነት ይህ ወገን መሬት አልባ እንዲኾን መደረጉን ግጥሙ ያስረዳል። ስለሆነም ፍትሓዊነት በጎደለው አሠራር ሠርቶ ያልጠገበው፣ ዕድሜው ከዐሥራ ስምንት እስከ ሠላሳ ዓመት የሚኾነው የኅብረተሰብ ክፍል የመሬት ባለቤትነት ተነፍጎት ሕይወቱን እንደሚገፋ ቃል ግጥሙ ያመላክታል።

5.2.2 የአረም ወቅት

ዐረም ከእኽል ጋር አብሮ የሚበቅልና አስፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ወሳኝ በኾነ ወቅት ተነቅሎ የሚጣል የዕፅዋት ዓይነት ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1993፡308)። በ07/01/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ በቡድን ተኮር ውይይቱ ከተሳተፉት መረጃ ሰጪዎቹ ባገኘሁት መረጃም ማንኛውም አርሶ አደር በሰብሉ ላይ የሚገኘውን ዐረም በእጅ ለማስወገድ ተገቢነት ባለው ኹኔታ በድግግሞሽ ማረም ይኖርበታል። ድግግሞሹ የሚከናወነውም አንደኛ፡- ሰብሉ ከበቀለ ከዐሥራ አምስት ቀናት በኋላ፣ ኹለተኛ፡- ከሦላሳ አምስት ቀናት በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ እንደኾነ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ከመስከረም 04 - 9/2013 ዓ.ም ባሉት ቀናት በነበረው የመስክ ቆይታዬ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ያገኘሁት መረጃ የሚያረጋግጠው በድግግሞሽ የሚከናወነው የዐረም ዐውድ ለቃል ግጥም መከወኛ ምቹ አጋጣሚ መኾኑን ነው። ይህንን በተመለከተ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

ቃል ግጥም 35፡- ምነው በበዓል ቢያርሱ፣ ቅዳሜ ቢያርሙ
ከባለጸጋው ደጅ ኼዶ ከመቆሙ
ቸግሮኛል ብሎ ሰው ፊት ከመቆሙ።
(ቃለ መጠይቅ፤ ዘይነባ አህመድ፣ 07/01/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው ማኅበረሰብ በሚከተለውና ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ በመጣው ልማድ መሠረት "አዝመራችንን በረዶ ይመታብናል፤ ጎርፍ ይወስድብናል" በሚል እምነት በሳምንት ውስጥ በግብርና ሥራ ላይ የማይሰማራባቸው ቀናት አሉ። ከዚህ በተጨማሪ በአካባቢው ያሉ አባጋሮች[21] ቀድመው እርሻ ማረስ ካልጀመሩ አርሶ አደሮቹም አንዳንድ ጊዜ የእርሻ ሥራቸውን የማይጀምሩበት ኹኔታ መኖሩን ከመስከረም 05 — 09/2013 ዓ.ም ድረስ ከተካኼደው የቡድን ተኮር ውይይት ተጨምቆ የቀረበው ሐሳብ ያስረዳል። በተለይ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖት በሥራ ባህል ላይ የሚያሳድረውን ጫና በተመለከተ ዋጋው ኃይሉ (2001፡20-21) የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸዋል። "አንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከሦላሳ ቀናት ውስጥ ቅዳሜንና እሑድን ጨምሮ በትንሹ ዐሥራ አንድ ቀናትን ያለ ሥራ እንዲያሳልፍ ወይም እንዲያከብር ይጠበቃል። እነዚህም ቀናት ለልዩ ልዩ ሰማዕታት፣ ዛድቃን፣ መላእክት፣... መታሰቢያነት የተመደቡ ናቸው።" በዚህ መሠረት እነዚህ

[21] አባጋር የኦሮምኛ ቃል ሲኾን ትርጉሙም የሰላም አባት፤ የሰላም መሪ ማለት ነው። አባጋሩ በአካባቢው ኅብረተሰብ የሚመረጥ ሲኾን፣ የመመረጫ መስፈርቱም በዕድሜ የገፋ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ሻል ብሎ ሰው ሠራሽም ኾነ የተፈጥሮ አደጋ በሚያጋጥምበት ወቅት ነዋሪውን በማስተባበር ለዱዓ (ለጸሎት) ውጡ የሚል፣ የተጣሉ ሰዎችም ካሉ ሊያስታርቅ የሚችል ሰው መኾን አለበት። አልፎ አልፎም የአባጋርነት ማዕረግ በዘር ሊተላለፍ ይችላል (ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ፣ 22/05/2012፣ወግዲ ወረዳ።

ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በምርታማነት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ስለሽነም ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም የተናገረው ገጣሚ ሐዘንና ጸጸት በተሞላበት ቃል “ምነው” በማለት ከባለ ሀብት ቤት ኼደው በመገተር አጣሁ፤ ተራብኩ፤ ደኸየሁ፤ እልሰው እቀምሰው አጣሁ እያሉ መለማመጥ፣ መለመንና የሰው ፊት ማየት እጅግ በጣም አሳፋሪ ድርጊት መኾኑን ይገልጻል፡፡ ከዚህ ይልቅ ማንኛውም አርሶ አደር ቅዳሜን ጨምሮ በሳምንት ውስጥ ሥራ የማይሠራባቸውን እና ታርፎ የሚዋልባቸውን የበዓል ቀናትን ሸሮ (ገድፎ) ሳይታክትና ሳይደክም እርሻ አርሶ፣ ከቡቃያ ውስጥ የሚገኙትን ቅጠላ ቅጠልና ሣርን ዐርሞ አጥጋቢ የኾነ ምርትን ማግኘት ከሰው ፊት ከመቆም እንደሚያድን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ማንኛውም አርሶ አደር እሾኽ፣ ብርድና ድካም ሳይበግረው ጠንክሮ በማረም ራሱን መቻል እንደሚገባው ገጣሚው ይናገራል፡፡

ቃል ግጥም 36፡- አረሙን እንረም በርትተን በለጋው
ቢያድግ አይደለም ወይ እሾኽ የሚወጋው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙራድ ገበየሁ፤ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ዐረም ወሳኝ በኾነ ወቅት ሳይታረም ቀርቶ እጅግ በጣም ከጠነከረ ቡቃያውን እንደሚጎዳ፣ በዚህ የተነሣም የሰብሉ ምርት እንደሚቀንስ፣ አርሶ አደሩም ቢኾን ዐረሙን በእጁ ነቅሎ ለመጣል እንደሚቸገር ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው አርሶ አደርም ከእኽል ጋር ዐብሮ የሚበቅለውን የዐረም ዓይነት ሳይጠነክር ገና በለጋው ጠንክረን በማረም ማስወገድ አለብን በማለት በእርሻ ሥራ ለሚተዳደሩት አርሶ አደር ጓደኞቹ ምክሩን ለግሷል፡፡ ይህ ካልኾነ ግን ለችግር እንጋለጣለን የሚለውንም ሐሳብ ለማስገንዘብ “የሚዋጋ እሾኽን” በማንጸሪያነት ተጠቅሟል፡፡ ስለኾነም ቁመቱ ያደገ እሾኻማ ተክል የሰውን አካል ወግቶ ጉዳት ላይ የሚጥለው በመጠንከሩ የተነሣ ነው፡፡ ስለዚህ ዐረሙ አዝመራችንን ሳይጎዳ በቀንበጡ እያረምን ማስወገድ አለብን በማለት ገጣሚው በቋጠራቸው መንቶ ስንኞች አማካይነት መሠረታዊ ሐሳቡን ሊያስተላልፍ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቃል ግጥሙ ውስጥ የተመሠጠረ ሐሳብ ያለ ይመስለኛል፡፡ ይኼውም በዐረም የተመሰለውን የሕፃናት እኩይ ባሕርይ እንዲስተካከልና ጥሩ እንዲኾን ገና ከእንጭጩ (ከጅምሩ) መግራት ይገባናል፡፡ ችግሩ ከጠነከረ በኋላ ግን ለማቃናት የሚያስቸግር መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝበናል፡፡

ቃል ግጥም 37፡- ዐረሙን ዐርሚው በኹለት እጆችሽ
እነ ማን ዋሉበት ታሠኝኛለሽ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አያሌው ሰይዱ፣ 19/05/2012/ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ያሉት ስንኞች የተገነቡባቸው ቃላት ጥንቃቄ የጎደለው ሥራ መሥራት ስምን እና ክብርን ሊያጎድፍ እንደሚችል ያመላክታሉ። በመኾኑም ገጣሚው በዐረም ሥራ አብራው ለተሰለፈችው የትዳር ጓደኛውም ትኹን ሌላ ሴት ሣርና ቅጠላ ቅጠሉን ከቡቃያው ውስጥ በኹለት እጆችሽ ከሥሩ ነቅለሽ ጣይ፤ ጥራት የጎደለው ሥራም እንዳትሠሪ። በተዝረከረከ ኹኔታ የምትሠሪው ሥራ የትኞቹ ሰዎች ናቸው ቀኑን ሙሉ በእዚህ በተበላሸ ሥራ ላይ የዋሉት ተብሎ በክብረ ነክ ስሜ እንዲጠራ ታደርጊኛለሽ በማለት ሥጋቱን ገልጿል። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ደግሞ ማንም ሰው ቢኾን በመጥፎ ተግባር ክብሩ እንዲደፈር የማይፈልግ መኾኑን ያስገነዝበናል።

ቃል ግጥም 38፡- ዐረምን ያረመ ጤዛውን ሳይፈራ
እንኳን ለሆዱና ይሞላል ጎተራ።
(ቃል ግጥም፣ ዘይነባ ይማም፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በክረምት ወራት አርሶ አደሩ በዕለት ተዕለት የእርሻ ተግባሩ በተለያዩ አስቸጋሪ ኹኔታዎች ይፈተናል። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥም እንደምንመለከተው ከእነዚህ አስቸጋሪ ኹኔታዎች መካከል አንደኛው በሣርና በቅጠላ ቅጠል ላይ ጢት ጢት ወይም ዝናም ከዘነበ በኋላ ተንቀርዞ በሚወርድ የውሃ ጠብታ ወይም ጤዛ በዐረም ወቅት የአርሶ አደሩ የእጅና የእግሩ ቆዳ ከመቆርፈዱም አልፎ ስንጥቅ ያወጣል። ይህንን የከፋ ችግር ተቋቁሞ በአስፈላጊው ወቅት ከቡቃያው ውስጥ አረሙን ያረመ አርሶ አደር የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ እንደሚችል ገጣሚው ያመላክታል። ስለዚህ የአየር ጠባዩ ያልበገረው አርሶ አደር አረሙን አርሞ ባገኘው አጥጋቢ ምርት ያለ ምንም ሠቀቀን ራሱንም ኾነ ቤተሰቦቹን በየቀኑ ይመግባል። ከዚያም አልፎ ጎተራውን ከአፍ እስከ ገደፉ ድረስ ጢም አድርጎ ሊሞላ እንደሚችል ቃል ግጥሙ አንጸባርቋል።

ቃል ግጥም 39፡- ዐረም ለምነኸኝ ከጎንህ ዋልኩኝ፣
ባይኔ ስላየሁህ በደኅና ከረምኩኝ።
ሐምሌና ነሐሴ ለኔ ምኔ ነው
ይምጣልኝ መስከረም የሚያገናኘው።
(ከቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች አንድ ሰው ብቻውን መሥራት የማይችላቸውን የግብርና ሥራዎች (የእርሻ፣ የዐረም፣ የዐጨዳ፣ የውቂያ፣ ወዘተ. ተግባራት) በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ዋነኛ የመደጋገፊያና የመረዳጃ ሠናይ ተግባር ደቦ መኾኑን በማኅበረ ባህላዊ ዳራ ላይ ተገልጿል። በተለይም ዐረሙ በጣም አስቸጋሪ የኾነበት ሰው ከቤቱ ድግስ ከደገሰ በኋላ

ዘመድ አዝማዱን በመሰብሰብ በደቦ እንዲያስተራርሙት ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች የሚቀርባቸውን ሰዎች በመለመን እና በወንፈል አማካይነት አዋኪ የሽነውን የዐረም ሥራ ያከናውናል። በደቦ፣ በወንፈልና በልመና የተሰማሩት ዐራሚዎችም በኅብረት ሲያርሙ ፍጥነታቸውን ለመጨመር፣ ድካም እንዳይሰማቸው ለማድረግና ሞራላቸውን ለማነቃቃት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህ ዘዴዎች መካከል የፍቅር ዘፈኖች ይገኙበታል።

ከላይ ባለው የዘፈን ግጥም ውስጥ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ሹለት ስንኞችም ይህንኑ ሐቅ ያረጋግጣሉ። ስለሽነም ዐረም አስተራርሚኝ ተብላ የተለመነችው ሴት ልጅ ከተለየችው ወይም ከናፈቀችው ሰው ጋር በአካል ለመገናኘት መብቃቷን ትናገራለች። ቀጥላም በቀኝህ ወይም በግራህ በኩል ሾኜ ከጪት እስከ ማታ ድረስ ዐብሬ በመዋል የፍቅር ናፍቆቴን ተወጣሁ። ይህ ለእኔ መልካም አጋጣሚ ስለነበር የክረምቱን ወራት በደህና አሳለፍኩ በማለት ገልጻለች። በእሱ በኩል ግን ምላሽ ሲሰጣት አይደመጥም። እንደሚታወቀው ሐምሌና ነሐሴ በይበልጥ የእርሻ ተግባራት የሚከናወንባቸው ወራት ናቸው። የእርሻ ተግባራት ደግሞ በወንዶች የሚከናወን በመሆኑ ልጃገረዶች ከከንፈር ወዳጆቻቸው ጋር ያን ያክልም የመገናኘት ዕድል የላቸውም። ለዚህም ነው ሐምሌና ነሐሴ የተባሉት ወራት ለእሷ ምኗም እንዳልሆኑ የተናገረችው። በአብዛኛው ዐረም የሚታረምበት ወቅት ግን የመስከረም ወር በመሆኑ አቀንቃኟ ከናፈቀችው ፍቅረኛዋ ጋር በአካል የሚያገናኛት ይሄው ወር በተደጋጋሚ እንዲጠባላት (እንዲመጣላት) በመጨረሻው ስንኝ ላይ አጥብቃ ተማጽናለች።

ቀደም ሲል በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ የቃል ግጥሞች በወንድም ሽነ በሴት ሲዜሙ አስተውለናል። አብዛኛውን ጊዜ ግን በልጃገረዶች ብቻ የሚዜሙት የቃል ግጥሞች ያሉ ሲሽን፣ ይዘታቸውም ስለከንፈር ወዳጅ ፍቅር የሚያንጸባርቁ ናቸው። የየስንኞቹ ርዝማኔም ቢሽን በጣም ቀልጠፍጠፍ ያሉ ሽነው ይታያሉ። በሌላ የዘፈን የመከወኛ አጋጣሚ ላይ እምብዛም የማይደመጠው “የእዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ” ዜማ በአረም ወቅት ዋነኛው የልጃገረዶች ማዜሚያ ሽኖ ይቀርባል። “የእዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ” ዜማ በአረም ወቅት ተመራጭ የሽነው ለእንቅስቃሴያቸው ምቹ በመሆኑ የተነሣ ነው። በዚህ ጊዜ ሴቶቹ ቀኝም ሆነ ግራ እጆቻቸው በዐረም ተግባር ላይ ስለሚጠመዱ ዐታሞ የመያዝ ዕድል የላቸውም። ጎረምሳዎቹ ግን “ሆ” ባይሉም ባንድ በኩል ጎን በጎን ሽነው ያለ ምንም የእግር እንቅስቃሴ እንዳመችነቱ በድምፅ ብቻ ሊጨፍሩ ይችላሉ።

ምንም እንኳን በዐረም ወቅት በልጆገረዶቹ የሚዘፈነው ቃል ግጥም በከንፈር ወዳጅ ፍቅር ላይ የሚያተኩር ነው ቢባልም ወቅታዊ ኹነትን የሚያንጸባርቅ ግጥምም በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ሊገኝ ችሏል። ይኽውም ከሚሊኒየሙ ዋዜማ ጀምሮ ወጣቶቹ ለሥራ ወደ ዐረብ ሀገራት መኼዱን እንደ ፋሽን (ጊዜ አመጣሽ ድርጊት) ይቆጥሩት ስለነበር ልጃገረዶቹም አረማቸውን እያረሙ የሩቅ ናፋቂነታቸውን እንዲህ በማለት አንጎራጉረዋል።

ቃል ግጥም 40፡- የእዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
የእዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ } ኹለት ጊዜ

ውልጮ አፋፍ ኾኖ ይታያል ታች ሚዳ
“ኢቃማ” ላክልኝ እንዲመጣ ጂዳ።
ይሄ ጂዳ ማለት በየት ነው መንገዱ
ወበሎ እነጫለሁ ጓደኞቼም ኼዱ።
አንተ የገብስ ወበሎ ኺድልኝ ከፊቴ
ቀልቤ ዱባይ ገብቷል ተባሮ ከቤቴ
የዱባይ ብርድ ልብስ ሲለብሱት ይሞቃል
ዕድል ቁራኛ ነው መች ቶሎ ይለቃል።
ዕድልን ቢወቅሡት ‹‹ሪያል›› አይኾንም
በቃጤ ሽምቼ ሚሶ አርሼ አልኖርም።
በሮችህን ሸጠህ ተው አባቴ ላከኝ
ላከኝ ግዴለህም አከብርሃለሁኝ።
ዝናቡን ሸሽቼ ቆሜያለሁ ከታዛ
አልቀርም ዘንድሮ ስደድልኝ ቢዛ (ቪዛ ለማለት ነው)።

(ቃለ መጠይቅ፣ ሰይድ ጎቸል፣02/06/2012 ፣ ቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ውልጮ የተባለው አካባቢ የቦረና ወረዳ ርእሰ ከተማ ከኾነችው ከመካነ ሰላም በስተምሥራቅ አቅጣጫ በአሻጋሪ የሚገኝ ቦታ ነው። ታች ሚዳም እንደዚሁ ከውልጮ በስተምሥራቅ አሻጋሪ ላይ ይገኛል። የእነዚህ ኹለት አካባቢዎች በስንኙ ውስጥ የመገኘት ፋይዳ ከቦረና ተነሥቶ በጎጃም አድርጎ ወደአዲስ አበባ መጓዝ ከመጀመሩ በፊት ከቦረና በደሴ በኩል ተደርጎ ወደአዲስ አበባ ይኼድ የነበረው እነዚህን ኹለት ቦታዎች በማቋረጥ ስለነበር የዱባይንም አቅጣጫ በዓይነ ህሊና ለማመልከት በማሰብ ይመስላል። የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የኾነችው ልጃገረድ ቀድሞ ጂዳ የኼደውን ዘመድም ኾነ የከንፈር ወዳጇን “ኢቃማ” የተባለውን የዐረብ ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ እንዲልክላት ትጠይቃለች፤ አሁን ባለችበት ወቅትም ግራ ተጋብታለች። ምክንያቱም ጂዳ የምትጓዝበት የመንገዱ አቅጣጫ ጠፍቶባት ሳይኾን ለየብስም ኾነ ለአየር ትራንስፖርት የሚውል ገንዘብ በማጣቷ የተነሣ ነው። ይህ በመኾኑም ብር ያላቸው ጓደኞቿ ወደዐረብ ሀገር ሲኼዱ እሷ ግን ከእኽል ውስጥ ወበሎ የተባለውን ዐረም እያረመች እንደኾነ ገልጻለች።

ግጥሙን የምታዜመው ልጃገረድ “ቀልቤ ዱባይ ገብቷል ተባሮ ከቤቱ” በሚለው ስንኝ ውስጥ ቤቷን እንደ ዐጸደ ሥጋ ቆጥራለች። በመኾኑም በመንፈስ ልቧን ከዐጸደ ሥጋዋ አውጥታ ዱባይ ወደተባለው የዐረብ ከተማ ስለላከችው ሀገር ቤት ውስጥ ያለውን የዐረም ሥራ ተረጋግታ ለማረም አልቻለችም፤ አንገሽግሿታል። ስለኾነም የሰውኛ ዘይቤን የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ተግባራዊ በማድረግ በገብስ ውስጥ የሚገኘውን የወበሎ ዐረም “ኪድልኝ ከፊቱ” በማለት ስታመናጭቀው ትደመጣለች። ውስጠ ወይራ በኾነ አነጋገርም “የዱባይ ብርድ ልብስ ሲለብሱት ይሞቃል” በሚለው ስንኝ ከዱባይ የሚገኘው ገንዘብ ከፍ ያለ ስለሚኾን የደስታ ስሜትን እንደሚያጎናጽፍ ገልጻለች። ይህን ዓይነቱን ደስታ እሷም እንዳትጎናጸፍ ዐብሯት የሚኖረው ዕጣ ክፍሏ በቀላሉ የማይለቃትና ዐብሯት የሚኖር ቁራኛ በመኾኑ ቶሎ ሊወገድላት እንደማይችል በቃል ግጥሙ ገልጻለች።

ይህ ዐብሯት የሚኖረው የዐርባ ቀን ዕድሏም “ሪያል” የተባለውን የዐረብ ሀገር ገንዘብ ሊኾን እንደማይችል በመገንዘብ የተሰማትን የሐዘን ስሜት በምሬት ይፋ አድርጋለች። ሀገር ቤትም እያለች ከቁና አነስ ባለች የስፌት ዕቃ እኽልን እየሰፈረች ወይም እየለካች ከገበያ በመግዛት፣ እንደዚሁም ከሰው ጋር በመዋዋል አርሳ፣ አርማ፣ አጭዳና ወቅታ ካመረተችው ምርት ሦስት አራተኛውን ለባለመሬቱ ሰጥታ አንድ አራተኛውን ደግሞ ለራሷ አድርጋ በመጠቀም መኖር እንደማትችል አስረድታለች። ይህ ኹኔታ ደግሞ ልጃገረዲ ሰማይ ተደፍቶባት የምታደርገውን ያጣች መኾኗን ያመላክታል፡ ከዚህ የችግር አረንቋ መውጣት የምትችለው በኹለት ዓይነት መንገዶች መኾኑን ያሰናሰነቻቸው ስንኞች ይጠቁማሉ።

ከእነዚህ መንገዶች አንደኛው ወላጅ አባቷ ሲኾኑ፣ እሳቸውም ጥማድ በሬዎቻቸውን ሸጠው የሚየገኙትን ገንዘብ ለእሷ መጓጓዣ እንዲሰጧት ተማጽናለች። ዐረብ ሀገር ከኼደች በኋላም ሠርታ ከምታገኘው ገንዘብ እየላከች አባቷን ሀብታም እንደምታደርጋቸውም ቃል ገብታለች። በሌላ በኩል ግን ወላጆች የእርሻ መሬታቸውን በዐራጣ ወይም በከፍተኛ የወለድ መጠን ገንዘብን ለሚያበድር ሰው በማስያዝ ልጆቻቸውን ሲልኩ እንደነበር፣ በአጋጣሚ ልጆቹ ዐረብ ሀገር እንደደረሱ ወዲያውኑ ታስረው ሲመለሱ ቤተሰቦቻቸው ለከፋ ችግር ሲጋለጡ እንደነበር አቶ ሰይድ ጎቸል (የቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የካቲት 01/2012) አስረድተውኛል። በመጨረሻም “ዝናቡን ሸሽቼ ቆሜያለሁ ከታዛ” በሚለው ስንኝ ውስጥ የግጥሙ አቀንቃኝ የኾነችው ልጃገረድ ዝናብን በችግር በመመሰል መፍትሔ በማፈላለግ ላይ መኾኗን አመላክታለች። ከዚያም ከችግሬ ማጥ ውስጥ እወጣበታለሁ ብላ ያሰበችው ኹለተኛው መንገድ ደግሞ ቀደም ሲል ጂዳ የኼደው ዘመዷም ኾነ የከንፈር ወዳጇ ነው። በዚህ መሠረት

ግጥሙ በቀረበበት ዓመት ፍጹም ከጉዞዋ ልትቀር እንደማትችል ለእሱም ከገለጸች በኋላ ቪዛ (የይለፍ ወረቀት) እንዲልክላት በመንፈስ ስትጠይቀው በዓይነ ኅሊናችን እናያታለን።

5.2.3 የአጨዳ ወቅት

በግብርና ሥራ የሚተዳደረው ሰው አርሶ ከዘራና ካረመ በኋላ ቀጥሎ የሚያከናውነው ተግባር ዐጨዳ ነው። ሰብሉ ለመታጨድ ደርሷል የሚባለውም የገረጣ መልክ ሲኖረው እንደኾነ በቃለ መጠይቅ ወቅት ያገኘሁት መረጃ ያመላክታል። በዚህን ጊዜ በእጅ ወይም በማጨጃ መሣሪያ የማጨዱ ተግባር ይከናወናል። እስካሁን ድረስ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮች በእጃቸው እንጂ የቴክኖሎጂ ውጤት የኾነውን የማጨጃ መሣሪያ የማይጠቀሙ መኾኑን በዓይነ ሥጋዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። የዐጨዳው ተግባር የሚከናወነውም በግል፣ በጥንድና በቡድን ሲኾን፣ በሥራው ላይ የሚሰማሩትም ወንዶች ብቻ ናቸው። ሴቶቹ ግን የጤፍ አጨዳ ከኾነ በመደንከል ተግባር ላይ ይሳተፋሉ፣ የስንዴ ከኾነ ደግሞ ነዶውን ይሰበስባሉ። የአጨዳ ወቅት ለቃል ግጥም መከወኛ ማለፊያ አጋጣሚ በመኾኑ ወንድ አርሶ አደሮች ታታሪነትን፣ ሙገሳን፣ ትችትን፣ ምክርን፣ ወዘተ. በቃል ግጥም በማዜም ይገልጻሉ። በምሳሌነትም የሚከተሉትን ቃል ግጥሞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 41፡- ማጭዱ ስለት ቅጠለ በላ
ቆርጦ አስቀማጭ ክንዱ ሳይላላ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አብዱ ሙሐመድ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

አርሶ አደሩ ሰብሉ የገረጣ መልክ ሲኖረው ለመታጨድ የደረሰ መኾኑን ስለሚያውቅ አስቀድሞ የማጨጃ መሣሪያዎቹን ያዘጋጃል። ዝግጅቱም አንድም “ሀልቤን” የተባለውን የፋብሪካ ውጤት ከገበያ በመግዛት፣ አለበለዚያም ከቤት ያለውን የሐበሻ ማጭድ በአካባቢ በሚገኙ በሀገር በቀል የብረት ሠራተኞች በጥንቃቄ በማሠራት ነው። ከዚያም በተባ ማጭድ የአጨዳ ተግባሩን ያከናውናል። ይህ በመኾኑም ነው ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም ያዜመው አርሶ አደር ኃይልና ጥንካሬ ሳያጣ ወይም ሳይደክም በባለሙያ በተሠራ የሰላ ማጭዱ ሰብሉን በፍጥነት እያጨደ ማስቀመጥ የቻለ መኾኑን በፉከራ ስልት ታታሪነቱን የገለጸው። እዚህ ላይ በፉከራ ስልት የተባለው በኹለት ዓይነት መንገድ ነው። አንደኛው አርሶ አደሩ ማጭዱን የያዘበት የቀኝ እጁና ሰብሉን የጨበጠበት የግራ እጁ በጣም ፍጥነት ስለሚኖራቸው የቃል ግጥሙም አከዋወን ፍጥነት ይስተዋልበታል። ኹለተኛው ደግሞ Okpewho (1992:127) ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ወቅት ሊመደቡ ይችላሉ ብለው በገለጹት መሠረት የፉከራ ቃል ግጥሞችም በአጨዳ ተግባር ጊዜ ሊዜሙ ይችላሉና ነው።

ቃል ግጥም 42፡- አልቤኑ ስለት ሰውዬው ደፋር
ይከምረዋል ነዶን እንደ ዐፈር፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አብደላ መኮንን፣ 19/05/2012) ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥም እንደ ጽሑፋዊ ግጥም ሁሉ የቃላቱ ኃይልና ውበት የሚገለጸው በዘይቤዎች አማካይነት ነው፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ባሉት መንቶ ስንኞችም ያሉት ቃላት በአነጻጻሪ ዘይቤ የተገነቡ ናቸው፡፡ በመኾኑም ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ምስልን ስለሚከሥት ከአምስቱ የስሜት ሕዋሳት መካከል በዓይነ ሥጋችን ያላየነውን ድርጊት ወይም ኹኔታ በዓይነ ኅሊናችን እንዲናየው በማድረግ የሚተላለፈውን ሐሳብ ልብ እንዲንልና እንዲንገነዘብ አድርጎናል፡፡ በዚህ መሠረት በግጥሙ ውስጥ “ሰውዬው” የተባለው ታታሪ አርሶ አደር አልቤን በተባለው የሰላ ማጭድ ያጨደውን ሰብል ኹለት ሦስት ጭብጥን በአንድ አድርጎ በማሰር አንዱ በአንዱ ላይ አነባብሮ እንደከመረው ወይም እንደቆለለው ገልጿል፡፡ ይህንን ሐሳብ ፍንትው አድርጎ ለአድማጭ ያቀረበው የተከመረውን ነዶ ከዐፈር ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ ስለዚህ በቃል ግጥሙ ውስጥ የተነጻጸሩት ነገሮች ማለትም የሰብሉ ነዶ እንደ ወርቅ (ተደብቆ፣ ተሸፍኖ፣ ወዘተ. የሚነገር ውስጠ ምሥጢር)፣ ዐፈሩ ደግሞ እንደ ሰም ኾነው አገልግለዋል፡፡ ወርቁን እና ሰሙን የሚያመሳስላቸው ድርጊት ወይም ኹኔታ ደግሞ የእኽሉ መከመር፣ መቆለል ነው፡፡ በአጭሩ አድማጭ በአካል ያላየውን የታጨደ የሰብል ነዶ ክምር ልብ ሊል የሚችለው ተመሳሳይ የኾነ ገጽታ ባለው ዐፈር አማካይነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ቃል ግጥም 43፡- መጥቷል መሰለኝ ያጨዳው ሞረድ ያጨዳው ቀበጥ
ደንካዩን ሁላ ትጥቅ የሚያስፈታ ጥላ የሚያስቀምጥ፡፡

(ከቀያፈር ከፍተኛ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኘ፣ 19/05/2012፣ቦረና ወረዳ)

ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ደግሞ የአንድን ነገር ድርጊት በሌላ በሚያመሳስለው ለዋጭ ዘይቤ የቀረበ ነው፡፡ በግጥሙ ውስጥ ያለው ምስስልም ሙሉና ፍጹም በመኾኑ በአጨዳ ተግባር በጣም ታታሪ የኾነው አርሶ አደር ብረትን ለማስላት ወይም ስለታም ለማድረግ የሚያገለግለውን ሞረድና በጠንካራነቱ ቀበጥ ተብሎ የሚሞገሰውን ሰው ባሕርይ ወርሷል፡፡ በዚህ መሠረት ሸካራነት ኖሮት በጠንካራነቱ ብረትን የሚያስላውን የሞረድና የቀበጥን ሰው ባሕርይ የወሰደው ትጉሁ አርሶ አደር ገጣሚ አጨዳው ወደሚታጨድበት ቦታ እንደደረሰ፣ ከዚያም በጣም ፍጥነት ባለው ኹኔታ አጭዶ በጭብጥ በጭብጥ እያደረገ ያስቀመጠውን ሰብል በአንድ ላይ ለሚሰበስቡት ደንካዮች አዳጋች እንደኾነባቸውና ድል እንደተደረጉ ወይም እንደተሸነፉ ያመለክታል፡፡ ለዚህም “ደንካዩን ሁላ ትጥቅ የሚያስፈታ” በማለት ራሱን አወድሷል፡፡

በመጨረሻም ደንካዮቹ ከድካማቸው የተነሣ የፀሐይ ጨረር በሌለበት የዛፍ ጥላ ሥር ለማረፍ እንደተገደዱ ገጣሚው በሙገሳ መልክ ቃል ግጥሙን አዚሟል። ምንም እንኳን በቃል ግጥሙ ውስጥ ያለው ለዋጭ ዘይቤ "ነው፣ ነች፣ ናቸው፣ ..." የሚባሉትን የመኾን ግሶች ባይገለገልም በውስጠ ታዋቂነት ግን የሐሳብ ሽግግሩ ተካኺዷል ማለት ይቻላል።

ቃል ግጥም 44፡- ማጨድ ሲገባን ፀሐይ ሳይበረታ
በከንቱ አሳለፍነው በቡና ጋጋታ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አሰፋ ግዛው፣ 08/01/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ድርጊት ሁሉ የሚከናወነው በጊዜ ተወስኖ መኾኑ የሚታወቅ ነው። ከጊዜ ውጭ የተደረገና ሊደረግ የሚችል ነገር የለም። ጊዜ ሮጦ የሚያስሮጥ መኾኑ ያልገባቸው ሰዎች ችግር ላይ ሊወድቁ የሚችሉ መኾኑ የሚያጠያይቅ ነገር አይኾንም። በዚህ መሠረት ለጊዜ አጠቃቀማቸው ተገቢ የኾነ ትኩረት ያልሰጡ አርሶ አደሮችን የሚተቸው ቃል ግጥምም ከላይ ቀርቧል። በመኾኑም ቃል ግጥሙን ያዜመው ግለሰብ በአጨዳ ተግባር ላይ የሚሰማሩት አርሶ አደሮች በቡና ሰበብ የሥራ ጊዜያቸውን በከንቱ እንደሚያሳልፉ ገልጿል። በእርግጥ የቡና ሥርዓት ከፍተኛ የኾነ ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው መኾኑ ይታወቃል። ኾኖም በአካባቢው ባህል መሠረት በመጀመሪያው ዙር ተፈልቶ ከሚጠጣው "አቦል" ቡና ጀምሮ፣ ለኹለተኛ ጊዜ ተመልሶ የሚፈላውን "ረኛ" ቡና ጨምሮ፣ "በረካ" ተብሎ የሚጠራው ሦስተኛው ዙር ቡና ተፈልቶ እስከሚጠጣበት ጊዜ ድረስ ዐያሌ ጊዜ ይባክናል። ይህ ደግሞ በአንድ ቀን በአንድ ሰው ቤት ብቻ የሚወሰን ሳይኾን በኹለትና በሦስት ሰዎች ቤትም በዙር ሊከናወን ይችላል። ለዚህም ነው በቃል ግጥሙ ውስጥ "በቡና ጋጋታ" የተባለው። ገጣሚው ይህንን የጊዜ መባከን ግምት ውስጥ በማስገባት በፀሐይ ሙቀት ተጎድተን ሳንደክም የማጨድ ተግባራችንን ማከናወን ሲገባን በየቤቱ እየዞርን ቡና ስንጠጣ ጊዜያችንን በከንቱ አሳለፍነው በማለት ራሱንም ኾነ ሌሎች ሰዎችን በፉከራ ሥልት በቀረበው ቃል ግጥም ሲተች ተደምጧል።

ቃል ግጥም 45፡- ማጨድ ነው እንጂ እያፍጫጨ
ጎተራ አይሞላም ፈጦ ቢረጨ፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ጀማል፣ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ይህን ቃል ግጥም ያዜመው አርሶ አደር በእርሻ ሥራ ለተሰማሩ ሰዎች ምክሩን ሲለግስ እንመለከተዋለን። ይኼውም አርሶ አደሩ ጠንክሮ በማረስ ያዘመረውን አዝመራ በኩራት ስሜት እጅግ የሚያምረውን የትንፋሽ ዜማ እያዜመ ማጨድ ሲገባው በባዶው ፈጦ በመርጨት

ጎተራው ሊሞላ እንደማይችል ባዋቀራቸው መንቶ ስንኞች ገልጿል። የAmare (1976፡10) የምርምር ውጤትም፡-

> *የደረቀው ፈጦ ተፈጭቶ በውሃ በመበጥበጥ ለከብቶች የሆድ በሽታ ያገለግላል። ዱቄቱ በፈላ ውሃ ተበጥብጦ ለተሰነጣጠቀ ከንፈር ለመድኀኒትነት ይጠቅማል። ለፀሐይ ምችና ለሌሎችም የቆዳ በሽታዎች ለመፈወሻነት ይውላል። ዱቄቱ በማር ተለውሶ ለአሜባ ሕመም መድኀኒትነት ይጠቅማል። በሞቀ ውሃ በመበጥበጥ ከትንኝና ከሌሎችም የነፍሳት ንክሻ መከላከል ይቻላል። የተፈጨውን ፈጦ ከጥቁር አዝሙድና ከጨው ጋር በመደባለቅ ለሰባት ቀናት ያኽል ከዘፈዘፉ በኋላ ለሆድ ሕመም ያገለግላል* (ትርገሙ የራሴው ነው)።

በማለት ያስረዳል። በዚህ መሠረት ፈጦ ከላይ ለተዘረዘሩት በሽታዎች መድኃኒት ከመኾን ውጭ የእርሻ ሥራን ተግተው ሳይሠሩ የቅመም ዓይነቱን በመርጨት የኾነ መስሎ በሚታይ ነገርና እንደ ሕልም ባለ ሰይጣናዊ ሥራ ወይም በምትሀት ጎተራን ከአፍ እስከ ገደፉ ድረስ በእኽል ጢም አድርጎ መሙላት እንደማይቻል ቃል ግጥሙ ያስረዳል።

5.2.4. የውቂያ ወቅት

አርሶ አደሮች በዓመቱ ውስጥ ከሚያከናውኗቸው የእርሻ ተግባራት መካከል የመጨረሻው እኽልን የመውቃት ወይም የማበራየት ሥራ ነው። ይህንንም ተግባር ለማከናወን በቅድሚያ ከማሳው ላይ በሴቶች ወገብ አማካይነት መኖሪያ አካባቢ ወዳለ ዐውድማ ነዶውን እንዲጋዝ ያደርጋሉ። ከዚያም ከመሬት ከፍ ብሎ በተዘጋጀው የመከመሪያ ቦታ ላይ ይከምራሉ። ይህ የሚደረገውም ሰብሉ ያልደረቀ ከኾነ እንዲደርቅ ጊዜ ለመስጠትና ለውቂያው ተገቢውን ወረፋ ወይም ተራ ለመጠበቅ እንደኾነ በቃለ መጠይቅ ባገኘሁት መረጃ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ቀጥሎም ዐውድማው ንጹህ መኾን ስላለበት በእበትና በውሃ ይለቀለቃል። በመጨረሻም ክምሩ በተለቀለቀው ዐውድማ ላይ እየተነሰነሰ በበሮችና አልፎ አልፎም በጋማ ከብቶች ጭምር ውቂያው ይካኼዳል።

የውቂያ ተግባር ብዙ የሰው ጉልበትን የሚጠይቅ በመኾኑ በቡድን ሲከናወን ይስተዋላል። በዚህ መሠረት የውቂያው ባለቤት የኾነው አርሶ አደር ወንፈል ወይም ደቦ በተባሉ ማኅበራዊ የመረዳጃ ተቋማት አማካይነት ሰዎችን በማሰባሰብ ሥራውን በጋራ ማከናወን ይኖርበታል። ይህ ወቅት ደግሞ ቃል ግጥምን ለመከወን ምቹ አጋጣሚ በመኾኑ በሬዎቹን በዐውድማ ላይ እያዞረ እኽሉን የሚያበራየው ሰው “አያ በሬ ሆይ! አያ በሬ ሆይ!” በሚል አዝማች ግጥሞችን

ያዜማል። በዚህን ወቅት በተለየ ሹኔታ ለበሬዎች ብቻ የሚቀርቡት የምስጋና እና የሙገሳ፣ እንደዚሁም ለሌሎች ርእሰ ጉዳዮች የሚዜሙ ስለሾነ በሬዎቹ እንደ ተሳታፊ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችሉ ይሾናል። ለዚህ ማረጋገጫ ይሾን ዘንድ የሚከተሉት ቃል ግጥሞች በምሳሌነት ቀርበዋል።

ቃል ግጥም 46፡- በርዬ የምን ክፉ በርዬ የምን ክፉ
ከጓሮ ሲገቡ ጥፍጥፉ
ከማጀት ቢገቡ ድፍድፉ
ዳቦውን ሲበሉት ይወስዳል እንቅልፉ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ሁሴን፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥሙን የገጠመው አርሶ አደር በበሮቹ አማካይነት ባገኘው ጠቀሜታ የተሰማውን ርካታ ሲያንጸባርቅ ተስተውሏል። በእርግጥ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ "በርዬ የምን ክፉ" በማለት በሬው ክፉ ነገር እንዳያጋጥመው ተመኝቷል። ምክንያቱም በእሱ አማካይነት የሚፈልገውን ነገር በማግኘቱ ተደስቷል፤ የልቡም ደርሷል። ከዚያም በቤት ጀርባ ባለ ዐጥር ግቢ ውስጥ ከበሬው እበት በተዘጋጀው ጥፍጥፍ (ኩበት) የማገዶ ችግሩ እንደተቃለለለት ገልጿል። አርሶ አደሩ ከሥራ መልስም ሾነ በሌላ ወቅት ውሃ ሲጠማው የሚጠጣውም ሾነ እንግዳ ሲመጣበት የሚያስተናገድበት የጠላ ድፍድፍ በቤት ውስጥ ባለ የዕቃ ማስቀመጫ ጓዳ እንደሚገኝ ከግጥሙ መረዳት ይቻላል። እንደዚሁም በበሬው ጫንቃ ታርሶ የተመረተውን የስንዴ ዳቦ መመገብ እንደ ልብ ሌሊታዊ ዕረፍትን ስለሚያስገኝ የሕዋሳት ቁልፍ የሾነውን እንቅልፍ በደንብ መተኛት እንደሚቻል ገጣሚው ገልጿል።

ቃል ግጥም 47፡- ሐምሌ እግር ብረቱ ነሐሴ ሰንሰለቱ
መስከረም ዳገቱ ጥቅምት ቁልቁለቱ
ጎዳር ገደምዳሜ ያ ታጎሣሥ ጀብራሬ
እንጀራውን ይዘህ ከየት መጣህ ዛሬ።
(ቃለ መጠይቅ፣ እንድሪስ አዳነ፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ጎዳርና ታጎሣሥ የተባሉት ስድስት ወራት በዓመቱ ውስጥ ባላቸው ቅደም ተከተል መሠረት ቀርበዋል። እነዚህ ወራት ደግሞ ከአርሶ አደሩ ሕይወት ጋር የተያያዘ ትርጉም አላቸው። በዚህ መሠረት በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው ማንኛውም ሰው በሐምሌና በነሐሴ ወራት በጎተራውና በጎታው ውስጥ ያለውን እኽል አውጥቶ በአህያ በመጫን በማሳው ላይ እንዲበቅልለት ዘሩን ይዘራል። ስለዚህ በአንዳንዱ

የጎብረተሰብ ክፍል ቤት በእነዚህ ወራት የሚላስና የሚቀመስ የሌለበት አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል በረኃብ ዐለንጋ የሚገረፍ ሰው ሊኖር ይችላል ማለት ነው። በመኾኑም የሐምሌ ወር ወንጀልን የፈጸመ ሰው እግሩን በሚታሰርበት እግር ብረት ወይም በእግረ መቅ ተለውጦ ቀርቧል። የነሐሴ ወርም ቢኾን የተለያዩ ነገሮችን ለማሰር የሚያገለግለውን የብረት ገመድ ወይም የሰንሰለትን ባሕርይ ተላብሷል። መስከረም ደግሞ ሰብሉ በአብዛኛው በቅጠልና በአበባ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ ጠኔው (ራስ የሚያዞር፣ዓይን የሚያጨልም ጽኑ ረኃብ) ከኹለቱ ወራት የከፋ ነው የሚኾነው። ለዚህም ነው የመስከረም ወር ለጉዞ በሚያቃቅት አስቸጋሪ መንገድ ወይም ቦታ የተወከለው።

የጥቅምት ወር ግን ከቀዳሚዎቹ ሦስት ወራት በተቃራኒነት የቆመ መኾኑን ገጣሚው አመላክቷል። ይኼውም ከመሬት ብዙ ጥቅም የሚገኝበት፣ እኽሉና ተክሉ ሁሉ ፍሬ መስጠት የሚጀምርበት የእሸት ጊዜ ነው። ስለዚህ አርሶ አደሩ በእዚህ ወር እሸት ጠብሶ የመብላት ዕድል ይኖረዋል። በተለይም የባቄላ እሸትን በመፈልፈል ቀቅሎና ቆልቶ መመገብ ይችላል። መከር ከመድረሱ ቀደም ብሎም ለችግር የሚውለውን የራቻ እኽል ወቅቶ ስለሚመገብ ጠግቦ ማደር ይችላል። ለዚህም ነው ወደተከታዮቹ ወራት መሻገሪያ በመኾኑ "ጥቅምት ቁልቁለቱ" የተባለው። ጎዳር ደግሞ ዳገትም ቁልቁለትም ሳይኾን ወደጎን በሚወስድ ጠምዝማዛ መንገድ ተመስሏል። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የጥራጥሬ ዓይነቶች ተወቅተው ወደ ጎተራና ጎታ የሚገቡበት ወቅት ስለኾነ አርሶ አደሩም በመብልና መጠጥ ሆዱ ሞልቶ የሚረካበት ወር ነው። ታጎሣሥን ግን ከጥቅምትና ከጎዳር ወራት በላቀ ኹኔታ ገጣሚው አወድሶታል። ምክንያቱም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው የጎብረተሰብ ክፍል ለወራት ያኽል ያረሰውን፣ የዘራውን እና ያጨደውን ሰብል ሙሉ በሙሉ አጠቃሎ በመውቃት ከጎተራው የሚያስገባው በዚህ ወር በመኾኑ ዛሬ ነገ ሳትል ለቀለባችን የሚኾነንን ነገር ከየት አቅጣጫ ይዘህልን መጣህ በማለትም ጠይቆታል።

ቃል ግጥም 48፡- በሬዋ ና ሂድ! በሬዋ ና ሂድ!
ታልሞላ ጎተራ ታልጠገበ ሆድ
ታልጫነ ዘመድ።

(ቃለ መጠይቅ፣ መሐመድ ኑር ሁሴን፣ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

የቃል ግጥሙ ባለቤት የኾነው አርሶ አደር በዐውድማ ላይ እኽሉን በሚወቃበት ጊዜ ከበሬዎቹ ኋላ ኋላ እየተከተለ ሲነዳ እነሱም ቶሎ ቶሎ ተግተው እየተራመዱ እንዲዞሩ ለማድረግ "በሬዋ" በማለት በዜማ አቆላምጧቸዋል። ይህ የሚኾነውም መሬቱ ተምሶ እንደ ጎተራ ለእኽል ማከማቻነት የሚያገለግለው ጉድጓድ ከአፍ እስከ ገደፉ እንዲሞላና የአርሶ አደሩም ኾነ የቤተሰቡ

ሆድ ሞልቶ እርካታ እንዲያገኝ በማሰብ ይመስላል። በድርቅ ወይም በሌላ ምክንያት የሚበላው ያጣ በትውልድ የአባት ወይም የእናት ወገን የኾነ ሰው ሁሉ በጋማ ከብት ወይም በመኪና የሚፈልገውን ያክል እክል እንዲጪን በመፈለግም ጭምር ነው። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአርሶ አደሩ ፍላጎቶች እስካልተሟሉ ድረስ በበሬዎቹ የማረስ፣ የማጨድና በዐውማ ላይ ሰብልን የመውቃት ወይም የማበራየቱ ተግባር ሊቋረጥ እንደማይችል ገጣሚው ባቀነቀነው ቃል ግጥም ሲገልጽ ይስተዋላል።

ቃል ግጥም 49፦ አያ በሬ ማሩ አያ በሬ ማሩ
በርዬ እሹሩሩ ላብላህ ከዳር ዳሩ
ላጠጣህ ከባሕሩ።
ባንተ ላይ ነውና የሚገኘው ሁሉ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ እንደቀረበው “አያ” የሚለው ቃል ታላቅ ወንድምን እና አጎትን በአክብሮት ለመጥራት ብቻ የሚያገለግል ሳይኾን፣ አርሶ አደሩም ቢኾን ክብርና ሞገስ ለመስጠት ሲፈልግ “አያ” ብሎ በሬውን እንደሚጠራ ከግጥሙ መረዳት እንችላለን። በመቀጠልም በጣዕም ከጣፋጭ ነገሮች ሁሉ በሚበልጠው “ማር”ም በሬው ሲወደስ በእዝነ ኅሊናችን እናዳምጣለን። በደምሳሳው “አያ በሬ ማሩ አያ በሬ ማሩ” በማለትም አርሶ አደሩ ለበሬው በዘፈን አዝማች አማካይነት በግጥሙ መጀመሪያ ላይ አዚሞለታል። በመቀጠልም የታዘለ ወይም በእቅፍ የተያዘ ሕፃን በሚያለቅስበት ጊዜ ዝም እንዲል ለማድረግ “እሺርሩ” እየተባለ እንደሚባበል ሁሉ ለበሬውም ይሄንኑ ቃል በመጠቀም አንጎራጉሯል። በሌሎቹ ስንኞች ደግሞ ገጣሚው ለበሬው የራሮት ስሜትን አሳይቶታል። ይኼውም በማሳዎች መካከል ባለውና በማይታረሰው ቦታ ላይ ሣሩ አድጎ ስለሚገኝ ወደዚያ ወስጄ አበላሃለሁ። እንደዚሁም በስፋትና በጥልቀት ከተከማቸው ውሃም አጠጣሃለሁ። ምክንያቱም ሁሉንም ነገር በእጄ ማድረግ ወይም መያዝ የምችለው ባንተ ላይ ነው በማለት አሞግሶታል። ይህ ደግሞ አርሶ አደሩ ሙሉ ሕይወቱ በበሬው ላይ ጥገኛ መኾኑን ያመለክታል ማለት ነው።

ቃል ግጥም 50፦ በርዬ አንተን ያጡ በርዬ አንተን ያጡ
ጎናቱ አንተን ያጡ
ማኅበር ቀላወጡ
አተላ ጨለጡ
እያሏቸው መጡ።
(ቃለ መጠይቅ፣ መንግሥቱ አበራ፣ 02/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ከመስከረም 05 - 09/ 2013 ዓ.ም ድረስ ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ተጨምቆ የተገኘው ሐሳብ የሚያመለክተው ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው የኅብረተሰብ ክፍል የማንኛውንም ሰው ማኅበራዊ ደረጃ ከሚወስንባቸው ነገሮች አንደኛው ለማረስና ለመውቃት የሚያገለግል በሬ መኖር አለመኖር ነው፡፡ በቃል ግጥሙ መሠረት ገጣሚው በግጥሙ ውስጥ “ጎናቴ” ወይም አካሌ ብሎ የሚጠራው በሬ የሌላቸው አርሶ አደሮች ወጥተው ወርደው በማረስና በመውቃት ራሳቸውንም ኾነ ቤተሰባቸውን መመገብ ባለመቻላቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ ባላቸው ደረጃ ዝቅ ተደርገው እንደሚታዩ አስረድቷል፡፡ በዚህ የተነሣ ተመሳሳይ እምነት ያላቸው ሰዎች በፈጣሪ ወይም በሌላ ቅዱስ ስም በየተራ እየደገሱ በየበዓሉ ቀን አንድ ላይ በመገናኘት በጋራ የሚቀምሱትን ጠበለ ጽድቅ እነዚህ ሰዎች ሳይጠሩ ወይም ሳይጋበዙ በማፍጠጥ በየቤቱ እየዞሩ “ቀላወጡ” በማለት ተችቷቸዋል፡፡ በዚህ ብቻም ሳያቆም ጠላ ተጠጥቶ ካለቀ በኋላ ከሥሩ የሚቀረውን “አተላ” ያለ ምንም ኀፍረት ጨልጠው ጠጡ እያሉ ሰዎች እየተናገሯቸው ነው በማለት ገጣሚው ትዝብቱን በቋጠራቸው ስንኞች ገልጿል፡፡ በግጥሙ ውስጥ ባሉት ስንኞች የተሰነዘሩት ኃይለኛ ትችቶች መሪር መኾናቸውን አድማጭ ልብ ሊል ይገባል፡፡ ምክንያቱም የገጣሚውን የጥላቻ ወይም የመጸየፍ ስሜትን አጉልተው ለማሳየት የቻሉ በመኾናቸው ነው፡፡

ከእነዚህ የእርሻ ሥራዎች በተጨማሪ ለቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች በከፍተኛ ኹኔታ የሚጠቀሱት የማኅበረሰቡ የሕይወት መሸጋገሪያ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ በመኾኑም እነዚህን የሽግግር ሥርዓቶች በቅደም ተከተል ቀጥሎ ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

5.3. የማኅበረሰቡ የሕይወት ሽግግር ኺደቶች

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ የሚያልፍባቸው ዓበይት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች መረገዝ፣ መወለድ፣ መጎርመስ፣ ኩርድና፣ ትዳር፣ እርጅና እና ሞት ናቸው (Green,1997፡732)፡፡ እነዚህም የቦታን፣ የማኅበራዊ ደረጃን፣ የአካልን እና የዕድሜ ለውጥን ያስከትላሉ፡፡ በሀገራችንም ከተለመዱት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች መካከል ሕፃናት ሲወለዱና ክርስትና ሲነሡ፣ በሰርግ፣ በለቅሶና በተዝካር ሥርዓቶች የሚከወኑት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ለቃል ግጥም መከወኛ ምቹ የኾኑ አጋጣሚዎች እንደኾኑ Finnegan (1992:102) አስረድተዋል፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍም ከላይ ከተጠቀሱት የሕይወት ሽግግሮሽ መካከል ቃል ግጥም በአብዛኛው በሚከወንባቸው በኩርድና፣ በሰርግና በቀብር ሥርዓቶች ላይ ብቻ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ሕፃናት ሲወለዱም ኾነ ክርስትና

ሲነሡ በሚከወን ሥርዓት ላይ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ባለመገኘታቸው እነሱን በጥናቱ ውስጥ ለመዳሰስ አልተቻለም።

5.3.1. የኩርድና (የልጃገረድነት) ዕድሜ

ከመስከረም 05 — 09/2013 ዓ.ም ድረስ በሦስቱም ወረዳዎች በነበረኝ የመስክ ቆይታ በቡድን ተኮር ውይይቱ የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎቹ እንደገለጹልኝ ማኅበረሰቡ ኮረዳ (ልጃገረድ) ብሎ የሚጠራቸው ዕድሜያቸው ከዐሥራ ሦስት ዓመት በላይ የኾኑ፣ ለዐቅመ ሔዋን የደረሱና ያላገቡ ሴት ልጆችን ነው። እነዚህ ልጃገረዶች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያዜሟቸው የቃል ግጥሞች በአብዛኛው "የቆንጆ" ዘፈን በመባል ይታወቃሉ። የልጃገረዶች የፍቅር ዘፈን የሚከወነው በአውራጅና በተቀባይ ሲኾን፣ አውራጆቹም የድምፅ መመሳሰል ያላቸው ኹለትም ሦስትም ሊኾኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን በየአጋጣሚዎቹ የልጃገረዶቹ ዘፈኖች ጎልተው ቢታዩም የጎረምሳዎቹ የሆታ፣ የድልቂያና የእስክስታ ከዋኔዎችም አብረው እንዳሉ ጥናቱ ይጠቁማል።

በቡድን ተኮር ውይይቱ ጭምቃ ሐሳብ መሠረት የልጃገረዶቹ ዘፈኖች የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው። ጎልተው የሚታዩት የመከወኛ አጋጣሚዎች ተበቺሳ፣ የተለያዩ የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች፣ የዐረም ወቅቶች፣ የተለያዩ ክብረ በዓላትና የሰብል መጠበቂያ ቦታዎች ናቸው። በዚህ የተነሣ በሰነድ፣ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው የተገኙት የልጃገረዶቹ ዘፈኖች መኾናቸውን በዐባሪነት የተዘረዘሩት ማረጋገጫዎች ይኾናሉ። የቃል ግጥም ዘፈኖቹ በቁጥር ረገድ ከፍተኛውን ደረጃ መያዛቸው ብቻ ሳይኾን በአንድ የዘፈን የዜማ ዓይነት ሥር በርካታ ስንኞች መደርደራቸው ደግሞ ለዘውጉ እንደ አንድ መገለጫ ባሕርይ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ምሳሌዎችን መሠረት በማድረግ እነዚህን የልጃገረዶች የዘፈን መከወኛ አጋጣሚዎች በቅደም ተከተል ቀጥሎ ለማየት ተችሏል።

5.3.1.1 ተበቺሳ

ተበቺሳ የሚለው ቃል ከኦሮምኛ ቋንቋ የተገኘ ሲኾን፣ ጥሬ ትርጉሙም አጫዋች ማለት ነው። ጨዋታውም ለሰርግ የሚኾነው ድግስ ከተጠነሰሰበት ዕለት ማታ ጀምሮ እስከ ሰርጉ ዋዜማ ድረስ በልጃገረዶችና በጎረምሳዎች አማካይነት ይካኼዳል (ይማም አብዱ፣2008፡42)። በመኾኑም በመጀመሪያው ቀን የሰፈሩ ልጃገረዶች ባህሉ ስለማይፈቅድላቸው በራሳቸው ፈቃድ ዝም ብለው የሰርጉ ድግስ ወደሚሰናዳበት ቤት ለተበቺሳው አይኼዱም፤ ወላጆቻቸውም አይፈቅዱላቸውም።

ከዚህ ይልቅ በሙሽራው ወይም በሙሽራይቱ መኖሪያ ቤት ወይም በጎረቤት ሴት ልጅ ካለች በእሷ አማካይነት ከዛሬ ምሽት ጀምሮ "ልጃችሁ ልጃችንን ታጫውትልን" በማለት የልጃገረዶቹን ቤተሰቦች ፈቃድ ይጠይቃሉ። ይህ ዓይነቱ ክብር የተሰጣቸው ቤተሰቦችም ያለ ምንም ማንገራገር ልጆቻቸው ማታ ማታ እየኼዱ እንዲጫወቱ ፈቃድ ይሰጧቸዋል። ልጃገረዶቹም በቤተሰቦቻቸው ፈቃድ መሠረት ማታ ማታ ከየመንደሩ እየተጠራሩ በመሰባሰብ ለዘፈኑ ማድመቂያ የምትኾን አታሞ[22] እና ሎሚ ይዘው ወደሚደገሰው ሰርግ ቤት ይኼዳሉ። ሎሚ የሚይዙበት ምክንያትም ለከንፈር ወዳኛቸው ለመስጠትና ተካፍለው ለመምጠጥ ነው፡



ሥዕላዊ መግለጫ ሦስት፡- የተበቺሳን ክዋኔ የሚያመለክት

ምንም እንኳን የጨዋታው ዋና ተዋናዮቹ ልጃገረዶቹ ቢኾኑም ጎረምሳዎቹም ያለ ማንም ከልካይ ከየአካባቢው ተጠራርተው የልጃገረዶች የዘፈን እና የአታሞ ድምፅ ወደሚሰማበት መንደር በቅባትና በጭስ ያዘጋጁትን የቀላ ዱላ ይዘው፣ እንዲሁም ጽዱ ጋቢያቸውን ተከናንበው በቡድን በቡድን ኾነው ይኼዳሉ። በዚህን ጊዜ ልጃገረዶቹ በጎበረት ኾነው በምሽት የጨረቃ ብርሃን ደምቀው፣ በክዋክብት ታጅበው፣ በቀጭንና ተስረቅራቂ ድምፅ የቃል ግጥም ዘፈኖችን ሲያዜሙ፣ ጎረምሳዎቹ ደግሞ በልጃገረዶቹ ዙሪያ ኾነው ምቱን በጠበቀ ኹኔታ በእግራቸው እየረገጡ ይደልቁ ነበር።

[22] አታሞ አነስተኛ ገበቴ በፍየል፣ በሰሳ ወይም በሚዳቋ ቆዳ ተለብዶ በልጃገረዶች በውስጥ ጣቶች የሚመታ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ወይም አነስተኛ ከበሮ ማለት ነው።



ፎቶግራፍ አራት፡- ልጃገረዶቹና ጎረምሳዎቹ በጸታቸው ተለያይተው ሲጨፍሩ

በዚህ የተበቺሳ ክዋኔ ጊዜ ልጃገረዶቹ ከሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን ለአብነት እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 51፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው ሠስት ጊዜ
ሸጌ እንደ ሽመሉ ሞት አይፈራም አለ፡፡

ማሬ ልጅ ላይ ሚዳ አልመጣም ገና ነው
ማሬ ልጅ ጎድጓዲት አልመጣም ገና ነው
ማሬ ልጅ ታች ሚዳ አልመጣም ገና ነው
የተሰበሰበው የዐተር ገለባ ነው፡፡
አንተ ያተር ገለባ ምን ይቆልለሃል
ሸጋው ልጅ ቀይ ዐፈር ይበታትንሃል፡፡
አሁን ይህን ጊዜ ያልመጣ ወዳጅ
እናቱ ገርድፋ ይሰልቃል እንጂ፡፡
ኮለል እንደ ውሃ ኮለል እንደ እንቧይ
እመጣለሁ ብለህ መቅረትህ ነው ወይ፡፡
ሸጌ የዱላው ዕለት የቀረህ እንደኾን
እንኳን ከንፈር ወዳጅ ጎረቤትም አንኾን፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አህመድ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በተበቺሳ ጨዋታ ታዋቂ ዘፋኝ የነበሩት ወይዘሮ ሙሉ አህመድ በመኖሪያ ቤታቸው በነበሩበት ወቅት እንደነገሩኝ ከኾነ በልጃገረዶች ዘፈኖች ውስጥ ከሚዘወተረው የዜማ ዓይነት “አያ በለው በለው” የሚለው ነው፡፡ ይህም ሲባል በማንኛውም የዘፈን መከወኛ አጋጣሚ ሊዜም ይችላል

ማለት ነው። በተለይ በተበቺሳ ጨዋታ ወቅት በስፋት አገልግሎት ላይ ይውላል። ይህ የሚኾነው የቃል ግጥሞቹ ባላቸው «የቃና» አቀራረብ ነው ሲሉም ወይዘሮ ሙሉ ገልጸውልኛል። በቃል ግጥሙ መነሻ ላይ በመደጋገም የቀረቡት "የአያ በለው በለው" የአዝማች ስንኞች ጀግንነትን፣ ወኔን፣ ድፍረትን በሚጠይቁ ኹኔታዎች ላይ ሁሉ ጎረምሳዎችን የሚያበረታቱ ናቸው። በዚህ መሠረት "ሽመል" የተባለው በትር ወይም ዱላ ጭስ ባለበት የቤት ጣሪያ ላይ ለወራት ያኽል ተሰቅሎ የተቀመጠው ጥንካሬ እንዲኖረው በመኾኑ በቀላሉ ተሰብሮ አይወድቅም። ልጃገረዶቹ ቆንጆና ውብ የኾነውን ጎረምሳም የጥንካሬ ባሕርይ ከተላበሰው ዱላ ጋር ጎን በጎን በማነጻጸር ነፍሴ ከሥጋዬ ትለያለች ብሎ አይሸበርም በማለት ወኔውን ሲቀሰቅሱት በእዝነ ልቦናችን እናዳምጣቸዋለን። ምክንያቱም በተበቺሳ ጨዋታ ወቅት "የከንፈር ወዳጄ ተሳመችብኝ" በሚል መነሻ የእርስ በርስ ጠብ በሚከሠትበት ጊዜ እንዳይሸሽ ለማደፋፈር ሲባል ነው።

በልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች ሥር በርካታ ስንኞች መደርደራቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚታወቅ ነው። ከላይ በማስረጃነት የቀረበውም የዘፈን ግጥም ይህንኑ እውነታ ያንጸባርቃል። በቃል ግጥሙ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ስንኞች ውስጥ ላይ ሚዳ፣ ጎድንዲትና ታች ሚዳ የሚባሉት ጎጦች በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል። እነዚህ ደግሞ የልጃገረዶቹ የከንፈር ወዳጆች ተወልደው ያደጉባቸው ናቸው። ነገር ግን ጎረምሳዎቹ ለልጃገረዶቹ በተበቺሳ ጨዋታው ላይ በወቅቱ ያልመጡላቸው መኾኑን ለማመልከትም "...አልመጣም ገና ነው" የሚለው ሐረግ በተደጋጋሚ ሊቀነቀን ችሏል። ይህ የኾነው በስመ ጎዳሪ ዘይቤን በመጠቀም መኖሪያውን ጠርቶ ነዋሪውን በሚያሳይ የንግግር ስልት መኾኑ ነው። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የትኛው ጎረምሳ ለየትኛዋ ልጃገረድ የከንፈር ወዳጅ እንደኾነ በአብዛኛዎቹ ልጃገረዶችና ጎረምሳዎች ላይታወቅ ስለሚችል ዘይቤውን የተጠቀሙት በምሥጢር ደብቆ ለመያዝም ጭምር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በከንፈር ወዳጆቹ መካከል ያለው ፍቅር በጣም ደስ የሚልና የሚጥም መኾኑን ለማሳየትም የማርን ጣፋጭነት በማላበስ "ማሬው ልጅ ..." እያሉ ሲያወድሱ ይሰማሉ። በወቅቱ የመጡት ጎረምሳዎች የልጃገረዶቹ የከንፈር ወዳጆች ባለመኾናቸው "የተሰበሰበው የዐተር ገለባ ነው" በሚለው ስንኝ ለመሰደብ በቅተዋል። ይሄውም በለዋጭ ዘይቤ ጎረምሳዎቹ ፍሬ ቢስና ቁም ነገር የሌላቸው መኾኑን ለማንጸባረቅ የዐተር ገለባው በንጽጽር መቅረቡን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ስድቡ በዚህ ብቻ አላቆመም። በባዶው ራሳችሁን ከመጠን በላይ ለምን ከፍ ከፍ ታደርጋላችሁ በማለትም ተሳልቀውባቸዋል። ቀጥሎም ቀያፈር ከተባለው ጎጥ የመጡት ሽጋዎቹ ጎረምሳዎች ጠብ በሚነሣበት ወቅት ብትንትናችሁን ያወጣችኋል በማለት አስፈራርተዋቸዋል።

በጨዋታው መጨረሻ ላይም ልጃገረዶቹ የከንፈር ወዳጆቻቸው ባለመምጣታቸው ተስፋ ቆርጠው በዚህን ጊዜ ያልመጣ ወዳጅ እናቱ የገረደፈችውን እኽል አልሞ (አድቅቆ) ይፍጭ በማለት ተዛብተውባቸዋል። ምክንያቱም ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ የመፍጨትና የመጋገር ሥራ ሴቶች ብቻ የሚያከናውኗቸው፣ ለወንድ ልጅ ግን ነውር ተግባራት በመኾናቸው የተነሣ ነው። በመቀጠልም የከንፈር ወዳጅ የኾኑት ጎረምሳዎች ከአሁን ቀደም የነበራቸውን ፈጣን አመጣጥ ኮለል ብሎ ከሚወርድ ውሃና እምቧይ ጋር ልጃገረዶቹ በዓይነ ኅሊናቸው ሊያነጻጽሯቸው ችለዋል። ከአሁን በኋላ ላላገኝህ ነው ወይ የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍም “እመጣለሁ ብለህ መቅረትህ ነው ወይ” በማለት ነገሩ ተስፋ የሌለው መኾኑን በስንኙ አማካይነት ገልጸዋል። ይህ ደግሞ በኹለቱ ወገኖች መካከል የከንፈር መሳሳም ክዋኔ መካሄድ አለመቻሉን ያስገነዝባል።

በመጨረሻም የጀግንነት መንፈስን የሚያንጸባርቁ ስንኞች በልጃገረዶቹ ተዚመዋል። ይኼውም የከንፈር ወዳጄን ተቀማሁ በሚል ምክንያት በሚፈጠረው ጠብ ላይ የማትገኝ ከኾነ በከንፈር ወዳጅነት ልንቀጥል ቀርቶ አጠገብ ለአጠገብ ጎረቤታሞች ኾነን ልንኖር አንችልም ሲሉ ተደምጠዋል። ይህ አስደማሚነት ያለው የተበቺሳ የጨዋታ ዓይነት አሁን አሁን ላይ እየቀረ መምጣቱን በቦረና ወረዳ በመስከረም 09/2013 ዓ.ም በነበረው ቡድን ተኮር ውይይት ወቅት ተገልጿል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በቀበሌ ደረጃ የተዋቀሩት የመንግሥት አካላት በከንፈር መሳሳም የHIV AIDS በሽታ ይተላለፋል። “የከንፈር ወዳጅ ተቀማን” በሚሉ ጎረምሳዎች አማካይነት የእርስ በርስ ግጭት ያላግባብ ተፈጥሮ ሕይወት እየጠፋ ነው። የጥርስ መውለቅና የዓይን መጥፋት አደጋም ያጋጥማል የሚሉ እንደሆኑመረጃው አመላክቷል።

5.3.1.2 የተለያዩ የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች

ከተበቺሳ በተጨማሪ የልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች እንደኾኑ ወይዘሮ ዘውዴ ሁሴን ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 19፣2012፣ ቦረና ወረዳ፣ በመኖሪያ ቤት)። አሁን አሁን ላይ ልጃገረዶቹ ተማሪዎች ስለኾኑ ቀረ እንጂ ቀደም ሲል በኩበትና በእንጨት ለቀማ ወቅት ዘፈኖችን እንዘፍን ነበር በማለት ተናግረዋል። ኺደቱም ልጃገረዶቹ በቤት ውስጥ ሥራ በሌለባቸው ጊዜ ተጠራርተው ወደዱር በመኼድ ለማገዶ የሚኾን ኩበት ሲለቅሙና እንጨት ሲሰብሩ የቃል ግጥም ዘፈኖችን ይዘፍኑ ነበር። የእነሱን የዘፈን ድምፅ የሰሙ ጎረምሳዎችም ዱካቸውን ተከትለው በመኼድ የከንፈር መሳሳም ኹኔታም ሲፈጠር እንደነበር ከመስክ የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል። ለማገዶ የሚኾነው ኩበት የሚለቀመው ከብቶች በብዛት ተሰማርተው ከሚውሉባቸው ሜዳዎች ላይ

ሲሸን፤ ልጃገረዶቹም የለቀሙትን ኩበት የሚሸከሙበት ድርብ[23] እና ቁና[24] መያዝ ይኖርባቸዋል። የኩበት ለቀማ ተግባሩን ሲያከናውኑ ደግሞ የተለያዩ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ። በዚህ ወቅት ከአስቸጋሪነቱ አንጻር አታሞ ሊይዙ አይችሉም። ከሚቀነቀኑት ዘፈኖች መካከልም አንደኛውን ቀጥለን በምሳሌነት እንመልከት።

ቃል ግጥም 52፡- እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ ሦስት ጊዜ
እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
ሜዳ ሜዳ ስኼድ አገኘሁ እሪጋ
ሁሉም ሸጋ ናቸወ በማንኛው ልርጋ።
አፋፍ ለአፋፍ ስኼድ እጀን እሾህ ወጋኝ
ገና በልጅነት ፍቅር አንገላታኝ።
አታሞውን ምቺው በግራው እጅሽ
አንጀት የሚበላ ወዳጅ እንዳለሽ።
ሸጌን የወለደ ዘሩ ሸጋ ይኹን
ጥዋት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን።
የገደል ሥር ውሃ ፈሳሹ ፈሳሹ
ማተብ ስደድልኝ ለተመላላሹ።
የሸግዬ ዱላ ጥቁር የነበረው
እየቀላ ኼደ ደም እየነሰረው።
የሰማይ አሞራ ላቀብልሽ ጥሬ
ትነግሪኝ እንደኾን የሸግዬን ወሬ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ዘይነባ ሰይድ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

እንደ “አያ በለው በለው” ሁሉ በልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች መካከል ከሚቀርበው የዜማ ዓይነት ሌለኛው ደግሞ “እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ” የሚለው ነው። ይህ የዜማ ዓይነት በዐረም ወቅትና በማገዶ ለቀማ ቦታ ሊዜም ይችላል። እዚሁ ላይ ሌላው መነሣት ያለበት ጉዳይ በልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈን ውስጥ አይቀሬ ኾኖ የሚታየው የአዝማች አጠቃቀም ነው። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥም ውስጥ በአዝማችነት ያገለገለው “እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ” የሚለው ነው። ይህ አዝማች በየሐረጋቱና በየስንኞቹ መጨረሻ ላይ እየገባ የዘፈኑ ማድመቂያ በመኾን

[23] ድርብ የቁናውን ኹለት እጥፍ ሊይዝ የሚችልና ለእኽል መስፈሪያ (መለኪያ) የሚያገለግል የስፌት እቃ ነው።
[24] ቁና ለእኽል መስፈሪያ (መለኪያ) የሚያገለግል የስፌት እቃ ነው።

ያገለግላል። ይኹንና አዝማቹ በይዘት ረገድ ከዋናው የዘፈን ግጥም ጋር ግንኙነት ላይኖረው ይችላል።

ከላይ በቀረበው የቃል ግጥም ዘፈን ውስጥ የተቀነቀኑት ስንኞች ልጃገረዶቹ የከንፈር ወዳጆቻቸውን ያወደሱባቸው ናቸው። በዚህ መሠረት በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ያቀነቀነችው ልጃገረድ ለኩበት ለቀማ ሜዳ ለሜዳ ስትዘዋወር በጥርስ መፋቂያ (እሪጋ) የተመሰሉትን የከንፈር ወዳጆቿን እንዳገኘች ገልጻለች። ነገር ግን በመልክ ደረጃ ሁሉም ጠይሞች በመኾናቸው በማንኛው ጸንታ ልትቆም እንደምትችል ግራ መጋባቷንም አመላክታለች። ይህ የኾነውም የከንፈር ወዳጅ ምርጫ በአብዛኛው በጠይሞች ላይ ያተኮረ በመኾኑ ነው። ልጃገረዲ ኩበት ለመልቀም የተዘዋወረችው ሜዳ ለሜዳ ብቻ ሳይኾን አፋፍ ለአፋፍም ጭምር ነው። ታዲያ በዚህ ወቅት በእሾህ በተመሰለው ፍቅር ገና በልጅነቷ ጉዳት እንደደረሰባትና እንደተንገላታች በዘፈኑ አማካይነት ገልጻለች።

ምንም እንኳን ልጃገረዲ ለኩበት መልቀሚያ የሚኾነውን ድርብ ወይም ቁና ስለምትሸከም በእጇ አታሞ ለመያዝ ብትቸገርም በሌላ ወቅትም ቢኾን አታሞ እየመታች አንጀት የሚበላ የከንፈር ወዳጅ ካላት በዘፈን ማወደስ እንደሚኖርባት በጓደኛዋ ስትመከር እናስተውላለን። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለች ልጃገረድ የከንፈር ወዳጇን ብቻ ሳይኾን ቤተሰቦቹንም በተለይም እናቱን በየዘፈን አጋጣሚዎቹ እያሸሞነሞነች ስታወድሳቸው ትደመጣለች። ሽጋ የኾነ ጎረምሳን የወለደች እናት አጠቃላይ ዘሮቿም ጭምር ውብና ቆንጆ እንዲኾኑም ትመኛለች። በሽጋ ልጅ ፍቅር በመማረኳም እሱን ፈልጋ ለማግኘት ስትል ከጧት እስከ ማታ ድረስ በሐሳብ የተዋጠች መኾኗን ለመግለጽ “ጥዋት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን” የሚለውን ስንኝ ቋጥራ አቀንቅናለች። በቃል ግጥም ዘፈኑ ውስጥ ጠይሙ ፍቅረኛዋ ከገደል ሥር ኮለል ብሎ በሚፈልቀው ውሃ ተመስሎ የቀረበ ሲኾን፣ እሱም ተመላላሽ ለኾነ ሰው በአንገት ላይ ለሚደረጉት ጌጣጌጦች በማንጠልጠያነት የሚያገለግለውን ማተብ እንዲልክላት ተማጽናዋለች።

በዚህ የዘፈን ግጥም ውስጥ “ማተብ” የሚለው ቃል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት መሠረት ለሃይማኖት ምልክትነት በአንገት ላይ የሚታሠረውን ክር ለማሳየት እንዳልኾነ ልብ ይሏል። ከዚያ ይልቅ በከንፈር ወዳጅነት የተጣመሩትን የተቃራኒ ጾታዎች መተማመንን እና ቃል ኪዳንን ያመለክት ይኾናል የሚል እሳቤ አለኝ። ቀጣዮቹ ኹለት ስንኞች ደግሞ በጎረምሳዎች መካከል ዐምባጓሮ ሲነሣ ጀግንነትንም ኾነ ውበትን የተላበሰው የከንፈር ወዳጇ የጠላትን ጭንቅላት ፈንክቶ በሚፈሰው ደም የዱላው መልክ ከጥቁርነት ወደቀይነት በመቀየሩ አሞግሳዋለች። ከዚህ ባለፈ ደግሞ “ቀይ” የሚለው አሐድ ጥናቱ

በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ ጎረምሳዎች ለከንፈር ወዳጆቻቸው ሲሉ መሥዋዕት መክፈል እንደሚኖርባቸው ያመለክታል። በመጨረሻም ልጃገረዷ የናፈቀችውና ሽጋ የኾነው የከንፈር ወዳጇ ያለበትን ኹኔታ በሰማይ ላይ የምትበረዋ አሞራ እንድትነግራት ትማለዳለች። ለዚህም ውለታዋ ጥሬ እንደምትሰጣት ቃል ገብታላታች።

ከኩበት ለቀማ በተጨማሪ የልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈን የመከወኛ አጋጣሚ የእንጨት መልቀሚያ ቦታ ነው። ልጃገረዶቹ በክረምት ወራት የሚማገደውን እንጨት የሚለቅሙት በአብዛኛው በግንቦትና በሰኔ ወራት በመኾኑ ይህ ወቅት ለቃል ግጥም ዘፈን መከወኛ ምቹ አጋጣሚ እንደነበር ወይዘሮ ወርቁ ዳውድ በትዝታ አጫውተውኛል። የአካባቢው ጎረምሳዎችም የእርሻም ኾነ ሌላ ሥራ ከሌለባቸው በፉጨት ተጠራርተው ልጃገረዶቹ እንጨት ወደሚለቅሙበት ጫካ በመኼድ ከንፈር የመሳም ዕድሉ እንደነበራቸው ከቃለ መጠይቁ ለመገንዘብ ተችሏል። ምናልባት በእንጨት ለቀማ ወቅት ከጓደኞቿ ተለይታ የቀረችና የከንፈር ወዳጇን የጥሪ ፉጨት የሰማች ልጃገረድ፡-

ቃል ግጥም 53፡- ለምን ትጣራለህ በፉጨት በፉጨት
እመጣልሃለሁ እሑድ ቅዳሜ እንጨት

(ቃለ መጠይቅ፣ ወርቁ ዳውድ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በማለት ታቀነቅናለች። በመኾኑም አሁን አትልፋ፤ እኔንም ትመጣለች ብለህ አትጠብቀኝ። መገናኛችን ቅዳሜና እሑድ ነው በማለት በስንኞቹ አማካይነት ቀጠሮ ታስይዘዋለች። በቀጠሮዋ ዕለት ልጃገረዷና ጓደኞቿ እንጨት ወደሚሰበርበት ቦታ እንደኼዱ ጎረምሳዎቹም ለከንፈር ወዳጆቻቸው በምሳር እንጨት ይፈልጡላቸዋል። በመጨረሻም ለልጃገረዶቹ በያዙት ማሠሪያ ያሥሩላቸዋል። ይህ ሁሉ ተግባር የሚከናወነው ከንፈር ለመሳም የሚደረግ ደጅ ጥናት በመኾኑ በከንፈር ወዳጅነት የተጣመሩት ተቃራኒ ጾታዎች የታሠረው እንጨት ላይ ተቀምጠው ይሳሳማሉ።

አልፎ አልፎ በክረምት ወራትም ቢኾን ልጃገረዶቹ የከንፈር ወዳጆቻቸው ወደከረሙበት ደረባ በመኼድ የማገዶ እንጨት ሊለቅሙ ይችላሉ። እንጨታቸውን ሰብረው ከጨረሱ በኋላም ተሸክመው ወደየቤታቸው በመመለስ ላይ እያሉ "በእዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ"ም ኾነ በሌሎች የዜማ ዓይነቶች የሚዘፍኗቸው ዘፈኖች እንደነበሩ ወይዘሮ ወርቁ ዳውድ ነግረውኛል። ደረባን በተመለከተ ከተዜመው የልጃገረዶች ቃል ግጥም መካከል የሚከተለውን ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 54፡- እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
} ሦስት ጊዜ

እንጨት እሰብራለሁ እንጨቴ ሙሀርባ
ወለቃ ነው አሉ የሸጉ ደረባ፡፡
የሸጉ ደረባ ያውም የትንሹ
ሎሚና ትርንጎ የሚለው ትንፋሹ፡፡
ሎሚና ትርንጎ የሚበላ ሰው
እጅግ የታደለ የጨዋ ልጅ ነው፡፡
የጨዋ ልጅ ጨዋ ንግግር ዐዋቂ
ሲቀመጥ ተጫዋች ሲኼድ ተናፋቂ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ዓይናለም በጸና፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የአየር ንብረቱ ወይና ደጋ ወይም ደጋ በኾነ አካባቢ የሚኖሩ ጎረምሳዎች በክረምቱ ወራት የቀንድ ከብቶቻቸውና ፍየሎቻቸው በቅዝቃዜና በግጦሽ እንዳይቸገሩ ሙቀት ወዳለበት ቆላማ ቦታ ወስደው እየጠበቁ ይከርማሉ፡፡ በዚህን ወቅት ከብቶቻቸው በዱር አራዊት እንዳይጠቁ እሾኻማ የኾነ ዛፍ በመቁረጥ በረት፤ ለራሳቸው መኖሪያ ደግሞ ደረባ ተብሎ የሚጠራውን ጎጆ ይሠራሉ፡፡ ከብቶቹን የሚጠብቁት ጎረምሳዎች ደግሞ ደረብተኛ በመባል ይጠራሉ፡፡ ቀለባቸውን በተመለከተ ጥገት ላሞች ካሉ ራሳቸው እያበሰሉ በወተታቸው ይመገባሉ፡፡ ይህ የማይቻል ከኾነ ግን ከቤተሰቦቻቸው ሥንቅ እየመጣላቸው ከብቶቻቸውን እየጠበቁ ይከርማሉ፡፡ እነዚህ ደረብተኞች ከከንፈር ወዳጆቻቸው ተነጥለው ስለሚከርሙ በመካከላቸው ከፍተኛ የኾነ ናፍቆት ይኖራል፡፡ ይህንን ናፍቆታቸውን የሚወጡት ደግሞ ልጃገረዶቹ ለእንጨት ለቀማ ወደደረባ የመኼድ አጋጣሚ ሲኖራቸው ነው፡፡ በዚህን ወቅት ከከንፈር መሳሳም በተጨማሪ ጎረምሳው የምትታለብ ላም ካለችው የከንፈር ወዳጁን ወተት ያጠጣታል፤ ጠጉሯንም ቅቤ ይቀባታል፡፡ ይህ ኹነት ለልጃገረዶቹ ከፍተኛ የኾነ ትዝታ ጥሎባቸው ያልፋል፡፡

የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የኾነችው ግለሰብም ለማገዶ የሚኾን እንጨት ለመስበር ወደቆላ ብትወርድም የከንፈር ወዳጇ የሚገኝበት ደረባ ወለቃ በተባለው ወንዝ አካባቢ በመኾኑ ልታገኘው አልቻለችም፡፡ በግጥሙ ሦስተኛው ስንኝ ላይ እንደተጠቀመው ልጂቷ በዕድሜ ተከታታይ የኾኑ የአንድ ሰው ወንድ ልጆችን በከንፈር ወዳጅነት ይዛለች፡፡ ከኹለቱ ግን ለትንሹ ልቧ አድልቷል፡፡ በዚህ የተነሣ ከአፉ የሚወጣው ትንፋሽ እንደሎሚና ትርንጎ ሽታ ይጣፍጣል በማለት አወድሳዋለች፡፡ በተለይም ሎሚ ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች የልጃገረዶችና የጎረምሳዎች የፍቅር መግለጫ ተምሳሌት ኾኖ ያገለግላል፡፡ ይኼውም ከንፈር ለከንፈር ለመሻማት ጋቢ ተከናንበው ቁጭ ባሉበት ጊዜ ከኹለት አንደኛቸው ያመጡትን ሎሚ ልጠው በመካፈል ይመጥጣሉ፡፡ አለበለዚያም በገጸ በረከትነት ይሰጣጣሉ፡፡

ግጥሙን ያዜመችው ልጃገረድ የከንፈር ወዳጇን በሎሚና በትርንጎ በመወከል በግብሩ ወይም በጠባዩ ጥሩ የኾነ ሥነ ምግባር ያለው፣ ከአጸያፊ ተግባር የራቀ በማለት አወድሳዋለች። ቀጥላም የዐዋቂ፣ የአስተዋይና የሽማግሌ ልጅ በመኾኑ ራሱም ቢኾን ጥሩ፣ ማለፊያ፣ ደግ የኾነ ንግግር የሚችል ወዳጇ እንደኾነ በስንኞቹ አማካይነት አስረድታለች። በእሷና በእሱ መካከል በሚደረግ ጭውውትም ኾነ የሐሳብ ልውውጥ አነጋገረ መልካም በመኾኑ ዐብረው ተቀምጠው ባሉበት ወቅት እንኳን አሥቂኝና ጥርስ የማያስከድን፣ የሚያዝናና ንግግር ዐዋቂ እንደኾነም ገልጻለች። ከእሷ በሚለይበት ወቅት ደግሞ በናፍቆት ስሜትና በጉጉት የሚፈለግ ተወዳጅ መኾኑንም መስክራለች። በአጠቃላይ ልጃገረዷ የከንፈር ወዳጇን የሰው ወዳድነቱን እና የፍቅር ዐዋቂነቱን ውስጣዊ ሰብዕና በማንጸባረቅ ከፍተኛ የኾነ የመውደድ ስሜቷን ባቀነቀነቻቸው ስንኞች ለመግለጽ በቅታለች።

5.3.1.3. ክብረ በዓላት

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች ከሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መካከል የተለያዩ ክብረ በዓላት ተጠቃሾች ናቸው። የደርግ አገዛዝ እስካከተመበት እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ምንም ዓይነት የሃይማኖት ልዩነት ሳይኖር በቅዱስ ዮሐንስና በመስቀል በዓላት ዋዜማ ማታ ላይ በየቤቱ በር ችቦ ከበራ በኋላ ልጃገረዶቹ ሎሚያቸውን እና አርቲያቸውን በመያዝ አማካይ በኾነ ቦታ ተሰባስበው ሌሊቱን በሙሉ ዐታሞ እየመቱ ዘፈኑን ያወርዱታል። ጎራ ዙረው፣ ወንዝ ተሻግረው የሚመጡት ጎረምሳዎች ደግሞ ድልቂያውንና ሆታውን ያቀልጡት ነበር። በበዓላቱ ዕለት ከሰዓት በኋላም ቢኾን ኹለቱም ጾታዎች ተገናኝተው ሲጫወቱ፣ ከንፈር ለከንፈር ሲሳሳሙ ይውሉ ነበር። በዚህም የየበዓላቱን መልካምነት ለጎብረተሰቡ ሲያበስሩ ነበር። ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በነበረው የመንግሥት አስተዳደር ግን የልጃገረዶቹም ኾነ የጎረምሳዎቹ የጨዋታ ክዋኔ እየተከለከለ በመምጣቱ እንደ ቀድሞው ድምቀት እንደሌለው ከመስከረም 05 — 09/2013 ዓ.ም በሦስቱም ወረዳዎች በተካኼደው የቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉትና የባህሉ ባለቤት የኾኑት ተወያዮች በቁጭት ነግረውኛል።

ከላይ በተጠቀሱት በዓላት በልጃገረዶቹ ይከወን የነበረው ዘፈን በአንድ ቦታ ላይ በመኾን በማንኛውም ጊዜና ቦታ የሚዘፈን እንጂ እንደከተሜዎቹ ወጣቶች ቤት ለቤት እየተዘዋወሩ “ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ” እንደሚሉት የዘፈን ዓይነት አይደለም። የዘፈኖቹ አዝማቾችም ቢኾኑ፦-

አያ በለው በለው ኧረ በለው፣
ሽጋው ባንተ ላይ ይደረባል ወይ።።

አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው፣
የሸጉ ሽመል የለም ወይ ባገር፣
አሸከርዋዬ ነይ በደመናው ላይ።።

ወፌ ይላላ ላላዬ
ነይ ነይ ደማማዬ።።
ሸጌ ለወዳጁ
ሎሚ ይሏል በእጁ።።
ሸጉ አትመጣም ወይ
ቅርብ አይደለም ወይ።።
ገደዋዬ ነይ ነይ ባይናማ ልጅ ሞት
ና ና እንጫወት ... የሚሉትይገኙበታል።።

እነዚህ አጋጣሚዎች ልጃገረዶቹ ለሰብእናቸው ጥንቃቄ የሚያደርጉባቸው፣ አምረውና ደምቀው የሚታዩባቸው ነበሩ።። ምክንያቱም የታጨ ካሉ እጮኛቸው ከእነጓደኞቹ ከሩቅ ቦታ ድረስ መጥቶ የሚያይበት፣ ያልታጨም ካሉ የሚመረጡበት አጋጣሚ ስለነበር ነው።።

ከእነዚህ በዓላት ውጭ በጥቅምት ወር "ሚጊራጉራ" እና "ጭንቁርሳ" የሚባሉ በዓላትም ቀደም ሲል በልጃገረዶች ይከበሩ ነበር።። እነዚህ በዓላት በየዓመቱ ጥቅምት አምስት "ሚጊራጉራ"፣ ጥቅምት ዐሥራ ኹለት ደግሞ "ጭንቁርሳ" እየተባሉ ይጠራሉ።። ወቅቱም "የአክርማና የስንደዶ ቀጨታ ሳምንት" እየተባለ ይጠራ ነበር።። በዚህ ሳምንት ልጃገረዶቹ ከሰዓት በኋላ ከየአካባቢያቸው ተጠራርተው የአክርማና የስንደዶ ሣር ወደሚገኝበት ቦታ ይጓዛሉ።። እግረ መንገዳቸውንም የከንፈር ወዳጆቻቸውን ያገኛሉ።። ከዚያም በሚቀጨበት ጊዜ ያለ አታሞ ዘፈኑን ያቀልጡታል።። በዚህን ወቅት የከንፈር ወዳጆቻቸው ካልመጡላቸው ልጃገረዶች መካከል አንዷ አውራጅ፡-

ቃል ግጥም 55፤- የሚጊራጉራ ያልተከተልከኝ
ባቄላ ፈልፍለህ ቀቅለህ ቆየኝ።።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አህመድ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በማለት ታዜም ነበር በማለት ወይዘሮ ሙሉ አህመድ ወደኋላ ተጉዘው በትዝታ ነግረውኛል። ልጃገረዷ በእነዚህ ስንኞች አማካይነት በአክርማውና በስንደዶ ቀጨታ ወቅት ያልመጣውን የከንፈር ወዳጅ የሴትን ሙያ አውርሰዋለች። ምክንያቱም ቀደም ሲል በነበረው የማኅበረሰቡ አስተሳሰብ ቤት ለቤት የምትውለው ሴት በመኾኗ ዱላ ፈርተህ ከቤት ከቀረህ እንደ ሴቶቹ ንፍሮ ቀቅለህ ቆየኝ በማለት በአሸሙር ሽንቆጥ አድርገዋለች። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚገኙ ልጃገረዶች የሚቀነቀኑት የቃል ግጥም ዘፈኖች ጀግኖች ይወደሳሉ፤ ይበረታታሉ። ፈሪዎች ደግሞ ይንኳሰሳሉ። በማንኛውም የቃል ግጥም ዘፈን መከወኛ የማን የከንፈር ወዳጅ ጀግና የማንኛዋ ደግሞ ፈሪ እንደኾነ የሚለይበት አጋጣሚ መኾኑንም መገንዘብ ይገባል።

የልጃገረዶቹን ዘፈን የሰሙ ጎረምሳዎችም ጋቢያቸውን ለብሰው በፉጨት በመጠራራት ልጃገረዶቹ ወዳሉበት ሥፍራ ይኼዳሉ። ከዚያም የከንፈር መሳሳም አጋጣሚ ይኖራል። በዚህም ኹለቱም ጾታዎች የወጣትነት ፍቅራቸውን ይወጡ ነበር። ከዚህ ኺደት በኋላም ጎረምሳዎቹ ይደልቃሉ፤ቀጥሎም “ሆ” ይላሉ። በመጨረሻም ወደየቤታቸው ሲኼዱ ልጃገረዶቹ እስከሚለያዩበት ጊዜ ድረስ ዘፈኑን ይቀጥሉበታል።

በእርግጥ ከላይ በተጠቀሰው የበዓል ሳምንት ጨዋታው ይደምቃል ለማለት ነው እንጂ ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናትም ቢኾን አክርማውን እና ስንደዶውን የቤት እንስሳት እስከሚግጡት ድረስ ልጃገረዶቹ በቀጨታ ቦታው ላይ እየተገኙ የቃል ግጥም ዘፈኑን ያዜሙ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የአክርማ ቀጨታው ሳምንት ሙሉ በሙሉ የቀረ መኾኑን በቦረና ወረዳ በቡድን ተኮር ውይይቱ የተሳተፉት አቶ ጠና ይመርና አቶ ንጉሴ ባሻ ነግረውኛል። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። አንደኛው ምክንያት አክርማና ስንደዶ የሚቀጨው መሶብ፣ ሌማት፣ ድርብ፣ ቁና፣ አገልግል፣ ወዘተ. የተባሉትን የቤት ዕቃዎች ለመስፋት ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን በኅብረተሰቡ የኑሮ ለውጥ የተነሣ ሰዎች የፋብሪካ ውጤቶችን ከሱቅ ገዝተው በመጠቀማቸውና ግራምጣ የተባለውንም ሣር ከገበያ በመግዛት ስፌት መስፋት በመቻላቸው ምክንያት ነው። ኹለተኛው ምክንያት፣ ልጃገረዶቹ የመደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመኾናቸው የአክርማውን እና የስንደዶውን ቀጨታ እንደኋላ ቀርነት ቆጥረውታል የሚሉ አካላትም አጋጥመውኛል። ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ አርሶ አደሮቹ ካለባቸው የግጦሽም ኾነ የሚታጨድ ሣር ዕጥረት የተነሣ ልጃገረዶቹ አክርማና ስንደዶ እንዲቀጩ ስለማይፈቅዱላቸው እንደኾነም ተጠቅሷል።

ከላይ በተጠቀሱት ክብረ በዓላት የተዘፈኑትን ቃላዊ ግጥሞች በተፈጥሯዊ ዐውድ ማግኘት ባይቻልም በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መካከል ጥቂት ስንኞችን ብቻ በመውሰድ ለአብነት እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 56፡- የዋርካ ቅጥይ የዋርካ ቅጥይ
አጠር ያለ ጠይም ዘለግ ያለ ቀይ፡፡
ከኪያ ከኹለቱ ምረጪ ቢሉኝ
እኔስ ለጠይሙ ልቤ አደላብኝ፡፡
ጠይም ጠይሞቹን ምን አሳመራቸው
የንጋት ጨረቃ ይመስላል ዓይናቸው፡፡
...ሽጉ አንተን ብረሳ አንተን ጠይሙን
የውሃ ላይ ሰርዶ የመሰልከውን፡፡
የውሃ ላይ ሰርዶ ሥፍራ የተመቸው
እንዳ ነው ፍቅራችን የማይሰለቸው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ማርቆስ መክብብ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በጥናቱ ማኅበረ ባህላዊ ዳራ ላይ አንዲት ልጃገረድ ለከንፈር ወዳጅነት በጎረምሳዎች የመመረጥ ዕድሏ ከፍተኛ እንደነበር፣ የሴቷ ምርጫ ግን በወንዶች ተጽዕኖ ሥር የወደቀ እንደሆነ ተገልጾ ነበር፡፡ ኾኖም ግን የልጃገረዶቹ የቃል ግጥም ዘፈኖች በአብዛኛው በጠይሞች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ባህሉ ስለማይፈቅድላቸው ነው እንጂ ልጃገረዶቹም ቢኾኑ የከንፈር ወዳጆቻቸው ጠይም ቢኾኑላቸው እንደሚመርጡ በአእምሯቸው ውስጥ ያለው አመለካከት ያንጸባርቃል፡፡ ለዚህም ማንጸሪያው ከላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ አምስቱ ስንኞች የተገነቡት ጠይምነትን መሠረት አድርገው ነው፡፡ በመጨረሻም ጠይም ሰው በተወዳጁ ዘንድ በቀላሉ የማይረሳና የማይሰለች መኾኑም ተገልጿል፡፡

ምንም እንኳን ዋርካ በርካታ ቅርንጫፎች ያሉትና በጣም ትልቅ ዛፍ ቢኾንም አጠር ያለውና ጠይሙ ጎረምሳ ግን ከዋርካው ቅጥያዎች ጋር ሲነጻጸር እንመለከተዋለን፡፡ እንዲህ ያለ ተክለ ሰውነትና ጠይም መልክ ያለው ጎረምሳ፣ እንደዚሁም ቀይ የኾነ ወጣት ለልጃገረዷ ለፍቅር ምርጫ እንደቀረቡላት ከግጥሙ እንገነዘባለን፡፡ እሷ ግን ኹለቱም ዓይነ ዐዋጅ ሳይኾኑባት ልቧ ለጠይሙ እንደሚያደላ ገልጻለች፡፡ በመቀጠልም ጠያይም በኾኑ ወጣቶች ውበት በጣም ስለተደነቀች "ጠይም ጠይሞቹን ምን አሳመራቸው" በማለት አቀንቃኟ ትጠይቃለች፡፡ እሷ የጠየቀችው ግን የሚታወቀውን እና የተረጋገጠውን ጉዳይ በመኾኑ ከተደራሹ ወይም ከአድማጩ መልስ የማያሻ የንግግር ዓይነት ነው፡፡ ምክንያቱም ማንም ሰው ቢኾን እንዲህ ያለ ጥያቄ ቢቀርብለት ፈጣሪ ሲሠራቸው ውሎ ሲሠራቸው ያደረ ስለኾነ በፈጣሪ ሥራ መግባት ክልክል ነው ሊል ይችላል፡፡ አለበለዚያም ከመልከኛ ቤተሰብ አብራክ ስለተገኙ ነው የሚልም

አይጠፋም። በመቀጠልም ጎረምሳዎቹ ጎላ ጎላ ያለ ዓይን ያላቸው መኾኑን ለአድማጭ አግዝፎ ለማሳየት ሲባልም ትላልቅ ዓይኖቻቸው በንጋት ወቅት የተፈጥሮ ብርሃኗ በሰማይ ላይ ደምቆ ከሚታይ ጨረቃ ጋር ተነጻጽረው ቀርበዋል።

በመጨረሻዎቹ አራት ስንኞች እንደተመለከትነው ደግሞ የጠይምነት ውበት የእርጥበትና የልምላሜ ሥረ መሠረት በኾነው ውሃ ላይ ሥር እየሰደደ ከተንሰራፋው የሰርዶ ሣር ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል። ከዚህ አኳያ ልጃገረዷ በሰርዶ የተመሰለውን የከንፈር ወዳጇን ፍጹም ልትዘነጋው ወይም ከአእምሮዋ ውስጥ ልታወጣው እንደማትችል ገልጻለች። ይህንንም ያደረገችው በአጠገቧ የሌለ ፍቅረኛዋን ግን ደግሞ ፊት ለፊቷ እንዳለ አድርጋ በመቁጠር የምታናግረው በማስመሰል ነው። በውሃ ላይ ሥር በመስደድ ከተንሰራፋው የሰርዶ ሣር ጋር የተነጻጸረው ጠይምነት ብቻ አይደለም። በእሷና በእሱ መካከል ያለው ከፍተኛ የመዋደድ ስሜትም ጭምር ነው። ስለዚህ የኹለቱም ፍቅር ምንም እንከን ስለማይወጣለት በጭራሽ ሊሰለች እንደማይችል ባቀነቀነቻቸው ስንኞች አስረድታለች። በጥቅሉ ልጃገረዷ የጠይም ልጅ ፍቅር አይሰለችምና ጠይም መውደዴን አልተውም ብላለች።

5.3.1.4. በሰብል መጠበቂያ ቦታ የምልልስ ግጥሞች

በቡድን ተኮር ውይይቶች እንደተገለጸው በማሳ ላይ ያለ ሰብል በቤት እንስሳት፣ በዝንጀሮ፣ በጦጣ፣ በወፍ፣... በመበላት ከፍተኛ የኾነ ጉዳት እንዳይደርስበት በሰዎች ይጠበቃል። በተለይም እንደ ማሽላና ዘንጋዳ የመሳሰሉት ሰብሎች ፍሬ በሚይዙበት ወይም በሚዘረዝሩበት ወቅት በወፍ እንዳይበሉ ከማሳው መካከል ማማ ተሠርቶ በደረሰ(ች) ወንድ ወይም ሴት ልጅ ይጠበቃሉ። ጠባቂዋ ሴት ልጅ ከኾነችና በተመሳሳይ ተግባር የተሰማራው ድንበርተኛ ጎረምሳ የእሷ የከንፈር ወዳጅ ከኾነ እርስ በርሳቸው እየተቀባበሉ የሚያቀነቅኗቸው ቃላዊ ግጥሞች ይኖራሉ። በዚህ መሠረት የወፍ ጥበቃ ለቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚ እንደኾነ መረዳት ይቻላል። ቃል ግጥሞቹ አዝማችና ዜማ የሌላቸው ባለ መንቶ ስንኞች እንደኾኑ ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ ቀጥሎ በአንድ ስፍራ (Scene) ላይ ወፍ ጠባቂዋ ልጃገረድ የከንፈር ወዳጇ እንደ እሷው ለጥበቃ መምጣቱን ካረጋገጠች በኋላ ጮክ ብላ ያንጎራጎረችውን ግጥም ቀጥሎ እንመልከት። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር የቀረቡትን ሁሉንም መንቶ ቃል ግጥሞች በ03/07/2012 ዓ.ም የነገረኝ በከለላ ወረዳ የሚኖር ሀሚድ አሸብር የተባለ መረጃ ሰጪ ነው።

ቃል ግጥም 57፡- በረሃ ወርጄ ወፍ እጠብቃለሁ
እበላው አልበላው እኔ ምን ዐውቃለሁ

በማለት አንጎራጉራለች። እዚህ ላይ ልጃገረዷ “እበላው አልበላው” ያለችው ለእኛ ለአድማጮች እየጠበቀችው ያለውን አዝመራ ይመስለን ይሆናል። ይኹን እንጂ ከዚህ በስተጀርባ ያመሰጠረችው ነገር አለ። ይሄውም ወፍ የምትጠብቀው በበረሓ አካባቢ ስለኾነ በወባ በሽታ ተይዤ ብሞት ከአንተ ከከንፈር ወዳጄ ጋር ተገናኝቼ ፍቅሬን ሳልጨርስ እንዳው በጅምር ትቀርብኝ ይሆን ወይ በማለት ማንም ሰው እንዳያውቅ አድርጋ የልቧን ትነግረዋለች። እሱ ደግሞ የእሷን ቃል ግጥም ሰምቶ፡-

ቃል ግጥም 58፡- እበላው አልበላው ብለሽ የዘፈንሺው
ምን ያሰብሺው አለ ምን የጠረጠርሺው

በማለት መልስ ሰጥቷታል። በአንድ በኩል ይፋ ያልኾነውን ድብቅ ጉዳይ እሱ ያልተረዳው ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ እሱም ቢኾን ሌላ ጎረምሳ አፍቅራ እኔን ተትወኝ ይኾን ወይ የሚለውን ፍራቻ በአእምሮው ውስጥ እያወጣ እያወረደ ሊኾን ይችላል። እሷ ደግሞ የምሥጢሩን ትርጓሜ በማቅለል፡-

ቃል ግጥም 59፡- ቆላ ተቀምጬ ከንዳዱ ሀገር
ማሰብ መጠርጠሬ እንደምን ይቅር

ብላዋለች። ሰብላችን በወፍ እንዳይጠቃ ቆላ ወርጄ እየጠበቅሁኝ እያለሁ ትኩሳት ባለው የወባ በሽታ ታምሜ እሞታለሁ ብዬ ሐሳብ ቢገባኝ፣ ሥጋት ቢያድርብኝ እንደዚህ መኾን አይገባሽም ነው ወይ የምትለኝ ስትለው እሱም በበኩሉ፡-

ቃል ግጥም 60፡- አይዞሽ የእኔ አንገቶ አይዞሽ የእኔ ዓይናማ ለአንች ነብስ እኔ አለሁ
የንዳድ መድኀኒት እኔ አመጣልሻለሁ

ብሏታል። በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ አንገትና ዓይን የተጠቀሱት የሰውነት ክፍሎች በመኾናቸው ብቻ አይደለም። ከቅርጽ አኳያ ሰውን የመሳብ ኃይል ያላቸውና ውበትን ገላጭ በመኾናቸው ነው። በዚህ መሠረት በልጃገረዷ ረኻም አንገትና ጎላ ጎላ ባሉ ዓይኖች የተማረከው ጎረምሳ እስከ ዕለተ ሞትሽ ድረስ ከሥጋሽ ጋር ተዋሕዳ የምትኖረው ነፍስሽ በወባ በሽታ፣ በችግር ወይም በአሳሳቢ ኹኔታ ላይ በምትኾንበት ጊዜ ፈውስ የሚሰጥ መድኀኒት አመጣልሻለሁ በማለት ቃል ገብቷል። በዚህን ጊዜ እሷም፡-

ቃል ግጥም 61፡- የንዳድ መድኀኒት ካመጣህልኝ
ውጣ ከማማው ላይ ትንሽ አጫውተኝ

በማለት የከንፈር ወዳጇ ለገባላት ቃል ውለታ ለመክፈል ስትል ለወፍ ጥበቃ እንዲያመች ተብሎ በአዝመራው መካከል በተዘጋጀው ረኻም አልጋ ወይም ማማ ላይ እንዲወጣና

እንዲያጫውታት በቋጠረቻቸው ስንኞች አማካይነት መልእክት አስተላልፋለች። እዚህ ላይ የከንፈር ወዳጅነት ጨዋታ እስከምን ድረስ ነው የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ቀድሞ በነበረው የአካባቢው ባህል መሠረት የከንፈር ወዳጅነት ክዋኔው ከንፈር ለከንፈር ከመሳሳም ያለፈ ወደሌላ ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽሞ የሚያመራ አልነበረም። በዚህ መሠረት የኹለቱ ግንኙነት በገደብ እንደነበር የተለያዩ መረጃ ሰጪዎች ገልጸዋል። ይህንን አጋጅ የኾነውን የማኅበረሰብ ልማድ አክባሪ ጎረምሳም፦

ቃል ግጥም 62፡ ከማማው ወጥቼ እንዳላጫውትሽ
አማረጣት ብለው ይቆጣሉ አባትሽ

እያለ አዚሟል። እንደሚታወቀው ወላጆች ለዐቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት ልጃቸው ምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳትፈጽም ድንግልናዋን ጠብቃ ለትዳር እንዲትበቃ በጽኑ ይፈልጋሉ። ለዚህም ነው ጎረምሳው ለከንፈር ወዳጁ ከማማው ላይ ወጥቼ በሚያዝናና ቀልድ፣ ወሬና በመሳሰሉት እንዳላጫውትሽ አባትሽ አባለጋት ብለው በቁጣ ስሜት ይዘልፉኛል በማለት ሥጋቱን በመንቶ ስንኞቹ ገልጿል። እሷም ለከንፈር ወዳጇ ልጨኛ ወይም ቁም ነገረኛ ናትና፦

ቃል ግጥም 63፡- እንዳውም ልጁ ብትኾን ይሉኝተኛ ነህ
አባቴ የት አይቶ ይቆጣል ብለህ

በማለት ከፍርሃት የተነሣ የተሸበረውን ጎረምሳ ስታደፋፍረው ታይታለች። በመቀጠልም አንተ ብትኾን ሙሉ በሙሉ የሰው አስተያየት የምትፈራ፣ ምን ይሉኝ የምትል፣ ሰዎች ይታዘቡኛል ብለህ አንድን ነገር ከማድረግ የምትቆጠብ ሰው ነህ። ግን አባቴ የት ኾኖ ያይሃልና ነው ይቆጣኛል ብለህ የምትፈራው ስትለው እሱም በበኩሉ፦

ቃል ግጥም 64- አባትሽ ካላዩ ካልተቆጡማ
ከምድር እንጫወት ውረጅ ከማማ

ብሏታል። ወጣቱ አፍቃሪ በቋጠራቸው መንቶ ስንኞች አማካይነት አባትሽ የትም ኾነው ካላዩኝ ለወፍ ጥበቃ እንዲያመች ብለው ከሠሩት ማማ ላይ ውረጂና በማሳው ውስጥ ባለው ሰብል ተደብቀን በነጻነት እንጫወት ባላት ጊዜ እሷ ግን በሐሳቡ አልተስማማችም። ምክንያቱም ከዚህ ውጪ የሚፈጸመውን የብልግና ተግባር የማኅበረሰቡ ባህል አይፈቅድላቸውምና ነው። እንዳውም እሷ፦

ቃል ግጥም 65፡- ትወጣ እንደኾነ ውጣ ከማማው ላይ
የማማው ሥርማ ሌላ አይኾንም ወይ

በማለት በልቧ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ገልጻለታለች። ይህ ደግሞ ከከንፈር መሳሳም ውጭ ሌላ ነገር መሥራት አለመፈለጓን ያመለክታል። ምክንያቱም “የማማው ሥርማ ሌላ አይሆንም ወይ” ማለቷ በኹኔታው እንዲትጠራጠር አድርጓታል። በፍርሃት ተውጣም ልታባልገኝ ነው ወይ ብላዋለች። ከበፊቱ የተለየ፣ መኾን ካለበትና ከተለመደው ነገር ውጪ ፍጹም ማድረግ እንደሌለባቸው ተናግራለች። እሱ ደግሞ፡-

ቃል ግጥም 66፡- ለጊዜው ነው እንጂ ለጊዜው ለዕለቱ
መች ይቀራል ብለሽ ዐብሮ መተኛቱ

ይላታል። እዚህ ላይ እነዚህ ስንኞች ኹለት ነገሮችን ያሳስቡናል። አንደኛው በማኅበረሰቡ ወግና ልማድ መሠረት አንዲት ልጃገረድ ክብረ ንጽሕናዋን ጠብቃ ካገባች በኋላ በዐሥራ አምስት ቀኗም ኾነ በወሯ ከጫጉላ ቤት ትወጣለች። ከዚያም ያላትን ናፍቆት ለማውጣት ወደቤተሰቦቿ ቤት ስትኼድ በድብቅ ውሃ ለመቅዳት ወይም እንጨት ለመስበር በሚል ሰበብ ከከንፈር ወዳጇ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልትፈጽም ትችላለች። እንደዚህ ያለው የአንዳንዶቹ ፍቅር ቶሎ ሊቋረጥ ይችላል። የአንዳንዶቹ ደግሞ የትዳር ጓደኛም ቢጠረጥር እስከመጨረሻው ድረስ ሊቀጥል ይችላል። ኹለተኛው ግን የከንፈር ወዳጅ ኾነው የቆዩ ፍቅረኛሞች እንዳጋጣሚ ኾኖ በደንቡና በሕጉ መሠረት ተጋብተው በጫጉላ ቤታቸው የሥጋ ግብር መፈጸም የሕይወታቸው ቀዳሚ ነገር ነው የሚኾነው። እነዚህን ኹለት እሳቤዎች ይዘን በእሷ አንደበት የተቀነቀኑትን ስንኞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 67፡- ዐብሮ መተኛቱ ይጠፋኛል ወይ
ማማውን ጫጉላ ማድረግህ ነው ወይ

ይህ ማለት በሀገር ወግ ልማድ መሠረት አባትህ ሽማግሌ ልከው “ልጃችሁን ለልጃችን” ተብሎ ተጫጭተን ከተጋባን በኋላ ነው በጫጉላ ቤታችን የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያለብን በማለት አቋሟን አሳውቀዋለች። በሰብል ውስጥ ያለውን ሜዳ የጫጉላ ቤት አድርገህ ልታባልገኝ ነው ወይ በማለትም በቃል ግጥሟ ሸንቁጣዋለች። ስለዚህ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በከንፈር ወዳጅነት ተቆራኝተው የቆዩ ወጣቶች ከከንፈር መሳሳም ውጭ ሌላ የብልግና ድርጊት አይሠሩም ነበር ማለት ነው። በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተፈላጊው ጉዳይ የነበረው የኮራች፣ ክብረ ንጽሕናዋን ባለማስወሰዷ የተነሣ አባትና እናቷን ያላሰደበች፣ የአካባቢውን ባህልና ወግ ያከበረች ልጃገረድ ልዕልና የምታገኝ መኾኗን ከላይ በምልልስ ከቀረቡት ስንኞች መረዳት ይቻላል።

5.3.2. በሰርግ ዕለት የሚኖረው ሥርዓት

ሰርግ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በትዳር (ባልና ሚስት ኾነው) ለመኖር እንዲችሉ የሚፈጽሙት ሥነ ሥርዓት መኾኑ የሚታወቅ ነው። የጥናቱ ተተኳሪ የኾኑት የጎብረተሰብ አባላት የሰርግ ሥርዓት የሚፈጽሙት በሀገር ባህል ወይም በሸማግሌዎች አማካይነት ሲኾን፣ ይህም ለዘመናት የኖረና አሁንም ቢኾን በሰፊው እየተተገበረ ያለ እንደኾነ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልጸውልኛል። በሰርጉ ዕለት በሙሽራውና በሙሽሪት ወገን ከእያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ሸማግሌዎች፣ እንደዚሁም አንድ አንድ የነገር አባት በተገኙበትና በምስክሮች ፊት በሀገር ባህል ደንብ መሠረት የኹለቱም ጋብቻ ዕውቅና ያገኛል። ተጋቢዎቹ ጉዳያቸው ከሸማግሌዎች በተጨማሪ በጽሑፍ ውል ከታሠረ በኋላ እነሱና ሸማግሌዎቻቸው እንዲፈርሙበት ይደረጋል። ይህ ዓይነቱ የሀገር ባህል ጋብቻ በብዙዎቹ አካባቢዎች "የሰማኒያ ጋብቻ" በመባል ይታወቃል (ዋጋው ኃይሉ፣2001፡ 47-48)።

በዚህ ጥናት ማኅበረ ባህላዊ ዳራ ላይ እንደተገለጸው የኹለቱም ተጋቢ ወላጆች ለጋብቻው ከተስማሙ በኋላ ርክክብና ፍጥጥም የሚባሉ ኺደቶች በቅደም ተከተል ይከናወናሉ። ከዚህ በኋላ ቀጣዩ ተግባር በሰርግ ዕለት የሚኖረው ሥነ ሥርዓት ነው። ይህ ዕለት የሙሽራውና የሙሽሪት ወላጆች የልጆቻቸውን አበባ የሚያዩበት፣ ልጆቹም ቢኾኑ ሦስት ጉልቻ የሚመሠርቱበት ነው። ስለዚህ ዕለቱ ከሚበላውና ከሚጠጣው መስተንግዶ በተጨማሪ ለበርካታ ቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚ ስለኾነ ሸማግሌዎች፣ ሙሽራውና ዐጃበዎቹ ሙሽራዋን ለማምጣት ከወንድ ወላጆች ቤት ባለው የስንብት፣ የጉዞ ወቅት፣ በሙሽራዋ ሰርግ ዕለትና ከቤተሰቦቿ የስንብት ወቅት ሙሽራውን እና ሙሽሪትን ለማሞገስም ሆነ ለማናደድ የተለያዩ ቃል ግጥሞች ይዜማሉ። የሚዜሙትንም ቃል ግጥሞች በቅደም ተከተል ቀጥለን እንመልከት።

5.3.2.1. ሸማግሌዎች፣ ሙሽራውና ዐጃቢዎቹ ከሙሽራው አባት ቤት በሚሸኙበትና ወደሙሽራዋ ቤት በሚጓዙበት ወቅት

ቀደም ሲል ሙሽራው ዐጃቢዎቹን፣ አባትዮው ደግሞ ታዋቂ የኾኑ ሸማግሌዎችን የሚመርጡባቸውን መስፈርቶች ለመግለጽ ተችሏል። በመኾኑም በመስፈርቱ መሠረት የተመረጡት ወጣቶችና ሸማግሌዎች ወደሙሽራው አባት ቤት እንዲመጡ በተነገሩበት ሰዓት ተሟልተው ይገኛሉ። እንደ ይማም አብዱ (2008፡47) ማብራሪያ በሙሽራው አባት ቤት በመጀመሪያ ምግብ ይበላል፤ ከዚያም አግብታ ባልተፈታች ሴት የተፈላው ቡና ይጠጣል። ይህ የሚኾነው የሙሽራው ትዳር እንደሴትዮዋ ይቃናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ቀጥሎም ሰርገኞቹ ከቤት ይወጣሉ። ልጃገረዶችም ኾኑ ያገቡት ሴቶች ለሙሽራው መሸኛ የሚኾኑ

ዘፈኖችን በደመቀ ኹኔታ ይዘፍናሉ። ጎረምሳዎቹም ዐቢራው እስከሚነሣ ድረስ ሆታውን ያቀልጡታል። በመጨረሻም ሆታው ሳያቋርጥ ሙሽራው ለእሱ የተመረጠውን ፈረስ ጋልቦ ከዐጃቢዎቹና ከሽማግሌዎቹ ጋር በመኾን ጉዞው ወደሴቷ አባት ቤት ይኾናል። በዚህ ዕለት የሙሽራው አባት ከሰርገኞቹ ጋር አብሮ አይኼድም። ምክንያቱም ጋብቻውን በተመለከተ አስፈላጊ የኾኑ ስምምነቶችን በሙሉ ከሙሽራዋ ቤተሰቦች ጋር አስቀድሞ ስለጨረሰና ለሰርጉ የጠራቸውን እንግዶች በመኖሪያ ቤቱ ኾኖ ማስተናገድ ስላለበት ነው።

ሙሽራው፣ ዐጃቢዎቹና ሽማግሌዎቹ ከቤት ወጥተው ወደሙሽራዋ ቤተሰቦች ቤት እስከሚደርሱ ድረስ ያሉት ኹነቶች የቃል ግጥም መከወኛ አጋጣሚዎች በመኾናቸው ከሴቶች የዘፈን እና ከጎረምሳዎቹ የሆታ ቃል ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን ብቻ ለአብነት በመውሰድ ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 68፡- ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ ሦስት ጊዜ
አለው መላ መላ›
ሸኝቼው ነበር በቦራው ፈረስ
እገሌ አበሉ ደኅና ቢመለስ።
ሞሰብ እሰፋለሁ አለላ ባለላ
እገሌ አበሉ ጌታው በምን ይብላ።
ሻሹ መቀነቴ ሻሹ መቀነቴ
እገልዬ አበሉን በይልኝ በሞቴ።

(ከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 03/07/2012)

እነዚህ ከላይ የቀረቡት የቃል ግጥም ስንኞች በልጃገረዶች ሳይኾን ጎረቤትና ቤተዘመድ በኾኑ ሴቶች የተቀነቀኑ ናቸው። እያንዳንዳቸው መንቶዎች ካልኾኑ በስተቀር ሁሉም ስንኞች የሐሳብ አንድነት የላቸውም። ቃል ግጥሙ የቀረበበት ዜማ ደግሞ “ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ፤ አለው መላ መላ” የሚል ሲኾን፣ ሴቶቹ የሚያቀነቅኑትም ሙሽራው ከአባቱ ቤት ሲወጣ ጀምሮ ከኋላ ከኋላ ኾነው በማጀብና ጥቂት መንገድ ዐብረው በመጓዝ እየሸኙ ባሉበት ወቅት ነው። “ሸኝቼው ነበር በቦራው ፈረስ” የሚለው ስንኝም የሚያስገነዝበን ይሄንኑ ጉዳይ ነው። በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ በሰርግ ዕለት ለሙሽራው ፈረስ፣ ለሙሽሪት ደግሞ በቅሎ ተመርጠው ለመጓጓዣነት ያገለግላሉ። ፈረሱና በቅሎው በመልክም ኾነ በአገልግሎት መናኛ ወይም አልባሌ መኾን የለባቸውም። ፈረሱ እንደ ኃይለኛ ውሃ ሙላት ወደላይ ወደላይ የሚያጋምር (የሚዘል)፣ እንደዚሁም ደንገላሳ ወይም በሽምጥ የሚጋለብ፣ በቅሎዋም ብትኾን ተቀማጩን ሰው ሳትነቀንቅ እንደ እንዝርት የምትሽከረከር መኾን አለባት።

ከዚህ በመቀጠል የዘፈኑ አውራጅ የኾነችዋም ሴት ሙሽራው ግንባሩ ላይ ጥቁር ወይም ቀይ ጸጉር ያለው ነጭ ፈረስ ጋልቦ ሙሽራዋን ለማምጣት ሲኼድ ከግራ ከቀኝ፣ ከፊት ከኋላ በመኾን ሸኝቹው ነበር ያለችው የፈረሱን ውበት ለማሳየት ነው። በቃል ግጥሙ ኹለተኛው ስንኝ ላይ “እገሌ አበሉ” የተባለበት ምክንያት በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያት በተለያዩ የሙሽሮች ስም እየተተካ ዘፈኑ የሚቀነቀን ስለኾነ ነው። ምን ጊዜም ቢኾን የወንድ ሙሽራ ወገኖች ሙሽራው መጥፎ ድርጊት ወይም አጋጣሚ ሳይደርስበት በደኅና ደርሶ እንዲመለስ ጸሎት ያደርጉለታል። በግልጽ አነጋገር ያለ ችግር፣ ያለ ሁከት ወደአባቱ ቤት እንዲመለስ መልካሙን ሁሉ ይመኙለታል።

ሙሽራው የጋብቻ ሥርዓቱን ከሚፈጽምበት ዕለት ጀምሮ ከጫጉላ ቤቱ እስከሚወጣ ድረስ የአለቃ አለቃ ወይም የበላይ አዛዥ ተደርጎ ስለሚቆጠር ጥናቱ በተካኼደበት ማኅበረሰብ ዘንድ “ጌታ” እየተባለ ነው የሚጠራው። ዐጃቢዎቹም ኾኑ እኩያዎቹ ደግሞ ለእሱ አሽከሮች ናቸው። ይህ ማለት ልክ እንደ የልፍኝ አሽከር አንጣፊ፣ አልባሽ፤ መጫሚያ አቀባይ፣ ... በመኾን ያገለግላሉ። አቀንቃኟም ለዚህ ዓይነቱ ጌታ በአሽከርነት ወይም በሎሌነት ያደረች በመኾኗ በቀለም በተነከረ ስንደዶ ወይም አክርማ ለመመገቢያ የሚኾን የስፌት ዕቃ እሰፋለታለሁ በማለትም አዚማለች። በመጨረሻ ላይ ወርዱ ጠባብ፣ ቁመቱ ረዥም የኾነና ከጥጥ ተሠርቶ እንደመቀነት የሚያገለግለውን ነጭ ራስ ማሠሪያ የሴትን ባሕርይ በማላበስ አዲሱን ሙሽራ ‹‹ላንተ ስል ነፍሴ ከሥጋዬ›› ትለይልህ በይልኝ በማለት ገልጻለች።

ልጃገረዶቹም ቢኾኑ በፊናቸው የሰርግ ሥርዓት በሚከወንበት አጋጣሚ ሁሉ እየተገኙ ሙሽራውን አወዳሽ የኾኑ የፍቅር ዘፈኖችን ሲያዜሙ ይደመጣሉ። ለአብነትም የሚከተሉትን ስንኞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 69፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው ሦስት ጊዜ
ሳብ አለ ገበሬ በጫጉማ በሬ
ሽጋ የወለደ ዘሩ ሽጋ ይሁን
ጧት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን
ኅፈሬው ይመስላል ንብ የሰፈረበት
ዐንገቱ ይመስላል ጠጅ የፈሰሰበት
የእሱ እናት ይውለዱ ሌላው ይምከንበት።
(ቃለ መጠይቅ፣ አሚናት ጌታሁን፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

አቀንቃኟ ለዘፈኗ በአዝማችነት በተገለገለችባቸው ስንኞች መነሻ ላይ አንድ ሰው ታላቅ ወንድሙን ወይም ዘመዱን ለመጥራት በሚጠቀምበት የአክብሮት ቃል “አያ” ካለች በኋላ ቀጥላ ደግሞ “በለው በለው” ትላለች። በዚህም ሞት አይፈሬ የኾነውን የጦር ገበሬ ምታው ወይም

ደብድበው ለማለት አይመስለኝም። ምንም እንኳን ዐውዱ ሰርግ ቢኾንም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረውን ጀግና አርሶ አደር ጫጉማ በሬውን ጠምዶ በሚያርስበት ጊዜ እንዲተጋና ጠንክሮ እንዲሠራ የጀግንነት መንፈሱን ለማነሣሣት ሲባል ሊኾን ይችላል። ምክንያቱም በማንኛውም የሙያ መስክ የተሰለፈ ሰው ውጤታማ እስከኾነ ደረስ ጀግና ሊሰኝ ይችላልና ነው። በመቀጠልም ያማረ፣ ቆንጆ፣ ውብና በፍቅር አማላይ የኾነውን ሙሽራ ከአብራኳ የወለደች እናት (ምንም እንኳን ስንኙ በወንዴ ዖታ የተገለጸ ቢኾንም) ተወላጅ የኾኑ ዘመዶቿ ሁሉ እንደ ልጇ ሽጋ እንዲኾኑላት ልጃገረዷ በስንኞቹ አማካይነት መልካም ምኞቷን ገልጻለች። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኹኔታም በፍቅር አማላይ በኾነው ወጣት የተነሣ የሐሳብ ማደሪያ የኾነው አእምሮዬ ከሥጋዬ ተለይቶ ንጋት ላይ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ቢበታተንም እስካሁኗ ሰዓት ድረስ ከኼደበት አልተመለሰም ብላለች።

በመጨረሻዎቹ ኹለት ስንኞች ደግሞ የጎረምሳውን ጎፈሬ በዛፍ ላይ ከሰፈረ ንብ፣ አንገቱን ደግሞ በጉሮሮ እየተንቆረቆረ ካለ ጠጅ ጋር የማነጻጸር ድርጊት ተፈጽሟል። ይህ የኾነበት ምክንያት በዛፍ ላይ የሰፈረው ንብ ከአካባቢው ተለይቶ እንደሚቆለል ሁሉ የወጣቱ ጸጉርም ተስተካክሎ የተከረከመ፣ በጥንቃቄ የተበጠረና ቀጥ ብሎ የቆመ መኾኑን ለማሳየት ነው። ማርና ጌሾን በማደባለቅ የሚጣለው ጠጅም መቃ በመሰለው የጎረምሳው አንገት ሲንቆረቆርና ኮለል ብሎ ሲወርድ የሚታይ መኾኑን የቃል ግጥሙ ዘፈን አድማጭ በቃላት አማካይነት ከአምስቱ የስሜት ሕዋሳት በእይታ ልብ እንዲልና እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው። ታዲያ እንዲህ ባለው ተፈጥሯዊ ውበት ያመረውን ወጣት ምንጊዜም መውለድ ያለባት የእሱ እናት ብቻ ስትሆን ሌላይቱ ግን መውለድ ወይም ፍሬ መስጠት የማትችል ኾና ለዘለዓለሙ ትምክን የሚለውን አንድምታም አቀንቃኟ ገልጻለች።

ከልጃገረዶቹ የቃል ግጥም ጎን ለጎን ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት ሰርገኞቹን ለመሸኘት የተለያዩ ተግባራት በቤት ውስጥ ይከናወናሉ። ከዚያም ሙሽራውና ዐጃቢዎቹ ከቤት ሲወጡ ቤተዘመዱ በዘፈንና በእልልታ ይሸኟቸዋል። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ እየተቀባበሉ በሚያወራርዱ “ሆ” ባዮች አማካይነት ጎረምሳዎቹ በጉሏቸው ላይ በማጀቢያነት የሚገለገሉበትን ዱላ ወደላይ አቁመው የሆታውን የቃል ግጥሞች በጎብረት ያወርዱታል። በእዚህ አጋጣሚ ከሚከወኑት ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን በሚከተለው ኹኔታ ለማየት እንሞክር።

ቃል ግጥም 70፡- ያሆ ያሆ
ቆሌ ታመረው
ና በለው ና በለው።

ኹለት ጊዜ

ትመታ እንደኾን ምታ በእግርህ
ና በለው ና በለው
እሾኽም የለው የሚወጋህ፡፡
ና በለው ና በለው፡፡

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 03/07/2012)

ከላይ ያሉትን ስንኞች እንደተመለከትነው የሆታ ቃል ግጥሞች ለፍቅር፣ ለሥራ፣ ወዘተ. ከማነሣሣት ይልቅ ደም ደም የመሸተት፣ ጠብ ወይም ዐምባጓሮ የመፈለግ መንፈስ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ስለኾነም በቃል ግጥሙ እንደቀረበው በተበቺሳና በሌሎች አጋጣሚዎች በተቧደኑ ጎረምሳዎች መካከል ግጭቶች በሚከሠቱበት ወቅት በተቃራኒ ወገን ያለውን ጎረምሳ ማጥቃትም ኾነ በመመከት ራስን መከላከል የሚቻለው ቆሌ ተብሎ በሚጠራው ጠንካራ ዱላ ነው፡፡ ስለዚህ የግጥሙ አዝማች ኾነው ባገለገሉት ስንኞች እንደምንመለከተው ዐምባጓሮ ያሻውን እና ዱላ የሸተተውን ጎረምሳ “ቆሌ ካመረው” ብሎ በመጥራት ደብድበው፣ ምታው፣ ወዘተ. የሚሉ መልእክቶች ተላልፈዋል፡፡ የሆታ ክዋኔ በቁም ሳይኾን ሰውነትን ለማሟሟቅ እንደሚደረግና ዝግ ባለ የአካል እንቅስቃሴ (ሶምሶማ ዓይነት) ስለኾነ የጎረምሳዎቹ እግር ዋና ማድመቂያ ኾኖ ያገለግላል፡፡ በመኾኑም መሬቱ እንደ መርፌ የሚዋጋ የዕዕዋት አካል የለውምና አጥብቀህ መሬቱን ምታ በማለት የሆታ አውራጁ ተቀባይ የኾኑትን ጎረምሳዎች ያነቃቃል፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ “እሾኽም የለው የሚወጋህ” ሲል እኛን የሚደፍር ክፉና ነገረኛ የኾነ ሰው አያጋጥመንም የሚለውንም ሐሳብ በተምሳሌታዊ የአነጋገር ብልሃት ለማስተላለፍ የተሞከረ ይመስላል፡፡

ቃል ግጥም 71፡- ያሆ ያሆ
መች ተዋጋና
ያሻዋል ገና ያሻዋል ገና
እያት ሽመሌን ተመልከታት
ያሻዋል ገና ያሻዋል ገና
ደም እንደ ውሃ የማጠጣት፡፡
ያሻዋል ገና ያሻዋል ገና

ኹለት ጊዜ

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣22/05/2012)

ከዚህ የሆታ ቃል ግጥም ውስጥ ሌላው አዝማችም ቢኾን “መች ተዋጋና” ሲል ጎረምሳዎቹ ወደፊት ዐምባጓሮን እንደሚሹ ያመላክታል፡፡ በእርግጥ ለዚህ አዝማች መነሻ የሚኾን አጋጣሚ ማንሣት ተገቢነት አለው፡፡ ይሄውም ሙሽራውና ዐጃቢዎቹ ከሙሽራዋ አባት ቤት ሰጋበዙ ቆይተው በመጨረሻ ላይ ሙሽሪትን ይዘው ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ሙሽራውና ሙሽራዋ ፈረስና በቅሎ ከጋለቡ በኋላ የሙሽራው ዐጃቢዎች “ሆ” ይላሉ፡፡ የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጅም እንደዚሁ

ከጓደኞቹ ጋር ኾኖ “ሆ” ይላል። ከኹለቱም “ሆ” ባዮቹ መካከል አንዱ ጎረምሳ ወደ ሌላው በመግባት ለመደባደብ ይሞክራል። ከዚያ እርስ በርስ መደባደብ ይጀምራሉ። ከ1980ዎቹ መጨረሻ በፊት ይህ ዓይነቱ ድርጊት ሲከወን የነበረው የከንፈር ወዳጇ ሙሽራዋን ለመንጠቅ፣ የሙሽራው ዐጃቢዎች ደግሞ ላለመቀማት ሲባል እንደነበር በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው ጭምቃ ሐሳብ ያመለክታል።

ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ይህ ዓይነቱ ክሥተት የቀረ ቢኾንም እንዳጋጣሚ በዱላ የሚፋለምና ጉዳት የሚያደርስ አካል ከመጣ እኛም ከአሁን ቀደም ተፋልመን አናውቅምና ሻ ብለናል (ፈልገናል) ለማለት ፈልገው ነው ጎረምሳዎቹ በአዝማቹ ያቀነቀኑት (ይማም አብዱ፣2008፡47)። የሙሽራው ዐጃቢዎች ድካም ካልተሰማቸው በስተቀር እነዚህን መሰል የሆታ ቃል ግጥሞች እያዜሙ ወደሙሽራዋ አባት ቤት ሲቀርቡ ደግሞ አንድም የእነሱን መምጣት ለማስታወቅ፣ በሌላ በኩል የከንፈር ወዳጅ የሚባሉትን በነገር ጎሸም ለማድረግ የያዝኩትን ዱላ ልብ ብለህ ተመልከት በማለት አቀንቃኙ ያዜማል። እዚህ ላይ ዱላ ዱላ ነው፤ ታዲያ ምንነቱን ነው በተቃራኒ ወገን ያሉ ጎረምሳዎች አስተውለው የሚመለከቱት የሚል ጥያቄ ይነሣ ይኾናል። በጥንቃቄ ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ የሚውለውን ዱላ ነው የሆታው አውራጅ ልብ ብለህ ተመልከት ያለው።

“ደም እንደ ውሃ የማጠጣት” በሚለው የመጨረሻው ስንኝ ላይ ደምና ውሃ በፈሳሽ ገጽታቸው ተመሳስለዋል። እንደሚታወቀው ውሃ ለመጠጥና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል ፈሳሽ ነው። ደም ደግሞ በሰው አካል ውስጥ የሚዘዋወርና ለሕይወት መሠረት የኾነ ነገር ነው። ስለዚህ ደም ከሸተተው ጎረምሳ ጋር ተደባድቤ እሱ የሚያዘራው ደም በዱላዬ ላይ ልክ እንደ ውሃ ይፈስባታል ለማለት ተፈልጎ ነው። እዚህ ላይ ሰብኣዊ ፍጡር ያልሆነው ዱላ ሰብዓዊ ድርጊትን በሚያላብሰው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት የተገለጸ መኾኑንም ልብ ይሏል።

5.3.2.2. ሙሽራዋ በሰርጓ ዕለትና ከቤተሰቦቿ የስንብት ጊዜ

በሙሽራዋ ሰርግ ዕለት ሙሽራውና ዐጃቢዎቹ ከዳስ[25] ገብተው ሲስተናገዱ ልጃገረዶቹ ደግሞ ከዳሱ ራቅ ባለ ሜዳ ላይ ይኾኑና የመሰነባበቻ ዘፈን ይዘፍናሉ። ምንም እንኳን ሙሽራዋ ውስጣዊ የደስታ ስሜት የሚሰማት ቢኾንም “ወግ ነውና ሲዳሩ ማልቀስ” እንደሚባለው ማልቀሷ አይቀሬ ነገር ነበር። ይህም የሚኾነው በኹለት ዓቢይ ምክንያቶች አንደነበር የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልጸውልኛል። አንደኛው፣ ቀደም ባለው ወቅት ልጃገረዶች የሚዳሩት

[25] በገጠሩ ማኅበረሰብ ድግስ ያለባቸው ሰዎች እንግዶቻቸውን በአንድነት ለመጋበዝ ያስችላቸው ዘንድ እንደ አጠና፣ ጨፈቃና ቅጠላ ቅጠል ባሉ የእንጨት ቅርንጫፎች የሚሠሩት ጊዜያዊ መጠለያ ነው።

በቤተሰቦቻቸው ፈቃድ በመኾኑ ምክንያት የሚያገቡትን ወጣት ሙሉ በሙሉ ባለማወቃቸው ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ ከከንፈር ወዳጆቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከቤተሰቦቻቸውና ካደጉበት አካባቢ የሚለዩበት በመኾኑ የተነሣ ነው። እነዚህን ጉዳዮች መሠረት በማድረግ በልጃገረዶች ከሚዜሙት ቃል ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 72፦- አላፈራም ወይ! አላፈራም ወይ } ኹለት ጊዜ
ያባይ ዳር እንኮይ }
እቴ ባልንጀሬ ጥቁር ማርዳሽን
ዐብረን አንውልም ወይ እንቁጣጣሽን።
ዐብረን እንውላለን ብየሽማ ነበር
ያገር ሽማግሌ ምቀኛ ባልነበር።
ያገር ሽማግሌ ቁንሳህን ያጥፋው
ልጃችን ገና ናት አይልም ወይ ሰው።
ጀንበሪቱ ገባች ተወረወረች
እገሊት አበሉ ልጅነት ቀረች።

(ቃለ መጠይቅ፣ ብርቱካን ጫኔ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ አዝማች ላይ የተጠቀሰው “እንኮይ” በበረሓ አካባቢ የሚበቅል ተክል ሲኾን፣ በተምሳሌነቱ ደግሞ ሴት ልጅን ለማሞካሻነት የሚያገለግል መጠሪያ ቃል ነው። ተክሉ ፍሬ አልያዘም ወይ የሚለውም ቢኾን ሙሽራዋ በዕድሜ ያልገፋች ወይም ያልደረሰች መኾኗን ለማመላከት ነው። ታዲያ ይቺ ዕድሜዋ ያልደረሰች ሙሽራና ባልንጀሮቿ በሕይወት ዘመናቸው ላለመነጣጠል ቃል ተገባብተው ነበር። ኾኖም ትዳር አይቀሬና ከተቃራኒ ጾታ ጋር ዐብሮ ለመኖር የሚያስችል የቁርኝት ሰንሰለት በመኾኑ የመለያየታቸው ጉዳይ የግድ ኾኗል። ጓደኞቿ ግን ቀድሞ የነበሩበትን ጊዜ በማንሣትና የገቡትንም ቃል በማስታወስ በዘመን መለወጫና የአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ቀን በኾነው እንቁጣጣሽ በአንዲነት ኾነን አናሳልፍም ወይ በማለት በአቀንቃኟ አማካይነት ጓደኞቿ ሙሽራዋን በሰርጓ ዕለት ሲጠይቋት በዓይነ ኅሊናችን እንመለከታለን። እዚህ ላይ ሙሽራዋ በአንገቷ ላይ ያደረገችው የማርዳ ጌጥ ቀለም ጥቁር መኾኑ የተገለጸው ደግሞ ማኅበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ ባለው ዕውቀት ጥቁር ነገርን በባህላዊ ተምሳሌት የመለያያ ሐሳብ መግለጫ አድርጎ በመጠቀሙ የተነሣ ይመስላል።

የሚቀጥሉት ኹለት ስንኞች ደግሞ ቀድሞ ለቀረበው ሐሳብ ምላሽ የሚሰጡ ኾነው ተገኝተዋል። በምልልስ መልክ የቀረበው ምላሽም በአቀንቃኟ እንጂ በሙሽራዋ አንደበት የተነገረ አይደለም። ምክንያቱም አቀንቃኟ የሙሽራዋን ስሜት በመረዳት ሥነ ልቦናዊ ማንነቷን አጉልታ ለማሳየት ሲባል በራሷ ድምፅ ምላሹን ስትሰጥ እንመለከታታለን። በዚህ ምልልስም ክረምቱን ዐብረን በማንጋት መስከረም አንድ ቀን በሚውለው እንቁጣጣሽ በዓል በአንድነት እንውላለን ብዬ

ብነግርሽም የሀገሩን ወግና ሥርዓት ያውቃል የተባለው አማላጅ ሽማግሌ ግን እኛን ለመለያየት ለትዳር ጓደኛ አሳልፎ ሰጠኝ ብላለች። ምንም እንኳን ሽማግሌ በአማላጅነት ተቃራኒ ጾታዎችን በጋብቻ እንዲተሳሰሩ ማድረጉ የተቀደሰ ተግባር ነው ቢባልም ልጃገረዶቹ ግን በቃል ግጥም ዘፈናቸው "ቴንሳህ ወይም ድራሽህ ይጥፋ" በማለት ተራግመዋል። ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ ማሰብና ማመዛዘን የሚችል ሰብዓዊ ፍጡር በዕድሜ ያልገፋቺውን ሴት ልጅ ገና ያልደረሰች ናት ብሎ ማከላከል አይችልም ወይ በሚል ነው።

በቃል ግጥሙ የመጨረሻዎቹ ስንኞች ላይ ከተፈጥሮ የተቀዳችዋ ጀንበር ተጠቅሳለች። በተምሳሌት የውክልና ስልት ጀንበሯ ደግሞ ተዛማጅ የኾነ ፍቺን ታሳስበናለች። ይሄውም እማሬያዊ በኾነ ፍቺ የጀንበር መግባት የአመሻሽ ድባብን ያስገነዝበናል። ምክንያቱም የምሽት የጀንበር መጥለቅ ጸዳልን ወይም ብርሃን ማጣትን ያስከትላል። ከዚህ ውጭ ፊት ለፊት በተነገረው ሐሳብ ትይዩ ግን አድማጩ ከቃል ግጥሙ ልብ እንዲል የሚፈለገው ሙሽራዋ ከከንፈር ወዳጇ፣ ከጓደኞቿ፣ ከቤተሰቦቿና ካደገችበት አካባቢ በጋብቻ የተነሣ የመለየቷ ነገር የጨለመባት መኾኑን ለማመላከት ነው - ብቸኝነት አለና። ወደ ባሏ ቤት ከኼደችም በኋላ እስከተወሰኑ ጊዜያት ድረስ በዙሪያዋ ካሉ ሰዎች ጋር በአካልም ኾነ በመንፈስ እንግዳና ባይተዋር ልትኾን ስለምትችል ነው። በመጨረሻም ልጅነትሽን ትተሽ ራስሽን የቻልሽ፣ አእምሮሽን የገዛሽ፣ ጎበዝ የቤተሰብ ኃላፊ መኾን ይገባሻል የሚለው ምክር በቃል ግጥሙ ተችሯታል።

ከላይ ስለመለያየት ከቀረበው ሐሳብ ጋር ተመሳሳይ የኾነው የልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈንም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ቃል ግጥም 73፡- እንጨት ስንሰብር አንለይም ያልሺው
ውሃ ስንቀዳ አንለይም ያልሺው
አክርማ ስንቀጭ አንለይም ያልሺው
አሁን ከምን ጊዜው ቃልሽን በላሽው።
(ቃለ መጠይቅ፣ አሚናት ጌታሁን፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ ልጃገረዶች ከየአካባቢያቸው እየተጠራሩ እንጨት ሲሰብሩ፣ ውሃ ሲቀዱ፣ አክርማና ስንደዶ ሲቀጩ ዘፈን እየዘፈኑ ከመዝናናታቸው በተጨማሪ የሆዳቸውን እያወጡ ይጨዋወታሉ። በዚህም ልጃገረዶቹ ወደፊት ባለው ሕይወታቸው እንደማይለያዩ እርስ በርሳቸው ቃል የተገባቡ መኾኑን ስንኞቹ ያንጸባርቃሉ። ኾኖም ሙሽራ የኾነችው ልጃገረድ የገባችውን ቃል ሳትፈጽም በመቅረቷ ቃሏን እንዳጠፈች ነው ቃል ግጥሙ

የሚያስገነዝበን፡፡ ከመቼውና እንዴት ባለ ፍጥነት ነው ቃልሺን ያጎደልሺው በሚልም ተወቃሽ ኾናለች፡፡

በጽንሰ ሐሳብ ቅኝቱ ላይ እንደተገለጸው ቃል ግጥሞች ከማዝናናት ተግባር በተጨማሪ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትምህርትን ይሰጣሉ፤ ዕውቀትንም ያስጨብጣሉ፡፡ የልጆችን እና የወጣቶችን ባሕርይ ገና ከለጋነታቸው ጀምሮ ለመቅረጽም ያገለግላሉ፡፡ የሚከተሉት መንቶ ስንኞችም አንዲት ልጃገረድ ትዳር መሥርታ ከአማቶቿ ጋር በምትኖርበት ወቅት ማድረግ ያለባትን ጥንቃቄ በጽኑ ያስገነዝባሉ፡፡

ቃል ግጥም 74- ከእንግዲህ የሰው ቤት ተጠንቅቆ ነው
ባጡም ግድግዳውም ተናጋሪ ነው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ዘቢባ ጥላሁን፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ ሙሽራዋን ተጠያፊ እንዲትኾን የሚያደርግ ነው፡፡ ይኼውም ሙሽራዋ ካሁኑ ጊዜ ጀምሮ ከቤተሰቦቿ ተለይታ ከዐማቶቿ ቤት ልትገባ ነው፡፡ ስለዚህ በቤት ውስጥ ሰውም ኖረ አልኖረ ለምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባት ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ እዚህ ላይ ባጥና ግድግዳ የሰውን ባሕርይ በመላበስ የአሳባቂነትን (የነገር ሠሪነትን) የንረት ደረጃ አጎናጽፈው ሐሳብን ለመግለጽ አገልግለዋል፡፡ በጥቅሉ ሙሽራዋ ለማንኛውም ነገር መጠንቀቅን፣ መንቃትን፣ ኮስታራ መኾንን፣ ወዘተ. የሕይወት መመሪያዋ አድርጋ እንድትጠቀምባቸው ቃል ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ በግልጽ አነጋገር ዝርክርክ መኾን እንደሌለባትና ምስጢር ጠባቂ መኾን እንደሚገባት ባልንጀሮቿ በአቀንቃኟ አማካይነት መክረዋታል፡፡ በተለይም አብዛኛዎቹ የሴት ዐማቶች ከወንድ ልጅ ሚስት ጋር ዓይንና ናጫ (ዐፈር) በመኾናቸው “ዓይኗን አያሳየኝ” በማለት ጥላቻቸውን ይገልጻሉ፡፡ በዚህ የተነሣ ምራቲቷ ከሠራቻቸውም ኾነ ካልሠራቻቸው ድርጊቶች መካከል ስሃ በማውጣት ለሀገር ምድሩ ታዳርሰዋለች፡፡

የሙሽራዋ ባልንጀሮች ከዳሱ ራቅ ባለ ሜዳ ላይ የመሰነባበቻ ዘፈን እየዘፈኑ ሙሽራዋን እያዝናኑ ባሉበት ጊዜ ሙሽራውና ዐጃቢዎቹ ደግሞ የምግብና የመጠጥ መስተንግዶ ከተደረገላቸው በኋላ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔዎችን ያካሂዳሉ፡፡ በቅድሚያ የጀግንትን ወኔ መቀስቀሻ የኾነው ቀረርቶ በዜማ ታጅቦ ይቀርባል፡፡ ምክንያቱም ያለ ቀረርቶ የፉከራ ክዋኔ አይታሰብምና ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ከተገኙት የቀረርቶ ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 75፡- በሳኡድ ጁዓዛት (ፖሊሶች) በኢትዮጵያ መለስ
ኧረ መሬት አልባው ወደ የት እንድረስ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ጌታቸው እብሬ፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የፖለቲካ መሪዎች ሕዝባቸውን ለማስተዳደር ሲሉ ቃል ግጥሞችን እንደሚጠቀሙ ሁሉ ማኅበረሰቡም ቢኾን በመሪዎቹ የሚደርስበትን ጭቆና፣ ግፍና በደል ያለ ምንም የሕግ ቁጥጥር በቃል ግጥሞቹ አማካይነት እነሱኑ ሲሸነቁጣቸው ይስተዋላል፡፡ በተለይም ባልተማረው ማኅበረሰብ ዘንድ ቃል ግጥም የኤሌክትሮኒክስ ግብዓቶችን እና የኅትመት ውጤቶችን ተክቶ የሚሠራ በመኾኑ ማኅበራዊ ብሶትን እና የፖለቲካ ምሬትን ለመግለጽ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በዚህ መሠረት በቃል ግጥሙ ላይ እንደተመለከተው መለስ የተባለው የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር የመንግሥትን አስተዳደር ከጨበጠበት ከ1983 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ የእርሻ መሬት ክፍፍል በማቆሙ ወጣቶች ትዳር መሥርተውና ልጅ ወልደው እንኳን የሚያርሱት ማሳ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ለዚህም ነው “ኧረ መሬት አልባው ወደየት እንድረስ” በማለት ተቃውሟቸውን የገለጹት፡፡ ገንዘብ ተበድረው ወደሳኡድ አረቢያ በመሰደድም በጉልበታቸው ሠርተው በሚያገኙት ገንዘብ ራሳቸውን ጠቅመው ቤተሰቦቻቸውንም መርዳት እንዳይችሉ የሀገሪቷ ፖሊሶች እያሳደዱ ከያዟቸው በኋላ በእስር ያንገላቷቸዋል፤ ከዚያም ወደየመጡበት እንዲመለሱ ያደርጓቸዋል፡፡ በመኾኑም ወጣቶቹ በተደጋጋሚ የደረሰባቸውን ብሶት ከቀረርቶው የቃል ግጥም መገንዘብ እንችላለን፡፡

ቃል ግጥም 76፡- የፊት ሰው ይሟታል እንዳንበላ አርሰን
መንገዱ ተዘግቷል እንዳንሠራ ሄደን
እንድንሞት ነው ወይ የተፈረደብን
(ቃለ መጠይቅ፣ ጌታቸው እብሬ፣ 19/05/2012፣ቦረና ወረዳ)

ቀደም ሲል የቀረበውን ርእሰ ጉዳይ የሚያጠናክረውና ወቅታዊ የኾነው የቀረርቶ ግጥም ከላይ ቀርቧል፡፡ በመኾኑም ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የእርሻ መሬቶች ቀደም ሲል በተደረገው ክፍፍል ትዳር መሥርተው በነበሩት ሰዎች በይዞታነት የተያዙ በመኾናቸው ሠርቶ ያልጠገበው፣ ጠንካራውና ብርቱው ወጣት አርሶ፣ ዘርቶ፣ ዐርሞ፣ ዐጭዶና ወቅቶ በሚያገኘው ምርት ራሱንም ኾነ ቤተሰቦቹን መመገብ አልቻለም፡፡ እነዚህ ወጣቶች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው እንዳይሠሩ ብሔርን እና ቋንቋን መሠረት በማድረግ በተካኼደው የክልሎች ክፍፍል እየተፈጸመ ባለው እኩይ ተግባር ዕልቂት እንዳይደርስባቸው ይፈራሉ፡፡ ችግር ጸንቶባቸው፣ ዕጦት አንገላቷቸው፣ ወዘተ. ሀገራቸውን ጥለው ወደውጭ እንዳይሰደዱም ዙሪያው ገደል ኾኖባቸዋል፡፡ በመጨረሻም የጀግንነትን ወኔ መቀስቀሻ የኾነውን ዜማ ያዜመው ሰው “እንድንሞት ነው ወይ የተፈረደብን” በማለት የወጣቶቹን ተደራራቢ ብሶት አቀንቅኗል፡፡

ቃል ግጥም 77፡- መሬት ዓይኗን ታማ ስትደናበር
በአንድ ሳጥን ቢራ ትመራ ጀመር፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ፈቃዱ ጤናው፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

መሬትን የተለያዩ የሃይማኖት ምእመናን በሕይወት ሳሉ ቆመው የሚጸልዩባት፣ ፈጣሪያቸውን የሚማለዱባት፣ ሕፃናትም ቦርቀው የሚያድጉባት፣ ማንኛውም ሰው ሲሞትም የሚቀበርባት፣ ወዘተ. መኾኗ ምስክር አያስፈልገውም፡፡ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት (1978፡53) እንደተጠቀሰው በመሬት ከበርቴው ሥርዓተ ማኅበር ባላባቶቹ መሬትን በማሳረስ፣ በማከራየት፣ በመግዛትና በመሸጥ ከፍተኛ የኾነ ሀብት የሰበሰቡባት መኾኑም ተብራርቷል፡፡ እንዲሁም የድንኳን ተካይ፣ የካህን ርስት፣ የወታደር ይዞታ እያሉ ከፋፍለዋትም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በከተማም ኾነ በገጠር ባሉ የመንግሥት መዋቅር ላይ የተመደቡ ባለስልጣናት አግባብ ባልኾነ መንገድ መሬትን እየቸረቸሩ ሲጠቀሙባት ይስተዋላል፡፡ ድርጊቱንም “የመሬት ወረራ” እያሉ አንዳንድ ሰዎች ሲጠሩም ይሰማሉ፡፡ ይህንን የተገነዘበው አርሶ አደር መሬት በትክክል ለዜጎች መከፋፈል አለመቻሏን በሰውኛ የዘይቤ አጠቃቀም ስልት ዓይኗን ታማ በመደናበር ላይ እንዳለች በቀረርቶ ግጥሙ ገልጿል፡፡ ይህ ዓይነቱ እኩይ ድርጊት የሚፈጸመው ደግሞ ፍትሕን በማጣመም፣ ገንዘብንና ሌሎች የተለያዩ ስጦታዎችን በዓይነት በመቀበል ነው፡፡ የተጣመመውን ድርጊት የፈጸመው ባለስልጣን እንዲህ በቀላሉ በአንድ ሣጥን ቢራ የሚሸነገል አለመኾኑን ቀረርቶውን ያቀነቀነው አርሶ አደር ልቡ ያውቀዋል፡፡ የሚያውቀውን ሁሉ ዘክዝኮ ላለማውራት በመፈለግ “በአንድ ሳጥን ቢራ” በሚለው የቋንቋ አጠቃቀም ለመግለጽ አስቦ ነው፡፡

ቃል ግጥም 78፡- የአንበሳውን ወዳጅ አንበሳ ስሞበት
ያም እየጎደራ ያም እያገሣበት፡፡
አንተም ተው አንተም ተው ብዬ እንዳልላቸው
ኹሉቱም ያገር ልጅ የወንዜ ልጅ ናቸው፡፡

(ከቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

በቀረርቶው ቃል ግጥም ውስጥ የሚገኙት ስንኞች አካባቢያዊና ሀገራዊ መንፈስ ይስተዋልባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አካባቢያዊ የተባለበት ምክንያት “አንበሳ” የሚለው ቃል በቀጥተኛ ትርጉሙ በደን፣ በዱር፣ በበረሓ የሚኖር፣ ኃይለኛና አስፈሪ የኾነ፣ ሥጋ በል የዱር እንስሳ የሚለውን ያስገነዘበናል፡፡ በተምሳሌትነቱ ደግሞ ጀግና፣ ልበ ሙሉና ደፋር የሚለውን እንረዳለን፡፡ በዚህ መሠረት በአንበሳ የተመሰለው ጀግናው ጎረምሳ በመሳም ብቻ ወዳጅ ወይም ፍቅረኛ ያደረጋትን ልጃገረድ እንደ እሱው ደፋር በኾነ ወጣት የከንፈር ወዳጁ የተሳመችበት መኾኑን የመጀመሪያው ስንኝ ያንጸባርቃል፡፡ በዚህን ጊዜ ኹሉቱም ወገኖች በየፊናቸው እንዴት ተደፋፈርን በሚል ስሜት ልክ እንደ አንበሳ ከፍተኛ የኾነ ድምፅ በፉከራ እያሰሙ ለዐምባጓሮ

የተነሣሡ መኾናቸውን እናስተውላለን፡፡ እያንዳንዳቸው ከዚህ ዓይነት ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አድርጎ ለማስታረቅ ደግሞ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ጎረምሳዎች በመኾናቸው በመካከላቸው በሽማግሌነት የተሳለው ገጸሰብ የተቸገረ መኾኑን እንረዳለን፡፡

ስንኞቹ ሀገራዊ መንፈስ የሚስተዋልባቸው ናቸው የተባለበት ምክንያት ደግሞ በቃል ግጥሙ ውስጥ አንበሳ ከቀጥተኛ ፍቹ ውጭ የአርበኛ፣ የጀግና ንጉሥና የባለስልጣናት ተምሳሌት ኾኖ ነው የቀረበው፡፡ በመኾኑም ከንፈሯን የተሳመችውን ልጃገረድ እንደ አንዲት ሀገር ወይም ብሔርን እና ቋንቋን መሠረት በማድረግ እንደተዋቀረ ክልል አድርገን ልንቆጥር የምንችል ይመስለኛል፡፡ በዚህ መሠረት የሀገሪቱ ወይም የየክልሎች ባለሥልጣናት እርስ በርሳቸው አልደማመጥ ብለው በመወነጃጀል ላይ እንዳሉ የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ያስረዳል፡፡ በኹለቱ መካከል ያለው ሽማግሌ ደግሞ ከእንዲህ ካለው እኩይ ድርጊታችሁና መጥፎ ልማዳችሁ መቆጠብ ይኖርባችኋል፡፡ ርግፍ አድርጋችሁ ትታችሁ ይቅር መባባል አለባችሁ ብሎ እንዳያስታርቃቸው ኹለቱም ወገኖች በአንዲት ሀገር ወይም አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በመኾናቸው መፍትሔ በመሻቱ ረገድ ግራ የተጋባ መኾኑን የመጨረሻዎቹ ስንኞች ያመላክቱናል፡፡

እንደ Getie Gelaye (2009፡1351) ማብራሪያ በታሪክ የፉከራ ግጥሞች ተደጋግመው ከሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንደኛው የሰርግ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ዳስ ውስጥ ባለው ሥርዓትም በተከወነው የቀረርቶ ቃል ግጥም ስሜታቸው የተነቃቃ ጎረምሳዎች ጀግንነትን እና ወኔን በሚቀሰቅስ ኹኔታ “ዘራፍ” እያሉ መፎከራቸውን ይያያዙታል፡፡ በዚህ ዓይነት አጋጣሚ በፉከራ እየቀረቡ ካሉት ቃላዊ ገጥሞች መካከል ጥቂቶቹን ቀጥሎ ለማየት እንሞክር፡፡

ቃል ግጥም 79፡- ዘራፍ ዘራፍ ዘራፍ
ከባልንጀራም አለው ብረ ሸሸ
ከአንጋዳ ቦታ ጥሎ የሚሸሸ፡፡
መሸሹን ይሸሸ ስፍራው ከከፋ
ከመንደር ኼዶ ማውራቱ ከፋ፡፡

(ከከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

ከላይ እንደተመለከትነው የፉከራውን ቃል ግጥም ያቀረበው ሰው ጀግንነቱን፣ ልበ ሙሉነቱን፣ ደፋርነቱን፣ ቆራጥነቱን፣ አልበገር ባይነቱን... ለማሳየት ከፍ ባለ ድምፅ “ዘራፍ” እያለ ፉከራውን ጀምሯል፡፡ ዘራፍ የሚለው ቃል በግጥሞቹ መጀመሪያ ላይ እየተደጋገመ የሚባል በመኾኑም “አዝማች” ሊባል ይችላል፡፡ በመቀጠልም ከሰዎች ጋር ዐምባንሮ በተፈጠረበት ወቅት

ተባብሮ መደባደብ የሚገባው ዐብሮ አደግ ጓደኛ ከፍርሃቱ የተነሣ ሰዋራ ወይም ድብቅ ቦታ ላይ ጀርባውን ሰጥቶ የሚሸሽ ይኖራል። በተቃራኒ ወገን ያለውን ባላጋራ መክቶ ለመደባደብ ስፍራው የማያመችና መጥፎ ከሾነበት ወደኋላ መሮጡና ጓደኞቹንም ትቶ መጥፋቱ ያን ያክል አስነዋሪ አልነበረውም። ከዚህ ሁሉ የከፋው ነገር ከመኖሪያ ሰፈር ኼዶ ራሱን ጀግና፣ ሌላውን ደግሞ ፈሪ በማድረግ ወሬን ከአንዱ ወስዶ ወደሌላው ማሳበቁ ወሸካታነቱን ያመላክታል በማለት አቀንቃኙ ሂሳዊ አስተያየቱን ሰንዝሯል።

ቃል ግጥም 80፡- ማረስ ነው እንጅ ዋጫ መንጥሮ
ቀይ ሴት በማየት አይሆንም ኑሮ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ማንኛውም ግለሰብ በሙያው ምግባረ መልካም መኾን እንዳለበት ይመክራል። ይሄውም እሾኻማ የኾነውን ጫካ ጨፍጭፎ የእርሻ መሬትን በተደጋጋሚ በማረስ አጥጋቢ የኾነውን ምርት ማግኘት ሲቻል የቀይ ሴትን ውጫዊ ገጽታ በመመልከት ከሥራ መቦዘን ተገቢነት እንደሌለው ያስገነዝባል። “ሴት አውል” ማለትም ብዙውን ጊዜ ከሴት ጋር ዐብሮ መዋልን የምትወድ ደካማ ሰው መኾን የለብህም። ይህንን የምታደርግ ከኾነ ደግሞ የዕለት ጉርሥህን ለማግኘት ስለሚያዳግትህ ትዳርህም ኾነ በዕድሜ ዘመንህ የምታሳልፈው ሕይወትህ የተበላሸ ነው የሚኾነው። ከዚህ ይልቅ ለቤቱ፣ ለቤተሰቤና ለትዳሬ ብለህ በማሰብ ተግተህ መሥራት ይገባሃል በማለት የፉከራ ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር አስረድቷል።

ቃል ግጥም 81፡- ትሰጠኝ እንደሁ ስጠኝ ጠብመንጃ
አልቀበልም ኮሳሳ ጥጃ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ዘበነ አሰፋ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ቀደም ባለው ወቅት በዳስ ውስጥ ቀረርቶውና ፉከራው እየተከወነ ባለበት ጊዜ የሙሽራዋ ቤተሰቦች ላልተደራጁ፣ እንደዚሁም የራሳቸውን ቤትና ትዳር ገና ለሚመሠርቱ ልጆቻቸው ለጎጆ መውጫ የሚኾን የገንዘብ፣ የእንስሳትና የቁሳቁስ ስጦታዎችን በሽልማት መልክ ለሙሽራው ይሰጡ ነበር። ይህንን ለማድረግ ዐቅም ካነሳቸውም በአልባሳት ያንቆጠቁጡታል። ፎካሪው ሰውዬ ግን ዐጅቦት ለመጣው ሙሽራ የተሰጠው የከሳች፣ የኮሰመነችና በአካል ያነሰች፣ እንደዚሁም ከእንቦሳ ከፍ የምትል፣ ሣር መብላት፣ ውሃ መጠጣት የጀመረች የላም ልጅ በመኾኗ ሽልማቱን አመርቂ ኾኖ ስላላገኘው የናቀው ይመስላል። ከዚህ ይልቅ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው የጎብረተሰብ ክፍል የጦር መሣሪያ ፍላጎቱ እጅግ በጣም

ከፍተኛ በመኾኑ የሚፎክረው ሰውዬም ሙሽራውን በመወከል ‹‹ትሸልመኝ እንደኾነ ከጠላት ራሴን የምጠብቅበት ጠብመንጃ ስጠኝ›› በማለት ሽላሚውን ሰው ጎሸመጥ አድርጎታል፡፡

የሙሽራው ዐጃቢዎች ከዳስ ውስጥ እያቅራሩና እየፎከሩ ከቆዩ በኋላ አቦል ቡና ተጠጥቶና የምርቃት ሥርዓቱ ተከናውኖ እንዳበቃ ሙሽራይቱን ተረክበው ከቤት ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ከደጅ ካለው ገላጣ ቦታ ላይ ሙሽራውና ሙሽሪት ጎን በጎን እንደተቀመጡ ከሙሽራው ጋር ዐብረው የመጡ ሽማግሌዎች የሙሽራዋን ዕቃ ቆጥረው ይረከባሉ፡፡ በዚህን ወቅት ጎረቤትና ቤተዘመድ የኾኑ ሴቶች፣ የሙሽራዋ ባልንጀሮች ዘፈኑን ሲያቀልጡት፣ የከንፈር ወዳጅና ጓደኞቹም በየፊናቸው “ሆ” ይላሉ፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች ከሚቀነቀኑት የቃል ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹን በሚከተለው ቅደም ተከተል እንመልከት፡፡

ጎረቤትና ቤተዘመድ በኾኑ ሴቶች ሙሽራውን ለማብሸቅ ከሚቀርቡት የቃል ግጥሞች መካከል፡-

ቃል ግጥም 82፡- ወፌ ይላላ ላላዬ
ነይ ደማማዬ፡፡
እናንተ አማሞቶች ላዩ ላዩን እለፉ
አህያ ሞታለች ጨንራ ዝረፉ፡፡
የጉመሮ ጫፍ የጉመሮ ጫፍ
ከአማሞቶች ሁሉ ሙሽራው ጭንጋፍ፡፡
ያለላ ወንፊት ያለላ ወንፊት
እቴን በምን አያት ይሄ ዐሻሮ ፊት፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ኑሪት ጌታቸው፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ምንም እንኳን “ወፌ ይላላ ላላዬ” የሚለው በዘፈን መጀመሪያ ላይ እየተመላለሰ በአዝማችነት የሚያገለግል ቢኾንም “ነይ ደማማዬ” የሚለው ግን ውበትን የተጎናጸፈችውን እና ደም ግባት ያላትን ሴት ልጅ ቶሎ ነይ ብሎ እንደ መጥራት ሊታሰብ ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት አዝማቹና ከሥር ያሉት ስንኞች የሐሳብ ዝምድና አይስተዋልባቸውም፡፡ ምክንያቱም አዝማቹ ውበትን ማንጸሪያ አድርጎ ሲያቀርብ ተከታዮቹ ስንኞች ግን ሙሽራውን ለማብሸቅ ሲባል ስድብን እና መልክ ጥፉነትን ሲያንጸባርቁ ተስተውሏል፡፡ በመቀጠልም ሴቶቹ ሥጋው የማይበላውን፣ ለጭነት ብቻ የሚያገለግለውን እና የጋማ ከብት የኾነውን አህያ ተመገቡት በማለት ሰርገኞቹን በዜማ በመሳደብ ሲያናድዷቸው እንመለከታለን፡፡ ባህል ስለኾነ ሰርገኞቹ እንደ ምንም ብለው በትዕግስት ስድቡን ይችሉት እንደኾነ ነው እንጂ የስድቡ አፍላቂዎች አስተሳሰብ ግን የዘቀጠ መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከሰርገኞቹ ስድብ ባለፈ ደግሞ የሙሽራውን ትክለ ሰውነት መነሻ አድርገው ጭንጋፍ በማለት አዋርደውታል፡፡ ይሄ ደግሞ ያለ ቀኑ የተወለደ፣ ድውይ፣ ኮስማና የሚል አንድምታ አለው፡፡

ሴቶቹ የጉመሮ እሾኸን በተምሳሌት በመጠቀም በነገር የሙሽራውን ሥነ ልቦና ጠቅ አድርገውታል። ይሄ ደግሞ ምን ጊዜም በሙሽርነት በተሳለው ገጸሰብ አእምሮ ውስጥ ሊጠፋ የሚችል ነገር አይኾንም። በተጨማሪም ሰድቦ ለሰዳቢ መስጠትም ይኾናል። በመጨረሻዎቹ ኹለት ስንኞች ደግሞ የዐለላ ወንፊትና የጥቁር ዐሻሮ ውጫዊ ገጽታ በትይዩ ቀርበዋል። በቀለም በተነከረ ስንደዶ ወይም አክርማ የተሰፋው ወንፊት ሳቢና ማራኪ ቢኾንም ሙሽራው ከውጭ በኩል ያለው አካሉ መልከ ጥፉ መኾኑን ለማንጸባረቅ ደግሞ ለጠላ መጥመቂያ የሚኾነውን እና እስከሚያር ድረስ የተቆላውን የማሽላ፣ የዘንጋዳ፣ የገብስ ወይም የስንዴ ጽልመተ መልክ በለዋጭ ዘይቤ የአነጋገር ስልት አማካይነት በቃል ግጥሙ ውስጥ ለመጠቀም ተችሏል። ስለኾነም ይህን መሰል መልክ ያለው ሰው እንዴት አድርጎ አይቷት ነው እህታችንን የትዳር ጓደኛ ያደረጋት በማለት ሴቶቹ በትችት አዚመዋል።

የሰርጉ ባለቤት ጎረቤታሞችና ቤተዘመድ የኾኑ ሴቶች በቃል ግጥሞቻቸው አማካይነት ሙሽራውን ሲያበሽቁት ብቻ ሳይኾን ሲያሞግሱትም ማየት የተለመደ ነው። በዚህ መሠረት መገሳን በተመለከተ ከተዜሙት መካከል የተወሰኑ ስንኞችን በአብነት ለማየት እንሞክር።

ቃል ግጥም 83፡- ወፌ ይላላ ላላዬ ሦስት ጊዜ
ነይ ነይ ደማማዬ።
አዲሱ ሙሽራ ገና ልጁ ልጁ፣
የፍቅር ዐለንጋ ይሏል በቀኝ እጁ።
እገልዬ አበሉ ሙሽራው ሙሽራው
እንዳለም ጎራዴ በልክ የተሠራው።

(ቃለ መጠይቅ፣ መሬማ አረጋ፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ የተቀነቀነለት ወጣት ጋብቻው በተፈጸመ ዓመት ከተዳሩት ውስጥ አጊጦና ተሸልሞ የታየው የመጀመሪያው ሙሽራ እንደኾነ ተገልጿል። ለዚህም ዐዲሱ ሙሽራ ለመባል በቅቷል። ይህ ገጸሰብ በዕድሜ ባለመግፋቱና ታዳጊ በመኾኑም በአቀንቃኞቹ አንደበት ተወድሷል። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ወጣት ለግላጋና ጥሩ አቋም ያለው ስለሚኾን ተመልካቾችን ይማርካል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ልብ ብለው የሚያዩትን ሁሉ ለአፍታም ቢኾን ስሜታቸውን ቆንጥጦ ሊይዝም ይችላል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ሙሽራው ከሰርጉ ዕለት ጀምሮ ከጫጉላ ቤቱ እስከሚወጣ ድረስ ከቀንድ ከብት ወይም ከጉማሬ ቆዳ የተሠራ ዐለንጋ ከእጁ አይነጠለውም። ይህ የሚኾንበት አንደኛው ምክንያት ሙሽራው በእነዚህ ቀናት ጌታ፣ አለቃ ወይም የበላይ አዛዥ ተደርጎ ስለሚቆጠር ዐለንጋው በተምሳሌትነት ያገለግላልና ነው። በማኅበረሰቡ ወግ መሠረት ሙሽራው የጫጉላ ቤት ቆይታውን ጨርሶ

በአቅራቢያ በሚገኝ ወንዝ የራሱን፣ የሙሽራዋን እና የቤተሰቡን ልብስ ከጓደኞቹ ጋር ካጠበና ከወላጆቹ ጋር ከተቀላቀለ በኋላ የጌታነት ወይም የአለቃነት ማእረጉ ይነሣል። ከዚያ በኋላ ዐለንጋ መያዙንም እርግፍ አድርጎ ይተዋል።

ኹለተኛው፣ በጌታነቱ ወቅት ዐጃቢዎቹም ኾኑ እኩያዎቹ የእሱ አሽከሮች (አገልጋዮች) በመኾናቸው አልታዘዝ ካሉ ሽንቆጥ ይደረጋሉ። ባህል ነውና ተገረፍኩ ብሎ የሚያኮርፍ ወይም የሚጣላ ጎረምሳ አይኖርም። ሙሽራዋም ብትኾን ጥፋት ከፈጸመች መገረፏ አይቀርም። ሦስተኛው ደግሞ ከወለደች ብዙ ያልቆየች አራስ ሴት ዐርባ ቀን እስከሚሞላት፣ ሙሽራም ከሰርጉ ዕለት ጀምሮ ከጫጉላ ቤቱ እስከሚወጣ ድረስ ብቻቸውን ከኾኑ ርኩስ መንፈስ ያድርባቸዋል ተብሎ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይታመናል። ስለዚህ ዐለንጋ ሙሽራውን ከአጋንንት ይጠብቀዋል ተብሎ ይታሰባል። ይህ ዓይነት ተግባር ያለው ዐለንጋ በኹለት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል በተለይም ሙሽራው ለሙሽሪት ያለውን ከፍተኛ የመውደድና የመሳሳብ ስሜት ወካይ ኾኖ የቀረበ መኾኑን ከቃል ግጥሙ መረዳት እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪ በግጥሙ ውስጥ ዐለንጋው የተያዘው በቀኝ እጅ መኾኑ የተገለጸው ያለ ምክንያት አይደለም። እንደሚታወቀው ግራ እጅ በግራው ለሚሠራና ለሚበላ ሰው አገልግሎት የሚሰጥ የሰውነት ክፍል ቢኾንም ለችግር፣ ለጭንቅ፣ ቀና ላልኾነ ነገር ተምሳሌት ኾኖም ይቀርባል።

ቀኝ እጅ ግን ለሥራ ኃይለኛ፣ ፈጣን፣ ምቹ፣ ቀና፣ የማያስቸግር መኾኑን በዕለት ተዕለት ሕይወታችን በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን። በአንድምታ ትርጓሜው ደግሞ ቅን፣ መከታ፣ መመኪያ፣ አለኝታ፣ ደጋፊ የሚለውንም ፍች መረዳት ይገባል። በዚህ መሠረት በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰው ቀኝ እጅ ኹለቱንም ሐሳቦች አጣምሮ የያዘ ይመስላል። ከዚህ በተጨማሪ ደስታ ተክለ ወልድ (1962፣1078) የቀኝን ዕሳቤ ጉልህ ኾኖ እንዲታይ ለማድረግ “ጌታ በፍርድ ቀን ጻድቃንን በቀኝ፣ ኃጥኣንን ደግሞ በግራ ያቆማቸዋል” በማለት ገልጸዋል። በመጨረሻም በግጥሙ ውስጥ የጋብቻ በዓሉን በማክበር ላይ ያለው ሙሽራ ዓለሙ ሁሉ በአሠራሩም ኾነ በቅርጹ ተስማምቶበት እየተገለገለበት ካለው ጎራዴ ጋር በንጽጽር ቀርቧል። ንጽጽሩም ሙሽራው ልክ እንደ ጎራዴው ቅርጹ ጎበጥ ብሎ በአንድ በኩል ብቻ ስለት ያለው የጦር መሣሪያ ነው ለማለት ሳይኾን በመጠን ረገድ ያላጠረ፣ ያልረዘመ፣ ምጥን ተደርጎ በአምላክ የተፈጠረ መኾኑን ለማመላከት ነው።

ጎረቤትና ቤተዘመድ የኾኑ ሴቶች እየዘፈኑ ካሉበት ቦታ ራቅ ብለው የሚጨፍሩት ልጃገረዶች ደግሞ ሙሽራዋን ትዳር የማይቀር መኾኑን እና ማግባቷን በጸጋ መቀበል እንደሚኖርባት በዘፈን አበረታታዋታል። ካዜሙላት የዘፈን ስንኞች መካከል ኹለቱን ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 84፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው ኹለት ጊዜ
አላፈራም ወይ የዐባይ ዳር እንኮይ፡፡
ሙሽሪት እባክሽ አታልቅሽ አይበጅም
ሴት ልጅ ከእናቷ ጋር ዕድሜዋን አትፈጅም፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ብርቱካን ጫኔ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ግጥሙ ተማፅኖ ይስተዋልበታል፡፡ ይኼውም ጓደኞቿ የጋብቻ ሥርዓቷን የምታከብረዋን ሴት ልጅ “እባክሽ” በሚለው የልመና ማቅረቢያ ቃል ማልቀስ ጥሩ እንዳልኾነ በመማፀን መክረዋታል፡፡ በእርግጥ ሴት ልጅ በጋብቻዋ ዕለት በሐዘን ብቻ ሳይኾን በደስታም ስሜቷ ስለሚቀሰቀስ እንባዋን ማፍሰሷ አይቀርም፡፡ በግጥሙ ዐውድ መሠረት ግን ሙሽራዋ ከወላጆቿ፣ ከጓደኞቿ፣... በመለየቷ ሆድ ብሷት ያነባች መኾኑን ልንገነዘብ እንችላለን፡፡ ስለዚህ እናት ለልጇ ደግና ሩኅሩኅ ብትኾንም ሴት ልጅ ከተወለደችበት ዕለት ጀምሮ ዐጸደ ነፍሷ ከዐጸደ ሥጋዋ እስከምትለይበት ጊዜ ድረስ ከወላጆቿ፣ በተለይም ከእናቷ ጋር ዐብራ ስለማትኖርና ዕድሜዋንም በዚያው ስለማትጨርስ ማልቀሱ ለእሷ መልካም ወይም ጥሩ ነገር አይደለም በማለት በልመና መልክ ሲያግባቧት እንመለከታለን፡፡

በመጨረሻም ሙሽራዋ ከትዳር ጓደኛዋና ከቤተሰቦቹ ጋር በምትቀላቀልበት ጊዜ ባይተዋር ስለምትኾን እንዳይከፋትና ብቸኝነት እንዳይሰማት ቀጥሎ ባሉት ስንኞች ለሙሽራው ቤተሰቦች በአደራ መልክ ስትሰጥ እናስተውላለን፡፡

ቃል ግጥም 85፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው } ኹለት ጊዜ
አላፈራም ወይ የዓባይ ዳር እንኮይ፡፡
የሙሽራው እናት እኅቴን አደራ
የሙሽራው አባት እኅቴን አደራ
የሙሽራው ወንድም እኅቴን አደራ
የሙሽራው እኅት እኅቴን አደራ
ሰጥቻችኋለሁ ያለ ባልንጀራ፡፡
ያለ ባልንጀራ ያለ ታናሽ እኅት፣
ስትገባ ስትወጣ የምታዋያት፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ብርቱካን ጫኔ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ እናት፣ አባት፣ ወንድምና እኅት ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ደግሞ የሥጋ ዝምድና ያላቸውና በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ ዓባላት ናቸው፡፡ ስለዚህ ልጃገረዶቹ ሙሽራዋ በፍርሃት ወይም በሥጋት ተሸማቅቃ እንዳትኖርና እንደራሷ ቤተሰቦች ደኅና አድርገው በመንከባከብ እንዲይዟት ለእነዚህ ወገኖች የጠበቀ ዐደራ ሲሰጧቸው እንመለከታለን፡፡

ዐደራውም ክብደት እንዲኖረው ሐዘኔታን በተላበሱ የዘፈን ስንኞች ልጃገረዶቹ ተማፅነዋል። ይሄውም ሙሽራዋ በአንድ ሥራ ወይም ድርጊት ላይ ስትሳተፍ "ከልማቱ ጥፋቱ" ተብላ በምትነወርበት ጊዜ ስሕተቷን የምታስተካክል፣ ምስጢረኛ የኾነች ዐብሮ አደግ ጓደኛ እንዳልተከተለቻት፣ እንደዚሁም ሐሳቧን የምታጋራት፣ በክፉም ኾነ በደጉ አስተያየት የምትሰጣት፣ በችግርና በመከራ ጊዜም የምታማክራት ታናሽ እኅትም ዐጅባት እንዳልኼደች በዘፈናቸው አማካይነት በአጽንዖት ገልጸዋል።

ከልጃገረዶቹ ዘፈን ጎን ለጎን ደግሞ የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጅ ከጓደኞቹ ጋር በአንድ በኩል፣ የሙሽራው ዐጃቢዎች በሌላ በኩል ኾነው "ሆ" ይላሉ። ሙሽራው፣ ዐጃበዎቹና ሽማግሌዎች ሙሽራዋን ይዘው ከወንዱ ሙሽራ አባት ቤት እስከሚደርሱ ድረስ ሆታውን ያቀልጡታል። በዚህን ወቅት የሚቀነቀኑት የቃል ግጥሞች ይዘታቸው በአብዛኛው የሚያተኩረው የሙሽራዋን የከንፈር ወዳጅ በማጥላላት ላይ ነው። ከእነዚህ መካከል ጥቂት ስንኞችን ለአብነት ወስደን እንመልከት።

ቃል ግጥም 86፦ ያሆ ያሆ ያሆ ያሆ } ኹለት ጊዜ
ቆሌ ታማረው ና በለው ና በለው
ያንቺማ ወዳጅ የኮራሽበት
ከዳገት ቀረ እንደ በሬ እበት
የበሬስ እበት ያገለገላል
ቢያዳፍኑበት እሳት ያውላል።

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

በከንፈር ላይ በተመሠረተ ፍቅር ያንች የነበረው ወዳጅሽ የተመካሽበትና አለኝታ ያደረግሺው ቢኾንም በቀውጢ ቀን (በአስቸጋሪ ጊዜ) ግን ከጭንቀቱና ከፍርሃቱ የተነሣ ድፍረት በማጣቱ የታሰበውን ዓላማ ወይም ድርጊት ሙሉ በሙሉ ሳያሳካ ቀረ በማለት የሆታ አውራጁ ሙሽራዋን በነገር ጎንተል አድርጓታል። ይሄውም በጎረምሳዎች መካከል ዐምባንሮ በሚነሣበት ወቅት ግንባሩ ሳይታጠፍ ድል መቀዳጀት ሲገባው እሱ ግን መካከል ላይ ገርርባውን ሰጥቶ ወደኋላ መሸሹን ቃል ግጥሙ ያመለክታል። በአጭሩ የከንፈር ወዳጇ ግንባሩን ቢሉት የማይፈራ፣ የማይመለስ ጎበዝ መኾን ነበረበት ለማለት ሙሽራዋን በነገር ጎሽምጧታል። የቃል ግጥሙ ዕንሰ ነገር በአድማጩ አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጽ ለማድረግም የከንፈር ወዳጅ ተብዬው ከቀንድ ከብት ፍግ (እበት) ባነሰ መልኩ በንጽጽር ቀርቧል። እንዳውም እንጨት ተቀጣጥሎ ነበልባሉ ካለቀ በኋላ ባለው ፍም ውስጥ የቀንድ ከብቱን ፍግ (እበት) ቢቀብሩት ሙሉ ቀን ወይም ሌሊት እሳትን ሊያቆይ ስለሚችል ጥቅም ሲኖረው፣ የእሷ ወዳጅ ግን ከፍርሃቱ የተነሣ

ገደል እንደሚገባና በዚህም ከፍተኛ የሾነ ችግር ላይ ሊወድቅ እንደሚችል የሆታ ቃል ግጥሙ ያስረዳል። በሬውን ፍካሬያዊ በሾነ መልኩ ስንተረጉመውም የሙሽራዋን የከንፈር ወዳጅ ጅል፣ የማይረባ፣ ሞኝ፣ ቂል... ብሎ ለመስደብም ሊያገለግል እንደሚቻል ማስተዋል ይገባል።

ቃል ግጥም 87፡- ነይ ዞማ ዓለም ዓለም
ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም
የማይልሽ የለም።
ሸጌ ሙቺ ሙቺ ንዳድ ይግደልሽ
አትመርጪም አሉ ቂሎና ጥንቅሽ።
በያዝከው ሽመል ካልሰነዘርክበት
ከዚያው መልሰው ከቆረጥከበት።

ኹለት ጊዜ

(ቃለ መጠይቅ፣ መልካሙ ሸዋ፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚከወኑት የሆታ ቃል ግጥሞች ላይ ከሚቀርቡት የዜማ ዓይነቶች መካከል አንደኛው "ነይ ዞማ ዓለም ዓለም" የሚለው ነው። ይሄ ዜማ ደግሞ ለሙሽራ ብቻ ሳይሾን ውበት፣ ደም ግባትና ወዘና ላላቸው ልጃገረዶች ሁሉ የሚቀነቀን ነው። በዚህ መሠረት "ዞማ" የሚለው ቃል ልጃገረዶቹ ንጽሕናቸውን የሚጠብቁ በመሾናቸው ለስላሳ፣ ያማረ፣ ማለፊያ የሾነ ረዥም፣ እንደዚሁም ቶሎ ቶሎ የሚያድግ ጸጉር ያላቸው መሾኑን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ "ዓለም" የሚለውን ቃል በፍካሬያዊ ትርጉሙ ስንመለከተው በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ልጃገረዶች በተድላና በደስታ እንደሚኖሩ ተደርጎ ቀርቧል። ይህ እንግዲህ ልጃገረዶቹ በውጫዊ ገጽታቸው ውብ ይኹኑ ወይም መልከ ጥፉ፣ ኑሮ የከፋባቸውም ይኹኑ ፍሥሓን ያገኙ እንዳው በደፈናው ጎረምሳዎቹ በግጥሞቻቸው የውዳሴ ቃል ግጥሞችን ሲያዜሙላቸው ይደመጣሉ። በውዳሴው የተገለጸውን ቁም ነገር እኛ ብቻ ሳንሾን ሣር ቅጠሉ (ሁሉም ሰው) የሚያውቀው ነው ለማለትም "የማይልሽ የለም" እያሉ ለመረጃ የሚሾን ምንጭ ሲጠቅሱ ይስተዋላሉ።

ከሙገሳው በተቃራኒ ደግሞ ጎረምሳዎቹ በሆታ ግጥማቸው ነፍስሽ ከሥጋሽ ትለይ፣ በወባ በሽታ አማካይነትም ሕይወትሽ የመጨረሻዋን ፍጻሜ ታግኝ በማለትም በሙሽራዋ ላይ ርግማን ሲያወርዱባት በእዝነ ልቦናችን እናዳምጣለን። ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የሚያነሡት የከንፈር ወዳጅ ምርጫሽ እሺ፣ ይኹን የሚያሰኝ አይደለም የሚል ነው። በዚህ የተነሣ የከንፈር ወዳጆችሽ መልከ ጥፉም ይኹኑ ቆንጆ ሳትለይ እንዳለ ያገኘሺውን ሁሉ ታግበሰብሻለሽ ብለው ሰዎች ያወሩብሻል የሚል ነው። ለአግበስባሽነቷም ማሳያ አድርገው ያቀረቧቸው ቂሎና ጥንቅሽ የተባሉ የአገዳ እኽሎችን ሲሾን፣ ኹለቱም በጣፋጭነት ረገድ በተቃርኖ የሚቆሙ ናቸው። ምክንያቱም ቂሎ የተባለው ቀጭን ኾኖ ረዥም አገዳ ያለው ዘንጋዳ ስለኾነ ጣፋጭነት የለውም። ጥንቅሹ

ደግሞ እንደ ሽንኮራ አገዳ ጣፋጭነት ያለው ነው። ስለዚህ ቂሎው ለመልከ ጥፉዎች፣ ጥንቅሹ ደግሞ ውበትን ለተላበሱ ጎረምሳዎች ተምሳሌት ሽነው መቅረባቸውን ልንገነዘብ እንችላለን።

በእርግጥ ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ወጣቶች እንደ ጋብቻ ሁሉ ዘር ሊቋጠሩ ይችሉ እንደሽነ ነው እንጂ አንዲት ልጃገረድ ያን ያክልም የከንፈር ወዳጇን የመምረጥ ዕድል አልነበራትም። በመጨረሻ ላይ ባሉት ሹለት ስንኞች የሆታ አውራጁ በጎብረት በሚካሄደው ጭፈራ ላይ ለሙሽራው ዐጃቢ ያስተላለፈው መልእክት ዐምባጓሮ በሚነሣበት ወቅት በተሸከምከው ዱላ ተቃራኒ የሽነውን ወገን ካልደበደብክበት ወዲያ ወርውረህ ጣለው የሚል ነው። "ከዚያው መልሰው ከቆረጥክበት" ሲል ግን ቀድሞ ከነበረበት ዛፍ ላይ ዐጽቁን ቀጥለው ማለት እንዳልሽነ መረዳት ይገባል። ምክንያቱም አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ከተቆረጠ በኋላ ዳግም ከግንዱ ጋር ዐጽቁ ቢጣበቅ ሕይወት ዘርቶ ሊጸድቅ አይችልምና ነው።

ቃል ግጥም 88፡- ነይ ዞማ ዓለም ዓለም
ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም
} ሹለት ጊዜ

ከማጆቱ ይዛ ስትቃኝ እስከ ደጁ
ሳትሸለም ኼደች የነጉላው[26] ወዳጁ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አደም ሁሴን፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቀደም ሲል ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ባለው የማኅበረሰብ ባህል አንዲት ልጃገረድ በምታገባበት ወቅት በከንፈር ወዳጆቿ አማካይነት የተለያዩ ሽልማቶች ይሰጧት ነበር። ከሽልማቶቹ መካከልም ጥላ፣ መስተዋት፣ መስቀል፣ ድንብል፣ ወዘተ. የሚሉት ይገኙበታል። ብዙ የከንፈር ወዳጆች ያሏት በርካታ ሽልማቶችን ትሸለም ነበር። የሆታው ቃል ግጥም ግን የነጉላው የከንፈር ወዳጅ የሽነችው ሙሽራ ከአባት ከእናቷ ቤት ተሰናብታ ልትወጣ ስትል በመከታ ከተከለለ የዕቃ ማስቀመጫ ጓዳ ጀምራ እስከ ቤቱ በር ድረስ ወዲያና ወዲህ እያለች በዓይኗ ብታማትርም ምንም ዓይነት የቁሳቁስ ሽልማት ሳትሰጥ ከትዳር ጓደኛዋ ጋር ተጓዘች የሚለውን መልእክት ያስገነዘበናል።

[26] ደስታ ተክለ ወልድ (1962፡839) ነጉላ የሚለውን ቃል ሞኝ፣ ቂል በማለት ተርጉመውታል። ‹‹አንቺን መሳይ ልጅ እንዲህ ስታምሪ ከዚህ ከነጉላ ጋር እንዴት ትኖሪ›› እየተባለ የሚነገረው የቃል ግጥምም ይህንኑ ትርጉም ያመላክታል።

በመጨረሻም ሰርገኞቹ ከሙሽራው አባት ቤት እየደረሱ ባሉበት ወቅት ተቀባይ የኾኑ ልጃገረዶች የሙሽራውን መምጣት በጉጉት በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ ፍንጭ ወይም ምልክት ማግኘታቸውን በማስመልከት ከሚያቀነቅኗቸው ስንኞች መካከል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 89፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው ኾለት ጊዜ
ያባይ ዳር እንኮይ
አላፊራም ወይ፡፡
ብርሌ ተንኳኳ ጠጁ ሸተተኝ
ደርባባው ሙሽራ መጣ መሰለኝ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ብርቱካን ጫኔ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ እንደተገለጸው በሙሽራዋ ወላጆች ቤት ለሰርገኞቹ ከተዘጋጁት መጠጦች መካከል አንዱ ጠጅ እንደኾነና በመስተንግዶ ወቅትም ዓይነ-ገብ እንዲኾን በብርሌ የቀረበ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ ውሃን፣ ማርን እና ጌሾን በማደባለቅ የተጣለው ጠጅም መናኛ አለመኾኑን ለማመላከት ሽታው በርቀት አፍንጫን ማወድ እንደቻለ ግነታዊ በኾነ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ተገልጿል፡፡ ለዚህም ነው ሰርገኞቹን በመቀበል ላይ ያሉ ልጃገረዶች በጉጉት ሲጠበቅ የነበረውን ሙሽራ የመምጣት ፍንጭ ያገኙ መኾናቸውን ለማንጸባረቅ በርቀት “ጠጁ ሸተተኝ” በማለት ያቀነቀኑት፡፡ ምክንያቱም ሰርገኞቹ በብርሌ የተሞላላቸውን ጠጅ በመንገድ ላይ እየተጎነጩ ወደሙሽራው አባት ቤት ሲመለሱ ሽታው ለሌሎች ሰዎችም አፍንጫ ሊሰማ ይችላልና ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በሰርጉ ማግስት ባለው ሥርዓት ብርሌ በጥሬው ካለው ትርጉም ውጪ ሌላ ነገርን ሊወክል ይችላል፡፡

ይሄውም ሚዜ ወጊዎች ብርሌውን በጠጅ ሞልተውና በመሐረብ ሸፍነው ወደሙሽራይቱ ወላጆች ቤት ይዘው በመኼድ ለተሰበሰበው ቤተዘመድ ያሳያሉ፡፡ ይህ በጠጅ የተሞላው ብርሌ የተዳረችው ሴት ልጅ ድንግል ኾና መገኘቷን በወካይነት ያበስራል፡፡ በዚህን ጊዜ ወላጆቿ ልጃቸው ክብረ ንጽህናዋን ጠብቃ በመቆየቷ ከመደሰታቸውም በላይ የኩራት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ባንጻሩ ደግሞ የብርሌው ጠጅ ጎደሎ ከኾነ መሸራዋ ድንግልና እንደሌላት ያመለክታል፡፡ ወላጆቿም በሀፍረት ይሸማቀቃሉ (አጥኚው በሕይወት ገጠመኙ ካስተዋለው)፡፡ በቃል ግጥሙ የመጨረሻው ስንኝ ላይ እንደተጠቀሰው መምጣቱ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው ሙሽራ ሰውነቱ ወፈር፣ ደልደል ያለ፣ ጭምት ሰው መኾኑን ልጃገረዶቹ በዜማቸው አወድሰውታል፡፡

የሰርገኞቹ ተቀባይ የኾኑት ልጃገረዶች በቃል ግጥም ዘፈናቸው ሙሽራውን ማወደስ ብቻ ሳይኾን ለሙሽራዋ የተሰጠው ጥሎሽ ከፍተኛ መኾኑን የተቹበት የቃል ግጥምም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ቃል ግጥም 90፡- አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው ┐
ያባይ ዳር እንኮይ │ ኹለት ጊዜ
አላፈራም ወይ፡፡ │
የበሬውን ዋጋ ዐሥር ሺህ ብር ወስደሽ ┘
ወይፈኑ ሲደክም ትጠመጃለሽ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አህመድ ሱለይማን፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ለጥናቱ በተካለሉት ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ በአሁኑ ወቅት ሙሽራው ለታጨችው ሴት ልጅ የሚሰጠው ጥሎሽ ከዐሥር ሺህ እስከ ዐሥራ አምስት ሺህ ብር ድረስ እያደገ መምጣቱን ከመስክ የተገኘውን መረጃ በማጣቀስ በጥናቱ ማኅበረ ባህላዊ ዳራ ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ ማመዘኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ ይሄውም የሙሽራው ወላጆች ለእርሻ ሥራ የሚገለገሉበትን በሬ ዐብሮ ከሚጠመደው ቀንጃ ለይተው በዐሥር ሺህ ብር ከሸጡ በኋላ ለልጃገረዷ ጥሎሽ በመስጠታቸው ከቤታቸው ያለውን በሬ ከሌላ ጋር አቀናጅተው ለማረስ አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሣ ችግር ላይ ወድቀዋል፡፡ ስለዚህ በዕድሜም ኾነ በአካል ከበሬ አነስ ያለው ወይፈን ተጠምዶ ዐቅም ወይም ብርታት ካጣ እሱን ተክተሽ ቀንበር ከተጫነብሽ በኋላ ተጠምደሽ ታርሻለሽ በማለት ፌዝ በተመላበት ስሜት ልጃገረዶቹ ሙሽራዋን በዘፈናቸው ተችተዋታል፡፡ በአጭሩ ያን ያኽል ገንዘብ አውጥቶ ለሴት ልጅ ጥሎሽ መጣል የአርሶ አደሩ ዐቅም ሊፈቅድ አለመቻሉን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡

5.3.3. የቀብር ሥርዓት

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ከሚያልፍባቸው ዓበይት የሽግግር ሥርዓቶች መካከል የመጨረሻው ሞት መኾኑ አሌ የማይባል ነው፡፡ ይኼ ደግሞ ነፍስ ከሥጋ መለየትን፣ በሕይወት መኖር ማቆምን፣ የሕይወት ፍጻሜን የሚያመላክት ነው፡፡ በዚህን ወቅት ቋሚ የኾነው የቅርብ ወገን ነፍሱ ከሥጋው ለተለየችው ሰው በሐዘን ስሜቱ ስለሚነካ እንባ በእንባ ይራጫል፤ አስለቃሽም ያቆማል፡፡ አስለቃሹም በመለቀሻ ቦታ መካከል ላይ በመቆም ሙሾ እያወረደና የሚቹን ስም በግጥም እያነሣ ሐዘንተኞችን ያስለቅሳል፡፡ Finnegan (1970:147-166) የሙሾ ቃል ግጥሞቹ ሁል ጊዜ በሴቶችና በባለሙያተኞች፣ አልፎ አልፎም በወንዶች እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባለው የኅብረተሰብ ከፍልም ያለው እውነታ ይሄው ነው፡፡ በእውነቱ ከኾነ የሙሾ ድርደራ ለቅሶን፣ ከወዲያ ወዲህ እያሉ ስቅስቅ

ማለትን፣ ማንባትን ያካትታል። ይህ ደግሞ በተለይ ለሴቶች ተስማሚ ወይም ምቹ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት በአጥኚው አእምሮ ውስጥ ዐድሯል። ምክንያቱም ሴቶች በተፈጥሯቸው የማዘን እና የመራራት ስሜት ስላላቸው እያለቀሱ ማስለቀስ የሚችሉ በመሆናቸው የተነሣ ነው።

የሙሾ አዚያዚያም "ዋይ ዋይ ምን አገኘህ/ሽ"፣ "ዋይ ዋይ እንዳው ወየሁ ወየሁ" እና "አዬ ጉድ ዋይ ዋይ፣ አፈሩ በላህ ወይ" የሚሉት እንደሆኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ዘንድም እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ እንደዚሁም ወንድምና እኅት በሚሞቱበት ጊዜ በሚከወኑት የለቅሶ ሥርዓቶች የሙሾ ግጥምን ለማውረድ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በመሆኑም በየአጋጣሚዎቹ ከሚደረደሩት የሙሾ ግጥሞች መካከል የተወሰኑትን በቅደም ተከተል ቀጥሎ እንመለከታለን።

5.3.3.1. ለእናት ለቅሶ

የእናት ሞት በልጆች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ መሆኑን የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ያመላክታሉ። ምክንያቱም በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ እናት ልጅን ዘጠኝ ወር አርግዛ፣ ወልዳ፣ አጥብታ ከማሳደጓም በላይ የቤተሰቧን አባላት ሕይወት ለመደገፍ በርካታ የኾኑ መሠረታዊ ሥራዎችን ትሠራለች። በዚህ የተነሣ እናት ለልጆቿ በጣም ቅርበት አላት። Alembiም (2002:95) "Women are the most primary and constant agents of child socialization" በማለት ገልጸዋል። በዚህ መሠረት እናት ለልጅ ያላትን የጠበቀ ቁርኝት በተመለከተ ከተደረደሩት ቃል ግጥሞች መካከል ኹለቱን ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 91፡- እናት የሌለው ልጅ ቀላል እንደ ጌሾ
ሳይበላም በላ ነው ሳይናገር ዋሾ።

(ቃለ መጠይቅ፣ አካሉ ወደደኝ 20/05/2019)፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ ሙሾ ደርዳሪው በተፈጥሮ የማይገናኙ ኹለት ነገሮችን ወስዷል - እናት የሌለውን ልጅና ጌሾን። ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንድ ተመሳሳይ ገጽታ ፈልጎ በማመሳሰል እንግዳና አዲስ ስሜትን በአድማጭ አእምሮ ውስጥ ለማስረጽ ችሏል። ተመሳሳይ የኾነ ገጽታ አላቸው የተባሉት ኹለቱም ነገሮች ከተለያዩ ጎራዎች የመጡ ናቸው። ይሄውም እናት አልባ የኾነው ልጅ ሰብዓዊ ፍጡር ሲኾን፣ ቅጠሉና እንጨቱ እየተወቀጠ ለጠላ መጥመቂያና ለጠጅ መጣያ የሚኾነው ጌሾ ደግሞ ምድቡ ከተክል ወገን ነው። በልጁና በተክሉ መካከል ያለው ተመሳሳይ ገጽታ ክብደት ማጣት ነው። ምክንያቱም ከስፍረት (volume) አንጻር በትልቅ ጆንያ

ውስጥ ያለ ጌሾ ሰፊ የኾነ ሥፍራ ቢይዝም ክብደት የለውም። እናት የሌለው ልጅም በሰዎች ዘንድ የመፈራትና የመከበር ጸጋው የተነጠቀ፣ ክብሩ የማይጠበቅለት ኾኖ ቀርቧል። በዚህ የተነሣም ሰዎች "ያልኾነውን ኾነ፤ ያልተናገረውን ተናገረ" በማለት ማንነቱን ያጎድፉታል። በመኾኑም የሚበላ ነገር አጥቶ እየራበው ሳለ ተመግቧል እየተባለ የምግብ ክልከላ ይደረግበታል። ከዚህ በተጨማሪ የውሸት ጎሬ አድርገው በመቁጠር እውነቱን እየተናገረ ሳለ ዐባይና ቀጣፊ አድርገው ያለ ስሙ ስም ሰጥተውታል። በአጭሩ ስመ ክፉ እንዲኾን አድርገውታል ማለት ነው።

ቃል ግጥም 92፡- አትቅበሩኝ አለች ካንገቴ በላይ
ሲወጡ ሲገቡ ልጆቼን እንዳይ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሪ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ሙሾ ደርዳሪው/ዋ/ በቃል ግጥሙ አማካይነት ዐጸደ ነፍሷ ከሥጋዋ ለተለየችዋ የልጆች እናት የሰውን ልጅ ባሕርይ ሰጥቶ/ታ/ ሲያናግራት ይደመጣል /ስታናግራት ትደመጣለች/። በመኾኑም በርካታ ልጆች የወለደች እናት አስከሬኔን ጉድጓድ ውስጥ አስገብታችሁ በዐፈርና በድንጋይ ስትሞሉና ግብኣተ መሬቴን ስትፈጽሙ ዓይኔ የሚገኝበትን የአንገት ክፍል እንዲትተውልኝ በማለት ተማጽናለች። ለዚህም ምክንያቱ እናታቸው የሞተችባቸው ልጆች ለሰውነታቸው የሚስማማ ምግብና መጠጥ፣ ማለፊያ የኾነ ኑሮ፣ ሐዘን፣ ቅርታ፣ ችግር፣... የሌለበት ሕይወት ሊኖሩ አንደማይችሉ ታውቃለች። ስለዚህ ምንም ነገር ማድረግ ባልችል እንኳን ልጆቼ ከቤት ወደውጭ፣ እንደዚሁም ከውጭ ወደቤት ውስጥ ሲገቡ ለብዙ ጊዜያት ያኽል ምግብ ከማጣታቸው የተነሣ በረኃብ ዐለንጋ መገረፋቸውን፣ በልብስ ዕጦትም ገላቸው የሚታይ ዕርዝተኛ መኾናቸውን በዓይኔ እንዲመለከታቸው አድርጉኝ የሚለውን ተማጽኖ ማሰማቷን በሙሾ አውራጁ/ጇ/ አማካይነት ተነግሮናል።

5.3.3.2 ለአባት ለቅሶ

አባትን በተመለከተ ከመስክ የተሰበሰቡት የሙሾ ቃል ግጥሞች ብዛታቸው አነስተኛ ኾኖ ተገኝቷል። በእርግጥ አባት ወላጅ ነው፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪም ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለልጆቹ መመኪያና አለኝታ መኾኑን የሚያመላክተው የሙሾ ቃል ግጥም ቀጥሎ ቀርቧል።

ቃል ግጥም 93፡- ለልጆችህ ኩራት መከታ ነበርክ
ዛሬስ ሳታስበው ድንገት ተሸነፍክ።

(ከቀያፈር አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኘ የጽሑፍ መረጃ፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

አትክልት ከተተከለ በኋላ ውሃ እየጠጣ፣ የለሰለሰ ዐፈር እየታቀፈና እየተኮተኮተ ካደገ መጨረሻ ላይ አጥጋቢ የኾነ ውጤትን ያስገኛል። ልጅም ቢኾን በእግሩ ቁሞ መኼድ ከጀመረበትና አፉንም ከፈታበት ጊዜ ጀምሮ በወላጆች በተለይም በአባት ምክር፣ ተግሣጽ፣ እንዲያም ሲል በቅጣት ከተኮተኮተ ጥሩ የኾነ ሥነ ምግባርን ተላብሶ የሚያድግ ይኾናል። ሥነ ምግባር የመላበሱ ኺደት በልጅነት ጊዜ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነገር ሳይኾን እስከመጨረሻው ድረስ ሊዘልቅ ይችላል። የአንድ ልጅ ሥነ ምግባር ዋጋ ሊኖረው የሚችለው በቤተሰቦቹ ዘንድ ብቻ አይደለም። በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ ጭምር ነው። በዚህ የተነሣ "የእገሌ ልጅ ምንኛ ታዛዥ ነው፤ ምንኛ ትሑት ነው" ያሰኘዋል። ይህንን ዓይነት ሥነ ምግባር ተላብሶ ያደገ ልጅ በአባቱ ኩራት ይሰማዋል፤ የመመካት ስሜት ያድርበታል። በተቃራኒው ደግሞ ክፉ ነገር አጋጥሞት እንዳይበሳጭና እንዳይተክዝ አባቱን አለኝታና መመኪያ ያደርጋል። በእንደነዚህ ባሉ ኹኔታዎች ለልጁ መከበሪያ የኾነ አባት ሳያስበው ድንገት በሞት ሲለይ ከእንግዲህ በኋላ ይህንን ሁሉ ለልጆችህ ማድረግ አልቻልክም፤ ተረታህ በማለት ሙሾ ደርዳሪው ለቀስተኞቹን ሐዘን ተሰምቷቸው እንዲያለቅሱ ያደርጋል።

5.3.3.3. ለልጅ ለቅሶ

የማንኛውም ሰው ያጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ቁራጭ የኾኑት ልጆች ለወላጆቻቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መኾኑ የሚታወቅ ነው። በቃል ኪዳን ተሳስረው ሕጋዊ በኾነ ጥምረት ትዳር መሥርተው የሚኖሩ ባልና ሚስት ትዳራቸው የሚሞቀውና የተሟላ ሊኾን የሚችለው ልጆች ሲኖሯቸው ነው። በተለይም በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ልጆች ከብት በማገድ፣ እርሻ በማረስ፣ ዐረም በማረም፣ ሰብል በማጨድና በመውቃት ተግባራት ላይ ስለሚሳተፉ ከፍተኛ የኾነ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አላቸው። ዘርም ሳይቋረጥ ቀጣይነት የሚኖረው ልጆች ሲወለዱ ነው። በዚህ የተነሣ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበትን ሰው ለመድረስ ከቤቱ የኼደ ለቀስተኛ "ለመኾኑ ልጅ ወልዷል/ለች/? ብሎ የሚጠይቀውም የዘርን ቀጣይነት ለማመልከት ነው። በመኾኑም ልጅን በተመለከተ ከተደረደሩት የሙሾ ግጥሞች መካከል አንዱን ቀጥሎ ለማየት እንሞክር።

ቃል ግጥም 94፡- ምናለች እኅቱ ምናለች እናቱ
እንደ አባጅኝ[27] ጎመን ዘፍ ሲል ዐንገቱ።

(ከከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/07/2012)

[27] አባጅኝ ማለት የጎመን ስም ሲኾን ‹‹አይደርቁ›› በመባልም ይታወቃል። ትርጉሙም በጋውን አቆየኸኝ፤ አሳለፍከኝ ማለት ነው።

በዚህ የሙሾ ቃል ግጥም ውስጥ ተጠቃሾቹ እኅትና እናት ናቸው። ለዚህ ምክንያት ሊኾን የሚችለው ደግሞ ሴቶች በተፈጥሯቸው ራሮት ስላላቸው ይኾናል ብሎ መናገር ይቻላል። ቀጥሎም እነዚህ የሥጋ ዝምድና ያላቸውና የሚተሳሰቡ ሰዎች የልጁን ሞት ሲሰሙ ምን ዓይነት ስሜት ውስጥ እንዳሉ ለማወቅ በመፈለጉ በምናዊ የጥያቄ አቀራረብ ስልት ሙሾ አውራጁ ሲጠይቅ እንሰማዋለን። የቃል ግጥሙ ደራሽ የሚጠይቀው ሌሎች ተደራሾች ጠንቅቀው የሚያውቁትን እውነታ ማለትም እነዚህ ወገኖች ከሚገባው በላይ ሐዘን የገባቸው መኾኑን ለማስረጽ ነው። ወደፊትም ቢኾን በሐዘን ሊቆራመዱ እንደሚችሉም ጥቁምታን ይሰጣል። በቃል ግጥሙ ውስጥ ነፍሱ ከሥጋው የተለየችው ልጅ ዐንገት በበጋ ወራት ሳይደርቅ ለዓመታት ያኽል ጥቅም ከሚሰጥ የአባጅኝ የጎመን ዓይነት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። በንጽጽሩም የተቆረጠ ጎመን በፀሐይና በነፋስ ልምላሜው ሲጠፋ የሚኖረው ገጽታ መጠውለግ ነው። ነፍሱ ከሥጋው የተለየችው ልጅ መቃ (ረኻቦም) አንገትም ጭንቅላቱን መሸከም ሲያቅተው ወደአንድ አቅጣጫ ከንበል ያለ መኾኑን በዓይነ ኅሊናችን እንዲንመለከተው አድርጎናል። በእርግጥ የማንኛውም ሰው አካል በድን ሲሆን ሚዛን ጠብቆ ሊሸከመው የሚችል ነገር ስለማይኖር አንገት ብቻ ሳይሆን ሙሉ አካሉም ቢኾን በቁመቱ መጋደሙ አይቀርም።

5.3.3.4. ለወንድም ለቅሶ

አጥኚው በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ካገኛቸው የሙሾ ግጥሞች መካከል በወንድም የለቅሶ ሥርዓት ወቅት የሚከወኑት ይገኙበታል። ቃል ግጥሞቹ ከሚያነሧቸው ፍሬ ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ በወንድም ሞት የተነሣ ያልተሟላ ሕይወትን መምራት እንደሚያጋጥም፣ ጠላት እንደሚበረክት፣ ወዘተ. የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። ለአብነትም ቀጣዮቹን ቃል ግጥሞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 95፡- ወንድም የሌለው ሰው አያድግም መስሏቸው
እያደገ ኼደ እየበለጣቸው።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ የሱፍ፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ወንድሙ የሞተበትን ልጅ የተመለከቱ ሰዎች በሥርዓተ ቀብሩ ወቅት የልጁን የወደፊት የሕይወት ዕጣ ፈንታ በማስመልከት እያነሡ ሲጥሉ የነበረውን መጥፎ ነገር በመስማት ቅር የተሰኘና ኹኔታዎችን የገመገመ ሙሾ አውራጅ በትዝብት መልክ ሐሳቡን በቃል ግጥም አንጸባርቋል። ይሄውም ሰዎቹ ከእናቱ ወይም ከአባቱ ወይም ከኹለቱም ወገኖች የተወለደው ወንድሙ ስለሞተበት ከእንግዲህ በኋላ ፈቃጅ የለውምና በአካልም ቁመቱ ሊመነደግ፣ በሀብትም ቢኾን ሊደረጅ አይችልም የሚል አስተያየት ነበራቸው በማለት ሙሾ

ደርዳሪው ገልጿል። ኾኖም ግን እነሱ ያሰቡት ቀርቶ ያላሰቡት ኾነና እንዳውም ከእነሱ በበለጠ ኹኔታ እየላቀ፣ ከፍ እያለና እየተሻሻለ የኼደ መኾኑን አስለቃሹ በቃል ግጥሙ ገልጿል። ሞት ለሁሉም አይቀሬ ነገር ነው። እውነታው ይህ ኾኖ ሳለ የሰዎቹ አስተያየት ግን የሚያቀባብር ሳይኾን የሚያቀያይምና የሚያጣላ መኾኑን በጊዘውና በቦታው የተገኙት ለቀስተኞች የሚገነዘቡት ጉዳይ መኾኑን ማጤን ይገባል።

ቃል ግጥም 96፡- ወንድሞቹ ዐልቀዋል ወልደሽ ተኪ እናቱ
በሣር በቅጠሉ ጠናብኝ ጠላቱ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽ አብዱ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የሙሾ ቃል ግጥሙ የተደረደረለት ግለሰብ ወንድሞቹ ከዚች ዓለም በሞት እንደተለዩ በምሬት ገልጿል። በዚህ የተነሣ ሁሉም ሰው ባላጋራ ወይም ጠላት ስለኾነበት በትንሽ ትልቁ ጥቃት እንደሚደርስበት ይናገራል። ለዚህ ደግሞ ዋናው መፍትሔ በሞቱት ልጆች ምትክ እናቱ ወንዶች ልጆችን ወልዳ እንዲትተካለት ተማጽኗል። ምክንያቱም በቀድሞ ጊዜ ከጎሽ፣ ከጉማሬ፣ ካውራሪሥና ከዝኖን ቆዳ የተሠራው ጋሻ በጦርነት ወቅት ለጀግና መከላከያ ኾኖ ያገለግል እንደነበረ ሁሉ ወንድምም ለወንድሙ መመኪያ፣ አለኝታ፣ ... ስለኾነ ጥቃት በሚከሠትበት ወቅት እንደ መከታ ኾኖ ሊከላከል ይችላል።

5.3.3.5. ለእኅት ለቅሶ

ለታናሽ እኅትና ወንድም ሞግዚት በመኾን በበላይነት የምትንከባከብ፣ ዳባሽና አጉራሽ፣ እንደዚሁም የናት አምሳያ የኾነች እኅት የሥጋዊና የደማዊ ሕይወቷ ፍጻሜ ካገኘ በኋላ በሥርዓተ ቀብሯ ወቅት ከሚደረደሩት የሙሾ ቃል ግጥሞች መካከል ኹለቱን ብቻ ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 97፡- ትድኛለሽ ብዬ ኮርቼ ነበረ
አኅት አለኝ ብዬ ኮርቼ ነበረ
ትንፋሽሽ ሲጠፋ ቅሥሜ ተሰበረ።

(ከቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

በዚህ የሙሾ ቃል ግጥም ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት በደዌ ዳኛ፣ ባልጋ ቁራኛ ተይዛ እንደነበር፣ ወንድሟ ግን ካደረባት ሕመሟ ትፈወሳለች ብሎ ተስፋ ከማድረጉም በላይ ጤነኛ ትኾናለች፣ ከሞት ትተርፋለች ብሎ በውስጡ ኩራት ዐድሮበት እንደነበር ተገልጿል። ነገሩ ተስፋ የሌለው፣ እሷም ብትኾን ታሞ አይድኔ ኾነችና ሕይወታዊ ነፍሷ ከሥጋዋ ተለይታ ለዘለዓለም አሸለበች። በዚህ የተነሣ ወንድምዮው እንዳለ ቅሥሜ ተሰብሮ ከሰውነት ውጭ ኾንኩ በማለት ይናገራል።

የቃል ግጥሙ ተደራሲም እኅቱ የሞተችበት ሰው በደረሰበት ሐዘን እና መከራ በጣም እንደተጎዳ፣ የጎሊና ስብራትም እንደደረሰበት ሊረዳ ይችላል።

ቃል ግጥም 98፡- ምነው እኔ በሞትኩ ድኻው ወንድምሽ
የምትሰጭበት (ምታበይበት) ከሚፈርስ ቤትሽ።

(ቃለ መጠይቅ፣ እንዳልካቸው ግዛው፣ 06/01/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

የሙሾ ደርዳሪው "ምነው" በሚል የሐዘን እና የጸጸት መንፈስ ቃል ግጥሙን የጀመረው እኅቱን በሞት የተነጠቀው ሰው ከፍተኛ የኾነ ጉዳት እንደደረሰበት ለማመላከት ነው። በመቀጠልም በወንድምነት የቀረበው ግለሰብ በምን ምክንያትና ለምን ሞትሽ እያለ በመጠይቃዊ ቃል ሲጠይቅ በእዝነ ልቦናችን እናዳምጠዋለን። ከሞተ ሞተ፣ ከተለየም ተለየ እንደሚባለው በቂ የኾነ መተዳደሪያ የሌለው የሟቿ ወንድም ዳግም እንደማይመለስ እያወቀው በአንች ምትክ እኔ ነዳዩ፣ የሰው እጅ ጠባቂው የሕይወቱ ፍጻሜ በኾነ፣ ነፍሴ ከሥጋዬ በተለየች ብሏል። ምክንያቱም እኅቱ ለኑሮው አስፈላጊ የኾኑ ነገሮችን ላጣው ወንድሟ ማሟላቷ ይቅርና ለሌላውም ቢኾን ቤቷን ሰው አያውቀውም የምትባል አይደለችም። ከቤት ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ማንኛውንም ምግብና መጠጥ የምታበላበትና የምታጠጣበት ጎጆዋ ከሚፈርስና ሀብትና ንብረቷም ከሚባክን በእሷ ፋንታ ወንድሟ ቢሞት የሚመርጥ መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል።

ምዕራፍ ስድስት፡- የቃል ግጥሞች የዘውግ ምደባ

ዘውግ በመጠንም ኾነ በዓይነት በአብዛኛው የማይገናኙ፣ እንደዚሁም እንዳመችነታቸው በዋና ወይንም በንኡስ የተከፋፈሉ ጽንሰ ሐሳቦች ጃንጥላ ነው (Harris,1995፡509)፡፡ ለምሳሌ በሥነ ጽሑፍ ምሁራን እንደተለመደው ሥነ ጽሑፍን በዋና ዋና ዘውጎች (ልቦለድ፣ ግጥምና ድራማ) ከመደቡ በኋላ እያንዳንዳቸውንም ቴክኒካዊ በኾነ መንገድ በተለያዩ ንኡሳን ዘውጎች ይከፋፍሏቸዋል፡፡ እንደ Harris ማብራሪያም ቃል ግጥም የሚለውን ዋና ዘውግ ወስደን ብንመለከት እንኳ የጀግንነት ግጥም፣ የጀብዱ ግጥም፣ ጀግናውን በተመለከተ የሚቀርብ የቀልድ፣ የፌዝ ግጥም፣ ግላዊ ስሜትን የሚገልጽ አጭር ግጥም፣ አወዳሽ ግጥም፣ የሙሾ ግጥም፣ አስደናቂ አባባሎችን እና ተረቦችን የያዘ ግጥም፣ ስለሚች የሚናገር በመቃብር ድንጋይ ላይ የሚቀረጽ አጭር መግለጫን የያዘ ግጥም፣ ለተለያዩ አካላት የሚላኩ መልእክቶችን አዘል ግጥም፣ የክብት አርቢ ግጥም፣ የገጠር ሕይወትን የሚያንጸባርቅ ግጥም የሚሉትን ንኡሳን እና የንኡሳን ንኡስ ምድቦችን ያካትታል፡፡

የቃል ግጥም ዘውጎችም ከሚቀርቡባቸው ማኅበራዊ ዐውዶችና አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ የፍቅር፣ የምርቃት፣ የሰርግ፣ የለቅሶ፣ የእንቁጣጣሽ፣ የሥራ፣ የፉከራ፣ የቀረርቶ፣ የእረኛ፣ የበገና፣ የክብረ በዓል፣ ... ብሎ መከፋፈል ይቻላል፡፡ በዚህ የምርምር ጽሑፍም በተለያዩ ዘዴዎች ከመስክ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች የግብርና ሥራ፣ የሰርግ፣ የሙሾ፣ የሆታ፣ የቀረርቶና የፉከራ በማለት ለመመደብ ተችሏል፡፡ እዚህ ላይ ለማስገንዘብ የምፈልገው የዘውግ ምደባው የተካኼደው ስሜቱ በመራኝ መንገድ ሳይኾን ማኅበረሰቡ እንዳለው ተጨባጭ የቃል ግጥም ሀብት አንጻርና ቃል ግጥሞቹ ከወቅታዊ አንሥቶ እስከ ዓመታዊ ክሥተቶች ድረስ በሚከወኑባቸው ጊዜያት ነው፡፡ በእርግጥ በአንድ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ቃል ግጥሞች በሌላ ምድብ ውስጥ የሚገኙ መኾናቸውን በዘውግ ምደባ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ለአብነትም የቀረርቶና የፉከራ ቃል ግጥሞች በእርሻና በአጨዳ የሥራ ወቅት እየተቀነቀኑ ይገኛሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዘውግ በዘውጋቸው የተመደቡት ቃል ግጥሞች በሚከተለው ኹኔታ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

6.1. የግብርና ሥራ ቃል ግጥሞች

ይህ ርእሰ ጉዳይ አርሶ አደሩ የጉልበት እንቅስቃሴን በሚጠይቁ የተለያዩ የግብርና የሥራ መስኮች ላይ ተሰማርቶ የሚያከናውናቸውን ተግባራት የሚመለከት ይኾናል፡፡ በመኾኑም ለጥናቱ በተመረጡት ወረዳዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ በማሳቸው ላይ ሲበትኑ፣

ብስባሽ ሲያዘጋጁ የዕርከን ሥራ ሲሠሩ፣ ፀረ ዐረም ኬሚካል በሰብላቸው ላይ ሲረጩ፣ ሲያርሱ፣ ሲያርሙ፣ ሲያጭዱና ሲወቁ የሚያዜሟቸውን ቃል ግጥሞች ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

ቃል ግጥም 99፡- ወጣቱ ተነሣ ማዳበሪያ ዝራ መሬትህን ደልድል
ነጭ ጤፍ አምርተህ እንዲትባል ሞዴል፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ወንድወሰን ታረቀኝ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ "ወጣት" ለሚለው ቃል አንድ ድንጋጌ ላይ መድረስ አስፈላጊ ኾኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሠረት የወጣቶችና የስፖርት ሚኒስቴር ብሔራዊ ፖሊሲ በሚያዘጋጅበት ወቅት ወጣት በሚለው ሥር ሊታቀፉ የሚችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከስንት እስከ ስንት ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኙ ደንብ ለማውጣት የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን እና የተለያዩ ሐገራትን ተመክሮ ተመልክቷል፡፡ በመኾኑም በኢትዮጵያ ከ15-29 ዕድሜ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ወጣት እንደሚባሉ ተደንግጓል (የወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲ፣ ያልታተመ)፡፡ በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ደግሞ ጠንካራዎችና ብርቱዎች፣ እንደዚሁም ሠርተው ያልጠገቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ወጣቶቹ በኑሯቸው ላይ ለውጥን ማምጣት እንዲችሉ ለሥራ መነሣሣት እንዳለባቸው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ይገልጻል፡፡ በመኾኑም የእርሻ ማሳችሁን ደግማችሁ ደጋግማችሁ በማረስ ካለሰለሳችሁና ካስተካከላችሁ በኋላ ዐፈሩ ለሰብሉ ጠቃሚታ እንዲኖረው የሚያደርገውን፣ በፋብሪካ የሚዘጋጀውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን ማዳበሪያ መጠቀም አለባችሁ በማለት ገጣሚው ይመክራል፡፡ በእነዚህ ጥረቶቻችሁም ነጭ ጤፍ ዘርታችሁ፣ ዐጭዳችሁና ወቅታችሁ ጥሩ ምርት ስለምታገኙ ካሁን በፊት ላሉ ወይም ወደፊት በእርሻ ተግባር ለሚሰማሩ አርሶ አደሮች እንደ ምሳሌ ኾናችሁ የምትቀርቡና የምትታዩ ትኾናላችሁ፤ በናሙናነትም ትሰየማላችሁ ወይም ስም ይሰጣችኋል በማለት ገጣሚው አዚሞላቸዋል፡፡

ቃል ግጥም 100፡- ስንፍና ነው እንጂ የሰው ልጅ ጠላቱ
ምርትን ይጨምራል በኮምፖስት መዝራቱ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 07/01/2013)፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ሰው ለተባለ ጠቅላላ ፍጡር ሁሉ ባላጋራውና ባላንጣው ስንፍና እንደኾነ በጽኑ ተገልጿል፡፡ ስንፍና ደግሞ ዐቅመ ቢስነትን እና ደካማነትን ብቻ ሳይኾን ለሥራ ያለ ቆራጥነት አናሳ መኾንን፣ ችልተኛነትን፣ ሥራ አለመውደድን ወይም ሥራ መጥላትን፣ እንደዚሁም መቦዘንን ያመለክታል፡፡ በአጭሩ ሥራን አታሳዩኝ ወይም አታምጡብኝ ማለት እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩት አርሶ አደሮች በሙሉ ለእድገት ማነቆ የኾነውን ስንፍናን እርግፍ አድርገው በመተው ምርትን

መጨመር እንደሚገባቸው ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል። ለዚህ ደግሞ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋትን ቅሪትና የሣር በል እንስሳትን ፍግ ከውሃ ጋር አዋሕደው በጉድጓድ ውስጥ እንዲብላላ ካደረጉ በኋላ ከዐፈር ጋር በመጨመር የተለያዩ የእኽል ዓይነቶችን መዝራት ይኖርባቸዋል። በዚህ የተነሣ አርሶ አደሮቹ በማሳቸው ላይ ከነበረው ሰብል የሚያገኙት ምርት ቀድሞ ከነበረው በላይ ውጤቱ ከፍ ይላል፤ ያድጋል በማለት ገጣሚው አዚሟል።

ቃል ግጥም 101 ዐፈሩን በውሃ በሙጃ አበስብሼ
ያንን ሾክኬ ማሳ እንደ ጨው አልሼ
ምርቴን ይገፍ ገባሁ እንደ ዐፈር አፍሼ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ እንድሪስ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

አርሶ አደሩ ብስባሽን አዘጋጅቶ በማሳው ላይ ካለው ዐፈር ጋር በማደባለቅ ምርቱን ማሳደግ እንደሚችል በሦስቱ ስንኞች የተዋቀረው ቃል ግጥም ይገልጻል። ይሄውም በግጥሙ ውስጥ የተሳለው ገጸ ሰብ የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት በቅድሚያ በክረምት ወራት በብዛት በቅሎ በቶሎ የሚያድገውን እና መስከረም ሲጠባ በፍጥነት የሚጠወልገውን የሙጃ ሣር በመጠነኛ ውሃ አዋሕዶ ብስባሽ ማዘጋጀት እንዳለበት ገልጿል። ከዚያም እርጥበቱ ቶሎ ከሚለየው ሾክኬ የማሳ ዐፈር ጋር ማደባለቅ እንደሚገባውም አመላክቷል። በዚህ ሁሉ ተግባርም አል - ሰዋዊ የኾኑ ነገሮች በንጽጽር ቀርበዋል። ተነጻጻሪዎቹም የዐፈር ለምነትን ለማሳደግ የሚያገለግለው ብስባሽና ጨው የተባለው ማእድን ናቸው። ለዕለት ፍጆታ የሚውለው ምግብ ጥሩ ጣዕም እንዲኖረው ጨው እንደሚጨመርበት ሁሉ ሾክኬው ዐፈር ላይም በከፍተኛ ልፋትና ድካም የተዘጋጀውን ብስባሽ በመበተን ምርትን ማሳደግ እንደሚቻል ገጣሚው ያስረዳል። በዚህ ዓይነት መልኩ የሚገኘው ምርትም ቢሾን እንደ ልብ ከሚዛቅ ዐፈር ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል። ምስስሉም ከተቆፈረ የመሬት አካል የሚገኘውን ዐፈር በቀላሉ ማፈስ እንደሚቻል ሁሉ በማሳ ላይ ያለው እኽልም ከታጨደ፣ ከተወቃ፣ በመጨረሻ ላይም ከእብቅና ከገለባ ከተለየ በኋላ የተጣራውን ከፍተኛ ምርት አርሶ አደሩ በእጁ አስገብቶ ወደቤቱ መጓዙን ገጣሚው ባሰናኛቸው ስንኞች ለመግለጽ ችሏል።

ቃል ግጥም 102፡- አዝመራውን ሁሉ ዐረም እንዳይበላው
ቤተሰብ ተጋግዞ በጋራ ማረም ነው።

(ከቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)

በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች ታትረውና ሥራን ተረዳድተው ማከናወን እንደሚገባቸው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ይመክራል። በመኾኑም አርሶ አደሮቹ በማሳቸው ላይ

ካለው ሰብል ከፍተኛ የኾነ ምርት ሊያገኙ የሚችሉት በብቋያ ደረጃ ካለው እኽል ውስጥ አላስፈላጊ የኾነውን ቅጠልና ሣር በመተጋገዝ በወቅቱ ነቅለው መጣል ሲችሉ እንደኾነ ይታወቃል። ነገር ግን ከብቋያ ጋር ዐብሮ የሚበቅለውና አስፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ተነቅሎ የሚጣለው ዕፅዋት በጊዜው ካልተወገደ ሰብሉ በሚገባው መጠን ሳያድግና ሳይወፍር ይቀራል - ይቀጭጫል። በዚህ ምክንያትም አርሶ አደሮቹ የሚፈለገውን የምርት መጠን ሊያገኙ አይችሉም። ስለዚህ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የሥጋ ዝምድና ያላቸውም ኾኑ የሌላቸው ሰዎች ተደጋግፈውና በአንድነት ኾነው ከአዝመራቸው ውስጥ የዐረም ማረሙን ሥራ በወቅቱ ካከናወኑ ከፍተኛ የኾነ ምርት ሊያገኙ እንደሚችሉ ቃል ግጥሙ ያመላክታል።

ቃል ግጥም 103፡- ዐፈር ታጥቦ እንዳይሄድ በንፋስ በጎርፉ
ዕርከንን እንሥራ ሁሉም በየዘርፉ።።
(ቃለ መጠይቅ፣ አየሉ ከማል፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ምክር አዘል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር በዕርከን መሥራቱ ተግባር ላይ ተሳታፊም፣ ቆስቋሽም ወይም ገፋፊ ኃይል ኾኖ ነው የቀረበው። ምክንያቱም በኃይል በሚንቀሳቀሰው ንፋስ፣ እንደዚሁም በብላጊና በክረምት ወቅት በሚጥለው ኃይለኛ ዝናም የተነሣ ዐፈርን፣ ሣርን፣ ቅጠልን፣ ድንጋይን፣... በሚወስደው ጎርፍ በአርሶ አደሮቹ የእርሻ መሬት ላይ ያለው ለም ዐፈር ምንም ሳይቀር ሙጥጥ ተደርጎ መወሰዱ አሳስቦታል። ስለዚህ በፍጥነት በሚከንፈው ንፋስ በየማሳው ላይ ያለው ለም ዐፈር እየተጠረገ እንዳይወሰድ፣ በዝናብ ወቅትም ቢኾን በብዛት መሬት ለመሬት በሚፈሰው ጎርፍ አማካይነት እንዳይሸረሸር ደግፎ የሚይዘውን የድንካይ ካብ ወይም የዕርከን ግንባታ ተግባሩን በትክክል እናከናውን በማለት ለሥራ ያለውን ቁርጠኝነት ባቀነቀናቸው ስንኞች ገልጿል። ለዚህ ተግባርም አቀንቃኙ እገሌ እገሌ ብሎ ሳይል ጠቅላላው የኅብረተሰብ ክፍል አንድም ሳይቀር ከየአካባቢው በመውጣት የዕርከን ሥራውን ማከናወን እንዳለበት መልእክቱን አስተላልፏል። ምክንያቱም አርሶ አደሮቹ በእርሻ መሬታቸው ላይ የዐፈር ዕጥበትን በመከላከል ምርታቸውን የሚያሳድጉት ዕርከንን በአግባቡ ሲሠሩ እንደኾነ ግለሰቡ በሚገባ ማወቅ በመቻሉ የተነሣ ነው።

ቃል ግጥም 104፡- ልማትን እናልማ በጋራ ኾነን
እድገት አይገኝም ዕርከንን ካልሠራን።።

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ምንም እንኳን ልማት የሚለው እሳቤ ሰፊና ውስብስብ ቢኾንም የአንድ ሀገር ኅብረተሰብ ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በኢኮኖሚውም ኾነ በማኅበራዊው፣ እንዲሁም በፖለቲካው ዘርፍ የመሻሻል ኹኔታ ማሳየት ሲችል እንደኾነ ሥዩም ተፈራ (1999፡165) ገልጸዋል። በቃል ግጥሙ ውስጥ

ግን ልማት የሚለው ቃል በአግባቡ ቢታረስ ጥሩ ምርት ሊያስገኝ በሚችለው መሬት ላይ ዕርከንን በመሥራት ለምነቱን መጠበቅ ማለት እንደኾነ ማጤን ይገባል። ዕድገትን ስንመለከት ደግሞ የለውጥ ውጤት በተለይም የዓይነት ለውጥ፣ ከዝቅተኛው ወደከፍተኛው የሚደረግ ሽግግር እንደኾነ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት (1978፡358) ያስረዳል። በዚህ መሠረት ከግለኝነት ይልቅ በዐብሮነት ላይ ትኩረቱን ያደረገው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የእርሻ መሬታችን ለም ዐፈር በተለያዩ የተፈጥሮ ክሥተቶች ተጠራርጎ እንዳይወሰድ በጋራ ኾነን ዕርከን በመሥራት ልማትን ማልማት አለብን የሚለውን መልእክት ለማኅበረሰቡ ማስተላለፍ ችሏል። ይህ ካልኾነ ግን የተሻለ ምርት ልናመርት አንችልም፤ በሕይወታችንም ለውጥን አናመጣም፤ የሀብት ባለቤት ልንኾንም አንችልም በማለት አስገንዝቧል።

ቃል ግጥም 105፡- ያጨዳው ንዳድ ያጨዳው ንዳድ
አይለውጥም ስንዴ በንክርዳድ።

(ከቀያፈር አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የፉከራ ቃል ግጥሙን የተናገረው ገጸሰብ ሰብሉን በማጨድ ተግባር ላይ እያለ ራሱን ሲያሞግስ ይስተዋላል። ምክንያቱም አንዳንድ አርሶ አደሮች ባገኙት ምርት ራሳቸውንም ኾነ ቤተሰቦቻቸውን እየመገቡ ዓመቱን በሙሉ መዝለቅ ሲያቅታቸው በአብዛኛው እንክርዳድ ያለበት እኽል[28] ተበድረው በምትኩ ንጹሕ ስንዴ ለአበዳሪዎቻቸው ይመልሳሉ። እሱ ግን ተግቶ የእርሻ ሥራውን በመሥራት ባገኘው የተሻለ ምርት ዐዳሩ የሞቀ ስለኾነ ሀብታም ዘንድ በመኼድ ደጅ ባለመጥናቱ ራሱን ለማሞገስ ችሏል። ግለሰቡ ራሱን ለማድነቅም "ያጨዳው ንዳድ የሚለውን ሐረግ በመደጋገም ሲጠቀም ተመልክተናል። ይህን ዓይነቱን የቋንቋ ስልት የተጠቀመው ለአንድ ውለኛ ጉዳይ ሲባል ነው። ይሄውም በዋናነት ያተኮረበትን ነገር ይበልጥ አንሮ ለመግለጽ ስለፈለገ ነው። ከድግግሞሽ ስልት በተጨማሪ ገጣሚው በለዋጭ ዘይቤ ንዳድ (ወባ) የተባለችውን የቆላ በሽታ ባሕርይ ለራሱ ተላብሷል። እንደሚታወቀው የወባ በሽታ የምታተኩስ፣ የምታንቀጠቅጥና የምታቃዥ ከመኾኗም በላይ ሕክምና በወቅቱ ካልተወሰደ ገዳይ በሽታም ናት። ለዚህም ነው በማጨድ ተግባር ላይ የተሰማራው አርሶ አደር የወባ በሽታን የኃይለኛነት ባሕርይ ለራሱ ወስዶ ሐሳቡን በጎላ ኹኔታና በምስል ሊገልጽ የቻለው።

ቃል ግጥም 106፡- ከሴት ወንድ ይሻላል ብዬ ባገባው
ለቡን ቁርስ አይበቃም የዓመት አዝመራው።

(ከከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 03/07/2012)

ቃል ግጥሙን የተናገረችው ሴት በትዳር ጓደኛዋ ላይ በማስረጃ የተደገፈ ትችት ስትሰነዝር ወይም አስተያየት ስትሰጥ በእዝነ ኅሊናችን እናዳምጣታለን። በማስረጃ የተደገፈው አስተያየቷም የሚጀምረው በተፈጥሮዬ የእንስትነት ባሕርይ ካለኝ ሰብዓዊ ፍጡር ይልቅ በብዙ ጎን ከእኔ

[28] የሚበደሩት አርሶ አደሮች ሙሉ በሙሉ እንክርዳድ ባይሆንም ከዋናው ምርት የተለየ መናኛ (ጥራት የሌለው) እኽል ሲኾን፣ ገጣሚውም ለጉዳዩ አጽንኦት ለመስጠት ሲል ቃሉን ተጠቅሞበታል።

ከሴቷ ልዩነት ያለውን ወንድ ይጠቅመኛል ብዬ፣ አሳዳሪዬ እንዲኾነኝ ጋብቻ ፈጽሜ፣ ትዳር በመያዝ ዐብሬው በቤቱ ተቀምጬ ነበር በሚል ነው። ነገር ግን ጎበዝ፣ ጀግናና ብርቱ ነው ያልኩት ሰው በዓመት ውስጥ ያመረተው የእርሻው ውጤት ወይም ምርት እንኳንስ በየጊዜው እያዘጋጀሁ ለማቀርበው ምግብ ሊበቃ ይቅርና በቤታችን ቡና ተፈልቶ በሚጠጣበት ወቅት ለተጠሩት ሰዎች በቁርስነት የሚቀርብ መጠነኛ ምግብ ስለሚያንስ ሁሉንም ሰዎች አያዳርስም በማለት ማስረጃ አጣቅሳ በአንደበቷ ተናግራለች።

ቃል ግጥም 107፡- አዝመራውን ሁላ ዐረም እንዳይበላው
ወንዱም ኾነ ሴቱ ጠንክሮ ማረም ነው።
ቃለ መጠይቅ፣ ሱለይማን እብራሂም፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በእርሻ በተለይ በዐረም ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው ሁሉ ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት ከላይ የተቀነቀነው ቃል ግጥም ያስገነዝባል። በመኾኑም ብዙ ምርት ሲሰጥ የነበረው የእርሻ መሬት ከእኽል ጋር ዐብሮ በሚበቅል፣ እንደዚሁም አስፈላጊ ባለመኾኑ የተነሣ ተነቅሎ በሚጣለው በማንኛውም ዓይነት ቅጠልና ሣር ከተጠቃና ከተጎዳ አጥጋቢ የኾነ ምርት የሚያስገኝ ሊኾን አይችልም። ስለዚህ ጾታ ሳይለይ ዐረም ማረም የሚችል ሁሉም ሰብዓዊ ፍጡር ከሰብሉ ውስጥ ዐረሙን በርትቶ ማስወገድ እንዳለበት ቃል ግጥሙ ያስረዳል።

ቃል ግጥም 108፡- በርዬ በርታልኝ ትንፋሽህ ምንድን ነው
ምርቱ የእኔ ቢኾን ገለባው የአንተ ነው።
(ቃለ መጠይቅ፣ ይማም አብዱ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

አርሶ አደሩ ለኑሮው መሻሻል አስተዋፅኦ የሚያደርግለትን በሬውን ከማንኛውም ነገር በላይ ተንከባክቦ ይይዛል። ከዚህ በተጨማሪ በእርሻ ወቅትም ኾነ የእኽሉን ክምር በዐውድማ ላይ ዘርግፎ በሚያበራይበት ወይም በሚወቃበት ጊዜ እንዲተጋለት ያሞግሰዋል። በዚህ ቃል ግጥምም አቀንቃኙ አርሶ አደር “በርዬ” በማለት የበሬውን ዋና ስም ቅርጽ ለወጥ አድርጎ ለመጥራት በሚያገለግል አጠራር በሬው በሥራ መታተርና መጠንከር እንዳለበት “በርታልኝ” እያለ አወድሶታል። በሬው ከድካሙ የተነሣ በውስጡ ታምቆ የቆየውን አየር ሲያስወጣም ገጣሚው የአንድ ያልታወቀን ነገር ምንነት ለማወቅ ሲፈለግ ጥያቄ ማቅረቢያ ኾኖ በሚያገለግል መጠይቃዊ ሐረግ “ትንፋሽህ ምንድን ነው” በማለት ያናግረዋል - በበሬው በኩል ምላሽ ማግኘት ባይችልም። በመቀጠልም አርሶ አደሩም ኾነ በሬው የዐቅማቸውን ያኽል ሠርተው ተፈጥሯዊ በኾነ ሕግ የየድርሻቸውን እንደሚወስዱ ገጣሚው በዜማ ሲገልጽ እናዳምጠዋለን። ይሄውም የደረቀው ሰብል በበሬው እግር ከተሰባበረና ከደቀቀ በኋላ ምርቱ በንፋስ አማካይነት ከገለባው ይለያል። መጨረሻ ላይ አርሶ አደሩ ከገለባው የተለየውን ምርት በጎተራው አስገብቶ ለዓመት

የምግብ ፍጆታው ሲያውል፣ ገለባውን ደግሞ በገለባ ቤት ውስጥ ለበሬው አስቀምጦ በየጊዜው እየቆነጠረ ያቀርብለታል።

ቃል ግጥም 109፡- በሬ ሆዬ በሬ ሆዬ } ሁለት ጊዜ
ላብላህ ሥራ ውዬ
ክረምት በጋ ብዬ
ውሎዬን ደልድዬ
ሣሩንም ቆልዬ
ገለባ ከምሬ
ማደሪያ አሳምሬ።

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣22፣05/2012)

ቃል ግጥሙን የተናገረው አርሶ አደር ለበሬው ያለውን አክብሮትና ፍቅር ለመግለጽ "በሬ ሆይ" የሚለውን የውዳሴ ሐረግ ሲጠቀም ተስተውሏል። ከዚያም በሬውን ተጠቅሞ እኽልን በዐውድማ ላይ ሲወቃ ቶሎ ቶሎ እንዲኼድለትና እንዲዞርለት በል በል እያለ ሲገፋፋው በዓይነ ኅሊናችን እንመለከታለን። በመቀጠልም ለበሬው ያለውን የራሮት ስሜት በማሳየት የጉልበት እንቅስቃሴን በሚሻ ወይም በሚጠይቅ ተግባር ላይ ቀኑን ሙሉ በሥራ ተጠምጀ ብውል እንኳን እንዳይርብህና እንዳይጠማህ እንደምንም ብዬ እመግብሃለሁ ብሎታል። በተጨማሪም ከአራቱ ዓመታዊ ወቅቶች መካከል ዝናም በሚበዛበት በክረምትም ኾነ በበጋ ወራት ያሉትን ጊዜያት አመቻችቼ በመከፋፈል ለመኖህ የሚኾነውን እንደ ሰርዶ፣ ሙጃና ሰንበሌጥ፣ የመሳሰሉትን ሁሉ በአንድ ላይ ሰብስቤ እቆልልሃለሁ፤ ገለባውንም ከምሬ አስቀምጥልሃለሁ። ሌሊቱን የምታድርበት የማደሪያ ቤት ወይም በረት ውብ አድርጌም እሠራልሃለሁ በማለት ለበሬው ያለውን ሐዘኔታ ገልጿል።

ቃል ግጥም 110፡- ያላረሰ ሰነፍ ዕርፍ ያልነቀነቀ
የሰኔ ሚካኤል ሙዛቻው ደረቀ
በሐምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አማን ሁሴን 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሰነፍ በኾነው አርሶ አደር ደካማ ጎን ላይ በማተኮር ነቀፌታውን አቅርቧል። ይሄውም የግብርናን ሥራ በመጥላት ተቀምጦ የሚውል ሰው በወቅቱ የእርሻ መሬቱን ደግሞ ደጋግሞ አርሶ በማለስለስ ለዘር ማዘጋጀት አይችልም። እንደዚሁም በአንድ በኩል ከማረሻና ከሞፈር ጋር የሚዋደደውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሲያርስ የሚጨብጠውን እና የማረሻውን ጥልቀትና ኺደት የሚቆጣጠርበትን ዕርፍ የተባለውን የበሬ ዕቃ በትክክል ይዞ አይገለገልበትም። በዚህ የበሬ ዕቃም ሰጎጥ የሚባለውን እና በእርሻ መሬት ውስጥ ለማረስ

የሚያስቸግረውን ድንጋይ ወይም የዛፍ ሥር መንግሎ ለማውጣት አይችልም። በዚህ የተነሣ ለዓመት ቀለብ የሚሆን ምርት ስለማያገኝ ሠኔ ወር በገባ በዐሥራ ኹለተኛው ቀን ሊጥ ወይም ቡኮ የሚዘጋጅበትና የሚቀመጥበት ቡሖቃው ሳይቦካበት ይቀራል። ገጣሚው ሠኔ ዐሥራ ኹለትን ያነሣው ያለ ምክንያት አይደለም። ምክንያቱም ዕለቱ የቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚከበርበት ስለኾነ ሰነፉ አርሶ አደር የሚላስ የሚቀመስ ነገር ከቤቱ ያጣበትን ጊዜ በበዓሉ አማካይነት አድማጮች በቀላሉ እንዲያስታውሱት ለማድረግ ነው። በመጨረሻ ላይም በሐምሌ ወር የመጀመሪያ ቀን ዐቅም በሚያሳጣ ጽኑ ረኃብ ተጨባብጦ እንደወደቀ ገጣሚው በሚኮሰኩስ አቀራረብ ትችቱን ለመሰንዘር በቅቷል። ይህ ወር ደግሞ ከላይም ውሃ ከታችም ውሃ ስለኾነ ለምግብነት የሚኾን ነገር አይገኝበትም።

ቃል ግጥም 111፡- በሰኔ ካልዘሩ፣ በጥቅምት ካልለቀሙ
እኽል የት ይገኛል በድንበር ቢቆሙ
(ቃለ መጠይቅ፣ እንድሪስ አበራ፣ 21/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቀደም ሲል ከቀረበው ትንተና በተመሳሰለ መልኩ ድክመትን ወይም ስሕተትን ለማረም ሲባል የቀረበውን እና ቂም በቀል የሌለበትን ትችት አዘል ቃል ግጥም ዳግም ለማየት ተችሏል። በመኾኑም በአየር ንብረት መለዋወጥ የተነሣ ከተመደቡት ከአራቱ ዓመታዊ ወቅቶች መካከል አንዱ የክረምት ጊዜ ነው። የክረምቱ ጊዜ የሚጀምረው ደግሞ በሠኔ ወር ነው። በዚህ ወር ታታሪው አርሶ አደር የእርሻውን መሬት ደጋግሞ በማረስ ካለሰለሰ በኋላ ዘርን መዝራት የሚጀምርበት ወቅት ነው። ነገር ግን አንድ አርሶ አደር በዚህ ወር ታርሶ በለሰለሰው የእርሻ መሬት ላይ ተገቢውን እኽል በመዝራት እንዲበቅልና አጥጋቢ ምርትም እንዲሰጥ ካላደረገ ለከፋ ችግር እንደሚጋለጥ ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል። ከዚህ በተጨማሪ የጥቅምት ወር ከመሬት ብዙ ጥቅም የሚገኝበት፣ እኽልና ተክል ሁሉ ፍሬ የሚሰጥበት ስለኾነ ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ ወር መሬት የሚሰጠውን ጥቅም ተግቶ መሰብሰብ ካልቻለ፣ በእርሻና በእርሻ መካከል ባለ በማይታረሰውና በማይፈልሰው ድንበር ላይ ቆሞ ቢመለከት ከማዘን በስተቀር የእኽል ባለቤት ሊኾን እንደማይችል ከውቂያ ቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል።

ቃል ግጥም 112፡- እኔስ ለበሮቼ ምንድን ልግዛላቸው
ከተማ ገጠሩን ያጠገቡ ናቸው።
ችግርን በወንጭፍ ያባረሩ ናቸው።
(ቃለ መጠይቅ፣ ዓይናለም በጸና፣ 22/02/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

አርሶ አደሩ በሚያርስበትም ኾነ በሚወቃብት ጊዜ ከሕይወቱ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸውን በሬዎቹን እንደሚያወድስና ምስጋናም እንደሚያቀርብላቸው ቀደም ሲል ተገልጿል። በእነዚህ

ሦስቶ ስንኞችም ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉትን በሬዎቹን ከማወደስና ከማመስገንም አልፎ ምን እንደሚያደርግላቸው ጨንቆት "ምንድን ልግዛላቸው?" እያለ ጥያቄ ሲያቀርብ እንመለከተዋለን። በእርግጥ ለበሬዎቹ በገንዘብ ሊገበይላቸው ወይም ሊሸምትላቸው የሚችለው በቤት ውስጥ ከሌለ ታጭዶ የደረቀ ሣርና ገለባ፣ እንደዚሁም ጨው ነው። ምክንያቱም በተፈጥሮ ሕግጋት መሠረት የቀንድ ከብቶች ሣረ በል (Herbivorous) በመኾናቸው የተነሣ ነው። አርሶ አደሩ በሬዎቹን ማወደስ የቻለው እውነታን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ አመክንዮ ነው። ይሄውም በከተማም ኾነ ከከተማ ውጪ የሚኖረው ሕዝብ ሆዱ የሚሞላው በበሬዎች ታርሶና ተወቅቶ በሚገኘው የእኽል ምርት ነው በማለት እውነታውን ለመግለጽ ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ውስጣዊ ስሜትን ለማንጸባረቅ በሚያስችል የአነጋገር ስልት ከጠፍር ወይም ከገመድ የሚሠራውን እና ሰብልን ከወፍ ለመጠበቅ ወይም ለማባረር ለድንጋይ መወርወሪያነት የሚያገለግለውን ወንጭፍ በቃል ግጥሙ ውስጥ ተጠቅሟል። በዚህ መሠረት ወንጭፍ ከሰብል ላይ ወፍን ለማባረር እንደሚያገለግል ሁሉ ዕጦትን፣ ጠኔን፣ ረሃብን፣ ወዘተ. በበሬዎች ታርሶ በሚገኘው እኽል አማካይነት ማስወገድ እንደሚቻል አርሶ አደሩ አስረድቷል።

6.2. የሰርግ ቃል ግጥሞች

ሰርግ የጋብቻን በዓል ለመከወን የሚደረግ የአከባበር ሥነ ሥርዓት ነው። የአከባበር ሥርዓቱም ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደሌላው የመሸጋገሪያ ወቅት ሲኾን፣ እንደየሀገራቱ ባህል የደስታው ኹነት በሙዚቃ፣ በዳንስ፣ በምግብና በመጠጥ ሊከወን ይችላል (Salamone, 2004:230)። ቀደም ባለው ወቅት የጥናቱ አካላይ በኾኑት ወረዳዎች የሰርግ ሥርዓት ለኹለት ወይም ለሦስት ቀናት ነበር። በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት በአሁኑ ጊዜ በአንድ ቀን ብቻ በመከወን ላይ ይገኛል። ይህ የኾነውም ከማኅበረሰቡ የኢኮኖሚ ዐቅም ማነስ የተነሣ ነው። በዚያን ወቅትም ኾነ አሁን ሰርግ ከሌሎቹ የሕይወት ኹነቶች የበለጠ የተለያዩ ዝግጅቶችና ከዋኔዎች ይቀርቡበታል። ከእነዚህ መካከልም በዋናነት የምግብና የመጠጥ ዝግጅቶች፣ እንደዚሁም ዘፈን፣ ሆታ፣ ቀረርቶና ፉከራ ይጠቀሳሉ። በሰርጉ ዕለት ማታ በሙሽራውና በሙሽራዋ ወላጆች ቤት በጎረቤትና በቤተዘመዱ የሚከወኑትን የቃል ግጥም ዘፈኖችን በሚከተለው ኹኔታ ለመተንተን ተሞክሯል።

በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት በሰርጉ ዕለት ማታ በሙሽራውም ኾነ በሙሽራዋ ቤተሰቦች ቤት ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው ኾነው የግጥም ዘፈኖችን የሚያቀነቅኑ ሲኾን፣ የሚጠቀሟቸው ዜማዎችም "ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ"፣ "መላ መላ ነው ዛሬስ የጉድ ነው"፣ "አባይም ቢሞላ ቢሞላ፣ መሻገሪያው ሌላ"፣ ወዘተ. የሚሉት ይገኙበታል። በቅድሚያ

በወንዶች አማካይነት “ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ” በሚለው የዜማ ስልት የቀረበውን የቃል ግጥም ዘፈን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 113፡- ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ ሦስት ጊዜ
አለው መላ መላ፡፡
የኔው ልጅ ጫቀታ ምንድን ነው ቀለቡ
እንደ ፈረስ ጭራ ቀጪን ናት ወገቡ፡፡

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

በአዝማቹ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ በኹለተኛ መደብ የተጠቀሰችው ሴት ዘይኛና ብልኀተኛ እንደኾነች ተገልጿል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሕይወት ገጠመኜ ስሰማ የነበረውና የሴትን ብልኀነት የሚያንጸባርቀው የቃል ግጥም ደግሞ “እቴ መላ ምቺ መላ ካንቺ ይገኛል፣ እኔማ ወንድ ነኝ ይደናገረኛል” የሚለው ተጠቃሽ ነው፡፡ ኹለቱም ቃል ግጥሞች ወንድ ልጅ አጣብቂኝ የኾነ ችግር ሲያጋጥመው ግራ የሚጋባ፣ የተረጋጋ አስተውሎትና ነገሮችን ፈጠን ብሎ የመረዳት ችሎታ የሚያጥረው ስለሚኾን መውጫ ቀዳዳ እንደሚያጣ፣ ሴቷ ግን ተመሳሳይ የኾነ ችግር ቢደርስባት የማስተዋል ችሎታ ስላላት ሳንካውን በምክንያትና በሰበብ ማለፍ የምትችል መኾኑን ያስገነዝቡናል፡፡ ዘፈን አውራጁ አዝማቹን በተደጋጋሚ አቀንቅኖ እንዳበቃ ቀጣዮቹን ስንኞች ማዜም ይጀምራል፡፡ በዚህን ወቅት ከዐጃቢዎቹ (ዘፈኑን ከሚያደምቁት ሰዎች) መካከል ግማሾቹ ሲያጨበጭቡ ሌሎቹ ደግሞ “እነ እከ፣ እነ እከ፣ እነ እከ፣ …” በማለት እስክስታ ይወርዳሉ፡፡

ከአዝማቹ ቀጥሎ የቀረቡት ስንኞች ደግሞ ውጫዊ ውበትን ያንጸባርቃሉ፡፡ በእርግጥ ውጫዊ ውበት የአንድን ሰው የመልክ፣ የድምፅ፣ የሰውነት ቅርጽ፣ ወዘተ. ማማር በአጠቃላይ ሌሎች ሰዎችን የመሳብ ኃይል ያመለክታል፡፡ በስንኞቹ ውስጥ ጎልቶ እንዲወጣ የተፈለገው በወግዲ ወረዳ ሥር ባለው የጫቀታ አካባቢ ተወልዶ ስላደገው ወጣት የወገብ ቅርጽ ነው፡፡ ይሄውም ለወጣቱ በየጊዜው እየተዘጋጀ የሚቀርብለት ምግብና መጠጥ ምን እንደኾነ ባይታወቅም ገጣሚው ግን የወጣቱን ወገብ ቀጭን መኾን አጉልቶ ለማሳየት ከፈረስ ጭራ ጋር ሊያነጻጽረው ችሏል፡፡ በመኾኑም ከጋማ ከብት ወገን የኾነው ፈረስ ጭራው ውፍረት የሌለውና የሣሣ እንደኾነ ሁሉ ወጣቱም ወገበ ቀጭን መኾኑን ገጣሚው ያመላክታል፡፡ ምንም እንኳን በሰብዓዊ ፍጡር አምሳያ የተፈጠረ ሰው ከፈረስ ጭራ ጋር የሚስተካከል ወገብ ስለሌለው ንጽጽሩ ግነት ቢስተዋልበትም ወጣቱ ግን ሸንቃጣ፣ አቋቋመ መልካምና ሸበላ መኾኑን በዓይነ ኅሊናችን ለማየት እንችላለን፡፡

ቃል ግጥም 114፡- መላ መላ ነው ሦስት ጊዜ
ዛሬስ የጉድ ነው፡፡
እኔ ከመካፍታ ፈሪ ቢገኝብኝ
እኔ ከጫቀታ ፈሪ ቢገኝብኝ
እኔ ከወግዲ ፈሪ ቢገኝብኝ
ከእምዬ ለሚ ላይ ፈሪ ቢገኝብኝ
ከመኪናው መንገድ ታክሲ ይነዳብኝ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ እንዳልካቸው ግዛው፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የግጥሙ አዝማች ኹለተኛው ስንኝ ያልተለመደ፣ እንግዳና አስገራሚ ነገር የተከሠተ መኾኑን በሚያመላክት ኹናቴ ነው የቀረበው፡፡ ይሄውም “ጉድ ኾነ”፤ “ጉድ ታየ” እንደሚባለው ወሬውን ሊሰሙት፣ ኹናቴውን ሊያዩት የማይገባ ነገር መፈጠሩን ያሳያል፡፡ “ዛሬስ የጉድ ነው፡፡” የሚለውን ስንኝ ከላይ በቀረበው ማብራሪያ መሠረት ብንረዳውም በሌላ እይታ ደግሞ ጉዳዩ ጥሩ የኾነ ነገርንም ለማዳነቅ እንደሚያገለግል መገንዘብ የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ከአዝማቹ ቀጥሎ ያሉት ስንኞች ደግሞ በወግዲ ወረዳ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች ያሉ ወጣቶች ፍርሃት የማይስተዋልባቸው፣ በጀግንነታቸው የተወደሱባቸው መኾናቸውን ያመላክታሉ፡፡ በመኾኑም ጥናቱ በተካኼደባቸው አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ ድፍረት የሌለውን እና ጀግንነትን ያልተላበሰውን ሰው በቃል ግጥም ብቻ ሳይኾን በአባባሎች ያወግዘዋል፡፡ ከሚያወግዝባቸው አባባሎች መካከልም “ፈሪ ውሃ ውስጥ ኾኖ ያልበዋል፡፡”፣ “ለፈሪ ሜዳን አይነሡም፡፡”፣ “ከፈሪም ፈሪ ይበልጣል፣ እኒያ ሲመጡ ሸሽቶ ያመልጣል፡፡” የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህን አባባሎች በጆሮው እየሰማ ተኮትኩቶ ያደገ ወጣት በማንኛውም ነገር ቢኾን የፍርሃት ስሜት አይስተዋልበትም፡፡ ለዚህም ነው ገጣሚው ማካፍታ፣ ጫቀታ፣ ወግዲና ለሚ ካሉ አካባቢዎች ፈሪ የኾነ ሰው ተፈጥሮ ወይም ተወልዶ ቢገኝ በላዬ ላይ የታክሲ ሾፌር መኪናውን ያሽከርክርብኝ በማለት መሐላ ሲፈጽም የምንመለከተው፡፡ መሐላው ደግሞ ገጣሚው የተናገረው ነገር እውነት መኾኑን ለማረጋገጥ፣ ከዚያም ዐልፎ ለማጽደቅና ለማጽናት፣ እንደዚሁም ለማሳመን ሲባል የገባ መኾኑን ማጤን ይገባል፡፡ ጀግንነትን በደምሳሳው ስንመለከተው ደግሞ ኃይለኛ፣ ጎበዝ፣ ብርቱ፣ አሸናፊ፣ ሞት አይፈሬ፣ ለሀገር፣ ለወገን መሥዋዕትነትን ከፍሎ ጥሩ ተግባር የፈጸመ፣ ወኔን እና ድፍረትን በሚጠይቅ ኹኔታ ላይ ሁሉ ጀብዱ የሠራ፣ እንደዚሁም ጥንካሬን በሚጠይቅ ሥራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ የሚለውን ያስገነዝበናል፡፡ ስለዚህ ማኅበረሰቡ ፈሪን ሲያወግዝ፣ ጀግናን ደግሞ ግርማ ሞገስ ሲያጎናጽፈው እንመለከታለን፡፡

ቃል ግጥም 115፡- ዐባይም ቢሞላ ቢሞላ ሦስት ጊዜ+
መሻገሪያው ሌላ፡፡

ዐባይም ሞላልሽ ሞላልሽ
እንዳልሺው ኾነልሽ፡፡
እንዳልሺው ኾነልሽ እንደተመኘሺው
የአንዱን ቀን ጨዋታ እንዴት አገኘሺው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ዘበነ አሰፋ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ ያሉት አራቱ የአዝማች ስንኞች ትኩረታቸውን ያደረጉት በአባይ ወንዝ ላይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አባይ ሰከላ ሚካኤል ከሚባል ቦታ ካለ ተራራ ሥር ፈልቆ፣ በጣና ላይ በማለፍ ምሥራቅ ጎጃምን እና ደቡብ ወሎን የሚያደናብር በጣም ትልቅ ወንዝ ነው፡፡ ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገባቸውን የቦረናን እና የወግዲን ወረዳዎች ከምሥራቅ ጎጃም ጋር እያዋሰነ፣ ከዚያም ወደካርቱም፣ በመጨረሻም ወደምስር (የአሁኗ ግብጽ) ለመግባት የረዥም ርቀት ጉዞውን ይያያዘዋል፡፡ በክረምቱ ወራት የወንዙ ሙላት በጣም ከፍተኛ በመኾኑ የተለያዩ የወንዝ ላይ መጓጓዣ ዘዴዎች ከሌሉ በስተቀር ማንም አይደፍረውም፡፡ ድምፁውያን የአባይን ስሙን እያወደሱ፣ በአወንታም ኾነ በአሉታ ግብሩን እያወሱ አዚመውለታል፡፡ ለጉዳዬ ማጽኛ ስለአባይ ይህንን ያኽል በአጭሩ ካብራራሁ ወደቃል ግጥሙ ርእሰ ጉዳይ ልሸጋገር፡፡

በቃል ግጥሙ ውስጥ ባለው የመጀመሪያው አዝማች እንደተንጸባረቀው አባይ ከአፍ አስከ ገደፉ ድረስ ጢም ብሎ ከሞላ በቀላሉ ለመሻገር ያዳግታል፡፡ ስለዚህ ቃል ግጥሙ በፈለቀባቸው አካባቢዎች ያሉ የጎብረተሰብ ክፍሎች ወንዙን ተሻግረው ፍቅርንም ለመጋራት ኾነ የናፈቁ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ይችገራሉ፡፡ ታዲያ የአዝማቹ አውራጅ “መሻገሪያው ሌላ” በማለት በመረማመጃ ድልድይ፣ በርብራብ፣ በታንኳ፣ ከተቻለም በጀልባ ወንዙን አቋርጦ በመኼድ ፍቅርን መጋራትም ኾነ የናፈቁ ዘመዶችን መጠየቅ እንደሚቻል ገልጿል፡፡ ቀጥሎ ያሉት ስንኞች ደግሞ የአባይን መሙላት የምትፈልግ እንስት መኖሯን ጠቁመዋል፡፡ በመኾኑም እንደፈለግሺው ተሳካልሽ፣ ተሟላልሽ በማለት አቀንቃኙ የሴትዮዋን የልብ መድረስ አጉልቶ ለማሳየት ችሏል፡፡ ከዚያም ኹለቱ ተቃራኒ ጸታዎች ካሳለፏቸው ቀናት መካከል በአንደኛው የነበረው ጨዋታ እንዴት እንደነበር ለማወቅ ወይም ለመረዳት ወንዱ ለሴቷ ጥያቄ አቅርቦላታል፡፡ ምናልባትም ጨዋታው በተቃራኒ ጸታዎቹ መካከል የነበረ ንግግር፣ ውይይት፣ ድሪያ (ለፍቅር የሚፈላለጉ ሴትና ወንድ የሚያደርጉት ልፊያ)፣ ቀልድ፣ የሚያስቅና የሚያዝናና ወሬ፣ ዘፈን፣ ዳንስ፣ ውዝዋዜ ሊኾን ይችላል፡፡ ለእኔ ግን እንደልብ የማይገኝ፣ በፊት የሌለ ወይንም ያልነበረ ነገር፣ ያም በኹለቱ ጸታዎች መካከል ያለና በወሲብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የመዋደድ ስሜት ሊኾን ይችላል፡፡

ቃል ግጥም 116፡- ዐባይም ቢሞላ ቢሞላ አለው መላ መላ፡፡ | ሦስት ጊዜ

አረጆች ላሚቷ ቀንዲ መነመነ
ከሥር የሚተካ ጊደር በነበረ፡፡

(ቃለ መመጠይቅ፣ ሱለይማን እብራ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቀደም ሲል ከቀረበው ማብራሪያ ጋር በተመሳሰለ መልኩ አባይ ከአፍ እስከ ገደፉ ድረስ ጢም ብሎ ሞልቶ በቀላሉ ለመሻገር የሚያዳግት ከኾነ ብልሃት ወይም ዘዴ አለው በማለት አርሶ አደሩ የቃል ግጥሙን አዝማች ተናግሯል፡፡ በመቀጠልም ሲሰሟቸው ደስ የሚያሰኙ፣ ይዘታቸው ውበትና ጥልቅ ምስጢር እንዲኖራቸው ተደርገው በቅኔ መልክ የቀረቡ መንቶ ስንኞች ቀርበዋል፡፡ በመኾኑም ላይ ላዩን የሚታየው ወይም ግልጽ ኾኖ ፊት ለፊት የተላለፈው ሐሳብ ባረጀችዋ ላም ምትክ ለመጠቃት የደረሰች ጊደር እንደምታስፈልግ ገጣሚው አመላክቷል፡፡ ተሸፍኖ በቀረበው ውስጠ ምስጢር ደግሞ ባረጀችዋ ላም የተመሰለችው አሮጊት ሴት በፍትወተ ሥጋዊ ሥራ ወቅት እርካታ የማይገኝባት መኾኑን፣ ምናልባትም የትዳር ጓደኛዋ በኾነ ግለሰብ አንደበት ለመዜም ተችሏል፡፡ “ሲያረጁ አይበጁ” የሚለው ብሂል ውስጠ ምስጢሩን ያጸናዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ባረጀችዋ ሴት ፋንታም በጊደር የተመሰለች፣ ኮረዳ፣ ለተቃራኒ ጾታ ተራክቦ የደረሰችና የተመቸች ልጃገረድ አስፈላጊ መኾኗን ከዘፈን ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቃል ግጥም 117፡- መላ መላ ነው ሦስት ጊዜ
ዛሬስ የጉድ ነው፡፡
አንቺ እናኒ እናኒ የቁኒ ቀዳዳ የቅቤ ቅሊቱ
ከባል ከውሽማ የትኛው ይመ·ቱ፡፡
ለማገልገልማ ባል ያገለግላል
ዐጥር ዘሎ ሲኼድ ውሽማም ደስ ይላል፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አያሌው ሰይዱ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን የተናገረው ግለሰብ በአጠገቡ ያለችን ሴት “አንቺ እናኒ” በማለት በተደጋጋሚ እያቆላመጠ ሲጠራት ይስተዋላል፡፡ ዋናውን የመጠሪያ ስሟን ለመለወጥ የቻለውም የመውደድ፣ የመለማመጥ፣ የማባበል ስሜቱን ለማንጸባረቅ ሲኾን፣ ድግግሞሹንም የተጠቀመው ሴትዮዋ ለእነዚህ ውስጣዊ ስሜቶቹ ትኩረት ሰጥታ እንዲትረዳው ለማድረግ ይመስላል፡፡ በመቀጠልም ሴቶች አደስ የተባለውን ተክል ቅጠሉን አድርቀው ከወቀጡ በኋላ ከቅቤ ጋር ለውሰው ጸጉራቸውን ለመቀባት እንደሚያዘጋጁ፣ ላዘጋጁት መዋቢያም በማስቀመጫነት አዘውትረው የሚጠቀሙባት ቅል እንዳለች፣ ከዚያች ጋር በማመሳሰልም “የቁኒ ቀዳዳ የቅቤ ቅሊቱ” በማለት የሴትዮዋን ውበት አጉልቶ ለማሳየት እንደቻለ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚያም ገጣሚው ከትዳር ጓደኛዋና ከውሽማዋ የትኛው ቢሞት እንደምትመርጥ ለሴትዮዋ ጥያቄ አቅርቦላታል፡፡

እንደሚታወቀው የትዳር ጓደኛ ሲባል ባለቤት፣ የቤት አሳዳሪ፣ ወልዶም ከኾነ የልጆች አባት ነው። ውሽማ ደግሞ በጋብቻ ያልታሠረ፣ በድብቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽም ፍቅረኛ ማለት ነው። ሲመቸው ፍቅሩን ይቀጥላል፤ ባይመቸው ደግሞ ግንኙነቱን ያቋርጣል። ሰውዬው ላቀረበላት ጥያቄ የሴትዮዋ መልስ ግን የትዳር ጓደኛዋም ኾነ ውሽማዋ ሕይወታቸው እንዲያልፍ የማትፈልግ መኾኗን ነው። ምክንያቱም ለጎጇቸው አስፈላጊ የኾኑትን ነገሮች በማሟላቱ ረገድ ባሏ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ተናግራለች። ውሽማ ደግሞ ባል በቤት በሌለበት ወቅት በድብቅ ከእሷ ጋር ያለውን ፍቅር የሚጋራ ሲኾን ባል ሲደርስበት ዐጥርን እመር ብሎ ዘሎ ሲኼድ በደስታ እንደምትፈነድቅ ገልጻለች። እዚህ ላይ የወንዱም ጥያቄ ኾነ የሴትዮዋ መልስ በቅብብሎሽ ሳይኾን በግጥሙ ተናጋሪ አማካይነት የቀረበ መኾኑን ልብ ይሏል።

ቃል ግጥም 118፡- መላ መላ ነው } ሦስት ጊዜ
ዛሬስ የጉድ ነው
አቦል ቀሃ ጀባ ዱበርቲ መጀን
በዓይናችን ያየነው በእጃችን ይኹን።

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሀገር ባህል ልማድ መሠረት በመጀመሪያው ዙር ላይ የተፈላው ቡና ተቀድቶ ከመጠጣቱ በፊት ለዱበርቲዎችም ኾነ ለሌሎች ታዳሚዎች "አቦል ጀባ፤ ቀሃ ጀባ" ይባላል። ትርጉሙም "እነሆ! ይሄው አቦል ቡና ቀርቧልና እባክዎን ይመርቁ፤ ይጋበዙ" ለማለት ነው። ታዳሚዎቹም ተስማምተው ቅድሚያ የሰጡትና የተከበረው ሰው "ዱበርቲ መጀን ..." ብሎ ምርቃቱን ይጀምራል። ዱበርቲዎች ደግሞ ሴቶች ሲኾኑ፣ ይህንን ማዕረግ የሚያገኙት በማኅበረሰቡ ውስጥ ተሰሚነት ኖሯቸው፣ በዕድሜ የገፉና መከበርን የተጎናጸፉ በመኾናቸው የተነሣ ነው። ምክንያቱም በማኅበረረሰቡ ዘንድ ፈጣሪ ከእኛ በላይ ትልቅ አድርጓቸዋል ስለሚባል ጸሎታቸውም ተሰሚነት አለው ተብሎ ይታመናልና ነው (ሰይድ፣ 2002፡38-39)። ለዚህም ነው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ለእሱም ኾነ ዐብረውት ላሉት ጓደኞቹ በዓይነ ሥጋችን የተመለከትነውን በእጃችን እናድርገው በማለት በዱበርቲዎቹ እየተመጀነ ፈጣሪውን የሚማለደው። እዚህ ላይ "በዓይናችን ያየነው በእጃችን ይኹን" የሚለውን አባባል በተለያየ መንገድ ዘርዝሮ ምስጢሩን ለመረዳት የአንድምታ ትርጉም ያስፈልጋል ብዬ አስባለሁ። በዚህ መሠረት በግልጽ ያልተባለውን ጉዳይ ለማወቅ አንድም ቃል ግጥሙ በሰርግ ዐውድ ላይ የቀረበ በመኾኑ የቆነጆች፣ ያማረች፣ የተዋበች ሴት በዓይነ ሥጋቸው እዚያው አይተው ፈጣሪያቸው እሷን የእነሱ እንዲያደርግላቸው በማሰብ፣ አንድም በሰዎች ዘንድ ያዩትን

ሀብት፣ ጌትነትና አዱኛ አምላክ ለእነሱም ሰጥቷቸው ባለጸጋ እንዲኾኑ በመፈለግ እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሰርግ ዕለት ማታ በሙሽራውና በሙሽራዋ ወላጆች ቤት በጎረቤትና በቤተዘመዱ የሚከወኑት የቃል ግጥም ዘፈኖች በወንዶች ብቻ የሚቀነቀኑ አይደሉም። ሴቶቹም ቢኾኑ በፊናቸው የዘፈኑ አውራጅ ስታዜም፣ ሌሎቹ ደግሞ አዝማቹን ተቀብለው እንደጨረሱ እስክታ ይወርዳሉ። ለአብነትም በ03/07/2012 ዓ.ም ከከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ተሰብስበው የተገኙትን እና ከ119 — 122 ያሉትን ቃል ግጥሞች ቀጥሎ እንመለከታለን።

ቃል ግጥም 119፡- አባይም ቢሞላ ቢሞላ መሻገሪያው ሌላ። ሦስት ጊዜ
አዳል[29] ለወደደው ይገዛል ኮፍያ
ማፍቀርም ያገር ልጅ ማግባትም እኩያ።

በቃል ግጥሙ ውስጥ አዳል ተብሎ የተጠቀሰው በአሁኑ ወቅት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታል። በመኾኑም ከፊሉን ጠርቶ ሙሉውን ገጽታ በሚያሳይ የዘይቤ ዓይነት አንድ የአፋር ክልል ተወላጅ ለፈቀደው፣ ላመነውና ለፈለገው ሰው ለዝናብና ለፀሓይ መከላከያ፣ እንዲሁም ለጌጥ በራስ ላይ የሚደረግ ኮፊያ ሊገዛለት ይችላል በማለት ገጣሚዋ ተናግራለች። ስለዚህ ከወሲባዊ ፍላጎት ጋር በተያያዘ ኹኔታ የሚወዱትም ወይም የሚያፈቅሩትም ሰው የአንድ ሀገር ወይም የአንድ አካባቢ ሰው ቢኾን እንደሚሻል ገልጻለች። ይህንንም ያለችው ያለ ምክንያት አይደለም። ምክንያቱም እሱ በእሷ ላይ ተገቢ ያልሆነ ነገር ቢፈጽምባት፣ እሷም በፊናዋ በእሱ ላይ ብትፈጽምበት በዘመድ ወይም በጓደኛ በመወቃቀስ በደል ፈጻሚው ሊመከር ይችላልና ነው። ባልና ሚስት ኾኖ ለመኖርም አቻና ተመጣጣኝ መኾን እንደሚያስፈልግ አቀንቃኟ አመላክታለች። አቻነት ደግሞ በተለያዩ መልኮች ማለትም በዕድሜ፣ በማዕረግ፣ በሥራ፣ በሀብት፣ በዕወቀት፣ በመልክ፣ በትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ. ሊገለጽ ይችላል። ስለዚህ የፍቅሩ ኹናቴ አቻነት ኖሮት እንደ ጥርስ የተጋጠመ ወይም የተስካከለ ካልኾነ ነገሩ "አላቻ ጋብቻ" ይኾናል ማለት ነው።

ቃልግጥም 120፡- አባይም ቢሞላ ቢሞላ አለው መላ መላ። ሦስት ጊዜ

[29] በአሰብና በትግሬ መካከል ባለው በረሓ የሚኖር ሕዝብ ማለት ሲኾን፣ ብርቱ የሚለውንም ትርጉም ያሳያል (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣86)።

ድንገት ተገናኝተን አጋጣሚ ቦታ
በፍቅርህ ተረታሁ ጧትም ኾነ ማታ።

ግጥሙን የተናገረችዋ ሴት ያፈቀረቺውን ወንድ በአንድ በኾነ ሥፍራ ላይ ባልታሰበ ጊዜ በድንገት በአካል ተገናኝተን ከተነጋገርን በኋላ ተዋውቀን ነበር ትላለች። በእርግጥ ድንገት የተከሠተ ግንኙነት ለጥሩ ወይም ለመጥፎ ነገር ቢኾንም በዚህ ቃል ግጥም ዐውድ ግን የተቃራኒ ጾታዎች ፍቅር የተፀነሰበት ስለኾነ ግንኙነቱን እንደ መልካም አጋጣሚ አድርገን ልንቆጥረው እንችላለን። ከዚያም "ከፍተኛ በኾነ ኹኔታ አንተን የመውደድ ስሜት ውስጥ ተስቤ ድል ኾንኩኝ" በማለትም ሴትዮዋ በአእምሮዋ ውስጥ ያለውን ኹኔታ አንጸባርቃለች። በመጨረሻም በኹለቱ ተቃራኒ ጾታዎች መካከል በወሲብ ፍላጎት ላይ በተጠነሰሰው የመዋደድ ስሜት ስለተሸነፈች ከፀሓይ መውጫ ካለው ጊዜ ጀምሮ ጀንበር እስከምትጠልቅበት ወቅት ድረስ በጽኑ መቸገሯን ገልጻለች።

ቃል ግጥም 121፡- መላ መላ ነው
ዛሬስ የጉድ ነው } ሦስት ጊዜ
ከላላ ሲዘልቁ ደገር ጉሙ ታዬ
ሰው እንዴት ይሞታል ድንገት በተያዬ።

በከለላ ወረዳ በቱሪዝም መስሕብነት ከሚጠቀሱት ቦታዎች መካከል አንዱ በሼህ ሸረፈዲን ኢብራሂም በ1860 ዓ.ም የተመሠረተው የደገር ጌታው ሼህዬ መስጂድ እንደኾነ በምዕራፍ ኹለት ላይ ተገልጿል። የከለላ ከተማና የደገር የመሬት አቀማመጥ ላይና ታች ነው። በመኾኑም የከለላ ከተማ ከፍታማ ቦታ ላይ ሲኾን፣ ደገር ደግሞ ዝቅተኛ ስፍራ ላይ ይገኛል። ለዚህም ነው ከለላ ከተማ ላይ ብቅ ሲሉ አብዛኛውን ጊዜ በክረምት ወራት የሚከሠተውና ምድርን የሚሸፍነው፣ እንደዚሁም ከምድር ወደሰማይ እየተነነ የሚወጣው ንድፍ መሳይ ነጭ ጉም ደገር ላይ ታየ በማለት አቀንቃኟ ያዜመቺው። ምናልባትም እሷ ከለላ ከተማ፣ በንድፍ መሳይ ነጭ ደመና የተመሰለው ተፈቃሪ ደግሞ ደገር በተባለው አካባቢ የሚኖሩ ይመስላል። አቀንቃኟ ከዚህ ሰው ጋር ከተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች መካከል (በሰርግ፣ በገበያ፣ በለቅሶ ...) በአንዱ ድንገት ፊት ለፊት በአካል ተገናኝታ እንደተዋወቀች፣ በፍቅርም እንደወደቀች፣ ከዚያም ኃይሏ በመዳከሙ የተነሣ ዐቅም እንዳጣች፣ በመጨረሻም ነፍሷ ከሥጋዋ እንደተለየች በቃል ግጥሙ ገልጻለች። በተጨማሪም እንዴት ማሰብና ማመዛዘን የሚችል ሰብዓዊ ፍጡር ባልታሰበ ወቅት በተከሠተ መተያየትና በፍቅር በመያዝ ሥጋዬ ከነፍሴ ይለያል በማለት ራሷን ወቅሳለች።

ቃል ግጥም 122፡- አባይም ቢሞላ ቢሞላ ሦስት ጊዜ
መሻገሪያው ሌላ፡፡
የሰንዶ ባሕርዛፍ ጥላው የሚያሳዝን
የሚተካህ አጣሁ ብመዝን ባስመዝን፡፡

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ፍሬው ከአውስትራሊያ እንዲመጣ ተደርጎ ኢትዮጵያ ውስጥ የለማው ባሕርዛፍ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለአገልግሎት የሚደርስ የትላልቅ ዛፎች ዓይነት መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ከከለላ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ ሰንዶ በተባለው አካባቢ ባሉ ነዋሪዎች ተተክሎ ትልቅ የኾነው ባሕርዛፍም በግንዱ ዙሪያ እስከ አናቱ ድረስ ባሉት ቅርንጫፎቹ ጥላው ከፀሓይና ከዝናብ ለመከላከል የሚያስችል በመኾኑ ለሰውም ኾነ ለእንስሳት ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንጻር የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የመሳሳት ስሜት አድሮባት ራሮቷን ገልጻለች፡፡ ይህቺው አቀንቃኝ በዚህ ዓይነቱ ረጅም ባሕርዛፍ በተመሰለውና ተክለ ሰውነቱም እንደ ዛፉ መለል ብሎ በወጣው ሰው ፍቅር ወድቃለች፡፡ ከጊዜ በኋላም ከፍቅር ጓደኛዋ የተለያየች በመኾኑ በተለያዩ አቅጣጫዎች ብመዝን ባስመዝን አንተ ምትክ የማይገኝልህ በመኾንህ የተመኘሁትን ሳላገኝ ቀረሁ በማለት አጠቃላይ ግምገማዋን አንጸባርቃለች፡፡

6.3. የሙሾ ግጥሞች

ሙሾ የለቅሶ ዜማን ማውረድ፣ ማንሳራጋር፣ የሞቱትን ሰዎች ስም በማንሣት “ዋይ ዋይ” እያሉ ግጥምን በመግጠም አልቅሶ ማስለቀስ ማለት እንደኾነ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው መዝገበ ቃላት (1993፡68) ሙሾ ሰው በሞተ ጊዜ በአውራጅና በተቀባይ አማካይነት በግጥምና በዜማ እየታጀበ የሚካኼድ ለቅሶ ሲኾን፣ ሙሾ አውራጅ ደግሞ አስለቃሽ፣ የለቅሶ ግጥምን በዜማ እያሰማ የሚያስለቅስ ሰው ማለት እንደኾነ ተገልጿል፡፡ ሙሾ በማውረድ የሚያስለቅሰው ሰው ብዙውን ጊዜ ሴት እንደኾነች ቀደም ሲል የተጠቀሰ ስለኾነ ማስታወስ ይገባል፡፡ በተካኼደው ቃለ መጠይቅ አቶ መኮንን ጌታሁን (ቃለ መጠይቅ፣ 25/06/2013፣ ቦረና ወረዳ) እንዳብራሩልኝ ከኾነ የሙሾ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ወቅት ሚቹ በሕይወት ዘመኑ በነበረበት ጊዜ ጀግንነቱ፣ ደግነቱ፣ ማብላት ማጠጣቱ፣ የሌሎች መከራና ደስታም ተካፋይ ከነበረ ውለታው፣ በጥሩም ኾነ በመጥፎ ሥራው ነፍሱ በፈጣረ ዘንድ ለፍርድ መቅረቧ፣ ድኻም እንደኾነ እንደከፋው መሞቱ፣ በጠቅላላው ሙያው በሙሾ (በወየሁ ባይ) እየተደረደረ፣ ደረት እየተደቃ ዘመድ የኾነ ሁሉ በእንባ እንዲታጠብ ይደረጋል፡፡ የሚችን የሙሾ ሥርዓት ሊያበላልጡ የሚችሉ ነገሮች አሉ፡፡ ሹምና ባለጸጋ ሲሞት አንድም ሳይጓደል የሙሾ ሥርዓቱ ይፈጸምለታል፡፡ ድኻ ከኾነ ግን ምንም እንኳን ክርስቲያን ቢኾንም እንበለ ሙሾ በኾነ መልኩ በለቅሶ ሥርኣት ብቻ እንደ ነገሩ ኾኖ ወደዐፈር የሚገባበት አጋጣሚ እንደሚኖር

አቶ መኮንን ገልጸውልኛል። በዚህ መነሻነት በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት ቃላዊ ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 123፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘህ?
አያ ጎበዝ ብላሽ እንዲሁ በለለ
ዘመድ ጥሎት መጣ ሥራው ተከተለ።

(ቃለ መጠይቅ፣ መሐመድ እንድሬ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የሙሾ ቃል ግጥሞች ከሚቀርቡባቸው መካከል አንደኛው "ዋ! ዋ! ምን አገኘህ?" የሚለው ነው። ይህም ለክዋኔው እንደመክፈቻ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። በመኾኑም ዋ! ዋ! የሚሉት የሐዘን፣ የትካዜ መግለጫ ኾነው የሚያገለግሉ ቃላት ሲኾኑ፣ ሙሾ አውራጁም በስለምናዊ መጠይቅ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት "ምን አገኘህ?" በማለት ምን ነክቶትና ምን አጋጥሞት እንደሞተ ሚቹን በመንፈስ ይጠይቃል። ከሚቹ በኩል ግን ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም። ከዚያም "አይያ"፣ "አይዋ" በሚባሉትና ታናሽ ታላቅ ወንድሙን ወይም ዘመዱን ለመጥራት በሚገለገልበት የአክብሮት ቃል "አያ" እያለ አቆላምጦታል። መልከኛ፣ ጉልበታም፣ ጀግና፣ ኃይለኛ፣ ብርቱ፣ ጠንካራ፣ ታታሪ፣ ትጉህ፣ በአንድ ሙያ ወይም በሌሎች የዕውቀት ዘርፎች ... ጥሩ ችሎታ ያለው ሰው መሞቱንም በእንጉርጉሮው ይገልጻል። ይህ ሁሉ ሙያው መና ኾኖ መቅረቱንም "እንዲሁ በለለ" እያለ የሚቹን ቤተዘመዶች ያስለቅሳል።

በመቀጠልም ሚቹ በሕይወት ዘመኑ በነበረበት ወቅት የፈጸማቸው በጎም ኾኑ መጥፎ ሥራዎች ከሞተ በኋላም ወደመቃብር ተከትለውት እንደሚኼዱ ሙሾ ደርዳሪው በቃል ግጥሙ ገልጿል። ይህንኑ ሐቅ የሚያረጋግጠው በሚያዝያ 04/2014 ዓ.ም በነበረው የረመዳን ጾም ተሀራዊይ ከመሰገዱ በፊት በነበረው ሃይማኖታዊ አስተምህሮት ሼህ አህመድ የተባሉት ዒማም የተናገሩት ነው። እሳቸውም "ሰው ሞቶ ወደመቃብር ሲኼድ ሦስት ነገሮች ይከተሉታል። አንደኛው ቀባሪና ዘመዶቹ፣ ኹለተኛው ሀብቱ፣ ሦስተኛው ሥራው ናቸው። ከእነዚህ ከሦስቱ ነገሮች መካከል ቀባሪና ዘመዶቹ፣ እንደዚሁም ሀብቱ በምድር ላይ ሲቀሩ ሥራው ግን አብሮ ከሥጋው ጋር ይቀበራል" ብለዋል፡፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ Green (1997:732) የሕይወት ሽግግሩ ቀጣይነት ያለው መኾኑን "Some may occur repeatedly transition from a profane to the holy one as a specialist of the sacred." በማለት አስረድቷል። በዚህ መሠረት በትውልድ የአባት ወይም የእናት ወገን የኾነ ተወላጅና ሌላውም ሰው ሁሉ የሚቹን አስከሬን ዐፈር ካለበሰ በኋላ ትቶት ወደቤት ሲመለስ እሱ ግን በፈጸመው መልካም ሥራ እስከ ዕለተ ምጽኣት ድረስ ወደገነት ወይም ወደሰማያዊ ቦታ ገብቶ እንደሚቆይ የሙሾ ቃል ግጥሙ ያመላክታል። "ቀብር ቀብር አሉ ቀበር ምናለበት፣ ደግ ሥራ ሠርቶ ገብቶ ቢተኙበት" የሚለው ብሂልም ይህንኑ

ሐሳብ ያጸናዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የጎጢኣት ሥራም ሠርቶ ከሾነ በፈጣሪ ዘንድ ቅጣቱን ተቀብሎ የሥቃይና የፍዳ ቦታ ወደሚባለው ገሃነም እንደሚገባ ሙሾ አውራጁ ያመላክታል፡፡

ቃል ግጥም 124፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘህ?
እኔስ እኼዳለሁ እግሬ እንዳደረሰኝ
ወንድሜን ገድለውት እኔም መግቢያ የለኝ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሬ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የሙሾ ቃል ግጥሙ በሕይወት ላለው ሰው ሞት ያስከተለበትን ጉዳት የሚያንጸባርቅ ሲሾን ሙሾ ደርዳሪው ደግሞ “እኔ” በሚል የአንደኛ መደብ የትረካ አንጻር የቀረበ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ራሱን የሚቹ ወንድም አድርጎ በማቅረቡ እንዲህ ያለ በደል ደረሰብኝ፤ እንዲህ ያለ መጥፎ ድርጊት ተፈጸመብኝ እያለ ሲያንጎራጉር የሚቹ ቤተዘመድ የሾነ ሁሉ ስሜቱ ስለሚነካ ዋይ፣ ዋይ፣ ወየሁ፣ ወየሁ፣ ... እያለ እንባ በእንባ ይራጫል፡፡ በመሾኑም በወንድምነት የተወከለው ሙሾ አውራጅ ሰዎች የወንድሜን ሕይወት ስላጠፉት እኔም ብሾን መጠጊያና መጠለያ የለኝም በማለት ውስጣዊ ስሜቱነ ገልጿል፡፡ ምናልባትም ሚቹ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ለወንድሙ የምግብ፣ የልብስ፣ የገንዘብ፣ ወዘተ. ስጦታ ሲያደርግለት ነበር ወይ ብለን እንዲናጠይቅ ያደርገናል፡፡ ስለሾነም አልባሽና አጉራሼ የነበረው ወንድሜ በሞት ሲለየኝ እኖርበት የነበረውን ቦታ ለቅቄ እግሬ እንዳደረሰኝ የትም እጓለሁ በማለት ውሳኔውን አስተላልፏል፡፡

ቃል ግጥም 125፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘህ?
አንተ የቀብር ዐፈር ሆዳሙ ሆዳሙ
ሰዎችን ብላና ይውጣልህ ራቡ፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ አብደላ መኮንን፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በሙሾ ቃል ግጥሙ ውስጥ የቀብር ዐፈር የሰውን ግብር በመላበስ ተወቃሽ ኾኖ ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም ሕይወት የሌለውን ግኡዝ ነገር “አንተ” ብሎ በመጥራትና በመሰውኘት እያናገሩ እምነታዊ ተግባርን ለማንጸባረቅ ተችሏልና ነው፡፡ የተሰወኘው ነገር ሲወቀሥ እንሰማለን እንጂ ለወቀሣው መልስ ሲሰጥ ወይም ሲናገር ግን አናዳምጠውም፡፡ በዚህ መሠረት በአብዛኛው የሞተን ሰው ዐፈር ኾነ፣ ወደመሬት ተመለሰ፣ ወደዐፈር ተለወጠ፣ ወዘተ. ይባል እንደኾነ ነው እንጂ አስከሬኑ የሚቀበርበትን ጉድጓድ ዐፈር ልክ እንደ ሰው ጠገብኩኝን የማያውቅ ሆዳም ተደርጎ መቆጠር ያለበት አይመስለኝም፡፡ በመቀጠልም ዐፈሩን ሰው በሌ ጨካኝ ነህና ሥጋ የለበሰውን፣ ነፍስ የነሣውን (የወረሰውን) ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ብላና የምግብ ፍላጎትህ ይርካ በማለት ሙሾ አውራጁ ራሱ አልቅሶ ሌሎችንም ማስለቀስ እንደቻለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቃል ግጥም 126፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘህ?
እገልዬ አበሉ የእናትህን አንጀት ቀና ብለህ እየው
የእጎትህን አንጀት ቀና ብለህ እየው
ታዲያ ምን ያደርጋል ዐፈር መስኮት የለው፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ እንድሪስ አዳነ፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ሙሾ በማውረድ ሰዎችን የሚያስለቅሱ አቀንቃኞች በተለያዩ የለቅሶ ሥርዓቶች ይህንን እና ሌሎች መሰል ቃል ግጥሞችን ስለሚጠቀሙ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሰዎችን ስም በቀጥታ መጥራት አልተቻለም፡፡ ከዚህ ይልቅ በስም ፋንታ እየተተካ ሊያገለግል የሚችለውንና “እገልዬ አበሉ” የሚባለውን ተውላጠ ስም በዚህ ጽሑፍ ለመጠቀም ተችሏል፡፡ በቃል ግጥሙ ውስጥ ሙሾ ደርዳሪው ሟቹ እንደሚሰማና መልስ እንደሚሰጥ አድርጎ በመቁጠሩ በመንፈስ የመገናኘት ኹኔታ ይስተዋላል፡፡ በዚህ መሠረት የእናትህን እና የእጎትህን አንጀት ቀና ብለህ እየው በማለት ያናግረዋል፡፡ እዚህ ላይ እናት የተጠቀሰችበት ምክንያት ወላጅ ከመኾኗም ባሻገር ደግ፣ ሩኅሩኅ፣ የዋህ በመኾኗ የተነሣ ነው፡፡ ስለእናት የተጠቀሱት ውስጣዊ ባሕርያት በእጎትም ላይ መንጸባረቃቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው፡፡ በተጨማሪም እጎት የእናት አምሳያም ናት፡፡ ስለዚህ እነዚህ ወገኖች በሞተው ሰው ሐዘን በጣም ተጎጂዎች በመኾናቸው ከል መስለው ከል ለብሰው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም አንድን ሐሳብ ቀደም ብሎ ከተነገረው ጋር ለማያያዝ የሚያስችለውን ቃል በመጠቀም ታዲያ አስከሬንህ ከተጋደመበት ቦታ ቀጥ ብሎ በአንተ ሞት የተነሣ የእናትህን እና የእጎትህን በሐዘን መቆራመድ እንዳትመለከት በመቃብር ውስጥ የተጫነህ ዐፈር መስኮት የለውም በማለት ሙሾ ደርዳሪው አንጎራጉሯል፡፡

ቃል ግጥም 127፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘሽ?
ዘጠና ቀን ሙሉ ከዐልጋ ተቆራኝታ
እያታለለችን አሳይታ ፈገግታ፡፡
ሕመሟ ሲጠና ሹልክ ብላ ኼደች
አላገኘናትም እንግዲህ ዐረፈች፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ እሸቱ ይመር፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ ለረጅም ጊዜ ታሞ የሞተ ሰው ዳግም ተመልሶ እንደማይመጣና ወደፊትም እንደማይገኝ በማመላከት በሕይወት ያለ ሰው የተስፋ መቁረጥ መንፈስ ያጠላበት መኾኑን ለማንጸባረቅ ችሏል፡፡ በመኾኑም ሟቿ ዘጠና ቀናት ሙሉ ቀንና ሌሊት በማይለቅ በሽታ በመታመሟ የተነሣ የዐልጋ ቁራኛ ኾና ቆይታለች፡፡ ኾኖም ሣቅ እያለችና የጥርሷን ብልጭታ እያሳየች ስላዘናጋችን ትድናለች ብለን አስበን ነበር በማለት ሙሾ ደርዳሪው የቤተዘመዱን ውስጣዊ ስሜት አንጸባርቋል፡፡ ከዚያ በኋላ የጤና ማጣቷ ኹኔታ የበለጠ እየጠነከረና እየበረታ ኼዶ ባላስብነውና ባልገመትነው ወቅት ሕይወቷ ዐለፈ፡፡ ስለዚህ ካሁን በኋላ ወይም ሌላ ጊዜ

ልናገኛትና በእጃችን ልናደርጋት አልቻልንም በማለት አስለቃሹ ሐዘኑ የራሱ እንደኾነ አድርጎ ገልጾልናል። ሐዘኑን የራሱ እንደኾነ አድርጎ ማቅረቡ ደግሞ የሟቿን ኹኔታ በቅርብ የተከታተለ ስለሚመስል ቤተዘመዱ ደረቱን እየደቃ እንባ በእንባ እንዲራጭ ያደርገዋል።

ቃል ግጥም 128፡- ዋ! ዋ! ምን አገኘሽ?
አይ ቆንጆ ብላሽ አይ ቆንጆ ብላሽ
የምታበይበት አይታሰር እጅሽ
ዘመድ የሚገባበት አይፍረስ ቤትሽ፡
እጅሽ አይታሰር ይቁም እንዳገዳ
ተሸኝቶበታል ታላላቅ እንግዳ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አረጋ አሰፋ፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ከሙሾ ቃል ግጥሙ ሟቿ በሕይወት ዘመኗ ቆንጆና ለጋስ እንደነበረች መገንዘብ ይቻላል። ስለሴት ልጅ ቁንጅና ደግሞ በሰዎች ሁሉ ወጥ የኾነ መለኪያ ያለው አይመስለኝም። ይህንን በተመለከተም Leslau and Kane (2001፡60) “እገሊት ይህ አነሳት፤ ይህ በዛባት፤ ትንሽ እንዲህ ባትኾን ኖሮ” እየተባለ በዓይን የሚታየው ሁሉ ለጎሊና ፍርድ ይቀርባል በማለት ገልጸዋል። በቃል ግጥም ዘፈንም ቢኾን አንድ ቆንጆ የኾነች ሴት ከጸጉሯ አንሥቶ እስከ ጫማዋ ድረስ ያለው የአካል ክፍሏ ሁሉ ይገጠምላታል። በዚህ መሠረት የሟቿ ቁንጅና በውጫዊ ገጽታዋ ጸጉሯ የአባይ ዳር ቁጠማ፣ ዐይኗ የአጥቢያ ኮከብ፣ ሰንዳዳ (ቀጥ ያለ) አፍንጫ፣ ጥርሰ በረዶ፣ ከንፈሯ ሊፈነዳ የደረሰ የጽጌረዳ እንቡጥ፣ ዐንገተ መቃ፣ ደረተ ሳንቃ፣ ጡቷ ሊተኮስ የተደገነ ሮኬት፣ ተረከዘ ሎሚ፣ ወዘተ. ኾና የምታምር ሴት እንደነበረች መገመት ይቻላል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተገለጸው ውበቷ በሞት የተነጣ መና ኾኖ እንደቀረ ከቃል ግጥሙ መረዳት ተገቢ ነው። በመቀጠልም በለጋስነቷ ሰዎች ሲርባቸው የምታጎርሥበትና የምታበላበት፣ እንደዚሁም ሲቸግራቸው የምትሰጥበት እጇ በሞተች ጊዜ በፈትል ክር መገነዝ (መታሠር) እንደሌለበት ሙሾ አውራጁ አንጎራጉሮላታል። የግነዛ ሥራው ደግሞ አንድ ሰው መሞቱ ከተረጋገጠ በኋላ ጨርቁ፣ ሰሌኑ፣ የፈትል ክሩ፣ ሌላውም ለከፈን የሚውለው ነገር ሁሉ ከተሰባሰበ በኋላ መጋረጃ ይጣልና የእጅና የእግር አውራ ጣቱ በፈትል ክር ይታሠራል፤ ሬሳው ደግሞ በሰሌን ወይም በጨርቅ ተከፍኖ ይገነዛል። ቃል ግጥሙ ይህንን ሁሉ የግነዛ ሥርዓት በሴትዮዋ ላይ ሲከናወን በዓይነ ኅሊናችን እንዲናስተውል አድርጎናል ማለት ይቻላል።

ቀጥሎም “... አይፍረስ ቤትሽ” የሚለውን ሐረግ በቁሙ ስንመለከተው በድንጋይና በጡብ፣ በጨፈቃ፣ በኖራ፣ በጭቃ፣ በሰንበሌጥ፣ በቆርቆሮ፣ በሳንቃ፣ በጠርብ የተሠራው የሰዎች መኖሪያ ቤት ባድማ (ባዶ) እንዳይኾን የሚለውን የሚያመላክተን ሲኾን በቃል ግጥሙ ዐውድ

ግን በትውልድ የአባትሽ ወይም የእናትሽ ወገን የኾነ ሰው ሁሉ በሚሰባሰብበት ቤትሽ ውስጥ ያለው ሀብትና ንብረትሽ እንዳይባክን እና እንዳልነበር እንዳይኾን በማለት ገጣሚው አቀንቅኗል። በመጨረሻም ሴትዮዋ በሕይወት በነበረችበት ወቅት ለተራበው ሰው ስታበላበት የነበረውን እጇን እንደ በቆሎ፣ ማሽላ ... ካሉ የአገዳ እኽሎች ግንድና ከሸንኮራ አገዳ ጋር በማነጻጸር በግነዛው ወቅት መታሠር የለበትም ይላል። ምክንያቱም በዕድሜ፣ በማዕረግ፣ በማኅበራዊ ኹኔታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች በእጇ እንደተጋበዙና እንደተስተናገዱ ለመግለጽ ተችሏልና ነው። በአጠቃላይ በሙሾ ደርዳሪው ከቀረበው ቃል ግጥም የምንገነዘበው ሴትዮዋ ዘመድ ወዳድ፣ ተቀባይ፣ ተንከባካቢ፣ አስተናጋጅ፣ ቤቷም ቢኾን የእንግዳ መቀበያ፣ ማረፊያና ማደሪያ መኾኑን ነው።

6.4. የሆታ ግጥሞች

የሆታ ቃል ግጥሞች በወንዶች አማካይነት በኅብረት የሚከወኑ ናቸው። አወራራጁ ወይም አስጨፋሪው ደግሞ "ሆ ባይ" በመባል ይጠራል። የሆታ ቃል ግጥሞች የሚከወኑት በተበቺሳ ወቅትና በሰርግ ዕለት ብቻ ሳይኾን በተለያዩ የመከወኛ አጋጣሚዎች እንደነበርም የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ የኾኑት አቶ ደመቀ አዳነ (መጋቢት10/2012) ነግረውኛል። እሳቸው እንዳሉት አሁን አሁን ቀረ እንጂ በአዲስ ዓመት መለወጫ ዋዜማ ዕለት ማታ ችቦ በርቶ እንዳበቃ ልጃገረዶቹ ዐታሚቸውን እየመቱ ሲዘፍኑ ወንዶቹ ደግሞ "ሆ" ይሉ ነበር። በገና ጨዋታ መጨረሻ ላይም ጀንበር እንደማቆልቆል ስትል አሸናፊው ወገን "ሆ" ይል እንደነበር ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅት ግን በጥምቀት በዓል የከተራ ዕለት ከሰዓት በኋላ ከየመንደሩ እየወጡ ታቦት የሚያጅቡት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የኾኑ ወጣቶች እስከ ጥምቀተ ባሕሩ ድረስ፣ በጥምቀት ዕለትም ታቦቱ ወደደብሩ ሲመለስ "ሆ" ይላሉ። በጅጌ ወቅትም ጀጌተኞቹ የእርሻ፣ የዐረም፣ የዐጨዳ፣ የውቂያ፣ የቤት ሥራ፣ የዐጥር ማጠር፣ ወዘተ. ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ሥራውን ሲያሠራ በዋለው ሰው ቤት ሲበሉና ሲጠጡ አምሽተው የደከመ ሰውነታቸውን ለማሳረፍ ወደየቤታቸው ሲኼዱ እስከሚለያዩበት ሰዓትና ቦታ ድረስ ሴቶቹ ይዘፍናሉ፤ ወንዶቹ ደግሞ "ሆ" ይላሉ በማለት አቶ ደመቀ በዝርዝር አስረድተውኛል። ከዚህ በመቀጠል በቃለ መጠይቅና በሰነድ ከተገኙት የሆታ ቃል ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት።

ቃል ግጥም 129፡ ሃይ ሃይ ሃይ ሎጋው ሽቦ
ሃይ ሃይ ሃይ ሎጋው ሽቦ።
ተዋጋ ብዬ ብሰጠው ጦር
ለአባቱ ሰጠው ለባጥ ማገር።

ኹለት ጊዜ

ተዋጋ ብዬ ብሰጠው ጋሻ
ለእናቱ ሰጣት ለዐመድ ማፈሻ።
(ቃለ መጠይቅ፣ አደም ሁሴን፣ 19/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

“ሎጋው ሽቦ” የጦረኛና የሐርበኛ ዘፈን ሲኾን፣ ሽቦ ያለበት፣ የተጠመጠመበት፣ ባለሽቦ ሎጋ ማለት እንደኾነ ደስታ ተክለ ወልድ (1962፡707 ገልጸዋል። በዚህ ጥናት ግን ሎጋው ሽቦ ባህላዊ የሆታ የዘፈን ዓይነት ሲኾን፣ በዜማ መልክም ቢኾን እየተመላለሰ የሚባል የግጥም አዝማች ነው። “ሎጋው” የሚለውን ቃል በተናጠል ስንመለከተው ቅርጹ ሰፋ ያለ፣ ረጅምና ጠንካራ የኾነ ጦር ከነሶማያው (ከነዘንጉ) ማለት ሲኾን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቁመናው የሚያምር ረጅም፣ መለሎ ወጣት ማለት እንደኾነ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993፡37) ያስገነዝበናል። የመጀመሪያውን ፍች ይዘን የሆታ ቃል ግጥሙ ሲመረመር አቀንቃኙ ግለሰብ ከብረት የተሠራውን፣ ስለታም የኾነውንና ሹል ጫፍ ያለውን፣ እንደዚሁም ለመዋጊያ የሚያገለግለውን መሣሪያ ተረክቦ በጦር ሜዳ ላይ ተፋለም የተባለው ሰው ለቤት ጣሪያ ማገር እንዲኾን ለአባቱ ሰጠው በማለት ትችቱን ሰንዝሯል። በተጨማሪም ከጎሽ፣ ከዝኖን፣ ከጉማሬ ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሠራውን፣ ብዙውን ጊዜ ክብ የኾነ ቅርጽ፣ ከውስጥ በኩልም የእጅ ማስገቢያ ወይም ማንገቻ ያለውን፣ እንደዚሁም በውጊያ ወቅት ለጦር ወይም ለጎራዴ፣ … መመከቻ የሚያገለግለውን ጋሻ (የጦር መሣሪያ) ቢሰጠውም ለዐመድ መዛቂያ እንዲኾናት ለእናቱ ሰጣት በማለት የነቀፌታ አስተያየቱን አቅርቧል። በአጭሩ በቃል ግጥሙ ውስጥ ጦር ጠማሽ የኾነው ተራኪ በሚኮሰኩሱ ስንኞች አማካይነት በጦርነት ወቅት ድፍረት የሌለውን ሰው ጎሊና በሚሰቀጥጥ ኹኔታ ሲያሸማቅቀው ለመመልከት ችለናል።

ቃል ግጥም 130፡- አበባ አበባ መውዜር አበባ } ሦስት ጊዜ
መውዜር አበባ
መውዜር ካማረህ
በደን ውስጥ ሽምቅ ዐባይ ዳር ወርደህ
ምን ታደርጋለህ ከሰንበሌጡ
ባልንጀሮችህ ወዳጅ ሲመርጡ።
ካንተ ወንድነት ይሻላል ዱባ
አጥር ላይ ወጥቶ ያደምቃል ዐምባ።
(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

በቃል ግጥሙ አዝማች ላይ “መውዜር” የሚል የጦር መሣሪያ ተጠቅሷል። የጎምሳ አለቃ አድማሱ ከበደ (ቃለ መጠይቅ፣ 21/05/2012፣ ቦረና ወረዳ) እንደነገሩኝ ከኾነ መውዜር የተባለው የጦር መሣሪያ አምስት ጥይት የሚጎርሥ፣ ፈረንሳይ ሠራሽ የኾነ ኋላ ቀር የጠብመንጃ ዓይነት ነው። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው የጎበረተሰብ ክፍል ከጦር

መሣሪያ ጋር ያለው ቁርኝት በጣም ከፍተኛ በመኾኑ በ“ሆ” ባዩ ሰው “መውዜር ካማረህ” የሚል የስንኝ ዘለላ ቀርቧል። የሆታው ቃል ግጥም አውራጅም መውዜር ላሠኘው፣ ላስፈለገው ሰው መፍትሔ አዘጋጅቶለታል። ይሄውም አባይ በመባል ወደሚታወቀው ታላቅ ወንዝ በመውረድ ጫካ ውስጥ ከደፈጥህ በኋላ ጠብመንጃ የያዘ ሰው ገድለህ በመቀማት የጦር መሣሪያ ባለቤት ትኾናለህ በማለት ምክር ለግሶታል። በእርግጥ ይህንን ለማድረግ ጀግንነትን ስለሚጠይቅ ተደብቆ መሣሪያ የሚቀማው ሰው “እገሌ ወንድ ወጣው” የሚባል ዓይነት መኾን እንዳለበት የሚታመን ነው።

ከላይ ከተነሣው ርእሰ ነገር ሥር ያሉት አራቱ ስንኞች ደግሞ ሰውን የመወረፍ ኹኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው። እንደሚታወቀው ሰንበሌጥ ለቤት ክዳን የሚያገለግል ረጅም የሣር ዓይነት ነው። ከዚህ ውጭ ያን ያኽል ሰው ተደብቆ በሌላው ላይ አደጋ ያደርስበታል ተብሎ ለመገመት ያስቸግራል። የሆታው አውራጅ ግን ዐብሮ አደጎችህ ወይም እኩዮችህ ከንፈርን በመሳም ብቻ ልጃገረድን ፍቅረኛ ለማድረግ የምትስማማቸውን ወይም የሚፈልጓትን ከሌላዎቹ ለይተው ሲመርጡ አንተ ምን ትሠራለህ? በማለት በባላንጣነት የሚመለከተውን ሰው ሲጠይቅ ይደመጣል። በማኅበረሰቡ ዘንድ ይህ ዓይነቱ ተግባርም ቢኾን ጀግንነትን የሚጠይቅ በመኾኑ የተነሣ ነው። በመቀጠልም አቀንቃኙ ይህንኑ ግለሰብ ከዱባ ጋር አነጻጽሮ በተፈጥሮ ካለው የሰብእና ክብር ዝቅ ሲያደርገው እንመለከታለን። ይሄውም ዱባ ትልቅ ፍሬ ያለው ሐረግማ ተክል በመኾኑ በአንድ አካባቢ ተቀራርበው የተሠሩ ቤቶች ያሉበትን ዐምባ ያሳምራል፤ ያሰውባል። አንተ ግን ከዚህም በታች ነህ በማለት ወንድነቱን በመፈታተን አላግጦበታል።

ቃል ግጥም 131፡- ወይ ዞማ ዓለም ዓለም
ህም ህም ወይ ዞማ ዓለም ዓለም
ይታከካል እንጂ ዛፍ አይወጣም በሬ
ዓይኗ የሚመስለው የተከበበ አውሬ።
(ቃለ መጠይቅ፣ እንዳልካቸው ግዛው፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ኹለት ጊዜ

ቀደም ሲል በሰርግ ዕለት የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች በተተነተኑበት ወቅት የዚህ ቃል ግጥም አዝማችም የታየ መኾኑን ማስታወስ ይገባል። ከአዝማቹ ቀጥሎ ያለው ስንኝ የሚያመላክተው ማንኛውም ነባራዊ የኾነ ነገር በለውጥ፣ በእንቅስቃሴና በእድገት ላይ ቢኾንም የተፈጥሮ ሕግ ተሽሮ ከቀንድ ከብት ወገን የኾነው በሬ ከምድር ተነሥቶ ዛፍ ላይ ሊወጣ የማይችል መኾኑን ነው። ከዚህ ይልቅ የቤት እንስሳው ገላውን ሲያሳክከው ከዛፉ ግንድ ጋር የሚፈጋፈግ መኾኑን መገንዘብ ይቻላል። በመጨረሻው ስንኝ ላይ የተሞገሰችዋ ልጃገረድ ደግሞ የዓይኗ ውበት ከተከበበ አውሬ ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። በእርግጥ የዓይን ውበት ከባቄላ አበባ፣ ከዛጎል፣

ከአጥቢያ ኮከብ፣ ወዘተ. ጋር ሊነጻጸር ይችላል። በዚህ ስንኝ ውስጥ ደግሞ የወጣቷ ዓይኖች ጎላ ጎላ ብለው ከሩቅ መታየታቸውና በጫካ ውስጥ ያለ አውሬ በዐደን ወቅት ተከብቦ መውጫ በርና መኼጃ መንገድ በማጣቱ ዓይኑ መፍጠጡ ተመሳስለው ቀርበዋል። የቃል ግጥሙ ገጣሚ በተፈጥሮ ከማይገናኙ ነገሮች መካከል እንዲህ የመሰለ የጋራ የኾነ ተመሳሳይ ገጽታ ወስዶ ማመሳሰሉ እሱ አይቶት የነበረውን የልጂቷን ዓይናማነት በአድማጭ ዓይነ ኅሊና ውስጥ ለማስረጽ ፈልጎ እንደኾነ ልብ ማለት ይገባል።

ቃል ግጥም 132፡- አበባ መውዜር አበባ መውዜር አበባ
ራሴን በቆሌ በደም ሳልነከር
ታፋዬን በጩቤ በደም ሳልነከር
ታዲያ የት ይገኛል የሸግዬ ከንፈር።

ኹለት ጊዜ

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ከፍተኛ በኾነ የልጃገረድ ፍቅር የወደቀው ጎረምሳ ከሌሎች ጋር ለመጣላት፣ ለመደባደብ፣ ወዘተ. ምክንያት የኾነችውን የከንፈር ወዳጁን የራሱ ለማድረግ ደሙን እስከሚያፈስበት ድረስ መሥዋዕት እንደሚከፍል ቃል ግጥሙን ባቀነቀነበት ወቅት በአንደበቱ ሲናገር ተደምጧል። በመኾኑም ቆሌ ከተባለው የበረሓ ዛፍ ተቆርጦ በተዘጋጀው ዱላ ልጅቷን በእጃቸው ለማድረግ በሚፈልጉ ጎረምሳዎች ጭንቅላቱ ተፈንክቶ በሚፈሰው ከፍተኛ ደም ገላው ሳይነከር፣ ከጭን በላይ፣ ከወገብ በታች፣ ከመቀመጫ በስተጎን በኩል ያለ ታፋው በጩቤ ተወግቶ የደም ዐበላ ሳይወስደው ውብ የኾነችውን የልጃገረድ ከንፈር መሳም እንደማይችል ገልጿል።

እዚህ ላይ ግለሰቡ በዱላ ጭንቅላቱን ተፈንክቶም ኾነ በጩቤ ታፋውን ተወግቶ በሚፈሰው ብዙ ደም ሰውነቱ ይዝላል፤ ዐቅም ያጣል፤ ይደክማል። በዚህ የተነሣም ራሱን መቆጣጠር ያዳግተዋል። ነገር ግን ላመነበት ጉዳይ እንዲህ ያለውን መሥዋዕት ከፍሎ ከጋብቻ በፊት በወጣትነት ጊዜ በመሳሳም ላይ ብቻ የተወሰነውን የሽጋ ልጅ የከንፈር ወዳጅነት እሱም በእጁ ማስገባት እንደሚገባው በቃል ግጥሙ ባሉት ስንኞች አንጸባርቋል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ ለከንፈር ወዳጅ ተብሎ የሚከፈለው መሥዋዕት ከፍተኛ መኾኑን ማስተዋል ይገባል።

ቃል ግጥም 133፡- ያሆ ያሆ ቆሌ ላመረው ና በለው ና በለው።

ኹለት ጊዜ

የክንድህን ያኽል ትሳደባለህ
ዙሪያው ገደል ነው መሸሻም የለህ፡፡
አልጠየቁም ወይ አልሰምቶም ወይ ወሬ
ማሬው ጊንጥ ዐምባ ያስጥሳል ደሬ፡፡

(ከወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

የቃል ግጥሙ አውራጅ በተቃራኒ ወገን ባለው ጎረምሳ ላይ የፍርሃት ስሜት ሲፈጥር ይስተዋላል፡፡ ይሄውም የክንድ ያኽል በሚረዝመው ምላስህ ሰዎችን በመዝለፍህ የተነሣ መጠጊያ እስከምታጣና ደሬ በተባለው የበረሓ እንጨት የተሠራውን ዐጥር እስከምትዘል ድረስ እርምጃ ይወሰድብሃል ብሎታል፡፡ እንደሚታወቀው ክንድ ከኩርማ (ከክርን) አንሥቶ እስከ እጅ ጣት መጨረሻ የሚደርስ የሰውነት ክፍል ሲኾን፣ እስካሁንም ድረስ በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ባህላዊ የርዝመት መለኪያ ኾኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በቃል ግጥሙ ውስጥ እንደዚህ ያለው የአካል ክፍል በግልጽ ባልተነገረው ምላስ ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡ ምንም እንኳን ኹለቱም የሰውነት ክፍሎች በመኾናቸው ከአንድ ጎራ የሚመደቡ ቢኾንም የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸው መኾናቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡

እዚህ ላይ አቀንቃኙ “የክንድህን ያኽል ትሳደባለህ” ሲል በተቃራኒ ወገን ያለው ጎረምሳ ምላስ የክንድ ያኽል ይረዝማል ማለት አለመኾኑን ማጤን ይገባል፡፡ ምክንያቱም “ምላሱን አስረዘመ” ሲባል ብዙ ተናገረ የሚለውን አንድምታ ያስጨብጣልና ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎችን በበርካታ መጥፎ ቃላት በመዝለፍህ፣ ከፍ ዝቅ አድርገህ በማዋረድህ፣ ወዘተ. የተነሣ የኃይል እርምጃ ሲወሰድብህ በአካባቢው የሚያዝና የሚጨበጥ ነገር ስለሌለ ከፍርሃትህ የተነሣ ገደል ትገባለህ እንጂ ወደኋላ ተመልሰህ በመሮጥ የምትሸሸበትም ኾነ የምትጠጋበትና የምትደበቅበት ቦታም አታገኝም ብሎታል፡፡ በአጭሩ የቃል ግጥሙ አውራጅ “ዙሪያው ገደል ነው” ሲል የጭንቀት ስሜት እንዲያድርበት የተፈለገው ጎረምሳ ትልቅ ችግር ላይ መውደቁን ለማመላከት ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል መኖሪያውን ጠርቶ ነዋሪውን በሚያሳይ የንግግር ስልት በወግዲ ወረዳ ውስጥ ካሉት አካባቢዎች መካከል “ጊንጥ ዐምባ” በግጥሙ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ስለዚህ ገጣሚው የአነጋገር ስልቱን በሐሳብ መግለጫነት የተጠቀመው ጊንጥ ዐምባ በተባለው አካባቢ የሚኖሩ ጎረምሳዎች ድፍረትን በሚጠይቁ ኹኔታዎች ላይ አሸናፊዎችና ሞት አይፈሬ መኾናቸውን አጉልቶ ለማሳየት ስለፈለገ ነው፡፡ በመኾኑም ዐምባጓሮ በሚነሣበት ወቅት ድል አድራጊ ኾነው በተቃራኒ ወገን ያሉትን ጎረምሳዎች በቆላ አካባቢ በሚገኘውና በጠንካራ እንጨት የተሠራውን ዐጥር የሚያስጥሱ ወይም የሚያዘልሉ ናቸው ብሏል፡፡ ስለዚህ በዙሪያው ያሉት ሰዎች የጊንጥ ዐምባ ጎረምሳዎችን ዝና አልሰሙም ወይ በማለት ያጠይቃል፡፡

6.5. የቀረርቶ ግጥሞች

ቀረርቶ የጀግንነትን ወኔ መቀስቀሻ መኾኑ የሚታወቅ ነው። በመኾኑም ቀረርቶ ዜማው ለዘብ፣ ረዘም፣ ሳብ ያለ ሐሳብን ወደሩቅ አምጥቆ፣ ትዝታን ከዓይነ ኅሊና ደቅኖ፣ ስሜትን የሚያሞቅ፣ ሲቃ የሚያሲዝ፣ ኹለንተናን የሚቀሰቅስ፣ የሚያስቆጣ፣ ወኔን የሚሸቀሸቅና የሚመስጥ ነው (Leslau & Kane (2001፡180):: የቃል ግጥሞቹም ቢኾኑ አንድም ኺድ፣ ተዋጋ፣ ግደል፣ ወዘተ. እያሉ መንፈስን የሚቀሰቅሱ መልእክቶችን ያስተላልፋሉ። ኹለትም ጀግናው ትካዜውን፣ በደሉን፣ ጸጸቱን፣ ምሬቱን እንዲገልጽ ያደርጉታል። አብዛኛውን ጊዜ ቀረርቶ የፉከራ መነሻ ኾኖ ይገኛል። በዚህ መሠረት ያለ ቀረርቶ ፉከራ ሊከወን አይችልም ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም ቀረርቶ በእርሻ ወቅት ያላንዳች ፉከራ ብቻውን የሚቀነቀንበት ጊዜ አለ።

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ከሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል መካከል የማቅራራት ፍላጎት ያለው ሰው በበረሓና በጫካ ውስጥ ሲጓዝ፣ ከብቶቹን በደረባ ሲጠብቅ፣ ከመኖሪያ ቤቱ ርቆ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን፣ ደቦ ባለበት ቤት ማታ ላይ ምግብ ተበልቶ ሲያበቃ መጠጥ እየተጠጣ ባለበት ወቅት፣ በየሰርጉና በየድግሱ ቤት መረዋ የኾነውን ድምፁን አርቆ በመልቀቅ እንደሚያቅራራ አቶ መኮንን ጌታሁን (ቃለ መጠይቅ፣ 25/06/2013፣ ቦረና ወረዳ) ገልጸዋል። በመኾኑም በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲቀነቀኑ ከነበሩት የቀረርቶ ቃል ግጥሞች መካከል ጥቂቶችን ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 134፡- ፈሪና ተራራ ምን ጊዜም ይኖራል
ጀግና ብርሌ ነው ወድቆ ይሰበራል።
(ምልከታ፣ አህመድ ጀማል፣ 02/07/2012፣ ከለላ)

በመስክ ላይ በነበረኝ ቆይታ አለልኝ ይማም ከተባለው ወጣት ሰርግ ላይ እንደተመለከትኩት አቅራሪው አቶ አህመድ ጀማል እ...እ...እ...ኣ...ኣ...ኣ ኧረ ደኑ ደኑ፣ ኧረ እናንተ ሆዬ ብሎ ሲጀምር ታዳሚዎች ደግሞ በጋራ ኾነው እ...እ...እ...አ....ኣ...ኣ...ኣ... በማለት ሲቀበሉ ነበር። ከዚያም የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን ያዘሉ የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን አቀንቅኗል። ለአብነትም ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም ፈሪን የሚተች ኾኖ ተገኝቷል። ይኼውም ጀግንነት፣ ድፍረት፣ ወዘተ. የሌለው ሰውና የምድር ራስ እየተባለ የሚታወቀው፣ በአካባቢው ካለው መሬት በጣም ከፍ ብሎ የሚገኘው ተራራ ምን ጊዜም ቢኾን በምድር ላይ ሊኖሩ እንደሚችሉ አቅራሪው ገልጿል። ስለኾነም ተራራ ከመሬት ከርሥ ውስጥ ፈንድቶ በሚወጣ እሳተ ገሞራ አማካይነት ተንዶ እንዳልነበር ካልኾነ በስተቀር ዘላለማዊ እንደሚኾን ሁሉ ፈሪም ቢኾን ዐምባንሮ በሚነሣበትም ኾነ በጦርነት ወቅት ሸሽቶ ስለሚያመልጥ ለረጅም ጊዜ በሕይወት የመኖር ዕድሉ ከፍተኛ

መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል። አቅራሪው ከላይ ካለው በተቃርኖ ጀግናና ብርሌ በመሬት ላይ ምን ጊዜም ህልው ኾነው እንደማይቆዩ ገልጿል። ምክንያቱም ብርሌው በሌላ ኃይል ወይም የራሱን ሚዛን ባለመጠበቅ ከላይ ወደታች በመወርወር ምድር ላይ ካረፈ እንክትክት ብሎ የሚሰበር መኾኑ ይታወቃል። አቅራሪው በለዋጭ ዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት የዚህን ግኡዝ አካል ድርጊት ለጀግናው አውርሶ ሐሳቡን በጉልሕና በምስል ለማሳየት ችሏል። በመኾኑም በጠብ ወይም በጦርነት ወቅት በሚካኼድ ፍልሚያ ኃይለኛ፣ ብርቱ፣ ሞት አይፈሬ የኾነው ጀግና ከባላጋራ በሚሰነዘር ጥቃት የእሱም ሕይወት ሊያልፍ ይችላል የሚለውን መልእክት አድማጭ እንዲገነዘበው አድርጓል።

ቃል ግጥም 135፡- ኧረ ተው እያሉት በራውን ሸጠና
ኧረ ተው እያሉት ምንሽር ገዛና
ደግሞ እንደ ወንዶቹ በሽሎ ወረደና
እመይ ድረሽ አለ ዘራፉ ቀረና።

(ቃለ መጠይቅ፣ በፈቃዱ ጤናው፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ እንዲህ ቢኾን ይሻላል ወይም ከዚህ ይልቅ ይህንን ብታደርግ ይጠቅመሃል ብለው ሰዎች የሰጡትን ምክረ ሐሳብ ያልተቀበለ ሰው ለችግር መዳረጉን የሚያንጸባርቁ ስንኞች ተሰናስለው ቀርበዋል። ይሄውም ለእርሻ አገልግሎት ሲያውለው የነበረውን በሬ ከቀንበሩ ነጥሎ ሲሸጥ መገረምን ለመግለጽ በሚያስችል ኹኔታ "ኧረ ተው"፤ ይቅርብህ ቢሉት በልቡ ያሰበውን ነገር ለማድረግ ስለተነሣሣ ግለሰቡ የሰዎችን ምክር ሊቀበል አልቻለም። ከዚያም ዐልፎ በሬው በተሸጠበት ዋጋ ምንሽር የተባለውን ጎላ ቀር ጠብመንጃ ሲገዛም ልመናን በተላበሰ መንፈስ "እባክህ" በማለት፣ እንደዚሁም ምክር ዐዘል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከዚህ አድራጎቱ እንዲቆጠብ ቢነግሩትም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ሊሰማቸው አልቻለም። በመቀጠልም ጀግና ኾኖ ወንድ ወጥቶት (በለበጣ አነጋገር) የገዛውን ጠብመንጃ በመያዝ "በለው በምንሽር፣ እንዳይሞት እንዳይሽር" ለማለት በሽሎ ወደተባለው ወንዝ መውረዱን የቃል ግጥሙ ተናጋሪ በዓይነ ልቡናችን አስቃኝቶናል። በመጨረሻ ላይ ግን የከፋ ችግር ሲያጋጥመው ጀግንነትን፣ ልበ ሙሉነትን፣ ድፍረትን፣ ቆራጥነትን፣ አልበገር ባይነትን፣... በሚያንጸባርቀው ፉከራ "ዐካኪ ዘራፍ" በማለት ከፍ ባለ ድምፅ መደንፋቱን ትቶ "እናቴ ድረሽ" ማለቱ ተገልጿል። ቃል ግጥሙ በመነጨበት አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ይህንን ዓይነት ድርጊት ውርደት፣ ቅሌት፣ አሳፋሪ ነገር አድርጎ ሊቆጥረው እንደሚችል ከተሰበሰቡት በርካታ የፉከራና የቀረርቶ ቃል ግጥሞች መገንዘብ ይቻላል።

ቃል ግጥም 136፡- አትራቂኝ ብትሬ አትራቂኝ አልወድም
ደም ተፈሰሰ ነው የሚደርሰው ወንድም፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/052012፣ ቦረና ወረዳ)

ቀደም ሲል በጥናቱ ማኅበራዊ ዳራ ላይ እንደተገለጸው በሦስቱም ወረዳዎች የሚኖሩ ወጣቶች በዋናነት ተለይተው የሚታወቁበትን በትር (ዱላ) ከእጃቸው እንደማይነጥሉ ለማየት ተችሏል። በምልከታ ወቅትም ይሄው ኹኔታ ተረጋግጧል። ወጣቶቹ በትራቸውን በጨለማ ወቅት ለምርኩዝ እንደሚጠቀሙበት፤ የሚተናኮሉ የዱር አራዊትንም እንደሚከላከሉበት፣ ከዚህ በላይ ደግሞ በተለያዩ ወቅቶች በሚከሠቱ አጋጣሚዎች ከባላጋራ የሚሰነዘረውን ምት እንደሚመክቱበት፣ መልሰውም እንደሚያጠቁበት ለማወቅ ተችሏል። ለዚህም ነው የቀረርቶው አቀንቃኝ በትሩን ከአጠገቤ ስትለይኝ ወይም ስትነጠይኝ አልፈልግም፤ ደስ አይለኝም ያለው። ወንድሜም ቢኾን የተፈጸመብኝን ግፍ ለመበቀልና ደም ለመመለስ የሚደርሰው ተፈንክቼ ደም በደም ከኾንኩኝ፣ ከዚያም አልፎ ከሞትኩኝ በኋላ ነው በማለት ውስጣዊ ስሜቱን ባሰናሰናቸው ስንኞች ለመግለጽ በቅቷል። ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ከተራ ቁጥር 137 — 139 ያሉት ቃል ግጥሞችም በወግዲ ወረዳ ከሚኖረው ከበፈቃዱ ጤናው በ23/05/2012 ዓ.ም የተነገሩኝ ሲኾን፣ እነሱንም በቅደም ተከተል ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 137፡- ቦረና ወርደ ጠባብ ቁመቱ ረጅም ነው
ከውስጡ ሲገቡ ተኳሹ ብዙ ነው።

በቦረና ወረዳ የሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ጀግንነቱና በጠላት አይነኬነቱ ቅኔያዊ በሆነው በቀረርቶ ቃል ግጥሙ ተንጸባርቃል። ይህ ማኅበረሰብ ከጦር መሣሪያ ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለው በመኾኑ አነጣጥሮ በመተኮስ ጠላትን ለመምታት እንዲችል ዕለት በዕለት ኢላማን እንደሚለማመድ፣ በዚህ የተነሣ ጠብመንጃን የያዘው አብዛኛው ሰው ተኩሶ እንደማይስት ኹለተኛው ስንኝ አመላክቷል። በዚህ መሠረት የጎኑ ስፋት አነስተኛ፣ ቁመቱ ደግሞ በጣም ትልቅ በኾነው የመልክዓ ምድር ክልል ውስጥ ከሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል መካከል ዐያሌ የሚኾነው ጠብመንጃን ተኩሶ ዒላማውን የመምታት ችሎታ ያለው፣ የማይስትና አነጣጣሪ መኾኑን ከስንኞቹ መገንዘብ ይቻላል። ይህ እና ሌሎች መሰል የቀረርቶ ቃል ግጥሞች የማኅበረሰቡ የጀግንነት፣ የቆራጥነት፣ የጽኑ እምነት፣ ወዘተ. መግለጫዎች በመኾናቸው አርኣያነታቸው ለቀጣዩ ትውልድም ሊሸጋገር እንደሚችል መገንዘብ ይገባል።

ቃል ግጥም 138፡- እባክህ ምንሽር ተኳሽክን ንገረኝ
ክላሽም በልጅግም ተኳሽክን ንገረኝ
ተሸካሚው ሁሉ እንዳያንገራግረኝ።

የቃል ግጥሙ አቅራሪ ግለሰብ አንድ ነገር እንዲኾንለትና እንዲደረግለት ለመጠየቅ ወይም ለመለመን በሚያስችል ቃል “እባክህ” እያለ ምንሽርን፣ ክላሽን እና በልጅግን ሲጠይቅ ተደምጧል። እዚህ ላይ ምንሽርና በልጅግ የተባሉት የጠብመንጃ ዓይነቶች ኂላ ቀር ሲኾኑ፣ ክላሽ ደግሞ በካዝና ሠላሳ ጥይቶችን የሚጎርሥ ወይም የሚጨመርበት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ መኾኑ የሚታወቅ ነው። አቀንቃኙ ሕይወት የሌላቸውን እነዚህን ግኡዝ ነገሮች እንደሚሰሙና መልስ እንደሚሰጡ አድርጎ በመቁጠር ሲጠይቃቸው የምንሰማው እንቶኔ በተባለው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ነው። ምክንያቱም በግጥሙ ውስጥ ያለው የንግግር አፍላቂ ‹‹እኔ›› የሚል ገጸሰብ ሲኾን፣ ተደራሾቹ (የጦር መሣሪያዎቹ) ደግሞ በኹለተኛ መደብ የቀረቡ ናቸው። ምንም እንኳን የጦር መሣሪያዎቹ ቢሰወኙም ተኩሶ ኢላማውን ሳይስት የመምታት ችሎታ ያለውን ሰው፣ አነጣጣሪውን ንገሩኝ፣ አሳውቁኝ እየተባሉ በአቅራሪው አንደበት ሲጠየቁ እንሰማለን እንጂ መልስ በመስጠቱ ረገድ ሰዋዊ ድርጊት ሲፈጽሙ አናይም። በመኾኑም አቅራሪው መሣሪያዎቹን የጠየቃቸው ኢላማውን ሳይስት አነጣጥሮ የሚተኩሰውን እና የማይተኩሰውን ለይተው እንዲነግሩት ነበር። ምክንያቱም አነጣጥሮ መተኮስ የማይችለው ሁሉ በትከሻው ላይ ጠብመንጃ ተሸክሞ፣ ባንገቱና በጀርባው ላይ አንግቶ ስለሚንዘ ከፍርሃት የተነሣ ደንገጩ ሽሽት ውስጥ እንዳልገባ በማለት ገልጿል።

ቃል ግጥም በተማረውም ኾነ ባልተማረው ማኅበረሰብ ዘንድ ጋዜጣዎችን እንደሚተካ፣ በወቅቱ ያሉትን ጉዳዮች ለመተቸትና ሪፖርት ለማድረግ እንደሚጠቅም በጽንሰ ሐሳባዊ ቅኝት ወቅት ለማየት ተችሏል። የሚከተሉት ስንኞችም በአሁኑ ወቅት ፖለቲካን እና የዘር ልዩነትን በተመለከተ ያለውን መንፈስ በጣም አጉልተው የሚያሳዩ ኾነው በመገኘታቸው ለትንተና ቀርበዋል።

ቃል ግጥም 139፡- ሰው እንኹን ብንል ሰው አንኾን አላችሁ
ደጉን ስማችንን በዘር ከፋፍላችሁ
አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ ነው ብላችሁ
እንዲህ እንዲንኾን ነበር ዱሮም ዓላማችሁ።

ከላይ የቀረበው የቀረርቶ ግጥም ጥናቱ የሚካኼድባቸውን አካባቢዎች ብቻ የሚመለከት ሳይኾን ሀገራዊ ይዘትን የሚያንጸባርቅ ኾኖ ተገኝቷል። ይኼውም በመንፈሳዊ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በቀደምት ስልጣኔ ገናና የኾነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይኹነኝ ብሎ አንዱን ዘር የመጉዳት ሌላውን የመጥቀም ድርጊት መፈጸም ተገቢ አለመኾኑን በቃል ግጥሙ ተገልጿል። በመኾኑም ገጣሚው “ሰው እንኹን ብንል ሰው አንኾን አላችሁ” ሲል እኩይ ወይም የክፉ ክፉ የኾኑ የፖለቲካ አመራሮችን ሰው የምትባሉት ሥጋ በመልበሳችሁ፣ ነፍስን ከፈጣሪ በመሰጠታችሁ

ብቻ አይደለም። ይልቁንም ማሰብና ማመዛዘን የምትችሉ ሰብዓዊ ፍጡር መኾን ሲገባችሁ፣ የሰውነት ቅርጻችሁን ሳትለቁ ሌላ ባሕርይ ገዝታችሁ፣ በአስተሳሰባችሁና በድርጊታችሁ ዘቅጣችሁና በዘር ላይ ተመሥርታችሁ በሰዎች ላይ የምታደርጉት አድልዎ ከሰውነት ጎራ አወረዳችሁ በማለት ትችቱን ሰንዝሮባቸዋል። በመቀጠልም በጀግንነታችን፣ በተፈጥሮ ሀብታችን፣ በእሴቶቻችን፣ ወዘተ. በዓለም ላይ የታወቅነውን እና በደግነቱ የተጠራውን ስማችንን በቋንቋ ሥረ መሠረት ላይ በመንጠልጠል አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ወዘተ. እያላችሁ በዘር ከፋፈላችሁን በማለት ፖለቲካዊ ተቃውሞውን አቅርቧል።

በእኔ አመለካከትም ቢኾን አንድ ሰው ሁልጊዜ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሶማሌ፣... ነው እየተባለ ቢነገርም ውሕድ ሊኾን እንደሚችል ፖለቲከኞቹ የተገነዘቡት አይመስልም። ቢገነዘቡትም እንኳ ይህ ዓይነቱ ሐሳብ እንዲነሣባቸው አይፈልጉም። ቃል ግጥሙ የወቅቱን የፖለቲካ መንፈስ በጎላ ኹኔታ የሚያንጸባርቅ ኾኖ ተስተውሏል። ምክንያቱም ገጣሚው ለችግሩ ተጠያቂ ያደረጋቸውን የፖለቲካ ባለሥልጣናት በዘር ማድላት ተጽዕኖ ሥር ወድቃችሁ፣ በልዩነት ታጥራችሁ፣ አንዱን ዘር በመደገፍና ከፍ ከፍ በማድረግ፣ ሌላውን ዘር በማግለል፣ በመጨቆን፣ ወዘተ. በሕዝቦች መካከል ልዩነትን ወይም አለመግባባትን በመፍጠር የምታካኺዱት የፖለቲካ የአገዛዝ ስልት ቀድሞውንም አቅዳችሁትና አልማችሁት የነበረ መሠሪ ተግባራችሁ ነው በማለት ኮንኗቸዋል። የቀረርቶ ቃል ግጥሙ በአሁኑ ወቅት ባለው የፖለቲካ ሥርዓት ገዥ የኾነው አካል ተገዥ በኾነው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ ያሳደረውን ብሶት የመግለጫ መሣሪያ ኾኖ ማገልገሉን መገንዘብ ይቻላል። እንደነዚህ ያሉ ቃል ግጥሞች በተነገሩበት ወቅት ተመዝግበው መቀመጣቸው ጥሩ የታሪክ ምንጭ ሊኾኑ እንደሚችሉ መገመት የሚያዳግት አይኾንም።

6.6. የፉከራ ግጥሞች

ደቦ ባለበት ቤት ማታ ላይ ምግብ ተበልቶ ሲያበቃ መጠጥ እየተጠጣ ባለበት ወቅት፣ በየሰርጉና በየድግሱ ቤት ኅበዛዝት ሁሉ በልቶና ጠጥቶ ሞቅ ባለው ጊዜ የማቅራራት ተሰጥዎና ፍላጎት ያለው ሰው ብድግ ብሎ የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን ከራሱም ኾነ ከሌሎች ሰዎች እየተቀበለ መረዋ በኾነው ድምፁ አርቆ ያዜማል። በዚህን ወቅት "በል በል፤ አድርግ አድርግ" በሚል ስሜት የተገፋፋው ፎካሪ ደግሞ ሞያውን፣ የፈጸመውን ጀብዱና ሌሎችንም በድንፋታ (ጀግንነትን ወይም ወኔን በሚቀሰቅስ ኹኔታ) የፉከራ የቃል ግጥሞችን ያወርዳል። በፉከራ ወቅት ፎካሪው በዐጃቢነት የሚጠቀመው ዱላ ከኾነ መሬቱን መታ መታ እያደረገ፣ ጠብመንጃም የያዘ ከኾነ ከፍና ዝቅ እያደረገ፣ ያለ ጥይት እያቀባበለና ቃታ እየሳበ፣ እንደዚሁም ከወዲያ

ከወዲህ እየተንጎራደደ፣ በርከክ ቆም እያለ በሚያስፈራራ የፊት ገጽታ ፉከራውን ያቀልጠዋል። የፉከራ ቃል ግጥሞች የራሳቸው የኾነ መግቢያ ያላቸው ሲኾን፣ ከእነዚህ መካከልም ተዘውትረው የሚከወኑት "ዘራፍ ዐካኪ ዘራፍ"፣ "አንበሳ ገዳይ"፤ "ዝኖን ገዳይ"፤ "ጠላት ገዳይ"፤ "ዘራፍ ያንተ ታማኝ፤ ያንተ አሸከር" የሚሉት ናቸው።

"አንበሳ ገዳይ፤ ዝኖን ገዳይ፣ ወዘተ." የሚሉት መግቢያዎች ታሪካዊ መነሻ ያላቸው ይመስላል። ምክንያቱም ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የአባቶቻችን የጀግንነት መገለጫዎች አንዱ አዳኝነት ስለነበር ግዳይ የጣሉ ጀግኖች እነዚህን መግቢያዎች ይጠቀሙ እንደነበር ማጤን ይገባል። ከዚህ ውጪ ግን በፍካሬያዊ ትርጓሜያቸው "አንበሳ ገዳይ" ሲባል ጀግናን እና ሐርበኛን፣ "ዝኖን ገዳይ" ሲባልም ግዙፍ የኾነውን ጠላት መግደልን ሊያመላክቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ከእነዚህ በተጨማሪ "ዱር ቤቴ" ብሎ በረሓ የገባው ሽፍታ ከጠላት ጋር ፍልሚያ በሚያካሂድበት ወቅት ተከታዮቹ ወይም በእርሱ ሥር ያደሩት ሰዎች ግዳይ የመጣል (የማረከውን ወይም ያደነውን አቅርቦ የማሳየት) በለስ ቀንቷቸው ከኾነ በሽፍታው ፊት ለፊት ላይ ኾነው ታማኝነታቸውን እና ጀግንነታቸውን ለመግለጽ "ዘራፍ ያንተ ታማኝ፤ ያንተ አሸከር" በሚሉ መነሻዎች የፉከራ ቃል ግጥሞችን ሊከውኑ ይችላሉ። አሁን ላይ ደግሞ ልጁ አባቱ ባለበት ዐውድ ላይ የሚፎክር ከኾነ ከፊት ለፊቱ በርከክ ብሎ "ዘራፍ ያንተ ታማኝ፤ ያንተ አሸከር" በማለት ፉከራውን እንደሚጀምር አቶ ደመቀ አዳነ (መጋቢት 10/2012) ነግረውኛል። ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ካተኮሩት የፉከራ ቃል ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት።

ቃል ግጥም 140፡- እንፎክር እንደሁ በእርሻ እንፎክር
ያልሠራነውን አንቀባጥር።

(ቃለ መጠይቅ፣ አብርሃም ዘለቀ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙ ከበጎ ምግባራት መካከል የሥራ ትጋትን ይሰብካል፤ የአነጋገር ሥርዓትንም ያስተምራል። ይዜውም ፎካሪው ግለሰብ ወኔን በሚቀሰቅስ ኹኔታ ዘራፍ እያልን ስንፎክር በተሰማራንበት የግብርና ሥራ ባገኘነው የምርት መጠን እና በፈጸምነው ጉልህ ሥራ እንጂ የባጥ የቆጡን መናገር፣ ያላደረግነውን ነገርና የኾነ ያልኾነውን መለፍለፍ አይገባም በማለት ሥነ ምግባርን ለማስተማር ችሏል። በመኾኑም አንድ ሰው መፎከር ያለበት በሙያው ተግቶ በመሥራት ባገኘው አመርቂ ውጤት ነው። ከዚያ ውጭ ግን ያልሠራውን የሠራ አስመስሎ በመዋሸት መቀባጠር ተገቢ አለመኾኑን ግለሰቡ አስረድቷል። በዚህ መሠረት ጥናቱ

በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው የኅብረተሰብ ክፍል በፉከራ ቃል ግጥሞቹ አማካይነት ማኅበራዊ እሴቱን መጠበቅ እንደቻለ መገንዘብ እንችላለን፡፡

ቃል ግጥም 141፡- ኧረ ማረስ ማለት ጎድጓዳ መሬት ነው
ኧረ መጥመድ ማለት የላም ልጅ በሬ ነው
ኧረ መጫን ማለት ዋርዳ በቅሎ ነው
ከዚህ በተረፈ ውሸልሸል ኑሮ ነው፡፡
(ከከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 03/07/2012)

በቃል ግጥሙ ውስጥ “ኧረ” በሚል የንግግር ቃል ሦስቱ ስንኞች የመጀመራቸው ዋናው ምክንያት በግብርና ሥራ ለሚተዳደረው አርሶ አደር ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት፣ እንደዚሁም አንድን ነገር ጠንክሮ መሥራት እንደሚገባ ለማበረታታት ነው፡፡ በዚህ መሠረት አርሶ አደሩ አዝርዕት ዘርቶ አጥጋቢ የኾነ ምርት ለማምረት እንዲችል ማረስ ያለበት ወደውስጥ የገባ፣ በገደልና በተራራ መካከል ያለ ማሳ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድም በጎርፍ አማካይነት ከገደላ ገደሉና ከተራራው ላይ ወደደልዳላው ማሳ የሚመጣው ዐፈር ለምነት ስለሚኖረው፣ ኹለትም የእርሻ መሬቱ እርጥበት ቶሎ ስለማይለየው አጥጋቢ የኾነ ምርት ሊሰጥ ይችላልና ነው፡፡ “ኧረ መጥመድ ማለት የላም ልጅ በሬ ነው” የሚለው ስንኝ የሚያመለክተው አርሶ በሌው እርሻውን ማረስ ያለበት በጠንካራ በሬ እንጂ በደንብ በማያርስና በአባያ ወይም በሚለግም በሬ አለመኾኑን ነው፡፡ ጥናቱ በተካኼደበት አካባቢ ጥማድ (ጥንድ) በሬ የሌለው ሰው በላም ሊያርስ ስለሚችል ከዚህ ችግር እንደምንም ብሎ መውጣት ያለበት መኾኑንም ለማስገንዘብ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ ከአንድ ቦታ ወደሌላው ሲጓዝ ዋርዳ በቅሎ መጫን እንዳለበት የፉከራው ቃል ግጥም ያመለክታል፡፡ “ዋርዳ” የሚለውን ቃል በጥሬው ስንመለከተው ጠቋራ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጠቆር ያለ መልክ ያለው፣ ለዕቃ ማጓጓዣነት የማይውል፣ ለኮርቻ ጭነት የተመደበና ሰው ብቻ የሚጓጓዝበት ሠጋር (ሲኼድ ወይም ሲራመድ ጋላቢውን የማይነቀንቅ) በቅሎ መጋለብ እንዳለበት ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ኑሮ ግን እንደነገሩ ወይም የማይረባ ነው በማለት ፎካሪው ያስረዳል፡፡ በቃል ግጥሙ መሠረት ኑሮ ማለት አንድ ሰው በዕድሜ ዘመኑ የሚያሳልፈው ሕይወትና ለሕይወትም አስፈላጊ የኾኑ ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ በስንኞቹ ውስጥ በዝርዝር የቀረቡት ነገሮች ተሟልተው እስካልተገኙ ድረስ ግን ትዳርም፣ ንብረትም የለም የሚለውን መልእክት ቃል ግጥሙ ያስተላልፋል፡፡

ቃል ግጥም 142፡- እክትትት ውርጩ በረደኝ
እኔስ ቂጣም ሰው ባይናገረኝ፡፡
እኔስ ቂጣም ሰው ከተናገረኝ
ያባትህን ቦታ ለቀህ ኺድ አለኝ፡፡

የአባትን ቦታ ለቀው ከኼዱ
ዕልፍኝ ከአዳራሽ እያነደዱ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ በለጠ አደላ፤ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው ግለሰብ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ “እክትትት ውርጩ በረደኝ” ያለው ክፉ ተናግሮ የሚያናግር ተንኮለኛ ሰው በነገር አስክሮት እንጂ እጁን እና እግሩን የማያንቀሳቅስ ወይም የሚያደነዝዝ ቆፈን ብርድ ይዞት አይደለም፡፡ ለዚህም ማረጋገጫው ትልቅ መቀመጫ ያለው (ቂጣም) ሰው (በአሽሙር መኾኑ ነው) በአእምሮው ውስጥ ያለውን ወይም ያሰበውን አጥንት የሚሰብር መጥፎ ንግግር ባይናገረው እንደሚመርጥ በምሬት ገልጿል፡፡ ምክንያቱም ሰውዬው ነገረ ሰይጣን ስለኾነ ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ የሚችል ነገር በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ በአግቦ በመናገር ጠብ እንደሚጭርና ነገር እንደሚያነሣሣ በቀላሉ ለመረዳት ችሏልና ነው፡፡ ቀደም ባለው ወቅት ከትውልድ ወደትውልድ እየተሸጋገረ በመጣው የማኅበረሰቡ ወግና ሥርዓት መሠረት የአባት ቦታ ወይም ርስት ለወንድ ልጅ ይተላለፍ ነበር፡፡ ነገር ግን የግለሰቡ አባት እያረሰ ሲጠቀምበት የነበረውን እና በኋላ ላይም ለእሱ በውርስ የተላለፈውን መሬት በሀኬተኛው ሰው አማካይነት ለቆ እንዲኼድ ሲነገረው ዕልፍኝ ከነአዳራሹ የኾነውን የሰውዬውን ቤት በእሣት አጋይቶ ዐመድ በማድረግ እግሩ እንደመራው የትም መንገዝ እንደሚችል ገልጿል፡፡

የፉከራ ቃል ግጥሙ በታሪክ ጠቃሽ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ስለቀረበ ተደራሲውን ከጠባብ መልክዓ ምድራዊ አካባቢና ከተወሰነ የዘመን ድንበር ለማዘለል የሚችል መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በግጥሙ የመጨረሻው ስንኝ ላይ ዕልፍኝና አዳራሽ ተጠቅሰዋል፡፡ አዳራሽ ሲል በአሁኑ ጊዜ ለስብሰባ፣ ለትርኢት ማሳያ፣... የሚያገለግለውን እና ብዙ ሰው የሚይዘውን ሰፊ ቤት ማለት ሳይኾን፣ ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓት ትመራ በነበረበት ወቅት ግብር የሚበላበት፣ ሞላላ ወይም ክብ ቅርጽ ያለው ትልቅ ቤት ነው፡፡ ዕልፍኝ ደግሞ በዚያው ዘመን ነገሥታቱና መኳንንቱ ታላላቅ እንግዶችን ለመቀበያና ለማስተናገጃ ይገለገሉበት የነበረና ጌጠኛ የኾነ ባዳራሹ ታልፎ የሚገባበት ቤት ነው፡፡ በዚህ መሠረት የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ በአሁኑ ወቅት ያለው ወጣቱ ትውልድ የማያውቃቸውን ግን ደግሞ በታሪክ የሚታወሱ ቤቶችን በመጥቀስ ሐሳቡን የማግዘፍ፣ የማስፋት፣ እንደዚሁም ከታሪክ ጋር የማዛመድ ተግባር አከናውኗል፡፡ በዚህ የተነሣም የቃል ግጥሙ አድማጭ የገጣሚውን ገጠመኝ ሊጋራ እንደሚችል ማጤኑ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ቃል ግጥም 143፡- ኹለት እጁ ቀኝ እንደ ሸማኔ
አንዱ በሳይንስ አንዱ በቅኔ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ አብርሃም ዘለቀ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን “ዘራፍ” እያለ ለመጀመሪያ ጊዜ የፎከረው ግለሰብ ዘመናዊም ኾነ የቤተ ክህነት ትምህርትን የተማረ መኾኑን ባሰናኛቸው መንቶ ስንኞች መገመት ይቻላል። በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ግለሰቡ የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን የሚገለገልባቸው ኹለቱም እጆቹ ኃይለኛ፣ ፈጣን፣ ምቹ፣ ቀና እና የማያስቸግሩ መኾናቸውን ገልጿል። እነዚህ እንደ ቀኝ የተቆጠሩት እጆቹ እንደኩታ፣ የሀገር ልብስ፣ ጃኖ የመሳሰሉትን ከሚሠራ ሸማኔ ወይም ጥበበኛ ሰው እጅ ጋር በንጽጽር ቀርበዋል። ተነጻጻሪዎቹም ከአንድ ጎራ የመጡ ናቸው - ከሰብዓዊ ፍጡር። በተነጻጻሪዎቹ መካከል ያለው የጋራ ባሕርይ ደግሞ የኹለቱም ሰዎች እጆች ኃይለኛ፣ ፈጣንና ቀና መኾናቸው ነው። ለአብነት የሸማኔውን እጆች ብንመለከት ማግን በድር መካል ለማስተላለፍ የሚረዳውን እና መወርወሪያ የተባለውን የሸመና መሣሪያ በጣም ፍጥነት በተሞላበት ኹኔታ ከቀኝ ወደግራ፣ ከግራ ወደቀኝ መወርወር በመቻሉ ኹለቱም እጆች እንደቀኝ እጅ ኾነው ተግባራቸውን ማከናወን ይችላሉ።

ሌላው በንጽጽር የቀረበውና በኹለተኛው ስንኝ ላይ የተጠቆመው ግለሰቡ ንድፉ ሐሳቦች፣ መላምቶች፣ ወዘተ... ተጨባጭ በኾነ መንገድና በምክንያታዊነት የሚረጋገጡበትን፣ ስለተፈጥሮና ስለኅብረተሰብ ጥናት የሚደረግበትን የሳይንስ ዘርፍ እንደቀኝ በተቆጠረው በአንድ እጁ እንደሚፈጽማቸው ተመላክቷል። የተለያዩና የተወሰኑ የዜማ ምጣኔዎች ያሉት፣ እንደግጥም ቤት የሚመታ፣ ውበት ያለው፣ ይዘቱ ጥልቅ የኾነ ምስጢር እንዲኖረው ተደርጎ የሚቀናበረውና በትምህርት አማካይነት የሚቀሰመውን ቅኔ ደግሞ በሌላኛው እጁ ሊያከናውን እንደሚችል ተገልጿል። በተለያዩ ችሎታዎችና ዕውቀቶች አማካይነት የተሠሩት ሁሉ የተከናወኑባቸው እጆች ሲታዘዙ የነበረው ደግሞ በአእምሮ አማካይነት መኾኑን ልብ ይሏል።

ቃል ግጥም 144፡- ይኼዳል ጊዜ ከመሸ
በሰፋ ዱላ እየመነሸ።
የያዘው ሰፋ እጁን የሞቀው
መች ይመለሳል ሳይደባልቀው።
(ቃለ መጠይቅ፣ አየለች ደርቤ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ የጀግና መንፈስ ተንጸባርቋል። ምክንያቱም ፎካሪው ከፀሓይ ጥልቀት በኋላ እስከ ሌሊት ባለው የጨለማ ወቅት ድረስ ምንም ዓይነት ፍርሃት ሳያድርበት ብቻውን በመንገዝ ቀጥና መለል ብሎ ከሚበቅል የሰፋ ተክል ቆርጦ ባዘጋጀው ዱላ ባላጋራውን እየተከታተለ እንደሚደበድብ ገልጿል። እዚህ ላይ ባትሪ በእጅ ሳይያዝ ወይንም ምንም ዓይነት የጨረቃ ብርሃን ሳይኖር በጨለማ መንገዝ በማንኛውም ሰው ዘንድ የሚደፈር ነገር አይደለም። ለምን ቢባል የሚያደናቀፉ ድንጋዮችና ጉቶዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የሚተናኮሉ የዱር አራዊትን

እና ጨለማን ተገን አድርገው በሰዎች ላይ አደጋ የሚያደርሱ ወንበዴዎች ያጋጥሙ ይኾናል። ስለዚህ ስንቱን ዓይነት አደጋ፣ ስንቱን ዓይነት ፍርሃት እያሰቡ መጓዝ በጣም አዳጋች ነው የሚኾነው። ፎካሪው ግለሰብ ግን እነዚህን አዋኪ ነገሮች ሁሉ ከምንም ሳይቆጥራቸው ጠላቱን በሰፋ ዱላ መነረቱን ተናግሯል። እንዲያውም የጨበጠው ዱላ የወንድነት ስሜትን አላብሶ የደስታና የኩራት መንፈስ እንዲሰማው ስላደረገው ጠላቱን ትርምስምሱን ሳያወጣ ወደኋላ እንደማይመለስ በፉከራ ቃል ግጥሙ አስረድቷል። ከላይ በቀረቡት ትንታኔዎች መሠረት የፉከራ ግጥሞች የሰውን ልጅ የተደበቀውን ውስጣዊ ስሜት በማውጣቱ ረገድ ከሌሎቹ የቃል ግጥም ዘውጎች የተለየ ያደርጋቸዋል።

ምዕራፍ ሰባት፡- የቃል ግጥሞች ይዘት ዐውዳዊ ትንተና

አንድ የቃል ግጥም ተመራማሪ መረጃዎችን ከመስክ ከሰበሰበ በኋላ በዘውግ በዘውግ በመመደብ በዐውድ መተንተን እንደሚኖርበት በምዕራፍ ሦስት ላይ ተገልጿል። በዚህ መሠረት ለዚህ ምዕራፍ የሚኾኑ ቃል ግጥሞች በምልከታ ከመስክ የተሰበሰቡ ሲኾን፣ እነሱንም በተለያዩ ንኡሳን ርእሶች በመከፋፈል በተነገሩበት ማኅበራዊ ዐውድ አማካይነት የይዘት ትንተና ለማድረግ ተችሏል። ይህ ተግባር ሲከናወንም ሥነ ቃሎቹ የትና መቼ እንደተነገሩ፣ ማን እንደተናገራቸውና አድማጮችም እነማን እንደኾኑ፣ የአድማጩ ወይም የተመልካቹ ተሳትፎና ሚና ምን እንደኾነ ለማየት ተሞክሯል። ከዚህ በተጨማሪ ተጨባጭ ዐውዶችን መሠረት በማድረግ ከዋኙ የሚያሳየውን የፊት፣ የዓይን፣ የእጅ፣ የእግር እንቅስቃሴ፣ የድምፅ አወጣጥ (ውፍረት ወይንም ቅጥነት) ኹኔታዎች፣ የአድማጮች ስሜት፣ ታዳሚዎች ለክወናው የሚሰጡት ምላሽ፣ በክዋኔው ወቅት የሚታዩትን እና ጥቅም ላይ የዋሉትን ቁሳቁሶች ጭምር ለመመልከት ተችሏል። ምንም እንኳን ቃል ግጥሞቹ የተቀናበሩባቸው ቃላት (The texts) እጅግ በጣም ጠቃሚ ነገር ቢኾኑም ያለ ዐውድ ሕይወት አልባ ኾነው እንደሚቀሩ መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ በመቀጠል በግብርና ሥራዎችና በሕይወት ጎዳና ሥርዓቶች ወቅት ክዋኔዎች ሲካኼዱ በየዐውዳቸው በመገኘት የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚከተለው ኹኔታ ትንተና ተካኺዶባቸዋል።

7.1. የሥራ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና

የዐፈርን ለምነት በመጠበቅ ምርትን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ባለው የማሳ ዕርከን ሥራ ላይ፣ በእርሻ፣ በዐረም፣ በዐጨዳና በውቂያ ወቅቶች በየዐውዱ በመገኘት አርሶ አደሮች ያቀነቀኗቸው ቃል ግጥሞች ተሰብሰበዋል። ከእነዚህ መካከል የተወሰኑት የቃል ግጥሞች የያዟቸውን ይዘቶች መሠረት አድርጎ በመከፋፈል ቀጥሎ ባለው መልኩ ለመተንተን ተችሏል።

7.1.1. የሙገሳና የርካታ ቃል ግጥሞች

በጥናቱ በተካለሉት ወረዳዎች የሚገኙት አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ለም ዐፈር በጎርፍ እየተሸረሸረና እየተጠረገ እንዳይወሰድ በየዓመቱ ዕርከንን ጠንክረው በመሥራታቸው ሰብላቸው የተመቸው መኾኑን በዓይነ ሥጋቸው በመመልከታቸው በቀጣዩ ዓመት በተካኼደው የዕርከን ሥራ ስንኞችን በማቀንቀን ቀድሞ ለነበረው ዕርከን መገሳ ሲያቀርቡለት በመስክ ቆይታዬ ወቅት በጆሮዬ ለመስማት በቅቻለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው የደረሰ ሰብላቸውን ዐጭደው በመውቃት ቤተሰባቸውንም ኾነ ሸማቹን የኅብረተሰብ ክፍል በአጥጋቢ

ኹኔታ ለመመገብ በመቻላቸው፣ በዐረም ወቅትም ቢኾን በደቦ ያሠማሯቸው ዐራሚዎች ዝናብና ቁር ሳይፈሩ ተግተው ዐርመው የተትረፈረፈ ምርት በማግኘታቸው ራሳቸውን፣ ሌሎች ሰዎችን እና የእርሻ በሬዎቻቸውን በቃል ግጥሞቻቸው ሲያሞግሱ የእርሻ ሥራዎቻቸውን በሚከውኑበት ጊዜና ቦታ ተገኝቼ ለመስማት ችያለሁ፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዕርከን ሥራ የማሳና የጋራ (የተራራ) ላይ በሚሉ ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ የዐፈርን ለምነት በመጠበቅ ምርትን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ባለው የማሳ ላይ ዕርከን ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ አርሶ አደሮችም በእርሻ መሬታቸው ላይ የዐፈር ዐጠባን በመከላከል ምርታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ በዓመት ውስጥ ከ40 — 60 ቀናት በጋራ በመረባረብ የማሳ ላይ የዕርከን ሥራን እንደሚያከናውኑ በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነትም በየካቲት 01/ 2012 ዓ.ም በመጀመሪያው ዙር በመስክ ቆይታዬ ወቅት በቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ ሲካኼድ በነበረው የማሳ ላይ የዕርከን ሥራን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ በዚህ ሥራም ወንዶችና ሴቶች የተሳተፉ ሲኾን፣ ለሥራውም አካፋ፣ እንደዚሁም ዛቢያው ቀጥ ያለና ወፍራም ኾኖ በጫፉ ላይ ማረሻ ወይም መጥረቢያ መሰል ዶማ የተዋደደበት መቆፈሪያ ወይም ደንጎራ ይዘዋል፡፡ የዕርከን ሥራው ከመጀመሩ በፊትም ከወረዳ በመጣ ሙያተኛ አማካይነት በጋራ ምክክር አካኺደዋል፡፡ ምክክሩም ያተኮረው ለዕለቱ ሥራ የተመረጡት ማሳዎች የትኞቹ እንደኾኑ፣ በምን ያኽል ርቀት ዕርከኑ መሠራት እንዳለበትና በማሳዎቹ ላይ ድንጋይ ስለማይገኝ የጎርፍ ውሃን ገድበው ሊይዙ የሚችሉ ጉድጓዶችን በቦይ መልክ መቆፈር በሚሉት ነጥቦች ላይ ነበር፡፡ ከምክክሩም በኋላ አርሶ አደሮቹ ለዕርከን ሥራው ወደተመረጡት ማሳዎች ሲጓዙም ኾነ የአንዱ ማሳ ሥራ አብቅቶ ወደሌላው ሲሸጋገሩ እንደዱላ በማጀቢያነት የተጠቀሚቸውን አካፋና ደንጎራ ወደላይ አድርገው “ሆ” ሲሉ ተመልክቻለሁ፡፡ እርስ በርሳቸውም በመቀላለድ እየተሣሣቁ የዕርከን ሥራውን በቀናነት ሲያከናውኑ እንደነበር ለማየት ችያለሁ፡፡ በዚህን ወቅት ነበር አቶ ይመር ሐሰን ከፎቶግራፉ ሥር የቀረበውን ቃል ግጥም ሲያዜም በማስታወሻዬ ለመያዝ የቻልኩት፡፡



ፎቶግራፍ አምስት፡- በቦረና ወረዳ፣ ቀያፈር ቀበሌ የሚገኙ አርሶ አደሮች የአንዱን የማሳ ላይ ዕርከን ሥራ ጨርሰው ወደሌላው ሲሸጋገሩ በነበሩበት ወቅት፡፡

ቃል ግጥም 145፡- አያችሁለት ወይ የዕርከንን ውለታ
እኽሉን ሲያዳብረው ሲመቸው መኝታ፡፡
(ምልከታ፣ ይመር ሐሰን፣ 01/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የዕርከን ሥራው ያደረገውን በጎ ተግባር፣ ወይም መልካም ሥራ ዓይናችሁን እና ልባችሁን ባንድ ላይ አድርጋችሁ ተመለከታችሁት ወይ፡፡ ጥቅሙንስ አስተዋላችሁት ወይ በማለት አቶ ይመር ሐሰን በቃል ግጥሙ ዐብረውት ላሉት ሰዎች ጥያቄ እያቀረበ እርከኑን አሞግሶታል፡፡ በወረዳው ለሚበቅለውና ለምግብ አገልግሎት ለሚውለው የአዝርዕት ዓይነት (ስንዴ፣ ዐጃ፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ ዐተር ሽንብራ፣ አደንጓሬ፣ ጓያ፣ ምስር፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ በቆሎ ጤፍ፣ ወዘተ.) ዕርከኑ የያዘው ለም ዐፈር ስለተመቸው ሰብሉ ቀደም ሲል ከነበረው መጠን የበለጠ እንዲያድግ፣ እንዲፋፋና ከዚያም በላይ ምርቱ ከፍ እንዲል አድርጎታል ሲልም አመስግኖታል፡፡

ከዕርከን ሥራው በተጨማሪ በታኅሳስ 22/ 2013 ዓ.ም ከቶ በተባለ ቀበሌ አቶ ዘለቀ መሐመድ የተባለው ሰው በደቦ የጤፍ ዐጨዳ በሚያሳጭድበት ዕለት ተገኝቼ በቀጥታ ተሳተፎም ኾነ በኢ-ተሳትፏዊ ዐውዱን ለመከታተል ችያለሁ። በደቦው ኻያ አምስት ሰዎች የተሳተፉ ሲኾን፣ እነሱም 6፡30 ላይ ለምሳ የተዘጋጀላቸውን ዳቦ ሲመገቡ፣ እንደየሃይማኖታቸው ቡቅሪ (ጌሾ የሌለው መጠጥ) እና ጠላ በፕላስቲክ ኩባያ እየተቀዳላቸው ሲጠጡ ተመልከቻለሁ። እኔም የመስተንግዶው ተካፋይ ኾኛለሁ። ብዙ የእግር መንገድ በመጓዜ የተነሣ በጣም ስለራበኝና በፀሓይ መቀት አማካይነትም ውሃ ስለጠማኝ ያለ ምንም ይሉኝታ በደንብ አድርጌ ዳቦውንም በልቻለሁ፤ መጠጡንም ጠጥቻለሁ። በዚህን ወቅት እኔ በዕለቱ በመካከላቸው የተገኘሁበትን ዓላማ ስነግራቸው እነሱም በየተራ “ደስ ይላል” እያሉ አበረታተውኛል።



ፎቶግራፍ ስድስት፡- እኔና በደቦ ጤፍ ሲያጭዱ የነበሩ ወጣቶች ለምሳ የተዘጋጀውን ዳቦ በመመገብ ላይ በነበርንበት ጊዜ።

ምግቡ ከተበላ በኋላ ኹለት ሦስት የሚኾኑት ወጣቶች የታጨደውን ጤፍ ሲደክኑ (በዕቅፍ ለመያዝ በሚያመች መልክ ሲሰበስቡ)፣ ሌሎች ሦስቱ ደግሞ የመከመር ተግባር አከናውነዋል።

አብዛኛዎቹ ደግሞ በበላና ባረፈ ጉልበታቸው የዐጨዳውን ሥራ ተያይዘውታል። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የፀሓይ ሙቀት እንዳይጎዳቸው ጭንቅላታቸው ላይ ጨርቅ ጣል ሲያደርጉ፣ ሌሎቹ ደግሞ የሰሌን ባርኔጣ ደፍተዋል። በዚህን ወቅት እኔ በቀጥተኛ ተሳታፊነት ለዐጭር ጊዜም ቢሆን የማጨድና የመደከን ተግባራትን አከናውኛለሁ። በዐጨዳው ወቅትም በረዳቱ አማካይነት የድምፅና የምስል ቀረጻ በቪዲዮ እንዲካኺድ አድርጌያለሁ። ቀጥሎ ያለውን የፉከራ ቃል ግጥም የተቀነቀነውም በዚህ የዐጨዳ ኺደት ላይ ነበር።

ቃል ግጥም 146:- ዐጫጅ ነህ አሉኝ በጧት ገስጋሽ
ወገንን አጥጋቢ የሕዝብ አጉራሽ።
(ምልከታ፣ ጀማል ይማም፣ ቦረና ወረዳ)

በግጥሙ መሠረት ሌሎች ሰዎች ገጣሚውን ንጋት ወይም ማለዳ ላይ ባለው ወቅት ተነሥቶ ወደማሳው ፈጥኖ በመኼድ ሰብሉን በትጋት ማጨድ የቻለ አርሶ አደር መኾኑን በማሳወቅ እንዳሞገሱት ገልጿል። በዚህ ትጋቱም የእሱ ወገን የሚባሉትን ዘመዶቹን፣ ጓደኞቹን፣ እንደዚሁም ሌሎች አካላትን በማብላቱና በማጠጣቱ የሚያረካና የሚያስደስት መልካም ተግባር በማከናወኑ እንዳመሰገኑትም በቃል ግጥሙ አማካይነት አንጸባርቋል።፣ ከዚህ በላይ ደግሞ አንድም በቤቱ ሕዝብን የሚያበላ፣ ለተቸገረውም ቢኾን የሚሰጥ፣ ኹለትም ካመረተው መካከል ለምግብ ፍጆታ የሚውለውን በገበያ ላይ ለሽያጭ ማቅረብ በመቻሉ የታዘቡት ሰዎች እንዳወደሱት አመላክቷል።

ከመስከረም 05 - 09፣ 2013 ዓ.ም ድረስ ለጥናቱ በተመረጡት አካባቢዎች አርሶ አደሮቹ ዐረም በሚያርሙበት ወቅት የሚያዜሟቸውን የፍቅርና የሥራ ቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። በእነዚህ ቀናት በአንዳንድ ቦታ ላይ ወጣት የኾኑት ዐራሚዎች በጎብረት ሲያርሙ ልጃገረዶቹ በአንድ በኩል ኾነው የፍቅር ዘፈን ሲዘፍኑ፣ ወንዶቹ ደግሞ በሌላ በኩል ኾነው “ሁኡ-ኡ-ው፣ ሁ-ኡ-ኡ-ው” በማለት እንደ አንበሳ እያገሱ ሲደልቁ አጋጥሞኛል። በሌሎች ቦታዎች ላይ ደግሞ እኔው ራሴው ልጃገረዶቹን “ለትምህርት ሥራ ነውና የእናንተን ዘፈን የምፈልገው እባካችሁ ዝፈኑልኝ” በማለት ተማፅኛቸዋለሁ። በዚህን ወቅት በፍርሃት እየተግደረደሩም ቢኾን የተለያዩ ዘፈኖችን አዚመውልኛል። ልጃገረዶቹ በቀኝም ኾነ በግራ እጃቸው ዐረም ስለሚነቅሉ የዘፈናቸው ማጀቢያ አድርገው የሚጠቀሙባትን አታሞ መያዝ አለመቻላቸውን ተረድቻለሁ። የልጃገረዶቹን መግደረደር በኹለት ዓይነት መልኩ ለመገንዘብ ችያለሁ። አንደኛው በአሁኑ ወቅት ወጣቶቹ ሕይወታቸውን በትምህርት ቤት በማሳለፋቸውና ወደአረብ ሀገር ኼደው በመመለሳቸው የተነሣ “ዘመናዊ ነን” ብለው ስለሚያስቡ ከባህሉ እየራቁ መኾኑን፣ ኹለተኛው ደግሞ ችሎታውም ኾነ ፍላጎቱ እያላቸው ለመዝፈን የማይፈልጉ መስለው መታየታቸው ነው



ፎቶግራፍ ሰባት፡- መስከረም 07/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ ወንድና ሴት ወጣቶች ወንፈል በተባለው የመረዳዳት ተግባር በጋራ ዐረም በሚያርሙበት ወቅት እኔም ለተወሰነ ጊዜ ተሳታፊ ነበርኩ፡፡

በዚህ ዐውድ አየለች ደርቤ ከተባለቺው ወጣት የዐረምን ተግባር የሚያመለክተውን ቀጣዩን ቃል ግጥም ለማግኘት ችያለሁ፡፡

ቃል ግጥም 147፡- ዝናብ ዘንቦ ዘንቦ ሲወጣ ፀሓይ
አቤት ማስደሰቱ ዐራሚው ሲታይ፡፡
(ምልከታ፣ አየለች ደርቤ፣ 07/01/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ በቦታው ላይ መረጃ የሰበሰብኩበትን ኹነትንም የሚያንጸባርቅ ኾኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም በዚህ የዐረም ቦታ ላይ የተገኘሁት 8፡00 ላይ ሲኾን፣ ከዚህ ሰዓት በፊት መካከለኛ ዝናብ ጥሎ ያባራበት ወቅት ነበር፡፡ ኹነቱና የቃል ግጥሙ መንፈስ የሚለያዩት ከላይ በተገለጸው ቀን የጣለው ዝናብ ኃይል ጠንከር ያለ ቢኾንም ለረጅም ጊዜ በተደጋጋሚ የዘነበ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን መረጃውን አየለች የተባለቺው ወጣት ብትሰጠኝም የቃል ግጥሙ ገጣሚ ግን ዝናቡ ያለ ማቋረጥ ጥሎ ካባራ ወይም ካቆመ በኋላ ፀሓይ እንደወጣ ገልጿል፡፡ በዚህን ጊዜ ከእኽሉ ጋር የበቀለውን ዐረም የሚያርመው ሰው በውሃ በራሰ ወይም በተጨማለቀ ዐፈር እበከላለሁ ብሎ ሳይፈራ የማረም ተግባሩን በማከናወን ላይ እንዳለ ሲያይ አድናቆትን ለመግለጽ በሚያገለግል ቃል “አቤት” በማለት የተሰማውን ርካታ በደስታ ለመግለጽ ችሏል ተብሎ ይታሰባል፡፡

አርሶ አደሮች ለእርሻ አገልግሎት ለሚጠቀሙባቸው በሬዎች መልክን መሠረት ያደረገ ስም ያወጡላቸዋል፡፡ ለአብነትም ቀይ መልክ ብቻ ያለውን ኩሌና ኳሊ፣ ቀይና ጠቆር ያለ መልክ

ያለውን መጋል፣ ሙሉ በሙሉ ጥቁር የኾነውን ኮልባ፣ ጥቁርና ነጭ ቀለማት ያለውን ጫጉ፣ በቀይና በነጭ ቀለማት የተሻርጎረጎረውን ደግሞ ሽልም በማለት እንደሚጠሩ አቶ ሙስጠፋ ሙሐሌ (ቃለ መጠይቅ፣ 06/11/2012፣ ቦረና ወረዳ) ነግሮኛል። አቶ አብዱ ጀማልም በቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ ውስጥ የሚኖር ሲኾን፣ በቀኝ በኩል ቀይ መልክ ያለውን፣ በግራ በኩል ደግሞ ጥቁር በሬ ጠምዶ ሲያርስ ነበር ያገኘሁት። እሱ እንደነገረኝ ከኾነ ይሄ አቅጣጫ ሁልጊዜ ቋሚ ነው። የበሬዎቹ አቅጣጫ በየወቅቱ እንዲቀያየር ቢደረግ ግን የበሬ ዕቃ ይሰባብራሉ እንጂ ሰልተው ወደፊት ሊኼዱ አይችሉም። ምክንያቱም አንድ በሬ ገና ከመጀመሪያውኑ በግራ በኩል ከገባ (ከለመደ፣ ከተገራ) "ግራ ገብ" እየተባለ በግራ አቅጣጫ ብቻ ነው በቋሚነት ተጠምዶ የሚያርሰው። በቀኝ በኩል ያለውም በተመሳሳይ መልኩ እንደዚሁ ነው። ይህም የበሬዎች ሙያ ተደርጎ ይቆጠራል። የጎረቤት ሰው የእርሻ በሬዎችን በልመና ጠይቆ "እሺ" ቢባል እንኳን አስቀድሞ ሙያቸውን ይጠይቃል በማለት ስለእርሻ በሬዎች ሙያ ከነገረኝ በኋላ በሬዎቹ ቶሎ ቶሎ እንዲራመዱለት ለማድረግ ቀዩን በሬ "ሂድ ኳሊ"፤ ጥቁሩን በሬ ደግሞ "አይዞህ ኮልባ" እያለ ከጠራ በኋላ የሚከተለውን የሆ! በሬ ቃል ግጥም በማዜም ሲያሞግሳቸው ሰምቻለሁ።

ቃል ግጥም 148፡- አያ በሬ በጎ፣ አያ በሬ በጎ
አድርጎ ሽማግሌ ያውላል ተሸንጎ
ያናግራል በጎ።
(ምልከታ፣ አብዱ ጀማል፣ 06/11/2012 ቦረና ወረዳ)

ለአርሶ አደሩ ሕይወት መሠረት የኾኑት የእርሻ በሬዎች መልካም ነገር እየሠሩ ያሉ መኾኑን ለማንጸባረቅ "አያ በሬ በጎ፣ አያ በሬ በጎ" እያለ ገጣሚው አሞግሷቸዋል። ለዚህ ማረጋገጫውም በበሬዎች ታርሶ የሚገኘው የተትረፈረፈ ምርት የኑሮ ደረጃን ከፍ ስለሚያደርግ ሰዎች ተደማጭነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በዚህ የተነሣም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ወይም ዳኛ ችሎት በሚያስችልበት ቦታና አደባባይ ላይ ሰዎችን የማስታረቅ፣ የማስማማት፣ የማማለድ ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ማኅበራዊ ደረጃን በሬዎቹ እንደሚያጎናጽፉ በቃል ግጥሙ አመላክቷል። በዚህ ማኅበራዊ ደረጃ በአደባባይ ላይ ደህና ደህና ነገር በማናገር ሐሳብ ለሐሳብ መለዋወጥ እንደሚቻልም ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል።

በከለላ ወረዳ ኗሪ የኾነው አቶ አማን ሁሴን ደግሞ በ04/11/2012 ዓ.ም እርሻውን እያረሰ ባለበት ጊዜ የበሬዎቹ የአረማመድ ፍጥነት ቀነስ ሲልበት በጅራፍ ሾጥ እያደረገ ‹‹ና ውጣ፣ ና ውረድ›› በማለት የዕለቱን ተግባር ሲያከናውን ተመልክቻለሁ። ዘር እየዘራ ስለነበረ ሌሎች ኹለት ሰዎች ከእሱ ኋላ ኋላ እየተከተሉ በፊር በፊሩ (ማረሻ ሰንጥቆ በኼደበት መሥመር ላይ) ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ እያንጠባጠቡ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ሲያደርጉ ነበር።



ፎቶግራፍ ስምንት፡- አቶ አማን ሁሴን በ04/11/2012 ዓ.ም እርሻውን እያረሰ ባለበት ጊዜ

ሌሎች ኹለት ሰዎች ማረሻ ሰንጥቆ በኼደበት ፈር ላይ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በማንጠባጠብ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ሲያደርጉ፡፡

በዚህ የሥራ ኺደት ነበር አቶ አማን ሁሴን ቀጥሎ ያለውን ቃል ግጥም ሲያዜም በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ለመመዝገብ የቻልኩት፡፡

ቃል ግጥም 149፡- ያርሳል በደመና ይቆፍራል በጉም
ከሰው ማሳ ኼዶ እጁን አይዘረጋም፡፡
(ምልከታ፣ አማን ሁሴን፣ 04/11/2012፣ ከለላ ወረዳ)

አቶ አማን ባዜመው ቃል ግጥም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው አርሶ አደር ምንም ዓይነት ፍርሃት በውስጡ ሳያድርበት ዝናብ ሊዘንብ በተቃረበበት ወቅት እንኳን ሳይቀር የአዝርዕት መዝሪያ ማሳውን ማረስ በመቻሉ ሙገሳን ችሮታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛውን ጊዜ በክረምት ወራት በሚከሠተውና አልፎ አልፎ ወደታች በመውረድ የምድርን አካል ለተወሰነ ጊዜ በሚሸፍነው ጉም ወቅት ለማረሻ የማይመቸውን መሬት በዶማ እየቆፈረ የተትረፈረፈ ምርት ለማግኘት በመብቃቱም አወድሶታል፡፡ በዚህ የተነሣ ዐጨዳ በሚታጨድበት ወቅት በየሰው ማሳ፣ ሰብሉ በሚወቃበት ወቅት ደግሞ በየዐውድማው እየኼደ ለልመና (ለምዕዋት) እጁን ባለመዘርጋቱም አመስግኖታል፡፡

7.1.2. የትችት ቃል ግጥሞች

አርሶ አደሩ በየወቅቱ በሚያከናውናቸው የግብርና ሥራዎች ላይ የተለያዩ የትችት ቃል ግጥሞችን ያዜማል፡፡ ለአብነትም የኬሚካል ማዳበሪያን ሲጠቀም፣ ብስባሽን ሲያዘጋጅ፣ የማሳም ኾነ የተራራ ዕርከንን ሲሠራ የነቀፋ አስተያየቶችን ያዘሉ ቃል ግጥሞችን ያቀነቅናል፡፡

እንደዚሁም ሲያርስ፣ ሲያርም፣ ሲያጭድና ሲወቃ ባየው ደካማ ጎን ላይ በማተኮር የትችት ቃል ግጥሞችን ያንጎራጉራል። በቃል ግጥሞቹ አማካይነት የሚሰጡ ትችቶች ድክመትን ወይም ስሕተትን ለማረም ሲባል የሚቀርቡና ቂም በቀል የሌለባቸው በመኾናቸው ሚዛናዊነትን የጠበቁ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። በዚህ መሠረት በተፈጥሮ ዐውድ የተገኙትን የትችት ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 150፡- ማዳበሪያ ታዞ ሰው ሁሉ ሲያወጣ
ብር የለኝም ይላል አረቄ እየጠጣ።
(ምልከታ፣ ሙሐዬ ሁሴን፣ 04/11/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ከላይ እንደተገለጸው አቶ አማን ሁሴን በሬዎቹን ጠምዶና ዘሩን ዘርቶ እርሻውን በማረስ ላይ በነበረበት ወቅት ከኋላ ከኋላ እየተከተለ ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ የሚያንጠባጥብው ደግሞ ሙህዬ ሁሴን የተባለው ታናሽ ወንድሙ ነበር። ሙህዬ እየሠራ ያለውን ነገር ተመልክቼ ስሙን እና ስለማዳበሪያ የተባለ የቃል ግጥም ካለ እንዲነግረኝ በትሕትና ጠየቅሁት። እሱም ስሙን ከነገረኝ በኋላ ሣቅ በማለት "ምን የማውቀው አለ ብለህ ነው?" በማለት ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም ድምፁን ዘለግ አድርጎ አቀነቀነልኝ። ቃል ግጥሙ ዐፈሩ ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ ነገር እንዲኖረው የሚያደርገውን፣ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ ለአርሶ አደሮች የሚቀርበውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን የኬሚካል ማዳበሪያ በአካባቢው ያለ ሰው ሁሉ በነቂስ ወጥቶ እንዲገዛ በቀበሌ ሊቀመንበር ታዝዞ እንደነበር ያመለክታል።

ነገር ግን ወደመሸታ ቤት በመኼድ አረቄ የተባለውን አልኮልነት ያለውን መጠጥ እየተጎነጨ ለማዳበሪያ መግዣ የሚኾን ገንዘብ የለኝም የሚለውን አርሶ አደር በከፍተኛ ኹኔታ የተነቀፈ እንዲኾን አድርጎታል። ምክንያቱም ገንዘቡን በመጠጥ ከሚያጠፋ ይልቅ ለአዝርዕቱ የሚኾን ማዳበሪያ ገዝቶ ምርታማ በመኾን በኑሮው ላይ ለውጥን እና መሻሻልን ማምጣት ነበረበት በማለት ገጣሚው ተግሣጹን ሰንዝሯል። መጠጥን አዘውትሮ እየገዛ ከሚጠጣ ሰው ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ሰዎችም "እጅግ ያስደንቃል የኛማ ነገር፤ ሠርተን ባገኘነው ጠጥቶ መስከር።" እያሉ ራሳቸውን ሲተቹ እንደነበር በሕይወት ተመክሮዬ ሰምቼ እንደነበር በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም ወድጃለሁ።

ቃል ግጥም 151፡- መሬት መሬት ቢሉ መሬት የት ተገኝቶ፣
በሥራ ዘመቻ ሹርባ ተሠርቶ።
(ምልከታ፣ ጌታቸው እብሬ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን የነገረኝ አርሶ አደር በቦረና ወረዳ ከቶ በተባለው ቀበሌ ከሚኖረው ሕዝብ ጋር የማሳ ላይ ዕርከን እየሠራ ባለበት ወቅት ነበር። በአቶ ጌታቸው አጠገብ ያሉት ሌሎች የሥራው

ተሳታፊ የኾኑ አርሶ አደሮች ደግሞ በቃል ግጥሙ እየተሣሣቁ “ምናልክ በል? እስቲ ድገመው በል!” ይሉት ነበር። ይህንን ያሉት አንድም የእነሱንም የውስጥ ስሜት መግለጽ በመቻሉ፣ ኹለትም ለነገሮች ያለውን አስተውሎት በአድናቆት ለመግለጽ የመሻት ስሜት እንዳላቸው እንደኾነ መረዳት ይቻላል። ከላይ እንደምንመለከተው በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ድግግሞሽ ይስተዋላል። ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት ታርሶ ለአዝርዕት መዝሪያ የለሰለሰው መሬት በአርሶ አደሩ ዘንድ ያለው ተፈላጊነት ከፍተኛ መኾኑን ገጣሚው በአፅንኦት ለመግለጽ ፈልጎ እንደኾነ መረዳት ይገባል። እዚያው ስንኝ ላይ ለእርሻ የሚኾነው መሬት ከየትም ቦታ ሊገኝ እንደማይችልም በምላሽ መልክ ተጠቁሟል።

እንደገጣሚው ሐሳብ ይህ ሊኾን የቻለበት መሠረተ ነገር በጎብረትና በርብርቦሽ አማካይነት በሚሠራው ዕርከን የሰብል መዝሪያው የእርሻ መሬት የተጣበበ በመኾኑ የተነሣ ነው። ገጣሚው ይህንን ኹኔታ በትችት መልክ የገለጸው ደግሞ ባህላዊ የኾነውን የሴቶችን የጸጉር አሠራር (ጉንጉን) በዘይቤያዊ የአነጋገር ስልት በመጠቀም ነው። አገላለጹንም ከተለመደው ወጣ ወይም ለየት ያደረገው ለጉዳዩ ልቀት ሰጥቶ የትችት ሐሳቡ ግብ እንዲመታ በማሰብ እንደኾነ መገንዘብ ይገባል። እዚህ ላይ የዕርከን ሥራ የዐፈርን ለምነት ከተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መኾኑ የሚታወቅ ነው። ታዲያ ዕርከኑ ያን ያክል ሰፊ ቦታ ሊወስድ እንደማይችል እየታወቀ ለአዝርዕት እድገትና መዳበር አስፈላጊ የኾነው ለም ዐፈር በዝናብ አማካይነት በሚፈጠር ጎርፍ ተጠራርጎ እንዳይወሰድ ደግፎ በሚይዘው ካብ ላይ ትችት ማቅረብ ተገቢ አለመኾኑን መረዳት ተገቢነት ይኖረዋል።

አርሶ አደሩ በዕለት ተዕለት የተለያዩ የግብርና ሥራዎችን ሲያከናውን በዓይነ ሥጋው የሚመለከታቸውን ዕኩይ ተግባራት በቃል ግጥሞች ትችት እንደሚሰነዝር ቀደም ሲል ተገልጿል። በቦረና ወረዳ ነዋሪ የኾነው አቶ ምትኩ አገኘሁም የደረሰ ጤፉን ሲያጭድ በነበረበት ዕለት ስለዳተኛና ልግመኛ አርሶ አደር የነገረኝን ትችት አዘል ቃል ግጥም ቀጥለን እንመልከት።



ፎቶግራፍ ዘጠኝ፡- በቦረና ወረዳ ከአቶ ምትኩ አገኘሁ ጋር ጤፍ እያጨድኩ ባለኹበት ወቅት

ቃል ግጥም 152፡- ዐጫጅ ዐጫጁን እኛ ስናውቀው
ማጭድ በዕቅፌን ማን ደባለቀው
(ምልከታ፣ ምትኩ አገኘሁ፣ 22/04/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን የነገረኝ አርሶ አደር ከላይ በተጠቀሰው ቀን 3፡00 ላይ በቀያፈር ቀበሌ ብቻውን ጤፍ ሲያጭድ ነበር ያገኘሁት፡፡ እኔም ማንነቱን እና በዚያ ቦታ ላይ የተገኘሁበትን ዓላማ ነገርኩት፡፡ ከዚያም በዐጨዳ ላይ የተባሉ የቃል ግጥሞችን በመንገር እንዲተባበረኝ በአክብሮት ጠየቅሁት፡፡ እሱም “ዛሬማ ምን ዋጋ አለው፡፡ ዕድሜያችንም ገፋ፤ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገን ትተነው የለም ወይ፡፡” በማለት መለሰልኝ፡፡ ልብ ለልብ ብንገናኝ አልኩና ለጉዞ የያዝኳትን ትንሽ ቦርሳ መሬት ላይ አስቀመጥኩ፡፡ ከዚያም በቀኝ ጎኑ በኩል ማጭድ ተቀምጦ ስለነበር ያንን አንስቼ ቁጭ በማለት እኔም ማጨድ ጀመርኩ፡፡ እሱም እንዲህ ያደርጋል ብሎ አልገመተኝም ነበር መሰለኝ ዐጨዳውን አቋርጦ ወደእኔ በመምጣት የአድናቆት ፈገግታ እያሳየኝ “ኧረ እባክህ ተወው፤ እንግዲህ ይበቃሃል” በማለት አጭድበት የነበረውን ማጭድ ተቀበለኝ፡፡ ዐጨዳውን በመቀጠልም ከላይ የተቀመጠውን ትችት አዘልና ሌሎችንም የቃል ግጥሞችን ሳይሠሥት ነገረኝ፡፡ እኔም በመጨረሻ ላይ አመስግኜው “የደቦ ዐጨዳ አለልህ፡፡” ተብዬ ወደተጠቆመኝ ከቶ ቀበሌ ዳገት ወርጄ፣ ወንዝ ተሻግሬ ወደተባለው ቦታ አመራሁ፡፡

ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ የደረሰ ሰብልን በትጋትና በቅልጥፍና በማጨድ ተግባር ላይ የተሰማራው አርሶ አደር በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ዝነኛና ስሙ የገነነ መኾኑን በሚገባ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ሰብልን ለማጨድ በሚያገለግለው የግብርና መሣሪያ የደረሰ ሰብሉን ማጨዱን ትቶ በዳተኝነትና በልግመኛነት ማጭዱን ወደደረቱ ጠጋ አድርጎ በመታቀፍ ለአፍታም ቢኾን ጊዜውን በከንቱ የሚያሳልፍ ሰው እንዳለ በመጠቆም ገጣሚው አነውሮታል፡፡ ሕይወታቸውን ለማሻሻል ሲሉ በሥራ ከሚታትሩት ጋር እንደዚህ ያለ ሕጸጽ

ያለበትን ሰው ዐብሮ እንዲሾን ማን ቀላቀለው በማለት አባጨጓሬ ሰውነትን ሲነካ የሚሰማውን ዓይነት ስሜት ልግመኛውንም ሰው አእምሮውን ሊያሻክር በሚችል አገላለጽ ተችቶታል።

ቃል ግጥም 153፡- ዐረሙን ካረሙ ከሥሩ መንቀል ነው
ከቆረጡትማ ያው መተካቱ ነው።
(ምልከታ፣ ሀውለት ሙሐመድ፣ 06/01/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ይህንን ቃል ግጥም የነገረችኝ ልጃገረድ በሰቀ ሸንብራ ቀበሌ የምትኖር ሲሾን፣ እሷንም ያገኘኋት ከሰዓት በኋላ ባለው ወቅት ከሌሎች ዐራሚዎች ጋር በመሾን ቀደም ሲል ለታገዘችው ሥራ ወንፈል እያወጣች ሳለች ነበር። ዐብረዋት ያሉትን ዐራሚዎች በሙሉ ስለዐረም የተነገሩ ቃል ግጥሞችን እንዲነግሩኝ በትሕትና ጠየቅኋቸው። ለጊዜው ፈቃደኞች ሾነው አላገኘኋቸውም። ከዚያም እኔ ከሀውለት ጎን ቁጭ ብዬ እንደእነሱው እያረምኩ ሳለሁ ገፋፊ (የሚያነሣሣ) ነገር ማብሰልሰል ጀመርኩ። ቀጥሎም ሁሉም ዐራሚዎች ትናንሽ ቢላዋዎችና ማጭዶች በነፍስ ወከፍ ይዘው ሰለነበር "ለምንድን ነው ቢላዋና ማጭድ የያዛችሁት" ብዬ ጠየቅኋት። እሷም "ዐረሙ ተቆርጦ እንዳይቀር ከሥሩ መንግሎ ለማውጣት ነው" አለችኝ። "ታዲያ ይኼንን በተመለከተ እንኳን የምታውቂውን ግጥም ብትነግሪኝ" አልኳት። ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ዐረሙን እየበጣጠሰና እያጉደፈደፈ ስለሚያርመው አርሶ አደር የሚተቸውን እና ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም የነገረችኝ።

ቃል ግጥሙ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ከቡቃያ ጋር ዐብሮ የሚበቅለውን እና አስፈላጊ ባለመሾኑ የተነሣ ተነቅሎ የሚጣለውን ቅጠልና ሣር ካረሙ ወይም ካስወገዱ አይቀር ከወለል በታች ያለውንም አካል ጭምር ከሥሩ መንግሎ መጣል ነው የሚለውን ሐሳብ አንጸባርቋል። አለበለዚያ ከመሬት በላይ ያለው ከተጎረደና ከተበጠሰ ጉራጅ በሥሩ አማካይነት ምግቡን ከዐፈር ውስጥ የሚያገኝ በመሾኑ ያው እንደቀድሞው በተመሳሳይ መልኩ ተመልሶ ሊወጣ ይችላል። ምክንያቱም ሥር ሲባል የፍጥረት፣ የነገር ሁሉ መጀመሪያ፣ መነሻ ስለሾነ ቀሪው ክፍል ወደታችና ወደላይ በማደግ በቡቃያው ላይ ጉዳት ያደርሳል። ስለዚህ አጥርቶ አለማረም ነውር መሾኑን በቃል ግጥሙ አማካይነት ለዳተኛው አርሶ አደር ተነግሮታል።

ቃል ግጥም 154፡- እኔና አንተ በለፋንበት
ቂጣውን ጠፍጥፋ ትበላለች ሴት
በቶፋ ቀቅላ ትበላለች ሴት።
(ምልከታ፣ ተስፋዬ ጌታቸው፣ 04/11/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ቃል ግጥሙን የነገረኝ አርሶ አደር በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ጤፍ ለመዝራት ማሳውን የመበሸል (ለሦስተኛ ጊዜ የማለስለስ) ተግባር በማከናወን ላይ ነበር። ከእኔ በስተቀር በአጠገቡ ማንም ሰው ስላልነበረ ጠምዶ እያረሰባቸው ያሉትን በሬዎች የቃል ግጥሙ ታዳሚ (አድማጭ) አድርጎ የቆጠራቸው ይመስለኛል። አቶ ተስፋዬ በሬዎቹን ከበላያቸው ላይ በጅራፉ ሾጥ እያደረገ፣ ሲያስፈልግም ላጥ እያደረገ፣ ቃል ግጥሙን ዜማ በተላበሰ ድምፀት ያሰማ ነበር። በሬዎቹም በጅራፉ ይሹን በሰሙት የቃል ግጥም ድምፀት "ኡፍ! ኡፍ! ኡፍ!" እያሉ በፍጥነት ወደፊት ይጓዙ ነበር። እኔም የማረስ ተግባሩን እንዳከናውን በአክብሮት ጠየቅሁት። በፈገግታ "ይሾንልኛል ብለህ ነው?" በማለት ፈቀደልኝና ለአጭር ጊዜም ቢሾን ከላይና ከታች በመላጋት ካረስኩ በኋላ ለእሱው አስረከብኩት።



ፎቶግራፍ ፀሥር፡- በ04/11/2012 ዓ.ም በከለላ ወረዳ የማረስ ተግባር በማከናወን ላይ በነበርኩበት ወቅት።

ከላይ ያለውን ቃል ግጥም እንደምንመለከተው አርሶ አደሩ በመጀመሪያው ስንኝ መነሻ ላይ የተጠቀመው በስም ፋንታ ተተክተው የገቡትን "እኔና አንተ" የሚሉትን ተውላጠ ስሞችን ነው። ቃላቱ ደግሞ በቅደም ተከተል አቶ ተስፋዬን እና በሬዎቹን ይወክላሉ። ስለዚህ ኹለቱም ወገኖች በእርሻም ኾነ በውቂያ ወቅት ቁርም ኾነ ሐሩር ሳይበግራቸው በየዕለቱ ያሉትን ተግባራት ስለሚያከናውኑ "እንዲህ ተንገላትተን ያገኘነውን ምርት እንደፈለገች አድርጋ

የምትጠቀምበት በቤት ውስጥ የምትውለዋ ሴት ናት" በማለት ገጣሚው በቃል ግጥሙ ትችት ሲያቀርብ ተደምጧል።

የታታሪ አርሶ አደር ሚስት ግን ሁለመናዋ ከእርሱ ሥራ ጋር የተዛመደ ሊኾን ስለሚችል በቃል ግጥሙ የተንጸባረቀው ሐሳብ እሷን ይመለከታል ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር የሚያስቸግር ይመስላል። ምክንያቱም ከሕይወት ልምዴ ተነሥቼ የምናገረው ነገር ቢኖር ትጉህ ለኾነችው የአርሶ አደር ሚስት ለእሷ ቀኑ የሚጀምረው ጎሕ ሳይቀድ ነው። ቀደም ባለው ወቅት በነዳጅ የሚሠራ የሞተር ወፍጮ ባልነበረበት ወቅት ሌሊት ተነሥታ እኽል ፈጭታ በመጋገር ቤተሰቧን የምትመግበው እሷው ናት። ሩቅ ቦታ በመጓዝ ውሃ ቀድታ የምታመጣው ይቺው ሴት ናት። ከዚያም ባልዮው በሬዎቹን እየነዳ ወደእርሻ ቦታ ሲኼድ እሷም ቀንበርና ዘር ይዛ ከኋላ ከኋላ ትከተላለች። በሬዎቹን ካጣመደቸው በኋላም እርሱ ሲያርስ እሷ ደግሞ ትጎለጉላለች። በሬዎቹ ሲፈቱም እሷ ቀደም ብላ ወደቤት በመኼድ የተለመደውን የቤቷን ሥራ ያለ ምንም ዕረፍት ታከናውናለች።

በዚህ መሠረት ትችት አዘል ቃል ግጥሙ የተዘመው እንደዚህ ላለችው ንቡት ሴት ሳይኾን ሙያ ለሌላት እና ዘወትር በቤት ውስጥ ለምትውል ለረኽጧ ሊኾን ይችላል። ከዚህ አንጻር ስንመለከተው በቃል ግጥሙ ውስጥ የተሳለቸው ሴት የፈሰሰ ውሃ የማታቀና፣ ምጣድ የለሽ በመኾኗ ባልዮው በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ውስጡ በግኖ ያዜመው ነው ብሎ መናገር ይቻላል። ለዚህ ማረጋገጫው ደግሞ በኹለተኛው ስንኝ ላይ የተቀመጠው "ቂጣውን ጠፍጥፋ ትበላለች ሴት" የሚለው ነው። በመኾኑም ቂጣ ጠፍጥፋ የምትበላ ሴት ምጣድ የሌላት ናት ማለት ነው። ምጣድ ከሌላት ደግሞ እንደሌሎቹ ሴቶች ማቡካትና እንጀራ መጋገር ስለማትችል ያላት አማራጭ ወፍራም የኾነ ሊጥን ባገኘችው ምጣድ በእጇ ወጋ ወጋ አድርጋ (ጠፍጥፋ) በመጋገር መመገብ ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ቃል ግጥሙ ማሰሮ በምትመስል ትንሽ የሸክላ ዕቃ የጥራጥሬ የእኽል ዓይነቶችን እያነፈረች የምትመገብ መኾኗን ያመለክታል። ለዚህም ነው በዝናብም ኾነ በፀሓይ ጧት ላይ በሬዎቹን ጠምዶ እርፋን በአንድ እጁ፣ ጅራፉን በሌላው እጁ ጨበጥ አድርጎ "ና ውጣ! ና ውረድ!" እያለ እስከሚመሽ ድረስ ብቻውን ሲያርስ የሚውል አርሶ አደር እቤት በዋለችዋ ሴት ላይ ከላይ በቀረቡት ሦስቱ ስንኞች አማካይነት ትችቱን የሰነዘረው።

ቃል ግጥም 155፡- እርሻ እንደ ኮሶ እየመረረው
ጠቅልሎ መጉረሥ ማን አስተማረው።
(ምልከታ፣ አደም ሁሴን፣ 06/11/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ሰነፍ የሾነውን አርሶ አደር ማጎበረሰቡ ሀብቱ በሾነው የፉከራ ቃል ግጥሙ ሸንቆጥ እያደረገ መተቸት ልማዱ ነው። የማጎበረሰቡ አባል የሾነው አቶ አደም ሁሴንም እርሻውን በማረስ ላይ እያለ አገኘሁትና የተለያዩ የትችት ቃል ግጥሞችን በቅንነት ነገረኝ። ከእነዚያም መካከል አንደኛው ከላይ የቀረበው ሲሾን፣ ይህም የእርሻ ሥራ አድካሚነት እያንገፈገፋቸው፣ ግን ደግሞ በተገኙበት ቦታ ሁሉ እንጀራን አግበስብሰው በሚመገቡ ሰነፍ ገበሬዎች ላይ የተቀነቀነ ትችት አዘል ቃል ግጥም ነው። ይህ ቃል ግጥም አቶ አደምን በወቅቱ አጋጥሞት ከነበረው ኹነት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚያገናኝ መስሎ ታየኝና ትኩረቴን ሳበው። ይሄውም በጊዜው እኔ በአጠገቡ እንዳለሁ ሰገጥ (መሬት ውስጥ ያለና ለማውጣት የሚያቅት ድንጋይ፣ እንደዚሁም ለመንቀል የሚያስቸግር የዛፍ ሥር) ውስጥ ማረሻው ገባበት። ያንን ለመንቀል ባደረገው እልክ አስጨራሽ ትግል በኹለት እጁ የጨበጠው ዕርፍ ከወዲያና ከወዲህ ሲያላጋው ከቆየ በኋላ ያስቸገረውን ድንጋይ መንግሎ አወጣው። ከዚያም ተግባሩ ሰውነቱን አሞቀውና (የደስታና የኩራት ስሜት ተሰማው) ከላይ የቀረበውን ሒስ ተኮር ቃል ግጥም ፉከራ በተላበሰ ኹኔታ አዚሟል።

በቃል ግጥሙ ወስጥም ለአዝርዕት መዝሪያ የሚሾነውን መሬት ማረስና ኮሶ የተባለውን ጥገኛ ትል ከሆድ ውስጥ ለመግደል ወይም ለማስወጣት ተወቅጦና ተበጥብጦ የሚጠጣው መራራ ፍሬ ጎን ለጎን ተነጻጽረዋል። ስለዚህ እርሻ ማረስ ልክ እንደ ኮሶ የሚያንገፈግፈውን ሰው በአንድ ላይ ሰብስብ አድርጎ እንጀራን መጉረሥ የትኛው ሰው ነው ያስተማረው በማለት ገጣሚው አእምሮን በሚሰቀጥጥ ኹኔታ አነውሮታል። እንኳንስ ሳይሠሩ ይቅርና ሠርተውም ቢሾን "እንዳገኙ መጉረሥ እድኽነት ያደርስ።" የሚለው ብሂልም የቃል ግጥሙን ሐሳብ የበለጠ የሚያጠናክረው መሾኑን ማስተዋል ይገባል።

7.1.3. ፈጣሪን እና ባለሥልጣንን መማጸንን የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞች

በእርሻ ተግባር ላይ የተሰማራው አርሶ አደር በየዕለቱ ሥራዎቹን ሲያከናወን በማወቅም ኾነ ባለማወቅ የተለያዩ ስሕተቶችን ሊፈጽም ይችላል። ምንም እንኳን "ያለፈው አይቆጭህ፤ ለሚመጣው ተጠንቀቅ" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር በማጎበረሰቡ ውስጥ ቢኖርም አርሶ አደሩ ግን በፈጸመው ስሕተት ከጊዜያት በኋላም ቢሾን መቆጨቱ ወይም መጸጸቱ አይቀርም። በቁጭቱም ውስጥ ውስጡን እየተብከነከነ የቃል ግጥሞችን ሊያንጎራጉር ይችላል። ለማስረጃ ያኽልም የኬሚካል ማዳበሪያ ለአዝርዕት ያለውን ጥቅም ቢያውቅም ያለ ማዳበሪያ ዘሩን ዘርቶ ዝቅተኛ የሾነ ምርት በማግኘቱ ለከፋ ችግር መዳረጉን ከዐውድ የተገኘው ቀጣዩ ቃል ግጥም ያመላክታል።

ቃል ግጥም 156፡- ጥቅሙ ከማዳበሪያ መኾኑን እያወቅሁት
እንዲሁ ዘርቼ ችግሬን አዘልኩት፡፡
(ምልከታ፣ ሙሐዬ ሁሴን፣ 04/11/2012፣ ከለላ ወረዳ)

አቶ ሙሐዬ ሁሴን ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም ያዜመው ታላቅ ወንድሙ በሬዎቹን ጠምዶ በትልም በትልም እያደረገ የስንዴ ዘሩን ከዘራ በኋላ እርሻውን በማረስ ላይ በነበረበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ እርሻውን ከሚያርሰው ወንድሙ ኋላ ኋላ እየተከተለ በግራ እጁ ወደደረቱ አስጠግቶ በቁና ከያዘው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በቀኝ እጁ ከቆነጠረ በኋላ ከወገቡ ወደመሬት ጎንበስ ብሎ በፈር በፈሩ ያንጠባጥብ ነበር፡፡ እኔም ስለማዳበሪያ ቀድሞ ከነገረኝ ቃል ግጥም በተጨማሪ ሌላ እንዲነግረኝ ስጠይቀው "እ...እ...እ" ብሎ ጉሮሮውን ለዜማ እንዲያመች ካጠራ በኋላ ከላይ የተቀመጠውን ቃል ግጥም ሊነግረኝ ችሏል፡፡

ከቃል ግጥሙም ለሰብል ተስማሚና ከፍተኛ የኾነ ርባና ያለው፣ እንደዚሁም ከልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች በመዋሓድ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ የሚቀርበው ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ጠቀሜታው ከፍተኛ መኾኑን አርሶ አደሩ ተገንዝቧል፤ በሚገባም ተረድቷል፡፡ ነገር ግን በተደጋጋሚ እያረሰ ባለሰለሰው ማሳ ላይ ማዳበሪያ ሳይጠቀም እኽሉን ቢዘራውም ዘሩ ሙሉ በሙሉ ዐፈሩን ፈንቅሎ በመውጣት ሊበቅል ካለመቻሉም በላይ በሚገባው መጠን ሳይፋፋና ሳያድግ በመቅረቱ አርሶ አደሩ ጥሩ ምርት ማግኘትና ምርታማ መኾን አልቻለም፡፡ በዚህም የሚሰውና የሚቀምሰው ዐጥቶ ለከፋ ችግር መዳረጉን አርሶ አደሩ በቋጠራቸው መንቶ ስንኞች ገልጿል፡፡ በኹኔታውም ተክሏል፤ አዝኗል፤ ዕለት በዕለትም "እህህ" ማለትን ተያይዞታል፡፡ በአጭሩ ጸጸት ውስጥ ገብቷል፡፡ ምናልባት ወደፊት ከፈጸመው ስሕተት ተመልሶ ቤቱን በማሸነፍ ቁጭቱን ይወጣ ይኾን? የሚል ማጣየቂያ ከአድማጮች መቅረቡ አይቀርም፡፡

ከላይ ከቀረበው ሐሳብ በተቃራኒው በመስክ ቆይታዬ ወቅት ያገኘሁት መረጃ የሚያመለክተው ደግሞ አርሶ አደሮቹ ሊበሰብሱ የሚችሉትን የዕፅዋት ቅሪትን እና የሣር በል እንስሳትን ፍግ በውሃ በማዋሓድ በጉድጓድ ውስጥ እንዲብላሉ አድርገው ከቀበሩ በኋላ ብስባሽን (Compostን) ለማዘጋጀት ኹለት ወራትን ይፈጅባቸዋል፡፡ ከዚያም የዘር መዝራት ሥራቸውን ከመጀመራቸው ከአንድ ወር በፊት ያዘጋጁትን ብስባሽ ማሳቸው ላይ እየበተኑ በማረሻ አማካይነት ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት በብስባሹ ውስጥ ያሉት ንጥረ ነገሮች በቀላሉ ለሰብሎች ስለሚደርሱ ምርትን እና ምርታማነትን ለማሳደግ እንደሚቻል ያዘጋጀውን ብስባሽ በማሳው ላይ ሲበትን ያገኘሁት አቶ ሰይድ ሁሴን ገልጸልኛል፡፡ ብስባሹን የማዘጋጀቱ ተግባር ግን ከፍተኛ

የኾነ ጉልበትን ስለሚጠይቅ አድካሚ መኾኑን አቶ ሰይድ አስረድቶኛል። ይህንኑ ኹኔታ በተመለከተ ቀጣዩን የተማጽኖ ቃል ግጥም ነግሮኛል።

ቃል ግጥም 157፡ እባክህ ጌታዬ ጉልበቴን ባርክልኝ
ኮምፖስቱንስ አጋዝኩ እኽሉ እንዲያፈራልኝ።
(ምልከታ፣ ሰይድ ሁሴን፣ 06/11/2012፣ ቦረና ወረዳ)

“እባክህ” የሚለው ቃል አንድ ነገር እንዲኾን፣ እንዲደረግ ለመጠየቅ ወይም ለመለመን ሲፈለግ ከሚጠየቀው ነገር ቀድሞ የሚነገር የልመና ማቅረቢያ መኾኑ ይታወቃል። ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደርም በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ይህንኑ ቃል ተጠቅሞ የሚፈልገው ነገር እንዲኾንለት ፈጣሪውን አጥብቆ ተማጽኗል። ይህንን ኹኔታም በእዝነ ልቦናችን አድምጠነዋል። ምክንያቱም አርሶ አደሩ የተለያዩ ኺደቶችን በማለፍ ያዘጋጀውን ብስባሽ ወደማሳው አንጉዞ በእርሻ መሬቱ ላይ እስከሚበትንበት ወቅት ድረስ ከሚገባው በላይ ያፈሰሰውን ጉልበት የሰማይና የምድር ጌታ የኾነው እንዲባርክለት ማልዶታል። ከዚያም ፈጣሪው ብርታቱን ሰጥቶት የዐፈር ለምነትን ከፍ የሚያደርገውን እና የምግብ እኽል ምርትን ለመጨመር የሚያስችለውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ብስባሽ) አዘጋጅቶ በማሳው ላይ ስለበተነ ሰብሉ ጥሩ የኾነ ምርት እንዲሰጠው አምላኩን በማራራት ጠይቋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢሕአዲግ[30] መንግሥት ሥልጣኑን ከጨበጠበት ወቅት ጀምሮ ትዳር የመሠረቱ ወጣት አርሶ አደሮች ፍትሓዊ በኾነ መንገድ መሬት ተከፋፍሎ ስላልተሰጣቸው በስም ነጻ ይኹኑ እንጂ ልክ እንደጨሰኛ የአባታቸውን የእርሻ መሬት በማረስ ላይ መኾናቸውን የቃል ግጥሞችን በመንገር የተባበሩኝ ወጣቶች ገልጸውልኛል። ወጣት አርሶ አደሮቹ አርሰው ካገኙት ምርትም እንደውለታቸው ሚሶውን ወይም እርቦውን ለራሳቸው ከወሰዱ በኋላ ሌላውን ደግሞ ለአባቶቻቸው ያስረክባሉ። በዚህም ዓመቱን ሙሉ ሊያዘልቅ የሚችል የምግብ እኽል ዕጥረት ስለሚያጋጥማቸው ለረኃብ ይዳረጋሉ። አርሶ አደሮቹ እንደዚህ ያለውን የከፋና የበረታ ችግር ዝም ብለው በአእምሯቸው ውስጥ ዐምቀው አያስቀምጡትም። ሀብታቸው በኾነው ቃል ግጥም ብሶታቸውን በመተንፈስ እፎይ ይላሉ። ይህንኑ እውነታ የሚያመላክተውን የብሶት ቃል ግጥም ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 158፡- አባትም ጥሎን መንግሥትም ጥሎን
ርቦም እናርሳለን ሚሶም እናርሳለን እንኖር ብለን።
(ምልከታ፣ ከማል ዳውድ፣ 06/11//2012፣ ቦረና ወረዳ)

[30] አህጽሮተ ቃሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ማለት ነው።

መረጃውን የሰጠኝ አርሶ አደር በማሳው ላይ በሬዎቹን ጠምዶ እያረሰ ባለበት ወቅት ነበር ያገኘሁት። በዚህን ጊዜ የትዳር ጓደኛው ከኋላ ከኋላ ፈሩን እየተከተለች ማዳበሪያ ታንጠባጥብ ነበር። ለኹለቱም ተገቢውን ሰላምታ አቅርቤ ስጨርስ ከየትና ለምን ዓላማ እንደመጣሁ በዝርዝር ለከማል ገለጽኩለት። ከዚያም በአካባቢው በእርሻ ሥራ ወቅት የሚነገሩ ቃል ግጥሞች ካሉ እንዲነግረኝ በትሕትና ጠየቅሁት። በዘመናዊ ትምህርት ቤት የተማረ ስላልነበር ቃል ግጥም የሚለው ምን ማለት እንደኾነ ለጊዜውም ቢኾን ለከማል ግርታን ፈጥሮበት ነበር። እኔ ግን በዚያው አካባቢ በተለያዩ ዐውዶች የተነገሩኝን ግጥሞች ሳዜምለት ፈገግ ብሎ "እንደነዚህ ያሉትማ መች ጠፍተውኝ" በማለት የተለያዩ ቃል ግጥሞችን አዜመልኝ። በተለይ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም እያቀነቀነ በነበረበት ጊዜ በመንግሥትም ኾነ በአባቱ በደል እንደተፈጸመበት አድርጎ በመቁጠሩ ድምፀቱ የቀረርቶ፣ የመከፋቱን ኹኔታ ለማሳየት ደግሞ ፊቱ ቅጭም ያለ ነበር።

በዚህ *መሠረት* ወላጆች የእርሻ መሬትን ከአብራካቸው ለተከፈሉት ወይም ለወለዷቸው ልጆች ለየብቻቸው ጎልሞ መስጠት ባለመቻላቸው የተነሣ የችግሩ ሰለባ የኾኑት ወጣቶች ራሳቸውን እንደመናኛ ዕቃ የትም ተወርውረው እንደወደቁ አድርገው የቆጠሩ መኾናቸውን በቃል ግጥሙ ተመልክቷል። በጎብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ሥርዓት ማስጠበቅና ግዛትን ማስከበር ዓላማውና ተግባሩ የኾነው መንግሥትም በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት ስላለው በተለያዩ የልማት ዘርፎች ወጣቱን እንዲሰማራ ማድረግ ሲገባው ትኩረት ባለመስጠቱ የተነሣ ለሥቃይ መጋለጡን ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው ግለሰብ አስረድቷል። ከላይ ካለው ቃል ግጥም እንደምንገነዘበውም እንደ ከማል ያሉና የችግሩ ሰለባ የኾኑት አርሶ አደሮች ትዳር መሥርተው ራሳቸውንም ኾነ ቤተሰቦቻቸውን ለማስተዳደር ሲሉ ልክ እንደጪሰኛ ውለታ በመግባት ከአባቶቻቸው የሚታረስ መሬትን ይወስዳሉ። ከዚያም አርሰው፣ ዐርመው፣ ዐጭደውና ወቅተው ካገኙት ምርት እንደውለታቸው አንድ ሦስተኛውን ወይም አንድ አራተኛውን ብቻ እነሱ ወስደው ሌላውን ግን ለወላጆቻቸው ያስረክባሉ። በዚህ ዓይነት ኹኔታ ሕይወታቸውን መምራት የተሳናቸውና በከፋ ሥቃይ ውስጥ የሚገኙ መኾናቸውን ለማሳየት ብሶት አዘል ቃል ግጥሞችን ለማዜም መብቃታቸውን መገንዘብ ይቻላል።

7.1.4. ጠንክሮ የመሥራትን ተገቢነት የሚያመላክቱ ቃል ግጥሞች

ከመስከረም 05 — 09፣ 2013 ዓ.ም በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያስረዳው ማንኛውም አርሶ አደር እስከ ዘር ባለው የእርሻ ወቅት ሌሊቱ ነግቶ የወፎች ዝማሬ ሲደምቅ አርሶ አደሩ የጧቱ ቆፈን ሳይበግረው ከመኝታው በመነሣት በሬዎቹን ከበረት አስወጥቶ ገለባ ያበላል። ከዚያም ምሳውን ከተመገበ በኋላ

ወደማሳው ኼዶ በሬዎቹን በመጥመድ የእርሻ መሬቱን ጠንክሮ ሲያርስ ይውላል። ፀሓይ ስታዘቀዝቅም በሬዎቹን ፈትቶ ከኋላ ከኋላ በመንዳት፣ የእርሻ ዕቃውንም በትከሻው ላይ በመሸከም ወደቤቱ ይመለሳል። የዘር ወቅትም ከሾነና የደረሰ ልጅ ካለው ቀንበር፣ እሱ ደግሞ ሞፈር በመሸከም፣ ዘሩንም በስልቻ በመቋጠር በአህያ ጭኖ ወደእርሻ ቦታው ይኼዳል። ከእርሻ ቦታው ከደረሰ በኋላም በሬዎቹን ጠምዶ ማሳውን በትልም በትልም ከፋፍሎና ዘሩንም በሸማው ላይ አድርጎ ይዘራል። ከዚያም ዕርፋን በአንድ እጁ፣ ጅራፉን ደግሞ በሌላው እጁ ጨብጦ በሬዎቹን "ሳብ፣ ና ውጣ፣ ና ውረድ" እያለ፣ እና እያፏጨ ጅራፉን ከበላያቸው ላይ ሾጥ እያደረገ፣ ሲያስፈልግም ገረፍ እያደረገ የእርሻ ሥራውን በትጋት ያከናውናል።

የትዳር ጓደኛው ንቡት (ባለሚያ) ከሾነች ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን የዕለት ሥራዋን እንዳጠናቀቀች ማሳው የሚቆፈር ነገር ካለው መቆፈሪያዋን በትከሻዋ ላይ በማድረግ ባለቤቷን ተከትላ ወደእርሻ ቦታው ትኼዳለች። ከዚያም ጠንክራ እየቆፈረችና እየጎለጎለች ትውላለች። ማታ ላይም ለቤት ሥራዋ እሷ ቀድማ ወደቤት ስትኼድ፣ ሌሎቹ ደግሞ በሬዎቻቸውን እየነዱ ይከተሏታል። ለችግር የማይፈታው ትጉሁ አርሶ አደር እኽሉ ሲበቅልም ከቡቃያው ጋር ያለውን ዐረም ከቤተሰቡ ጋር ኾኖ በተደጋጋሚ ለማረም ይኼዳል። ከዐቅሙ በላይ ከሾነበትም በማኅበረሰቡ ዘንድ ዋነኛ የመደጋገፊያና የመረዳጃ ሠናይ ተግባራት በኾኑት በደቦና በወንፈል ያሳርማል። ቀጥሎም ሰብሉ በስሎ ለዐጨዳ ሲደርስ ከፍተኛ የኾነ የፀሓይ ሙቀት ባለበት ወቅት እንኳን ሳይቀር አርሶ አደሩ የማጨድ ተግባሩን በየዕለቱ በጥንካሬ ይያያዘዋል። በመጨረሻም በዐውድማ ዙሪያ የከመረውን ክምር ዘርግፎ ፍሬውን ከገለባ ለመለየት በከብቶች ካበራየና በነፋስ አማካይነት ፍሬውን ከገለባ ከለየ በኋላ ምርቱን ሰብስቦ ወደጎተራ ያስገባል። እነዚህን በዐደት የሚተገበሩ የግብርና ሥራዎችን ወቅታቸውን በመጠበቅ በርትቶና ጸንቶ ያከናወነ አርሶ አደር የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ እንደሚችል የቡድን ተኮር ውይይቱ ተሳታፊዎች ገልጸውልኛል። ይሄንኑ ሐሳብ የሚያረጋግጡትን እና የጠንክሮ መሥራትን ተገቢነት የሚያመላክቱትን ቃል ግጥሞች ቀጥሎ እንመለከታለን።

ቃል ግጥም 159፡- ማጭድ ምን ይላል መታዘዝ እንጂ
ቆርጦ የሚጥል ሰውዬው ነው እንጂ።
(ምልከታ፣ አቶ ምትኩ አገኘሁ፣ 22/04/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በጥናቱ በተካለሉት ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮች ዕረፍት አልባ በኾነ ኹኔታ የጤፍ ዐጨዳን ተግባር የተያያዙት በታኅሳስ ወር መጨረሻ ላይ እንደነበር በመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ቃል ግጥሙን ያቀነቀኑልኝ አርሶ አደርም የ76 ዓመት ዐዛውንት ቢኾኑም ጉልበታቸውን ዐጥፈው መሬት ለመሬት እየተንፏቀቁ ያለ የሌለ ዐቅማቸውን ተጠቅመው

ብቻቸውን እያጨዱ ያገኟቸው በታኅሳስ 22/ 2013 ዓ.ም ሐሙስ ዕለት ነበር። ዐዛውንቱ ጥኑና ጠንካራ በመኾናቸው እንጂ የጤፍ ዐጨዳው ሥራ እንኳን ለእሳቸው ቀርቶ ለሌላውም ቢኾን አዳጋች ነበር። ምክንያቱም ከሰብሎች ኹሉ የሚከፋው የጤፍ ዐጨዳ ስለነበር ነው። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ እሳቸው ማጭዱ አንድም ነገር እንደማይናገር ገልጸዋል።

ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከብረት የሚሠራውና እንደ ደጋን ኅበጥ ብሎ በአንድ በኩል እስከ ጫፉ ድረስ ስለት ኖሮት ሣርን፣ ሰብልን፣ ... ለማጨድ የሚያገለግለው ባለእጀታ የግብርና መሣሪያ ግዑዝ ነገር በመኾኑ የተነሣ ነው። የሥራ መሥሪያ የኾነው ማጭድ በእጁ አዳሪ በኾነው አርሶ አደር አእምሮ በሚገዛው እጅ አማካይነት ሲታዘዝ ግን ከመሬት በታች የሚውለውን የሰብሉን ሥር ብቻ በመተው ቆርጦ የሚጥል መኾኑን ቃል ግጥሙን የነገሩኝ አርሶ አደር አመላክተዋል። በኹለተኛው ስንኝ ላይ ደግሞ "ሰውዬው" በሚለው ቃል ጠንካራ፣ ኃይለኛና ብርቱው አርሶ አደር በጧት ቁር የማይፈራ፣ ቀን ላይ ሐሩር የማይበግረው ስለኾነ ለዐጨዳ የደረሰውን ሰብል ጎምዶ ጎምዶ የሚጥል መኾኑን ግጥሙን ያቀነቀኑት አርሶ አደር ገልጸዋል።

ዕድሜው ኻያ ሰባት የኾነው ወጣት ሙስጠፋ የሱፍ ደግሞ በመስከረም 09/ 2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ ከቶ በተባለው ቀበሌ በአረንዛና (ድንጋይ በበዛበት) ቁጥቋጦ ባለበት ማሳ ላይ ነበር ጤፍ ሲያርም ያገኘሁት። ከዚያም ቀኝ እጁን ዘርግቼ ተገቢውን ሰላምታ ካቀረብኩለት በኋላ ስሜን፣ ከየት‌ና ለምን ዓላማ እንደመጣሁ በዝርዝር አስረዳሁት። እሱም እስከ አሥረኛ ክፍል ድረስ የተማረ በመኾኑ በዓላማዬ መሠረት መረጃ በመስጠት እንደሚተባበረኝ ፈገግታ በተሞላበት ኹኔታ ገለጸልኝ። በመቀጠልም የአረንዛውን እና የቁጥቋጦውን አስቸጋሪነት ተመልክቼ "ዐረሙ እንዴት አዋኪ ነው?" በማለት ጠየቅሁት። አቶ ሙስጠፋም "እንዲህ ኾነው ካልሠሩ እስኪጠግቡ ድረስ መብላት የት ይገኛል" አለኝ። የማረሙን ሥራ ሳያቋርጥም በቀኙም ኾነ በግራ እጁ ጣቶች ዐረሙን በኩራት እየነቀለ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ነገረኝ።

ቃል ግጥም 160፡- ሸኮሪና ዐጣጥ ጨብጦ ነቃይ
ከሰው ማሳ ላይ ነጭ ጤፍ አብቃይ።
(ምልከታ፣ ሙስጠፋ የሱፍ፣ 09/01/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ እንደተገለጸው ሸኮሪና ዐጣጥ ትናንሽ እሾኽ ያላቸው የቁጥቋጦ ዓይነቶች ናቸው። በመኾኑም አቶ ሙስጠፋም ኾነ ሌሎች አርሶ አደሮች ዐረማቸውን በሚያርሙበት ወቅት ከአዝርዕታቸው ውስጥ እነዚህን የቁጥቋጦ ዓይነቶች በጣቶቻቸውና በመዳፎቻቸው አስገብተው በመያዝ ነቅለው እንደሚጥሉ ቃል ግጥሙ ያስረዳል። ይህንንም

በማድረጋቸው ከራሳቸው ማሳ አልፈው በሌላው ግለሰብ የእርሻ መሬት ላይ ተፈጭቶና በቀጭኑ ተቦክቶ ሲጋገር ንድፍ የመሰለ እንጀራ የሚኾን የጤፍ ዓይነት እንደሚያመርቱ አቶ መስጠፋ ካዜማቸው ስንኞች መገንዘብ ይቻላል። በእርግጥ የሸኮሪን እና የአጣጥን እሾኽ ነቅሎ መጣል በዘይቤ ረገድ ስንመለከት አርሶ አደሮች ጠንክረው በማረሳቸው፣ በማረማቸው፣ በማጨዳቸውና በመውቃታቸው የተነሣ ከረኃብ፣ ከችግር፣... የተላቀቁ መኾኑን በግጥሙ አማካይነት ጥቁምታ መስጠት ይቻላል።

በወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ ኗሪ የኾነውን አቶ ተሾመ እንድሬን ያገኘሁት ደግሞ በ2012 ዓ.ም በሐምሌ ወር መጀመሪያ ሳምንት ላይ ማሳውን ለጤፍ ዘር ምቹ ለማድረግ ለብሸላ (ለሦስተኛ ጊዜ ለማለስለስ) በሬዎቹን ጠምዶ እርሻውን እያረሰ ባለበት ጊዜ ነበር። በዚህን ወቅት እሱ አርሶ በሌነቱ የኩራት ስሜት የፈጠረበትና የመንፈስ ጥንካሬ የተሰማው፣ በሬዎቹ ደግሞ "እኔ እቀድም፣ እኔ እቀድም" እያሉ የሚፎካከሩ ይመስሉ ነበር። ይህ ዓይነቱ ዐውድ ባለበት ኹኔታ ነበር አቶ ተሾመ ብዙ ከመቀመጥ የተነሣ ለሚፈጠረው የቤት ውስጥ ችጋር ዋነኛ የማቃለያ ወይም የማስወገጃ መንገዱ ጠንክሮ ማረስና ማረም እንደኾነ የሚያመላክተውን ቃል ግጥም እንዲህ በማለት የነገረኝ።

ቃል ግጥም 161፦ ያርሳል በጠራራ ያርማል በጤዛ
ችግር ቤት ይፈታል መቀመጥ ከበዛ።
(ምልከታ፣ ተሾመ እንድሬ፣ 05/11/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

አቶ ተሾመ ካቀነቀነው ቃል ግጥም መገንዘብ እንደሚቻለው ታታሪው አርሶ አደር ኃይለኛ በኾነው የፀሓይ ሙቀት ሳይበገር ለአዝርዕት መዝሪያና ማብቀያ የሚኾነውን የእርሻ መሬት በተደጋጋሚ በማረስ ያለሰልሳል። ከዚያ በኋላም ቢኾን በሣርና በቅጠል ላይ ጧት ጧት ወይም ዝናብ ከዘነበ በኋላ በሚንቆረዘዘው የውሃ ጠብታ (ጤዛ) እጅና እግሩ እየተሰነጣጠቀም ከእኽሉ ጋር የበቀለውን ዐረም በጥንካሬው እየነቀለ ያስወግዳል። በዚህ የተነሣ የተትረፈረፈ ምርትን ስለሚያገኝ ራሱንም ኾነ ቤተሰቦቹን በሚገባ ሊያስተዳድር እንደሚችል ከግጥሙ ለመረዳት አያዳግትም። ከዚህ በተቃራኒው ግን የእርሻ ተግባሩን በወቅቱ ማከናወኑን ትቶ በማይረባ ነገር ጊዜውን የሚያሳልፍ ቦዘኔ አርሶ አደር በምግብ እኽል ዕጦት ምክንያት የሚልሰው የሚቀምሰው የሌለው ድኻ ስለሚኾን ለረኃብ መጋለጡ አይቀሬ ነው የሚኾነው።

ከላይ የተጠቀሰው አርሶ አደር ቃል ግጥሙን ከነገረኝ በኋላ አንዳንድ ጊዜ የበሬዎቹ የአረማመድ ፍጥነት ትንሽ ቀነስ ሲልበት ከልጥ የተበጀውን እና ጫፉ ላይ የተፈተለ ቃጫ ያለውን ጅራፍ ከቀኝ ወደግራ በአየር ላይ በማወዛወዝ "ኺድ" እያለ፣ ሲያስፈልግም በሬዎቹን

በዚያው ሾጥ እያደረገ እርሻውን ማረስ ቀጥሏል። እኔም ከብሸላ በኋላ ያለውን የጤፍ ዘር መቼ እንደሚያከናውን ጠየቅሁት። የእሱ መልስ ደግሞ "የተለመደው ወቅት ከሐምሌ 15 እስከ 30 ድረስ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የጤፍ ዘር ከፍተኛ የኾነ የዝናብ መጠን የሚፈልግ በመኾኑ ነው" የሚል ነበር። ከዚያም እኔ ሳልጠይቀው ራሱን ለሥራው ለማትጋት ሲል ይመስለኛል ልመና አዘል የኾነውን ቀጣዩን የቀረርቶ ቃል ግጥም ሲያዜም በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ለመመዝገብ ችያለሁ።

ቃል ግጥም 162፡- ተው ጎልጉል ገበሬ ተው ጠንክረህ ሥራ
ካልተጎለጎለ አይኾንም አዝመራ።
(ምልከታ፣ ተሾመ እንድሬ፣ 05/11/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ "ተው" የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ተቀንቅኗል። ቃሉ በቁሙ ለኹለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕት ጾታ አንድም ለልመና፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለትእዛዝ አገልግሎት ይውላል። በዚህ መሠረት ከአቀንቃኙ ቅላጼና ከዐውዱ በመነሣት ቃሉ "እባክኽ ወይም በል ተነሥ" የሚል የልመና አንድምታ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። በመኾኑም ገጣሚው "አንተ" በሚል በውስጠ ታዋቂነት የተጠቀሰውን አርሶ አደር ጠንክረህ በመሥራት በዶማ ወይም በማረሻ ከተነቀለው ዐረም ዐፈሩን በማራገፍ ወይም በመጎልጎል ከእርሻው ላይ እንዲታስወግድ በማለት በቃል ግጥሙ አማካይነት በልመና መልክ ሲመክረው እናስተውላለን። ነገር ግን ዐራሙቻው ተጎልጉሎ ከማሳው ላይ ካልወጣ በስተቀር እኽልን ከመሬት ላይ በመዝራት ብቻ አርሶ በሌው የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ እንደማይችል ገጣሚው አመላክቷል። ስለኾነም ማንኛውም በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ሰው ይህንን ዓይነቱን የዋዛ ፈዛዛ (ብላሽ የኾነ) ተግባር የሚያከናውን ከኾነ "አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ" ይኾናል ነገሩ ማለት ነው።

7.2. የሕይወት ሽግግር ሥርዓትን የሚያመለክቱ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ የሚያልፍባቸው ዓበይት የሕይወት ሽግግሮሽ መረገዝ፣ መወለድ፣ መጎርመስ፣ ኩርድና፣ ትዳር፣ እርጅና እና ሞት መኾናቸውን ቀደም ሲል Greenን (1997፡732) በመጥቀስ ለመግለጽ ተችሏል። ከላይ ከተጠቀሱት የሕይወት ሽግግሮሽ መካከል በኩርድና እና ትዳርን ለመመሥረት በሚከናወነው የሰርግ ሥርዓት ወቅቶች ብቻ በተዜሙት የቃል ግጥሞች ላይ ዐውዳዊ ትንተና ለማድረግ ተችሏል። ኾኖም ተፈጥሯዊ መቼትን ተጠቅሞ በሞት ወቅት የሙሾን እና የቀብር ሥርዓቶችን በየዐውዳቸው በድምፅና በምስል መቅረጫ መሣሪያ ለመቅረጽ፣ ሰው ሠራሽና ቅንብራዊ ተፈጥሮንም በአገልግሎት ላይ ለማዋል ባህላዊና ልማዳዊ ተጽዕኖዎች አግደውኛል። በዚህ መሠረት እነዚህን ኹነቶች በተመለከተ በቃለ

መጠይቅና በየወረዳዎቹ ባሉ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሙያተኞች በጽሑፍ በተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ጥናቱ የተገደበ መኾኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

ተፈጥሯዊ ዐውድን መሠረት በማድረግ በኩርድና እና ትዳርን ለመመሥረት በሚከናወነው የሰርግ ሥርዓት ወቅት የተዜሙት የቃል ግጥሞች ይዘታቸው ያተኮረው በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ነው። ውበትን ስለማድነቅ፣ የጠይም ሰው ፍቅር ኃያል መኾኑን ስለመግለጽ፣ በልጅነት ወቅት በተከሠተ ፍቅር ስለመንገላታት፣ የከንፈር ወዳጅን ቤተሰቦች ሰለማወደስ፣ ጀግናን ስለማድነቅ፣ በፍቅር አቻ ስላለመኾን፣ ስለመለያየት አስከፊነት፣ ፈሪን እና ነገረኛን ስለመተቸት፣ ስለጦር መሣሪያ አስፈላጊነት፣ በሕይወት ላይ ስለሚያጋጥም መከፋት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በእነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ሥር በዐውድ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹ በሚከተለው ኹኔታ ተተንትነው ቀርበዋል።

7.2.1. በጉርምስና ዕድሜ ውበትን ስለማድነቅ፣

ውበትን ውስጣዊና ውጫዊ ብሎ መክፈል የሚቻል ቢኾንም ጥናቱ ካተኮረባቸው ወረዳዎች የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ግን አጽንዖታቸውን ያደረጉት በውጫዊ ውበት ላይ ብቻ መኾኑን ለማወቅ ተችሏል። ውጫዊ ውበት ደግሞ መልክን፣ ደም ግባትን፣ በጥቅሉ ላሕይን፣ እንደዚሁም የድምፅን፣ የቅርጽን፣ የአቋቋምን፣ ... ቁንጅና፣ ማማርና የመሳብ ኃይል ያመለክታል። እነዚህን ነገሮች በከፊልም ኾነ በአጠቃላይ አሚልቶ (ታ) የተገኘ (ች) ወጣት አስገራሚ፣ ከፍተኛ ዝና ያለው(ላት)፣ ዕጹብ ድንቅ የተባለ(ች)፣ ዐጀብ ያሰኘ(ች) ይኾናል ማለት ነው። ቀጥሎ ባለው የከንፈር ወዳጅ ግጥም ውስጥ የአንድ ጎረምሳ ውበት እንዴት እንደተገለጸ እንመልከት።

ቃል ግጥም 163፦ ሽንጡ የወር መንገድ የሚያስገሠግሠው
አፍንጫው በስንዝር የማይደረሰው።
...ቱሉ ለሚ ኾኖ ይታያል ወለቃ
አንገቱ ይመስላል የማሽላ መቃ።
ጎፈሬው እንደ ጭድ የተከመረው
እኔ እፈራዋለሁ ማን ብዬ ልጥራው
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ይህ ቃል ግጥም የተገኘው በወግዲ ወረዳ፣ ሌንጮ በተባለው ቀበሌ አቶ ካሳው ይመር ሰርካለም ካሳው የተባለቺውን ሴት ልጃቸውን በሚድሩበት የሰርግ ዕለት ሲኾን፣ ወንዱ ሙሽራና ዐጃቢዎቹ ከዳስ ውስጥ ኾነው መጠጥ ተቀድቶላቸው እየጠጡ ነበር። የሙሽራዋ ጓደኞችም እሷን ለማጫወት የክት ልብሳቸውን ለብሰውና ጸጉራቸውን ተሠርተው ከግቢ ውጭ ኾነው

ዐታሞ እየመቱ ዘፈኑን ያቀልጡት ነበር። በዚህን ወቅት ኩብራ መላኩ የተባለች ልጃገረድ በትከሻዋ ትይዩ በግራ እጇ የያዘችውን ዐታሞ በቀኝ የውስጥ እጇ በመምታትና የ"አያ በለው በለው"ን ዜማ በመጠቀም ከሩቅ በሚጣራው መረዋ ድምፅዋ ዘፈኗን ስትለቀው ጓደኞቿ ደግሞ ከጉልበታቸው ዝቅ፣ እንደገና ቆም በማለት እስክስታ ሲወርዱ ነበር። ከዚህ ጎን በጎን የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጆች ከጓደኞቻቸው ጋር ጽዱ የሆነውን ነጠላቸውን ለብሰውና ክብ ሠርተው በቡድን በቡድን ይደልቁ ነበር።

ከቃል ግጥሙ እንደምንመለከተው በኩብራ መላኩ በተዜመው የከንፈር ወዳጅ የሙገሳ ዘፈን ውስጥ ሽንጥ፣ አፍንጫ፣ ዐንገትና ጎፈሬ የወንድ ልጅ የውበት መለኪያ ሆነው ቀርበዋል። በሙገሳ ዘፈኑም የወጣቱን አካላዊ ውበት ከተፈጥሮ ባሕርይው እጅግ በጣም ንረት ሰጥቶ ለማቅረብ ሲባል ግነታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት አገልግሎት ላይ ውሏል። የዚህ ዋነኛ ዓላማም የጎረምሳውን ውበት ብሩህ አድርጎ፣ አድምቆና አጉልቶ ለማሳየት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መሠረት በመጀመሪያው ስንኝ ላይ በግጥሙ ውስጥ የተሳለው ወጣት ከትከሻው ግርጌ አንሥቶ እስከ ዳሌው አካባቢ ድረስ ያለው ሽንጡ ርዝመቱ ተከታታይነት ያላቸው ሠላሳ ቀናትን ከሚያስጉዝ መንገድ ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። ቀጥሎም የወጣቱ ሰልካካ አፍንጫ ከአውራ ጣት ጫፍ አንሥቶ እስከ መካከለኛ ጣት ጫፍ ድረስ ተከንድቶ ቢለካ ርዝመቱ ፍጹም ሊደረስበት የማይቻል መሆኑ ተገልጿል።

በመቀጠልም ቱሉ ለሚ የተባለው አካባቢና የወለቃ ወንዝ በቃል ግጥሙ ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነዚህ የተጠቀሱት ለቃል ግጥሙ ማካኼጃ ብቻ አይመስለኝም። ወለቃ እንደ የአባይና የየሹም ወንዞች ወግዲ ወረዳን ከማካለሉ በተጨማሪ በክረምት ወራት ጎረምሳዎቹ ከብቶቻቸውን በደረባ በሚጠብቁበት፣ ልጃገረዶቹ ደግሞ ለማገዶ የሚሆን እንጨት በሚለቅሙበት ወቅት የከንፈር ወዳጅነት ፍቅራቸውን የሚወጡበት ምቹ አካባቢ በመሆኑ የተነሣ ነው። ቱሉ ለሚም ቢሆን ውበትን የተላበሱ ወጣቶች መፍለቂያ ነው ተብሎ በመገመቱ እንደሆነ ይገለጻል። በግጥሙ ውስጥ የውበት መለኪያ ሆኖ ለቀረበው ረዥም አንገትም ሰበበ ንጽጽር ተደርጎ የተወሰደው ረዣዥም አንን ያለው የማሽላ አገዳ ነው። ከዚያም ከተከረከመና ከተበጠረ በኋላ የቆመው ጸጉርም ከተቆለለ የጤፍ ገለባ ጋር ተነጻጽሯል። በመጨረሻም ልጃገረዷ በእንደዚህ ያለ ኹኔታ የተፈጥሮ ውበት የተላበሰውን ወጣት ስሙን ለመጥራት እንኳ ድፍረት በማጣቷ የተነሣ እንደተርበደበደች ባዜመችው ዘፈን ለመግለጽ ችላለች።

ኩብራ መላኩ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም አዚማ እንደጨረሰች የዐታሞውን ምት ሳታቋርጥ አንድም ደክሟት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች ጓደኞቿ ዕድል ለመስጠት ፈልጋ ይመስላል

ስም እየጠራች “አንች ዝፈኝ፤ አንቺ ዝፈኝ” በማለት መጋበዝ ብትጀምርም ፈቃደኛ የኾነች ልጃገረድ ልታገኝ አልቻለችም። ስለዚህ እሷው ቀድማ ስታዜምበት በነበረው በ“አያ በለው በለው” ዜማ ቀጣዩን ቃል ግጥም አቀንቅናለች። በዙሪያዋ ያሉት ልጃገረዶችም ቀደም ሲል ያደርጉት እንደነበረው ከጉልበታቸው ዝቅ፣ እንደገና ቆም በማለት እስክስታ ሲወርዱ፣ ጎረምሳዎቹም በፊናቸው ይደልቁ ነበር።

ቃል ግጥም 164፡- ...ጎፈሬው ለሚዶ ካመረልኝ ለእኔ
ትከሻው ለኩታ ካመረልኝ ለእኔ
ጥርሱ ለውቅራት ካመረልኝ ለእኔ
ወገቡ ለዝናር ከተስማማኝ ለእኔ
ዐጥንቱን አልበላው ውሻ አይደለሁኝ እኔ።
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ከላይ ከተተነተነው ቃል ግጥም ጋር በተመሳሰለ ኹኔታ ጎፈሬ፣ ትከሻ፣ ጥርስና ወገብ በውበት መግለጫነታቸው ለዘፈኑ ዋና ምሰሶ ኾነው ቀርበዋል። በዚህ መሠረት የገጸሰቡ ጎፈሬ ከእንጨት፣ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ ለተሠራ ማበጠሪያ የሚስማማ ከኾነ ለልጃገረዷ ሐሜትን የሚያጎናጽፋት መኾኑን መረዳት ይቻላል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የሚኖረው የጎብረተሰብ ክፍል ርቃኑን ለመሸፈን፣ ጎፍረቱን ለመሰወር ሲል ዘወትር ከሚለብሰው ልብስ ሌላ በሰርግ፣ በበዓላት፣ በገበያ፣ በለቅሶ፣ ... ወቅቶች ጸዳ ያሉ፣ አዲስነትም ያላቸው የክት ልብሶችን ይለብሳል። ከእነዚህ የክት ልብሶች መካከልም ኩታ ተጠቃሽ ነው። በዚህ መሠረት ጎረምሳው ኩታ የተባለውን ሸማ በኹለቱም ትከሻዎቹ ላይ ዐጠፍ አድርጎ በሚደርብበት ጊዜ አለባበሱ የሰመረለት ከኾነ የከንፈር ወዳጁም ርካታን ማግኘት የምትችል መኾኑን ለመረዳት አያዳግትም። የፊት ጥርሶቹም ለንቅሳት፣ ወገቡም ከቆዳ የተሠራ ኾኖ ዙሪያውን የጥይት መያዣ ኪሶች ላሉት ዝናር ተስማሚ ከኾነ ደስተኛ መኾን እንደምትችልም ማጤን ይቻላል። ከላይ የቀረቡትን የውበት መገለጫዎች ፈጣሪ አሚልቶ የሰጠውን ወጣት በቀድሞ ጊዜ ይነገር እንደነበረው ዘሩ ወይም ትውልዱ ከሀብታም፣ ከባላባት፣ ከጨዋ ዘር ይኹን አይኹን ልጃገረዷን የሚገዳት ነገር እንዳልኾነ በቃል ግጥሙ ገልጻለች። ምክንያቱም እሷ በሕይወት ዘመኗ በውበቱ ርካታን ታግኝ እንጂ ዐጥንተ ጥሩ በመኾኑ ከጅብ፣ ከተኩላ፣ ከቀበሮ በጥንተ ፍጥረቱ ተለይቶ ከአዳም ዘር (ከሰው) ጋር የሚኖረውን ውሻ ኾና እንደማትበላው በጽኑ አስረግጣ አስረድታለች። በቃል ግጥሙ ውስጥ “ወገቡ ለዝናር ...” ከሚለው ሐረግ የጎብረተሰቡ ፍላጎት ከጦር መሣሪያ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መኾኑንም በድጋሜ ልናስተውል እንችላለን።

ውበትን በተመለከተ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ጎረምሳዎችን ብቻ ሳይኾን ልጃገረዶችንም አወዳሽ ኾነው የቀረቡ ናቸው። ለአብነትም በቦረና ወረዳ፣ 035 ቀያፈር ቀበሌ አቶ በላይ አሰን

እስማኤል በላይ የተባለውን ወንድ ልጃቸውን በመጋቢት 14/ 2013 ዓ.ም በሚድሩበት ዕለት የሙሽራው ዐጃቢዎች ሙሽሪትን ለማምጣት መንገድ ላይ በነበሩበት ወቅት በአቶ መከተ አያሌው "ያሆ ባይነት" ከተቀነቀኑት ስንኞች መካከል ቀጣዮቹን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 165፡- የሣር ውስጥ መንገድ ይመስላል ወገቧ
በምን ያስታውቃል ረኃብ ጥጋቧ
(ምልከታ፣ መከተ አያሌው፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ከላይ ያለው ቃል ግጥም በ"ሆታ" በተከወነበት ወቅት እኔም ተመልካችና በቀጥታም ተሳታፊ ነበርኩ፡፡ የ"ያሆ" ባዮቹ አካኼድ ሶምሶማ (ዝግ ያለና ሰውነትን ለሚሚቅ የሚደረግ የሩጫ ዓይነት) ነበር፡፡ ለሆታው ቃል ግጥሞች ማካኼጃ ከነበሩት ዜማዎች መካከልም "ወርደህ አበባ፤ አዛኸርህ ማነው፣ ያው ትለሜ ነው፤ ወይ ዞማ ዓለም ዓለም፤ እኔ ላንቺ ብዬ፣ ልምጣ ወይ ኮብልዬ፤ አንቺ ዓለም ዓለም፣ የማይልሽ የለም፤ ቆሌ ካማረው፣ ና በለው" የሚሉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የሙሽራው ዐጃቢዎች በሙሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ስለነበሩ በሆታው ወቅት ኹለት ያኽሉ "አህመድ የመዲናው[31]" እንበል የሚል ፍላጎት ነበራቸው፡፡ በዚህን ወቅት ሸማግሌዎቹ ጽዱ የኾነ ነጠላ የለበሱ ሲኾን፣ ጎረምሳዎቹ ግን በኮትና በሱሪ ብቻ ነበሩ፡፡ በሆታው ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉት ማጀቢያዎችም ከጥሩምባ በስተቀር የቀርከሃ፣ የሰፋና የቆሌ ዱላዎች መኾናቸውን በምልከታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ቀደም ሲል ግን በሰርግ ዕለት ከዱላ ማጀቢያ በተጨማሪ ከፍተኛ የኾነ ድምፅ የሚያወጣና በትንፋሽ ብቻ የሚሠራ ጥሩምባ ይነፋ እንደነበር ያነጋገርኳቸው ወጣቶች ነግረውኛል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በሌላ ዐውድ ላይ ጥሩምባ የሆታ ማጀቢያ ኾኖ ማገልገሉን ተመልክቻለሁ፡፡

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ከጸጉር አንሥቶ እስከ ጫማ ድረስ ያሉት አካላት ሁሉ የውበት መለኪያ በመኾን በቃል ይገጠምላቸዋል፤ ይዘፈንላቸዋል፡፡ በተለይ ሴት ልጅ ወንድን ከምትማርክባቸው የውበት መለዮዎች መካከል ጸጉርዋ፣ ዓይኗ፣ ፊቷ፣ ጡቷ፣ ወገቧና ዳሌዋ መኾናቸውን ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከላይ በቀረበው የሆታ ቃል ግጥምም የተሳለቺው ልጃገረድ ወገበ ሸንቃጣ መኾኗ ተገልጿል፡፡ ስለኾነም የልጂቷ የአካል ቅርጽና በሣር ውስጥ ያለች እንደዚሁም ጎነ ሰፊ ያልኾነች የሰዎች መመላለሻ መንገድ ተነጻጽረው ቀርበዋል፡፡ ሰበበ ንጽጽራቸወም መጠን ነው፡፡ ይኼውም ወገበ ቀጪን ልጃገረድና በጣም ጠባብ የኾነች የሰዎች መተላለፊያ መንገድ ማለት ነው፡፡ በንጽጽሩ መሠረት የቃል ግጥሙ አድማጪም የልጂቷን ሸበላነት በዓይነ ኅሊናው ሊመለከት ይችላል፡፡ ይህንኑ የተዋበ አካል የበለጠ አጉልቶ ለማሳየት ልጃገረዷ በዕለት ተዕለት ሕይወቷ በምግብና በመጠጥ ዕጦት

[31] የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወጣቶች የሚያሰሙት የዜማ ዓይነት ነው፡፡

የተነሣ የአካል ጉዳት ይድረስባት ወይም በምግብና በመጠጥ ሆዷ ይሙላ ማረጋገጥ እንደማይቻል በግጥሙ ተንጸባርቋል።

በጎረምሳዎቹ ሆታ ቀርቦ የነበረውን ቃል ግጥም ይዘት በሚያመላክት ኹኔታ አካላዊ ውበትን የተጎናጸፈች ልጃገረድ በተበቸሳ፣ በማገዶ ለቀማ፣ በአክርማና በስንደዶ ቀጨታ፣ በልዩ ልዩ በዓላት ወቅት በጓደኛዋ ልትወደስ ትችላለች። በተከታይ የቀረበው አወዳሽ ቃል ግጥምም በወግዲ ወረዳ፣ በሌንጮ ቀበሌ ሰርካለም ካሳው የተባለቺው ሴት ልጅ በምታገባበት ዕለት በኩብራ መላኩ የተዜመ ሲኾን፣ የውበት መገለጫ ኾኖ የቀረበውም በመሬማ አሊ ጭንቅላት ላይ ረገርምና ብዛት ያለው ጸጉር በመብቀሉ የተነሣ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ከበርካታ ስንኞች መካከል ተቀንጭበው የቀረቡትን ኹለቱን ብቻ እንመለከታለን።

ቃል ግጥም 166፡- ...መሬምዬ ዓሊ ጸጉርሽን ልዋሰው
ሳረገርግ ውዬ ማታ ልመልሰው።
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

የጥናቱ ተተኳሪ በኾኑት አካባቢዎች ያሉት ልጃገረዶች በሰርግ፣ በልዩ ልዩ ክብረ በዓላት ወቅት፣ ወዘተ. የጸዳ ልብስ ከመልበሳቸው በተጨማሪ የሴት ጸጉርን በሚሠሩ ሙያተኞች ሽሩባ በመሠራት ይዋባሉ። ቀደም ባለው ወቅት ግን መደበኛ ትምህርት ቤት ባለመስፋፋቱና አብዛኛዎቹ ልጃገረዶችም የተማሩ ስላልነበሩ፣ አንዳንዶቹ በጭንቅላታቸው መኻል ላይ ያለውን ጸጉር ተላጭተው በዙሪያው የሚቀረውን ደግሞ "ጋሜ" የተባለውን ባህላዊ የጸጉር አሠራር ይሠሩ ነበር። ሌሎቹ ደግሞ በጭንቅላታቸው ጎንና ጎን ያለውን ጸጉራቸውን ተላጭተው ከላይ የሚቀረውን ክፍል "ኮልኮሎ" የተባለውን አሠራር በመሠራት ይዋቡ እንደነበር የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅት ግን ተማሪዎች ይኹኑም አይኹኑም ጋሜና ኮልኮሎ የተባሉትን ባህላዊ የጸጉር አሠራሮች የተው መኾናቸውን በዓይነ ሥጋ ለማረጋገጥ ተችሏል። በመኾኑም በሰርጉ ዕለት በቃል ግጥሙ የተጠቀሰችው ልጃገረድ በጭንቅላትዋ ላይ ብዛት ያለውን እና ረገርም ጸጉሯን ሙሉ በሙሉ ሽሩባ ተሠርታ ነበር። ኩብራ መላኩ ደግሞ ይህ ዓይነቱ ጸጉር ለአንድ ቀን እንኳን ቢኾን ለራሷ እንዲኖራት በከፍተኛ ኹኔታ ተመኝታለች። ለዚህ መፍትሔው ደግሞ ለአንድ ቀን ብቻ ተገልግላ በኋላ ላይ እንዳለ ለመመለስ ቃል በመግባት ተውሳ ለመውሰድ የፈለገች መኾኑንም ከግጥሙ መገንዘብ እንችላለን። በውሰት መልክ ለመውሰዷ በምክንያትነት ያቀረበችውም ከጧት አንሥታ ቀኑን ሙሉ በኩራት አካኼድ ነጠር ነጠር እያለች በመንገዝ ካጌጠችበት በኋላ ፀሓይ ጠልቃ እስከ ጨለማ ባለው ወቅት ወይም ለዓይን ያዝ እስከሚያደርግበት ጊዜ ድረስ የተዋሰችውን ጸጉር ለባለቤቷ ማስረከብ እንደሚኖርባትም ገልጻለች።

7.2.2 የጠይም ሰው ፍቅር ኃያል ስለመኾኑ፣

ከላይ በቀረቡት ቃል ግጥሞች ውስጥ የጎረምሳም ኾነ የልጃገረድ ተክለ ቁመና ማለትም ሽንጥ፣ አፍንጫ፣ ጎፈሬ፣ ዐንገት፣ ወገብ፣ ትከሻ፣ ጥርስ፣ ጸጉር፣ ወዘተ. ዐውዳዊ ትንተና ተካኺዶባቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ልጃገረዶቹ ባዜሟቸው ቃል ግጥሞች አማካይነት ትክለ መልካምነታቸው (የፊት መልካቸው) ጠይም የኾኑ የከንፈር ወዳጆቻቸውን አወድሰዋቸዋል። ለአብነትም በምልከታ ወቅት የሰማኋቸውን ቅንጫቢ ስንኞች ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 167፦ ... ቀይ ሰው ምንድን ነው በርበሬ ይመስል
ጥቁር ሰው ምንድን ነው ዐሻሮ ይመስል
ጠይሙ ይምጣልኝ ዓሳ የሚመስል
(ምልከታ፣ አረጉ ይመር፣ 21/06/2013 ቦረና ወረዳ)

ይህ ቃል ግጥም የተቀነቀነው በቦረና ወረዳ፣ ከቶ በተባለው ቀበሌ፣ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ በምታገባ ዕለት ነው። አቀንቃኟ ደግሞ አረጉ ይመር ስትኾን፣ ሰርገኞቹ ከዳስ ወጥተው የሙሽራይቱን ዕቃ ከተረካከቡ በኋላ ሙሽራይቱ በበቅሎ፣ ሙሽራውም በፈረስ ላይ ኾነው መንገድ በጀመሩበት ወቅት ነው። በዚህን ጊዜ ጥሩምባ እየተነፋ የሙሽራው ዐጃቢዎች በአንድ በኩል፣ የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጆችና ሌሎች ጎረምሳዎች ደግሞ በሌላ በኩል ኾነው ሆታውን ያቀልጡት ነበር። አንዳንድ ሽማግሌዎችም በኹለቱ ቡድኖች መካከል ግጭት እንዳይነሣ “ወደዚያ፣ ወደዚያ ኺዱ” በማለት ይከላከሉ ነበር። ቤተዘመድ የኾኑት የሙሽራዋ ሸኚዎችም ለመደማመጥ በሚያስቸግር ኹኔታ ይጫጫሁ ነበር። ሙሽራውም ነጭ ፈረስ ላይ ኾኖ በሁሉም አቅጣጫ ዐንገቱን እያዟዟረ የታሸገ ከረሜላ እየበተነ ማደሉን ተያያዘው። ይህ አጋጣሚ ደግሞ የእሱ ቀይ ፊት በግልጽ እንዲታይ ያደረገ ስለነበር ቃል ግጥሙን ለማዜም ምቹ ኹኔታን የፈጠረ መኾኑን በምልከታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ይህ ኹነት እየተከወነ ባለበት ወቅት እኔ ደግሞ ፍጹም ተመልካች ነበርኩ። ምክንያቱም ዐውዱ የደመቀ ስለነበር እያንዳንዱ ነገር ሳያልፈኝ በድምዕና በምስል መቅረጫ መሣሪያዎች፣ እንደዚሁም በማስታወሻ መረጃዎችን ለመያዝ በማሰብ እንደኾነ ለመግለጽ እወዳለሁ።



ፎቶግራፍ ዐሥራ አንድ፡- በቦረና ወረዳ፣ ከቶ በተባለው ቀበሌ፣ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ ባገባች ዕለት ሙሽራይቱ በበቅሎ፣ ሙሽራውም በፈረስ ላይ ኾነው መንገድ በጀመሩበት ጊዜ ነው።

በቃል ግጥሙ ውስጥ እንደሚታየው ቀይና ጥቁር መልክ ያላቸው ሰዎች ዝቅ ተደርገው ሲታዩ፣ ጠይሞች ደግሞ ልዕልና ተሰጥቷቸዋል። ምንም እንኳን ውበት እንደተመልካቹ ነው ቢባልም ቀይ መልክ ያለውን ሰው "እጅግ አያምርም፤ ደመ ግቡ አይደለም።" የሚሉ የሰዎችን አስተያየቶች ቃል ግጥሙ የሚያንጸባርቅ ኾኖ ተገኝቷል። ለዚህም ነው የቀዩን ሰው መልክ ለማጣጣል ሲባል "ምንድን ነው" በሚል የጥያቄ ማቅረቢያ ቃል በድልኽ ወይም በዐዋዜ መልክ ከሚዘጋጀውና ሲበሉት ከሚያቃጥለው በርበሬ ጋር መልኩ እንዲመሳሰል ተደርጎ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የተገለጸው።

ጥቁር መልክ ያለው ሰውም ቢኾን ለጠላ መጥመቂያ ከሚኾንና በመጠኑ ዐረር እስኪል ድረስ ከተቆላው የገብስ፣ የስንዴ ወይም የበቆሎ እኽል ጋር በንጽጽር ቀርቧል። ይህም ቢኾን ሰውዬውን መልክ ጥፉ አድርጎ የመቁጠርና ገጽታውንም ዝቅ አድርጎ የማየት ኹኔታ ይስተዋልበታል። ጠይም የሚባለው ሰው ደግሞ በውሃ ውስጥ ከሚኖረውና ለምግብነት ከሚያገለግለው አሳ መልክ ጋር ተመሳስሏል። ይህ ዓይነት መልክ ያለው ሰው ከሌሎቹ ይልቅ በከንፈር ወዳጅነት ለሚመሠረተው ፍቅር ወይም የመሳሳብ ሰሜት በጣም ተመራጭ እንደኾነ ቃል ግጥሙ ያመላክታል። ለዚህም ነው ልጃገረዷ እሷ ወዳለችበት አካባቢ "ጠይሙ ይምጣልኝ" በማለት ቃል ግጥሙን ያቀነቀነችው።

ቀደም ሲል የተተነተነው ቃል ግጥም በተዜመበት ዕለት ቀጣዩ ግጥምም የቀረበ ሲኾን፣ በሦስተኛ መደብ የተጠቀሰውና ጠይም መልክ ያለው ጎረምሳ የከንፈር ወዳጁ የኾነቺውን

ልጃገረድ በንቀት አቃልሎና ዝቅ አድርጎ በመመልከቱ ተገቢ የኾነውን ክብር ነፍጓታል። በዚህ የተነሣ በመኩራራት ጥሏት የኼደ መኾኑን ከመጀመሪያው ስንኝ እንገነዘባለን። ይህንን የልጃገረዷን በደል የተመለከተች ጓደኛዋ ግን ብቀላ እንዲትፈጽምበት የመከረቻት መኾኑን ከቀጣዮቹ ስንኞች መረዳት እንችላለን።

ቃል ግጥም 168፡- ... እኼዳለሁ ሲልሽ መኼድ አታቋርጪው
የሱን ባልንጀራ ጠይሙን ውደጂው።
የሱን ባልንጀራ ጠይሙን ወደሽ
አታነጅውም ወይ ከሆዱ ገብተሽ
ከሆዱ ገብቼ ባነድደው ባነድደው
እኽል እየበላ ውሃ እያበረደው።
(ምልከታ፣ አረጉ ይመር፣ 21/06/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ የቀረቡት ስንኞች በኹለት ገጸሰቦች ምልልስ የተቀነቀኑ ይምሰሉ እንጂ በአረጉ ይመር አንደበት ብቻ የተዜሙ መኾናቸውን በምልከታዬ ወቅት ተገንዝቤያለሁ። በመቅረጸ ድምፅም ለመያዝ ችያለሁ። በስንኞቹ መጀመሪያ ላይ እንደምንመለከተው መካሪ የተባለችው ልጃገረድ ለጓደኛዋ "በከንፈር መሳሳም ብቻ ያፈቀረሽ ጠይሙ ወዳጅሽ ትቶሽ እንደሚኼድ ሐሳቡን ሲገልጽልሽ ተው አትኺድ አትበይው፣ አታስቀሪው። ከዚህ ይልቅ የሱ ጓደኛ፣ አብሮ አደግ፣ ወዘተ. የኾነውን ጎረምሳ አፍቅሪው። በዚህ የተነሣም ጎሊናውን ወይም ልቦናውን በቅናት በማቃጠል አብሺቂው" በማለት ስትመክራት በእዝነ ልቦናችን ለማዳመጥ ችለናል። የጠይሙ ጎረምሳ ኃያል ፍቅር የጠናባት ልጃገረድ ግን የሰጠችው ምላሽ ከውስጡ ገብቼ ባናድደውም፣ ባቃጥለውም በሚመገበው ምግብና በሚጠጣው ውሃ እያበረደውና እያስታገሰው ይገኛል የሚል ነበር።

7.2.3. በልጅነት ወቅት በተከሠተ ፍቅር ስለመጎዳት

እንደሚታወቀው የፍቅር ዓይነቱ ብዙ ነው። ለአብነትም የሀገር ፍቅር፣ የእናት ፍቅር፣ መንፈሳዊ ፍቅር፣ በኹለት ተቃራኒ ጾታዎች መካከል ያለ ፍቅር፣ ወዘተ. ተጠቃሾች ናቸው። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር ግን በከንፈር ወዳጅነት ላይ በተመሠረተ ፍቅር ብቻ ትኩረት ተደርጓል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች የከንፈር ወዳጅነትን የሚመሠርቱት ልጃገረዶች ደግሞ ዕድሜያቸው ከዐሥራ ሦስት ዓመት በላይ የኾኑ፣ ለዐቅመ ሔዋን የደረሱና ያላገቡ ሴት ልጆች መኾናቸው ቀደም ሲል ተገልጿል። ከእነዚህ ሴቶች መካከልም በዕድሜ ያልገፉች ልጃገረድ በለጋ ዕድሜዋ ወቅት በተፈጠረ ከፍተኛ የመውደድ ስሜት የተጎዳች መኾኑን የሚገልጹ ስንኞችን ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 169፡ …አፋፍ ለአፋፍ ስኼድ እጀን እሾክ ወጋኝ
ገና በልጅነት ፍቅር አንገላታኝ፡፡
ገና በልጅነት ጥፍጥሬ ሳኽል
ፍቅር አቀመሰኝ እኽል ይመስል፡፡
(ምልከታ፣ ዘይነባ ሰይድ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ የተዜመው በወግዲ ወረዳ ሌንጮ በተባለው ቀበሌ በነበረው የሰርግ ዐውድ ላይ ሲኾን፣ በምልከታዬ ወቅት እንዳረጋገጥኩት ዘይነባ ሰይድ ቃል ግጥሙን ያዜመቺው በለጋ ዕድሜ ላይ ስለነበረች አልነበረም፡፡ በመኾኑም በሌላዋ ሴት ልጅ ላይ የደረሰው ኹነት ለቃል ግጥሙ መፈጠር ምክንያት መኾኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ከግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ እንደተመለከተው ልጅ እግር የኾነችዋ ሴት በገደል አፋፍ ላይ ስትጓዝ እንደ አጋም፣ ግራር፣ … ባሉ ዕፅዋት ጫፍ ላይ በሚገኝ፣ እንደመርፌ ሹል በኾነና በሚዋጋ እሾኽ መሳዳቷን ብትገልጽም በተምሳሌትነቱ ደግሞ በቀጣይ የፍቅር ሕይወቷ ላይ ክፉ ነገር ሊያጋጥማት እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቀጣዮቹ ስንኞች ደግሞ የራሷን አካል በጥጥ ውስጥ ከሚገኝ አነስተኛ ፍሬ ጋር በማነጻጸር “በልጅነት ዕድሜዬና ለፍቅር ባልደረስኩበት ጊዜ የሚበላና የሚጠጣ ይመስል የከንፈር መሳሳምን ፍቅር ለመጀመሪያ ጊዜ አቅምሶኝ በጣም ተንገላታሁ” በማለት ጉዳቷን ለመግለጽ ችላለች፡፡

በቦረና ወረዳ ከቶ በተባለው ቀበሌ አረጉ ይመር የተባለችው ልጃገረድ ከላይ ከተተነተነው ቃል ግጥም ጋር ተመሳሳይ የኾነ ይዘት ያለውን ግጥም አዚማለች፡፡ ለይዘት ትንተናው አመቺ ናቸው ተብለው የተቀነጨቡትን ስንኞች ቀጥለን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 170፡- የልጅነት ወዳጅ የልጅነቴን
ፍቅር እንደ ዳዊት ያስተማረኝን
ሳይሰናበተኝ ኼደ ድንገቱን፡፡
ትኼዳለህ አሉ ትገሠግሣለህ
ዓይናሙ በእኔ ሞት መች ትመለሳለህ
(ምልከታ፣ አረጉ ይመር፣ 21/06/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ኹለተኛው ስንኝ ላይ መዝሙረ ዳዊት ተጠቅሷል፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት በጠቃሽ ዘይቤ አማካይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ዕሳቤ ወስዶ ለግጥሙ ጭብጥ ማስረገጫ ለማዋል ሲባል እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መዝሙረ ዳዊት ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ አንድ ክፍል ወይም ራሱን ችሎ ያለ፣ በገና ደርዳሪው ንጉሥ ዳዊትና ሌሎች መዘምራን በየጊዜው የደረሱት (የዘመሩት) የጸሎት መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመዝሙረ ዳዊቱ ውስጥ ያለው ጸሎት በሰዎች ዘንድ እንዲሠርጽ ዘወትር እንደሚደገም ሁሉ የቃል

ግጥሙ አቀንቃኝም ልጅ በነበረችበት ወቅት ከንፈሯን በመሳም ብቻ ወዳጅ ያደረጋት ጎረምሳ ከፍተኛ የኾነ የመውደድን ስሜት በልቦናዋ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ ያደረገ መኾኑን ገልጻለች። ነገር ግን ባልታሰበ ጊዜ "ደኅና ሰንብች" ወይም "ደኅና ኹኚ" ብሎ ሳይሰናበት በመለየቱ እጅግ በጣም የከፋት መኾኑን በዐውዱ ውስጥ ካለው አሐድ መረዳት ተችሏል። በመቀጠልም አቀንቃኟ ቶሎ ቶሎ ወይም በፍጥነት ትጓዛለህ ብለው ሰዎች ቢናገሩም "ነፍሴ ከሥጋዬ ትለይልህና ወደእኔ መቼ ተመልሰህ ትመጣለህ?" በማለት ጎላ ጎላ ያሉ ዓይኖች ያሉትን ጎረምሳ በአካል ሳይኾን በመንፈስ ጠይቃዋለች። ለጥያቄዋም አዎንታዊ መልስ እንዲሰጣት "ዓይናሙ" በማለትም አወድሰዋለች።

7.2.4. የከንፈር ወዳጅን ቤተሰቦች ስለማወደስ፣

ትዳርን ለመመሥረት በተከናወነው የሰርግ ሥርዓት ወቅት ልጃገረዶች የውዳሴ ቃል ግጥሞችን ሲያዜሙ በተፈጥሯዊ ዐውድ ለማዳመጥ ተችሏል። ከእነዚህ መካከልም የከንፈር ወዳጅን የሚያወድሱ ግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው ተገኝተዋል። የከንፈር ወዳጁ የቤተሰብ አባላትም የምርቃትን መንፈስ በተላበሰ መልኩ እንደተወደሱ ከዐውዱ ለማረጋገጥ ተችሏል። በተለይም እናት አጊያጊያጧን በማስመልከት ተሸሞንሙና ቀርባለች። የከንፈር ወዳጅ ወንድሞችም በልጃገረዶቹ የዘፈን ግጥም ተወድሰዋል። ለዚህ ርእሰ ጉዳይ ማስረገጫ ከሚኾኑት ቃል ግጥሞች መካከል የተወሰኑ ስንኞችን በመቀንጨብ ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 171፡- ... ሸጌን የወለደ ዘሩ ሽጋ ይኹን
ጧት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን።
(ምልከታ፣ ሰርኬ ይማም፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

እነዚህ መንቶ ስንኞች በቦረና ወረዳ፣ 035 ቀያፈር ቀበሌ እስማኤል በላይ የተባለው ወጣት በሚያገባበት ዕለት ሰርኬ ይማም የተባለችው ልጃገረድ ካቀነቀነችው ዘፈን ተቀንጭበው የቀረቡ ናቸው። ቃል ግጥሙ ቀደም ባለው ወቅት በተለያዩ አጋጣሚዎች በሌሎች ልጃገረዶች የተዜመ ሊኾን ይችላል። ሰርጉ ግን ሰርኬ ይማም ግጥሙን መከወን እንዲትችል ምቹ አጋጣሚን ፈጥሮላታል ማለት ይቻላል። ይሄውም ሙሽራይቱን ለማምጣት ኃላፊነት የተሰጣቸው ሽማግሊዎች ንጹህ የኾነውን ልብሳቸውን ከለበሱና ነጠላቸውን ከደረቡ በኋላ በአካባቢው አጠራር "ከሙሽራይቱ ወላጆች ቤት የመግቢያ መታወቂያ" እየተባለ የሚጠራውን አነስተኛ ርጥብ የወይራ ቅርንጫፍ (ዘለላ) በሙሽራው ቤተሰቦች መኖሪያ አካባቢ ባለው ክፍት ቦታ ላይ በሙሽራው አባት ይታደሉ ነበር። ሽማግሌዎቹም የታደሉትን የወይራ ዘለላውን ማታ ሲመለሱ ለሙሽራው አባት አስረክበዋል። የወይራ ቅርንጫፉ (ዘለላው) ተምሳሌት የሙሽራውና የሙሽሪት

የወደፊት ሕይወታቸው የለመለመ እንዲኾን በማሰብ መኾኑን አቶ አባተ ቦጋለና አቶ እንድሪስ አዳነ ከተባሉት ሽማግሌዎች ጋር በነበረኝ ጭውውት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ የሙሽራው ዐጃቢ ጎረምሳዎችም በበኩላቸው ነጠላ ሳይደርቡ ለዚያ ዕለት ይኾናል ብለው ያሰቡትን ልብሳቸውን ለብሰውና ዱላቸውን ይዘው ተኮልኩለው ቆመው ነበር፡፡ ተክለ ቁመናቸው፣ አለባበሳቸው፣ ዱላ አያያዛቸው፣ ወዘተ. የእነሱን ሽጋነት ስላጎሉላቸው ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለሰርኬ ይማም ቃል ግጥም ማቀንቀን ዋነኛ ምክንያት መኾኑን መገመት ተችሏል፡፡

የሙገሳ ቃል ግጥሙ የቀረበው በጎ ሥራ ለሠራ ሰው “ተባረክ፣ ዕድሜ ይስጥህ” በማለት በሚሰነዘረው የመልካም ምኞት መግለጫ ወይም የምርቃት መንፈስ ነው፡፡ ይኼውም ያማረ፣ ቆንጆ፣ ውብ የኾነ ልጅ የወለደ ሰው “የእሱ የአብራኩ ክፋይ፣ ወገኑ፣ ዘመድ ትውልዱ ሁሉ ሳይቀር ይባረክ፤ ደኅና ልጆች ይብቀሉለት፣ ይበርክቱለት፣ ይብዙለት” የሚለው የመልካም ምኞት መግለጫ በግጥሙ ውስጥ ተንጸባርቋልና ነው፡፡ ምክንያቱም ሽጋ ኾኖ በተወለደው ጎረምሳ የከንፈር መሳሳም ፍቅር የተጠመደችው ልጃገረድ በሐሳብ የተዋጠው ልቦናዋ (ውስን ጊዜው ባይታወቅም) ከማለዳ ጀምሮ የወጣ እስካሁን ድረስ ቀድሞ ወደነበረበት ኹኔት አለመመለሱን ለመግለጽ ችላለች፡፡

ከቤተሰብ አባላት መካከል እናትን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች በተፈጥሮ ዐውድ እንደተሰበሰቡ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የይዘት ትንታኔያቸውን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡፡ እናት ከወለደችው (ቻት) ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት ከፍተኛ የኾነ ፍቅርና ክብር አላት፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እናት በተፈጥሮዋ ደግ፣ ሩኅሩኅ፣ ቸር፣ … በመኾኗ የተነሣ ነው፡፡ በቀጣዩ የውዳሴ ቃል ግጥም ግን የከንፈር ወዳጅ እናት ውጫዊ ውበቷ እንጂ እንደነዚህ ያሉ ውስጣዊ ሰብዕናዎቿ አልተንጸባረቁም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የቃል ግጥሙ ፈጣሪ የኾነችዋ ልጃገረድ በቅርብ ኾና የከንፈር ወዳጇን እናት ውስጣዊ ማንነት ከድርጊቷ በጥልቀት ባለመረዳቷ ነው ብሎ መገመት ይቻላል ፡፡

ቃል ግጥም 172፡-- ---- ቁልቁለቱን ወርዶ ያለ ሰቀላ ቤት
ላይ ላዩን ሸንበቆ ውስጡ ነጋሪት
ኺዱ ተሳለሚት ያይናሙን እናት፡፡

--- የራሷ ወለባ የእጇ ቀለበት
እያደር ያበራል እንደ መስተዋት
እስኪ ጥሯትና ወዲህ ነይ በሏት!
(ምልከታ፣ ሰርኬ ይማም፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ውስጥ እንደተመለከትነው አቀንቃኟ የከንፈር ወዳጇን “ዓይናሙ” ብላ ጠርታዋለች። እናቱ ደግሞ ተዳፋቱን ወርዶ ካለው ሰቀላ ቤት እንደምትኖር ለጓደኞቿ ጥቁምታን ሰጥታለች። ከዚህ በተጨማሪ የሰቀላ ቤቱ የውጪው አካል በሸንበቆ፣ ነጋሪት የተባለው ውስጠኛው ደግሞ እንደ ዋርካ፣ ዋንዛ፣... ከመሳሰሉ የዛፍ ግንዶች ቁራጭ ተፈልፍሎ የተዋቀረ መኾኑንም ገልጻለች። እነዚህን አቅጣጫዎች የጠቆመችበት ምክንያት ሽጋ ለኾነው የከንፈር ወዳጇ እናት ጓደኞቿ ክብር ሰጥተው ያለ ምንም መደናገር ኼደው እንዲሳለሟት ለማድረግ እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል። በእርግጥ መሳለም ቤተክርስቲያንን፣ መስቀልን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ የቁስ እጅን፣ ... በመሳምና እጅ በመንሣት ፈጣሪ ያለውን አምላካዊ ክብር ለመግለጽ ሊኾን ይችላል። በዚህ ቃል ግጥም ግን አሐዱ ለከንፈር ወዳጅ እናት ሰላምታ በመስጠት ከፍተኛ የኾነ ክብርና ሞገስ ማቅረብ የሚለውን አንድምታ ያመለክታል። ከመኖሪያ ቤቷ በተጨማሪ እናትዮይቷ በትክክል እሷ መኾኗን ለማረጋገጥ እንዲቻልም የውዳሴ ስንኞች ተሰናስለው ቀርበዋል። ይሄውም ከብር ወይም ከወርቅ ወይም ከንሐስ፣ ... አሠርታ በጸጉሯ ላይ የሰካችው ወለባዋና የጣት ቀለበቷ እየቆየ ሲኼድ ቀስ በቀስ ያሸበረቀ እንደኾነም ልጃገረዷ ገልጻለች። በመጨረሻም የከንፈር ወዳጇ እናት እንደነዚህ ያሉ መገለጫዎች ያሏት ናትና “ነይ ወደዚህ” ብላችሁ ሰላምታ አቅርቡላት በማለት ለጓደኞቿ መልእክት ለማስተላለፍ ችላለች።

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ ልጃገረዶች አልፎ አልፎ ወንድማማቾችን በከንፈር ወዳጅነት በመያዝ የሚስሙበት አጋጣሚም እንዳለ ለመረዳት ተችሏል። ቀጣዩ ውዳሴ አዘል የኾነው ቃል ግጥም እንደሚያመለክተው አንዲት ልጃገረድ ሽጋ የኾኑ ሦስት ወንድማማቾችን በከንፈር ወዳጅነት ይዛ በፍቅር ወድቃለች። ነገር ግን በየትኛው ላይ ጸንታ መቆም እንዳለባት ለመወሰን አቅቷታል። በዚህም ግራ ተጋብታለች። ከሦስቱ ወንድማማቾችም ፍቅሯን የሚያስጨርሳት የትኛው እንደኾነ በቀጣይ ካሉት ስንኞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 173፡- ... አፋፍ ላፋፍ ስኼድ አገኘሁ ሪጋ
ሁሉም ሽጋ ናቸው በማንኛው ልርጋ።
ልቤ እንደ ቀለበት የሚዋልለው
ለትንሹም አይደል ለትልቁ ነው።
ትልቁም ደግ ነው ትንሹም ደግ ነው
ፍቅር አስጨራሹ መካከለኛው ነው።
(ምልከታ፣ ሉባባ አስፋው፣ 21/06/2013፣ቦረና ወረዳ)

ይህ ቃል ግጥም ከቶ በተባለው ቀበሌ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ በምታገባ ዕለት በሉባባ አስፋው የተዜመ ነው። ቀድማ የፍቅር ዘፈን ስትዘፍን የነበረችው አረጉ ይመር የድካም ስሜት የተሰማት መኾኑን የተመለከተቺው ሉባባ አስፋው አታሞውን አፈፍ አድርጋ በመውሰድ በ“አያ

በለው በለው" ዜማ ከላይ ተቀንጭቦ የቀረበውን ቃል ግጥም ስትዘፍን ተከታትያለሁ። በዕለቱ የሙሽራዋ የከንፈር ወዳጆችና የአካባቢው ጎረምሳዎች በምድብ በምድብ በመኾን ነጠላቸውን ተከናንበወና ዱላቸውን ትከሻቸው ላይ አድርገው የልጃገረዶችን የፍቅር ዘፈን በሞቀ ድልቂያ በማጀብ ላይ ነበሩ። ሉባባ አስፋው ግጥሙን ለማቀንቀን ያነሣሣት ከጎረምሳዎች መካከል የከንፈር ወዳጅ ያደረጓትን ሦስት ወንድማማቾች በዓይነ ሥጋዋ መመልከቷ ሊኾን ይችላል የሚል ሐሳብ አለኝ።

አቀንቃኟ በተራራ ወይም በኮረብታ ጫፍ ላይ ስትኼድ በነበረችበት ጊዜ "ሪጋ" የተባለውን የጥርስ መሚጫ እንዳገኘች ገልጻለች። ሪጋው ደግሞ ኹለት ፋይዳዎች አሉት። አንደኛው በሪጋው ጥርሷን በሚገባ ካጸዳች በከንፈር መሳሳም ወቅት አፏ ለከንፈር ወዳጆቿ አፍንጫ መልካም መዓዛ እንዲኖረው የሚያደርግ ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ ሪጋ አባጣ ጎባጣ ያልኾነ፣ ቀጥ ብሎ ረዘም ያለ በመኾኑ የከንፈር ወዳጆቿ ተክለ ቁመና ሽጋ (የተዋበ) መኾኑን ለማመላከት፣ እንደዚሁም የወደፊት ሕይወቷ ቀና እንዲኾን ምኞቷን ለመግለጽ ነው። በመኾኑም ሦስቱም የከንፈር ወዳጆቿ በጣም የሚያማምሩ በመኾናቸው በየትኛው ጸንታ መቆም እንደምትችል ለመወሰን ተቸግራ ነገሩ ሁሉ ግራ ኾኖባታል። በዚህ የተነሣ አእምሮዋ አንዱ ወዳጇ ላይ ረግቶ መቀመጥ አልቻለም። በኋላ ላይ ግን ታላቁም ኾነ ታናሽ ወንድማማቾቹ መልካም፣ ቁም ነገራም፣ ዐጥንታቸውን የሚቆራጭቸው (የሚዛማዷቸው) ቢኾኑም ከፍተኛ የኾነውን የፍቅር ስሜት የሚያስጨርሳት ግን መካከለኛው እንደኾነ በመጨረሻ ላይ በአጽንዖት ገልጻለች።

7.2.5. ጀግናን ስለማድነቅ፣

ጀግና ማለት ለሀገርና ለወገን መሥዋዕትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር ያከናወነ፣ ወኔን፣ ድፍረትን፣ ወዘተ. በሚጠይቅ ኹኔታ ላይ ጀብዱ የሠራ ነው በማለት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣488) ተገልጿል። ከዌብ ሳይት በተገኘው መረጃ መሠረት ደግሞ ስድስት የጀግንነት ዓይነቶች አሉ። አንደኛው/ አካላዊ ነው። ይህም አብዛኛው ሰው አስቀድሞ የሚያሰበውና በጉልበትና በአካላዊ ጥንካሬ ላይ የተመሠረተ ነው። ኹለተኛው/ ማኅበራዊ የሚባለው ሲኾን፣ ኀፍረትን ወይም ገለልተኝነትን፣ መጠላትን ወይም ተቀባይነት ማጣትን፣ ወዘተ. ቆርጦ መቋቋም የሚችል ነው። ሦስተኛው/ አእምሯዊ የተባለው ቀስቃሽ በኾኑ ሐሳቦች የሚሳብ፣ አስተያየቶችን የሚመረምር፣ ስሕተትን ከመሥራት የሚቆጠብ ሰብእና ያለው ነው። አራተኛው/ ግብረ ገባዊ ሲኾን፣ ትክክለኛ የኾነውን ነገር በመሥራት አቋሙ የጸና ነው።

አምስተኛው/ ስሜታዊ የተባለው ደግሞ አሉታዊ ነገር ሲያጋጥም ታግሎ የሚያሸንፍ፣ መጠነ ሰፊ ለኾኑ አዎንታዊ ስሜቶች፣ አስተያየቶች፣ ወዘተ. ልቦናውን ክፍት የሚያደርግ ነው። በተጨማሪም ከደስታ ጋር ይዛመዳል። ስድስተኛው/ መንፈሳዊ የተባለው ሲኾን፡- ሃይማኖትም ኾነ ሃይማኖት ባልኾኑ ጉዳዮች ላይ እምነትን፣ ፍላጎትን፣ ትርጉምን በተመለከተ በጥያቄዎች መፋጠጥ ሲፈጠር ጥንካሬን እና ብርታትን አግኝቶ ማሸነፍ የሚችል ማለት ነው (http://www.lionswhiskers.com/p/six-types-of-courage.html)። በዚህ መሠረት ከመስክ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች አካላዊ በሚባለው የጀግንነት ዓይነት የሚመደቡ ናቸው። ምክንያቱም ወኔን፣ ድፍረትን፣ አካላዊ ብርታትን እና ጥንካሬን የሚያመለክቱ ኾነው በመገኘታቸው ነው። ለአብነትም ተከታዮቹን የቁልምጫ ቅንጫቢ ቃል ግጥሞች እንመልከት።

ቃል ግጥም 174፡- የብር እንኩትኳች የብር እንኩትኳች

የእኔ እስማኤል በላይ በእንብርክኩ መካች።
መሸ ወይ መሸ ወይ ተዘጋ ወይ በሩ
ኧረ በምን ምክንያት እነ አለቤ ቀሩ።
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ከልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች መካከል አንዳንዶቹ የመጀመሪያው ስንኞቻቸው ከሌሎቹ ተከታታይ ስንኞች ጋር የሐሳብ ተዛምዶ ላይኖራቸው ይችላል። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም የታየው ይሄው እውነታ ነው። ምክንያቱም ብር የተባለው የወረቀቱ ገንዘብ ሳይኾን ጠገራው ነው። ይሄ ደግሞ መዳብ፣ ኒኬልና ንሐስ ያልኾነ፣ ለመገበያያነት ሲውል የነበረ ክቡር ገንዘብ ሲኾን፣ ከዐፈር ተነጥሮ የሚወጣ፣ ደረጃው ከወርቅ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ነጭ የማእድን ዓይነት ነው። ብር የሚለው አሐድ በገባበት ዐውድ ባለው ትርጉም መሠረት የወጣቱን መልክ በንጽጽር ለመግለጽ ታስቦ ነው ቢባል እንኳን እንኩትኳቹ (ደቃቃው) ብርስ የሚለው ደግሞ ሌላ ማጠየቂያ ያስነሣል። በዚህ መሠረት ስንኙ ከተከታዮቹ ጋር ምንም የሐሳብ ግንኙነት የለውም ማለት ይቻላል።

ምንም እንኳን በተለያዩ የመከወኛ አጋጣሚዎች በልጃገረዶቹ በሚዘፈኑት የቃል ግጥም ዘፈኖች ውስጥ የጎረምሳዎቹ ስም በሙገሳ ቢነሣም ቋሚ ግን አይደለም - በአንዱ የመከወኛ አጋጣሚ "ተፈራ" ተብሎ እንደኾነ በሌላ አጋጣሚ በዚያው ቃል ግጥም ውስጥ "ታደሰ" ሊባል ይችላል። በዚህ መሠረት በተለያዩ አጋጣሚዎች በኹለተኛው ስንኝ ላይ የተለያዩ ጎረምሳዎች ስማቸው እየተነሣ ቢወደሱም በመጋቢት 14/ 2013 ዓ.ም ላይ በነበረው የሰርግ አጋጣሚ ላይ ደግሞ አሚናት ጌታሁን ባዜመችው ዘፈን "እስማኤል በላይ" ተወድሷል። በዚህ አጋጣሚ አሚናት እስማኤልን ያወደሰችበት መነሻ ምክንያት አላት። ምንም እንኳን ቀደም ባሉት ጊዜያት

የእስማኤል ጀግንነት በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ የታወቀ ሊኾንም ላይኾንም ይችላል። በሰርጉ ዕለት ግን በሽማግሌዎቹና በዐጃቢዎቹ መካከል ደምቆ በመታየቱ የተነሣ ነው ቃል ግጥሙን ባዜመችው ልጃገረድ መወደስ የቻለው የሚለው ሐሳብ ሚዛን የሚደፋ ይመስለኛል። የጀግንነት ውዳሴው ያተኮረው ደግሞ እስማኤል ባላጋራው በያዘው ዱላ እንዳይመታ በጉልበቱ መሬት ላይ ተንበርክኮ መከላከል ወይም መቋቋም እንደሚችል በማስገንዘብ ነው።

ቃል ግጥሙን ያዜመችው ልጃገረድ በወቅቱ በአካባቢው የተሰበሰቡትን ጎረምሳዎች በዓይኗ ከቃኘች በኋላ "አለቤ" እና ሌሎች ጎረምሳዎች (አለባቸውና ወንድሞቹ ማለት ነው) እንደሌሉ ለማረጋገጥ ችላለች። ከዚያም እነሱ ሊቀሩ የቻሉበትን መሠረተ ነገር (ምክንያት) ለማወቅ ጥያቄ ስታቀርብ ተደምጣለች። እነአለባቸው የቀሩበት መንሥኤ ጊዜው መሸቶ፣ የግቢው መውጫና መግቢያ በር ተዝግቶ ሳይኾን ልጃገረዷም ኾነች ተደራሹ ጠንቅቀው የሚያውቁት ሐቅ ያለ መኾኑን እኔ ጠይቄ ባገኘሁት መረጃ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ይሄውም አለባቸው ከነወንድሞቹና የሚያገባው እስማኤል በላይ በአንድ መንደር ከመኖራቸው በተጨማሪ አያት ወለዶች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ እስማኤል በላይ የሚያገባት በእነአለባቸው አባት አማጪነት የአጎታቸው ልጅ (የአባታቸው የታናሽ ወንድሙ ልጅ) ናት። በዚህ መሠረት አለባቸው ከወንድሞቹ ጋር በአጎታቸው ሰርግ ላይ ለመታደም በመኼዳቸው ምክንያት እስማኤልን ሊያጅቡት አልቻሉም። ይህንን እውነታ ደግሞ አቀንቃኟን ጨምሮ በዕለቱ በሰርጉ ላይ የታደመው ሁሉ በሚገባ የሚያውቁት ጉዳይ ነበር።

ተከታዩ ቃል ግጥም የተገኘው ሰርካለም ካሳው የተባለች ልጃገረድ በምታገባ ዕለት በተከወነው ተፈጥሯዊ ዐውድ ሲኾን፣ ቦታውም በወግዲ ወረዳ ፣ሌንጮ በተባለው ቀበሌ ነው። የቀበሌው መልክዓ ምድር አቀማመጥ በጣም ዝቅተኛና ሞቃታማ መኾኑን በአካል ተገኝቼ አረጋግጫለሁ። አካባቢው የሹም ለተባለው ወንዝ ቅርበት ስላለው በተለይም በክረምት ወራት በቂ የኾነ የግጦሽ ሣር የሚገኝበት ነው። ይህ በመኾኑም የአካባቢው ጎረምሳዎች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ደረባ ቤት በመሥራት ፍየሎችን ጨምሮ እንደ በሬና ላም ያሉ የቀንድ ከብቶች የማርባት ሥራ ያከናውናሉ። በዚህን ጊዜ ጎረምሳዎቹ ከየቤተሰቦቻቸው ካመጡት ዱቄት ራሳቸው ቂጣ ከጋገሩ በኋላ ከላሞቻቸው ባለቡት ወተት ፉት እያሉ ይመገባሉ። አልፎ አልፎ ደግሞ የረጋውን ወተት በባህላዊ መንገድ ገፍተው ቅቤውን ካወጡ በኋላ የጋገሩትን ቂጣ በአሬራው እያማጉ ይበላሉ። ከዚህ ውጭ ግን የየሹም ወንዝ ከደፈረሰ ጎረምሳዎቹ ውሃ ሲጠማቸው አሬራውን ይጠጣሉ። ይህ ኹነት ለቀጣዮቹ ስንኞች መፈጠር ዓይነተኛ ምክንያት ኾኗል ብሎ መውሰድ ይቻላል።

ቃል ግጥም 175፡- ... አሬራ ጠጥቶ ካልሰከረ በቀር
የሼግዬን ወዳጅ አይነካም ባላገር፡፡
አሬራ ጠጥቶ ሆዱን ለነፋው
አባ ስበር መንዝር መድኃኒቱ ነው፡፡
(ምልከታ፣ አሚናት ጌታሁን፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ውብ የሾነውን ወጣት የከንፈር ወዳጅ የሚደፍር ጎረምሳ ካለ አሬራ (ወገሜት) ጠጥቶ በመስከር የሚሠራውን ነገር መቆጣጠር ያቃተውና ጎሊና ቢስ እንደሾነ ነው እንጂ ያልሰለጠነና ቅልጥፍና የሌለው ሰው ሊሾን እንደማይችል ተገልጿል፡፡ በዚህ መሠረት አሬራ በአንድ በኩል የአልኮል መጠጥን ባሕርይ ተላብሷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቀጥታ በተነገረው ሐሳብ ሳይሾን ተቃራኒ የሾነውን ትርጉም በሚያሳይ ምፀታዊ ስልት ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም አሬራ ጠጥቶ አካሉ የገዘፈውን እና የተወጣጠረውን ጎረምሳ “አባ ስበርና አባ መንዝር” እየተባሉ በአካባቢው በሚወደሱት ጀግና ወጣቶች ርምጃ እንደሚወሰድበት በቃል ግጥሙ ውስጥ ተገልጿል፡፡ እዚህ ላይ “አባ” የሚለው ለብቻው ወንድ መነኩሴን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል መሾኑ ይታወቃል፡፡ አሐዱ ግን በግጥሙ ውስጥ ባለው ዐውድ ከስሞች ጋር በመጣመር ጀግንነትን እንዳንጸባረቀ መረዳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን በሌሎች አካባቢዎች አባ ስበርና አባመንዝር የሚሉት ስሞች የፈረስ ስሞች ሊሆኑ ቢችሉም በዚህ ዐውድ ግን ጀግንነትን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

ከመስክ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ጀግናን በማወደስ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ የልጃገረዶቹ የቃል ግጥም ዘፈኖች “በለው በለው” የሚሉ ናቸው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ፈሪን የሚነቅፉ፣ የሚያጥላሉ ሾነውም ተገኝተዋል፡፡ ለአብነትም በየካቲት 21/ 2013 ዓ.ም ከቶ በተባለው ቀበሌ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ በምታገባ ዕለት አረጉ ይመር ስታዜም የነበረውን ቃል ግጥም በኢ - ንቁ ተሳታፊነት አዳምጩ በማስታወሻዬ ያሰፈርኩትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 176፡- ረዥም ግራር ላይ ይሰቀላል ቀፎ
የዓይናምዬን ወዳጅ በለው በወጨፎ፡፡
እንኳን በወጨፎ ድገመው በዱላ
አምስት ብር እንጂ ሌላም አትበላ፡፡
ያቺን አምስት ብር እኔ እከፍላታለሁ
ፈሪና ጀግናውን እኔ እለይበታለሁ፡፡
ፈሪና ጀግናውን እንዴት ልለየው
አሜሪካ ለብሶ ሆይ ሆይ የሚለው፡፡
አሜሪካ ለብሶ ሆይ ሆይ ከማለት
አቡጀዲውን ለብሶ ወርዶ መመከት፡፡
(ምልከታ፣ አረጉ ይመር፣ 21/06/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ካሉት አርሶ አደሮች መካከል አንዳንዶቹ ቁመታቸው በጣም ትላልቅ በኾኑ ዛፎች ላይ ከሸንበቆ፣ ከሐረግ ወይም ከቀጫጭን እንጨቶች ተወሳስቦ የተሠራ ባዶ ቀፎ (የንብ ቤት) ይሰቅላሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ንቡ አንድም ቀድሞ የነበረበት ቀፎ ሳይመቸው ቀርቶ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእርባታ ወቅት ለቆ ሲኼድ እንዲገባበት ለማድረግ ነው፡፡ በዕለቱ በምልከታዬ ወቅት እንደተመለከትኩት በግጥሙ ውስጥ ግራር የተጠቀሰው በአካባቢው በብዛት የሚበቅል የዛፍ ዓይነት በመኾኑ ብቻ ነው እንጂ ሌሎች ረዣዥም ዛፎችም ለዚሁ አገልግሎት ይውላሉ፡፡ ይህን ሐሳብ የያዘው የመጀመሪያው ስንኝ ከቀጣዮቹ ስንኞች ጋር መሰናሰል አይታይበትም፡፡ ይህ ደግሞ የአንዳንድ የልጃገረድ ቃል ግጥሞች መገለጫ እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

በኹለተኛው ስንኝ ላይ እንደምንመለከተው ጎላ ጎላ ያሉ ዓይኖች ያሏት ልጃገረድ ተጠቅሳለች፡፡ የእሷን የከንፈር ወዳጅ የኾነውን ጎረምሳ በቀድሞ ጊዜ አምስት ጎራሽ በኾነውና ወጨፎ በሚባለው የጣሊያን የጠብመንጃ ዓይነት “ተኩሰህ ምታው” በማለት አቀንቃኟ ምናልባትም ለልጃገረዲ እጮኛ ለኾነው ወጣት መልእክት ስታስተላልፍ በእዝነ ጆሯችን መስማት ችለናል፡፡ በጠብመንጃ የተመታው ሰው በሕይወት ይኑርም ይሙትም ሳይታወቅ “በዱላ ድገመው” በማለት አደፋፍረዋለች፡፡ ይህን ዓይነቱን ጀብዱ የፈጸመ ጀግና በአካባቢው ባህል መሠረት ለተበዳዩ ግለሰብ የሚከፍለው ካሳ[32] አምስት ብር ብቻ እንጂ ከተለመደው ውጭ ሌላ ተጨማሪ ነገር እንደማይሰጥ አስረድታዋለች፡፡ “ካሳ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም” በማለት ፈራ ተባ ቢል እንኳን አምስቷን ብር እሷ እንደምትከፍል የዘፈኑ አውራጅ ገልጻለች፡፡ በዚህ ድርጊቷም ፈሪውን እና ጀግናውን መለየት እንደምትችል አመላክታለች፡፡ በሰባተኛው ስንኝ ላይ ግን ብጥብጥ ባለበት ዐውድ ጀግናውን፣ እንደዚሁም ድፍረት የሌለውን እና ፈሪውን ጎረምሳ መለየት ባለመቻሏ ግራ መጋባቷን አመላክታለች፡፡ ቆየት ብላ ግን በቀድሞ ጊዜ በአካባቢው አጠራር “አሜሪካ” እየተባለ የሚጠራውን እና ቅጠልማ ቀለም ያለውን ካኪ ልብስ ለብሶ “ሆይ ሆይ” በማለት ሌላውን ወጣት ለብጥብጡ የሚገፋፋውን ጎረምሳ ስትነቅፈውም ተስተውላለች፡፡ ከዚህ ይልቅ አቡጀዲ የተባለውን ልብስ ለብሶ በዱላው እየመከተ ባላጋራውን ማጥቃት እንደሚገባው አስረድታለች፡፡ በዚህን ወቅት በቦታው የተገኙት ጎረምሳዎች በእግራቸው መሬቱን እየመቱ በመደለቅ ከወናውን ሲያደምቁት ተመልክቻለሁ፡፡

[32] በአሁኑ ወቅት ለተደበደበ ሰው እንደጉዳቱ መጠን ከፍተኛ የኾነ ካሳ፣ በሰው እጅ ሕይወቱ ለጠፋ ሰው ደግሞ እስከ 0ርባ ሺህ ብር የነፍስ ዋጋ እንደሚከፈል አቶ አራጋው ሐሰን በመጋቢት 04/ 20112 ዓ.ም ገልጸውልኛል፡፡

7.2.6. በፍቅር አቻ አለመኾን፣

በተለያዩ ኣጋጣሚዎች በልጃገረዶች ከሚቀነቀኑት የቃል ግጥሞች መካከል አብዛኛዎቹ በከንፈር መሳሳም ብቻ በተመሠረተ የፍቅር፣ የመሳሳብ ስሜት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ መኾኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። የጥናቱ ተተኳሪ በኾነው ማኅበረሰብ ባህል መሠረት ልጃገረዶች የከንፈር ወዳጆቻቸውን ለመምረጥ ዕድሉ የላቸውም። በመልክም ኾነ በትክለ ሰውነታቸው ቆንጆ የኾኑ ሴት ልጆች ግን ለከንፈር ወዳጅነት በጎረምሳዎች የመመረጥ ዕድላቸው በጣም ከፍተኛ ነው። በዚህ ዓይነት ኹኔታ የሚመሠረተው ፍቅር እውነተኛ፣ ከልብ የሚመነጭና ትክክለኛ ስሜትም የሚንጸባረቅበት ይኾናል ተብሎ ይታሰባል። በመኾኑም ጎረምሳውም ኾነ ልጃገረዷ ዘወትር የሚታያቸው ያፈቀሩት ሰው ስለኾነ ሌትም ኾነ ቀን እሱን ወይም እሷን በማሰብ ነው የሚውሉትና የሚያድሩት። ነገር ግን በቁንጅና፣ በትክለ መልካምነት፣ በዕድሜ፣ በሀብት፣ ወዘተ. በእኩል ደረጃ የማይገናኙ ከኾኑ ፍቅራቸውም ቢኾን አቻነት አይታይበትም። ይሄንኑ ሐሳብ ለማስረገጥም በምልከታ ያገኘሁትን የፍቅር ግጥም ቀጥሎ እንመልከት።

ቃል ግጥም 177፡- ዕንጨት ሰባብሬ እድንጋይ ላይ ቁጭ
ያንተ ወዳጅነት ቢቀርም አይቆጭ።
ትታዘበኛለህ ያንተን ያኽል ባጣ
በጠይሙ ጠይም በቀዩ ቀይ ላምጣ።
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ቀደም ሲል የማገዶ እንጨት መልቀሚያ ቦታዎች ለልጃገረዶች የቃል ግጥም መከወኛ ምቹ ኣጋጣሚዎች እንደኾኑ ለማየት ችለናል። በወግዲ ወረዳ ሌንጮ በተባለው ቀበሌ የሚገኘው የየሹም ወንዝ አካባቢም ልጃገረዶች የማገዶ እንጨት የሚለቅሙበት ቦታ ስለኾነ ከላይ ለቀረበው ቃል ግጥም መከወኛ መልካም ኣጋጣሚ ኾኗል ማለት ይቻላል። የልጃገረዶቹ ቃል ግጥሞች በእንደዚህና በሌሎችም የመከወኛ ኣጋጣሚዎች የተፈጠሩ ቢኾንም ድንበር ሳይገድባቸው በተለያዩ ዐውዶችም ሊከወኑ ይችላሉ። ለአብነትም ሠርካለም ካሳው በምታገባ ዕለት ኩብራ መላኩ የተባለችው ልጃገረድ መረዋ በኾነው ድምፅዋ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም በአታሞ ዐጅባ ስታቀነቅን በአካል ተገኝቼ በማዳመጥ በማስታወሻ ለመያዝ ችያለሁ። በወቅቱ በነበረኝ ምልከታም የኩብራ መላኩ ድምፅ (tone) በቃል ግጥሙ ውስጥ ያለውን ኹነት በእሷ ላይ የደረሰ ያስመስለው ነበር። በዚህ መነሻነት እኔም በፍቅር አቻ ባለመኾን በኩብራ መላኩ ላይ የተፈጠረውን ስሜት መረዳት እንድችል መልኳንም ኾነ ትክለ መልካምነቷን በአንክሮ ተመለከትኩ። ከከንፈር ወዳጇ ጋር ያለውን የዕድሜና የሀብት ደረጃ ልዩነት ለማወቅ

ኹኔታዎች ባይፈቅዱልኝም እሷ ግን በውጫዊ ገጽታዋ ምንም የሚጎድላት ነገር የሌለ መኾኑን ለማረጋገጥ ችያለሁ።።

ከኩብራ መላኩ ስሜት በስተጀርባ ግን የማገዶ እንጨት ለቃቅማ ካሠረች በኋላ ከድንጋይ ላይ ቁጭ ብላ አቻነት በሌለው ፍቅር ምክንያት በደረሰባት በደል እየቆዘመች ስላለች ገጸሰብ ቃል ግጥሙ እንድናስብ ያደርገናል።። ተምሳሌታዊ በኾነ የአነጋገር ስልት ቁጭ ያለችበት ድንጋይ የከንፈር ወዳጇ የእሷ ፍቅር የማይገባው መኾኑን ያመላክተናል።። በዚህ የተነሣ "ያንተን ፍቅር ቢተውትም አያናድድም" በማለት ራሷን ለማጽናናት ሞክራለች።። በመቀጠልም ወዳጇ በፍቅረኛነት ከያዛቸው ልጃገረዶች ጋር ራሷን አነጻጽራለች።። በመጨረሻም ልጃገረዷ በፍቅር አቻ ባለመኾን የተነሣ ትቷት ለኼደው ጎረምሳ "አዲሶቹ የክንፈር ወዳጆችህ ሴቶች ቢኾኑም እነሱን የመሰሉ፣ በጠይሙ ጠይም፣ በቀዩ ቀይ የኾኑ የከንፈር ወዳጅ ጎረምሳዎችን እኔ ሳላገኝ ብቀር ትንቀኛለህ" በማለት ገልጻለታለች።።

ቃል ግጥም 178፡- ብሳና ሞኝ ነው ላይበሉት ያፈራል
ያለ እኩያ መውደድ እጅግ ያሳፍራል።።
ያለ እኩያ መውደድ ያለ ባልንጀራ
ቃር ቃር ያሠኛል እንደ ገብስ እንጀራ።።
(ምልከታ፣ ኩብራ መላኩ፣ 10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ቀደም ሲል ከተቀነቀነው ቃል ግጥም ተከታይ በኾነው ቅንጫቢ ደግሞ የ"ብሳና" ዛፍ ተጠቅሷል።። ቅጠሉ ሰፋ ያለና ሸካራ የኾነው ይህ ዛፍ በአብዛኛው የሚበቅለው በወይና ደጋ አካባቢ ሲኾን፣ የማፍሪያ ጊዜውም ሲደርስ አብቦ ያፈራል።። ነገር ግን ፍሬውን ሰዎች የማይመገቡት መኾኑን ተወልጇ ባደግሁበት ማኅበረሰብ ዘንድ በነበረኝ መስተጋብር ያረጋገጥኩት ጉዳይ ነው።። ሰዎች እንብላው ቢሉ እንኳን ጣዕሙ መራራ ስለኾነ መመገብ አይችሉም።። ግንዱም ቢኾን የሚነቅዝና በቀላሉ የሚያቦካቡክ (የሚበሰብስ) ስለኾነ ለቤት መሥሪያም ኾነ ለተለያዩ አገልግሎቶች አይውልም።። ቅርንጫፉም ቢኾን "ባልና ሚስትን ያጣላል" የሚል አስተሳሰብ በማኅበረሰቡ ዘንድ ስላለና ጭሱም ቢኾን በከፍተኛ ኹኔታ ዓይንን ስለሚለበልብ ማገዶ ሊኾን አይችልም።። ይህ ቃል ግጥምም አቻነት የሌለው ፍቅር የሚሰለች፣ በጥብቅ የሚጠላና የማንገፍገፍ ስሜትን የሚፈጥር መኾኑን በብሳና ተምሳሌትነት አስገንዝቦናል።። ከዚህም አልፎ ያለ እኩያ ማፍቀር በሰዎች ዘንድ በጣም አዋርዶ ነውረኛ እንደሚያደርግ ኩብራ መላኩ ቃል ግጥሙን ስታዜም ፊቷን አቀጭማ አንደነበር በዓይነ ሥጋዬ ለመመልከት ችያለሁ።። በመጨረሻው ስንኝ ላይ ደግሞ ያለ አቻው የወደደና የገብስ እንጀራ ተመግቦ የጨጓራ መታወክና የማቃጠል ስሜት የተፈጠረበት ሰው በንጽጽር ቀርበዋል፡

ቃል ግጥም 179፡- እኔስ እኼዳለሁ አገር ጥዬ የትም
የጎደለ መሙሊያ ኾኜ አልቀመጥም፡፡
... የሀብታም ቀብራራ ምን ያደርግልሃል
የኔ ቢጤ ድኻ ፍቅር ያጠግብሃል፡፡
(ምልከታ፣ መዲና ሁሴን፣ 21/06/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ይህን ቃል ግጥም ያዜመቺው ልጃገረድ በኹለተኛው ስንኝ ላይ ያለ አቻ በኾነ ፍቅር ምክንያት ቅስሟ የተሰበረ፣ ተስፋ የቆረጠች፣ ኅሊናዊ ክብሯ የወደቀና ስሜቷ የተጎዳ ልጃገረድን በምናባችን እንዲናይ አድርጋናለች፡፡ ለዚህ ማረጋገጫውም የጎደለ መሙሊያ ወይም ማስተካከያ ኾና መኖር ስለማትፈልግ የትውልድ ስፍራዋን ወይም አካባቢዋን ለቃ ወደ ሌላ ቦታ እንደምትጓዝ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ገልጻለች፡፡ ይህ ደግሞ ራሷን ደብቃ እንዲትኖር እንደሚያደርጋት መገንዘብ ይቻላል፡፡ መዲና ሁሴን ባዜመቻቸው የመጨረሻዎቹ ኹለት ስንኞች ደግሞ የባለጸጋ ልጅ ኾና በመንደላቀቅ የምትኖረዋን ልጃገረድ በመውደድ አፍቃሪው የኾነችውን የድኻ ልጅ ገሸሽ ላደረገው ጎረምሳ ምክር ተለግሶታል፡፡ የተሰጠው የምክር ትኩረትም የተንቀባረረችዋን የሀብታም ልጅ መውደድ ምንም አያደርግልህም፡፡ ያጣች፣ የተቸገረችና በቂ መተዳደሪያ የሌላትን ልጃገረድ ማፍቀር ግን ከፍተኛ የኾነ ርካታን ይሰጥሃል የሚል ነው፡፡

7.2.7. ተፋቅሮ የመለያየት አስከፊነት፣

መለየት ማለት በሞት ወይም በሕይወት የመነጠል ክሥተት ነው፡፡ በሞት የሚከሠተውን መለየት ትተን በሕይወት ያለውን ስንመለከት አንድ ሰው ከወላጆቹ፣ ከትዳር ጓደኛውና ከፍቅረኛው ተነጥሎ ወደሌላ አካባቢ ወይም ሀገር ኼዶ መኖር ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድነትን ያሳጣል፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር የቀረቡት ቃል ግጥሞች የመለየትን አስከፊነት የሚያንጸባርቁ ስለኾኑ በትኩረት እንመልከታቸው፡፡

ቃል ግጥም 180፡- ይመራል ይላሉ ኮሶ መጠጣት
የሚመርስ ባየህ ወዶ መለየት፡፡
መለየት መለየት መለየት ምናባቱን
ምጣዱን ነው ብዬ ጣድኩት ሌማቱን፡፡
እባክህ ሌማቱ አትንደድብኝ
የልጅ መንገደኛ ተሳፋሪ ነኝ፡፡
የልጅ መንገደኛ ሥንቁ የተቦካ
እንጫወት ሽጉ እስኪጋገር እንኳ፡፡
(ምልከታ፣ ተምር አደም፣ 14/07፣ 2013፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙ የተዜመው በቦረና ወረዳ ቀያፊር ቀበሌ እስማኤል በላይ የተባለው ወጣት በሚያገባበት ዕለት ዋዜማ ምሽት ላይ በነበረው ጨዋታ ወቅት ነው፡፡ በወቅቱ የግጥሙ

አቀንቃኝ የሾነችው ተምር አደም በግራ እጇ የያዘችውን አታሞ በቀኟ “ድም ድም” እያደረገች ስትዘፍን፣ በዙሪያዋ ያሉ ልጃገረዶች ደግሞ ከትከሻቸው ከፍና ዝቅ እያሉ እስክስታ ሲወርዱ በምልከታዬ ለማረጋገጥ ችያለሁ። በምልከታዬ ወቅትም በልጃገረዶቹ አቅራቢያ የሚገኙ ጎረምሳዎች ነጠላቸውን ተከናንበውና ዱላቸውን ተመርኩዘው በመቆም ልጃገረዶቹን እየተመለከቱ ያወሩ ነበር። ጎረምሳዎቹም ከልጃገረዶቹ መካከል ለስሞሽ የሚሾኗቸውን በመምረጥ ሊስሙ የተዘጋጁ ይመስላሉ። በቅርብ ባሉ ዓመታት ያገቡ ሴቶች ግን በልጃገረዶቹ ዙሪያ ሾነው የቃል ግጥሙን ይዘት ያዳምጡ ነበር እንጂ ከባህሉ አንጻር ሌላ ሚና ያልነበራቸው መሾኑን በምልከታዬ ወቅት በማረጋገጥ ታዝቤያለሁ። እነዚህ ሴቶች በማግባታቸው የተነሣ ከከንፈር ወዳጆቻቸው ጋር የተነጠሉ በመሾናቸው የመለየትን አስከፊነት የሚያንጸባርቀውን ቃል ግጥም ጆሯቸውን ሰጥተው ያዳምጡ ነበር።

ከቃል ግጥሙ እንደምንገነዘበው ኮሶ የተባለውን ትል ከሆድ ውስጥ ለመግደል ወይም ለማስወጣት ተወቅጦና ተበጥብጦ የሚጠጣው የኮሶ ፍሬ መራራ እንደሾነ ሁሉ አፍቅሮ መለየትም የሚጎፈንን (የሚያንገሸግሽ) መሾኑን አቀንቃኟ ገልጻለች። ከዚሁ ጎን ለጎን ኮሶ የተዋዶ መለየት ተምሳሌት ሾኖ ሲቀርብም አጥብቆ የመጥላት ወይም የማንገፍገፍ ስሜት ወካይ መሾኑንም መረዳት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ካፈቀሩ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሠተውን መነጠል የተስፋ መቁረጥ፣ የንዴት፣... መግለጫ በሾነው የስድብ ቃል አቀንቃኟ “ምናባቱን” ለማለት ችላለች። አስከፊ የሾነው መለየት ባስከተለባት ብስጭትም በእሳት ላይ የሚጣደውን እና የማይጣደውን ለመለየት አልችል ብላ በልበ ዕውርነት በምጣዱ ምትክ ከአክርማና ከስንደዶ የተሠራውን እና ለእንጀራ ማስቀመጫነት የሚያገለግለውን ሌማት እሳት በተቀጣጠለበት ምድጃ ላይ መጣዷን ከግጥሙ ልብ ልንል እንችላለን። በመሾኑም አቀንቃኟ “በዕድሜ ያልገፋሁ ገና ለጋ ወጣት ስለሾንኩና ወደሌላ ቦታ ለመጓዝ ስለተነሣሁ ነው በእሳት ላይ የጣድኩህ” በማለት ሌማቱን በጸጸት “እባክህ አትቃጠልብኝ” ብላ ለምናዋለች። ሽጋ የሾነውን እና በቀጣይ የምትለየውን የከንፈር ወዳጇን ደግሞ “ለእኔ ለመንገደኛይቱ ሥንቅ ይሾናል ተብሎ የተቦካው ነገር ተጋግሮ እስከሚበስል ድረስ ባለን ዐጭር ጊዜ እየተጫወትን እንዝናና” ብላዋለች።

ቃል ግጥም 181፡- ... አድሩሱን ከደሴ ቡና ከሲዳሞ
ያለያየን ጌታ ያገናኘን ደግሞ።
ምን አላህ ሻተብን ይሄን መለያየት
ግማሹን በመኼድ ግማሹን በመሞት።
(ምልከታ፣ ይርገዱ ታደሰ፣ 21/06/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ይህ ቃል ግጥም በቦረና ወረዳ ከቶ በተባለው ቀበሌ አገሬ ታለማ የተባለቺው ልጃገረድ ባገባችበት ዕለት ማታ ላይ ቤተዘመዱ ጠላ እየጠጣ ባለበት ወቅት ወይዘሮ ይርገዱ ታደሰ የተባለችው ሴት ያዜመችው ነው። በዚህን ወቅት የዘፈን ስሜት ያላቸው ወንዶችም ኾኑ ሴቶች እያጨበጨቡና አዝማቹን እየተቀበሉ ዘፈኑን ሲያደምቁት ነበር። እኔም በጭብጨባውና በአዝማች መቀበሉ ረገድ ተሳታፊ ነበርኩ። ይርገዱ የዘፈኑን አዝማች አብቅታ ዋናውን ዘፈን መዝፈን ስትጀምር ከፊሎቹ እስክስታ ወርደው ነበር። ከፊሎቹ ደግሞ "አሸነፈቻት፤ አሸነፈቻት" በማለት እያጨበጨቡ ጭፈራውን አሟሙቀውታል። በኹኔታው የተደሰቱና ሞቅታ የተሰማቸው ወንድም ኾነ ሴት ዐሥር ዐሥር ብር እያወጡ ለዘፋኟም ኾነ ለእስክስታ ወራጆቹ ሲሸልሙ ታይተዋል። ይርገዱ የጀመረችው የቃል ግጥም ዘፈን እስኪጠናቀቅ ድረስ እስክስታውን ያላቋረጡት ሰዎች ደግሞ የአሸናፊነት ስሜት ስለተሰማቸው እየዘለሉ ደስታቸውን ሲገልጹ ተመልክቻለሁ።

ይርገዱ ባዜመቺው የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ከደሴ አዱሩስ፣ ቀደም ባለው ወቅት ሲዳሞ እየተባለ ሲጠራ ከነበረው ክፍለ ሀገር ደግሞ ቡና ለአካባቢው ጎብረተሰብ በመቅረብ ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል። ቡናና አዱሩስ ደግሞ የጠበቀ ትስስር ስላላቸው፡ በየትኛውም አጋጣሚ ሁሉ ቡና ሲፈላ ጥሩ መዓዛ ያለው አዱሩስ ይጨሳል። ለአብነትም "ልጅህን ለልጄ" በሚባልበት ወቅት በወንዱ በኩል የተላኩት ሽማግሌዎች "አባት ኹኑን፣ ልጅ እንኹናችሁ" ብለን ነው የመጣነው ሲሉ የሴት ወላጆች መልሳቸው የእሺታ ከኾነ ምግብ ከተበላ በኋላ ቡና ተፈልቶ ይጠጣል። በሰዎች መካከል ግጭት ተፈጥሮ ሽማግሌዎች የተቻላቸውን ያክል አድርገው ካስታረቁ በኋላም ቡና ይፈላል። አንድ ሰው የሞተ እንደኾነ የጎረቤት ሰዎች ቡና እያፈሉ በጋራ በመጠጣት ቤተሰቦቹን ያስተዛዝናሉ። እዚህ ላይ የቡና ማፍላት ፋይዳው ለሱስ ሳይኾን ረዥም ጊዜ ወስዶ በጋራ ለመጫወት ታስቦ ነው። በተለይም በፈጣሪ ዘንድ ዱዓ (ጸሎት) እንዲያደርጉ ልዕልና ተሰጥቷቸዋል የሚባሉት ሰዎች በመኖሪያ ቤትም ኾነ በውጭ ሥርዓቱን በሚከውኑበት ወቅት በተደጋጋሚ ቡና እየተፈላ ይጠጣል። ከላይ እንደተጠቀሰው ቡና ተፈልቶ በተጠጣባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ አዱሩሱ ይጨሳል።

ወደተከታዮቹ ስንኞች ትንተና ስንሸጋገር ደግሞ ጥናቱ በተካኼደባቸው አካባቢዎች ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ በሕይወት የተለየ ሰው ካለ በማንኛውም ወቅት ቡና ተፈልቶ የቡናው መራቂ የኾነው አካል የተለያዩትን ሰዎች አምላክ እንደገና እንዲያገናኛቸው ይማጸናል። በቃል ግጥሙ ውስጥ ከፊሉ ሰው በሕይወት እያለ ከቦታ ቦታ በመንዙ፣ ከፊሉ ደግሞ ነፍሱ ከሥጋው በመለየቷ ምክንያት የተከሠተውን የመነጣጠል አስከፊነት የፈጣሪ ፍርጃ ተደርጎ ተቆጥሯል። ለዚህም ነው "ምነው አላህ ሻተብን (ጣለብን)" የሚለው አባባል በአቀንቃኟ አንደበት ሊገለጽ የቻለው።

ቃል ግጥም 182፡- ...ትኼዳለህ አሉ ምናኔ ምናኔ
እንዴት እንኾናለን እናትህ እና እኔ
እኔስ ግድ የለኝም ይብላኝ ለእናትህ
ዘጠኝ ወር አርግዘው ዓመት ላጠቡህ፡፡
ዘጠኝ ወር አርግገፍ ዓመት ባጠባው
ላንችም ወዳጅሽ ነው ለእኔም ልጄ ነው፡፡
(ምልከታ፣ መሬማ ሽፈራው፣ 14/07/2013 ቦረና ወረዳ)

ግጥሙ እስማኤል በላይ ባገባ ዕለት ማታ ሰርገኞቹ ሙሽራዋን ይዘው ከሙሽራው አባት ቤት ሲደርሱ ተቀባይ ከኾኑት ልጃገረዶች መካከል አታሞ ይዛ ትመታ በነበረቺው በመሬማ ሽፈራው አማካይነት የተዘመ ነው፡፡ በዚህን ወቅት ለሙሽሮቹ አቀባበል ለማድረግ ከቤት በወጣው ቤተዘመድና ከጎረቤት በመጣው ሰው አካባቢው በመጨናነቁ፣ እንደዚሁም የወንዱ ቤተሰቦች የሙሽራይቱን ዕቃ እየቆጠሩ በመረካከብ ላይ በመኾናቸው የተነሣ በተፈጠረው ግርግር ለልጃገረዲ ዘፈን ትኩረት የሰጠ ማንም አነልበረም፡፡ በአቅራቢያ ያሉት ጎረምሳዎችም ቢኾኑ ሙሽራዋን ለማየት በመጓጓታቸው ምክንያት ለዘፈኑ ደንታ ስላልነበራቸው መደለቅ አልቻሉም ነበር፡፡ በሌላ በኩል መሬማ ሽፈራው ያዜመችውን ቃል ግጥም ሐሳብ ከዐውዱ ጋር አስተሳስሮ ለማስተንተን አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም ልጃገረዲ ቀደም ሲል በአእምሮዋ የነበረውን ዘፈን አስታውሳ ዘፈነችው እንጂ ግጥሙ ይዞት በተነሣው መሠረተ ነገርና በዐውዱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበረምና ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ቃል ግጥሙ በአቀንቃኟች መካከል በሚካኼድ ምልልስ የቀረበ ነው፡፡ ገጸሰቦቹም ተለይቷቸው ሊኼድ የተነሣው ጎረምሳ የከንፈር ወዳጅና ወላጅ እናቱ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ቃል ግጥሙ በመሬማ ሽፈራው ድምፅ ይቅረብ እንጂ ገጸሰቦቹ እንደ ንግግራዊ ተግባቦት ተራቸውን እየጠበቁ ነው ምልልሱን ሲያካኺዱት የነበረው ማለት ይቻላል፡፡ በመኾኑም በግጥሙ ውስጥ የተሳለችው ልጃገረድ የከንፈር ወዳጇ የዓለምን ነገር፣ ተድላን፣ ደስታን ንቆና ትቶ ከሰው በመለየት በዋሻ፣ በዱር፣ በጫካ ወይም በገዳም ለመኖር፣ ሀገር ጥሎ ቁርበት ጠቅልሎ ለነፍሱ ለማደር ቆርጦ እንደሚኼድ ገልጻለች፡፡ በዚህ የተነሣ እሷም ኾነች እናቱ ከእሱ ተለይተው መኖር ያለውን አስከፊነት በመረዳት “እንዴት እንኾናለን እናትህና እኔ” ስትል ተደምጣለች፡፡ በመቀጠል ደግሞ አንጻራዊ በኾነ ኹኔታ መለየት ለእናትዮዋ ከባድ እንደኾነም በማስረጃ ለማሳየት ችላለች፡፡ ይሄውም ዘጠኝ ወር በማሕፀናቸው ተሸክመው፣ ለዓመታት ጡታቸውን አጥብተው ያሳደጉህ እናትህ “ይብላኝላቸው” በማለት የሐዘን፣ የትካዜና የጸጸት መግለጫ በኾነው ቃል ገልጻለች፡፡ እሷ ግን ከከንፈር ወዳጇ መለየቷ ያን ያኽልም ስላላሳሰባትና ስላላስጨነቃት “እኔስ ግድ የለኝም” ብላለች፡፡ እናትዮዋም በበኩላቸው “ዘጠኝ ወር

አርግገፍ፣ ጡት አጥብቹ ባሳድገውና ከአብራኬ የወጣ ቢኾንም ለአንቺም ብርቱ ፍቅረኛሽ በመኾኑ ልትተክኝር ይገባል" ሲሉ በምላሻቸው አስረድተዋታል።

7.2.8. ፈሪን ስለመተቸት፣

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሥር ለትንተና የቀረቡት ቃል ግጥሞች በቀረርቶ ወቅት ከነበረው ዐውድ የተገኙ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቀረርቶ ለዘብ፣ ረዘም ያለ፣ ሐሳብን ወደሩቅ አምጥቆ፣ ትዝታን ከዓይነ ኅሊና ደቅኖ፣ ኹለንተናዊ ስሜትን የሚቀሰቅስ፣ የሚያስቆጣ፣ ወኔን የሚሸቀሽቅ የዜማ ስልት ነው። አንድ ሰው ትካዜውን፣ በደሉን፣ ጸጸቱን፣ ምሬቱን፣ ወዘተ. በቀረርቶ ሊገልጽ ይችላል። የቀረርቶ ቃል ግጥሞች የመከወኛ መነሻዎች በጣም በርካታ ቢኾኑም በዚህ ቦታ ላይ ትንተና የተካኼደባቸው በሰርግ ዐውድ ላይ ብቻ የተገኙ ናቸው። እነዚህም ግጥሞች ፈሪን በመተቸት የተቀነቀኑ ሲኾኑ ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 183፡- ምንሽሩን ሰጡት ኧረ ዛላ እያዩ
ወንድ ይኹን ሴት ይኹን ጸታውን ሳይለዩ።
(ምልከታ፣ ታለማ ዳኜ፣10/072013፣ ወግዲ ወረዳ

ይህ የቀረርቶ ቃል ግጥም የተከወነው በወግዲ ወረዳ ሌንጮ በተባለው ቀበሌ ሠርካለም ካሳው በምታገባ ዕለት በነበረው የሰርግ ዐወድ ላይ ነው። አቶ ታለማ ዳኜም ሙሽራውን ዐጅቦ የመጣ ሲኾን፣ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ፣ በያዘው ዱላ መሬቱን የለካ በሚመስል ኹኔታ ወደፊት በመሰንዘርና "እ.እ.እ. ኧረ ደኑ ደኑ፣ ኧረ መርዙ መርዙ" በሚል ረኻጮም የዜማ ስልት ነበር ቀረርቶውን ሲያዜም የተመለከትኩት። ታዳሚዎቹ ደግሞ "ሃ.ሃ.ይ" እያሉ ያጅቡት ነበር። በመቀጠልም የተወሰኑት ሰዎች የፉከራ ቃል ግጥሞችን ተራ በተራ ለታለማ ዳኜ ነግረው እንደጨረሱ ስሜታቸው ለፉከራ መቀስቀሱን ለማስተዋል ችያለሁ። ከዚያም እነዚሁ ሰዎች ፊታቸውን ኮስተር ፈካ እያደረጉ፣ በዱላቸው መሬቱን እየመቱ፣ ጠብመንጃም የያዙት ቃታ ስበው የተኮሱ እየመሰሉ፣ እየተንበረከኩና ወደዚያና ወደዚህ እየተዘዋወሩ "እምቢ በላቸው፤ እምቢ በላቸው" ብለው በመጀመር ሲፎክሩ አዳምጫለሁ። የፉከራ ቃል ግጥሞች ይዘትም የፎካሪዎቹን ጠንካራ ገበሬነትን፣ አምራችነትን እና ጀግንነትን የሚዘክሩ ናቸው። እነዚህ መሰል የፉከራ ቃል ግጥሞች በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ሥር የተተነተኑ በመኾናቸው እዚህ ላይ መድገሙ ተገቢነት የለውም። ከሰርጉ ታዳሚዎች መካከል አንዳንዶቹ አቅራሪውን "አብሽር" ሲሉ ፎካሪዎቹን ደግሞ "ያላችሁት እውነት ነው" ለማለት "አይዞህ፤ አይዞህ፤ እንዲያ ነው እንጂ፣ እንዲያ ነው" እያሉ ያበረታቷቸው ነበር።

ከላይ በቀረበው ቃል ግጥም ውስጥ ምንሽር የተባለው የጥንት የጠብመንጃ ዓይነት ተጠቅሷል። በሆታ ወቅትም "በለው በምንሽር፣ እንዳይሞት እንዳይሸር" በማለት ጀግና የሚበረታታበት መኾኑ ይታወቃል። ታለማ ዳኜ ባቀነቀነው የቀረርቶ ቃል ግጥም ግን ድፍረት ያለውና የሌለው መኾኑን ሰዎች መርምረው ሳያውቁ አቋሙና ቁመናው ለሚያምረው ሰው ሁሉ ምንሽር ዐደሉት በማለት በአግራሞት ተገልጿል። በኹለተኛው ስንኝ ላይ ደግሞ የወንድና የሴት ጾታዎች ቀርበዋል። እነዚህ ጾታዎች ደግሞ እርስ በርሳቸው የሚለያዩበት ተፈጥሯዊ የኾኑ ምልክቶች አሏቸው። ነገር ግን በማኅበረሰቡ ዘንድ ወንድ ለኅበዝ፣ ለጀግና፣ ለብርቱ፣ ወዘተ. ወካይ ኾኖ ይቀርባል። ለዚህም ነው "እከሌ ወንድ ወጣው" የሚባለው። በተቃራኒው ደግሞ ሴት የሚለው ቃል ለፈሪና ድፍረት ለሌለው ሰው ተምሳሌት ይኾናል። ከቃል ግጥሙ መሠረተ ሐሳብ የምንገነዘበውም ጀግናው ማን እንደኾነ፣ ፈሪውስ ማን ነው ብለው ሰዎች ሳይመረምሩ እንዳው በደፈናው ምንሽር የተባለውን የጦር መሣሪያ ዐደሉት የሚል ትችት የተሰነዘረ መኾኑን ነው።

ቃል ግጥም 184፡- ምኑ ሞኙ ነው ምኑ ጅሉ ነው
ሲሰድቡት ዝም ያለ ሲመቱትም ያው ነው።
(ምልከታ፣ ታለማ ዳኜ፣10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ

ከተለያዩ የቆላ እንጨቶችና ከደደሆ ቅጠል በተሠራው ዳስ ውስጥ በታለማ ዳኜ የሚቀርቡት አብዛኛዎቹ የቀረርቶ ቃል ግጥሞች ባለ መንቶ ስንኞች መኾናቸውን በምልከታዬ ወቅት በያዝኩት ማስታወሻ ለማረጋገጥ ችያለሁ። ሌንጮ በተባለው ቀበሌ በነበረው የሰርግ ዕለት የተቀነቀነው ይህ መንቶ የቀረርቶ ቃል ግጥምም ገና ከመነሻው "ምኑ" በሚለው የንዴት መግለጫ ቃል የተዋቀረ ሲኾን፣ በተከታዩ ስንኝም በማኅበረሰቡ ዘንድ ፈሪ ሰው ሞኝና ጅል መኾኑ በጥብቅ ተተችቶበታል። በዚህ ትችትም ፈሪ የኾነውን ሰው ሲዘልፉት፣ ሲያዋርዱት፣ ከፍ ዝቅ አድርገው ሲናገሩት ምንም ሳይል ከቀረ፣ ጭጭ እምጭጭ ካለ፣ ምንም ዓይነት ርምጃ ለመውሰድ ካልቻለ፣ እንደዚሁም የማጥቃት እንቅስቃሴ የማያደርግ ከኾነ፣ ሲደበድቡትም ቢኾን እንደዚያው ነው የሚኾነው። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱ ፍርሀት የነገሠበት ፍጡር ቂል፣ ጅል፣ ወዘተ. ነው በማለት ማኅበረሰቡ ሀብቱ በኾነው ቃል ግጥሙ የሰላ ትችት አቅርቦበታል።

ቃል ግጥም 185፡- ይብላኝልህ ፈሪ ይብላኝልህ
እርጅናውም መጣ ሞቱም አይቀርልህ።
(ምልከታ፣ ታለማ ዳኜ፣10/07/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው የኅብረተሰብ ክፍል በሰዎች ላይ አስነዋሪ የኾኑና ተቀባይነት የሌላቸውን ባሕርያት ካየ ለማስተካከል በማሰብ በቃል ግጥሙ ይተቻል። ከእነዚህ አስነዋሪ ባሕርያት መካከል አንደኛው ደግሞ ፍርሀት ነው። ምክንያቱም ራስንና ቤተሰብን

ከጥቃት አለመከላከል፣ መሥዋዕትነትን በሚጠይቁ ተግባራት ላይ ተሳታፊ አለመኾን በኅብረተሰቡ ዘንድ ያስተቻል፤ እንደ ሰርግና ለቅሶ ባሉ አጋጣሚዎችም ያሰድባል። ታለማ ዳኜ ባቀነቀነው በዚህ ቃል ግጥምም ፈሪ የኾነው ሰው “ይብላኝልህ” ተብሏል። ፍርሀቱም የዕድሜ ልክ እንዳይኾን በማሰብ ለሽምግልናውም ተቃርበሃል፤ ነፍስህም ከሥጋዋ መለየቷ እንደኾነ አይቀርላትምና የጀግንነት ተግባር በመፈጸም ማኅበራዊ ግዴታህን ተወጣ የሚል ትችት ቀርቦበታል። በዕለቱ በዳስ ውስጥ ተቀምጬ ኾኑቱን በአንክሮ ስከታተል በነበርኩበት ወቅት የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር የሰርጉ ታዳሚዎች እንደየእምነታቸው የተለያዩ የመጠጥ ዓይነቶችን ሲጠጡ ታለማ ዳኜ ያቀነቀነውን ይህን ዓይነቱን ሐሳበ ምጡቅ የቀረርቶ ቃል ግጥም በማዳመጣቸው የተነሣ ስሜታቸው በመነካቱ ካገጫቸው በላይ ያለውን አካላቸውን ወደፊት እያንቀሳቀሱ አዎንታቸውን ይገልጹ ነበር።

ቃል ግጥም 186፡- እምቢ ብሎ እምቢ ብሎ እንዳው እምቢ ብሎ
ሸሽት ያሳምራል ፈሪና ዝንጆሮ።
(ምልከታ፣ ይመር ዳውድ፣ 14/07/2013፣ ቦረና ወረዳ)

ከላይ በተጠቀሰው ቀን እስማኤል በላይ ያገባበት ዕለት ነበር። በዚሁ ዕለት ከሰዓት በኋላ ባለው ወቅት ሙሽራዋን ለማምጣት እስማኤል በላይን ዐጅበውት ከኼዱት ሰዎች መካከል የፉከራ ቃል ግጥሙን ያቀነቀነው አቶ ይመር ዳውድ ነበር። በሙሽራዋ ወላጆች ቤት ካለው ዳስ ውስጥ ምግብ ተበልቶ ካበቃ በኋላ ቡና ተፈልቶ እስከሚጠጣበት ጊዜ ድረስ ዐጃቢዎቹ የተለያዩ የመጠጥ ዓይነቶችን እየጠጡ ባሉበት ወቅት አቶ ይመር በራሱ ከአእምሮው እያፈለቀ ሲያቅራራ ከቆየ በኋላ ጠና ይመር የተባለው የሙሽራው ዐጃቢ ጎረምሳ ከላይ ያለውን የፉከራ ቃል ግጥም ለአቶ ይመር ዳውድ ሲነግረው አዳምጫለሁ፤ ኾኑቱንም ተከታትያለሁ።

ቀደም ሲል በዚህ ጽሑፍ የፅንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ የቃል ግጥሞች የሰዎችን ጥዩፍ ባሕርያትን መስፋፋት ሊቆጣጠሩ እንደሚችሉ ተመልክተናል። በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ዘንድም ከጥዩፍ ባሕርያት መካከል አንዱ የኾነው ፍርሀት ተቀባይነት የሌለው መኾኑን ለመረዳት ተችሏል። ይሄው ጥዩፍ ባሕርይ ለወደፊትም ቀጣይነት እንዳይኖረው ለማድረግ በቀረርቶ ቃል ግጥሞች አማካይነት ግሣጼ ደርሶበታል። ከላይ በቀረበው የቀረርቶ ቃል ግጥምም መገንዘብ የምንችለው ይሄንኑ ነው። ይሄውም ፈሪ የኾነውን ሰው ሥነ ልቦና ወይም በአእምሮው ውስጥ ያለውን ስሜት ለማሸማቀቅ (ለማሳፈር) ሲባል በአፈጣጠሩም ኾነ በዕድሜ ዘመኑ በሚያሳልፈው ሕይወት ከሰው ተራ ከወረደው ከዝንጆሮ ጋር ጎን ለጎን ተነጻጽሮ እንዲቀርብ ተደርጓል። እንደሚታወቀው የዝንጆሮ መንጋ የአርሶ አደሩን አዝመራ በማውደም ይታወቃል። የአዝመራ ጠባቂ ሲመጣበት ደግሞ በመጀመሪያ ነፍስ አውቄኝ ብሎ በጅምላ ሮጦ ያመልጣል። እየራቀ

ሲኼድ ደግሞ መንጋው ተራ በተራ ሰልፍ ሠርቶ ይሸሻል። ፈሪው ሰውም ቢኾን ሁከት በሚፈጠርበት ወቅት ችግር ፈጣሪውን ለመቋቋም "እንዳው እምቢ ብሎ" ድፍረት ስለማይኖረው እግሬ አውጭኝ ብሎ ፍርጠጣውን ይቀጥላል። በአጠቃላይ ከላይ በትንተና የተመለከትናቸው የቀረርቶ ቃል ግጥሞች የማኅበረሰቡ አባላት ፍርሀትን አስወግደው የጀግንነትን ባሕርይ እንዲላበሱ የማድረጊያ መሣሪያዎች መኾናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

7.2.9. ነገረኛን ስለመተቸት፣

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚኖረው ማኅበረሰብ ዘንድ ከማይፈለጉ ባሕርያት ውስጥ ሌላኛው ነገረኛነት ነው። ምክንያቱም ነገርን የሚሠሩ ተንኮለኞች ያንዱን ነገር ለሌላው በማቀበል ወይም በማመላለስ ሰዎች እርስ በርስ እንዲጣሉ የሚያደርጉ በመኾናቸው የተነሣ ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች አሳባቂነት ባሕርያቸው ስለኾነ ብቻ ነው እንጂ ነገር ካቀበሏቸው ወገኖች የሚያገኙት ነገር የሚኖር አይመስለኝም። ይህንን ዓይነቱን እኩይ ተግባር በትችት መልክ የሚያንኳስሱና ባለበት ለመግታትም የሚያስችሉ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ቃላዊ ግጥሞች፣ ወዘተ. በማኅበረሰቡ አንደበት ሲነገሩ ይስተዋላሉ። ከዚህ በታች በአቶ አባተ ወርቅነህ የተቀነቀኑት የቀረርቶ ቃል ግጥሞችም በሰርግ ዐውድ ላይ የተገኙ ሲኾኑ፣ የሸውከኛን ወይም የነገረኛን ሰው መጥፎነት የሚነቅፉ ናቸው።

ቃል ግጥም 187፡- ይህ ነገር ሠሪ አፉ አሞጠሞጠ
እኽል ብላ ቢሉት ሰው እያላመጠ።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 07/06/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ከላይ ያለውና ቀጣዮቹ ቃል ግጥሞች የተቀነቀኑት በወግዲ ወረዳ፣ በ015 ጎዲንዲት በተባለው ቀበሌ በነበረው የሰርግ ዐውድ ላይ ነው። አቶ አባተ ወርቅነህም በአካባቢው በጣም የታወቀ አቅራሪ ስለኾነ በዚሁ ችሎታው ጋሻው አስፋው ለተባለው ሙሽራ ዐጃቢ ለመኾን በቅቷል። የቀረርቶውን ኺደት ስንመለከት ከሙሽራዋ ቤተሰቦች ግቢ ባለው ዳስ ለሰርገኞች የቀረበው ምግብ ተበልቶ እንዳበቃ ማዱ ተነሣ። ከዚያም አቶ አባተ ቀድሞ በአእምሮው የሚያስታውሳቸውን እና የተለያዩ ይዘት ያላቸውን የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን ወዲያና ወዲህ እየተንጎራደደ ሲያቀነቅን በነበረበት ወቅት ያለውን መረጃ በማስታወሻ ደብተርና በመቅረጸ ድምፅ ለመያዝ ችያለሁ። ቀጥሎም "ተቀበል" በሚል ዓይነት አቀራረብ የሚከተሉትን ትችት አዘል ግጥሞች ከተለያዩ የሙሽራው ዐጃቢዎች ተራ በተራ እየተቀበለ ማቅራራቱን ቀጠለ። አቀባዮቹም ቃል ግጥሙን ሰጥተው ካበቁ በኋላ ብቻቸውን "ዘራፍ" እያሉ መፎከር ሲጀምሩ

ወንድም ካላቸው ወንድማቸው፣ አለበዚያም ዘመዳቸው ወይም የቅርብ ጓደኛቸው የኾነ ጎረምሳ ድንገት ተነሥቶ እየፎከረ ያጅባቸው ነበር።

ከላይ በቀረበው የቀረርቶ ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ ነገር የሚሠራው፣ ክፉና ተንኮለኛ የኾነው ሰው በቅርብ እንዳለ ተደርጎ ተቆጥሯል። አቶ አባተ ወርቅነህም አሳባቂውን ሰው ፊት ለፊቱ በዓይኑ አተኩሮ እየተመለከተው በሚመስል ኹኔታ ቀረርቶውን ይከውን ነበር። በግጥሙም ነገረኛውን ሰው "በአእምሮው የያዘውን ወይም ያሰበውን ክፉ ነገር ለሌላው ሰው ለመናገር አፉን አሾለ፤ አቆበቆበ፤ ተናገር ተናገር በሚል አባዜ አፉን በላው" ብሎታል። በኹለተኛው ስንኝ ላይም ሰውን በክፉ አነሣ፣ ሰውን ዐጣ፣ ወዘተ. የሚለውን ሐሳብ አጠናክሮ ለማቅረብ በመፈለግ "ምግብ ተመገብ" ብለውት እንኳን "ሰው አላመጠ" በሚል አዋራጅ ሐረግ ገልጾታል።

ቃል ግጥም 188፡- መረረኝ እንደ ሬት በላኝ እንደ ሳማ
የነገረኛን ወሬ ጆሮዬ እየሰማ።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 0706/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ ኹለተኛው ስንኝ ላይ ለማዳመጥ የሚያገለግለውና ጆሮ የተባለው የሰውነት ክፍል ተጠቅሷል። ጆሮ ደግሞ በቃል ተግባቦት ኺደት ከሌላው ሰው የሚተላለፈውን ሐሳብ ወደአእምሮ የማፍሰስ ተግባሩን በየጊዜው ያከናውናል። ሰብቀኛ የኾነ ሰው የሚያስተላልፈውን መጥፎ ነገርንም እንዲሁ ወደሰው አእምሮ ያደርሳል። ይህ ዓይነት ባህርይ ያለው ሰው ሰይጣን የለከፈው እኩይ ፍጡር በመኾኑ ከአንዱ ሰምቶ ለሌላው በሚያቀብለው ነገር የሰውን ጎሊና በእጅጉ ይጎዳል። በቃል ግጥሙም እንደምንመለከተው የጉዳቱ መጠን ከሬት መራራነትና ከሳማ ቅጠል መለብለብ ጋር በንጽጽር ቀርቧል። ይሄውም የቀረርቶ ቃል ግጥሙን ለአቶ አባተ ወርቅነህ ያቀበለው ግለሰብ በሰብቀኛ አማካይነት በየጊዜው በጆሮው የሚሰማው መጥፎ ነገር ሬት ኾኖበታል። ገላን እንደሚለበልብ የሳማ ቅጠልም ውስጣዊ ስሜቱ ተንገብግቧል። በአእምሮው ውስጥ ታምቆ የተቀመጠው ይህ መሰል ችግርም አንገሽግሾታል።

ቃል ግጥም 189፡- የነገረኛ ሰው ምላሱ ሰው ነካ፤ አፉ አሞጠሞጠ
በእርሳስ ይቆርጠዋል ሆዱ የቆረጠ።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 07/06/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

በምልከታዬ መሠረት አቶ አባተ ወርቅነህ በዕለቱ ያቀነቀናቸው ግጥሞች የነገረኝነትን ብቻ ሳይኾን ሌሎች ርእሰ ጉዳዮችንም ያካተቱ እንደነበር ለማስገንዘብ እወዳለሁ። በዚህ የቀረርቶ ቃል ግጥም እንደምንመለከተው ጥናቱ በተካኼደባቸው አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ ነገረኛ የኾነውን እና በምላሱ ሰውን የሚነካውን ግለሰብ በተባ አንደበቱ የተቸው መኾኑን በቀጣዩ

ትንተና መገንዘብ ይገባል። እንደሚታወቀው ምላስ በአፍ ውስጥ ወደፊትና ወደኋላ፣ ወደላይና ወደታች በመንቀሳቀስ ለመናገር የሚያስችል አካል ነው። የነገረኛ ሰው ምላሱ ደግሞ መርዘኛ በመኾኑ የሌላውን ሰው ጎሊና ይጎዳል፤ ያሳምማል፣ ያቆስላልም። ይህንን ለማድረግም የምላሰኛው ሰው አፍ "ተናገር ተናገር" የሚል አባዜ የተጠናወተው ስለኾነ በቅድሚያ ያሞጠሙጣል ተብሏል። በዚህ እኩይ ተግባር ውስጣዊ ስሜቱ የተቃጠለው ግለሰብ ነገረኛውን ሰው ዝም ብሎ ስለማያየው በጥይት ዐረር በጥሶ ሊጥለው እንደሚችል አቶ አባተ ወርቅነህ ካቀነቀነው ቃል ግጥም መገንዘብ ይቻላል።

7.2.10. ስለጦር መሣሪያ አስፈላጊነት፣

የጦር መሣሪያ ሲባል የሞት፣ የማቁሰል አደጋ ወይም ሌላ ጥፋት ሊያደርስ የሚችልና እንደጦር፣ ጠብመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ቦምብ፣ ወዘተ. ያሉትን የሚያካትት መኾኑ ይታወቃል። ከእነዚህ የጦር መሣሪያዎች መካከል ጠብመንጃ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የኾነ ቦታ (ደረጃ) አለው። በተከታይ ከቀረቡት ቃል ግጥሞች መካከልም በአንደኛው ከብዙ ወንድሞችና ከበርካታ ሀብት ይልቅ ጠብመንጃ ተመራጭ እንደኾነ ተገልጿል። በመኾኑም አንድ ሰው ገንዘብ ካለው ራሱን ከጠላት መጠበቅ እንዲችል የሚፈልገውን የጠብመንጃ ዓይነት ገዝቶ ይይዛል። ከመስከረም 05 - 09 /2013 ዓ.ም ድረስ በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው ጭምቃ ሀሳብ የሚያስገነዝበው አሁን አሁን ላይ ቀረ እንጂ ወንድ ልጅ ሲዳር በሀብት የላቀ ደረጃ ያለው ወላጅ አባትም ኾነ ወንድ ዐማት ለሰርጉ በታደመው ሰው ፊት ለሙሽራው ጠብመንጃ ይሸልሙት ነበር። ጠብመንጃ የተሸለመው ሙሽራም የእሱንም ኾነ የሚስቱን ቤተሰቦች ከጥቃት የመጠበቅ ማኅበራዊ ግዴታ አለበት። በእነዚህ መንገዶች ጠብመንጃን በእጁ ያላስገባ ሰው ደግሞ በቤቱ ውስጥ ያሉትን እንስሳት ሸጦ መግዛት ይፈልጋል የሚል ነው። ይህንን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ ከመስክ ከተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች መካክል በአቶ አባተ ወርቅነህ የተቀነቀኑትን ለአብነት ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 190፡- ኧረ ምን ይኾናል የነጭ ላም ብዙ
የተንቀለቀለ ምንሽር ታልገዙ።።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 07/06/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

የቀንድ ከብቶች ለወሎ ቦረና አርሶ አደር ኹለመናው ናቸው ማለት ይቻላል። ይኼውም እርሻውን ያርስባቸዋል። የሀብቱ መለኪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ዕጦት ሲያጋጥመው ከከብቶቹ መካከል የተወሰኑትን ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ ችግሩን ይወጣል። ሲፈልግም ዐርዶ

ሥጋቸውን ይመገባል። ቆዳቸውንም በአካባቢው ባሉ የእደ ጥበብ ሙያተኞች እያስፋቀና እያስለፉ ጀንዲ (ምንጣፍ)፣ መጫኛ፣ አንቀልባ (የሕፃን ልጅ ማዘያ)፣ ለአገልግል መለበጃ እያደረገ ይጠቀም ነበር። በተለይ ላሞችን ለእርባታ ይገለገልባቸዋል፣ ወተትም ያገኝባቸዋል። እንደነዚህ ያሉ ጠቀሜታዎች ካሏቸው የቀንድ ከብቶች መካከል ብዛት ያላቸው ላሞች በቤት ወስጥ መኖር ያለ ጦር መሣሪያ የቱንም ያክል ረብ እንደሌላቸው ለማመላከት "ኧረ ምን ይኾናል" የሚል ጥያቄ በቀረርቶ ቃል ግጥሙ መነሻ ላይ ተነሥቷል። በቃል ግጥሙ መሠረት አንድ ሰው በርካታ ላሞች ከሚኖሩት ይልቅ ምንሽር የተባለና የተንቀለቀለ የጠብመንጃ ዓይነት በገንዘብ ገዝቶ ካልያዘ ዋጋ እንደሌለው ተገልጿል።

ከላይ ያለውንም ኾነ ከዚህ በታች ያሉትን የቀረርቶ ግጥሞች እንዲያቀነቅን ለአቶ አባተ ወርቅነህ መነሻ ምክንያት የኾነው በወግዲ ወረዳ፣ 015 ጎዲንዲት በተባለ ቀበሌ የተከወነው የአቶ ጋሻው አስፋው ሰርግ ነው። በዚህን ወቅት እንደተመለከትኩት በሰርጉ ዕለት በነበረው የምሽት ወቅት ሽማግሌዎች፣ ሙሽራውና ዐጃቢዎች ሙሽራዋን ይዘው ከሙሽራው አባት ቤት ከደረሱ በኋላ ራት ተበልቶ አበቃ። ከዚያም ሚዜውና ሌሎች ሰዎች ሙሽራውን እና ሙሽሪትን ይዘው ወደጫጉላ ቤት ሲኼዱ የተቀሩት የቤተዘመድ አባላትና ጎረምሳዎች ደግሞ በሙሽራው አባት ቤት መጠጥ እየጠጡ ባሉበት ወቅት የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ ተጀመረ። በዚህን ጊዜ ኹለት ወጣቶች ከወዲያና ከወዲህ እያሉ፣ በአካባቢው አጠራር "ግማሽ ክላንሽኮቭ" የተባለውን ጠብመንጃ ወደላይና ወደጎን እያደረጉ፣ ከዚያም ጥይት የሌለው ቃታ እየሳቡ ሲፎክሩ ነበር። አቶ አባተ ወርቅነህም የተለያዩ የቀረርቶ ቃል ግጥሞችን ከማቅራራቱ ጎን ለጎን የእነዚህን ወጣቶች ድርጊት በዓይነ ሥጋው ማየት ችሏል። በዚህ መሠረት ሌሎች ሰዎችም ጠብመንጃ እንዲኖራቸው የመፈለግ ስሜቱ በመቀስቀሱ የተነሣ ይመስላል ቀጣዩን የቀረርቶ ቃል ግጥም ስንኞችን ለማቀንቀን የቻለው የሚል ዕሳቤ አለኝ።

ቃል ግጥም 191፡- ካምስት ወንድማማች ካንድ በረት ከብት
ሰባራ እንኳን ቢኾን ይሻላል ብረት
ባይመቱበት እንኳን ለማስፈራራት።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 07/06/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው ማኅበረሰብ ለጠብመንጃ ያለው ሥየታ (ጉጉት) በጣም ከፍተኛ ነው። አቶ አባተ ባቀነቀነው በዚህ ቃል ግጥምም ከአባት ወይም ከእናት፣ አለበለዚያም ከኹለቱም ከተወለዱ ወንድሞች፣ እንደዚሁም በአንድ በረት ውስጥ ካሉ የቀንድ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ወዘተ. ይልቅ ሰባራ በመኾኑ የተነሣ በትክክል የማይሠራው ጠብመንጃ የተሻለ መኾኑ በንጽጽር ቀርቧል። ሰባራው ጠብመንጃ ካባትና ከእናት

ልጆች፣ እንደዚሁም ከበረት ሙሉ የቤት እንስሳት የበለጠ የተመረጠበት ምክንያትም ተኩሶ በጥይት ዐረር ሰውን ማቁሰል ወይም መግደል ባይቻልም መሣሪያ ይሏል ተብሎ በሌሎች ዘንድ የፍርሃት ስሜትን ለመፍጠርና ለማስጨነቅ ያስችላል ማለት ነው።

ቃል ግጥም 192፡- ኧረ ታየኝ መላ ታየኝ ብልኀት
በሬውን ጠብመንጃ ወይፈኑን ጥይት።
(ምልከታ፣ አባተ ወርቅነህ፣ 07/06/2013፣ ወግዲ ወረዳ)

በዚህ የቀረርቶ ቃል ግጥም ውስጥ ያለው ገጸሰብ ደግሞ አውጥቶና አውርዶ፣ እንደዚሁም መርምሮ በተረዳው መሠረት አንድ ዋና ነገር የዘየደ መኾኑን ገልጿል። ይሄውም ከቀንድ ከብት ወገን የኾነውን፣ ብዙውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚያገለግለውን እና በሬ የተባለውን ተባእት የቤት እንስሳ፣ በተጨማሪም ያልተቀጠቀጠውን ወይፈን ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ ጠብመንጃና ውስጡ በባሩድ በመሞላት ዐረር የተገጠመለትን ጥይት መግዛት ያለበት መኾኑን ባሰናኛቸው መንቶ ስንኞች ለመግለጽ ችሏል።

7.2.11. በሕይወት ዘመን ስለሚያጋጥም ብሶት

ሰዎች የሰመረ ወይም የተሳካ የሕይወት ዘመን እንደሚኖራቸው ሁሉ፣ በተቃራኒው ደግሞ የጠና ብሶት (ችግር) የሚደርስባቸው እንዳሉም መረዳት አያዳግትም። ይህ ጥናት ባካለላቸው አካባቢዎች ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በኑሮ ዘመናቸው የሚደርስባቸውን የባሰ መከራና ሥቃይ በአእምሯቸው ውስጥ ዐምቀው አያስቀምጡም። ከዚህ ይልቅ ሀብታቸው በኾነው ቃል ግጥም በመተንፈስ ሥነ ልቦናዊ ዕረፍትን ሊያገኙ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል። በንግግር ወቅትም እንኳ በደልን እያብሰለሰለ ያለውን ሰው "እስከመቼ ዝም ትላለህ፤ ተንፍስ እንጂ" ይባላል። በዚህ ንኡስ ርእስ ሥር በምንመለከታቸው የቀረርቶ ግጥሞችም የማኅበረሰቡ አባል የኾነው ግለሰብ በራሱ ላይ በደረሰበት ብሶት የተሰማውን የውስጥ ስሜት እንዴት መግለጽ እንደቻለ ቀጥለን እንመለከታለን። ቃል ግጥሞቹ የተከወኑት በቦረና ወረዳ፣ ቀያፈር ቀበሌ በመጋቢት 14፣ 2013 ዓ. ም በነበረው የእስማኤል በላይ የሰርግ ዕለት ማታ ላይ ሲኾን፣ አቅራሪታው አቶ አያሌው ሰይዱ የተባለው ሰው መኾኑን ልብ ይሏል።

ቃል ግጥም 193፡- ብችለው ብችለው በደሉንም ቢኾን
ብሶቱንም ቢኾን ችግሩንም ቢኾን።
ብችለው ብችለው ሞላና በሆዴ ዐንገቱ ደረሰ
እየጓሸ እንቢ አለኝ እየደፈረሰ።
(ምልከታ፣ አያሌው ሰይዱ፣ 14/07/2013፣ ቦረና)

በሰርጉ ዕለት ማታ በአካል ተገኝቼ እንደተመለከትኩት የሰርጉ ታዳሚዎች ምግብ በልተው እንደጨረሱ የጠላ መጠጥ በገፍ ቀርቦላቸው በጎማ መጠጫ በመጠጣት ላይ እንዳሉ አቶ አያሌው ሰይዱም ቆሞ እያቅራራ መጠጡንም ይወስድ ነበር። በዚህን ጊዜ እሱ በርካታ የቀረርቶ ግጥሞችን በአእምሮው ውስጥ ዐምቆ የያዘ መኾኑን ለመገንዘብ ችያለሁ። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት ሌሎች ሰዎች "ተቀበለን" እያሉ ግጥሞችን ቢነግሩትም ሰምቶ እንዳልሰማ በመምሰል የራሱን ግጥሞች ብቻ ያቸኮዳጉድ ነበር። በተለይ የብሶት ቃል ግጥሞችን ማቅራራት ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ ያዜም ነበር። "ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል" እንደሚባለው አቶ አያሌውም መጠጥ እየጠጣ ሞቅ ባለበት አጋጣሚ እንደነዚህ ያሉ ግጥሞችን ማቀንቀኑ በሌሎች ሰዎች እየተበደለ የሚኖር ሰው መኾኑን መገመት ይቻላል። በዚህ መሠረት ከላይ በቀረበው የቀረርቶ ግጥም ውስጥ የተሳለው ገጸሰብ በከፍተኛ ኹኔታ በደል፣ ብሶትና ችግር ደርሶበታል። ይህንን ተገቢ ያልኾነ የግፍ ሥራ ልበ ሰፊ ኾኖ ቢችለውና ትዕግሥት ቢያደርግም ከሚገባው በላይ መከራው ሞልቶ ከመትረፍረፉ የተነሣ ከዐንገቱ መድረሱን ገልጿል። በመቀጠልም ከድንበር ያለፈውን በደሉን ለመተው ወይም ለመርሳት ቢፈልግ እንኳ "እየጓሸ እንቢ አለኝ እየደፈረሰ" በማለት ምሬቱን በሚያንገፈግፍ ስሜት ለማስረዳት ችሏል።

ቃል ግጥም 194፡- ኧረ ተው አንተ ሰው ኧረ ግፉ በዛ!
ዐብሮ አይሰነብትም ሥልጣንና ጤዛ።
(ምልከታ፣ አያሌው ሰይዱ፣ 14/07/2013፣ ቦረና)

የጥናቱ አካላይ በኾኑ ወረዳዎች ያሉ የጎብረተሰብ ክፍሎች በሚኖሩበት አካባቢ በሰላም ሠርተው ሕይወታቸውን መምራት እንዳይችሉ የሚያደርጉና የሚያደናቅፉ አስተዳደራዊ በደሎች መኖራቸውን ከተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች መገንዘብ ተችሏል። በአቶ አያሌው ሰይዱ የተዜመውን ይህን ቃል ግጥም ስንመረምረውም አስተዳደራዊ ብሶትን የሚያመላክት ነው። ይህ ዓይነቱ ብሶት ደግሞ ከመልካም አስተዳደር ዕጦት የሚመነጭ ነው። በመኾኑም በመንግሥት የአስተዳደር ወይም የአመራር መዋቅር ላይ ያለ ሰው ሥጋዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ በሌላው ላይ የሚፈጽመው በደልና ክፉ ሥራ ከመጠን በላይ አልፎ እንደነበር ከቀረርቶ ቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል። "ኧረ ተው ... ይህንን እኩይ ተግባር ከማድረግ ተቆጠብ" በማለት ግለሰቡ በአንደበቱ ሲናገር ተደምጧል። ይህንኑ ሐሳብ በደል ፈጻሚው አስረግጦ እንዲገነዘበው ለማድረግ የሥልጣን ዘመኑን ከሚረግፍ ጤዛ ጋር አነጻጽሮ አቅርቦለታል። ይሄውም በሣርና በቅጠል ላይ ጧት ጧት ወይም ዝናብ ከዘነበ በኋላ ተንቆርዞ የሚታየው ጤዛ (የውሃ ጠብታ) ረፋድ ላይ ፀሓይ ሲመታው እንደሚረግፍ ሁሉ ማንኛውንም ነገር ለመሥራት የሚያስችልህ

ሹመት ወይም የኃላፊነት ቦታ ከአንተ ጋር ኾኖ ብዙ ዘመን አይኖርም፤ አያረጅም አያፈጅም ብሎታል።

ቃል ግጥም 195፡- ኧረ ተው አንተ ሰው ደጀን አትረሰው
አይተህ አታውቅም ወይ ጊዜ የጣለው ሰው።
(ምልከታ፣ አያሌው ሰይዱ፣ 14/07/2013፣ ቦረና)

በአቶ አያሌው ሰይዱ በተዜመው በዚህ የቀረርቶ ቃል ግጥም ውስጥ በኹለት ጎራ የተመደቡ ሰዎችን እናገኛለን። አንደኛው የፈለገውን ለማድረግ ወቅቱ ያመቸውና ኑሮው የተሳካለት ሰው በበደለኛነት ወገን የተቀመጠ ሲኾን፣ ቀን የጎደለበት ብሶተኛው ሰው ደግሞ በኹለተኛ ጎራ የተደለደለ ኾኗል ማለት ነው። በመኾኑም ቀን ጎድሎበት ብሶተኛ የኾነው ሰው መግቢያና መውጫ በመኾን ሲያገለግለው የነበረው ደጁ ወቅት በገጠመው ሰው ታርሶበታል። በእንደዚህ ያለ ኹኔታ በደል የተፈጸመበት ሰው የሚሰማው ስሜት በጣም ኃይለኛ ነው የሚኾነው። ምንም እንኳን በአካባቢው ያለ ማንኛውም የማኅበረሰቡ አባል "በአባት መሬትና በሚስት የለም ዋዛ" የሚለው አባባል በአባቶቹ እየተነገረው ያደገ ቢኾንም ጊዜ የጣለው ሰው ግን ለተፈጸመበት ክፉ ድርጊት ምላሽ ለመስጠት የማይችል መኾኑን ገልጿል። ቀን የጎደለብኝ መኾኔን ተረድተህ ከቤቱ ውጭ ያለውን ቦታዬን ከማረስ ተቆጠብ በማለት በዳዩን ሰው ተማጽኖታል።

ምዕራፍ ስምንት፡- የቃል ግጥሞቹ ፋይዳ

እንደሌሎቹ የፎክሎር ዘርፎች ቃል ግጥምም በርካታ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑን በጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ Bascomን (1954፡343-349)፣ Baumanን (1971፡38—39)፣ Douglasን (2000፡84) እና Dundesን (2007:56) በመጥቀስ ለመግለጽ ተችሏል። በተለይም በእርሻ ሥራ በሚተዳደር ማኅበረሰብ ዘንድ ብዙ ጉልበትን የሚጠይቁ በርካታ ሥራዎች ስላሉ የቃል ግጥሞች ስሜትን በማነሣሣት፣ በማስተባበር፣ በማበረታታት፣ ሥራውን የበለጠ አስደሳች በማድረግ፣ በማዝናናት፣ ወዘተ. በኩል በጣም በርካታ ፋይዳዎች ያሏቸው መኾኑንም Peek, M. and Yankah (2004:220) አብራርተዋል። ይህ ጥናት በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚገኙ አርሶ አደሮች አንደበት የተቀነቀኑት የቃል ግጥሞችም ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ፋይዳዎች ያሏቸው መኾኑን ለመመርመር ተችሏል። በዚህ መሠረት በቃል ግጥሞቹ አማካይነት የተገኙት ፋይዳዎች በሚከተለው ኹኔታ ቀርበዋል።

8.1. ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ ፋይዳ

ቃል ግጥሞች ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ፈጸሟቸው የሚባሉትን የጀግንነት ተግባራት ለተከታዩ ትውልድ በታሪክነት በማስተላለፍ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላሉ። በዚህ መሠረት በሀገራችን ጀግና የኾኑትን ሰዎች የቆራጥነት፣ የጽኑ እምነት፣ የታጋይነት፣ ወዘተ. ትእምርት (symbol) መኾናቸውን በማሳየት አርኣያነታቸውን ዘላለማዊ የማድረግ ኃይል አላቸው ማለት ይቻላል። ከእነዚህ ጀግኖች መካከልም ድምፃውያን ሕዝባዊ በኾኑ የቃል ግጥሞቻቸው አማካይነት ስሙን እያወደሱ፣ በሕይወት ዘመኑ የፈጸማቸውን ተግባራት እያወሡ ያዜሙለትን በላይ ዘለቀን[33] እናገኛለን። የሰባ አምስቱ የዕድሜ ባለጸጋ የኾኑት አቶ አሰን እንድሬ በ07/01/2013 ዓ.ም እንደነገሩኝ ከኾነ በላይ ዘለቀ በቀድሞው አጠራር በወሎ ክፍለ ሀገር፣ በቦረና ሳይንት አውራጃ፣ በወግዲ ወረዳ፣ ጫቀታ በተባለው አካባቢ፣ ገዛዛ አቦ ቀበሌ ከአባቱ ከባሻ ዘለቀ ላቀውና ከእናቱ እመት ጣይቱ አሰኔ በ1904ዓ.ም የተወለደ ሲኾን፣ በስህተት ነጋሽ አሰኔ የተባሉትን አጎቱን ከገደለ በኋላ "ዱር ቤቴ" ብሎ ወደአባይ በረሓ ገባ። ከዚያ በኋላ በጣሊያን የሀገሩ መደፈር እንደእግር እሳት አንገብግቦት ጠላትን መግቢያና መውጫ ያሳጣው ጀመር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ የጀግንነት ታሪኩ እስካሁንና ወደፊትም ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርጉትን አራት ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት።

[33] በንኡስ ርእሱ በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ሥር በላይ ዘለቀ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ‹‹ዱር ቤቴ›› በማለት ኢትዮጵያን ለመውረር ከመጣው ጣሊያን ጋር ለመዋጋት በረሓ እስከገባበት ወቅት ድረስ ያለው ታሪክ አልተካተተም። ምክንያቱም የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ያንን ታሪክ የሚያሳዩ ኾነው ባለመገኘታቸው የተነሣ ነው።

ቃል ግጥም 196፡- የእነ በላይ እናት የመነመነችው በርበራዋን ወልዳ ጣሊያንን ፈጀችው፡፡

(ቃለ መጠይቅ፣ ይመር አሰን፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በላይ ዘለቀ ከአርበኞች የትግል አጋሮቹ ጋር በመኾን ለአምስት ዓመታት ያኽል በአባይ ወንዝ አካባቢ ያሉ ዋሻዎችን እና ተራራዎችን ምሽግ አድርጎ ከውጭ የመጣውን ጠላት መፈናፈኛ በማሳጣት ታላቅ የጀግንነት ተጋድሎን እንደሠራና በዚህም በርካታ ጠላትን እንደፈጀ አቶ አሰን እንድሬ ገልጸውልኛል፡፡ ይህንን የጀግንነት ተግባሩን መሠረት በማድረግ አቶ አበራ ጀምበሬ በ1983 ዓ.ም ባሳተሙት ታሪካዊ ልቦለድ በላይ ዘለቀን “አባ ኮስትር” በማለት ዋና ገጸ ባሕርይ ከማድረጋቸው በተጨማሪ የመጽሐፉንም ርእስ በዚሁ የገጸ ባሕርይ ስም ሰይመውታል፡፡ ደራሲው በላይ ዘለቀን “ኮስትር” በማለት የጠሩትም ግለሰቡ ጽኑ እምነት የነበረው፣ ኃይለኛ፣ ዋዛ ፈዛዛን የማይወድ፣ ጠላቱን በቆራጥነት የፈጀ ባለታሪክ መኾኑን በማሳወቅ በተከታዩ ትውልድ ልቡና ውስጥ የእሱን የጀግንነት ስሜት ለመትከልና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡

ወደቃል ግጥሙ ስንመለስ “እናት” የሚለውን ቃል በመጀመሪያው ስንኝ ላይ እናገኛለን፡፡ ቃሉ ደግሞ ሦስት ፍቺዎችን ይጠቁመናል፡፡ አንደኛው አንዲት ሴት ከወለደችው ልጅ ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት መኾኑን ያመለክታል፡፡ ኹለተኛው ደግነትን፣ ሩኅሩኀነትን፣ ወዘተ. ያሳየናል፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ሕዝቦች በውስጧ ለሚኖሩባት፣ የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልልና አንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ላላት ሀገር በተምሳሌትነት ይቆማል፡፡ በመጀመሪያው ትርጉም መሠረት “የእነ በላይ እናት … ሲል የበላይ ዘለቀን እናት እመት ጣይቱ አሰኔን እንዲናስብ ያደርገናል፡፡ በመኾኑም ሴትዮዋ ትክለ ሰውነታቸው የከሳ፣ የቀጠነና የኮሰመነ ቢኾንም ከአብራካቸው የተወለዱት በላይ ዘለቀና እጅጉ ዘለቀ ግን በበርበሬ በመመሰል ባሕር አቋርጦ የመጣውን የጣሊያንን ጦር በኃይል ወግተው መፍጀታቸውን ወይም መጨረሳቸውን ታሪክ ተኮር ቃል ግጥሙ ያስገነዝበናል፡፡ በሦስተኛው ፍች መሠረት እናት በሀገር ተምሳሌትነት ስትቆም ደግሞ ከበላይ ዘለቀ ጋር የጀግንነትን ባሕርይ ተላብሰው በአርበኝነት ዘመናቸው አኩሪ ታሪክ የሠሩት ጀግኖች ዛላው በድልህ፣ በአዋዜ ወይም በዱቄት መልክ ተዘጋጅቶ ሲበሉት በሚፋጅ ወይም በሚያቃጥል በርበሬ ተወክለው ጠላትን በመጨረስ ታላቅ ተጋድሎ መፈጸማቸውን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሙ ጀግኖቹ እንዲዘከሩ፣ ተጋድሏቸውም ቢኾን ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍና አርኣያነታቸውም ቀጣይነት እንዲኖረው አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ የበላይ ዘለቀን የጀግንነት ታሪካዊ ፋይዳ ማንሣቱ ተገቢ ስለመሆኑ ተከታዩን ቃል ግጥም እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 197፡- ጥጡም ተወደደ ከበደ ሽሬታው
አንድ ሱሪ ነበር በላይ አስወደደው፡፡

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቀድሞ ጊዜ የቤት እመቤቶች በቆላ አካባቢ የሚበቅለውን ጥጥ ጊዜ ፈጅተው በመዳመጥ፣ በማባዛት፣ በመፍተል፣ እንደዚሁም ድርና ማግ አድርገው በሸማኔ በማሠራት የራሳቸውንም ኾነ የቤተሰቦቻቸውን ዕርቃን ለመሸፈን፣ ጎፍረተ ሥጋቸውን ለመሰወር ይችሉ እንደነበር ከታሪክ መገንዘብ እንችላለን፡፡ በዚያን ወቅት ከላይ የተዘረዘሩትን ኺደቶች አልፎ ለቀሚስ፣ ለነጠላ፣ ለእጀ ጠባብ፣ ለሱሪ፣ ለጋቢ፣ ወዘተ. አገልግሎት ይውል የነበረው ጥጥ ዋጋው በመናሩ የተነሣ በገንዘብ አማካይነት ሽሬታ (ልውውጥ) ለማካኼድ እጅግ በጣም ማስቸገሩን ቃል ግጥሙ ያመላክታል፡፡ በዚህ ምክንያት የሚለበስ ልብስ መጥፋቱን፣ አንድ ሱሪ በገበያ ላይ ቢገኝ እንኳ በላይ ዘለቀ በውድ ገዝቶ መታጠቁን እማሬያዊ በኾነ ፍች እንገነዘባለን፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎችም ኾነ በሌላው የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብ ዘንድ ግን ሱሪን በጀግንነት ይፈክረዋል (ይተረጉመዋል ወይም ይፈታዋል)፡፡ ለአብነትም "ሱሪ ታጠቀ" ሲባል ወንድ ወጣው፣ የጀግንነት ሞያ ሠራ ማለት እንደኾነ መረዳት ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት በላይ ዘለቀ የታጠቀው ሱሪ የጀግንነት ትእምርት መኾኑን ቃል ግጥሙ ማሳየት ችሏል፡፡

የቃል ግጥሞች በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ገናን የጀግንነት ተግባራትን ቀጣይነት እንዲኖራቸው እንደሚያደርጉ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ በጎብረተሰቡ አንደበት የሚቀነቀኑት የቃል ግጥምች በየዘመናቱ ገኸር የኾኑ መንግሥታት "አልጋዬን ይነቀንቃል" ብለው በጠረጠሩት ጀግና ላይ የሚወስዱትን ርምጃ ማንጸባረቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ አቶ አሰን እንድሬ በነገሩኝ መሠረትም በ1933 ዓ.ም የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ እንደወጣ ሌሎች ሹማምንት የተሻለ ሹመት ሲያገኙ በላይ ዘለቀ ግን ከዓመት በኋላ የቢቸና አውራጃ አስተዳዳሪ ኾኖ ተሾመ፡፡ ግለሰቡ ለሀገሩ ጽኑ እምነት የነበረው፣ ኃይለኛ፣ ጠላቱን በቆራጥነት የተዋጋ ቢኾንም፣ ይህ ዓይነቱ የጀግንነት ድርጊቱ ካልተዋጠላቸው ከዘመኑ ሹማምንት ጋር አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ በኋላ ላይም በባንዳዎች አቀናባሪነት ንጉሠ ነገሥቱ ጦር አዘመቱበት፡፡ ከዚያም ሶማ በተባለው በረሓ አስከፊ የኾነ ውጊያ እየተደረገ ሳለ ለድርድር ከመንግሥት በተላኩ ካህናት አማካይነት አባ ኮስትር በላይ እጁን እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ በመጨረሻም ሀገሪቷ በነበራት ልዩ ፍርድ ቤት በስቅላት እንዲቀጣ ስለተወሰነበት ጥር 5 ቀን

1937 ዓ.ም ማተቡ ገመድ ኾኖ ስቅላቱ ተፈጸመበት በማለት አቶ አሰን እንድሬ በዝርዝር ገልጸዋል። ይህንኑ አሳፋሪ ድርጊት የሚያመለክቱትን የቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 198፡- ፈሪ ንጉሥ ፈርቶ ከባንዳዎች ጋራ
አርቀው ሰቀሉት እንዳይንጠራራ።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

እንደ አሰን እንድሬ ገለጻ በላይ ዘለቀ "ንጉሡን ተቃውሞ በመሸፈት አልጋቸውን ሊነቀንቅ ነው" የሚለው የተሳሳተ መረጃ ለኢጣሊያ መንግሥት ዐድረው በነበሩት ባንዳዎች አማካይነት በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ ተቀምጠው ለነበሩት ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ ይነገራቸዋል። እሳቸውም የሀገሪቷ የሕዝብ እረኛ፣ አውራ፣ መሪና ዐሳዳሪ መኾናቸው የሚታወቅ ቢኾንም በባንዳዎቹ በተነገራቸው የተሳሳተ መረጃ የተነሣ በከፍተኛ ኹኔታ ፍርሃት እንዳደረባቸው ቃል ግጥሙ ያመለክታል። በዚህ ምክንያት ወዳጆቻቸው ለኾኑት ባንዳዎች ሹመትና ሽልማት ሲሰጡ ጠላቱ ነው ብለው የፈረጁትን በላይ ዘለቀን ግን በቀላሉ ከማይደረስበት ቦታ ላይ ተሰቅሎ እንዲገደል ማድረጋቸውን ታሪክ ነጋሪ ከኾነው ቃል ግጥም መገንዘብ እንችላለን።

ቃል ግጥም 199፡- አሳዘነኝ በሬው አሳዘነኝ ከሞቱ አሟሟቱ
አልቆረጥ አለ ገመዱ ካንገቱ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ከሙሐመድ ይማም፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ "በሬ" የሚለው አሐድ ተጠቅሷል። አሐዱን እማሬያዊ በኾነ መልኩ ስንመለከተው ከቀንድ ከብት ወገን የኾነ፣ ብዙውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚያገለግል የቤት እንስሳ መኾኑን እንረዳለን። በሌላ በኩል ደግሞ አሐዱን "ጀግና" በሚለው መፈከር እንችላለን። በዚህኛው ትርጓሜ ለሀገሩ፣ ለወገኑ መሥዋዕትነት ከፍሎ ጥሩ የጀግንነት ተግባር ላከናወነው በላይ ዘለቀ በውክልና ቆሟል። በመኾኑም ይህ ጀግና ከቃጫና ከሌሎች ነገሮች ተሸርቦ በተዘጋጀው ጠንካራ ገመድ ተሰቅሎ ነፍሱ ከሥጋው እንዲትለይ ወይም ሕይወቱ ፍጻሜዋን እንዲታገኝ ለማድረግ ሲባል ክፉ ነገር መሠራቱ አስተከዘኝ፣ አስከፋኝ፣ አስቀየመኝ፣ ወዘተ. በማለት የቃል ግጥሙ ባለቤት አቀንቅኗል። እኛም በላይ ዘለቀ በዐንገቱ ገመድ ገብቶ ክፉ አሟሟት እንዲሞት መደረጉና አስከሬኑንም በስለት ቆርጦ ማላቀቅ አለመቻሉ ትልቅ ቅሌትና ውርደት መኾኑን እንገነዘባለን።

8.2. የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን የማስተማር ፋይዳ

ማኅበራዊ ትስስር ኖሮት በተወሰነ አካባቢ ወይም ቦታ የሚኖር ሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸው መልካም ዕሴቶች (ስጦታዎች) አሉት፡፡ እነዚህ መልካም ዕሴቶችም በቃል ግጥሞች ይገለጻሉ፡፡ በዚህ መሠረት ሞራልን ወይም ግብረ ገብነትን፣ እንደዚሁም ጥሩ ወይም መልካም ሥራን የሚያንጸባርቁ ዕሴቶችን በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆችን እና ወጣቶችን በማስተማር ገና ከለጋነታቸው ጊዜ ጀምሮ ባሕርያቸውን መቅረጽ ይቻላል፡፡ በዚህም ምግባረ መልካምና ትሑት ትውልድን ማፍራት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ቃል ግጥሞች ማኅበረሰቡ የተስማማባቸውን መልካም ዕሴቶች ተከታዩ ትውልድም ተቀብሎ በተግባር ላይ እንዲያውላቸው ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡ ከመስክ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን የማስተማር ፋይዳ ካላቸው መካከል ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ቃል ግጥም 200፡- አይሰርቅ አይቀማ እንደ ጎረምሳ
አባቱን በጅል የማያስነሣ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ በለጠ አደላ፤ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም መሠረት ከ14 — 18 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወንዶች ልጆች መካከል አንዳንዶች በመጎርመሳቸው የተነሣ የተለያዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የሰውን ንብረት ይሰርቃሉ፤ ይቀማሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ ሁሉ በፊት ግን በጎ ምግባርን ለማስተማር በማኅበረሰቡ አንደበት የሚነገሩት ቃል ግጥሞች ልጆች ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምሮ የሰውን ንብረት በመዝረፍና በመቀማት በእኩይ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ያስተምራሉ፡፡ ግጥሙን የነገረኝ ጎረምሳም ምግባሩ የቀና በመኾኑ እንደ ሌሎቹ ዕድሜ እኩዮቹ በመስረቅና በመቀማት ወላጆቹን በክፉ የማያስነሣ መኾኑን ገልጿል፡፡ በዚህ የተነሣ በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆች ወላጆቻቸውን በመጥፎ እንዳያስጠሩና በክፉ ነገርም እንዳያሳሙ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ኹኔታ ያደጉ ልጆችም በተራቸው ዐዋቂ ኾነው ወልደው ሲከብዱ በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆቻቸው ከንቱ የኾኑ ነገሮችን እንዳይከተሉ ይመክሯቸዋል፤ ያስተምሯቸዋልም፡፡ ይህ ዓይነቱ ማኅበራዊ መልካም ዕሴት እንዲህ እንዲህ እያለ ሲተላለፍ እውነተኛና ደግ የኾነ ትውልድን ማፍራት ይቻላል ማለት ነው፡፡

ቃል ግጥም 201፡- ዱብ ዱብ እንደ ወጥ ሠሪ
ለባልንጀራው ቁም ነገር ሠሪ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሰሚራ ጌቶ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የዚህ ቃል ግጥም ባለቤት የሆነው ግለሰብ በፉከራ የዜማ ስልት ዱብ ዱብ ማለቱን ገልጿል፡፡ በዚህ አካላዊ እንቅስቃሴውም ከላይና ከታች ተፍ ተፍ በማለት ጣት የሚያስመጥጥ ወጥን

ከሚያዘጋጅ ሰው ጋር በንጽጽር ቀርቧል። ዱብ ዱብ ማለቱ ደግሞ ለባልንጀራው ጠቃሚ የኾነ ነገር በሚሠራበት ወቅት መኾኑን መረዳት እንችላለን። ምክንያቱም ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለልጆቻቸው "በመከራና በጭንቅ ቀን ጥሎህ ከሚሸሽ ሰው ጋር ባልንጀራ አትኹን፤ እንደዚሁም በመከራና በጭንቅ ቀን ባልንጀራችሁን አትጣሉት። ባልንጀራችሁን በሙሉ ልባችሁ ከወደዳችሁት በመከራችሁ ቀን አይለያችሁም" በማለት ማኅበረሰቡ መልካም የኾኑ ማኅበራዊ ዕሴቶችን በማስተማር ላይ እንደሚገኝ በመስከረም 07/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊ የነበሩት አቶ አብዱ ሰይድና ሁሴን አደም ገልጸውልኛል። ከላይ ያለውን ቃል ግጥም የነገረኝ ግለሰብም የማኅበረሰቡ አባል እንደመኾኑ ማንኛውም ሰው ለጓደኛ ወይም ለባልንጀራ ጠቃሚ የኾነ ጉዳይ ወይም ቁም ነገር ማድረግ እንደሚገባ ሐሳቡን በማስተማሪያነት ማቅረቡን መገንዘብ እችላለን። ይህ ዓይነቱ ቃል ግጥም "ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ" ከሚለው ከፈጣሪ ትእዛዝ ጋር በጣም ቁርኝት ያለው በመኾኑ ሰዎች በመተጋገዝ፣ በመረዳዳትና በመተሳሰብ እንዲኖሩ በማስተማር መልካም የኾነው የማኅበረሰብም ዕሴት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይችላል።

ቃል ግጥም 202፦ ትከሻው ደማቅ እንደ ጨረቃ
የተናገረው አንዱ የሚበቃ።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ዘይቤዎች ለቃል ግጥሞች ርእሰ ጉዳይ ማንጸሪያ መኾናቸው የሚታወቅ ነው። ምክንያቱም ግጥሞቹ ጥልቀት ያላቸው ትርጉሞችን እንዲሰጡና ውበትን የተላበሱ እንዲኾኑ ለማድረግ ሲባል እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል። በዚህ ጥናት ትንተና በተካኼደባቸው ቃል ግጥሞችም በአብዛኛው አነጻጻሪ ዘይቤ በአገልግሎት ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ ግጥምም የሰው ትከሻና ጨረቃ በንጽጽር ቀርበዋል። እንደሚታወቀው በሌሊት ወቅት ሙሉ የኾነችው ጨረቃ ከፀሓይ የምታገኘውን ብርሃን ወደመሬት በምትፈነጥቅበት ወቅት በሰማይ ላይ ጎላ ብላና አምራ፣ደምቃ የምትታይ አካል ናት። በንጽጽሩ መሠረት በቃል ግጥሙ የተሳለው ገጸሰብ ትከሻም የጎላ፣ ያማረ፣ እንደ ጨረቃ ብርሃን ደምቆ የሚታይ መኾኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ዓይነት ትክለ ሰውነት ያለው ሰው ሐሳቡን ለሌላው አካል በሚገልጽበት ወቅት በንግግሩ ወጥ የኾነ አቋም እንዳለው፣ የመጨረሻ ውሳኔው ፍጹም ኾኖ አንዱ እንደሚበቃ በአንደበቱ ባሰናኛቸው ቃል ግጥሞች ገልጿል። "የተናገረው አንዱ የሚበቃ" የሚለው አባባል በሌላ መንገድ ሲተረጎምም ግለሰቡ ሐሰት፣ ከእውነት የራቀ ነገር የማይናገር፣ ዕብለት የማይታይበት መኾኑን

እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሙ ለተከታዩ ትውልድ የአነጋገር ሥርዓትን በማስተማር ረገድ ተግባራዊ የሕይወት መመሪያ በመኾን ማገልገል ይችላል ማለት ነው፡፡

ቃል ግጥም 203፡- ቀብር ቀብር አሉ ቀብር ምን አለበት
መልካም ሥራ ሠርተው ኼደው ቢተኙበት፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሬ፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

የሰው ልጅ ክፉ ወይም ደግ የሚኾነው በራሱ ምርጫ እንጂ በፈጣሪው አለመኾኑን የሚያስገነዝበውን ሐሳብ ሼህ ሙሐመድ አሜን በሚያዝያ 22/ 2013 ዓ.ም በደሴ ከተማ አባ ሰርባ በተባለው መስጊድ የዐርብ ሶላት ከመሰገዱ በፊት ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሲያስተምሩ የሰማሁት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተመሳሰለ መልኩ አንድ ሰው ክፉ ሥራን የሚሠራ ከኾነ ቅጣትን የሚቀበል፣ ሌላው ሰው ደግሞ ምርጫው መልካም ሥራ ከኾነ ደግ ወይም ጥሩ ነገርን ከፈጣሪው የሚያገኝ መኾኑን ከማኅበረሰቡ የቃል ግጥሞች አስተምህሮ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም ማለፊያ ወይም መልካም የኾነ ሥራን የሠራ ሰው ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ አስከሬኑ ወደመቃብር ከወረደ በኋላ ሲፀነስ ጀምሮ በሥጋው ያደረችው ሕይወቱ ጻድቃን እስከምጽኣት ድረስ ይኖሩበታል ተብሎ በሚታሰበው የገነት ቦታ እንደምትቀይ ተገልጿል፡፡ በዚህ የተነሣም አስከሬኑ በመቃብር ውስጥ ዐፈርና ድንጋይ የሚጫነው ቢኾንም የማይጎዳና የማይቸገር መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ በኾነ መልኩ ቃል ግጥሙ ሲፈከር ደግሞ ክፉ ሥራን የሠራ ሰው ከሞተ በኋላ ክፉዎች የሥራቸውን ዋጋ ያገኙበታል ተብሎ ወደሚታሰበው ወደገሃነም ነፍሱ እንደምትገባ ማጤን አስፈላጊ ይኾናል፡፡ በመኾኑም ቃል ግጥሞች ልጆች መልካም የኾኑ ምግባሮችን መከተል፣ ከክፉ ነገሮች ኹሉ መራቅ እንደሚገባቸው የሚያስተምሩ መኾናቸውን ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ቃል ግጥም 204፡- መገን ያቺ ቆንጆ የምታቀርበው ማድ
ሁሉም ይበላዋል አይለይበትም ባዳና ዘመድ፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽ አብዱ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

“ሰው ብቻውን ይኾን ዘንድ መልካም አይደለምና ረዳት እንፍጠርለት” (መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዘፍጥረት፣ 1980፣ 2፣18) የሚለው የፈጣሪ ቃል ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረት መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ፈጣሪ ሰውን በኑሮው በኩል ከሌላው ሰው ጋር እንጂ ብቻውን በሕይወት እንዲኖር ያልፈጠረው መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነትም የሰው ልጅ እስካሁን ድረስ ከሌሎች ጋር መኖርና ከእነሱም ጋር በማኅበራዊ ሕይወት ተባባሪ መኾን ችሏል ማለት ነው፡፡ ከላይ በለቅሶ ወቅት ለሐዘን በተገጠመው ቃል ግጥምም ውብ የኾነች አንዲት ሴት በሕይወት

በነበረችበት ወቅት በማኅበራዊ ኑሮዋ ከሌሎች ጋር ተባባሪ በመኾኗ የተነሣ “ይሄ የሥጋ ዘመዴ ያልኾነ ባዕድ ነው፤ ይኼ ደግሞ በትውልድ የአባቱ ወይም የእናቱ ወገን ነው” ብላ ሳትለይ ሁሉንም በአንድነት በማየት ምግብ አዘጋጅታ ታበላ እንደነበር ተገልጿል። በመኾኑም ከማኅበራዊ ዕሴቶች መካከል አንዱ የኾነውን ለጋስነት በቃል ግጥሞች አማካይነት ለቀጣይ ትውልድ ማስተማር እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል። ከላይ ከቀረበው ትንተና ጋር በይዘት ተመሳሳይነት ያለውን የለቅሶ ግጥም በተጨማሪነት ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 205፦ አትጨክኝም ነበር ሰው ታመመ ቢሉሽ
ልብስ፣ ምግብ፣ ገንዘብ ተቸገረ ቢሉሽ
ካለሽም መንዝረሽ ካጣሽ ተበድረሽ
ወዲህ ወዲያ ብለሽ አለዚያም ለምነሽ።
ክፉ እንኳን አልነበርሽ ትረጂኝ ነበረ
ዛሬ ብትለይኝ ሁሉም ነገር ቀረ።
(ቃለ መጠይቅ፣አካሉ ወደደኝ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

የሙሾ ቃል ግጥሙ ለጋስ የኾነች ሴት በሞተች ጊዜ በአስለቃሿ አማካይነት የተቀነቀነ ነው። ከቃል ግጥሙ አኳያ ሴትዮዋ በሕይወት በነበረችበት ዘመን በማንኛውም ነገር ራሮት የሚሰማት መኾኑን እንገነዘባለን። በመኾኑም የቃል ግጥሙ አውራጅ በቀጥታ ስላቀነቀነለት ችግረኛ ሰውና ለችግረኛውም እርዳታ ስላደረገችለት ሴት ለአንድ አፍታ እንዲናስብ አድርጎናል። በዚህ መሠረት ችግረኛ የኾነው ሰው “ጤና ዐጣ፤ በሽተኛ ኾነ፣ ወዘተ.” የሚለውን መልእክት ሩጎሩጎ የኾነችዋ ሴት ከሰማች ልቧ ስለማይጠና እንደምትረዳው ተገልጿል። በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ሴትዮዋ ከችግሩ በስተቀር ምንም ዓይነት ሌላ መሥፈርት ስላላወጣች “ሰው” የሚለውን እሳቤ የተረዳችው የአዳም ዘር የኾነውን፣ ነፍስና ሥጋ ያለውን፣ ማሰብና ማመዛዘን የሚችለውን ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር መኾኑን አንባቢያን ልብ ሊሉ ይገባል። በመኾኑም የተቸገረው ሰው ገንዘብ በማጣቱ የተነሣ “እገሌ ታረዘ፣ ተራበ፣ ተጠማ” ካሏትም በቤቷ ውስጥ ገንዘብ ካላት ለልብስና ለምግብ ከፋፍላ እንደምትደግፈው፣ ካጣች ደግሞ ከሌላ ሰው ተበድራ፣ አለበለዚያም ርዳታ አድርጉልኝ ብላ በመለመን እገዛ የምታደርግለት መኾኑ ታውቋል። በመጨረሻም ሴትዮዋ በአሁኑ ጊዜ በመሞቷ የተነሣ ያ መልካም የኾነው ተግባሯ ሁሉ ሊቀር ችሏል። ስለዚህ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ. ሲደገፍ የነበረው ሰው ዐጣሁ ነጣሁ፤ ባዶ እጁን ኾንኩ፤ መና ቀረሁ የሚለውን ሐሳብ በግጥሙ አውራጅ በኩል ሲናገር ተደምጧል። በአጠቃላይ የሙሾ ቃል ግጥሞቹ የማኅበራዊነትን፣ እንደዚሁም የመተባበርን ዕሴቶች ጠቀሜታ የማስተማር ፋይዳ ያላቸው መኾኑን መገንዘብ ይገባል።

8.3. የታታሪነትን ጥቅም የማሳወቅ ፋይዳ

በዚህ የመረጃ ትንተና መትጋት የሚለው ቃል በሥራ መበርታትን፣ መታተርን፣ ጥረት ማድረግን፣ መጠንከርን፣ ከስንፍና መራቅን፣ ሥራ መውደድን የሚያመለክት መሾኑን በቅድሚያ ማጤን ይገባል። “ምንም ነገር ሳትሞክር አይሳካልኝም ብለህ ስንፍናን አትማር” የሚለው አባባል የትጋትን ብያኔ ያጠናክረዋል የሚል እምነት በአጥኚው አእምሮ ውስጥ አድሯል። የአባባሉ አፍላቂ የሾነው የኅብረተሰብ ክፍልም የታታሪ ሠራተኞች መፍለቂያ እንጂ የሰነፎች መኖሪያ እንዳይሾን ያሰበ መሾኑን መረዳት ይኖርብናል። ከአባባሉ በላቀ ደረጃ ደግሞ ቃል ግጥሞች በሥራ የመትጋትን ባህል ይሰብካሉ። በዚህ መሠረት የቃል ግጥሞች የሥራ ፍቅር እንዲኖር በማድረግ ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊው ልማት የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። ተከታዮቹ ቃል ግጥሞችም በሥራ የመትጋትን ባህል ለትውልድ እያሳወቁ የቆዩ መኾናቸውን ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 206፡- ኧረ ሰዎች ሰዎች መሥራት ነው ጠንክሮ
ማዳበሪያ አምጥቶ መክበር ነው ዘንድሮ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ወንድወሰን ታረቀኝ፣ 22/05/2018፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ “ሰዎች” የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ቀርቧል። ይህ የኾነበት ምክንያት የግጥሙን ርእሰ ጉዳይ ለማጠንከርና በዋናው ነጥብ ላይ ትኩረት ለመስጠት ሲባል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ “ኧረ” በሚል መነሻ አርሶ አደር ለኾኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ላይ አተኩሯል። ምክር አዘል ማስጠንቀቂያውም አርሶ አደሮቹ አንድን ነገር በርትተውና ጠንክረው ማከናወን ያለባቸው መኾኑን ለመግለጽ ነው። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮችም ጠንክረው ማከናወን ካለባቸው ነገሮች መካከል አንደኛው የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ ተጠቅመው ምርታማነታቸውን በማሳደግ ድኽነትን ማስወገድ፣ ራስን በመቻል ሕይወትን መምራትና በቂ የኾነ ሀብትን ማጠራቀም ይገባቸዋል የሚል ነው። ምክንያቱም ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ የኾነውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ በዘርና በዐረም ወቅት ከዐፈር ጋር ቀላቅሎ የተትረፈረፈ ምርት በማግኘት ባለጸጋ ወይም ሀብታም መኾን እንደሚቻል አቀንቃኙ በአንክሮ ገልጿልና ነው ።

ቃል ግጥም 207፡- የበጎቹን በጠጥ ልዛቀው በአካፋ
እንጀራ አይበላም ቁጭ ብዬ ሳልለፋ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም የምናገኘው አርሶ አደር ኪደታዊ የኾኑ የእርሻ ተግባራትን በትጋት በማከናወን ላይ የሚገኝ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ ይኼውም በመጀመሪያ ደረጃ የበጎች ማደሪያ ከኾነው ጋጣ የእንስሳቱን ፍግ በአካፋ ያፍሳል፡፡ ቀጥሎም ፍጉን ቀድሞ በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ከጨመረ በኋላ ለኹለት ወራት ያኽል ከውሃ ጋር በማዋሓድ ብስባሽ ያዘጋጃል፡፡ ከዚያም የዘር ሥራ ከመካኼዱ ከአንድ ወር በፊት ደጋግሞ ወዳረሰው ማሳ በተደጋጋሚ ብስባሹን በጆንያ እየተሸከመ ካደረሰ በኋላ እየበተነ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ያደርጋል፡፡ አርሶ አደሩ እነዚህን ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት ሳይታክት የሚያከናውነው ብስባሹ በውስጡ በያዛቸው ንጥረ ነገሮች አማካይነት ሰብሎቹ ዳብረው የተትረፈረፈ ምርት ማግኘት ስለሚችል ነው፡፡ በዚህ ዓይነት የሥራ ኪደት በመትጋት ፋንታ ዝም ብሎ የሚቀመጥ ከኾነ ግን እንጀራ መብላት፣ ከዚያም ዐልፎ ሀብት ማግኘት እንደማይችል ባቀነቀነው ቃል ግጥም አስረድቷል፡፡ በዚህ መሠረት “እንጀራ አይበላም” የሚለው ሐረግ አንድም ጠንክሮ የማይሠራው አርሶ አደር ወቅት ጠብቆ ምግብ አለመመገቡን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለመተዳደሪያ የሚኾን ሀብት አለማግኘቱን ለማመልከት ነው፡፡

ቃል ግጥም 208፡- *ሀገር ጥሎ መኼድ ምን ያደርግልሃል*
ጠንክረህ ብታጭድ ላንተው ይጠቅመሃል፡፡

(ከቀያፈር አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 19/05/2012፣ቦረና ወረዳ)

ሰዎች የትውልድ ሀገራቸውን ለቀው ወደሌላ ከሚሰደዱባቸው በርካታ ምክንያቶች መካከል አንደኛው ኢኮኖሚያዊ ችግር መኾኑን ቃል ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ ስደት ደግሞ የተሻለ ኑሮ በመኖር ረገድ ጥቅም አለው ተብሎ ቢታመንም ከወገን በመራቅ፣ ላገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ወይም ባይተዋር በመኾን፣ ለአዲስ ባህል በመጋለጥ፣ ወዘተ. ረገድ ከፍተኛ የኾነ ጉዳት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሠረት ገጣሚውም አጠገቡ ላለና ሀገሩን ለቆ ወደሌላ ቦታ ለመኼድ በአእምሮው ውስጥ ላቀደው ሰው “ስደተኛ መኾን ምንም አይሠራልህምና ቢቀርብህ ይሻልሃል” የሚለውን ምክር የሰነዘረ መኾኑን ከመጀመሪያው ስንኝ መረዳት ይገባል፡፡ በመጨረሻም ገጣሚው ከመሰደድ ይልቅ ጠንክረህ ሰብልህን የማጨድ ተግባር ብታከናውን ይበጅሃል የሚለውንም ሐሳብ ሰጥቷል፡፡ ሰብልን ከማጨድ በፊት ግን ማረስ፣ መዝራትና ማረም የሚባሉ ኪደታዊ የአርሶ አደሮች ተግባራት ስላሉ እነዚህንም ቢኾን ወቅታቸውን በመጠበቅ ጠንክሮ መሥራት ያለበት መኾኑን መገንዘብ ያስልጋል፡፡ በአጭሩ ቃል ግጥሙ ተግቶ መሥራት ለሰው ልጅ የህልውናው መሠረት በመኾኑ ሀገርን ጥሎ መሰደድ እንደማይኖር ያስገነዝባል፡፡

ቃል ግጥም 209፡- ዐረሙን ዕረሙ በጣም ተጣጣሩ
ችግርን በፍጥነት እንዲታባርሩ፡፡
(ቃል ግጥም፣ ዘይነባ ይማም፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮች ያሉባቸውን ችግሮች ማስወገድ የሚችሉት ተግተው ሲሠሩ እንደኾነ ቃል ግጥሙ ያመለክታል፡፡ በመኾኑም አርሶ አደሮቹ ወቅት ጠብቀው የእርሻ መሬታቸውን ከገመሱ፣ ካየሙ (በተደጋጋሚ ካረሱ) እና ዘር ከዘሩ በኋላ ከእኽሉ ጋር ዐብረው የሚበቅሉትን እና አስፈላጊ ባለመኾናቸው የተነሣ የሚታረሙትን ማንኛውም ዓይነት ዕፅዋት በርትተው ነቅለው እንዲጥሉ ገጣሚው ይመክራል፡፡ ዐራሙቻው በወቅቱ ተነቅሎ ካልተጣለ ግን ሰብሉ በሚገባው መጠን ስለማያድግ አርሶ አደሮቹ አጥጋቢ የኾነ ምርት ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ስለዚህ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለፍተውና ደክመው የእርሻ ተግባራቸውን ካከናወኑ የተትረፈረፈ ምርት ስለሚያገኙ ከድኽነትና ከዕጦት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊላቀቁ እንደሚችሉ ገጣሚው ገልጿል፡፡

ቃል ግጥም 210፡- ሁል ጊዜ ደግፉኝ እናት አባት ደክሟል
በእጅም በእግርም ሠርቶ ራስን መቻል፡፡
(ቃለ መጠይቅ፣ ፈቃዱ ጤናው፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ከመጀመሪያው ስንኝ ኹለተኛውን ሐረግ በተለያየ መንገድ መፈከር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ አንደኛው ፍካሬ “ሁል ጊዜ ደግፉኝ” የሚለው ሰው ወላጆች ብርታትና ዐቅም ዐጥተዋል፤ አርጅተዋል፤ ጉልበታቸው ዐልቋል የሚል ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ ለልጃቸው ድጋፍ ማድረግ ተስኗቸዋል፤ ታክቷቸዋል ወይም ሰልችተዋል የሚል ነው፡፡ በኹለቱም ትርጓሜ ቢኾን ማንኛውም ከአብራክ የተገኘ ሰው እናትና አባቱን ዘወትር አግዙኝ ወይም ደግፉኝ ከማለት ይልቅ በአጭር ታጥቆና እግሩ እስከከሚነቃም ድረስ ኼዶ ተግቶ መሥራት እንዳለበት ቃል ግጥሙ ያስረዳል፡፡ በግጥሙ ውስጥ “ራስን” የሚለው ቃል የተጠቀሰው በቤተሰብ እርዳታ የሚኖረውን ሰው በአጽንዖት ለመግለጽ በሚያገለግል ተውላጠ ስም (የስም ምትክ) ለማመላከት ሲኾን፣ ይህ ሰው በርትቶ ወይም ጠንክሮ ከሠራ ራሱን በራሱ ማስተዳደር እንደሚችል፣ ያጋጠመውን ችግር እንደሚቋቋም፣ የሌላውን ሰው እርዳታ ከመሻት እንደሚድን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡

8.4. እኩይ የኾኑ ባሕርያትን የመግታት ፋይዳ

እኩይ የሚለውን ቃል በባሕርይ ረገድ ክፉ ወይም መጥፎ ብሎ መተርጎም የሚቻል ሲኾን፣ እነዚህን መጥፎ የኾኑ የሰው ልጅ ልማዶችን ለመቆጣጠርና ለመግታት የሚያስችሉ ቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ አንደበት ሲነገሩ ይደመጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት ማኅበረሰቡ ምስጉን እና

ድንቅ ናቸው ከሚላቸው ዕሴቶች የሚያፈነግጡትን፣ እንደዚሁም ተግባራቸው እኩይ የኾኑትን ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ግሣጼ ያደርስባቸዋል። ጥናቱ በተካኼደባቸው አካባቢዎች እኩይ ባሕርያትን በተመለከተ እየተነገሩ ያሉት የቃል ግጥሞችም በስንፍና፣ በዳተኝነት፣ በሐሜት፣ በክሕደት፣ በአመንዝራነት፣ ጠንቋይን በማመን፣ በመታበይ (በመኩራት) በመዋሸት፣ በሙስና፣ ወዘተ. ላይ ያተኮሩ ናቸው። ማኅበረሰቡ እነዚህ እኩይ ተግባራት ወደተከታዩ ትውልድ እንዳይሸጋገሩ የሚገታባቸውን የቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት።

ቃል ግጥም 211፡- ቃጤ እኽል ዘርተሽ ቃጤ ካወጣሽ
እግዚአብሔር ይማርሽ ዐፈር በነካሽ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

አርሶ አደር የኾነችዋ ሴት በስንፍናዋ የተነሣ ከእርሻ ሥራ ያገኘችው ምርት ከዘራችው ዘር ጋር መሣ በመሣ (እኩል በእኩል) ኾኗል። ይህንን የታዘበው ገጣሚም ውጤት አልባ ለኾነው ሥራዋ ገላዋን ዐፈር ስለነካው "የኹሉ የበላይ የኾነው አምላክ ይቅር ይበልሽ" ብሏታል። ሴትዮዋ የእርሻ መሬቷን በተደጋጋሚ አሳርሳ ማለስለስ አልቻለችም። በዚሁ መሬት ላይም ከቁና አነስ ባለች የእኽል መስፈሪያ (ቁልቢጥ) ዘር ለክታ ብትዘራም በተገቢው ወቅት ዐረም ማረም ባለመቻሏ ዐላባው (ከማሳው ላይ ያገኘችው ምርት) ከዘራችው ዘር ጋር እኩል ኾኖ ተገኝቷል። ለውጥ ባላመጣችበት የእርሻ ተግባር አካሏ በጭቃ በመበከሉ "የሰማይና የምድሩ ጌታ በማዘን ምሕረት ያድርግልሽ" በማለት ገጣሚው በምፀት መልካሙን ተመኝቶላታል። ቃጤ እኽል ዘርታ ቃጤ እንዳወጣችው ሴት ላሉ ሰነፍ አርሶ አደሮች ትልቅ ምክር የሚሰጣቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም ቦዘኔው ገበሬ ወቅቱን በመጠበቅ ጠንክሮ ካልሠራ ለረኃብ የሚጋለጥ መኾኑን ይጠቁማል። ከላይ የቀረበው ቃል ግጥምም ኾነ አባባሉ የስንፍናን ባሕርይ በመኮነን ሥራ ፈትነት ወደተከታዩ ትውልድ እንዳይሸጋገር የማድረግ ፋይዳ ያለው መኾኑን መገንዘብ ይገባል።

ቃል ግጥም 212፡- ወገቡ ከረረ
ወደ ኋላ ቀረ
ማጭዱን ንጠቁት
ሚስቱ ትጨድለት።
(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም መሠረት የዐጨዳው ተግባር ሲከናወን የነበረው በጎብረት ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም "ወደ ኋላ ቀረ" የሚለው ስንኝ በቃል ግጥሙ ትችት የቀረበበት ሰው ዐብረውት ከነበሩት ዐጫጆች ጋር ሲነጻጸር ከኋላ መቅረቱን የሚጠቁም ኾኖ በመገኘቱ የተነሣ ነው። በመስክ ምልከታዬ እንደተገነዘብኩት በዐጨዳ ተግባር ወቅት ዐጫጁ ሰው ቆሞ የሚያጭድ

ከኾነ ከዐንገቱ፣ ከትከሻውና ከወገቡ ወደመሬት ጎንበስ ሊል፣ ቁጭ ካለ ደግሞ ትከሻውን፣ ቀኝና ግራ እጆቹን፣ መቀመጫውን እና እግሮቹን ሊያንቀሳቅስ ይችላል። በግጦሙ የተጠቀሰው ገጸሰብ ግን አጎንብሶም ኾነ ተቀምጦ ሲያጭድ ከትከሻው በታች ያለው የአካል ክፍሉ ወይም ወገቡ ስለገረረ ዳተኛ ኾኗል። በዚህም የማጨድ ተግባሩን በፍጥነት ባለማከናወኑ የተነሣ ከሌሎች ጓደኞቹ ወደኋላ ሊዘገይ ችሏል። ይህንን የታዘበው ገጣሚ ደግሞ ወደኋላ የቀረው ሰው ሲያጭድበት የነበረውን ማጭድ ቀምታችሁ ለትዳር ጓደኛው ስጧትና እሷው ዐጨዳውን ታምሽክው በማለት በዳተኛው ላይ ነቀፌታ አቅርቦበታል። እዚህ ላይ የአንዳንድ አርሶ አደር የትዳር ጓደኞች በቤት ውስጥ ያላቸውን ሥራ በጥዋቱ ካጠናቀቁ በኋላ ዐጨዳ የእኔ ሥራ አይደለም ሳይሉ ከወንዶች ያልተናነሰ ተግባር ማከናወን እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል።

ቃል ግጥም 213፡ መንደር ለመንደር ሰው ከማማት
በሰዓቱ ዐጭዶ ከቤት መግባት።
(ቃለ መጠይቅ፣ ምትኩ አገኘሁ፣ 21/04/2013፣ ቦረና ወረዳ)

በቅዱስ ቁርኣን (1961፣ 452)) “ሐሜተኛ ኹሉ ወዮለት፤ ከዚህ አድራጎቱ ይከልከል፤ አለበለዚያ በሰባሪይቱ እሳት ውስጥ በእርግጥ ይጣላል” በማለት ተገልጿል። ይህ ደግሞ የሐሜት ጎጢያትን የፈጸመ ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ በእሳት ላይ ተጥላ በሥራዋ ቅጣት እንደሚፈጸምባት ለማስተማር ነው። አባባሉ ለሃይማኖቱ ተከታዮች ለማስተማርና በዚህም የሐሜተኛን እኩይ ተግባር ለመግታት ሲባል ነው። በአምላካዊ ቃል ውጉዝ ወይም መጥፎ የተባለው እኩይ ተግባር በማኅበረሰቡ አንደበት በተነገረው ቃል ግጥምም በሐሜት የተሰማራ ሰው ሲነቀፍ ተመልክተናል። በመኾኑም በዐጨዳ ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው መንደር ለመንደር እየዞረ አንድን ሰው በሌለበት መንቀፍ፣ ስሙን ማጥፋት፣ ወይም በጥፋቱም ኾነ ያለ ጥፋቱ በክፉ ማንሣት ተገቢ አለመኾኑን በቃል ግጥሙ ተገልጿል። ከዚህ ይልቅ የማጨድ ተግባሩን በወቅቱ አከናውኖ ወደመኖሪያ ቤቱ መኼድ እንዳለበት ገጣሚው አስረድቷል። በዚህ መሠረት ሐሜት የተባለው መጥፎ ልማድ የተጠናወታቸው ሰዎች አድራጎታቸውን በመቆጣጠርና በመግታት ረገድ ቃል ግጥም ፋይዳው የጎላ ነው ማለት ይቻላል።

ቃል ግጥም 214፡- ማረስ ነው እንጂ በጥቂቁር በሬ
መንደር ለመንደር ከማውራት ወሬ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ የሱፍ፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

ሥራውን ፈትቶ ወሬ የሚያወራውን ሰው “ወሬ ዘርግቷል፤ ወሬውን ይሰልቃል” እየተባለ በማኅበረሰቡ ዘንድ ነቀፋ ሲደርስበት ይስተዋላል። “የወሬ የለው ፍሬ” የሚለውም አባባል ወሬ ካገኘ ለሥራ እምብዛም ግድ ለሌለው ሰው የተነገረ መኾኑን መረዳት ይቻላል። አባባሎቹ

በሰዎች መካከል የሚደረገውን ጭውውት ወይም አንዱ ለሌላው የሚያስተላልፈውን የሐሳብ ልውውጥ የሚያንጸባርቁ ሳይኾን ቁም ነገር የሌለውን ተራ ወሬ በስፋት በማውራት ላይ የሚገኘውን ሰው መጥፎ ልማድ ለመቆጣጠር የተነገሩ መኾናቸውን ልብ ልንል ይገባል። በፉከራ ቃል ግጥሙ ለተጠቀሰውና ወሬ ምሳው (ወሬ ወዳድ) ለኾነው ሰውም መንደር ለመንደር እየተዘዋወረ ቁም ነገር የሌለውን እና ወጤት አልባ የኾነውን ተራ ወሬ ከማውራት ይልቅ በጠንካራ በሬዎች የእርሻ መሬቱን በመግመስ፣ በማየም፣ በመበሸል፣ ወዘተ. አለስልሶ አጥጋቢ የኾነ ምርት ማምረት አለበት በማለት ገጣሚው ገልጿል።

ቃል ግጥም 215፡- ወይ ዐርመህ አብላት ወይ አንተ ሙትላት
ሰነፍ ባል አግብታ ምነው ባታሰኛት።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ስንፍና ወይም ሥራ ጠልነት በሰዎች ዘንድ የሚኮነን እኩይ ባሕርይ ነው። ዘነብም (1944፡12) “ረኃብ ውሎውና አዳሩ ከማን ነው?” ብለው ራሳቸውን ከጠየቁ በኋላ “ሥራ ከማይወድ ከሰነፍ ሰው ጋር ነው” በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ ሠራተኛ ሰው ባለጸጋ መኾን ሲችል ሰነፍ ሰው ግን ዕለት ተዕለት እየከሰረ ኼዶ በመጨረሻም የመራብና የመጠማት ማደሪያ ኾኖ እንደሚኖር ከአለቃ ዘነብ አባባል መገንዘብ ይቻላል። እንደዚህ ያለ ሰው ደግሞ ሥራ ትልቅ ተራራ መስሎ ነው የሚታየው። ስለዚህ እሱ ከሚሠራ ይልቅ ሌላ ሰው የሠራውን ነው መብላት የሚወደው። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም የስንፍና እኩይ ባሕርይ የተጠናወተው ሰው ጥፋተኛ ተደርጎ በመቅረቡ ተኮንኗል። ምክንያቱም ሰነፉ ባል መሥራት የሚገባውን የወንድ ሥራ በአግባቡ ባለመወጣቱ የተነሣ ነው። በመኾኑም ገጣሚው ኮትኳችና ዐራሚ የሌለው ሰብል የተትረፈረፈ ምርት ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህ ከአዝመራህ ውስጥ የበቀለውን እና አላስፈላጊ የኾነውን ቅጠልና ሣር በወቅቱ ነቅለህ በመጣል የተትረፈረፈ ምርትን በማግኘት የትዳር ጓደኛህን እየመገብክና የሚያስፈልጋትን ነገር እያሟላህ አስተዳድራት። አለበለዚያ በሕይወት ኖረህ አልበጀሃትምና “ሰነፍ ባል አግብታ” እየተባለ ስሟ ከሚጠራ መቀተህ ብትቀበር ይሻላል በማለት የስንፍና ማደሪያ የኾነውን ሰው ገጣሚው አውግዞታል። በዚህ መሠረት ይህ ዓይነቱ ቃል ግጥም የስንፍናን እኩይ ባሕርይ ለመግታት ጠቀሜታ ይኖረዋል ማለት ነው።

ቃል ግጥም 216፡- ግርም ያደርገኛል ያመኑት ሲከዳ ያመኑት ሲሸሽ
ስብር እንደ አገዳ ሽምልል እንደ አብሽ።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃሉን የሚያጥፍና እምነት የማይጣልበት ከሓዲ የኾነ ሰው በማኅበረሰቡ ባህል መሠረት ነውር የኾነ ተግባር እንደፈጸመ ተደርጎ የሚቆጠር በመኾኑ ነቀፋ ይደርስበታል። ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም ነውር ጌጡ የኾነ ሰው በገጣሚው ወይም በሌላው ላይ ክሕደትን በመፈጸሙ ድርጊቱ የሚያስገርም መኾኑ ተገልጿል። ይኼውም ኹለቱ ሰዎች በጋራ ኾነው ያልጠበቁትን እና ያለ መጠራጠር የተማመኑበትን ጉዳይ ከሓዲው ውል በማፍረሱ ወይም በመክዳቱ የተነሣ ከአቋሙ ተንሸራትቷል። ከሓዲው በዚህ እኩይ በኾነው ድርጊቱም እንደደረቀ የበቆሎ፣ የማሽላ፣ ወዘተ. ... እኽሎች አገዳ እንክትክት ብሎ እንደተሰባበረ፣ እንደዚሁም ባኺዶ (በውቂያ) ጊዜ በከብት እግር አማካይነት ጥቅልል እንደሚል የአብሽ ገለባ ሽምልል ብሎ እንደወደቀ ቃል ግጥሙ ያመለክታል።

ቃል ግጥም 217፡- ማረስ ነው እንጂ ጎራውን ዙሮ
ማረስ ነው እንጂ ድቡን ጎርጉሮ
ቀይ ሴት ቢያዩ አይኾንም ኑሮ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ራህመት ማህሙድ፣ 04/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

“ያረሰ ነገሠ” በሚለው የአርሶ አደር አባባል መሠረት ከፍተኛ የኾነ ቦታን ተጉዞና ወደሌላ ቦታ ኼዶ የእርሻ ማሳውን በመግመስ፣ በማየም፣ በመበሸል አለስልሶ፣ ድብ የኾነውንም መሬቱን በመደንጎሪያ ቆፍሮ ካዘመረው ሰብል አጥጋቢ የኾነ ምርት ማግኘት የቻለው አርሶ አደር በቤቱ ውስጥ ችግርና ጉድለት የሌለበትና ማለፊያ የኾነ ኑሮ መምራት የሚችል መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል። ከዚህ ውጭ ግን “በዓይኑ አይቶ በልቡ አመነዘረ” እንደሚለው የአምላክ ቃል ሥራውን ትቶ በአመንዝራነት እኩይ ባሕርይው ከዓላማው የምታስተውን ቀይ መልክ ያላትን ሴት ሲመለከት የሚውል አርሶ አደር እኽልን ዘርቶ፣ ዐርሞ፣ ዐጭዶና ወቅቶ የሚያገኘው ምርት አይኖርም። በመኾኑም በሕይወት ዘመኑ አስፈላጊ የኾኑ ነገሮችን ስለማያገኝ አኗኗሩ ያሽቆለቁልና በችግር ምክንያት የተጎሳቆለ እንደሚኾን ከግጥሙ መረዳት ይቻላል። ቃል ግጥሙ በውጫዊ ገጽታዋ መልካም የኾነችዋን ሴት በማየት የከፋ ችግር ላይ ከመውደቅ ይልቅ “በል አርፈህ ተቀመጥ” በሚል ግሣጼ ከላይ የቀረበውን እኩይ ባሕርይ ለመግታት ረድቷል ማለት ይቻላል።

ቃል ግጥም 218፡- ማረስ ነው እንጂ ዕርፋ እስኪቆመጥ
ዐሥር ብር ይዞ ጠንቋይ ቤት ከመሮጥ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ የሱፍ፣ 03/07/2012፣ ከለላ ወረዳ)

በእርሻ ሥራ የሚተዳደር አርሶ አደር ጠንክሮ ሠርቶ አጥጋቢ የኾነ ምርት በማግኘት ፈንታ ጨሌ ጣይ፣ መጽሐፍና ሞራ ገላጭ፣ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ወዘተ. የኾነ ሰው ቤት

መኼድ መጥፎ ባሕርይ መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል። ገጣሚው እያረሰ ያለው መሬት ምቹና ለጥ ያለ ሜዳ ሳይኾን ዳገትና ቁልቁለት፣ እንደዚሁም ጎጥ የበዛበት በመኾኑ እርሻውን ሲያርስ ዕርፉ እየተቆመጠ ያለ መኾኑን በመጀመሪያው ስንኝ መድረሻ ሐረግ ላይ አመልክቷል። ኾኖም በዚህ ምቹነት በሌለው የእርሻ መሬት ላይ ከሞፈርና ከማረሻ ጋር የተዋደደው፣ ከኹለት ድግር ጋራ ወገልና ማረሻ የጎረሰው፣ እንደዚሁም አርሶ አደሩ ሲያርስ የሚጨብጠው፣ የማረሻውን ጥልቀትና ኺደት የሚቆጣጠርበት የበሬ ዕቃ ከኹለት ቦታ እስከሚቆመጥ ድረስ ተግቶ በማረስ የተትረፈረፈ ምርት ማምረት እንደሚኖርበት ገጣሚው በአንደበቱ ገልጿል። ከዚህ በተቃራኒው ግን የሚያስጠነቁልበትን ገንዘብ ይዞ የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን ይፈጽማል ተብሎ ወደሚነገርለት ጨሌ ጣይ፣ መጽሐፍና ሞራ ገላጭ፣ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ወዘተ. ቤት ቶሎ ቶሎ የሚኼድ አርሶ አደር የሚነቀፍ ተግባር እየፈጸመ ያለ መኾኑን ገጣሚው በሚገባ አስረድቷል። ከቃል ግጥሙ በተጨማሪ እንደዚህ አርሶ አደር ያሉ አስጠንቋይ ሰዎች ተግባራቸው እኩይ መኾኑን ተገንዝበው ከአድራጎታቸው እንዲገቱ ለማድረግ ሥነ ቃሎች ሲመክሩ ይስተዋላል።

ቃል ግጥም 219፡- ሲነግዱ አትነግድ ሲያርሱ አትረስና

አሚረቱብኝ በል ተኝተህ ዋልና።
(ቃለ መጠይቅ፣ ፱ አለቃ አድማሱ ከበደ፣ 21/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ እኩይ ባሕርይ ተደርጎ የተወሰደው ሚርት ነው። ሚርት ደግሞ በሌላው ላይ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲደርስ ተብሎ በሰው ቤትና መሬት ላይ መድኀኒትና አስማት የመቅበር ድርጊት ማለት ነው። በግጥሙ ውስጥ በእኩይ ድርጊቱ የተኮነነው ገጸሰብ ሌሎች ነጋዴዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ሩቅ ሀገር ኼዶ ወይም በአቅራቢያው ካሉ መደብሮች ሸቀጦችን ገዝቶ በመሸጥ ራሱም ትርፍ ማግኘትና ለኅብረተሰቡም አገልግሎት መስጠት ሲገባው፣ እንደዚሁም የእርሻ መሬትን በማረስ፣ በማረም፣ በማጨድና በመውቃት አጥጋቢ የኾነ ምርት ማግኘት ሲኖርበት “መድኃኒት ተቀበረብኝ፣ መተት ተጣለብኝ” ማለት እንደሌለበት ግጥሙ ያስረዳል። ከዚህ በተጨማሪ ግለሰቡ በኑሮው ላይ መሻሻልን ለማምጣት በተለያዩ የሥራ መስኮች መታተሩን ትቶ በሰበብ አስባቡ አብዛኛውን ጊዜውን ሥራ ፈትቶ ተኝቶ በመዋል “ተሚረተብኝ” በማለት ሰዎችን ያለ ሥራቸው ወንጀለኛ ማድረጉም ቢኾን ምግባረ እኩይ አስተሳሰብ መኾኑን ከግጥሙ መገንዘብ ይቻላል።

ቃል ግጥም 220፡- እነጣተ ለምለም እነ ታፋው ለምለም
ታሞ የተኛ ዕለት የሚቀምሰው የለም።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ተቀምጦ የሚውለው ሰነፉ አርሶ አደር ሥራ ባለመሥራቱ የተነሣ የእጁ ጣቶች በጣም የለሰለሱ መኾናቸው በቃል ግጥሙ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ ይሄው የስንፍና እኩይ ልማድ የተጠናወተው ሰው በዐረምና በዐጨዳ ወቅት ተቀምጦ የግብርና ሥራውን ስለማያከናውን መቀመጫውና ታፋው በዐፈርና በድንጋይ አልተፋተገም ወይም አልተፈጋፈገም። በዚህ የተነሣ ከመቀመጫው በታች ያለው የአካል ክፍሉ የለመለመ መኾኑን ከቃል ግጥሙ መረዳት ተችሏል። እንዲህ ያለው ግለሰብ ጠንክሮ አርሶ በጥሪትነት ወይም በአንጡራነት የሚያገለግል ምርት ስለሌለው ጤና አጥቶ በደዌ ዳኛ፣ ባልጋ ቁራኛ ሲያዝ እስከሚጠግብ ድረስ ሊበላ ቀርቶ ለቅምሻ እንኳን የሚኾን ምግብ ሊያገኝ እንደማይችል በግጥሙ ተገልጿል። በመኾኑም ከላይ የተጠቀሰውም ኾነ ሌሎች የስንፍና መጥፎ በሽታ የተጠናወታቸው አርሶ አደሮች ጠንክረው አርሰው የዕለት ጉርሣቸውን ማሟላትና ወደፊት ላለው ሕይወታቸው የሚኾን ጥሪትም ማስቀመጥ ባለመቻላቸው በታመሙ ወቅት የሚልሱትና የሚቀምሱት ማጣታቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚነቀፍ ተግባር መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል።

ቃል ግጥም 221፦ ጸጉርህን ከመንቀስ ልብህን ንቀሰው
ሚስትህን ወሰዳት ነጭ ጤፍ ያለው ሰው።
(ቃለ መጠይቅ፣ ትዕግስት ክብረት፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ከመስከረም 05 — 09/ 2013 ዓ.ም ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ተጨምቆ የቀረበው ሐሳብ እንደሚያስረዳው ቃል ግጥሙ በተነገረበት አካባቢ ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ አንድ አባት ጎረምሳ ልጁ ጸጉሩን ካሳደገና በተለየ ኹኔታ አበጥሮ ካየው "ሚስት ዳሩኝ" የሚል ትእምርት መኾኑን ተገንዝቦ በራሱም ኾነ በዘመድ የትዳር ጓደኛ አፈላልጎ ይድረዋል። ከዚህ ውጭ ግን ትዳር መሥርቶ የራሱን ሕይወት እየመራ ያለ ሰው ያደገ ጸጉሩን ዘወትር በሚዶ አበጥሮ በመከምከም የሚዋብ ከኾነ ዓላማው ሴትን ለማማለልና ከቤቱ ያለችውን የትዳር ጓደኛውን ትቶ ወደሌላዋ ለመኼድ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የሴሰኛነትን ስም ያተርፋል። ይህ ዓይነቱ እኩይ ባሕርይ ደግሞ በኅብረተሰቡ ዘንድ የተጠላና የተናቀ ነው። ገጣሚው ይህንን ዓይነቱን ሰው ከዚህ አድራጎቱ ተቆጥቦ አስተዋይ፣ በሥራ የማይፈታ፣ ኃይለኛ መኾን እንዳለበት አስረድቶታል። ከዚህ ውጭ ግን የግብርና ሥራውን በመተው ጸጉሩን አሳምሮ ሌላ ሴት ሲፈልግ የሚለሰልሰውን ነጭ ጤፍ ያመረተ ሰው በሕጋዊ ጋብቻ የተጣመራትን የትዳር ጓደኛውን ነጥቆ ወደሌላ ቦታ ሊወስድበት እንደሚችል ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል።

ቃል ግጥም 222፦ ከቀብር ገብቼ ጎኔን ብዳብሰው
ከወንጀል በስተቀር ዐጣሁኝ አንድ ሰው።
(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሬ፣ 23/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ዘነብ (1944፡2) “መቃብር መልካም ጎታ ነው፤ ብስሉንና ጥሬውን ይከታልና” በሚለው አባባላቸው መቃብር አነስተኛና የእኽል ማስቀማጫ የሾነውን ጎታ ባሕርይ እንዲላበስ አድርገውታል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቶቹ ኹለት ነገሮች ይመስሉኛል። የመጀመሪያው መቃብሩና ጎታው በመጠን አነስተኛ በመኾናቸው ሲኾን፣ ሌላኛው ደግሞ ኹለቱም መጥፎና መልካም የኾኑ ነገሮች የሚገቡባቸው ስለኾኑ ነው። ከቃል ግጥሙ አንጻር ብስል ሲባል ለዐዋቂ፣ ማመዛዘን ለሚችል፣ ጥሩ፣ ማለፊያና ደግ ለኾነ ሰው ወኪል ኾኖ ሲቀርብ፣ ጥሬ የሚለው ደግሞ ማስተዋል የሚያንሰው፣ ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሰ፣ ጎጢያተኛ፣ ክፉና ተንኮለኛ የኾነውን ሰው ያመለክተናል። በመኾኑም ከላይ ከተጠቀሱት ወገኖች መካከል በጥሬ የተመሰለው፣ ክፉና ጎጢያተኛ የኾነው ሰው ነፍሱ ከሥጋው የተለየችው በድን ቢኾንም ቃል ግጥሙን በሰውኛ ዘይቤ ለማቀንቀን በቅቷል።

ግጥሙም ሰውዬው በሞተበት ዕለት ጉድጓድ ተምሶ በቀባሪዎች ከተቀበረ በኋላ ከሌሎች ሰዎች ተለይቶ በመቃብር ውስጥ ብቻውን በቀረበት ጊዜ በመንፈስ የተናገረው ነው። ንግግሩም የሚያመለክተው አሰከሬኑ በመቃብር ውስጥ ከተጋደመ፣ ጉድጓዱም በዐፈርና በድንጋይ ከተሞላ በኋላ በቀኙ ወይም በግራው በኩል ያለውን የአካል ክፍሉን ቢዳብሰው በሕይወት ዘመኑ ከሠራው ኃጢያትና ከፈጸመው ወንጀል በስተቀር ሌላ ሰው ማግኘት አለመቻሉን ነው። ሟቹ ሰው “ዓለማዊ በነበርኩበት ጊዜ በሠራሁት ወንጀል የተነሣ ሰማያዊ ጸጋን ሳላገኝ ቀረሁ” በሚል የተጸጸተ ይመስላል። በዚህ መሠረት ማንኛውም ሰው እሞታለሁ ብሎ በመፍራት ለዚያኛው ዓለም መልካም የኾነ ነገር መሥራት እንጂ የፈጣሪውን ሕግ መተላለፍና የማይገባ ተግባር መፈጸም እንደማይኖርበት ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል።

ቃል ግጥም 223፡- ጎበዝ በጉብዝናህ ምንድን ነው ኩራቱ?
ቆንጆ በቁንጅናሽ ምንድን ነው ኩራቱ?
ያበለሻሸዋል እሱው ባለቤቱ።
(ቃለ መጠይቅ፣አካሉ ወደደኝ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

“ኩራት ምንድን ነው?” ብለው ዘነብ (1944፣4) ራሳቸውን ከጠየቁ በኋላ “እንደርሱ ኾኖ የተፈጠረውን ሰው መናቅ ነው” የሚለውን ምላሽም ሰጥተዋል። አንድ ሰው በመልክ፣ በቀለም፣... ከሱው ጋር አምሳያ ኾኖ የተፈጠረውን ወገን በኩራት መናቅ እኩይ ድርጊት መኾኑን ከዘነብ አባባል መገንዘብ ይቻላል። ቃል ግጥሙም ቢኾን በወንድነቱ ጎበዝ የኾነ በአምሳያው፣ በሴትም ቢኾን ቆንጆ የኾነች በአምሳያዋ ላይ የኩራት ስሜት ማሳደር እንደሌለበት/ባት ይገልጻል። ጉብዝና ሲባል ጉልበት ያለውን፣ ጀግና የኾነውን፣ በሥራ የሚተጋውን፣ አእምሮን በሚጠይቅ ጉዳይ ጥሩ ችሎታ ያለውን ሰው የሚያመለክት ሲኾን፣

ቁንጅና ደግሞ በውጫዊ ገጽታዋ ውብ ለኾነች ልጃገረድና ለምታምር ሴት በስያሜነት የሚያገለግል ነው፡፡ በጉብዝናም ኾነ በቁንጅና ግርማ ሞገስን የተላበሱ ሰዎች በሌሎች ላይ የሚታበዩ ከኾነ በፍጥረታት ላይ የማዘዝና የመወሰን መብት ያለው አምላክ ያለ ጊዜያቸው አበለሻሽቶ ከምድረ ገጽ ሊያጠፋቸው እንደሚችል ተገልጿል፡፡ ስለዚህ የጥናቱ አካል በኾነው ማኅበረሰብ ዘንድ በጉብዝና እና በቁንጅና በመመካት መታበይ እኩይ ባሕርይ በመኾኑ ሊገታ እንደሚገባው ቃል ግጥሙ ያስረዳል፡፡

ቃል ግጥም 224፡- ቀሚስ ጠፋ መሰል ሁሉም ሱሪ ለብሷል
ከእንግዲህ ወንድነት በምን ያስታውቃል፡፡
(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ቃል ግጥሙ ገና ከመነሻው ሴቶችን በአለባበሳቸው ሲገሥጽ ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም አንዲት ሴት ልጅ ጥሩ ወይም መጥፎ ሥነ ምግባር እንዳላት ማኅበረሰቡ ፍረጃ ከሚያካኺድባቸው ባህላዊ መስፈርቶች መካከል አንደኛው አለባበሷ በመኾኑ የተነሣ ነው፡፡ ቀደም ባለው ዘመን ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች ትኖር የነበረች ማንኛዋም ሴት ባህሉ በፈቀደላት መሠረት ትለብስ የነበረው እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ ቀሚስ እንደነበር ከሕይወት ገጠመኜ በመነሣት የምመሰክረው ጉዳይ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ዘመናዊነት ባመጣው ሥልጣኔ እንደከተሜዎቹ ሴቶች ኹሉ በገጠር አካባቢ ከሚኖሩት መካከል የአንዳንድ ወጣት ሴቶች የቀሚስ አለባበስ እያደር ወደባት፣ አሁን አሁን ላይ ደግሞ ከጉልበት በላይ እየኾነ መጥቷል፡፡ ይህ ዓይነቱ አለባበስ ወንድን ለመማረክ ታስቦ ነው ተብሎ ስለሚገመት በጎብረተሰቡ ዘንድ የተናቀና የተጠላ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከሀገራችን ባህል አንጻር የሴትነትን ተፈጥሯዊ ጸታ የሚያመለክተው ቀሚስ ከጊዜ ወደጊዜ የመለበሱ ኹኔታ እየቀነሰ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት ሴቶች ሱሪ በመልበስ ላይ መኾናቸውን ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ምክንያታዊ ባልኾነ መንገድ ቁሱ በአለባበስ ረገድ ባህላዊነቱን ያልጠበቀ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ኹኔታ ገጣሚው ግር ብሎታል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሱሪ የወንድን እና የሴትን ተፈጥሯዊ ጸታ ሊያመለክት ባለመቻሉ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ የቃል ግጥሙ ማዕከላዊ ሐሳብ በዋናነት ያጠነጠነው “ከእንግዲህ ወንድነት በምን ያስታውቃል” በሚለው ስንኝ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሱሪን የጀግንነት ሞያ ያለው ወንድ እንጂ ማንኛዋም ሴት የምትለብሰው ባለመኾኑ የተነሣ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን በአሁኑ ጊዜ ባለው ዘመናዊነት በሴቶች አለባበስ ላይ ለውጥ እየታየ ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ቃል ግጥም 225፡- የወንድሙን መልቀቅ

ወንድሙ መውደዱ ግቢው ይሰፋኛል እያለ በሆዱ።

(ቃለ መጠይቅ፣ ትዕግስት ክብረት፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በወግዲ ወረዳ የተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያመለክተው በሕዝብ ብዛት ምክንያት የእርሻ መሬት ከዘመን ዘመን እያነሰና እየጠበበ በመኼድ ላይ ይገኛል። በዚህ የተነሣ በወሰን መጋፋት ምክንያት የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል እንኳን ሳይቀር ጠብና ጭቅጭቅ መፈጠሩ የማይቀር ነገር ኾኗል። ይህ በመኾኑም ወንድማማቾቹ ከአንድ እንዳልተወለዱ "ይህ ለእኔ ይገባል፤ ይህ ለእኔ መኾን አለበት፤ እስከዚህ ድረስ ያለው ደግሞ ለእኔ ይኾናል" በሚል አስተሳሰብ የወንድምን መሬት ሌላው የራስ የማድረግ ዝንባሌ ይስተዋላል።



ፎቶግራፍ ዐሥራ ሁለት፡- በ07/01/2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ቡድን ተኮር ውይይት ሲካኼድ።

በቃል ግጥሙ እንደተመለከተው ከእናት ወይም ከአባት ወይም ከኹለቱም የተወለደው አንደኛው ወንድ ልጅ የመኖሪያ ስፍራውን በመልቀቅ ለሕይወቱ የተሻለ ኢኮኖሚ ወደሚያገኝበት ክልል ወይም ሌላ ሀገር ሊኼድ ችሏል። ይህ ከኾነ በኋላ በቦታው ላይ የቀረው ወንድም አካባቢውን ለቆ ከኼደው ሰው መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ካለው የእርሻ ቦታ በቁመትም ኾነ በወርድ ወይም ከዙሪያው ቀንሶ በራሱ ላይ ለመጨመር ከፍተኛ የኾነ ፍላጎት ያለው መኾኑን መገንዘብ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት የስግብግብነት መጥፎ ባሕርይ የተላበሰው ሰው በማንኛውም ነገር መከታ የሚኾነው ወንድሙ በዚያው በወጣበት እንዲቀር እንጂ በሰላምና በጤና ወደትውልድ ሀገሩ እንዲመለስ ለፈጣሪው ጸሎት ሲያቀርብ አልተስተዋልም። ቤተሰቦች ካሉትም እነሱን ለመንከባከብ አልፈለገም። "እኔን ከተመቸኝ" በሚል አጉል ፍልስፍና ተሸብቦ

የወንድሙን መሬት በቁመ ለመውረስ መጓጓቱ ጸያፍ ተግባር ስለኾነ ሊገታ እንደሚገባ ቃል ግጥሙ ይጠቁማል።

ቃል ግጥም 226፡- ኧረ ውሼታሜው ትዋሻለህ አሉ
ገደልኩት ያልከው ሰው ገበያ ታየ አሉ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ፈቃዱ ጤናው፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

በቃል ግጥሙ እንደምንመለከተው "ኧረ" በሚለውና መገረምን ለመግለጽ በሚያገለግለው ቃል መነሻነት ዕብለት ወዳድ የኾነውን ሰው "ውሼታሜው" በማለት በቀጣፊነቱ፣ በመልቲነቱ፣ በቆርጦ ቀጥልነቱ፣ ወዘተ. ሊወገዝ ችሏል። በመቀጠልም "ውሸትና ሥንቅ እያደር ይቀላል" እንደሚባለው በቃል ግጥሙ የሐሰተኛ ባሕርይ ያለው ሰው በውሸት ሕይወቱን አጥፍቼዋለሁ ብሎ ያወራበት ግለሰብ የንግድ ልውውጥ በሚካኼድበትና ሕዝብ በበዛበት የገበያ ቦታ ላይ በአካል በመገኘቱ ዐባይነቱ ወይም ዋሾነቱ ተረጋግጧል። ከላይ ባለው ግጥም መሠረት በቀጥታ በተባለው ጉዳይ መነሻነት የማይኾነውን ኾኗል እያሉ ከመናገርና "የበሬ ወለደ" ወሬን ከማውራት ይልቅ እውነተኛና ትክክለኛ ኾኖ የተረጋገጠውን ነገር ማውራት ተገቢ መኾኑን መገንዘብ ይገባል። በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ መዋሸትን በእኩይነቱ ተጽይፎ ቀጣይነት እንዳይኖረው በቃል ግጥሙ እየታገለ ያለ መኾኑን መረዳት ተችሏል።

ቃል ግጥም 227፡- ለሰባት ኮሚቴ ሰባት ብር ዐጥቼ
ያለ በቆሎ እሸት ከረሙ ልጆቼ።

(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012፣ ወግዲ ወረዳ)

ከቃል ግጥሙ መገንዘብ እንደሚቻለው በሙስና የተነሣ ሕዝብን እንዲያስተዳድር ፖለቲካዊ ኃላፊነት የተሰጠው ወገን በአንድ በኩል ሥልጣኑን አላግባብ በመገልገል ራሱንም ኾነ ከእሱ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ሰዎች የመጥቀም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላውን ሰው ችግር ላይ የመጣል ተግባር መፈጸሙን እንመለከታለን። ይኼውም ለመንግሥት ባላቸው ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ከሕዝቡ መካከል የተመረጡት የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ኮሚቴዎች ፍትሓዊነት ባለው መልኩ የእርሻ መሬትን ለአርሶ አደሩ ባለማከፋፈላቸው የተነሣ ግፍ የተፈጸመበት ግለሰብ ከላይ ያለውን የብሶት ቃል ግጥም ለማንሳራጎር በቅቷል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለኮሚቴዎቹ የኪስ ገንዘብ የሸኘጠው ሰው ለም የኾነ መሬት በሙስና ሲሰጠው፣ ምድራዊ ሀብትን ሳያገኝ የኖረው ድኻ ደግሞ ለመማለጃ የሚኾን ገንዘብ መስጠት ባለመቻሉ ሲታረስ ጥሩ ምርት ሊሰጥ የሚችል መሬት ሊያገኝ አልቻለም። በዚህ ምክንያት ያጥንቱ ፍላጭ የሥጋው ቁራጭ የኾኑት ልጆቹ ያለ በቆሎ እሸት መክረማቸውን ተበዳዩ ግለሰብ በቃል ግጥሙ

ገልጿል። በአጠቃላይ በቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ብቻ ሳይኾን ፖለቲካዊ መሠረትነት ባለው የመንግሥት መዋቅር በተዘረጉት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ውስጥ እኩይ በኾነው የሙስና ተግባር የተዘፈቁ ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥም አማካይነት ሲወገዙ ይስተዋላል።

ቃል ግጥም 228፡- ማረስ ነው እንጂ እጅ እስኪቆስል
ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል?
(ቃለ መጠይቅ፣ ጀማነሽ አባቡ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)

ቃል ግጥሙን ያዜመው አርሶ አደር በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የሥራ መሥሪያ የኾነው እጁ እስኪላጥ፣ እስኪደማና ጉዳት እስኪደርስበት ድረስ ለእርሻ ሥራ በሚያገለግሉ መሣሪያዎች መሬትን አርሶ በማለስለስ አጥጋቢ የኾነ ምርትን ማግኘት እንደሚገባ ጀግንነትን ወይም ወኔን በሚቀሰቅስ ኹኔታ ገልጿል። በኹለተኛው ስንኝ ላይ ግን በምን ምክንያት ነው ብሎ በመጠየቅ ቤትን ቆፍሮ፣ ሰርስሮ ወይም ነድሎ የራሱ ያልኾነውን ንብረት ደብቆ የሚወስደውን፣ እንደዚሁም ሳይታይ የሰውን ኪስ በርብሮ ገንዘብ የሚሰርቀውን ሌባ ድርጊቱ መጥፎ በመኾኑ በጽኑ አውግዞታል። በግብሩ ከውሻም ጋር በማነጻጸር በልክስክስነቱ በሰዎች ዘንድ እንዲነቀፍ አድርጎታል።

በዚሁ ጥናት የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን የቃል ግጥም ፋይዳዎች በምዕራፍ ስምንት ካሉት ግኝቶች ጋር ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት ጠቅለል ባለ መልኩ ማየት ተገቢ መኾኑን አምኜበታለሁ። በዚህ መሠረት በዓለም ላይ በተለያዩ ከዋኞች የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች ለፈጣሪ ምስጋናን የማቅረብ፣ ታሪክን ለቀጣዩ ትውልድ የማሸጋገር፣ ፖለቲካዊ ሚናን የመጫወት፣ ለማኅበረሰብ ማንነትን የማሳወቅ፣ ሕፃናትን በማስተማር በሥነ ምግባር የማነጽ፣ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ቀለል አድርጎ የማቅረብ፣ ብዙ ጉልበትን በሚጠይቁ ሥራዎች ወቅት የማነሣሣት ፋይዳ እንዳላቸው በጽንሰ ሐሳብ ቅኝቱ ላይ ተገልጿል። በBascom (1954፡333) ማብራሪያ መሠረት ደግሞ ቃል ግጥሞች የማስደሰት ወይም የማዝናናት፣ የባህልን ተገቢነት የማረጋገጥ፣ መልካም የኾኑ ማኅበራዊ ዕሴቶች ሳይከስሙ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የሰውን ልጅ ዕኩይ ልማዶችን የመቆጣጠርና የመግታት ፋይዳ እንዳላቸውም ተረጋግጧል።

ከእነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ በእኔም የጥናት ትንተና ውስጥ በዝርዝር የተስተዋሉ ሲኾን፣ በተለይ የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን እና ታሪክን የማስተማር፣ በሥራ የመትጋትን ጥቅም የማሳወቅ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ የሆኑ ጉዳዮችን የመግለጽ፣ እኩይ የኾኑ ባሕርያትን የመግታት

የሚሉት ፋይዳዎች በግኙቱ ውስጥ በዋናነት በተመሳስሎ የታዩ ናቸው። የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ባደረግኋቸው ሥራዎች ያላየሁትና አሁን ላይ በልዩነት የተመለከትኩት ጉዳይ ግን ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ ፋይዳ የሚለው ነው። ይህም ቢኾን ባልቃኘኋቸው በሌሎች የምሁራን የምርምር ሥራዎች ውስጥ ሊገኝ ስለሚችል ርእሰ ጉዳዩን ለሌሎች ተመራማሪዎች ክፍት አድርጌዋለሁ።

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ለውጥና ቀጣይነት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ከተዜሙ ቃል ግጥሞችና ከመከወኛ አጋጣሚዎች አንጻር

ለውጥ ቀደም ሲል ከነበረው ነገር ወይም ኹኔታ ላይ አዲስና የተለየ ነገር ማምጣት ማለት ነው። ስለዚህ ለውጥ በተለያዩ ቅርጾች፣ ይዘቶች፣ ሥርዓቶች፣ ወዘተ. ውስጥና መካከል ባለው መስተጋብር አማካይነት ሊከናወን የሚችል ክሥተት ነው። ይህ ክሥተት የነገሮች ሁሉ ተፈጥሯዊ ኹኔታና በየትኛውም ቦታ የሚኖር መኾኑንም Strasser (1977፡2) ገልጸዋል። በተለይም የቴክኖሎጂ መሻሻሎችና የኢኮኖሚ ልማቶች በኅብረተሰብ ዘንድ ለውጥ እንዲመጣ ሊያደደርጉ ይችላሉ። ምንም እንኳን ለውጥ በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የማያቋርጥ ክሥተት ቢኾንም ቀጣይነትም በበኩሉ አንድ ነገር በጊዜ ኺደት ሳይቋረጥ መቀጠልን የሚያመለክት እሳቤ ነው። እዚህ ላይ ግን የአንድ ነገር ቀጣይነቱ የሚታወቀው የሚለወጥ ነገር ሲኖር እንደኾነ መታወቅ አለበት። ስለዚህ ማኅበራዊ ቀጣይነት ያለ ማኅበራዊ ለውጥ ሊገለጽ አይችልም ማለት ነው። በዚህ መሠረት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ የታዩትን ለውጦች፣ እንደዚሁም ከመከወኛ አጋጣሚዎቹ መካከል ቀጣይነት ያላቸውን ጉዳዮች ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን።

9.1. የባህል ለውጥ በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች

እንደ Inglehart እና Welzzel (2005:15) ገለጻ የባህል ለውጥ ከማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ስለዚህ ማኅበረሰብና ባህል የተሳሰሩ እስከኾኑ ድረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከመጣ የባህል ለውጥ አይቀሬ ነው። የሰው ልጅ ፍላጎቱን በማሟላትና ኑሮውን ከጊዜ ወደጊዜ በማሻሻል ከፍተኛ የኾነ የእድገት ደረጃ ላይ መድረሱ፣ በንግድ፣ በፖለቲካዊ ግንኙነት፣ በትምህርትና በመሳሰሉት አማካይነት የባህል ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል Ascher and Heffron (2010፤2) ገልጸዋል። በአጭሩ ባህል በማያቋርጥ ለውጥ ላይ የሚገኝ እንጂ ሳይለወጥ እንዳለ የሚገኝ አይደለም። ይህ በመኾኑም የመንፈሳዊ ባህል ዘርፍ የኾኑትና መልእክትን ለማስተላለፍ፣ መረጃዎችን ለማከማቸት፣ ዕውቀትን ለማሳደግ፣ ወዘተ. በሚያስችሉ ቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውም ላይ ለውጥ ሊከሠት ይችላል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት በቃል ግጥሞችና በመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ ለተከሠቱ ለውጦች ምክንያት ናቸው ከሚባሉት መካክል ዋና ዋናዎቹን ቀጥለን እንመለከታለን።

❖ **ወጣቱ የጎብረተሰብ ክፍል ለቃል ግጥሞች ያለው አመለካከት አናሳ መሆን፡-** ከማጎበረሰቡ አባላት መካከል የተወሰኑት ወጣቶች የቃል ግጥሞችን ፋይዳ ባለመገንዘብ ዝቅ አድርገው የማየት ዝንባታ ያላቸው መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለዚህ ማረጋገጫውም ከጥር 19 እስከ 22/ 2012 ዓ.ም ድረስ በቦረና እና በወግዲ ወረዳዎች፣ እንደዚሁም ከመጋቢት 02 እስከ 04/ 2012 ዓ.ም ድረስ በከለላ ወረዳ እየተዘዋወርኩ በቃለ መጠይቅ መረጃ በሰበሰብኩበት ወቅት በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት የጎብረተሰብ ክፍሎች የሰጧቸው ሐሳቦች ሲጠቃለሉ “ይሄ ምናርኩሴ[34]፣ የማይረባ ነገር፣ ድሮ የቀረ፣ አሁን ከየት ላመጣው ብለህ ነው? አንተ ተምረህ ያላወቅከውን…” የሚሉ ናቸው፡፡ በተለይ በቦረና ወረዳ 035 ቀያፈር ቀበሌ በተገኘሁበት ዕለት ይመር አሰን የተባለ የማውቀው ወጣት “ትልቅ ቦታ ላይ የነበርክ ሰው እንዴት ታች ወርደህ ይህንን ንገረኝ ትለኛለህ?” በማለት ምላሽ ሰጥቶኛል፡፡ ይህን መሰል ሐሳብ በሌሎች ወጣቶችም ዘንድ ይንጸባረቃል የሚለውን ነገር ማጤን ችያለሁ፡፡ እዚህ ላይ ቃል ግጥሞች የማጎበረሰቡ መንፈሳዊ ሀብት መሆናቸውን ባለመገንዘብና በግድ የለሽነት ቃል ግጥሞች የማይረቡ ተደርገው መቆጠራቸው የሚያሳዝን እና የሚከነክን ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ “ድሮ የቀረ፣ አሁን ከየት ላመጣው ብለህ ነው?” የሚሉት አባባሎችም በአሁኑ ወቅት ቃል ግጥሞች የሚከወኑ አለመሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ ላለመከወናቸው ደግሞ ምቹ የሆኑ አጋጣሚዎች ባለመኖራቸው የተነሣ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም፡፡ የቃል ግጥሞች ደግሞ ህልውናቸው የሚረጋገጠው ሲከወኑ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

❖ **የመንግሥታት የፖለቲካ ሥርዓት መለዋወጥ፡-** ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ባለው ማጎበረሰብ ከጥንት አንሥቶ እስከደርግ የአገዛዝ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ወጣቶቹ የቃል ግጥሞቻቸውን የሚከውኑባቸው የተለያዩ ማጎበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች ነበሯቸው፡፡ ለአብነትም የተበቺሳን ጨዋታ ጨምሮ በአዲስ ዓመት፣ በመስቀል፣ በገና ዋዜማ ማታ ላይ በየመንደሩ ያሉ ልጃገረዶች ከተጠራሩ በኋላ አታሚቸውን ይዘው አማካይ በሆነ ቦታ ላይ ተሰባስበው የቃል ግጥም ዘፈኖቻቸውን ያቀልጡት ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ሾን ብለው የአታሞ ድምፅ ሲያዳምጡ የነበሩ ጎረምሳዎች በፉጨት በመጠራራት ወደልጃገረዶቹ ከመጡ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ይደልቃሉ፡፡ ከዚያም የወዳጆቻቸውን እጅ ይዘው በመቀመጥ ከንፈሮቻቸውን ይስማሉ፡፡ በመጨረሻም ሆታቸውን ካቀለጡ በኋላ እኩለ ሌሊት ሲሆን ኹለቱም ጾታዎች ወደየመጡበት ይመለሱ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በየበዓላቱ ዕለት ከሰዓት በኋላ ልክ እንደዋዜማው በጋራ በመገናኘት ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ተግባራት ይከውኑ ነበር፡፡

[34] ቃል ግጥምን ጥቅም የሌለው፣ ርባና ቢስ፣ ዋጋ የሌለው አድርጎ መቁጠር ማለት ነው፡፡

ከመስከረም 05 እስከ 09/ 2013 ዓ.ም ድረስ በሦስቱም ወረዳዎች ከተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ጭምቃ ሐሳብም ወጣቶቹ ጋብቻ እንዲመሠርቱ በሚደረገው ዝግጅት ከጠላ ጥንሰሳው አንሥቶ እስከሰርጉ ዋዜማ ድረስ በደመቀ ኹኔታ የተበቺሳ ጨዋታ ይከወን ነበር፡፡ በደርግ የአገዛዝ ሥርዓት በነበረው ርእዮተ ዓለምም “ኪነት ለልማት” በሚለው መፈክር በየቀበሌው የኪነት ቡድኖች ተቋቁመው ነበር፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ቡድኖች ዋና ዓላማቸው አብዮቱን ማገልገል ቢኾንም ለወጣቶቹ የቃል ግጥም መከወኛ ምቹ አጋጣሚዎች ነበር፡፡ በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ሚያዝያ 23 የወዛደሮች ቀን እና ደርግ ለሥልጣን መደላድል የበቃበት መስከረም ኾለት የአደባባይ ብሔራዊ ክብረ በዓላት ስለነበሩ፣ በእነዚህ ዕለት በደመቀ ኹኔታ ልጃገረዶች የፍቅር ዘፈኖቻቸውን፣ ጎረምሳዎች ደግሞ ሆታቸውን ያቀልጡት ነበር የሚል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር የፖለቲካ ሥርዓት ወቅት ግን ከላይ በዝርዝር የቀረቡት የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች ቀርተው ነገሩ ኹሉ ሌላ መልክ እየያዘ መምጣቱን በግል ከተካኼደው ቃለ መጠይቅም ኾነ በሦስቱም ወረዳዎች በቡድን ተኮር ውይይት ወቅት ከተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች በቁጭት የተገለጸው ጭምቃ ሐሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የፖለቲካ ሥርዓቱ ጥቅሙን ለማስከበርና የበላይነቱን ለማረጋገጥ በቀበሌ ደረጃ ባዋቀራቸው የመንግሥት አካላት አማካይነት በከንፈር መሳሳም የHIV AIDS በሽታ ይተላለፋል፡፡ “የከንፈር ወዳጅ ተቀማን” በሚሉ ጎረምሳዎች አማካይነት የእርስ በርስ ግጭት ያላግባብ ተፈጥሮ ሕይወት እየጠፋ ነው፡፡ የጥርስ መውለቅና የዓይን መጥፋት አደጋም ያጋጥማል በሚሉ ሰበብ አስባቦች ከሰው ግቢ ሰዓት እላፊ ላይ መገኘት ወንጀል ነው እየተባለ የወጣቶቹ የተበቺሳ ጨዋታ እንዲቀር ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በራስ ባህል ላይ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ይተዳደር የነበረውን የራያን የሆታ ስልት የመበረዝ ኹኔታም ታይቷል (ቃለ መጠይቅ፣ አራጋው አሰን፣ ከለላ ወረዳ፣ 04/07/2012)፡፡ ይህ የኾነውም ጎብረተሰቡ የዕርከን ሥራ ሲሠራ በዋለበት ዕለት መጨረሻ ላይና በየዓመቱ ግንቦት ኻያ በሚከበርበት ቀን በቀበሌ ደረጃ የሚገኙት የመንግሥት ኃላፊዎች ራሳቸው አውራጅ (የሆታ መሪ) ኾነው “እያያ አሚናት በለው፤ እያያ እሸም እንደ ራያ” የሚሉትን የሆታ የአዝማች ዓይነቶች ይከውኑ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ወጣቶቹ የሌላው የተሻለ ነው የሚል እንጂ የራሳቸውን ጠቃሚ አድርገው ስለማይመለከቱ ያንኑ የራያውን የሆታ ስልት ነበር የሚከውኑት (ቃለ መጠይቅ፣ ፯ አለቃ አድማሱ ከበደ፣ ቦረና ወረዳ፣ 21/05/2012)፡፡ ስለዚህ ለረኀቦም ጊዜ የሕዝብ የነበረው መንፈሳዊ ባህል በገኀቦው መደብ ሥር በመውደቁ የተነሣ ያለ አሳማኝ ምክንያት የመናድ አደጋ እንደደረሰበት መረዳት ይቻላል፡፡

ሐሳብን የመግለጽ፣ ታሪክን፣ ባህልን እና እምነትን ሰንዶ የማቆየት፣ በማኅበረሰብ ውስጥ ሥነ ምግባርን የማስተማር ፋይዳ ያላቸው የቃል ግጥም ሀብቶች እንዳይረሱ በተለያዩ ስልቶች የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውን ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል ሲሉ በመስከረም 09/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሳተፉት ሁሉም መረጃ ሰጭዎች አስረድተዋል። ለማሳያ ያክልም በተበቺሳ ጨዋታ ወቅት ሕይወት እንዳይጠፋ፣ የጥርስ መውለቅና የዓይን መጥፋት አደጋ እንዳያጋጥም፣ እንደዚሁም በቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ ለውጥ እንዳይከሠት ከተፈለገ በቅድሚያ የጎረምሳዎቹን ግጭት ከሥሩ ማድረቅ እንደሚቻል ከተወያዮቹ የተጨመቀው ሐሳብ ቀጥሎ ቀርቧል።

> *ጠላ ከተጠነሰሰበት ዕለት ጀምሮ እስከ ሰርጉ ዋዜማ ድረስ የተበቺሳ ጨዋታ ባለበት ወቅት የልጃገረዶችን የአታሞ ድምፅ የሰሙ ጎረምሳዎች ከሦስትና ከአራት ጎጦች ሊመጡ ይችላሉ። ከዚያም ጎረምሳዎቹ የየራሳቸውን አሳዳሪ በቅድሚያ እንዲመርጡ ይደረጋሉ። ከዚህ ቀጥሎ አሳዳሪዎቹም በአካባቢው ከተገኘው ሸማግሌ ጋር ኾነው የየጎጡን ጎረምሳዎች ዱላ ለየብቻ እንዲሰበሰብ ያደርጋሉ። ከዚህ በኋላ ከልጃገረዶቹ መካከል በአጋጣሚ አንዷ ትመረጥና አንደኛ፣ ኹለተኛ፣ ሦስተኛ፣ ... በማለት ከየጎጡ ከተሰበሰቡት ዱላዎች ዕጣ ታወጣለች። በአንደኛ ደረጃ ዕጣ የወጣላቸው ጎረምሳዎች በልጃገረዶቹ አጠገብ ኾነው ጨዋታቸውን ሲቀጥሉ፣ የሌሎቹ ጎጥ ጎረምሳዎች ግን ተራቸው እስከሚደርሳቸው ድረስ ዱላቸውን ሳይዙ በአሳዳሪዎቻቸው አማካይነት ከልጃገረዶቹ ራቅ ብለው ይቀመጡና የየራሳቸውን ጨዋታ ይጨዋወታሉ። ይሄ ራቅ ብሎ ተራ የመጠበቁ ኹኔታም "የበለል" በመባል ይታወቃል። ይህ የሚደረገው ከየጎጡ በመጡት ጎረምሳዎች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግ ነው።*
>
> *በልጃገረዶቹ አጠገብ ኾነው ጨዋታ የጀመሩት ጎረምሳዎች ደግሞ በቅድሚያ የልጃገረዶቹን የዘፈን የዜማ ስልት እየተከተሉ ሲደልቁ፣ ከወዳጆቻቸው ጋር ከንፈር ለከንፈር ሲሳሳሙ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ላይ ዱላቸውን ከሸማግሌው ተረክበው "ሆ" በማለት አካባቢውን ለቅቀው ወደየመጡበት እንዲመለሱ ይደረጋሉ። ከሌሎቹ ጎጦች የመጡ ጎረምሳዎችም በዕጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት ከደለቁ፣ የወዳጆቻቸውን ከንፈር ከሳሙ በኋላ የተወሰነላቸው ጊዜ ሲያበቃ ዱላቸውን ወስደው "ሆ" እያሉ ወደየቤታቸው ይኼዳሉ። ከልጃገረዶቹ ጋር የሚቆዩበት ጊዜ የሚወሰነው በአሳዳሪዎቻቸውና በሸማግሌው የጋራ ስምምነት ነው የሚኾነው። እንደሚታወቀው ልጃገረዶቹ በጎረምሳዎቹ እጃቸውን ተይዘው ከተወሰዱ በኋላ በቀጥታ አይሳሙም፤ ይግደረደራሉ። አንሳምም፤ እምቢ ብለው ካለቀሱም ይለቀቃሉ እንጂ አይገደዱም። በዚህ ዓይነት ኹኔታ ከልጃገረዶቹና ከጎረምሳዎች ጋር የሚጋጨ ካሉ በአሳዳሪዎቹም ኾነ በሸማግሌዎች አማካይነት አካባቢውን ለቅቀው እንድኼዱ ይደረጋል። የባህል ጉዳይ ስለኾነ አንኼድም የሚል ጎረምሳ አይኖርም።*

በማለት የቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊዎች ገልጸዋል። በዚህ መሠረት የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎችን ከትውልድ ወደትውልድ ቀጣይነት እንድኖራቸውና ቃል ግጥሞቹንም እንዳይረሱ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል።

❖ ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በአካባቢው በብዛት መሰራጨት፡-

በአሁኑ ወቅት ባለው ሕዝባዊ ባህል (popular culture) አማካይነት የዘመኑ የቴክኖሎጂ ውጤት የኾኑት የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሣሪያዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ በስፋት መሰራጨታቸውን Green (1997፡649) ገልጸዋል። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የሙዚቃ መሣሪያዎቹን በኢንዱስትሪ ማምረት የሚችል ባለሀብትና ያንን የሚያመርት ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል መኖር፣ በእነዚህ አማካይነትም የሙዚቃ መሣሪያዎቹ በገፍ መመረታቸው ነው። በዚህ የተነሣ የሥነ ቃል ዘውጎች በቃል መዜማቸው፣ መወጋታቸውና መተረታቸው ይቀርና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ሊሰራጩ ይችላሉ። ስለዚህ ሕዝባዊ ባህል (popular culture) ከገበያ ንግድ ጋር የተያያዘ ስለኾነ የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሣሪያዎችን የመሸመት ዐቅም ያለው ሰው ሁሉ ከገበያ እየገዛ ሊዝናና ይችላል። ይህ ደግሞ ማኅበረሰቡ ቀድሞ የነበረውን ነገር ትቶ አዲስ ነገር እንዲቀበል ያደርገዋል ማለት ነው። በዚህ መሠረት የሥነ ቃል ዘውጎቹ ልክ እንደቡድናዊ ባህል (Folk culture) በጎብረተሰቡ ካልተከወኑ ተዳሳሽ ቅርስ (Intangible Heritage) ኾነው ይቀራሉ እንጂ ባህል ሊባሉ አይችሉም ማለት ነው።

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚገኙ ወጣቶችም እጅ የቴክኖሎጂ ውጤት የኾኑት ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በብዛት በመግባታቸው የተነሣ በተለያዩ የመከወኛ አጋጣሚዎች በግለሰቦች አንደበት ይከወኑ የነበሩትን የቃል ግጥም ዘፈኖች ከማዳመጥ ይልቅ በሙያተኞች የተቀነባበሩትን ባህላዊ ሙዚቃዎች ማዳመጥ የተሻለ ነው የሚል አመለካከት እንዳለ ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያመለክታሉ። አቶ ይማሙ እብሬ (ቃለ መጠይቅ፣20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ) እንዳብራሩልኝ ከኾነ በአሁኑ ወቅት ያሉት ወጣቶች በየሞባይላቸው ላይ በተጫኑ ባህላዊ ሙዚቃዎች አማካይነት ስለሚዝናኑ፣ ቀደም ሲል በተለያዩ አጋጣሚዎች በቃል ሲዘፈኑ የነበሩ ቃል ግጥሞች በመረሳት ላይ ናቸው። በተለይ ልማድ እስከሚባል ድረስ ወጣቶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱም ኾነ ከጓደኞቻቸው ጋር ኾነው በአንድ ቦታ ላይ ሲቀመጡ፣ እንደዚሁም የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ በሞባይል ስልካቸው ባህላዊ ሙዚቃን ማዳመጥ በመቻላቸው በቃል የሚቀርቡትን ዘፈኖች ከክዋኔ እያስወጧቸው እንደኾነ በመስክረም 07/ 2013 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉት መረጃ ሰጭዎች ገልጸዋል።

እነዚህ የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሣሪያዎች አረጋውያን እና የሀብት እጥረት ያለባቸውን የጎብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ ስለማያደርጉ፣ እንደዚሁም መሣሪያዎቹን እንደልብ ለመገልገል (manipulate ለማድረግ) ስለማይቻል ችግሮች መከሠታቸው አይቀሬ ነው። በሰርግ ወቅትም ቢኾን በተወሰኑ በገጠር አካባቢዎች “ፍላሽ” በሚቀበል ቴፕ፣ በከተማዎች ደግሞ

“ጂፓዝ” በተባሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚቀርቡት ባህላዊ መዝሙሮች የሰርጉ ታዳሚዎች በጋራ አዝማቹን እየተቀበሉ፣ በዘፈኑ ጊዜ ደግሞ እስክስታ እየወረዱ እንደሚጨፍሩ ይማም አብዱ (ቃለ መጠይቅ፣22/ 05/2012 ዓ.ም፣ወግዲ ወረዳ) አስረድተዋል። ስለዚህ የኤሌክትሮኒክስ የመዝሙር መሣሪያዎቹ የቃል ግጥሞቹን የፋብሪካ ውጤት እየኾኑ እንዲመጡ ስላደረጓቸው ገጣሚያንን ከፈጠራ ሥራ እያፋቷቸው ነው። እነዚህ ኹኔታዎች ደግሞ በቃል ግጥሞችና በመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ችለዋል ማለት ነው።

❖ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እምነታቸውን አጠንክረው መያዛቸው፡- ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ ወጣቶች በኢኮኖሚ የተሻለ ደረጃ ላይ ለመድረስ ወደተለያዩ የዐረብ ሀገራት እንደሚሰደዱ ቀደም ሲል በተካኼደው የቃል ግጥም ትንተና ላይ ለማየት ተችሏል። በዚህ መሠረት የእስልምና እምነት ተከታይ የኾኑት ሴትና ወንድ ወጣቶች ከስደት ሲመለሱ ሃይማኖታቸውን አጠንክረው በመያዛቸው ወደተለያዩ የቃል ግጥም መከወኛ አካባቢዎች እንደማይኼዱ፣ ቢኼዱም እንኳን ዓለማዊ ዘፈኖችን እንደማይዘፍኑ፣ የሚፎክርና የሚያቅራራም እንደሌለ በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ይህም የኾነው “የሐዲስ”[35] ትምህርት እየተስፋፋ በመምጣቱ የተነሣ “ባህልና ሃይማኖት ዐብረው አይኼዱም” ስለሚባል ወጣቶቹ የፊተኞቹን ባህሎች በመተው ላይ በመኾናቸው ነው። ዘፈኑም ቢኾን “ሃራም” ነው ስለተባለ የቃል ግጥም ክዋኔ ከጊዜ ወደጊዜ ለመቀነስ ችሏል (ቃለ መጠይቅ፣ ከረን ሐሰን እንድሪስ፣ ከለላ ወረዳ፣ 04/07/2012)። ሐዲሱም ቢኾን በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ በወንድና በሴት መካከል የሚካኼደውን ጭፈራ በጥብቅ እንደሚቃወም Gulevich (2004፡233) ገልጸዋል። ለዚህ የቀረበው ምክንያት ጭፈራው ኹለቱንም ጾታዎች ለወሲብ ያነሣሣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለወሲብ የሚያማልሉ ዓለማዊ ዘፈኖችም ቢኾኑ የተወገዙ መኾናቸውን Gulevich (2004፡235) አስረድተዋል። ይህ በመኾኑም ሙስሊም የኾነ(ች) ወጣት በሚያገባ (በምታገባ) ዕለት የልጃገረዶች የቃል ግጥም ዘፈኖች፣ እንደዚሁም የጎረምሳዎች ሆታ፣ ቀረርቶና ፉከራ እንደማይከወኑ፣ በእነዚህ ምትክ ግን “አህመድ የመዲናው፣ መኣሊከ መኣሊከ፣ ወዘተ.” የሚሉ መወድሳዊ ዜማዎች እንደሚዜሙ በመስከረም 05 እና 07/2013 ዓ.ም በከለላና በወግዲ ወረዳዎች ከተካኼዱት የቡድን ተኮር ውይይቶች የተገኘው ጭምቃ ሐሳብ ያስረዳል።

[35] ነቢዩ መሐመድ ከሞቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሙስሊሞች የነቢዩ ናቸው የሚባሉትን እና አርዓያነት ያላቸውን ተግባሮቻቸውን፣ እንደዚሁም አስተማሪ የኾኑ አባባሎቻቸውን መሰብሰብ ጀመሩ። የሃይማኖቱ ልሂቃን ደግሞ ከተሰበሰቡት መካከል ሊታመኑ የማይችሉትን ለይተው ካወጡ በኋላ ጠቃሚ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ደግሞ ይብዛም ይነስም እውነተኛና ትክክለኛ አባባሎች መኾናቸውን ለማረጋገጥ የደረጃ ድልድል (rating) በማካኼድ በጽሑፍ አስፍረዋል። በዚህ ዓይነት መንገድ ተለይተው የተጻፉትና የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሕይወት መመሪያ የኾኑት የነቢዩ መሐመድ አባባሎች “ሐዲስ” በመባል ይታወቃሉ (Gulevich, 2004፡43)።

ነገር ግን የመንፈሳዊ እንጉርጉሮ ይዘት የሚንጸባረቅባቸው መንዙማዎች በሙስሊሞች ሰርግ ጊዜ መከወን እንደማይችሉ ከቡድን ተኮር ውይይቱ ለመገንዘብ ተችሏል።

❖ **የዘመናዊነት[36] መስፋፋት፡-** ዘመናዊነት ከከተሞች መስፋፋትና ከኢንዱስትሪው መበልጸግ፣ እንደዚሁም ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ የተነሣ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ሲባል የሰዎች ከቦታ ቦታ መፈናቀል ይከሠታል። በአሁኑ ወቅት ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች የሚገኙ ወጣቶችም በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት የተወለዱበትን አካባቢ ለቅቀው ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችም ሆነ ወደውጭ ሀገር ሄደው ይቆያሉ። እነዚህ ወጣቶች ከሄዱበት ሲመለሱ፣ ሌሎቹ ደግሞ መደበኛ ትምህርትን የመማር ዕድል ሲያገኙ የአኗኗር ኹኔታቸው እንደሚለወጥ አቶ በላይ አሰን ገልጸዋል (ቃለ መጠይቅ፣ 20/05/2012፣ ቦረና ወረዳ)። ስለዚህ ወጣቶቹ ከላይ በቀረቡት ምክንያቶች ቃል ግጥሞቹንም ሆነ የመከወኛ አጋጣሚዎቹን ጎላ ቀር አድርገው የመመልከት ኹኔታ የሚስተዋልባቸው መሆኑን በቃለ መጠይቅ የተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች አረጋግጠዋል።

ለማስረጃ ያክልም ቀደም ባለው ወቅት ልጃገረዶች በየግላቸው የቤታቸውን ሥራ አጠናቅቀው እንዳበቁ ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው ለእንጨት ሰበራና ለኩበት ለቀማ ወደጫካና ወደሜዳ ይኼዱ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በክረምት ወራት ከየቤታቸው ተጠራርተው ወደበረሓ በመውረድ እንጨት ይሰብሩ ነበር። በእነዚህ አጋጣሚዎች ልጃገረዶቹ ዘለግ ባለና በሚያስደስት ድምፅ የፍቅር ዘፈኖችን ያዜሙ ነበር። አሁን ላይ ግን ወጣቶቹ የመደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመሆናቸው፣ ከተለያዩ ሀገራትና ቦታዎች በመመለሳቸው ዘመናዊነትን ለመከተል በቅተዋል። የማኅበረሰቡ አባላትም በወል መሬት ላይ የሚገኙትን ዛፎች እየቆረጡ በመከፋፈል የማገዶ ችግራቸውን በማስወገድ ላይ ናቸው። በዚህ የተነሣ ልጃገረዶቹ በእንጨትም ሆነ በኩበት ለቀማ ተግባራት ስለማይሳተፉ የቃል ግጥሞችን መከወን አለመቻላቸውን ከመስከረም 05 እስከ 09 /2013 ዓ.ም ድረስ በሦስቱም ወረዳዎች በነበረው ቡድን ተኮር ውይይት ከተጨመቀው ሐሳብ ለማወቅ ተችሏል። ወጣት ወንዶቹም ቢሆኑ በክረምት ወራት የቤት እንስሳትን ለመጠበቅ ደረባ በሚከርሙበት ወቅትም ሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች የቀረርቶ ቃላዊ ግጥሞችን ተናጠላዊ በሆነ መንገድ ማቀንቀናቸው እየቀረ መምጣቱን መረጃ ሰጪዎቹ ገልጸዋል። ከዚህ ሌላ ቀደም ባሉት ጊዜያት በኹለቱም ጾታ ያሉት ወጣቶች ሰብልን ከዝንጀሮ፣ ከጦጣ፣ ከወፍ፣ ወዘተ. በሚጠብቁባቸውና ከብቶችንም በሚያግዱባቸው ጊዜያት የቃል ግጥሞችን ያዜሙ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ሰብልን

[36] በወቅቱ ያለውን አዲስ የአስተሳሰብ፣ የአኗኗር ኹኔታ፣ ወዘተ. መከተል ማለት ነው።

የመጠበቁም ኾነ እንስሳቱን የማገዱ ተግባራት የወላጆች በመኾኑ ቃል ግጥሞቹ የመከወን ዕድል የላቸውም።

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ የአክርማና የስንደዶ ቀጨታ ሳምንት ሙሉ በሙሉ የቀረ በመኾኑ ልጃገረዶቹ በዚህ አጋጣሚ ያቀነቅኗቸው የነበሩት የፍቅር ዘፈኖች አለመከወናቸውን መረጃ ሰጪዎች አስረድተዋል። ለዚህ ደግሞ አንደኛው ምክንያት አክርማና ስንደዶ የሚቀጨው መሶብ፣ ሌማት፣ ድርብ፣ ቁና፣ ሰፌድ፣ አገልግል፣ ወዘተ. የተባሉትን የቤት ዕቃዎች ለመስፋት ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን በጎብረተሰቡ የኑሮ ለውጥ (ዘመናዊነት) ምክንያት ሰዎቹ የፋብሪካ ውጤቶችን ከሱቅ ገዝተው በመጠቀማቸውና ግራምጣ የተባለውንም ሣር ከገበያ በመግዛት ስፌት መስፋት በመቻላቸው የተነሣ ነው። ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ ካለ እናቶች በስተቀር ልጃገረዶቹ የመደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመኾናቸው የአክርማውን እና የስንደዶ ቀጨታውን እንደ ኋላ ቀር ቆጥረውታል በማለት በመስከረም 09/2013 ዓ.ም በቦረና ወረዳ በተካኼደው ቡድን ተኮር የተሳተፉት አቶ ጠና ይመርና አቶ ንጉሤ ባሻ ገልጸዋል።

9.2. ቀጣይነት በወሎ ቦረና ማኅበረሰብ የቃል ግጥሞችና የመከወኛ አጋጣሚዎች

ቀጣይነት የሚባለው በአንድ ኅብረተሰብ አኗኗር ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ሳያቋርጡ ወደፊት ሲቀጥሉ እንደኾነ በጽንሰ ሐሳብ ቅኝት ላይ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው የኅብረተሰብ ክፍል ምርታማነቱን ከሚያሳድግባቸው ግብኣቶች መካከል አንደኛው የኬማካል ማዳበሪያ ሲኾን፣ ማዳበሪያውም ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ ጥቅም ላይ መዋሉን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ (2012፡ 18) ገልጿል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉት አርሶ አደሮችም ኬሚካሉን በመጠቀም ብዙ ምርት የማምረት ተግባራቸውን የቀጠሉ በመኾኑ ጉዳዩን በተመለከተ የሚቀርቡት የቃል ግጥም ክዋኔዎችም ሳይቋረጡ በተከታታይነት እየተካኼዱ መኾኑን ከመስክ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ቃል ግጥሞቹም አርሶ አደሮቹ በተወሰነ የእርሻ መሬት ይዞታቸው ላይ ማዳበሪያን ተጠቅመው የተትረፈረፈ ምርት ማምረት ስለመቻላቸው፣ በአቅርቦት ማነስ የተነሣ ሁሉም አርሶ አደሮች ማዳበሪያ ባለማግኘታቸው የሥርጭት መዛባት ስለመኖሩ፣ እንደዚሁም ማዳበሪያው በመንግሥት አማካይነት በብድር የሚቀርብ ቢኾንም ዋጋው በጣም በመወደዱ የተነሣ አርሶ አደሮቹ ዕዳ በዕዳ መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት የማያቋርጡ

እስከኾኑ ድረስ የውዳሴም ኾነ ትችት አዘል ቃል ግጥሞቹ የመከወናቸው ኹኔታ ቀጣይነት ያለው መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በኹለተኛ ደረጃ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለው የግብኣት ዓይነት ብስባሽ የተባለው የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የግብኣት ዓይነቱም ከጥንት ጀምሮ አርሶ አደሮች በግል ልምዳቸው ሲጠቀሙበት የነበረ፣ ከትውልድ ወደትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና የሀገር በቀል ዕውቀት ውጤት መኾኑን በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘው መረጃ አመላክቷል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አርሶ አደሮቹ ከግብርና ሙያተኞቹ በተሰጣቸው ትምህርት አማካይነት ሊበሰብሱ የሚችሉ የዕፅዋት ቅሪቶችን እና የሣር በል እንስሳትን ፍግ ከውሃ ጋር አዋሕደው በጉድጓድ ውስጥ እንዲብላሉ ካደረጉ ከአንድ ወር በኋላ የተለያዩ የመጓጓዣ መንገዶችን ተጠቅመው በማሳቸው ላይ ካለው ዐፈር ጋር በመጨመር ምርታማነትን ማሳደግ የቻሉ መኾኑን በተመለከተ ቀጣይነት ያላቸውን የሙገሳ ቃል ግጥሞች ማዜማቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሥራ ጠል የኾነውና በሰበብ አስባቡ ተቀምጦ የሚውለው ሰው ብስባሽ የተባለውን ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ አዘጋጅቶ በእርሻ መሬቱ ላይ ባለመበተኑ ምክንያት የተትረፈረፈ ምርት ሊያገኝ ቀርቶ በማሳው ላይ የዘራውን እኽል እንኳ መተካት አለመቻሉን በተመለከተ ትችት አዘል ግጥሞች የሚቀነቀኑ መኾኑንም መረጃዎቹ አመላክተዋል፡፡

ፀረ ዐረም ኬሚካልን መጠቀም ሌላው የምርታማነት ግብኣት መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ምንም እንኳን በሰብል ውስጥ ያለውን ዐረም በተቻለ መጠን በእጅ ማረም ጥሩ ተግባር ቢኾንም የጉልበት ዕጥረት በሚያጋጥምበትና ዐረሙ አዳጋች በሚኾንበት ወቅት ቅጠለ ሰፋፊ የኾኑትን፣ እንደዚሁም የተለያዩ የሣር ዐረሞችን በፀረ ዐረም ኬሚካል በማስወገድ አርሶ አደሩ ከፍተኛ ምርት ማግኘት መቻሉን አስመልክቶ የቃል ግጥሞችን ማቀንቀን ችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእርሻ ሥራ የሚተዳደረው አርሶ አደር በሐሩር፣ በቁር፣ እንደዚሁም በዝናብ ወቅት ዐረምን በማረም መውጣትና መውረዱ፣ መልፋት መድከሙ ስለቀረለት ፀረ ዐረም ኬሚካሉን በቃል ግጥም ሲያሞግሰው ተደምጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ ዐረም ኬሚካል ከገበያ የሚገዛበት ዋጋ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ኾኖ እያለ ያንን በገንዘብ ገዝቶ በሰብሉ ላይ በመርጨት የተሻለ ምርት ያላገኘ አርሶ አደር በሚሰቀጥጡ የቃል ግጥሞች መተቸቱን ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ከእኽል ጋር የበቀለውን ዐረም በኬሚካሉ የማስወገዱ ተግባር የማያቋርጥ እስከኾነ ድረስ ቃል ግጥሞቹም የመከወን ዕድላቸው ቀጣይነት ያለው መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የእርሻ መሬት ለም ዐፈር በጎርፍ አማካይነት እየተሸረሸረና እየተጠረገ እንዳይወሰድ በድንጋይ ካብ አማካይነት ደግፎ በመያዝ ምርትን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ባለው የማሳ ዕርከን ሥራ ላይ የቃል ግጥሞች እንደሚቀነቀኑ በሰነድም ሽነ በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ። ከእነዚህ ቃል ግጥሞች መካከልም የተወሰኑት የዕርከን ሥራውን በጋራ፣ በአንድነት፣ በመደጋገፍ፣ በትጋት፣ ወዘተ. የሚሠሩትን የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያበረታቱ፣ ምክርን የሚለግሱ፣ ወዘተ. ሲሽኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ በድንጋይ ካብ የተሠራው ዕርከን በማሳ ላይ ያለውን ሰብል በመብላት ጥፋት ለሚያደርሰው ዐይጥ ምቹ መኖሪያ ጉድጓድ መሽኑን በተመለከተ ትችትን የሚሰነዝሩ ሽነው ተገኝተዋል። ይህ በመሽኑም በሀገራችን ረጅም ዕድሜ ያለው የዕርከን ሥራ ያለማቋረጥ ከትውልድ ወደትውልድ የሚሸጋገር እስከሽነ ድረስ ከላይ የተጠቀሱ ጭብጦች ያሏቸውም ሽነ ሌሎች የቃል ግጥሞች ቀጣይነት ባለው ኹኔታ መከወናቸው አይቀሬ መሽኑን ለመረዳት አያዳግትም።

ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያገለግሉ ግብኣቶች በተጨማሪ የግብርና የሥራ ዘርፎች ለቃል ግጥሞችና ለመከወኛ አጋጣሚዎች ቀጣይነት የላቀ አስተዋፅኦ ያላቸው መሽኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ መነሻነት ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ላለው የኅብረተሰብ ክፍል የህልውናው መሠረት ከእርሻ ሥራ የሚገኘው ምርት መሽኑ ይታወቃል። ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ማንኛውም የእርሻ ሥራ የሚከናወነው በበሬ በሚጎተት ማረሻ በማረስ፣ ለማረስ የማያመቸውን ደግሞ በዶማ በመቆፈር እንጂ በትራክተር አይደለም። ይህ በመሽኑም አንድ አርሶ አደር አጥጋቢ የሽነ ምርት ለማምረት የእርሻ ማሳውን በአማካይ እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ በበሬ ደጋግሞ ማረስ አለበት (የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ፣2012፡18)። ስለዚህ አርሶ አደሩ የእርሻ መሬቶቹ ወጣ ገባ በመሽናቸው የሰዎች ፈጠራ የታከለባቸውን እና በእርሻ ምርት ኺደት ውስጥ ዋነኛ ስፍራ ያላቸውን ማሽኖች (እንደትራክተር ያሉ የእርሻ መሣሪያዎች) በአሁኑ ወቅትም ቢሽን ሲጠቀም አይስተዋልም። ይኽ በመሽኑም ከመጀመሪያው ዙር አንሥቶ ዘር እስከሚዘራበት ወቅት ድረስ በበሬዎች አማካይነት የእርሻ ሥራውን ሲያከናውን ያለማቋረጥ በሬዎቹን እያሞገሰ ቃል ግጥሞችን ማዜም እንደቻለ በመረጃ ትንተናው ወቅት ተረጋግጧል። የተትረፈረፈ ምርት ሲያገኝም ለችግር ሳይፈታ፣ ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ዝናብና ፀሐይ ሳይፈራ፣ ብርድና ነፋስ ሳይበግረው እያረሰ ያለ ጠንካራ ገበሬ መሽኑን በፉከራ ስልት ራሱን አወድሷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ታታሪው አርሶ አደር ሰነፍ ለሽነው ሰው የእርሻ ተግባር ቢልት ወይም ቀልድ አለመሽኑን ትችት አዘል በሽነው ቃል ግጥም ሲመክረው በመረጃው ታይቷል። ከዚህ በተጨማሪ ትዳር መሥርቶና ልጅ ወልዶ የሚያርሰው መሬት የሌለው ወጣት የወላጆቹን እና

የሌሎች ሰዎችን መሬት አርሶ ከሚያገኘው ምርት አንድ ሦስተኛውን ብቻ ለራሱ አስቀርቶ ሌላውን ለእነሱ በመስጠት ላይ እንደሚገኝ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በዚህ የተነሣ የመሬት ባለቤቶቹ በማምረት ተግባር ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ሳያደርጉ ሌሎች የደከሙበትን ምርት የሚያጋብሱ በመኾናቸው ሚሶ አራሹ ገበሬ በቃል ግጥም ነቀፋ አቅርቦባቸዋል። ስለዚህ በበሬዎች አማካይነት የሚከናወነው የእርሻ ተግባር የማያቋርጥ የቃል ግጥም መከሠቻ በመኾኑ ከላይ የተጠቀሱትንም ኾነ ሌሎች ርእሰ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ የቃል ግጥሞች ቀጣይነት ባላቸው ኹኔታ ሊከወኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል።

አርሶ አደሩ ከእርሻ ቀጥሎ ባለው ተግባር ቅጠለ ሰፋፊ የኾኑትን፣ እንደዚሁም የተለያዩ የሣር ዐረሞችን በፀረ ዐረም ኬሚካል በማስወገድ ከፍተኛ የኾነ ምርት ማግኘት እንደቻለ ቀደም ሲል በቀረበው ትንተና ለማየት ተችሏል። ይህ ዓይነቱ የቴክኖሎጂ ውጤት ምንም ያክል የተራቀቀ ቢኾንም ያለ ሰው ተሳትፎ ዋጋ የለውም። ስለኾነም በምርት ኺደት ውስጥ ዋናውና ወሳኙ ሰው በመኾኑ ኬሚካል በመጠቀምም ኾነ በእጅ በማረም የሚከናወነው ተግባር ለቃል ግጥም መከወኛ መልካም አጋጣሚ መኾኑን ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ ማንኛውም አርሶ አደር እሾኽ፣ ብርድና ድካም ሳይበግረው ጠንክሮ በማረም የተትረፈረፈ ምርት ማግኘት እንደቻለ የሚያመላክቱ ቃል ግጥሞች መቀንቀናቸውን በጥናቱ ለማየት ተችሏል። ዐረሙ በጣም አስቸጋሪ የኾነበት ሰውም ቢኾን በልመና፣ በወንፈል፣ በደቦ፣ ወዘተ. አማካይነት አዋኪ የኾነውን ዐረም በሚያሳርምበት ወቅት ዐራሚዎቹ ፍጥነታቸውን ለመጨመር፣ ድካም እንዳይሰማቸው ለማድረግና ሞራላቸውን ለማነቃቃት ሲባል የተለያዩ የፍቅር ቃል ግጥም ዘፈኖች በልጃገረዶች መዜማቸውን በዐውድ ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ መሠረት የዐረም ተግባር የማያቋርጥ በመኾኑ የቃል ግጥሞችም ቀጣይነት ባለው ኹኔታ ሊከወኑ እንደሚችሉ መረዳት ይገባል።

ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያስገኛቸውን አዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች መጠቀም ከምንጊዜውም በበለጠ ኹኔታ በብዛትና በጥራት፣ እንደዚሁም ያለ ምንም ብክነት ምርት እንዲመረት የሚያስችል መኾኑ አጠያያቂ አይደለም። ነገር ግን ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያሉ አርሶ አደሮች ሰብላቸውን የሚያመርቱባቸው መሬቶች በአብዛኛው ወጣ ገባ ያሉ መኾናቸውን በምዕራፍ ኹለት ለመቃኘት ተሞክሯል። በዚህ መሠረት አርሶ አደሮቹ የማጨዱን ተግባር በእጃቸው እንጂ የቴክኖሎጂ ውጤት የኾነውን የማጨጃ መሣሪያ የማይጠቀሙ መኾኑንም በመስክ ቆይታ ወቅት ለማየት ችያለሁ። ይህ በመኾኑም አርሶ አደሮቹ በባለሙያ በተሠራ የሰላ ማጭድ ሰብላቸውን በፍጥነት ማጨዳቸውን በተመለከተ በቃል ግጥም መግለጽ መቻላቸውን በመረጃ ትንተናው ላይ እውን ኾኗል። በታታሪነታቸውም በፉከራ

ስልት ራሳቸውን አሞግሰዋል። በአጨዳ ተግባር ላይ የተሰማሩ አንዳንድ አርሶ አደሮችም በሰበብ አስባቡ የሥራ ጊዜያቸውን በከንቱ ሲያሳልፉ በመታየታቸው በቃል ግጥሞች ተተችተዋል። ስለዚህ በጥናቱ የተካለሉት አርሶ አደሮች ማጭድን ተጠቅመው ሰብላቸውን በእጃቸው የማጨድ ተግባራቸው ከጊዜ ወደጊዜ የሚሸጋገር በመኾኑ ለቃል ግጥሞችና ለመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ቀጣይነት አስተዋፅኦ ያለው መኾኑን ማጤን ይቻላል።

አርሶ አደሩ በዓመቱ ውስጥ ከሚያከናውናቸው የግብርና ተግባራት መካከል የመጨረሻው እኽልን መውቃት ነው። የታጨደውን እኽል በዐውድማ ላይ አድርጎ የመውቃት ተግባር ደግሞ ብዙ የሰው ጉልበትን የሚጠይቅ በመኾኑ ምን ጊዜም በባሕርይው ማኅበራዊ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ብቻውን ኾኖ በአንድ ጊዜ የተከመረውን እኽል የመናድ፣ በሬዎችን ባውድማ ላይ የማኼድ (የማዞር)፣ እኽሉን በመንሽ የመበርበር (የላዩን ወደውስጥ፣ የውስጡን ወደላይ የማድረግ፣ የማገላበጥ)፣ በላይዳ አማካይነት ምርቱን ከእብቅና ከገለባ በነፋስ የመለየት፣ ወዘተ. ተግባራትን ማከናወን አይችልም። ስለዚህ አርሶ አደሩ እነዚህን የውቂያ ተግባራትን ሲያከናውን ከሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት ጋር መተባበርና መተጋገዝ ይኖርበታል። በዚህ ኺደትም ሙሉ ሕይወቱ በበሬው ላይ ጥገኛ በመኾኑ የቤት እንስሳው ክፉ ነገር እንዳያጋጥመው መመኘቱን ከመስክ የተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች አመላክተዋል።

ምክንያቱም በበሬው አማካይነት የሚፈልገውን ነገር ስላገኘና የልቡም ስለደረሰ ተደስቷልና ነው። በሬው እንዳይርበውና እንዳይጠማውም የሚያስፈልገውን ነገር በማሟላት የራሮት ስሜቱን በቃል ግጥም መግለጹንም በተሰበሰቡት መረጃዎች ተረጋግጧል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ አርሶ አደሮች ወጥተው ወርደው በማረስና በመውቃት ራሳቸውንም ኾነ ቤተሰቦቻቸውን መመገብ ባለመቻላቸው የተነሣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ዝቅ ተደርገው ስለሚታዩ የጥላቻ ወይም የመጸየፍ ስሜትን አጉልተው በሚያሳዩ የቃል ግጥሞች የተተቹ መኾኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ስለዚህ አርሶ አደሩ የሚኖርበት መልክዓ ምድር በአብዛኛው ወጣ ገባ ያለ በመኾኑ የተነሣ እስካሁን ድረስ የእኽል መውቂያ ማሽን ስለማይጠቀምና ከላይ የተጠቀሱት የእኽል መውቃት ተግባራትም በተከታታይነት በሰውና በበሬ ጉልበት ብቻ ስለሚከናወኑ የቃል ግጥሞቹም ቀጣይነት ባለው ኹኔታ የሚቀነቀኑ መኾናቸውን መረዳት ይቻላል።

ከግብርና የሥራ ዘርፎች በተጨማሪ የቃል ግጥሞች ከሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንደኛው የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ የሚያልፍባቸው ዓበይት የሽግግር ሥርዓቶች ናቸው። ከእነዚህ ሥርዓቶች መካከልም አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሕጋዊ በኾነ መንገድ ዐብረው ለመኖር በሚያስችላቸው የኑሮ ትስስር ወቅት በሚካኼደው ጋብቻ ሰሞን ሲከወን የነበረው

የተበቺሳ ጨዋታ በተለያዩ ምክንያቶች የቀረ ቢኾንም በሰርግ ዕለት በሚኖረው ሥርዓት ግን የልጃገረዶች ዘፈን፣ የጎረምሳዎች ሆታ፣ እንደዚሁም በተለያዩ ታዳሚዎች የሚቀነቀኑት የቀረርቶና የፉከራ ቃል ግጥሞች ቀጣይነት ባለው ኹኔታ በመከወን ላይ መኾናቸውን በዐውድም ኾነ በቃለ መጠይቅ የተገኙት ማስረጃዎች አመልክተዋል።

በልጃገረዶቹ የሚቀርቡት ዘፈኖችም ሙሽራዋ ከቤተሰቦቿ የመለየቷን አስከፊነት፣ በመልክ፣ በቁመት፣ ወዘተ. ረገድም ሙሽራውን የማብሸቅ፣ ሆታው ደግሞ ደም ደም የመሸተት፣ ጠብ ወይም ዐምባጓሮ የመፈለግ፣ ወዘተ. ኹኔታ የተንጸባረቀባቸው መኾኑን በመረጃ ትንተና ወቅት ለመረዳት ተችሏል። የቀረርቶ ግጥሞችም ቢኾኑ ወኔን ቀስቃሽና ብሶትን ገላጭ፣ የፉከራዎቹ ደግሞ ዘራፍ ባዩ ግለሰብ በተሰለፈበት የሥራ መስክ ጀግንነቱን፣ ልበ ሙሉነቱን፣ ደፋርነቱን፣ ቆራጥነቱን፣ አልበገር ባይነቱን... ለሌሎች ያስረዳባቸው መኾናቸውን መረጃዎቹ አሳይተዋል። በዚህ መሠረት ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ጋብቻ እስካለ ድረስ የጋብቻውን በዓል ለማክበር በሚደረገው የሰርግ ሥርዓት ዕለት የሚከወኑት የልጃገረዶች ዘፈን፣ የጎረምሳዎች ሆታ፣ ቀረርቶና ፉከራ ቀጣይነት ያላቸው መኾኑን መገንዘቡ ተገቢነት ይኖረዋል።

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ከአንድ የዕድገት ደረጃ ወደሌላ ከሚያልፍባቸው ሽግግሮሽ መካከል አንዱ ሞት ሲኾን፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከኾነው የማኅበረሰብ አባላት ውስጥ እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ እንደዚሁም ወንድምና እኅት በሚሞቱበት ዕለት በሚከወኑት የለቅሶ ሥርዓቶች የሙሾ ቃል ግጥሞች ያለማቋረጥ የሚደረደሩባቸው አካባቢዎች መኖራቸውን በቃለ መጠይቅና ከተለያዩ ሰነዶች በተገኙት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል። በዚህ መሠረት እናት ለልጆቿ ያላትን የጠበቀ ቁርኝት፣ እሷ ከሞተች በኋላም ልጆቿ ለብዙ ጊዜያት ያኽል ምግብ በማጣታቸው የተነሣ በረኃብ ዐለንጋ መገረፋቸውን፣ በልብስ ዕጦትም ዕርዝተኛ መኾናቸውን፣ ወዘተ. የሚያመላክቱ የሙሾ ቃል ግጥሞች በተከታታይ እንደሚደረደሩ የተሰበሰቡት መረጃዎች አረጋግጠዋል። አባትም ወላጅነቱን፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱን፣ ከዚህ በተጨማሪም ለልጆቹ መመኪያነቱን እና አለኝታነቱን የሚያመላክቱ የቃል ግጥሞች በሙሾ ዐውራጆች የሚደረደሩ መኾናቸውን ለመረዳት ተችሏል። በተለይም በገጠሩ ማኅበረሰብ ዘንድ ልጆች ከብት በማገድ፣ እርሻ በማረስ፣ ዐረም በማረም፣ ሰብል በማጨድና በመውቃት ተግባራት ላይ የሚሳተፉና ከፍተኛ የኾነ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው መኾኑን የሚያሳዩ የሙሾ ቃል ግጥሞችም እንደሚቀነቀኑ መረጃዎቹ አመላክተዋል። ስለዚህ ሞት የተፈጥሮ ክሥተት በመኾኑና ሳይለዋወጥ እንዳለ በመደጋገሙ የተነሣ ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ርእስ ጉዳዮች የሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞች ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚከወኑ መረዳት ይቻላል።

ምዕራፍ ዐሥር፡- ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች

በዚህ ምዕራፍ ሥር ዅለት ዓበይት ርእሰ ጉዳዮች በቅደም ተከተል ተካትተዋል፡፡ አንደኛው በጥናቱ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች ሲኾኑ፣ ዅለተኛው ደግሞ የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ የቀረቡ የይሁንታ ሐሳቦች ናቸው፡፡

10.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት «የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና» በሚል ርእስ የተካኼደ ሲኾን፣ ዓቢይ ዓላማውም ከመስክ የተሰበሰቡትን የቃል ግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸውን መለየት፣ በቃል ግጥሞቹ ላይ የዘውግ ምደባ ማካኼድ፤ ዐውዳዊ ትንተና ማድረግ፣ ቃል ግጥሞቹ ያሏቸውን ፋይዳዎች መመርመር፣ ለውጥና ቀጣይነታቸውንም ማየት የሚል ነው፡፡ ዓላማውን መሠረት በማድረግ በጥናቱ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የተዘጋጁት ጥያቄዎችም ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው? በምን በምን ዘውጎች ላይ ያተኮሩ ናቸው? ቃል ግጥሞቹ በዐውድ ሲተነተኑ የሚያስተላልፉት ይዘት ምንድን ነው? የቃል ግጥሞቹ ለማኅበረሰቡ ያሏቸው ፋይዳዎች ምን ምን ናቸው? በማኅበረሰቡ የአኗኗር ለውጥ የተነሣ በቃል ግጥሞቹና በመከወኛ አጋጣሚዎቹ ላይ የተከሠተው ለውጥና ቀጣይነት ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው፡፡

ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን እና ገላጭ የምርምር ዓይነትን የተከተለ ሲኾን፣ የዓላማ ተኮርን እና የጠቋሚ የናሞና ዘዴዎችን በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በእነዚህ የንሞና ዘዴዎች አማካይነት ጥሬ መረጃዎቹ በሰነድ ፍተሻ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና፣ በቡድን ተኮር ውይይት ከተሰበሰቡ በኋላ በክዋኔያዊ፣ በተግባራዊ እና በዐውዳዊ ንድፈ ሐሳቦች ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው ወቅት ዘይቤያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ስልቶች ቃላዊ ግጥሞቹን ሳቢና ቀላል ያደረጓቸው በመኾኑ እነሱንም በተጓዳኝነት ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚያም ከትንተናው የተገኙት ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ጥናቱ ባካለላቸው ወረዳዎች የሚገኘው አርሶ አደር ምርታማነቱን ለማሳደግ የኬሚካል ማዳበሪያ፣ ብስባሽ፣ ፀረ ዐረም እና ዕርከን ሥራ የተባሉትን ግብዓቶች ይጠቀማል፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸው መልካም አጋጣሚዎች መኾናቸውን በመስክ ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመረጃ ትንተናው መሠረት አርሶ አደሮቹ ወቅት ጠብቀው የሚያከናውኗቸው የማረስ፣ የማረም፣ የማጨድና የመውቃት የሥራ ዓይነቶች ለቃል ግጥም መከወኛ ምቹ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ትንተና መሠረት

ቃል ግጥሞች በእርሻ ሥራ የሚተዳደረውን አርሶ አደር የድካም ስሜቱን ያስወግዱለታል፤ ለሥራ ያነሣሡታል፤ ያበረታቱታል። አላስፈላጊ የኾኑትንም ነገሮች ይተቹለታል፤ ከዚያም አልፎ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሥራውን ሲያከናውን ያስተባብሩለታል።

ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያገለግሉ ግብዓቶችና ከግብርና የሥራ ዓይነቶች በተጨማሪ ተበቺሳ፣ የተለያዩ የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች፣ የሰርግ ሥርዓት፣ የተለያዩ ክብረ በዓላትና የሰብል መጠበቂያ ቦታዎች፣ ወዘተ. በልጃገረዶች ለሚከወኑት የቃል ግጥም ዘፈኖች ማለፊያ የመከወኛ አጋጣሚዎች እንደነበሩ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። በዚህን ወቅት ዘፈኖቹን ሰምተው ከተለያዩ አካባቢዎች ከንፈር ለመሳም ለሚመጡ ጎረምሳዎችም የሆታ ቃል ግጥሞችን እንዲያዜሙ በር ከፍተውላቸዋል።

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ከሚያልፍባቸው ዓበይት የዕድሜ ሽግግር ሥርዓቶች መካከል የመጨረሻው ሞት መኾኑ ይታወቃል። ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ እንደዚሁም ወንድምና እኅት በሚሞቱበት ጊዜ የሚከወኑት የለቅሶ ሥርዓቶች የሙሾ ግጥምን ለማውረድ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው‹‹ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሞቹም እናት ለልጇ ያላትን የጠበቀ ቁርኝት፣ አባት ለልጆቹ ያለውን መመኪያነትና አለኝታነት፣ ያለ ወንድም የተሟላ ሕይወት መምራት አለመቻሉን፣ እኅትም ብትኾን የእናት አምሳያነቷን፣ ወዘተ. የሚያንጸባርቁ ናቸው።

የቃል ግጥም ዘውጎቹም ከሚቀርቡባቸው ማኅበራዊ ዐውዶችና አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ የፍቅር፣ የምርቃት፣ የሰርግ፣ የለቅሶ፣ የእንቁጣጣሽ፣ የሥራ፣ የፉከራ፣ የቀረርቶ፣ የእረኛ፣ የበገና፣ የክብረ በዓል፣ ... ብሎ መከፋፈል እንደሚቻል በምዕራፍ ስድስት ለማየት ተችሏል። በዚህ የምርምር ጽሑፍም በተለያዩ ዘዴዎች ከመስክ ተሰብስበው በክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች የግብርና ሥራ፣ የሰርግ፣ የለቅሶ፣ የሆታ፣ የቀረርቶና የፉከራ በማለት ለመመደብ ተችሏል። ጽሑፉ የአዝማሪ ግጥሞችን እንዳልተመለከተ መገንዘብ ይቻላል። በእርግጥ በአንድ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ቃል ግጥሞች በሌላ ምድብ ውስጥ የሚገኙ መኾናቸውን በዘውግ ውገና ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። ለአብነትም በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከወኑት የፉከራ ቃል ግጥሞች በእርሻና በአጨዳ የሥራ ወቅት እየተቀነቀኑ ይገኛሉ።

በዚህ ጥናት ውስጥ ከላይ ከተዘረዘሩት ርእሰ ጉዳዮች በተጨማሪ በተለያዩ ዘዴዎች ከመስክ የተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች በየዘውጋቸው ከተፈረጁ በኋላ በዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ትንተና ተካሺዶባቸዋል። ስለኾነም በተለይ የሥራ ቃል ግጥሞቹ ዐውዳዊ ትንተናቸው ያተኮረው በሙገሳና በእርካታ፣ በትችት፣ በብሶት፣ በቁጭት፣ በመማጸን፣ በጠንክሮ መሥራት ተገቢነት ላይ ነው። በሕይወት ሽግግር ሥርዓት ወቅት የተቀነቀኑት ቃል ግጥሞችም ቢኾኑ ዐውዳዊ ትንተናቸው በዋናነት ውበትን በማድነቅ፣ በልጅነት ወቅት በተከሠተ ፍቅር በመንገላታት፣ የከንፈር ወዳጅን ቤተሰቦች በማወደስ፣ ጀግናን በማድነቅ፣ በፍቅር አቻ ባለመኾን፣ በመለያየት አስከፊነት፣ ፈሪን እና ነገረኛን በመተቸት፣ በጦር መሣሪያ አስፈላጊነት ላይ ያነጣጠረ ነው።

በአርሶ አደሮቹ አንደበት የተዜሙት ቃል ግጥሞች የተለያዩ ተግባራት ያሏቸው መኾኑንም በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በተተነተኑት መረጃዎች አማካይነት የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። በዚህ መሠረት ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ ተግባር ያላቸው ቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ አንደበት የሚቀነቀኑ መኾናቸውን ከመስክ የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል። በመኾኑም ግጥሞቹ ጀግኖቹ እንዲዘከሩ፣ ተጋድሏቸውም ቢኾን ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍና አርኣያነታቸውም ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ችለዋል ማለት ነው። ቃል ግጥሞቹ የማኅበረሰቡን መልካም ዕሴቶች ለተከታዩ ትውልድ የማስተማር ፋይዳም እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በዚህም ሞራልን ወይም ግብረ ገብነትን፣ እንደዚሁም ጥሩ ወይም መልካም ሥራን የሚያንጸባርቁ ዕሴቶችን በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆችን እና ወጣቶችን በማስተማር ገና ከለጋነታቸው ጊዜ ጀምሮ ባሕርያቸውን መቅረጽ እንደሚገባ መረዳት ተችሏል። የቃል ግጥሞች በሥራ የመትጋትን ጥቅም ለማኅበረሰቡ የማሳወቅ ተግባር እንዳላቸውም ለመገንዘብ ተችሏል። በመኾኑም የቃል ግጥሞቹ የሥራ ፍቅር እንዲኖር በማድረግ ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊው ልማት የሚያደርጉት አስተዋዕኦ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። ቃል ግጥሞቹ እኩይ የኾኑ ባሕርያትን የመግታት ተግባር እንዳላቸውም ለማወቅ ተችሏል። እኩይ በኾነው ተግባር የተዘፈቁ ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥሞች አማካይነት በማኅበረሰቡ ሲወገዙ ተስተውሏል።

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች በቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች ላይ ለውጦች ተከሥተዋል። ለለውጦቹ ምክንያት ናቸው ከሚባሉት መካከል አንደኛው የተወሰኑ ወጣቶች የቃል ግጥሞቹ የማኅበረሰቡ መንፈሳዊ ሀብት መኾናቸውን ባለመገንዘብ ዘርፉን ዝቅ አድርገው የመመልከት ኹኔታ ያላቸው መኾኑን መረጃዎቹ አመላክተዋል። ኹለተኛው ደግሞ በመንግሥታት የፖለቲካ ሥርዓት መለወጥ የተነሣ በቃል ግጥሞችም ኾነ በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ላይ ለውጦች ታይተዋል። በተለይም በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ

ዲሞክራሲያዊ ግንባር የፖለቲካ ሥርዓት ወቅት በራስ ባህል ላይ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ይተዳደር የነበረውን የራያን የሆታ ስልት በመበረዝ "እያያ አሚናት በለው፡ እያያ፣ እሽም እንደ ራያ" የሚሉትን የሆታ የዜማ ዓይነቶች የመከወን ኹኔታ አጋጥሟል። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል በማኅበረሰቡ ውስጥ የተለመዱት የክብረ በዓላትና የተበቺሳ የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች አሳማኝ ባልኾኑ ምክንያቶች እንዲቀሩ ተደርገዋል።

በሦስተኛ ደረጃ ለቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚዎች ለውጥ በምክንያትነት የተገለጸው የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሣሪያዎች በየአካባቢው በብዛት መሰራጨታቸው ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በተለያዩ የመከወኛ አጋጣሚዎች በግለሰቦች አንደበት ይከወኑ የነበሩትን የቃል ግጥም ዘፈኖች ከማዳመጥ ይልቅ በሙያተኞች የተቀነባበሩትን ባህላዊ ሙዚቃዎች በሞባይልና "ፍላሽ" በሚቀበል ቴፕ፣ በከተማዎች ደግሞ "ጂፓዝ" በተባሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማዳመጥ የተሻለ ነው የሚል ነው። አራተኛው ምክንያት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የኾኑ ሴትና ወንድ ወጣቶች እምነታቸውን አጠንክረው በመያዛቸው የተነሣ "ሃራም ነው" በማለት ወደተለያዩ የቃል ግጥም መከወኛ አካባቢዎች እንደማይኼዱ፣ ቢኼዱም እንኳን ዓለማዊ ዘፈኖችን እንደማይዘፍኑ፣ የሚፎክርና የሚያቅራራም እንደሌለ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። በመኾኑም እነዚህ የጎበረተሰብ ክፍሎች በራሳቸው የጋብቻ ዕለት እንኳን ቢኾን ሃይማኖታዊ የመወድስ ዜማዎች ይዜማሉ እንጂ ዓለማዊ ዘፈኖችን አይከውኑም። የመጨረሻው ደግሞ በዘመናዊነት መስፋፋትና በመደበኛ ትምህርት የተነሣ ቃል ግጥሞቹንም ኾነ የመከወኛ አጋጣሚዎቹን ኋላ ቀር አድርጎ የመመልከት ኹኔታ በወጣቶቹ ዘንድ ተስተውሏል።

በጥናቱ ውጤት መሠረት የቃል ግጥሞቹና የመከወኛ አጋጣሚዎቹ በተከታታይነት ቀጣይነት የሚኖራቸው አርሶ አደሮቹ ማዳበሪያን፣ ብስባሽን፣ ፀረ ዐረም ኬሚካልን እና የማሳ ላይ ዕርከን ሥራን ተጠቅመው የተትረፈረፈ ምርት ማምረት ከቻሉና እነዚህ ተግባራትም የማያቋርጡ ከኾኑ የውዳሴም ኾኑ ትችት አዘል ቃል ግጥሞች የመከወናቸው ኹኔታ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል መረዳት ተችሏል። ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚያገለግሉ ግብኣቶች በተጨማሪ አርሶ አደሩ በበሬዎች አማካይነት የእርሻ ሥራውን ያለማቋረጥ ሲያከናውን፤ እሾኽ፣ ብርድና ድካም ሳይበግረው ጠንክሮ ዐረሙን ሲያርም፣ ማጭድን ተጠቅሞ ሰብሉን በእጁ የማጨድ ተግባር ሲያከናውን፣ የታጨደውን እኽል በዐውድማ ላይ አድርጎ ሲወቃ፣ ወዘተ. ራሱንም ኾነ በሬዎቹን እያሞገስ፣ ሕጹጽ የኾኑ ድርጊቶችም ሲያጋጥሙት እየተቸ ቃል ግጥሞችን ቀጣይነት ባለው ኹኔታ የሚከውን መኾኑን መረዳት ይገባል።

ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ጋብቻ እስካለ ድረስ ሥርዓቱን ለማክበር በሚዘጋጀው ሰርግ የሚከወኑት የልጃገረዶች ዘፈን፣ የጎረምሳዎች ሆታ፣ ቀረርቶና ፉከራ ቀጣይነት ያላቸው መኾኑን መገንዘቡ ተገቢነት ይኖረዋል። በመጨረሻም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ከኾነው የማኅበረሰብ አባላት እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ እንደዚሁም ወንድምና እኅት በሚሞቱበት ዕለት በሚከወኑት የለቅሶ ሥርዓቶች የሙሾ ቃል ግጥሞች ያለማቋረጥ በተከታታይ የሚደረደሩ መኾኑን ጥናቱ አመላክቷል።

10.2. የይሁንታ ሐሳቦች

ቃል ግጥሞች ከትውልድ ወደትውልድ እንዲሸጋገሩና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፦

- ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎች ያለው ማኅበረሰብ የጋራ ሀብቱ ለኾኑትና የራሱንም ማንነት ለሚያሳዩለት ልዩ ልዩ ቃል ግጥሞች ክብር የመስጠት ኹኔታ እንዲፈጥር ቢደረግ፣ ለዚህ ተግባራዊነትም በመጀመሪያ እየሠራሁበት ላለው የወሎ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ጥናቱ ለተካኼደባቸው ወረዳዎች የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ሙያተኞች ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሉኝን የውሎ አበል፣ የመጓጓዣና የጽሕፈት መሣሪያ ወጪዎችን እንዲሸፍንልኝ ትብብር መጠየቅ፣ እነዚህ ወጪዎች ከተፈቀዱ በኋላ ለየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የባህል ዕሴት ሙያተኞች በመምሪያ የታገዘ ሥልጠና መስጠት፣ በመጨረሻም ሙያተኞቹ በወሰዱት ሥልጠና መሠረት ተገቢ የኾነ ትምህርት ለማኅበረሰቡ በመስጠት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ማድረግና ተግባራዊነቱንም መከታተል የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። ከዚህ ተጨማሪ በዓመት አንድ ጊዜ በየወረዳዎቹ “የባህል ቀን” ስለሚከበር የየወረዳዎቹ ኃላፊዎች ምቹ ኹኔታን እንድፈጥሩ ከተደረገ በኋላ የጥናቱን ዋና ዋና ክፍሎች በየበዓላቱ ዕለት ለታደመው የኅብረተሰብ ክፍል በማቅረብ የይሁንታ ሐሳቡን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል የሚል ዕሳቤ አለኝ።
- በተበቺሳ፣ በተለያዩ የማገዶ መልቀሚያ ቦታዎች፣ በዐረም ወቅቶች፣ በተለያዩ ክብረ በዓላትና በሰብል መጠበቂያ ቦታዎች ሲቀነቀኑ የነበሩትን የፍቅር ቃል ግጥሞች የባህል መዚቃ አቀናባሪዎች በሥራዎቻቸው ውስጥ በተግባር ላይ ቢያውሏቸው፣ ለዚህ ተግባር መሳካትም ኹለት አቅጣጫዎችን ማመላከት ተችሏል። አንደኛው ይህ ጥናት ለመጨረሻ ተቋቁሞ ከቀረበ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባለው ዲጂታል ቤተ መጻሕፍት ድረ ገጽ ላይ ከተጫነና በዩኒቨርሲቲው ሥር ባለው የያሬድ የመዚቃ

ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የጥናቱን ውጤት ሊያገኙት ከቻሉ የፍቅር ቃል ግጥሞቹን በሥራዎቻቸው ውስጥ መጠቀም እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል። ለሌሎች የባህል ሙዚቃ አቀናባሪዎችም መረጃዎችን ሊያቀብሉ ይችላሉ። ኹለተኛው ደግሞ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የሙዚቃ ትምህርት ክፍል ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛል። ስለዚህ ተማሪዎቹ ወደፊት ባለው የሕይወት ዘመናቸው የፍቅር ቃል ግጥሞችን በሥራዎቻቸው ውስጥ እንድጠቀሙባቸው ለትምህርት ክፍሉ አቅጣጫ ከተሰጠ ቃል ግጥሞቹን እና ዜማዎቹን ከለውጥ በመጠበቅ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል።

- በአማርኛ ቋንቋ የሚጽፉ የልቦለድ መጻሕፍትና የፊልም ደራስያን መቼታቸውን የገጠሩን ማኅበረሰብ የሚደርጉ ከኾነ በሚጽፏቸው ልቦለድ መጻሕፍትና ፊልሞች ውስጥ የሚፈጥሯቸው ገጸ ባሕርያት ምርታማነትን ለማሳደግ በሚውሉ ግብዓቶች፣ በተለያዩ የግብርና የሥራ ዓይነቶችና በሕይወት የሽግግር ሥርዓቶች ወቅት በማኅበረሰቡ በቃል የሚገጠሙትን ቃል ግጥሞች በአንደበታቸው እንዲናገሩ ቢያደርጉ፣ በዚህም ሥራዎቻቸው በአንባቢ ዘንድ ተወዳጅነትን ሊያተርፉላቸው ይችላሉ። ምክንያቱም አንባቢያኑ እነዚህን ገጸ ባህርያት በሕይወት ዘመናቸው የሚያውቋቸው አድርገው ሊመለከቷቸው ይችላሉ። ለዚህ ስኬትም ደራስያን ለሚጽፏቸው ልቦለድ መጻሕፍት ለመነሻ የሚኾኗቸውን ሐሳቦች ለማግኘት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ካሉት ቤተ መጻሕፍት መካከል የዚህ ጥናት የመጨረሻ ውጤት የሚገኝባቸውን የኬኔዲን፣ የዲጂታልን እና የኢትዮጵያ ጥናት ተቋምን ቤተ መጻሕፍት መቃኘታቸው አይቀርምና ነው።
- የትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች በየደረጃው ባሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ይዘቶችን እና ምንባቦችን ከልዩ ልዩ መጻሕፍት፣ ጋዜጣዎች፣ መጽሔቶችና የምርምር ውጤቶች በማጣቀሻነት የሚወስዱ መኾናቸው የሚታወቅ ነው። እነዚህን ማጣቀሻዎች ደግሞ በቀላሉ የሚያገኟቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ባሉ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው። ስለዚህ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የትምህርት ባለሙያዎች በተጠቀሱት ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይህንን ጥናት ስለሚያገኙት አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ቃል ግጥሞች በይዘትነት ቢያካትቱ፣ በክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራንም በሙያተኞቹ የተዘጋጁላቸውን የትምህርት መሣሪያዎች ተጠቅመው ቃል ግጥሞችን በይዘትነት ቢያስተምሩ፣ ተማሪዎቹም

በበኩላቸው በየመማሪያ መጻሕፍታቸው ውስጥ የቃል ግጥሞችን የሚያገኟቸው ከኾነ በእነሱ አማካይነት እየተዝናኑ ቋንቋውን ይማራሉ፤ ሳይረሷቸውም ለቀጣዩ ትውልድ በቀላሉ ሊያስተላልፏቸው ይችላሉ፡፡

- የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የቃል ግጥሞችን እንደ ቅርስ ለመመዝገብ፣ ለማቆየት እና ለማስተዋወቅ ጥናቱ ያግዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥሞቹ ቀጣይነት እንድኖራቸው ባህላዊ ገጣሚዎችን ለመደገፍና ወጣቶቹም እነዚህን የሕዝብ ሐብቶች እንዲማሩ መድረኮችን ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡

- የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ማንነት፣ ባህል፣ ወዘተ. ማጥናት የሚፈልጉ የታሪክ፣ የሥነ ማኅበረሰብ፣ የሥነ ልቡና፣ የሥነ ሰብ፣ የሥነ ልሣን እና የሥነ ቃል ተመራማሪዎች የቃል ግጥሞችን በመረጃ ምንጭነት ቢጠቀሙባቸው፣ ምክንያቱም ቃል ግጥሞች ያለፈውን ነገር ለማጥናት፣ ለማወቅ፣ የወደፊቱንም ለማቃናት ያገለግላሉና ነው፡፡ በተጨማሪም ቃል ግጥሞቹ ካለፈው ትውልድ አንሥቶ አሁን እስካለንበትም ድረስ ኾነ ወደፊት ቃላዊ በኾነ መንገድ የሚተላለፉ በመኾናቸው በኅብረተሰቡ ዘንድ የታሪክና የዕውቀት ማቆያ መዘክር ኾነው ሊያገለግሉ ስለሚችሉ ነው፡፡

ማጣቀሻ ጽሑፎች

ሀብታም ግዛት፡፡ (2006)፡፡ “የዳባት ወረዳ ገበሬዎች የሥራ ግጥሞች ክዋኔና ማኅበራዊ ሕይወታቸው፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፡፡

ለማ ንጋቱ፡፡ (2006)፡፡ “የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፡፡

መኮንን አስማማው፡፡ (2007)፡፡ “በደላንታ ወረዳ የአበሹቱ እና የቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር የአርት ማስተር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት፡፡

ማሞ ተፈራ፡፡ (2002)፡፡ “በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፡፡

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፡፡ (1978)፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሞላ መኮንን:: (1986):: “በቆቦ ወረዳ የተነገሩ ፖለቲካ ቀመስ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና” የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ ድ.ማ.ጽ፣ አ.አ.ዩ፡፡

ሞገስ ሚካኤል፡፡ (2002)፡፡ “በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካኼድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው፡፡” የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር፡፡

ሥዩም ተፈራ፡፡ (1999)፡፡ ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ፤ትምህርትና ልማት በኢትዮጵያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ርህቦት አሳታሚ ድርጅት፡፡

ስለሺ አባተ፡፡ (2008)፡፡ “የምንጃር ሸንኮራ ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ማኅበራዊ ፋይዳ፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፡፡

ሰይድ ይማም። (2002)። “በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ።” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድኅረ ምረቃ መርሓ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም. ኤ. ዲግሪ ለማግኘት የቀረበ ጥናት።

ቦረና ወረዳ አስተዳደር። (2000)። “የቦረና መካነ ሰላም ሚሊኒየም የልማት ባዛር።” መካነ ሰላም፣ (ያልታተመ)።

ኃይሉ አርኣያና ሌሎችም። (2009)። “የፌዴራል ግብርና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ለክልልና ወረዳ ባለሙያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ቴክኒካል ማኑዋል” አዳማ (ያልታተመ)።

ነጃሽ አሳታሚ ድርጅት። (1961)። ቅዱስ ቁርኣን። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አለም እሸቱ። (1992)። መሠረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ። አዲስ አበባ፣ ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊብራል አርትስ ፋኩልቲ።

አማረ ሞላ። (2009)። “የአማርኛ ቃል ግጥሞች ምደባ፣ ዐውዳዊ ትንተና እና ማኅበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ።” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ በፎክሎር የፒ.ኤች. ዲግሪ. ማሟያ ጥናት።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ። (2012)። “የ2012/2013 ምርት ዘመን የሰብል አመራረት ፓኬጅ።” ባሕርዳር (ያልታተመ)።

አስቴር ሙሉ። (2007)። “ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ።” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር።

አበራ ጀንበሬ። (1983)። አባ ኮስትር። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1993)። ኣማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። (1980)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዘፍጥረት። አዲስ አበባ።

እንድሪስ ይማም፡፡ (1997)፡፡ “የዛር ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በወግዲ ወረዳ፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡

ከለላ ወረዳ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት የ2012 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት፡፡

ካሳው ደሳለው፡፡ (1997)፡፡ “የደብረሲና ወረዳ የለቅሶ ሥርዓትና የሙሾ ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡” የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ ዲማጽ፣ አ.አ.ዩ፡፡

ክፍሌ ሙላት፡፡ (1980)፡፡ “ቦረና ቦረና ቦረና ገነቴ...”፣ አዲስ ዘመን፣ 46ኛ ዓመት፣ ቁጥር 714፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፡፡ “የወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲ”፤ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ ጥራዝ፡፡

የወግዲ ወረዳ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት፡፡ (2011)፡፡ “የወግዲ ወረዳ የልማት አጋሮች ፓናል ውይይት፡፡” ወግዲ ከተማ፡፡

ዋጋው ኃይሉ፡፡ (2001)፡፡ የአማራ ሕዝብና ቋንቋ፤ የአማራ ባህል ገጽታዎች፡፡ ባሕር ዳር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ የሥነ ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፣ 2012)::

ደብተራ ዘነብ (የአባት ስም ያልተጠቀሰ)፡፡ (1944)፡፡ መጽሐፈ ጨዋታ፡፡ ሥጋዊ፣ ወመንፈሳዊ፡፡ አዲስ አበባ፣ በመርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ያለው እንዳወቀ:: (1998):: የምርምር መሠረታዊ መርሖዎችና አተገባበር:: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች::

ይማም አብዱ፡፡ (2008) “ወግዲ ማኅደረ ታሪክ ከትላንት እስከ ዛሬ፡፡” ወግዲ (ያልታተመ)፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (1962)፡፡ ዐዲስ፣ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ደስታ ካሳ (1985)፡፡ ‹‹በደርግ መንግሥት ላይ የተገጠሙ ሥነ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና››፡፡ አ.አ.ዩ.፣ድ.ማ.ዕ፡፡

ጋሻው አሻግሬ። (2005)። “በእብናት ወረዳ ከባሀላዊ ወፍጮ ዐውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች።” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር።

ጌታቸው መኮንን ሐሰን። (1984)። ወሎ -‹‹ያገር ድባብ››። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ኅበና ጌታነህ። (1986)። “በወሎ ቦረና ‹የቆንጆ› ዘፈን ግጥሞች።” የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፣ ዲማጽ፣ አ.አ.ዩ።

ፈቃደ አዘዘ:: (1991):: የሥነ ቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች::

……። (1996)። ሰሚ ያጡ ድምፆች፣ አዲስ አበባ።

Abraham Melkie. (2007). “Thematic and Technical Analysis of Oral Poetry in and around Debre Tabor.” Addis Ababa University School of Graduate Studies Institute of Language Studies Department of Foreign Languages and Literature.

Alemmaya Mulugeta. (2002). Change and Continuity in Islamic Community; The Case of Muslim Women Statuses At Kamissie and its surrounding. School of Graduate Studies As partial fulfillment of the requirement for The Degree of Master of Arts in Social Anthropology Addis Ababa University.

Alembi, Ezekiel. (1995): Narrative Performance in a Changning World: the Case of the Story tellers in Kenya. A Research Paper Presented at the 11th Congress of the International Society For Folk Narrative Research in Mysore.

-------. (2002). ‘’The Construction of the Abanyole perceptions on Death through Oral Funeral Poetry.” Department of Helsinki University, Finland.

Amare Getahun. (1976). Some Common Medicinal and Poisonous Plants Used in Ethiopian Folk Medicine. Addis Ababa, Faculty of Science, Addis Ababa Univresity.

Ascher, William and John M. Heffron. (2010). Cultural Change and Persistence New Perspectives on Development. New York, Palgrave Macmillan.

Bascom, William. (1954). Four Functions of Folklore. The Journal of American Folklore, Vol.67, No. 266. pp. 333-349, Published by American Folklore Society.

--------. (1973). Folklore and Africanist. The Journal of American Folklore, Vol. 86, No. 341. PP. 253- 259.

Bauman, Richard. (1971). Differential Identity and the Social Base of Folklorre. The Journal of American Folklore, Vol. 84, No. 331, 31-41.

--------, (1975). Verbal Art as Performance. New Series, Vol. 77, No. 22, PP.290-311. Published by American Anthropological Association.

---------. (1977). Verbal Art as Performance. Rowley, Mass: Newbury House.

…….. (1983). "The Field Study of Folklore in Context" In A Hand Book of American Folklore. Dorson, Richard (Ed), pp.362-368; Bloomington, Indiana University Press.

------. (Ed). (1992). Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments. New york, Oxford University press.

Beakal Nigussie. (2010). "The Social Function of Amharic Folk poetry with Reference to SHÄNÄĈĈA in Rayya Qobbo." Addis Ababa University School of Graduate Studies Institute of Language Studies Department of Foreign Languages and Literature.

Ben-Amos, Dan. (1971). Toward a Definition of Folkore in Context. The Journal of American Folklore, Vol. 84, No. 331, Toward New Perspectives in Folklore, PP.3-15.

--------. (1993). ''Context'' in Context**.** Western Folklore Society,Vol.52, No. 2/4,pp. 209-226, Western States Folklore Society.

Berhanu Gebeyehu. (1998). “Islamic Oral Poetry in Wollo; A Preliminary Descriptive Analysis.” Addis Ababa University, A Thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Literature.

Best, J.W. (1981). Research in Education. New Delhi; Prentice Hall of India Private Limited.

Carol R. and Ember. (2009). Cross-Cultural Research Methods. (Second Edition). New York, ALTA Mira Press.

Danieal Legese (1998). ‹‹A Thematic Approach To Amharic Oral Poems Associted With the Derg Red Terror in Gonder and Gojam.›› School of Graduate Studies; M.A Thesis; AAU.

Donald A. (1972). “Field Work: Collecting Oral Literature.” In Richard M. Dorson (ed), Folklore and folk life: An Introduction. (pp. 407-430), Chicago and London; The University of Chicago Press.

Douglas, Paul. (2000). Folklore from the Grassroots. The Journal of American Folklore, Vol. 113, No. 447, pp. 83-86 American Folklore Society Stable URL: https://www.jstor.org/stable/541267 Accessed: 02-01-2019 06:21 UTC.

Dorson, Richard M. (ed.) (1972). Introduction: Concepts of Folklore and Folk Life Studies. London: University of Kentucky.

Dundes, A. (ed.). (1965), The Study of Folklore. Englewood Cliffs, N.J.:Prentice-Hall,

----------. (1980). Interpreting folklore, United States of America; Indiana university press,

---------. (2005). “Folkloristics in the Twenty- First Century.” The Journal of American Folklore; v.118 (407), pp.384-408: The Board of Trustees of the University Of Illinois.

-------. (2007). The Meaning of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dundes Book Editor(s): Simon J. Bronner. Logan, Utah; Utah state University Press.

Fife, Wayne. (2005). Doing Fieldwork Ethnographic Methods for Research in Developing Countries and Beyond. New York, Palgrave Macmillan.

Finnegan, Ruth.(1970). Oral Literature in Africa. Nairobi; Kenya; Oxford University press.

----------. (1970). A Note on Oral Tradition and Historical Evidence. History and Theory, Vol.9, No.2, PP. 195-201.

--------. (1974). How Oral is Oral Literature? Bulletin of the School of Oriental and African Studies, University of London, Vol. 37, No.1, In Memory of W.H. Whitely, PP. 52-64.

--------.(1977). Oral Poetry: Its Nature, Significance and social Context. London; Cambridge University Press.

---------.(1992). Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices. New York, Routledge Publishing Company.

--------.(2012). Oral Literature in Africa. (World Oral Literature Series: Volume 1). Cambridge, Open Book Publishers.

Flick, Uwe. (2006). An Introduction to Qualitative Research. (Third Edition), London, SAGE Publications Ltd.

Fukata,Azio.(1987).Fieldwork in Folklore Studies. Current Anthropology,Vol.28,No.4, Supplement: An Anthropological Profile of Japan, PP. 91 - 94).

Friedland, Roger and John Mohr (ed). (No Year, 71). Culture and Continuity: Casual Structures in Socio — Cultural Persistence. Cambrige University Press.

Getie Gelaye, (1999). *Contemporary Amharic Oral Poetryfrom Gojjam: Classification and a Sample Analysi*ń. Aethiopica. 2: 124-141.

…... (2002). *Text Analysis of Children's Songs in Amharic.* Aktuelle Forschungen in Afrikanische Sprachen. Cologne. Ruediger Koeppe Verlag. pp.291- 305.

……(2009). Amharic Praise Poems Related to Emperors Tewodros II and Yohannes IV. Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies Volume 4.

Goldstein, S. Kenneth. (1974). A Guide for Field Workers in Folklore. Pennysylvania: Gale Research Company.

Green, A. Thomas. (ed.) (1997). Folklore: an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.. Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England.

Gulevich, Tanya. (2004). Understanding Islam and Muslim Traditions: An Introduction to the religious practices, Celebrations,Festivals, Observances, Beliefs, Folklore, Customs, and Caleder System of the World's Muslim Communitities, Including an Overview of Islamic History and Geography. USA., Omnigraphics Inc.

Harris, Trudier. (1995). The Journal of American Folklore, Vol. 108, No. 430, Common Ground; Keywords for the Study of Expressie Culture, pp. 509 — 527.

Http://www.lionswhiskers.com/p/six-types-of-courage.html.

Hufford, Mary. (1995). Context. The Journal of American Folklore, Vol.108, No. 430, PP. 528-549. Common Ground: Keywords for the Study of Expressive Culture,

Hussen Adal Mohammed. (2014). ''Plant Diversity and Ethno Botany of Borena Sayint National Park, Northern Ethiopia.'' Unpuplished Doctoral Dissertation.

Addis Ababa University, The Department of Plant Biology and Biodiversity Management.

Hymes, Dell. (1971). The Contribution of Folkore to Sciolinguistic Research. The Journal of American Folklore, Vol. 84, No. 331, PP. 42-50.

Inglehart, Ronald and Christian Welzel. (2005). Modernization,Cultural Change, and Democracy: The Human Development Sequence. New York, Cambridge University press.

Jackson, Bruce (1987). Field Works. Chicago; Urbaana; University of Illinois Press.

Joyner, Charles W. (1975). A Model for the Analysis of Folklore Performance in Historical Context. The Journal of American Folklore, Vol. 88, No. 349,PP. 254-265.

Kabira, W. and Mutahi, K. (1988). Gikuyu Oral Literature. Nairobi.

Kothari, C.R. (2004). Research Methodology Methods and Techniques. (Second Revised Edition). New Delhi,New Age International Private Ltd. Publishers.

Leslau, Wolf and Thomas L.Kane. (2001). Amharic Cultural Reader. Harrassowitz, wIesbaden.

Marshal, C. & Rossman, G. (2006). Designing Qualitative Research. United States of America: (4th Ed.). Saga Publication Inc.

Maykut, P. & More, House (1994). Beginning Qualitative Research a Philosophic and Practical Guide. London, Washington D.C: The Flamer Press.

Mesfin Messele. (2000). ‘’Abbawudde Oral Poetry in South Wollo: A Descriptive Analysis.’’ A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Literature.

Miruka, O. (1994). Encounter with Oral Literature. Nairobi.

Morris, Tracie and Jean “Binta” Breeze. (2004). Oral Poetry and Performance in Black Culture. University of Ca’Foscari Venezia.

Mouton, Johann & H.C Marais. (1988). Basic Concepts in the Methodology of the Social Sciences. Pretoria; South Africa, HSRC Publishers.

Myrvold, Kristina. (2008). Inside the Guru's Gate: Ritual Uses of Texts Among the Sikhs in Varanasi, Lund, Sweden; Lund University.

Okpewho, Isidore. (ed.). (1985). The Heritage of African Poetry. London, Longman.

----------. (1992). African Oral Literature: Background, Character, and Continuity. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.

Olajubu, O. (1978). The Yoruba Verbal Artist and His Work. In Journal of American Folklore 360 .

Oring, Elliott. (1976). Three Functions of Folklore: Traditional Functionalism as Explanation in Folkloristics. The Journal of American Folklore Society, Vol. 89, No. 351. PP. 67-80.

----------. (1991). On the Future of American Folklore Studies: Current Problems and Future: Prospects in American Folklore Studies. Vol. 50, No. 1, pp. 75-81: Published by: Western States Folklore Society.

Peek, M. Philip, and Kwesi Yankah. (ed). (2004). African Folklore: And Encyclopedia. New York, London, Routledge 29 West 35th Street. Quick, Catherine S. Ethnopoetics. Folklore Forum 30: 1/2 (1999).

Perecman, Ellen and Sara R. Curran. (eds.) (2006). A Handbook for Social Science Field Research Essays & Bibliographic Sources on Research Design and Methods. London; Sage Publications Ltd.

Salamone, Frank A. (Ed.) (2004). Encyclopedia of Religious Rites, Rituals and Festivals. New York, London; published by Routledge.

Schensul, Jean J. (ed). (1999). Enhanced Ethnographic Methods. New York, Altamira Press.

Seifu Metaferia, (1982), *Oral Literature of Ethiopia as a Source of Material for Children's Books: sample study,* Addis Ababa, The National Children's Commission and Italian Cultural Institute

Shebeshi Lemma.(1986)." A Thematic Approach to Famine-Inspired Amharic Oral Poetry;AAU;School of Graduate Studies.

Sims, C. Martha and Stephen, Martine. (2005). Living Folrlore: An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan; Utah state University Press.

Strasser, Hermann. (1977). Functionalism and Social Change. Vienna, Institute for Advanced Studies.

UNESCO. (1998). UNESCO - WIPO World Forum — on the Protection of Folklore — Thailand, Bildangentu, A.g.

Vansina, Jan. (1985). Oral Tradition as History. London, The University of Wisconsin Press.

Vanderstoep, Scott W. and Deirdre D. Johnston. (2009). Research Methods for Everyday Life: Blending Qualitative and Quantitative Approaches. USA, Jossey-Bass.

Zelalem Zewudie. (2010). ‹‹Thematic Analysis of Amharic Oral Lyric Poetry of West Gojam Zone.›› Addis Ababa University School of Graduate Studies Institute of Language Studies Department of Foreign Languages and Literature.

አባሪዎች

አባሪ አንድ፡- የመረጃ ሰጪዎች አጭር ግለ ታሪክ

ተ.ቁ	የመረጃ ሰጪው ስም	ጾታ	ዕድሜ	መረጃው የተሰበሰበበት ቀበሌ	መረጃው የተሰበሰበበት ቀን
1	አቶ ይመር አሰን	ወ	30	ቦረና ወረዳ ከቶ ቀበሌ	20/05/2012
2	፱ አለቃ አድማሱ ከበደ	ወ	74	ቦረና ወረዳ ከቶ ቀበሌ	20/05/2012
3	አቶ መ.ሐመድ ይማም	ወ	28	ቦረና ወረዳ ከቶ ቀበሌ	20/05/2012
4	አቶ ምትኩ አገኘሁ	ወ	76	ቦረና ወረዳ ከቶ ቀበሌ	21/04/2013
5	አቶ በለጠ አደላ	ወ	25	ቦረና ወረዳ ከቶ ቀበሌ	22/05/2012
6	ወ/ሮ ሰሚራ ጌቶ	ሴ	29	ቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ	21/05/2012
7	አቶ መ.ሐመድ እንድሬ	ወ	35	ቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ	23/05/2012
8	ወ/ሮ ፈንታነሽ አብዱ	ሴ	35	ቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ	20/05/2012
9	አቶ አካሉ ወደደኝ	ወ	27	ቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ	21/05/2012
10	አቶ ወንደወሰን ታረቀኝ	ወ	22	ቦረና ወረዳ ቀያፈር ቀበሌ	22/05/2012)
11	ወ/ሮ ገንዘቤ በለጠ	ሴ	26	ቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ	20/05/2012
12	ወ/ሮ ዘይነባ ይማም	ሴ	32	ቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ	23/05/2012
13	አቶ ፈቃዱ ጤናው	ወ	24	ቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ	22/05/2012
14	ወ/ሮ ሐዋ የሱፍ	ሴ	39	ቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ	23/05/2012
15	ጌታቸው እብሬ	ወ	34	ቦረና ወረዳ ዋላ ቀበሌ	02/06/2012
16	አቶ መ.ሐመድ እንድሬ	ወ	37	ወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ	22/05/12
17	አቶ በፈቃዱ ጤናው	ወ	31	ወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ	22/05/2012
18	ወ/ሮ ብርቱካን ጫኔ	ሴ	28	ወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ	22/05/2012
19	አቶ እንዳልካቸው ግዛው	ወ	37	ወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ	07/06/2013

20	አቶ ይማም አብዱ	ወ	32	ወግዲ ወረዳ ሰቀ ሸንብራ ቀበሌ	22/05/2012
21	አቶ አባተ ወርቅነህ	ወ	37	ወግዲ ወረዳ ሌንጮ ቀበሌ	07/062013
22	ወ/ሮ ኩብራ መላኩ	ሴ	28	ወግዲ ወረዳ ሌንጮ ቀበሌ	10/07/2013
23	አቶ ታለማ ዳኜ	ወ	30	ወግዲ ወረዳ ሌንጮ ቀበሌ	10/07/2013
24	አቶ አብዱ ሙሐመድ	ወ	45	ወግዲ ወረዳ ሌንጮ ቀበሌ	22/05/2012
25	ወንድወሰን ታረቀኝ	ወ	29	ወግዲ ወረዳ ሌንጮ ቀበሌ	22/05/2012
26	አቶ ማርቆስ መክብብ	ወ	39	ወግዲ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ	22/05/2012
27	ወ/ሮ አየሉ ከማል	ሴ	35	ወግዲ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ	23/05/2012
28	ወ/ሮ ሀውለት ሙሐመድ	ሴ	25	ወግዲ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ	07/01/2013
29	ወ/ሮ ዘይነባ አህመድ	ሴ	22	ወግዲ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ	07/01/2013
30	አቶ አረጋ አሰፋ	ወ	67	ወግዲ ወረዳ ሮቢት ቀበሌ	23/05/2012
31	አቶ አህመድ ጀማል	ወ	53	ከለላ ወረዳ ሰንቦ ቀበሌ	02/07/2012
32	አቶ አራጋው ሀሰን	ወ	65	ከለላ ወረዳ ሰንቦ ቀበሌ	05/07/2012
33	ወ/ሮ ራህመት ሙሐመድ	ሴ	35	ከለላ ወረዳ ሰንቦ ቀበሌ	04/07/2012
34	ወ/ሮ ዘይነባ ይማም	ሴ	39	ከለላ ወረዳ ሰንቦ ቀበሌ	03/07/2012
35	አቶ ዘበነ አሰፋ	ወ	36	ከለላ ወረዳ ሰንቦ ቀበሌ	04/07/2012
36	ወ/ሮ ሐዋ የሱፍ	ሴ	31	ከለላ ወረዳ እንዶዴ ቀበሌ	03/072012
37	አቶ አማን ሁሴን	ወ	29	ከለላ ወረዳ እንዶዴ ቀበሌ	04/11//2012
38	አቶ ሙህዬ ሁሴን	ወ	33	ከለላ ወረዳ እንዶዴ ቀበሌ	04/11//2012
39	አቶ ሙራድ ገበየሁ	ወ	37	ከለላ ወረዳ እንዶዴ ቀበሌ	02/07/2012
40	አቶ ሙሐመድ ኑርሁሴን	ወ	32	ከለላ ወረዳ እንዶዴ ቀበሌ	02/07/2012
41	አቶ መንግሥቱ አበራ	ወ	67	ከለላ ወረዳ ጉቢሳ ቀበሌ	02/07/2012
42	አቶ ሐሚድ አሸብር	ወ	47	ከለላ ወረዳ ጉቢሳ ቀበሌ	03/07/2012
43	ወ/ሮ ዘቢባ ጥላሁን	ሴ	28	ከለላ ወረዳ ጉቢሳ ቀበሌ	03/07/2012

44	ወ/ሮ መሬማ አረጋ	ሴ	43	ከለላ ወረዳ ጉቢሳ ቀበሌ	03/07/2012
45	ወ/ሮ ሐዋ እንድሪስ	ሴ	38	ከለላ ወረዳ ጉቢሳ ቀበሌ	04/07/2012
46	አቶ ኃይሉ ታደሰ	ወ	58	ደቡብ ወሎ ባህልና ቱሪዝም የባህል አሴት ባለሙያ	18/05/2012
47	አቶ ሰይድ ጎቸል	ወ	30	የቦረና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም የባህል አሴት ባለሙያ	02/06/2012
48	ዓይናለም በፀና	ሴ	29	የወግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም የባህል አሴት ባለሙያ	22/05/2012
49	ወ/ሮ ከረን ሐሰን	ሴ	28	ከለላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም የባህል አሴት ባለሙያ	04/07/2012

አባሪ ሁለት፡- ከመስክ ተሰብስበው ያልተተነተኑ ቃል ግጥሞች

1.ማዳበሪያን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1.1. በኑሮ ላይ ለውጥን ለማምጣትን /መሻሻልን/ በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ማሽላ ብዘራ ቂጥኝ ይበላዋል
   ስንዴንም ብዘራ መስክ ይበላዋል
   ማዳበሪያ መጥቶ ፍሬ ያደርገዋል፡፡

2. እንሻሻል ካሉ ሰዎች ካሰቡት
   ማዳበሪያ አውጥቶ ምርጥ ዘር መዝራት፡፡
3. የማዳበሪያን ጥቅም በውል የተረዳ
   ከራሱም አልፎ ለወገኑ ረዳ፡፡
4. ህዝባችን ተሰድዶ ካገሩ ሲወጣ
   እግዜር መለኛ ነው ማዳበሪያ አመጣ፡፡

5. ገበሬን ከችግር የገላገለው
   ዘመኑ ያፈራው ማዳበሪያ ነው፡፡
6. አዝመራችን አምሮ እንዲለቅ ድህነት
   ማዳበሪያ አመጣ ይህ ፀሐይ መንግሥት፡፡
7. እንዴት ያለ መንግሥት ዕድሉ የወጣ
   ማዳበሪያ የሚባል ቅመምን አመጣ፡፡
8. ለማዳበሪያውማ ምስጋና ያንሰዋል
   ድህነትን ቀርፎ ሀብታም አድርጎናል፡፡
9. ጥበብ ነሽ ድንቅ ነሽ ኢትዮጵያ ሀገሬ

ኮሞፖስት አዘጋጅተሽ ታፈሪያለሽ ፍሬ።
10. ቦረሌውን መሬት ስንዴ እናብቅልበት
ማዳበሪያ አውጥተን እንነስንስበት።
11. ገበያ ቢጠግብ በማዳበሪያ ነው
ጎተራም ቢሞላ በማዳበሪያ ነው
ያለ ማዳበሪያ የሚጠግበው ማን ነው።
12. ማዳበሪያ ማለት ልዩ ነው ድንቅ ነው
የጠፋውን ሰብል የተካው እሱ ነው።
13. ችግር ባገሩ ላይ እየገሰገሰ
ማዳበሪያ መጥቶ ስንዴን አሳፈሰ።
14. እርዳታ አለ ብሎ ከመንከራተት
ማዳበሪያ አውጥቶ ስንዴ ነው መዝራት።
15. ማዳበሪያ መጣ እኛ ሀገር ደረሰ
ከማይረባ መሬት ምርትን አሳፈሰ።
16. ይሄ ማዳበሪያ እንዴት ያስደንቃል
ከማይረባ መሬት ምርትን ያሳፍሳል።
17. ማዳበሪያ ዘርቶ ጥቅሙን ያላወቀ
ምርቱን ባየ ጊዜ ደንግጦ ወደቀ።
18. ይህን ማዳበሪያ ላላየ አሳየው
እንኳን ክምሩና ያምራል ቡቃያው።
19. ማዳበሪያ ያላወጣ ያልተጠቀመ ሰው
ምርትም አያገኝ መነሻም የለው።
20. አሁን አያችሁ ወይ የዳፕን ውለታ
ስንዴውን በጎተራ ጤፉንም በጎታ።
21. ቆጋ መሬት የሚል አሁን የት ተገኝቶ
ፈረፈሩን መሬት በግሎባል ስንዴ ጎተራውን ሞልቶ።

1.2. ተስፋ አዘል ቃል ግጥሞች

1. የታባቱ ችግር መድረሻ ሲያሳጣኝ
ማዳበሪያ መጣ ጤፍን ሊያሳፍሰኝ።
2. ይሄ ማዳበሪያ ሽጋ ሰው ሽጋ ሰው
አንተ ካለህልኝ መሬቱን ልረሰው።
3. ጤፍ ዝሩ ጤፍ ዝሩ ማዳበሪያ አድርጋችሁ
መሬቱ ለክርሞ እንዲወጣላችሁ።
4. ስጠኝ ማዳበሪያ ቢሆንም የዱቤ
ችግሬን ላስወግድ በዱላ ደብድቤ
5. መሬትክን አለስልስ ዝራ በማዳበሪያ
ችግርን ለመጣል እንደማዳወሪያ።
6. አዝመራው እምቢ አለ ያለ ማዳበሪያ
ልገዛ ልሄድ ነው ዳፕና ዩሪያ።

1.3. ለችግር መጋለጥን የሚያመለክቱ ቃል ግጥሞች

1. ዩሪያ ማዳበሪያ ተፋሰስ ከመጣ
እንኳንስ መሬቱ ሰው ሁሉ ገረጣ።
2. ማዳበሪያ የሚሉት ሰውን በረበረ
እህሉን ሲወቁት አመድ ሆኖ ቀረ።
3. ማዳበሪያ መጥቶ የውጭ ሀገር መርዝ
መሬቱም አፈራ አዳዲስ ነቀዝ።
4. የድሮውማ አፈር ይሰጥ ነበር ምርት ይሰጥ ነበር ነዶ
ማዳበሪያ መጥቶ አደረገው ባዶ።
5. ገበያ ሲሄዱ በጧት በማለዳ
ገበሬው ተይሂል በማዳበሪያ ዕዳ።
6. በጥዋቱ ተነስቶ ገበያ ሊነዳ
ገበሬው ተይሂል በማዳበሪያ ዕዳ።
7. ማዳበሪያ የሚባል አስቸጋሪ መጥቶ
በሬዬን አሸጠኝ ያውም ለአራት መቶ።
8. ላሚቱም ተሸጠች ሙክቱም ተነዳ
አላስቀምጥ ቢለኝ የማዳበሪያ እዳ።

2. በኮምፖስት (በብስባሽ) ዙሪያ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

2.1 ምርት መጨመርን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ጥበብ ነሽ ድንቅ ነሽ ኢትዮጵያ ሀገሬ
ኮምፖስት አዘጋጅተሽ ታፈሪያለሽ ፍሬ።

2. ኢትዮጵያ ሀገሬ አቤት ማስደሰቷ
ኮምፖስት አዘጋጅታ ለፍሬ መብቃቷ።
3. አንቺ ውድ ሀገሬ በጣም ታምሪያለሽ
ከጋራው ሲዘልቁ ሳር ልምላሜሽ
ኮምፖስት አዘጋጅተሽ ምርታማ እየሆንሽ።

4. ኮምፖስት ጥሩ ነገር ጥቅሙን ላወቀ ሰው
እህሉንም አዳብሮ ምርቱን አሳፈሰው።
5. አያችሁለት ወይ የፍግን ውለታ
በቆሎው ሲዳብር ሲመቼው መኝታ።
6. ኮምፖስቴን አፍስሼ እቤቴ ስገባ
እህል አሳፈሰኝ ያው እንደገለባ።
7. መሬቱ ተራቁቶ ማብቀል አቅቶት
አይ ቴክኖሎጂ መጣልኝ ኮምፖስት።
8. ኮምፖስት አዘጋጅቶ የዘራ ገበሬ
አመረተ ስንዴ ገለባም ለበሬ።
9. እኔ በማረሱ አንች በኮምፖስትሽ
እናመርተዋለን ምንም አይጭነቅሽ።
10. አፈሩ ተሟጦ እህል ማብቀል አቅቶት

መንግሥት መለኛ ነው አመጣልን ኮምፖስት።።

2.2. ምክር አዘል ቃል ግጥሞች

1. አይሏችሁ ወጣቶች ኮምፖስት አዘጋጁ
ምርታማ ለመሆን አሁኑ ዝግጁ።።
2. ማዳበሪያ አነሰ እያሉ ከመኖር
እርጥበቱ ሳይደርቅ ኮምፖስትን እንቅበር።።
3. ፍግና በጠጡ ያለ አግባብ አይውደቅ
የኮምፖስትን ጥቅም ሁላችን እንወቅ፡
4. የባለሙያን ምክር አምኖ በመቀበል
ኮምፖስት በማዘጋጀት ድህነትን እንበቀል።።
5. ኮምፖስት እንጠቀም መላው ከኛው ነው
ገንዘቡ ተወዷል የማዳበሪያው።።

3. በፀረ አረም ላይ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

3.1. ሙገሳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. አቤት ቴክኖሎጂ በጣም ረቀቀ
ፀረ አረም አምጥቶ ካረም አላቀቀ።።
2.. ኧረ ቴክኖሎጂ በጣም ተሻሻለ
ፀረ አረም አምጥቶ ቡቃያ አሳመረ።።
3. ፀረ አረም መጣልን ነጭ የደም ሴላችን
የአረም ወታደር እንቁ ተዋጊያችን።።
4. እንታገል ነበር በእጅ ልናጠፋ
ፀረ አረም ኬሚካል መጣ ያ ቀልጣፋ።።
5. እህላችን ሊወድም ሊጠፋ ከሥሩ
ፀረ አረም መጣልን ከነሥራ ሥሩ።።
6. መንግሥትን ያቆየው ፀረ አረም ሲያመጣ
ጤፌን አጭጃለሁ አረም ሳያወጣ።።
7. አባቴና እናቴ አትልፉ ቀን ከሌት
እንጠቀማለን ፀረ አረም መድሃኒት።።
8. ቁጭ ብዬ ስንፏቀቅ ቀኑን እቆጥራለሁ
ፀረ-አረም መጣልኝ ተገላግያለሁ
በውርጭ በጤዛ መነከር ትቻለሁ።።
9. እኔም ብቻ አይደለሁ ቤተሰቡም አርፏል
አረምን ከተውነው ብዙ ጊዜ ሆኗል።።
10. የፀረ አረም መድሃኒት ከመጣ
እህሉ ካረም ዳነ ከተባይ አፍ ወጣ፡

4. በዕርከን ሥራ ላይ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

4.1 ምክር አዘል ቃል ግጥሞች

1. የተራቆተው ዳገት እንዲያገግም
እርከን እንሥራለት ጎበዝ እንዳንለግም።
ስምህ ባገር ባህል ይጻፋል ዘላለም።
2. መሬቱ በውሃ ተጎድቶ ከማየት
እርከንን መሥራት ነው ተባብሮ ባንድነት።
3. አካፋም ተሸከም ዶማውንም እንዳትተው
አገሬውን ሁሉ አንድ ላይ ቀስቅሰው።

4. ሀገሬው ተነሳ እርከንህን ሥራ
በጎርፍ የተነሳ ይመጣል መከራ።
5. ቡድኑ ጥሪው ይድረሳቸው
ሁሉም ይደርሳሉ ለየግል ሥራቸው።

4.2 ሙገሳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. መሬቱ ተፍቆ ውሃ ሸርሽሮት
እርከን ሥሩ መጣ እንዲህ ያለ ልማት።
2. የተፋሰስ ልማት እኒህ ጠቢባን
አፈር ለማስቀረት እንሥራ አሉ እርከን።
3. መሬትን አጣጥቦ ውሃ ሲበላው
በርከን ተመለሰ ሙያ ደግ ነው።
4. አሁን አያችሁ ወይ የእርከንን ጥቅም
ውሃ አይበላውም እስከ ዘላለም።

5. አጨዳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

5.1 ታታሪነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ሄደ ነጎደ ሄደ ወረደ
ማጭዱ እንደ እሳት እየነደደ
የቆመውን ጤፍ እየጎመደ።
2. ማጭዱ ቦራ ልጁ ብርብራ
ማን ተወዳድሮ ከአጅሬ ጋራ።
3. አጨዳ የምናውቅብሽ
ትተንሽ ነበር ተነሳንብሽ።
4. አጫጅና አጫጅ ይፎካከራል
ማጭዱ ከፊት ይመሰክራል።
5. የጎበዝ ማጭድ ታስታውቃለች
እንደ ሀዘንተኛ ፊቷን በልታለች
ራሷን ታማ ፊቷን ነጭታለች።
6. እንዴት ያለ ገበሬ ተሰማርቀ/አ/ቶበታል
ጠቅሎ ጠቅሎ ነዶ ብቻ አድርጎታል።

7. ካልቤኑ ጋራ አለው መሃላ
ከእጁ ላይለይ ክንዱ ሳይላላ።።

5.2 ሙገሳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. አልቤን ሽው ሽው አልቤን ሽው ሽው
በሰማኒያ ብር የተገዛሺው
በመቶ ሃምሳ ብር የተገዛሺው
የእኔን ምርጥ ዘር ቆርጠሽ ጨረሺው።።
2. አንቺ ማጭዴ እንሂድ ደቦ
አበላሻለሁ ዓይን ያለው ዳቦ።።
3. ከጅል ማጭድ ጋር ከመላቀስ
ሀልቤኑን ገዝቶ ልብ ነው ማድረስ።።
4. ያጨዳው ንዳድ ያጨዳው ንዳድ
አይለውጥም ስንዴ በንክርዳድ።።
5. ማጭዱ ሲቆርጥ ሲመስል ማሽን
አዬ ማስደሰቱ ገበሬው በእውን።።
6. ካልቤኑ ጋራ አለው መሃላ
ከእጁ ላይለይ ክንዱ ሳይላላ።።

5.3 ምክርን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. መኸር ነው ጎበዝ እህል እንጨድ
በረዶ ሲጥል እንዳንሰደድ።።

2. ጤፎ ላይ በይ እግርሽን
እንዳትቆረጭ ጭንቅላትሽን።።
3. ልንገራት እኔስ ለአልቤኔ መላ
እየቆረጠች እንዲትበላ።።
4. እንጨድ አዝመራ እንሸክፍ በወቅቱ
አቅማችን ሳይደክም ሳይበላብን ከብቱ።።
5. አጨዳ ማጨድ በጧት ወጥቶ ነው
ተረፈደማ ጸሀዩ እዳ ነው።።
6. ማጨድ ነው እንጂ ሰኞ ገስግሶ
አንተ ያገር ልጅ ከማለት ደርሶ።።
7. ማጨድ ነው እንጂ ጠርጎ ከሥሩ
እህል ላይገኝ ማሳ ቢጭሩ።።

5.6 ርካታን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. የአልቤኑ መስላት የእህሉ ማማር
አይሰለቸኝም ስቆርጠው ባድር።።
2. የአጨዳው ሞረድ የእንኩቶው ንዳድ

አያስመርጥም ስንዴ ከእንክርዳድ፡፡

3. የአይናሚት ወዳጅ የአልቤኑ ዳኛ
ጤፍ እንደ ድርቆ አጭዶ የሚያስተኛ፡፡

4. አይ ደስ ማለቱ ያጨዳው ወራት
ክምሩን ከምሮ ዞር ብለው ሲያዩት፡፡

6. የተበቺሳ ቃል ግጥሞች

6.1 የከንፈር ወዳጅን በተመለከተ አዝማቾች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ደሴ አለ አሉ ገና
በለጋው ደመና፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ሽጋው ባንተ ላይ ይደረባል ወይ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ሽጌ እንደ ሽመሉ
ሞት አይፈራም አሉ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የወዲያ ማዶው
ዘሚል ጎፈሬው፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የሽጉ ሽመል
የለም ወይ ባገር፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
በሳር በለምለሙ
ብቅ በል ዓይናሙ፡፡
አያ በለው በለው ሎምዬ
እረ ነይ ነይ
በደመናው ላይ
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እያረበረበ
ደጋ ላይ ዘነበ፡፡
አያ በለው በለው ሎምዬ ኧረ በለው በለው
ሽጉ አትመጣም ወይ
ቀረህ አይደለም ወይ
ቅርብ አይደለም ወይ፡፡
አያ በለው በለው እረ በለው በለው
አላፈራም ወይ የዓባይ ዳር እንኮይ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
አላበበም ወይ የዓባይ ዳር እንኮይ፡፡
ወፌ ይላላ ላላዬ
ነይ ነይ ደማማዬ፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የሽመሌው ነኝ ፈሪው አትንካኝ፡፡
የኔ ውብ ዓይናማ የኔ ውብ ታምር
የሚመጣው ዘመን ወተትና ማር

አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የእኔ አያሌው በሽር በለው በምንሽር፡፡

አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
አያሌው ዘገዬ ያንተን ጉድ ያላየ፡፡

በሸዋ ላይ ደሴ ታቹን በቦረና
ዓለም መጣች ገና፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ዓይኔ ዞሮ ዞሮ ጉድ አየ ዘንድሮ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ሸጌ እንደ ሽመሉ ሞት አይፈራም አሉ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ደራ ነው አገሩ ያበራል ዝናሩ፡፡

አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ጎፈሬው በላይ የጠይም አታላይ፡፡

አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የሸጉ ጎፈሬ ይለውጣል በሬ፡፡

አሸከርዋዬ ነይ አሸከርዋዬ ነይ
እዋበባዬ ነሽ እዋበባ

6.2. ውበትን ማድነቅ በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ብቅ በይ በሉልኝ የሸጉን እናት

የራሷ ወለባ የእጇ ቀለበት
ሲያበራ ይውላል እንደ መስተዋት፡፡
የሰማይ ስባሪ እሷ ቤት ይገኛል
የኛ መገናኛ ምናብ ይመስለኛል፡፡
ከኣባይ ወዳ ማዶ አባይ የለም ወይ
ሞትና መለየት አንድ አይደለም ወይ፡፡
እረብ እረብ ነው የግራር አጥር
መልኩ ሸሞንሚና ቁመቱ ቢያጥር፡፡

2. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ጨረቃይቱ ድመቂላቸው
እነ ሸግዬ ደረባ ናቸው
ማታ ሲመጡ እንዲታያቸው፡፡
እንጨት እሰብራለሁ እንጨቴ አረንጓዴ
ወፍ እጠብቃለሁ ወንበዴ ወንበዴ
የበላውን ይብላ አትጨነቅ ሆዴ፡፡
እንጨት እሰብራለሁ እንጨት መሳራባ
ወለል ብሎ ታዬ የሸጉ ደረባ፡፡
የሸጉ ደረባ ተለቅልቋል በበት
ጎፈሬው ይመስላል ንብ የሰፈረበት፡፡
እንጨት እሰብራለሁ እንጨተ ክትክታ
አላያችሁም ወይ ነጭ ባለ ኩታ፡፡
የደሴ ቆርቆሮ እባብ ያንሻልላል
ያንተ ልብ እንዴት ነው የኔስ ይዋልላል፡፡
እዩት እዛ ማዶ ይካባል ይናዳል
ውርጋጥ ተቀምጦ ሽማግሌ ያብዳል፡፡
አንተ ሽማግሌ ምን ያሳብደሃል
ፍቅር እንደሆነ ገደል ይሰደሃል፡፡

3. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ጨረቃ ቢወጣ የነጋ መስሎኝ
አውላላ ሜዳ ላይ ጅብ አቆራረጠኝ፡፡
ኧረ ጅቡ ጅቡ አታቆራርጠኝ
ካገሬ ወጥቼ ከሰው አገር ነኝ፡፡
መገን የሰው አገር መገን የሰው ቦታ
ተከለከለ አሉ ሳቅና ጨዋታ፡፡
ሳቅ አይከልከል ጥርስም አይከልከል
ሂጂ አይቼው መጣሁ አረዳው መካከል፡፡
ከምንጩ ልጠጣ ከሚቀዘቅዘው
መቼም አይጠገብ ውሃና ጠይም ሰው፡፡
ኧረ ጠይም ጠይም ምን አሳመራችሁ
የወተት አረፋ ይመስላል ጥርሳችሁ፡፡
ውሃ ቦይ ለቦይ ውሃ ቦይ ለቦይ
ያሳደጉት ውሻ ይናከሳል ወይ፡፡
ያሳደጉት ውሻ ወትሮም ይናከሳል
አመሉ ነው እንጂ መልኩ ከማን ያንሳል፡፡
ከላይ ቤት ከታች ቤት ማለቱን ተውና
እግርህን ታጠበው ውሃ ወዝትና፡፡
የድንጋይ ሥር ውሃ ይረጫል በፍኝ

ምነው ባላየሁህ በቀረህብኝ፡፡

4. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
የግራር አጥር የግራር አጥር

መልኩ ሸሞንሟና ቁመቱ ቢያጥር፡፡
እኔ ለቁመናው አልጎዳበትም
አሁን ተነስቼ እሄዳለሁ የትም፡፡
እሄዳለሁ የትም አልፋለሁ ቦረና
የተናገሩኝን ያሉኝን ልሰማ፡፡
የተናገሩኝን ያሉኝን ሰምቼ
ሀገሬ እገባለሁ አዋጅን ሰምቼ፡፡
አዋጅ ታወጀ አሉ ትላንትና ሐሙስ
ነጋዴም ይነግድ ገበሬም ይረስ
ውርጋጥና ቆንጆ ፍቅሩን ይጨርስ፡፡

ጉድ አለ ቦረና ጉድ አለ ሳይንቱ

ዘመም ዘመም አለ ሊፈርስ ነው ቤቱ፡፡
ቢሻው ቤቱ ይፍረስ ጥማዴ ይፈታ
አንተ አይደለህም ወይ የልቤ በሽታ፡፡
የልቤ በሽታ የልቤ ኩራቱ
ይወለድ የለም ወይ ሽጋ በየቤቱ፡፡
ሽጋ የወለደ ዘሩ ሽጋ ይሁን
ጧት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን፡፡

5. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ጨረቃይቱ ድመቂላቸው
እነ ሸግዬ ደረባ ናቸው፡፡
ከብቶቹን ሲያልቡ እንዲታያቸው
ዘፈን ሲሄዱ እንዲታያቸው፡፡
ኧረ ባባትዬ ባዲሱ ፍቅራችን
ሁለት ጤፍ እንጀራ ይብቃን እራታችን፡፡
ሁለት ጤፍ እንጀራ በስሱ ጋግራችሁ
ሸረላ በሉልኝ ቀኝ እጁን ይዛችሁ፡፡
መቼም የኮራ ነው አያናግራችሁ
ባይንና በጥርሱ ትለዩታላችሁ፡፡
ፍየል መንታ ወልዳ ይታረዳል አንዱ
እስኪ እንደ ሸግዬ ጨዋታ ልመዱ፡፡

6. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ
ከአባይ ወዲያ ማዶ ነጭ ላም ቆማለች

ከአባይ ወዲህ ማዶ ነጭ ላም ቆማለች
ማርና ወተቷን ታሳልበዋለች፡፡
ወተቱን አኑሬ ማሩን ብቀምሰው
ሰለምለም ሰለምለም እንደ ሞተ ሰው፡፡
የተሰበሰበው ያተር ገለባ ነው
ሸጌ ጠንበለሉ አልመጣም ገና ነው፡፡
ትመጣለህ ብዬ ባይ ማዶ ባይ ማዶ
የልጅነት ዓይኔ ሟሟ እንደ በረዶ፡፡
ልሙተው ልሙተው መቼም ቁሜ አልደላኝ

ጥርሱ ጉራማይሌ እባብ ሆኖ በላኝ፡፡

7. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ሐምሌና ነሐሴ ይለበሳል ገሳ
የተንቆረዘዘው የከንፈሩ ለዛ፡፡
የከንፈሩ ጤዛ የማተቡ ወዝ
ይግዛኝ ሰባት ዓመት ያለ ደመወዝ፡፡
እንኳን ሠባት ዓመት አልገዛም ወር
ጋሻው የወንዜ ልጅ ባለበት አገር፡፡
ሸግዬ በእኔ ሞት እኔ አፈር ስሆን
አንደዬ ሳቅና ልየው ጥርስህን፡፡
የጣዝማ ወለላ የሸጉ ከንፈር
አዙሮ ይጥላል እንደ ምች አደር፡፡
እገልዬ አቦሉ ባለ ቦራ ፈረስ ባለ ቀይ ኮርቻ
የሚያረገርገው ወገቡ ለብቻ፡፡
አጣጥፌው ነበር ደግሞ ልዘርጋው
እገልዬ እገሌ የብር አለንጋ ነው፡፡
ብርሌው ተንኳኳ ጠጁ ሸተተኝ
እገልዬ እገሌ መጣ መሰለኝ፡፡
ሳሚልኝ ሳሚልኝ ሳንቃ ጎበኑን
እገልዬ እገሌ የረገጠውን፡፡
እገልዬ እገሌ ምንድን ነው ቀለቡ
እንደ ፈረስ ጭራ ቀጭን ነው ወገቡ፡፡
እገልዬ እገሌ ያልሸልኝ እንደሆን
ሺ ብር እከፍላለሁ ተበድሬም ቢሆን፡፡
ዓይናሙ በእኔ ሞት እኔ አፈር ስሆን
አንደዬ ሳቅና ልየው ጥርስህን፡፡
አይቼው አይቼው እንደ መስታወት
ልሰንብት አልልም ዕለቱን ልሙት፡፡
ልሙተው ልሙተው ለምን ልሰንብት

ለአፈር አይደለም ወይ የተሠራሁት፡፡
ያብከነክነኛል ያብከንክን አለብኝ
ያይናምዬ ወዳጅ ሰው ባይኑ ገድሎብኝ፡፡
ባይኑና በጥርሱ ሰው ገዳዩ ማን ነው፡፡
እገልዬ አበሉ ያው ልማደኛው ነው፡፡
ቱሉ ለሚ ሆኖ ይታያል ሰኮሩ
ዓይኑ የሚመስሉት የተኸርጎረጎሩ፡፡
እኔ ከሌሎች ዘር እለውጣለሁ
ቡቃያቸው መልካም መሆኑን አውቃለሁ፡፡

8. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

ከለላ ከጥጉ ላይ ያበቀለች ሾላ
የለቃሚ ያለህ የእኩል የሚበላ፡፡

ሳሩን በሬ በላው ቅጠሉን አንበጣ

ምን ይጎዘጎዛል ሽጋው ልጅ ሲመጣ፡፡
አልመጣም አልመጣም አልመጣም ገና ነው
እሱ ሲመጣማ ለጋ ዳመና ነው፡፡
ከአባይ ወዲያ ማዶ ማሽላ ጠባቂ
እስኪ አገዳ ስጡኝ ያንን ስንጣቂ፡፡
አገዳም ስላልኩኝ አሳምሮ መልጦ
ወዳጅም ሲስሙ የጨዋ ልጅ መርጦ፡፡
አሻቅበው ሲያዩት ዳለቻ ነው ጓሳ
አሁን ከየት ይገኛል ሰውና ሰው መሳ፡፡
ሰውና ሰው መሳ ይገኝ ይመስል
ከጓሳው ስር አደርኩ ከገመራው ሥር፡፡
ከለላ ሲዘልቁ ይታያል ጀጀባ
ላይኑ እና ለጥርሱ ጥንድ በሬ ጀባ፡፡
ዓይኗን ገለጥ አድርጋ ብታደርገው ከደን
አንበሳው ከጫካ ጅብ ይወጣል ከደን፡፡
እንደ አጠቋቆሩ ጥርሱ ባልነበር
ጀበና ነው ብዬ ልጥደው ነበረ፡፡

9. እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ እዋ አበባ ነሽ እዋ አበባ

የቁልቋል አበባ ድምድሜ በራሴ
ገዳም እገባለሁ ቆርጬ በነፍሴ፡፡
የገዳም መነኩሴ ይታጠቃል ሹራብ
ጅል በልቶ ከመጥገብ ሽጋ በልቶ መራብ፡፡
አዲስ አበባ ላይ ይሸጣል ምሳር

ወገቡ ይመስላል ኩሌ ምንሽር።።
የኩሌ ምንሽር አጭር ነው ሰደፉ
የሩቅ ሰው ቢወዱት ትዝታ ነው ትርፉ።።
እንዲህ ወደግራ ወደ ቀኝ ነው ቤቱ
ጎራዬው ናፈቀኝ እንኳን ሰውነቱ።።
እንኳን ሰውነቱ የምወደውን
ሳየው እውላለሁ ባልንጀራውን።።
ባልንጀራው ጠይም እሱ የቀይ ዳማ
አያነፋፍቅም የሠራኸኝማ።።
የሠራኸኝማ የበደልከኝ በደል
አገሩም ይራጋ ሹሙም ይደላደል።።
10. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ሰማይ ለሰማይ ይሄዳል ገዬ
እንደምን አለህ አያ ገርጋዬ።።
አያ ገርጋዬ የውሃ ወንድም
የታጠበበት ቢፈስ አይወደድም።።
አያ ገርጋዬ ኧርግድ እያልክ
ልቤን አውልቀህ ይዘህ ተጓዝክ።።
ሸጌን ቤት አስገቡትና ይንገሩኝ መልእክቱን
ይንገረኝ ይንገረኝ ቁርጡን
ወይ እንዲመነኩስ ወይ እንዲመንን።።
እመነኩሳለሁ እመንናለሁ ስል
እዚሁ ተገኘ ሸጉን የሚመስል።።
11. እዋበባ ነሽ እዋበባ
በስርጡ ወርዳችሁ እዋበባ
እንዬት ነህ በሉልኝ እዋበባ
ቀኝ እጁን ይዛችሁ እዋበባ።።
መቼም የኮራ ነው እዋበባ
አያናግራችሁ እዋበባ
ባይንና በጥርሱ እዋበባ
ትለዩታላችሁ እዋበባ
ያይንና የጥርሱ እዋበባ
የእግዜር ሥራ ነው እዋበባ
እኔን የገረመኝ እዋበባ
አስተጣጠቁ ነው እዋበባ።።
12. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ውበትህ የጠዳ እንደ ስንዬ ቆሎ
ካንተ ጋር ጀነት ነው አዳርና ውሎ።።
ማለዳ ማለዳ ይደፋል አመድ
ሽንጥህ የሚመስለው የመብራት ገመድ።።

እየከረከሩት አይወድቅም ወይ ዛፍ
እንደነው ከናፍሩ የጥርሱ ድጋፍ፡፡
እባብ እርሻ ይረስ ዘንዶ ያብቅል ዘር፣
በጨረቃ ዳኛ በኮከብ ምስክር፡፡
ቁልቁለቱን ወርዶ እዘብጡ ያለው ቤት
ወለል ወለል አለ ልቤ እንደ ቀለበት፡፡
የዛ የልጅ ፍቅር የብቻ የብቻ
ተሰቅሎ ያመሻል ልቤ እንደ ኮርቻ፡፡
ልቤ እንደ ኮርቻ የተሰቀለው
ለትልቁ አይደለም ለትንሹ ነው፡፡
ትንሹም ደግ ነው ትልቁም ደግ ነው
ፍቅር አስጨራሹ መካከለኛው ነው፡፡
አፋፍ ላይ ዘልቄ አፋፍ ላይ ዘልቀህ
ነጠላ ለብሼ ነጠላ ለብሰህ
ያቺ ልጅ አብዳለች ታስብለኛለህ፡፡
እንዳውም እብድ ነኝ ከእብድ ተወልጄ
ወንድማማቾቹን ካንድ ቤት ወድጀ፡፡

13. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እንጨት እሰብራለሁ እንጨቴ ሙሀርባ
ወለቃ ነው አሉ የሸጉ ደረባ፡፡

የሸጉ ደረባ ያውም የትንሹ
ሎሚና ትርንጎ የሚለው ትንፋሹ፡፡
ኧረ ሸጋ ሸጋ ማን እንደ ትንሹ
ሎሚና ትርንጎ የሚለው ትንፋሹ፡፡
ሎሚና ትርንጎ የሚበላ ሰው
እጅግ የታደለ የጨዋ ልጅ ነው፡፡
የጨዋ ልጅ ጨዋ ንግግር አዋቂ
ሲቀመጥ ተጫዋች ሲሄድ ተናፋቂ፡፡
እሷ የምትወደው ሰዓት ያሰረ ነው
ያቺኑ ጊደሬን ሰኞ መንዳቴ ነው፡፡
ተከታታይ ናቸው እንደ ኩታ ጥለት
እገልዬ ብሎ እገልዬ ለማለት፡፡

ሁለት ወንድማማች ከአንድ ቤት ወደሽ

ይቺ ልጅ አበደች ታስብያለሽ፡፡
እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ይላል ጎፈሬያቸው
እባክህ ፈጣሪ ሞትን ያዝላቸው፡፡
የጤፍ አራሙቻ የጤፍ አራሙቻ

እገሌ አባበሉ በይልኝ ለብቻ፡፡
አፋፍ ላይ ዘልቄ ዓይናሙ ብልህ
የለም ቆላ ወርዷል አሉኝ እናትህ፡፡
ላላጣኸው ሥፍራ አፋፍ ላይ ሠርተህ
አብዳ ገደል ገባች ታሰኝኛለህ፡፡
እንዳውም እብድ ነኝ ተብድ ተወልጄ
ሁለት ወንድማማቾች ካንድ ቤት ወድጄ፡፡
ሁለት ወንድማማቾች ሦስተኛ ጋሻቸው
አጥንቱ ይረግፋል ሳልሰናበታቸው
እባክህ ፈጣሪ አትነጥላቸው፡፡

14. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

አፋፍ ላፋፍ ስሄድ አገኘሁ እሪጋ
ሁለቱም ውብ ናቸው በማንኛው ልርጋ፡፡
ማን እንደ ትልቁ ማን እንደ ትንሹ
ሎሚና ትርንጎ የሚለው ትንፋሹ፡፡
ሎሚና ትርንጎ የሚበላ ሰው
እጅግ የታደለ የጨዋ ልጅ ነው፡፡
የጨዋ ልጅ ጨዋ ንግግር ዐዋቂ
ሲቀመጥ ተጫዋች ሲሄድ ተናፋቂ፡፡
ወንድማማቾቹ ሲሄዱ በተራ
እኔ ለትንሹ ጅብ ይብላኝ አሞራ፡፡
እኔን ይብላኝ አሞራ ጅብ ይጨርሰኝ
እኔ ለትንሹ ልቤ አደላብኝ፡፡

6.3. ***መልክን መሠረት ያደረጉ ቃል ግጥሞች***

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ኧረ ሰዎች ዎች ጠይም አትውደዱ
እኔን አታዩም ወይ ሲጠፉኝ መንገዱ፡፡
እነዚያ ጥርሶችህ ከወተት የነጡ፤
አላስተኛኝ አሉ ሌሊት እየመጡ፡፡

ይሄ ወንዛ ወንዙ ያበቅላል እንዶድ
ያካል መጨረሻ ጠይም ልጅ መውደድ፡፡

ጠይም ወደው ወደው በአካል ሲመለሱ
ልብ ይበረብራል ጠጅ እንደቀመሱ፡፡
ጠጅ የቀመሰ ሰው አረቂ ይመኛል
አሁን መናፈቄን ማን ይነግርልኛል፡፡
አሁን መናፈቄን ለነገረልኝ ሰው
ግራ ቀለበቴን ድምብሌን ልካሰው፡፡

ለድምበሉ ነው ወይ ደሴ ለረከሰው
ለማተቡ ነው ወይ ለሚበጣጠሰው
ልጅነት ነው እንጂ የማይመለሰው።።

ጠይሙ ልጃቸው ሻሽ የጠመጠመው

ልቤን እንደ ቆሎ አሽቶ ቆረጠመው።።
የነጭ ጤፍ ገንፎ ይላል ዋጡኝ ዋጡኝ
አንተን ስመለከት ሌሎቹ አመለጡኝ።።
2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እጎታ ላይ ሁና ታስካካለች ዶሮ
እሜቴ ሙሽሪት የጠይም ወይዘሮ።።
አልቅሽ አልቅሽ አለኝ ውሃ ሁኚ ውሃ ሁኚ
ከእሜቴ ሙሽሪት ለምን ተለየሁኝ።።
ያለላ ሌማት ያለላ ሌማት
ጎንበስ ቀና ብለህ እግሯን እጠባት
ሚስትህም አይደለች እመቤትህ ናት።።
ጠይም ጠይሞቹን ምን አሳመራቸው
የወተት አረፋ ይመስላል ጥርሳቸው
የንጋት ጨረቃ ይመስላል ዓይናቸው።።።
አምባረ ሽልሙ አምባረ ሽልሙ
ለቀዩ ታምሜ ልሙት ለጠይሙ።።
ለጠይሙ ብለሽ አትሙቺለት
ውሃውም ጠይም ነው ገርገጭ አድርጊለት።።
እንጨት ሰብሮ ማሰር የቆንጆ ወጉ ነው
አሸካሚ ማጣት ወድቆ መነሳት ነው።።
3. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ውሃ ወርዶ ወርዶ ማረፊያው ቆላ ነው
የዚያ የጠይም ልጅ ቤቱ ሰቀላ ነው።።
ለሰቀላው ነው ወይ ለሾከኪላው
ደሴም ግንቡ ፈርሷል ጣሊያን የሠራው።።
የጣሊያን ቆርቆሮ እባብ ያንሻልላል
ያንተ ልብ እንዴት ነው የኔስ ይዋልላል።።
ደሴን ቁልቁለቱን ልበል ከንበል ደፋ
ያገኘሁት እንደሁ መኪና ሲሰፋ።።
የመኪናው ጓሮ የሚያጉረመርመው
እምቢ ጠይም አሽከር ባርኔጣው ጥቁር ነው።።
ጥቁር ነው ጥቁር ነው ጥቁር ነው ኮርቻ
አፉ ይጣፍጣል እንደ ማር እንጎቻ።።
4. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

አፋፍ ለአፋፍ ስሄድ ቀጭን እሾህ ወጋኝ
ገና በልጅነት ጠይም አዘነጋኝ፡፡
የድንጋይ ሥር ውሃ የጓሳ ፀሐይ
ጠይም ዓይነ መልካም ይጠገባል ወይ፡፡
ጠይም ዓይነ መልካም ፈንጣጣ የወጋው
እሱ ነው መሰለ\ኝ ልቤን ያዘነጋው፡፡
ትዬዳለህ አሉ በረጅም ጎዳና
ለእግርህ ጫማ ልሁን ለራስህ ዳመና፡፡
ለእግርህ ጫማ እንዳልሆን እሾህ ይወጋኛል
ለራስህ ዳመና ብሆን ይሻለኛል፡፡
ከራስህ ላይ አድርገኝ ከሚወዱህ በላይ
ካርቲው ካሽኩቲው እከብዳለሁ ወይ፡፡
ዓይኑን በቀጫጭን የተኳኳለው
ጥርሱን ጉራማይሌ የተወቀረው
እንደ ነብር ጅራት የሚወራጨው
እንዴት ነው ጠይም ልጅ ወግዲ ያለው፡፡

5. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ዝናብ ጥሎ ጥሎ ሲያበቃ ያካፋል
ጠይም የወደደ ሲሄድ ያንቀላፋል፡፡
ዝናብ ጥሎ ጥሎ ደጋ ደጋውን
ጎርፉ ያመጣህ እንደሆን ከወንዙ ልሁን፡፡
ጠይም የወደደ ገና ነው አሳሩ
ውሃው እየሞላ እያደገ ሳሩ፡፡
ጠይም ጠይሞቹን ምን አሳመራቸው
የወተት አረፋ ይመስላል ጥርሳቸው፡፡
እባብ ሰለክላኬ ሲሄድ አይታይም
እገልዬ እገሌ ዘለግ ያለ ጠይም፡፡
አፋፍ ለአፋፍ ስሄድ አጋም እሾህ ወጋኝ
ገና በልጅነት ጠይም አዘነጋኝ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ሐምሌና ነሐሴ ይለበሳል ገሳ
የተንቆረዘዘው የከንፈሩ ጤዛ፡፡
የከንፈሩ ጤዛ የማተቡ ወዝ
ይግዛኝ ሰባት ዓመት ያለ ደመወዝ፡፡
እንኳን ሰባት ዓመት አልገዛም ወር
ሸጋው የወንዜ ልጅ ባለበት አገር፡፡

6. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እዩት እዚያ ማዶ ከገደሉ ሥር

ጠይም ልጅ ይፈልቃል ውሃ ይመስል፡፡
በከላላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት
ደሴም ታረሰ አሉ እስከ ከተማው
ጠይም አሳ መሳይ ውሃም አይጠማው፡፡
ለቀይቱ ቢሉኝ በርበሬ ገዛሁኝ
ለጠይሟ ቢሉኝ ከምንጩ ጠጣሁኝ
ለጥቁሪቷ ቢሉኝ አሻሮ ቆላሁኝ
ለዛች ለቀይ ዳማ መድሃኒት አጣሁኝ፡፡
ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም አትውደዱ
እኔን አታዩም ወይ ሲጠፋኝ መንገዱ፡፡
ያየና ስንዴ እንጂ አያበቅልም ጓያ
ዕዳ ነው ጠይም ልጅ የውሃው አምሳያ፡፡
የውሐው አምሳያ የውሐው ወንድም
ቢጓሽም አልጠላ ቢደፈርስም፡፡
እየጓሸ ልቤ እየደፈረሰ
የመለያያችን ቀኑ እየደረሰ፡፡
ወዘፍዘፍ ያለ ነው የግራር አጥር
መልኩ ሸሞንሟና ቁመቱ ቢያጥር
እኔ በቁመቱ አልጎዳበትም
ማሬ ያገሬ ልጅ ያባክናል የትም፡፡
አባካኝ ይለኛል አባካኝ ለራሱ
እያብከነከነኝ በዓይንና በጥርሱ፡፡
ባልንጀራው ጠይም እሱ የቀይ ዳማ
ሰፈራቸው ደማቅ እንደ ንጉሥ ከተማ፡፡

7. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እሄድ እሄድና እላለሁ ታከተኝ
መውደድ በጎራዴው እየከተከተኝ፡፡
መውደድ በጎራዴ በጣም አስገድዶ

እንዴት ሰው ይሞታል ጠይም አሸከር ወዶ፡፡
ጠይም አሸከርና ቤተስኪያን አንድ ነው
እንዳልስመው ልቤ ምናምን ነው፡፡
ምናምኑን ሁሉ በልቼ በልቼ
አስታውከዋለሁ ግራዋ ጠጥቼ፡፡
ግራዋ ግራዋ የሚመረውን
እሪጋ አደረገችው ሽጋ ደማሙን፡፡
የዋርካ ቅጥይ የዋርካ ቅጥይ
አጠር ያለው መልካም ዘለግ ያለ ቀይ፡፡
ከኪያ ከጠይሞች ምረጪ ቢሉኝ

እኔስ ለጠይሙ ልቤ አደላብኝ፡፡
ቀይና ጠይሙ ሲሄዱ በጋራ
እኔስ ለጠይሙ ጅብ ይብላኝ አሞራ፡፡
አሞራ በሰማይ ጅብ ይሄዳል በምድር
ያለህበት አገር ሸዋ ነው በጌምድር፡፡
አረሙን አርሜ ከዳሩ ስደርስ
ሸግዬ ሸተተኝ ጮርቃ ጮርቃ ገብስ፡፡
ያንን ጠይም ልጅ ሁሉ ወደደው
ማጭድ አምጡና እንቃደደው፡፡
ከአንገቱ በላይ ለእኔ ስጡኝ
የልጅነቴ ወዳጁ ነኝ፡፡
የኔ ጠይም አሸከር ከናቱ ጋር ያለው
ይሸጣል ይላሉ ዋጋው ምን ያህል ነው፡፡
ዋጋው ምን ያህል ነው ስንት ነው ዋጋው
ፈረስና በቅሎ ከነሙሉ ዕቃው
ፈረስና በቅሎ ዛብና ኮርቻ
የሚያረገርገው ወገቡ ለበቻ፡፡
አረገርጋለሁ ያረግራጊ አለብኝ
ሸጉ የኔ ዓይናማ ባይኑ ሰው ገድሎብኝ፡፡
ባይኑ መቶ ገዳይ በጥርሱ ሠላሳ
ሰው ጉድ አይልም ወይ እኔ አንተን ብረሳ፡፡
ሸጉ አንተን ብረሳ አንተን ጠይሙን
የውሃ ላይ ሰርዶ የመሰልከውን፡፡
የውሃ ላይ ሰርዶ ሥፍራ የተመቸው
እንዳ ነው ፍቅራችን የማይሰለቸው፡፡
ጠይም ዓሳ ሆኖ ጠይም ዓሳ መውደድ
ረጅም ጎዳና ከብት የሌለበት መንገድ፡፡
አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እኔስ እሄዳለሁ በደንቆሮ በኩል
ዓይኔ ተሸክሚል ጠይም ልጅ እንደ ኩል፡፡
የእኔም አገር ጠይም እንዳላበቀለ
በሰው አገር ጠይም ልቤ ተሰቀለ፡፡
ዝናብ ጥሎ ጥሎ ሲያባራ ያካፋል
ጠይም የወደደ ሲሄድ ያንቀላፋል፡፡

6.4ገና በልጅነት በፍቅር መንገላታትን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ረ በለው በለው
   አዲስ አበባ ላይ ይሸጣል እንቦሳ
   ፍቅር ወሰወሰኝ ከምድር ሳልነሳ፡፡
   እንጫወት እንደሁ እንጫወት በጣም

እንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም።
ውሃ ቅጂ ብላ ብትሰደኝ እናቴ
ወለሹን ቀዳሁት አወይ ልጅነቴ።
እንዳው ዛሬ ብሆን ነፍስ እንደ ማወቁ
ማረኝ እለው ነበር ከጫማው ወድቄ።
ከጫማው ወድቄ በጫማው ልነሳ
የሠራ አካላቴ ወርቅ ይዞ ተነሳ።
የዳገት ደደሆ አይቆርጡም ጥላ ነው
የልጅነት ወዳጅ የአባት ርስት ነው።
የልጅነት ወዳጅ የልጅነቴ ነው
በቃኝ ካላልኩኝ የማልተወውን።
ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ
ያገር ሽማግሌ የገላጋይ ያለህ።
ያገር ሽማግሌ ገላጋይ ባልነበር
ልቤ ገደል ገብቶ ሊሰባበር ነበር።
የበረሃ ሎሚ ቅጠሉ ለጋ ነው
የልጅነት ፍቅር የማር ወለላ ነው።

6.5. የሸጋን ወላጆች፣ ወንድችና ቤተሰቦች ማወደስ

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

የሰማይ አሞራ ላቀብልሽ ጥሬ
ትነግሪኝ እንደሆን የሸግዬን ወሬ።
የገደል ሥር ውሃ ፈሳሹ ፈሳሹ
ማተብ ስደድልኝ ለተመላላሹ።
አያ ሂድ አያ ሂድ ምን ያቋቁመሃል
እስከ አሞራው ገደል ዓይኔ ይሸኝሃል።
እስከ አሞራው ገደል ዓይንሽ ከሸኘኝ
እኔም ከዚያ ኋላ ጎንደር ገቢ ነኝ።
ሸጋ የወለደ ዘሩ ሸጋ ይሁን
ጧት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን።
ጎፈሬው ይመስላል ንብ የሰፈረበት
አንገቱ ይመስላል ጠጅ የፈሰሰበት
የእሱ እናት ይውለዱ ሌላው ይምከንበት።
የሸግዬን እናት ብቅ በይ በሏት
እንዲህ አሳምረሽ ማን ውለጅ አላት።
እንዲህ አሳምሬ ብወልደው ምነው
ላንችም ወዳጅሽ ነው ለእኔም ልጄ ነው።
የማናት ይሉኛል እኔስ የማነኝ
ያዳሙ ተፈሪ ታናሽ እህት ነኝ።

እኔ ምን አለብኝ የነ አልዩ እህት
ክንዱን ሳይንተራስ ጎራዴው ሳይሞት።።
ቁልቁለት አልወርድም እፈራለሁ ናዳ
እሰይ የኔ ወንድም ያንበሳው ለማዳ።።
ያንበሳው ለማዳ የነብር ግልገል
ተንደርድረህ ወርደህ በለው በሽመል።።
ምነው በሽመሉ በሚሰበረው
ተንደርድረህ ወርደህ በጥፊ በለው።።

6.6 ጀግንነትን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

የሸግዬ ዱላ ጥቁር የነበረው
እየቀላ ሄደ ደም እየነሰረው።።

የዘውድዬ ዱላ ጥቁር የነበረው
የይመሩ ዱላ ጥቀር የነበረው
እየቀላ ሄደ ደም እየነሰረው።።
ማሬው ልጅ የጀርሳ አልመጣም ገና ነው
ማሬው ልጅ ጎሽ አምባ አልመጣም ገና ነው
የተሰበሰበው ያተር ገለባ ነው።።
አንች አተር ገለባ ምን ይቆልልሻል
ማርዬ ------ይበታትንሻል።።
የነጭ ጤፍ ወፍጮ ይላል እሸም እሸም
ይመክታል እንጂ ወንድ ልጅ አይሸሽም።።
መሸሹንስ ይሸሽ ያባቱ ነው አሉ
እኔስ የገረመኝ ዱላውን መጣሉ።።
ወርደህ ግደል እንጂ አዳል ከሜዳው
ምን አለ ዝሆኑ ቅጠለ በላው።።
ቅጠሌ ቅጠሌ ቅጠሌ ጣጤሳ
ከባህር አውጥቶ ጅብ አይበላም አሳ
የጅብን ትራፊ አይበላም አንበሳ።።
የአንበሳውን ወዳጅ አንበሳ ስሞበት
ያም እየጎደራ ያም እያገሳበት።።
አንተም ተው አንተም ተው ብዬ እንዳልላቸው
ሁለቱም ያገር ልጅ የወንዜ ልጅ ናቸው።።
ረጅም ግራር ላይ ይሰቀላል ቀፎ
የዓይናማዬን ወዳጅ በለው በወጨፎ።።
የዓይናማዬ ወዳጅ ብሎ ሲደነፋ
የአንገቱ ጅማሬ ብር ብሎ ጠፋ።።

ብር ብዬ ሂጄ ብር ብዬ ልምጣ
ናስና ቆርቆሮ ታገራም አላጣ፡፡
እወድህ አልወድህ ማን ይጠይቀኛል
ውሃ እንደ ቁም ነገር ስጠጣው ያንቀኛል፡፡
እና አጅሬ ቀዬ ማን ደርሶ ማን ደርሶ
ምንሽር ተጠምዷል አሥራ ሁለት ጎርሶ፡፡
ባይ ወዲህ ማዶ ወግዲ ነው ቤቱ
ማተብና ድንብል ላክልኝ በሞቴ፡፡
ማተቡም ይቅርብኝ ድንብሉም ይቅርብኝ
ሸጌ የዱላው ዕለት እንዳትሸሽብኝ፡፡
ሸጌ የዱላው ዕለት የቀረህ እንደሆን
እንኳን ከንፈር ወዳጅ ጎረቤትም አንሆን፡፡
ከመፋቂያው ሁሉ የጭጮ ያነጣል
ደግሞ ከጎበዞች እገሌ ይበልጣል፡፡

ሞት ይርሳኝ ሞት ይርሳኝ ሰው እረስቻለሁ

እገልዬ እገሌ ሳልል ቀርቻለሁ፡፡
ሽመላቸው በቀኝ ባትሪያቸው በግራ
ማን ይወዳደራል ከቦረኖች ጋራ፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ገደዋዬ ነይ ነይ ገደዋዬ ነይ ነይ
እከደከ ሰይጣን ቀየው ከበደኝ
እነ ሞት አይፈሬ መጡ መሰለኝ፡፡
የስንዴ ክምር የስንዴ ክምር
የጀገነ ይምጣ የፈራ ይቅር፡፡
አንዱን ከዚያ ማዶ ና ብየዋለሁኝ
አንዱን ከዚህ ማዶ ና ብየዋለሁኝ
ፈሪና ጀግናውን እለየዋለሁኝ፡፡
ፈሪና ጀግናውን በምን ልለየው
ይህን አሜሪካ ሁሉ ላበላው፡፡
እኔ ከዚህ ሁሉ ምረጭ ቢሉኝ
ለአዲሱ ወዳጀ ልቤ አደላብኝ፡፡
እኔው ተሞኝቼ እኔው ተጃጅዬ
የተቆረጠ ዛፍ ያቀጥላል ብዬ፡፡
ይሄን ወሬ ብለሽ አታውጊው ለሰው
ምኑ ያቀጥላል ሥሩ የፈለሰው፡፡
እገልዬ አበሉ መሄድህ ነው ወይ
የታጠቅከው ሱሪ ተውሰህ ነው ወይ፡፡
ጫቀታን አሻግሮ ለሚን ያስጨነቀው
የእነ እገሌ ዱላ በወርቅ የታነቀው፡፡

ዱላውን አንስቶ ሻሹን ሲጠመጥም
ራብ ራብ አለኝ ውሃ ጥም ውሃ ጥም፡፡
እገልዬ አበሉ የጣሰው ግራር
ዓመት ያስጋግራል ከሽልሽል ጋር፡፡
ጓደና መኮንን ጓደና መኮንን
ሄደ አሉ ሄደ አሉ ሄደ አሉ መንኖ
ምንሽሩን አምኖ፡፡

3. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ዱላው ባለ ጅና ቦንቡ ባለ አምባር
ይሄ ያገሬ ልጅ የውርማው ነብር፡፡
በመስከረም ወራት ይዘራል ሽንብራ
ሸተት ብለህ ሞክር እኛ አንፈራም ዱላ፡፡
ወዘፍወዘፍ ያለ ነው የግራር አጥር
እኛ ለጉረኛ እምብዛም አንጥር፡፡
አንተም ትላለህ ወይ ወንድ እኩል ወንድ እኩል
የሸሚዝህ ቅማል አንድ ቁና ተኩል፡፡
የጓንጉቸር ኮርማ ድብ አይራመድም
አንተ አራም ጉረኛ ቆይ አንሳደድም፡፡
ብመታም ራሴን ብታሰር ከለላ
ያቺን ልጅ ነክታችሁ አሳር እንዳይፈላ፡፡
እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጎበኘው
የጀግኖችን አገር ባለጌ ተመኘው፡፡
ነካካው ነካካው አትስጣቸው ጤና
ምን ጊዜም ደህና ሰው አልተባልንምና፡፡
ትለሙም ትለም ነው አንድ ነው ዓይነቱ
ጎበዝ ይላል እንጂ ክትት ያለ አሞቱ፡፡
ምን ያደርጋል ሽመል ምን ያደርጋል ትለም ጅና ቢበዛበት
አንድ ሰባራ ቅል ካልተረተሩበት፡፡

4. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ይባዘታል እንጂ ጥጥ አይመነሽም
ይመክታል እንጂ ወንድ ልጅ አይሸሽም፡፡
ወፍዬ እረ በለው በለው
ወንድ የለም ወይ ብዬ ዞሬ ዞሬ ሳይ
እገልዬ አበሉ ደረስክልኝ ወይ፡፡
እገልዬ አበሉ የአዲስ አበባው
የኩታውን ጌታ ምን አመጣው፡፡
አንዱን ከቀላዱ ና ብየዋለሁኝ
አንዱን ከለሚ ላይ ና ብየዋለሁኝ
አንዱንም ከሌንጮ ና ብየዋለሁኝ
ፈሪና ጀግናውን እለየዋለሁኝ፡፡

ኧረ ፈሪ ፈሪ ፈሪ በጉድ ወጣ
አደባባይ ወጥቶ የሚተኩስ መጣ፡፡
አደባባይ ወጥቶ የሚተኩሰው ማነው
ማሬው ልጅ የቀላድ ያው ልማደኛው ነው፡፡
ማሬው ልጅ የቀላድ በላቸው በላቸው
ጨርሶ እንኳን ተኳሽ መካችም የላቸው፡፡

5. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
በዘርዛራ ማጭድ ይታጨዳል ጓሳ
ቁልቋል ተደግፎ ይውላል አንበሳ
አብሮት የሚውለው ባልንጀራውሳ፡፡
ባልበዘርዛራ ወንፊት ይነፋል ዳጉሳ
ንጀራው ጠይም እሱ የቀይ ዳማ
ሽርሽር ይወዳል እንደ ንጉሥ ከተማ፡፡
እንጉሥ ቤት ገብቼ መካከሉ ከሴ
የጀግና ወዳጅ ነኝ አትንካኝ ኮሳሴ፡፡
አትንካኝ አትንካኝ አትንካኝ በጅህ
እኔም ይቀፈኛል ላንተም አይበጅህ፡፡
ዓባይ አለቱ ላይ ያበቅላል ጣጤሳ
ድጉን ጣል አድርጎ ዝናሩን ሲያነሳ
የቀባሪ ያለህ ሁኛለሁ ሬሳ፡፡
ቀባሪ ምን ገዶ ቦረና መሬት
ያበቅለው የለም ወይ አረንዛው ሳይንት፡፡
ሳይንት ወደ ግራ ጓሳ ወደ ቀኝ
ምን ትጠቀማለህ አንተን ስል ብገኝ
አንተን ስል ነው እንጂ እንዲህ መዋተቴ
ገንዘቤ አልተያዘ አልታገቴ ከብቴ፡፡

6. ወፌ ይላላ ላላዬ ነይ ነይ ደማማዬ
የኔ ውቢቱ እረ በለው በለው
የኔ ውቢቱ እረ በለው በለው
የኔ ውቢቱ ያም ወርዶ ያም ወርዶ
የኔ ውቢቱ ዲቡን ነቀነቀው
የኔ ውቢቱ ለጀግናም ደስ አለው
የኔ ውቢቱ ለፈሪም ጨነቀው፡፡
ማሬው የቀላዱ አትፍራ ሞት
ማሬው የለሚው አትፍራ ሞት
ማሬው ‹‹የሌንጮው›› አትፍራ ሞት
ስምህ ተጽፏል በወረቀት
በፈሪ አይደለም በጀግንነት፡፡
በተራዘመ ዱላ ታላንጎራደደው
እኔ እናቱ ነኝ ወይ ሲሸሽ የምወደው፡፡

ካንተ ወንድነት ይሻላል ዱባ
ባንተ ላይ ዘምቶ ያደምቃል አምባ፡፡
ቢሰማመሩ እንደ ቅቤ ቅል
መመከትና መሸሽ እየቅል፡፡
አይሸሽም ያልሺው ይመርም ሸሸ
የለሚን ስንዴ እያበላሸ፡፡

6.7 በፍቅር አቻ አለመሆን

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
በጨለማ ስሄድ ጅብ አላገኘኝም
እድሌ ሆነና ዝንጆሮ አያጣኝም፡፡
ተወደድኩ ብለህ አትበል ጠብረር ጠብረር
እኔም አንድ ሰሞን እንዲህ አድርጎኝ ነበር፡፡
የቆላ ማሽላ መሃከሉ መንገድ
ተወኝ አላልኩም ወይ ችላ እያሉ መውደድ፡፡
ችላ እያሉ መውደድ የዘርህ ነው አሉ
ምነው በቀረብኝ ካንተ መዋዋሉ፡፡
ጅል የወደደና በበግ የነገደ
ዘላለም ይኖራል ሆዱ እንደነደደ፡፡-
እንክትክት ስብርብር እንደ ኑግ አገዳ
ከቤት አይወጣም ወይ ባላገር እንግዳ፡፡
ባላገሩ ልቤ ባላገር ይመኛል
ወታደሩ ልቤ ወታደር ይመኛል
አትሸበር ሆዴ የበለጥ ይገኛል
ላንተ የተባለው ተቀምጦልሃል፡፡
ትደልቅ እንደሆን አሳምረህ ደልቅ
አትደልቅ እንደሆን አትጨማለቅ
አትደልቅ እንደሆን ሀድራውን ልቀቅ፡፡
ያተር እንጉላይ ያተር እንጉላይ
አንተን ለማስደለቅ እኔ አንሳለሁ ወይ፡፡
ውረድ እንውረድ እንጂ ለምን ገተር ገተር
እንዳውም ይሉናል የክትክታ ብትር፡፡
የክትክታ ብትር አባጣ ጎርባጣ
እማማ ላይ ሆኜ ወፍ እጠብቃለሁ
እሺ በል ያገር ልጅ ፍቅር የጋራ ነው፡፡
ኧረ ፍቅር ፍቅር ፍቅር እልቢሶ
ሲጀምሩት ማር ማር ሲጨርሱት ኮሶ፡፡
እገልዬ አበሉ አትደልቅም ወይ
አንተን ለማስደለቅ አንሼ ነው ወይ፡፡
ፍቅር የጋራ ነው ቢሉ ገረመኝ

ገርጋዳዬ ታሞ ሄዱ መሰለኝ፡፡
ሲታመሙ ታሞ ሲሞቱ ካልሞቱ
በምን ያስታውቃል ሰው ወዳጅነቱ፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
አሞራው ሲዞረኝ ጅቡ ሲያጋምር
የቃልቻ ልጅ ነው አያውቅም ፍቅር፡፡
የቃልቻ ልጅ ነው የሶላት አጥባቂ
የገበሬ ልጅ ነው የሞፈር አራቂ፡፡
የነጋዴ ልጅ ነው የአህያ ጠባቂ
የወታደር ልጅ ነው የዝናር ታጣቂ
ታምሜያለሁና ሂዱልኝ ዐዋቂ፡፡
ዐዋቂ ሂዳችሁ ምን አሉ ምን አሉ
ሠላሳ ወረቀት አስጥፉለት አሉ፡፡
ሠላሳ ወረቀት አንድ ነው ዓይነቱ
የወሎ ባልቴቶች እስኪ ጨሌ ምቱ፡፡
ብወድሽ ባልወድሽ ማን ይጠይቀኛል
ውሃም እንደቁም ነገር ስጠጣው ያንቀኛል፡፡
ቆለኛ ሞኝ ነው ይማታል በድግር
ትተሸው ነይና ቂጣውን ይጋግር፡፡
የበጎች ማሠሪያ ውልክፍክፍ እግር
አንተም ትላለህ ወይ ልምጣ ወይ ልቅር
የወለቃ ውሃ ፍሳሹ ፍሳሹ
ማተብ ስደድልኝ ለተመላላሹ፡፡
የሰደድከው ማተብ ሰላላ መላላ
መልሰህ ውሰደው ጉዳይም አይሞላ፡፡
እንቧይ ከብለል ብላ አለፈች በደጄ
ባይኔ አየኋት እንጂ መቼ ነካኋት በእጄ
ሙት አባቴ ይሙት አንተ ነህ ወዳጄ፡፡
ሙት አባቴ ይሙት እኔ አንተን ይንሳኝ
አልደርስብህም ልቤን ካልነሳኝ፡፡

3. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እዩት እዚያ ማዶ እገደሉ ሥር
ፍየል መንታ ወልዳ አራሹ ነብር
ውሃ በብርሌ ወዝቶ ማደር፡፡
ውሃ በብርሌ ወዝቼ አድሬያለሁ
ከማይሆን ሰው ጋራ ፍቅር ጀምሬለሁ፡፡
ከማይሆን ሰው ጋራ ከማያዋጣኝ
ውሰድ በሽታህን ጤናየን ስጠኝ፡፡
ጤፍ እሰልቃለሁ እንግዳ መጥቶብኝ
ገርጋዳው ወዳጄ አሽከሩን ልኮብኝ

አሸከሩን ከሚልክ እሱ አይመጣም ወይ
መቼም ባላገር ናት ተብዬ ነው ወይ፡፡
እኔ የባላገር ልጅ መሸ ነጋ ባይ
እሱ የጌታ ልጅ እንጫወት ባይ
እንዲህ ሆኖ ፍቅር ይዘለቃል ወይ፡፡
ባላገሩ ልቤ ባላገር ይመኛል
ወታደሩ ልቤ ወታደር ይመኛል
አትሸበር ልቤ የበለጥ ይገኛል፡፡

4. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እምም ይላል ወፍጮ ይከተላል መጅ
ካንተ ወዲያ ጎበዝ ከኔ ወዲያ ልጅ
ኮከብህ ኮከቤ ባይገጥም ነው እንጂ
ኮከብህ ኮከቤ የገጠመ ለታ
ለማርያም መቀነት ለሥላሴ ኩታ፡፡
ተው በሉት ልቤን ትችሉት እንደሆን
ዓባይ ወረደና አስጠመደ ዝሆን
አንበሳ ቢበላው መፋረጃ ሊሆን፡፡
አውራማ በልቶት አንጀቴን ባራሰው
የማይሆን የማይሆን እንዴት ይመኛል ሰው፡፡
የሸንብራ አበባ ንፋስ ያበነነው
ትተኸኝ እንደሆን ልቤን ተው ልበለው፡፡

6.8 የሚወዱት የከንፈር ወዳጅ የተወለደበትን አካባቢ ማድነቅ በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው **በለው**
በተራ በተራ ይተከላል ሎሚ
ሌንጮን ጠቀስ አድርጎ ዘወርዋራው ለሚ፡፡
ይሄ ለሚ ነው ወይ ብሃርዛፍ ያለበት
ልቤ እንደ ጆቢራ ሂዶ ዘፍ አለበት፡፡
ፍቅርህ አውቶማቲክ ማርከሻም የለው
ከትምህርቴ ጋራ እንዴት ልቻለው፡፡
እዩት እዛ ማዶ ሁለት ዛፎች አሉ
አትገደፏቸው ልብ ይዘውራሉ
ዘውረው ዘውረው ገደል ይሰዳሉ፡፡
ገደሉ ተንዶ ተይሏል በብረት
እንገናኛለን ፈጣሪ ያለ ዕለት፡፡
አገልግል ሰፍቼ እፊያው ገና ገና
ማሬው ልጅ ቀያፈር ጎፈሬው ደመና፡፡
ሰተት መለል ያሉ እንደ ምስርች
ገና አሁን ዘለቁ ያገሬ ልጆች፡፡

ሲደልቁ ማማር ሆ ሲሉ መድመቅ
እኔ እንደ ወንዜ ልጅ አይቼም አላውቅ፡፡
የዱላ እንክትካች የዱላ እንክትካች
ማሬው ልጅ ቦረና ተንበርክኮ መካች፡፡
አንዱን ከሰንቦ ልጅ ና ብዬዋለኝ
አንዱን ከደብር ልጅ ና ብዬዋለሁኝ
ፈሪና ጀግናውን እለየዋለሁኝ፡፡
ማሬው ልጅ ይላሙ ምታና ምታና
ማሬው ልጅ ጭላሉ ምታና ምታና
ማሬው ልጅ ደንቢ ምታና ምታና
ውሰደው ማተቤን ከአንገቴ ፍታና፡፡
የአንገቴንም አይደል የትንሽ ጣቴን
እንደ አንተ አልወዳትም የእናት ልጅ እቴን፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እወቀረዋለሁ ጥርሴን በአመራሮ
የሸጋ አገር ልጅ እንደምን ነው ዋሮ፡፡

እኔ በያየና ላይ መዝለቄን አልተውም
እኔ በደንቢ ላይ መዝለቄን አልተውም
እኔ በሜታ ላይ መዝለቄን አልተውም
እኔ በቀያፈር መዝለቄን አልተውም
ሰውን በሽታ እንጂ ሀሜት አይገድለውም፡፡
ማሬ ልጅ ላይ ሚዳ አልመጣም ገና ነው
ማሬ ልጅ ጎድጓዲት አልመጣም ገና ነው
ማሬ ልጅ ታች ሚዳ አልመጣም ገና ነው
የተሰበሰበው የአተር ገለባ ነው፡፡
ማሬ ልጅ ሁላጎሽ አልገባም ገና ነው
ማሬ ልጅ ምስካቤ አልገባም ገና ነው
ማሬ ልጅ የወርቁ አልገባም ገና ነው
አንተ ያተር ገለባ ምን ይቆልለሃል

ሸጋው ቀይ አፈር ይበታትንሃል፡፡

3. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የዱላ ካካታ አይወድም ገላዬ
ማርዬ ከለላ ና ዙር ከኋላዬ፡፡
ማርዬ ከለላ የወረደበት
መሬቱ ጎድጉዶ ውሃ ሞላበት፡፡
ፍየሊቱን አርደው ቢሏት አልሞተች
ቤቱም ከለላ ነው ከመንገድ በታች፡፡
ካሁን ከቅድሙ አሁን ተሻለኝ

ማርዬ ከለላ መጣ መሰለኝ፡፡
ከከለላ ሎሚ ከአለልቱ እንኮይ
አንተንም እንደ እኔ ከለከሉህ ወይ፡፡
አንተንስ እንደ እኔ አይከለክሉህም
እንደ ልጅነትህ ሃይማኖት የለህም፡፡
ከከለላ ሎሚ ካለልቱ ሽንብራ
ምድርና ሰማይን አንድ አድርጎ የሠራ
አወይ የፈጣሪ አወይ የአምላክ ሥራ
ማኖር አቃተው ወይ አንቺን ከእኔ ጋራ፡፡
ሲደልቁ ማማር ሲዘፍኑ መድመቅ
እኔ እንደ ከለላ አይቼም አላውቅ፡፡
የከንፈሩ ጤዛ የማተቡ ወዝ
4. አያ በለው በለው ሽረ በለው በለው
ይግዛኝ ሰባት ዓመት ያለ ደመወዝ፡፡
እንኳን ሰባት ዓመት አልገዛም ወር
ማርዬ ወግዲ ባለበት አገር፡፡
ተበድሬ አልበላ ጦሜንም አላድር፡፡
ብርሌው ተንኳኳ ጠጁ ሸተተኝ
ማሬው ልጅ የጀርሳ መጣ መሰለኝ፡፡
መለል መለል ያሉ እንደ ምስርች
ገና አሁን ዘለቁ የልጎ ልጆች፡፡

6.9 የከንፈር ወዳጅን የፍቅር መጠን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ሽረ በለው በለው
አፋፍ ለአፋፍ ስሄድ ነከሰኝ እባቡ
ቁመህ አስቀብረኝ ባንተ ነው ስበቡ፡፡
ማስቀበሩንማ አስቀብርሻለሁ
አንቺ መ·ተሺ እኔ ለማን እቀራለሁ፡፡
አንተ ቀጣፊ ዋሾ የልጅ አታላይ
እንኳን ልትሞትልኝ ታመመክልኝ ወይ፡፡
መታመሙን እንኳን እታመምልሻለሁ
ፍቅር ማንን ገድሎ እሞትልሻለሁ፡፡
እሄድ እሄድና እላለሁ ታከተኝ
መውደድ በጎራዴ እያነካከተኝ፡፡
አምስት መቶ ፍቅር ሦስት መቶ ትዝታ
አስቀይሜህ እንደሁ አርግልኝ ይቅርታ፡፡
እኔስ እሄዳለሁ ዋ ብዬ ዋ ብዬ
ሀገሩ ደንቆሮ ማን ይሰማኝ ብዬ፡፡
ሀገሩ ደንቆሮ ሥፍራው የወንበዴ
ስንቱን ጎራ ዙሮ አንተን አለኝ ሆዴ፡፡

ትምህርት ቤት ሁኜ ትዝ ብትለኝ
በአማርኛው ደብተር ሂሳብ ሠራሁኝ፡፡
ትምህርት እማራለሁ ይገባኝ ይመስል
ውጤት ዜሮ መጣ አንተን ሳብሰለስል፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

ያፋፍ ላይ ደደሆ ባይቆርጡት ጥሩ ነው
የልጅነት ወዳጅ ያባት ርስት ነው፡፡
ያባት ርስትና የምስር እሸት
ቢበሉት ቢበሉት ጠብ አይል ካንጀት፡፡
እዚያ ማዶ መንደር ቢጣሉ እወዳለሁ
ገላጋይ መስዬ ያንን ልጅ አያለሁ፡፡
ያባይ ጥቁር እንጨት መንትያው ተልጧል
ዛሬስ ያገሬ ልጅ ባህሪው ተለውጧል፡፡
የጌታ ልጅ ጌታ ንግግር አዋቂ

ሲቀመጥ አጫዋች ሲሄድ ተናፋቂ፡፡
አፋፍ ላፈፍ ስሄድ አገኘሁ ሙዳይ
በዛች ሙሉ መውደድ አይበቃንም ወይ፡፡
እንኳን በዚያች ሙሉ ይበቃናል በፍኝ
ወይ አንተ ካልከዳህ ወይ እኔ ካልተውኩኝ፡፡
ሀሳብ የሌለበት ናፈቀኝ ዘመኔ
ካንተ ተለይቼ መኖር አልችል እኔ፡፡
አትራቅ ከጎራ ጠብቀኝ ሸግዬ
እመጣልሃለሁ እንጨት ልስበር ብዬ፡፡
ትመጣለች ብለህ አትሰብ ግድ የለም
መለኛ ነኝና ከሴት መላ አይጠፋም፡፡

3. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

ብቅ በል ሸግዬ ጉዳይ ልንገርህ
አንተንም እንደ እኔ ባይከለክሉህ፡፡

ማተብ ስደድልኝ ጅማሬ ጅማሬ
አንተን አይደለም ወይ ገና መጀመሬ፡፡
ገና ስጀምረው ስደረድረው
እንደ እኔና እንዳንተ የሆነው ማን ነው፡፡
እንደ እኔና እንዳንተ የሆነም አላየሁ
እንደ አደረ ሬሳ በምን ተለያየሁ፡፡
ቤትህ እጎራው ሥር መሆኑን አውቃለሁ
አበባ ሁንልኝ መጥቼ እቀስማለሁ፡፡
ቤትህና ቤቴ አግድመት ላግድመት

አንገቱ ጠመመ ሥጋ እንዳየ ድመት፡፡
ቤትህና ቤቴ ማዶ ለማዶ ነው
ድምጽህን አሰማኝ ነፍሴ ሊወጣ ነው፡፡
ቤትህና ቤቴ ማዶ ለማዶ ነው
የሚጠጣ ውሃ ምንጫችን አንድ ነው፡፡
የእዛ ማዶ ጎራ ይካባል ይናዳል
ውርጋጥ ተቀምጦ ሽማግሌው ያብዳል፡፡
አንተ ሽማግሌ ምን ያሳብደሃል
ፍቅር እንደሆነ ገደል ይሰድሃል፡፡
4. አያ በለው በለው ረ በለው በለው
የጭጮ እሪጋ መሃከሉ መንታ
አንዱ የሸግዬ አንዱ የኔ ፈንታ፡፡
ሸግዬን ስትሉት ዓይናማን ስትሉት
ታምሜለሁና ታመምልኝ በሉት፡፡
እቴ መሰረቴ እቴ የብቻዬ
ከጆሮዬ ላርግሽ እንደ ጉትቻዬ፡፡
የጆሮ ጉትቻ ቢያወልቁት ይወልቃል
እቴ ያንቺ ፍቅር በስንት ዓመት ያልቃል፡፡
ሁለት ጤፍ እንጀራ በስሱ በስሱ
ለቁንጥ አይደለም ወይ ሸረፍ ያለው ጥርሱ፡፡
የውሃ ላይ ሰርዶ ውሃ የተመቸው
ናልኝ ያገሬ ልጅ የማትሰለቸው፡፡
ያንን ማዶ ጋራ አሳርሰዋለሁ
ሎሚና ትርንጎ አስተክለዋለሁ፡፡
ትርንጎውን ላንተ ሎሚውን ለራሴ
እነ ራስ ከበደ ተዋጉ አሉ ደሴ፡፡
እነ ራስ ከበደ ተቀምጠው ባልጋ
ሸጉ ያንተ ወዳጅ በምን ልቤ ይርጋ፡፡
ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ
ያገር ሽማግሌ የገላጋይ ያለህ፡፡
አዲስ ቤት ሲሠራ ይላል ማገር ማገር
ሸግዬ አልመጣም ወይ ከሄደበት ሐገር፡፡
የሄደበት ሀገር አቢራው መላሙ
ያረፈበት ጥላ ዛፉ መለምለሙ፡፡
አቢራውን ስሜ ዛፉን ተሳልሜ
እሞትልሃለሁ ሁለት ወር ታምሜ፡፡
ታምሜ ታምሜ ስሆን ገመምተኛ
አገረሸህ አሉ ደግሞ ሁለተኛ፡፡
አታሞውን ምቺው በግራው እጅሽ
አንጀት የሚበላ ወዳጅ እንዳለሽ፡፡

ውሃ ወርዶ ወርዶ ወንዙ ያረገርጋል
ሙሃባ ነው እንጂ መልክ ምን ያደርጋል፡፡

5. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

ሲታመሙ ታመው ሲሞቱ ካልሞቱ

በምን ያስታውቃል ባልንጀራነቱ፡፡
እቱ ባልንጀሬ ልንገርሽ ስሞታ
አዲሱ ማተቤ ተቃጠለ ማታ፡፡
የሸግዬን ነገር ስቋጥር ስፈታ፡፡
የሸግዬን ነገር ተይው አታንሺው
ጫር ጫር አድርገሽ አፈር አልበሺው፡፡
የቀይ በሬ እበት የቀይ በሬ እበት
ናፈቀኝ ዳገቱ የምንውልበት፡፡
ገደም ገደም አለ ሰው ሁሉ ሊተኛ
እኔ ብቻ ቀረሁ ያንቺ ወሰንተኛ፡፡
የብርቱካን ልጫ የሎሚ ጭማቂ
እንደምን ከርመሃል የእኔ ተናፋቂ፡፡
አታሞውን ምቺው በግራው እጅሽ
አንጆት የሚበላ ወዳጅ እንዳለሽ፡፡
አንጆት የሚበላ ወዳጅ ምናባቱ
ጎራዴው ሲመዘዝ ይላል ባዛኙቱ፡፡
እንኳን ባዛኙቱ ይበል በሥላሴ
እኔ እወደዋለሁ እስኪወጣ ነፍሴ፡፡
ብወደው ባልወደው ማን ይጠይቀኛል
ውሃ እንደ ቁም ነገር ስጠጣው ያንቀኛል፡፡
ውሃ እንደ ቁም ነገር ስጠጣው ካነቀኝ
እህል ብቀምስበት ዋ እኔን ባደረገኝ፡፡

5. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እንዴት ነው ታች ለሚ የበርበሬው ተራ
የዘንድሮው ፍቅር እናትም አይፈራ፡፡
እገልዬ እገሌ አንድ ጊዜ ምታና
እገልዬ እገሌ አንድ ጊዜ ምታና
ውሰድ ቀለበቴን ከአንገቴ ፍታና፡፡
ያንገቴንም አይደል የትንሽ ጣቴን
እንደ አንተም አልወዳት ወላጅ እናቴን፡፡
እኔስ ከቅድሙ አሁን ተሻለኝ
የገለቤ ልጆች መጡ መሰለኝ፡፡
ከጥርሶቹ መሃል እርከኑ ላይ ቆሜ
እገልዬ እገሌ ስል አድራለሁ በህልሜ፡፡

የሰንበሌጥ ጉቶ ወጋኝ ተረከዜን
ሁሉም ሰው አወቀው ባንተ መተከዜን፡፡
እምቧ ስል እምቧ ስል ደረስኩ ከደጃፋቸው
ከቤት አይወጣም ወይ ሀረጉ ልጃቸው፡፡
ሀረጉ ልጅሁን አስጠይቁልኝ
ሳልወደው ወደደኝ ሳልጠላው ጠላኝ፡፡
የወግዲ ሎሚ ወደ ለሚ አዝሚል
እንኳን የወደደህ ያየህ ዓይኑን ታሚል፡፡
ውሃ የቡይቱ ውሃ የቡይቱ
ዘመም ዘመም አለ መፍረሱ ነው ቤቱ፡፡
ቢሻው ቤቱ ይፍረስ ጥማዱ ይፈታ
አንተ አይደለህም ወይ የልቤ በሽታ፡፡
የልቤ በሽታ የልቤ ኩራቱ
ይወለድ የለም ወይ ሽጋ በየቤቱ፡፡
ሽጋ የወለደ ዘሩ ሽጋ ይሁን
ጧት የወጣው ልቤ አልገባም እስካሁን፡፡
7. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ቅዳሜ ቅዳሜ አልቀርም ከእንጨት
ከጎራው ላይ ሆነህ ጥራኝ በዋሽንት፡፡
አልቀርም ከእንጨቱ ብዬ ስነግርህ
ያልጋ ጠገግ ልቁረጥ ብለህ በመጣህ፡፡
እርጋልኝ እርጋልኝ እርጋልኝ መራቱ
በሌሊት ጨረቃ በቀን ጀንበሪቱ፡፡
ጀንበሪቱ ገባች ተወረወረች
አዳራሹን አልፋ የልፍኙ ገባች፡፡
አዳራሽ ገብቼ የልፍኝ ስሚገት
አንተን አንተን ስል ነው የተረታሁት፡፡
እኔ ካዳራሹ ከእልፍኙ ምን አለኝ
ሽጋ ልጅ ብቅ በል ካንተ ጉዳይ አለኝ፡፡
ከጎድጓዳ ቦታ ይቆረጣል ሞፈር
ለሚና ጫቀታ ዋልካና ቀይ አፈር
ምንጊዜም ያንተው ነኝ እስኪጫነኝ አፈር፡፡

8. አያ በለው በለው □ረ በለው በለው
እዩት እዚያ ማዶ ነጭ ላም ቁማለች
ማርና ወተቷን ትታለበዋለች፡፡

ወተቱን አኑሬ ማሩን ብቀምሰው

ሰለምለም ሰለምለም እንደ ሞተ ሰው፡፡

የሞተ ሰው እንኳን ይሄዳል በታንኳ

ልቤን ስደድልኝ ከኩሌታው እንኳ።

በረሃ ደፋር ነው እንደ አዳል ነጋዴ
አያወላውልም ይወድሃል ሆዴ።
አይመነጠርም ሎሚ ቢዳንት
ወዳጀ ታሞብኝ ወንድሜ ይሙት።
አባይ ወዲያ ማዶ ማሽላ ዘርቼ
ወፍ ጠረጠረው መሻገሪያ አጥቼ።
ኧረ ወፍ ኧረ ወፍ ወፍ መከራ ነው
እሽ በል ያገር ልጅ ፍቅር የጋራ ነው።
ውሃ እንኳን ነፍስ ዐውቆ ለብሷል አረንጓዴ
እንኳን ሸመልና ቢመዘዝ ጎራዴ
እኔ ካገሬ ልጅ መቼ ቆርጦ ሆዴ።
ከለላ ካፋፉ ብርሌ ተክዬ
ስባንን አድራለሁ ተሰበረች ብዬ።
ዝናብ ጥሎ ጥሎ ክፉ ክፉ ባሰኝ
እባክህ ሸማዬ ከሸማህ አልብሰኝ።
እንኳን ከሸማዬ ልበሽ ከገላዬ
አንቺ አይደለሽም ወይ ጥና በሽታዬ።
እሽት እሽት አድርገሽ ላኪልኝ ቀይ ሎሚ
ልበላው አይደለም ለልቤ አስታማሚ።
እርኩም አጎንብሶ ይለምናል ዕድሜ
በሽታ ሰጠሽኝ እስከ ዘላለሜ።
የጨለማ መንገድ አላወቅም ነበረ
ፍቅርሽ መብራት ሆኖ ይመራኝ ጀመረ።
ከብቶች አግዳለሁ የቀይ ቡራቡሬ
ያለሽበት ሀገር ልምጣ ወይ በርሬ።
ከደጅሽ ይቅበሩ አመልማሉ ምሰው
እንዳይቆረቁረኝ አንቺን አንተርሰው።
አንዱም ዓይኔ ጠፍቷል አንዱም ጥሎበታል
እልም ድርግም ይበል ሁሉንም አይቶታል።
ተላኪኝ ተላኪኝ ተላኪኝ ድመት
ባንቺ ያምራልና ከሰው ቤት መግባት።
ቤትሽና ቤቱ ማዶ ለማዶ ነው
የምንጠጣው ውሃ ምንጫችን አንድ ነው።
የጨርቁ ማጠቢያ ሃለልቱ ነው ወንዙ
እመጣልሻለሁ ለማጠማዘዙ።
የወለቃ ውሃ ውስጡ ቦረቦር
ጧት አይቼህ ማታ ይመስለኛል ወር።
ጥርሱን ጉራማይሌ ተወቅሮት ቢመጣ

ታልታመም ሞትኩኝ ሳልሞት ነፍሴ ወጣ፡፡
ጉራማይሌ ጥርሱ እያለ ብልጭ
ልቤን አቃጠለው እንደ ሰናፍጭ፡፡
ቀይ ሎሚ ቀይ ሎሚ ቀይ ሎሚ ለሽታ
የጎረቤት ወዳጅ ህመም ነው በሽታ፡፡

9. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ያንን ማዶ ጎራ አሳርሰዋለሁ
ሎሚና ብርተካን አስተክለዋለሁ፡፡
ብርቱካኑን ላንተ ሎሚውን ለራሴ
እነ ራስ ከበደ ተዋጉ አሉ ደሴ፡፡
እነ ራስ ከበደ ተቀምጠው ባልጋ
ፈረሰኛ ወርዶ እግረኛ ሊዋጋ
ያንተ ወዳጅ ሆኜ ልቤ እንደምን ይርጋ፡፡
ከረጅም ሸንበቆ ከጫፉ ወድቄ
ተሰበርሽ ይሉኛል ምን አለሁ ደቅቄ፡፡
ተሰበርኩ እንዳልል እጅ እግሬ ደህና ነው
የተወረወረው ልቤ ብቻውን ነው፡፡
ዓባይ ወዲያ ማዶ ሸንብራ ዘርቼ
ወፍ ጠረጠረው መሻገሪያ አጥቼ፡፡
ኧረ ወፉ ወፉ ወፉ መከራ ነው
እሺ በል ዓይናሙ ፍቅር የጋራ ነው፡፡
ኧረ ፍቅር ፍቅር ፍቅር አሊ-ባሶ
ሲጀምሩት ማር ማር ሲጨርሱት ኮሶ፡፡
ሸጉ እንደ ብሳና ክረምት አይወድልህ
ከሆዴ ግባና መስከረም ይንጋልህ፡፡
መስከረም ሲነጋ ህዳር ሲታጠን
እልክልሃለሁ ልቤን በሳጥን፡፡
ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ
ያገር ሽማግሌ የገላጋይ ያለህ፡፡
ያገር ሽማግሌ አያጣም ኩነኔ
አሁን ምን አልኩኝና ፈረዱብኝ በእኔ፡፡
አሁን ምን አልኩና አሁን ምን ወጣኝ፤
በጥርሱ እየሳቀ በዓይኑ የሚቆጣኝ፡፡
ማሽላ ዘርቼ ጥንቅሽ አልዘራሁም
አንተን የሚያስረሳ ሰው አላገኘሁም፡፡
አንተን የሚያስረሳ አገኘሁ መድሃኒት
እህልና ውሃ እንቅልፍና ሌሊት፡፡

10. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የወፍ ሥጋ በላሁ በቅመም ተሠርቶ
ፍቅርህ አሳበደኝ በደም ሥሬ ገብቶ፡፡

እስኪ መርፌ ስጡኝ የምሞረከዘው

አቀበት አይወጣም ፍቅር የያዘው ሰው፡፡
የሰማይ ስባሪ ከማን ቤት ይገኛል
አሁን መናፈቄን ማን ይነግርልኛል፡፡
አንበሳው ቢታሰር ከበራፍህ ላይ
ዘንዶ ቢጠመጠም ከወገብህ ላይ
አንተ ልከህብኝ እቀራለሁ ወይ፡፡
እዛ ማዶ ሆኖ ፉጨቱን ቢለቀው
ከነ ሊጤ ወጣሁ ሳልለቃለቀው፡፡
ማሽላ ዘርቼ ጥንቅሽ አልዘራሁም
እሱን የሚያስረሳ ሰው አላገኘሁም፡፡
እንግዲህ ይበቃል ወረቀት አለቀ
እስክምንገናኝ ልቤ ተጨነቀ፡፡
ፍቅር ሲጀምሩት ይላል ፍራት ፍራት
ከጀመሩት ወዲያ አያስበላም እራት፡፡
ትምህርት ቤት ሆኜ ትዝ ብትለኝ
በአማርኛው ደብተር ሂሳብ ሠራሁኝ፡፡
አንተን ተመልክቼ ሌሎቹን ሳያቸው
ድንጋይ ይመስሉኛል ህይወት የሌላቸው፡፡
ዝንጆሮ በገደል ወድቆ አይሰበርም
እኔን ያንተ ፍቅር ሳይገለኝ አይቀርም፡፡
እንኳን ዐቅም ላገኝ አንተን የሚያስረሳ
አድርጌህ የለም ወይ ራትና ምሳ፡፡
ልንገርህ እውነቱን ሁሉም ነገር ያምራል
የፈካው ፍቅራችን አሸቶ ያፈራል፡፡
ይሄ ፍቅር ማለት እኔንም ጀመረኝ
እንዳልፈላ ሽሮ ልቤን ገመጨረኝ፡፡
ራዲዮ ሲዘፍን ማንሳራሳር ያበዛል
እኛ ከተዋደድን ማን አባቱ ያዛል፡፡
የደረቀ ሎሚ አይመጠመጥም
ፍቅር የያዘው ሰው አርፎ አይቀመጥም፡፡
ትምህርት ቤት ግቢ አበባ በቀለ
እስክምንገናኝ ልቤ ተሰቀለ፡፡
አሻግሬ አየሁኝ ማዶ ማዶውን
ሣር ቅጠሉ ሁሉ መሰለኝ አንተን፡፡

እራቴን ስበላ ትዝ ብትለኝ
ያቀረብኩት ትሪ ከፊቴ ጠፋኝ፡፡

የቻይና መኪና ሲሄድ እልም ነው
እኔ ላንተ ብዬ ትምህርቴን ልተው ነው።።

6.10 የከንፈር ወዳጅን ማወደስ በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
   አታሞውን ምቺው አርጊው ደንቢ ደንቢ
   እንደወለደች ላም አታሰኚው እምቢ።።
   እምቢ ስል እምቢ ስል ደረስኩ ከደጃቸው
   ከቤት አይወጣም ወይ ሐረጉ ልጃቸው።።
   ሐረጉ ልጃቸው ሻሽ የጠመጠመው
   ልቤን እንደ ቆሎ አሽቶ ቆረጠመው።።
   ልቤን እንደ ቆሎ አሽተህ ቆርጥመህ
   እንጨት ይሰበርልህ ውሃ ይቀዳልህ።።
   ማሽላ ቢቆርጡት አገዳው ቀሪ ነው
   እንጫወት ሽጌ ዓለም ኃላፊ ነው።።
   እንጫወት ሽጉ እንጫወት በጣም
   ከእንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም።።
   ልጅነት ልጅነት ልጅነት ዓለሙ
   በወርቅ አይገዛ በሠላሳ ዓመቱ።።
   እንኳን በሠላሳ ቢገዛ በመቶ
   እኔ እገዛው ነበር ልጅነት ተገኝቶ።።
   ፍቅር የሚባለው አደንዛዥ በሽታ
   አወይ ምን ይሻላል የተያዝኩ ለታ።።
   እራሴንም ቢያመኝ እታገመዋለሁ
   ሆዴንም ቢቆርጠኝ ግራዋ እጠጣለሁ
   የፍቅርን ነገር እንዴት አደርጋለሁ።።
   የፍቅርን ነገር አይታችሁ ገምግሙት
   የልብ በሽታ ነው የማይታገሙት።።
   እንዴት ያደርጉታል የልብን ህመም
   ማጭድ አይገባበት በጅ አይታረም።።
2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
   ቁና ሙሉ አዴስ ቁና ሙሉ አዴስ
   ከደሴ ጀምሮ ቦረና ድረስ
   ፍቅር ያሰረውን አይፈታውም ቁስ።።
   ኧረ ቁሱ ቁሱ መምሬ መምሬ
   የፍቅር መድሃኒት ክተብልኝ ለኔ።።
   የፍቅር መድሃኒት እኔም ቸግሮኛል
   እራሴ ላይ ሆኖ ይወዘውዘኛል።።
   ኧረ ቁሱ ቁሱ መምሬ መምሬ
   ወዶ የሞተ ሰው አለው ወይ ኩነኔ።።

ሸጉ ታሚል አሉ ሂደን እንየው
ሂጂ አይቼው መጣሁ ብሎም ደግ ነው።።
እጓሳው ወጥቼ በረዶ ፈላና
እናትና አባቴ ዋኔ ልጄ አሉና
እህትና ወንድሜ የናት ልጅ አሉና
ደግሞም ለሸግዬ ተላከበትና
ሎሚና ትርንጎ ቅሬዬን ጫነና
እቀብሬ ላይ ሆኖ ቢለኝ ደማሚቱ
የሞትኩት ተነሳሁ የፍቅር ጥናቱ።።
ጥቁር ሰው አጠብኩኝ የማይቀላውን
አሸዋም ፍጭ አሉኝ የማይልመውን
ድንጋይ ቀቅይ አሉኝ የማይበስለውን
ሸግዬን ተይ አሉኝ የማልተወውን።።
እወርዳለሁ ቆላ እጠጣለሁ አምቦ
ፍቅር ተጠንስሷል በእንሥራ በገንቦ።።
በእንሥራ በገንቦ በትንሽ ኮሪት
ሳልቀምስለት መጣሁ ወይ እኔ ልጂት።።
እኔ እንኳን ልጅቷ ገና እምወጣው
ሸማግሌው ያብዳል ቡን እሚጠጣው።።
አንተ ሸማግሌ ምን ያሳብደሃል
ተባራሪ ፍቅር ገደል ይሰድሃል።።
አፋፍ ላይ ዘልቄ ኮለል እንደ እንቧይ
ያዙኝ እወድቃለሁ እሸግዬ ላይ።።
ሸግዬ ሸግዬ ሸግዬ ማርያም
እኔ ላንተ ብዬ ልግባ ወይ ገዳም።።
ገዳም ገዳም ቢሉኝ ቤተስኪያን ነው ብዬ
የሰው ገዳም አለው እረ እናንተ ሆዬ።።
ኧረ እናንተ ሆዬ ሰው አይድንም ታሞ
ያምናው በሽታዬ አገረሸ ደግሞ።።

6.11 የመደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪን ማፍቀር በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

አንቺ የሰማይ ኮከብ ነይ ውረጅ አልወርድም

እኔ በሰው ወዳጅ አልወራረድም።።

እንጨት ሰባብሬ ይዣለሁ በራሴ

የተማሪ ፍቅር ሐምሌና ነሐሴ።።

ሐምሌና ነሐሴ ለኔ ምኔ ነው

ይመጣል መስከረም የሚያጫውተው።።

ጸጉርህ ABCD በቅባት ያበደ

እኔ ባንተ ፍቅር አንጀቴ ነደደ።

400 ፍቅር 300 ትዝታ

አስቀይሜህ እንደሁ ሦስት ጊዜ ይቅርታ።

የጥቁር ላም ሥጋ የለውም ኩላሊት

ትዝ ትለኛለህ በደረቀ ሌሊት።

አታሞውን ምቺው በግራው እጅሽ

አንጀት የሚበላ ወዳጅ እንዳለሽ።

አንጀት የሚበላ ወዳጅስ ነበረኝ

ተማሪ ሆነና ርቆ አስቸገረኝ።

የተማሪ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ

ጎራዴ ሲመዘዝ ይላል ባዛኙቱ።

እንኳን ባዛኙቱ ይበል በሥላሴ

እኔ እወደዋለሁ እስኪወጣ ነፍሴ።

6.12 የመለያየትን አስከፊነት በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

የሰማይ ዳመና የተረገረገው

ያንተን ወዶ መሄድ ለኔ ባደረገው።

ያንተን ወዳ ወዳ የእኔን ወዲህ ወዲህ

እንደተለያየን ቀረን ወይ ከእንግዲህ።

እንደተለያየን ምነው መቅረታችን

እኔስ እመጣለሁ ለክራሞታችን።

እንኳን ያንተ ፍቅር ተጨምሮበት

እንዳውም ይከብዳል ሰኔና ግንቦት።

ሰኔና ግንቦት የሚሉት ወራት

እንኳን ለባልንጀር ይለያል ከእናት።

ውሃ ወርዶ ወርዶ ማረፊያው ዓባይ
እናት ወልዳ ወልዳ ለሰው አገልጋይ፡፡
ያገዳ ማገዶ ያገዳ ማገዶ
ልቤ ተሻገረ ካባይ ወዳ ማዶ፡፡
ካባይ ወዳ ማዶ አባይ የለም ወይ
ሞትና መለየት አንድ አይደለም ወይ፡፡
ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው
ሞት አይሻልም ወይ ቁርጡ የታወቀው፡፡
እቴ ሙሽሪት አታልቅሽ አይበጅም
ሴት ልጅ ከእናቷ ጋር እድሜዋን አትፈጅም፡፡
መጫኛውን አንሱት ጅብ እንዳይበላው
ሙሽሪት ከሄደች ፈላጊም የለው፡፡
የሙሽራው አባት እህቱን አደራ
የሙሽራው እናት እህቱን አደራ
የሙሽራው ወንድም እህቱን አደራ
የሙሽራው እህት እህቱን አደራ
ሰጥቻችኋለሁ ያለ ባልንጀራ
ወገቧ ጭራ ነው አይችልም እንሥራ፡፡
ያለ ባልንጀራ ያለ ትልቅ እህት
ስትገባ ስትወጣ የምታጫወት፡፡
እቴ ያገሬ ልጅ ሥሪ ጉልቻ
ከእንግዲህ ቀረ የእናት እንጎቻ፡፡
እህቶች ተነሱ ታጠቁ ትላለች
ይች ሴት ወይዘሮ ወደ የት አስባለች፡፡

2. አያ በለው በለው ሽረ በለው በለው
የወለቃ ውሃ ውስጡ ቦረቦር
ጧት አይቼህ ማታ ይመስለኛል ወር፡፡
ሸንበቆ ቢያፈራ የለውም አበባ
ልቤ ገሰገሰ ወደ አዲስ አበባ፡፡
አዲስ አበባ ላይ ታስሬያለሁና
ያገር ልጅ አስፈታኝ ደብዳቤ ላክና፡፡
የላከው ደብዳቤ መድረሱን ደርሶኛል
እንባዬ እያነቀኝ ማንበብ ተስኖኛል፡፡
ዛሬስ ያገሬ ልጅ ምን ይሏል በሆዱ
እቴ ደህና ሰንብቺ ሳይለኝ መሄዱ፡፡
አትባባ ሆዴ አትበል ናድ ናድ
ወዶ መለየቱን አድርገነዋል ልማድ፡፡
እንግዲህ ላልበላ ቀይ ሎሚ ልጩ
መለየትን ያህል አደጋ አስቀምጩ፡፡

3. አያ በለው በለው ሽረ በለው በለው

ደሴ ዙሪያው ገደል በሩ በዘበኛ
ምነው ሀቹ ራቀ የእኛ መገናኛ፡፡
የሰማይ አሞራ ግንባረ ቦቃው
ዋ ብሎ መቅረትን ማን አስተማረው፡፡
ዋ ብሎ ዋ ብሎ ዋ ብሎ ሲያበቃ
ደሴ ውረጅ አለኝ ወንበሩን ጥየቃ፡፡
ወንበሩን ጠይቂ ወዲህ ስመለስ
አባቱ በበቅሎ ልጁ በፈረስ፡፡
ሸኝቻቸው መጣሁ ወግዲ ድረስ፡፡
ወግዲ ካፋፉ ሁለት ዛፎች አሉ
አትገደፏቸው ልብ ይሰውራሉ
ሰውረው ሰውረው ገደል ይሰዳሉ፡፡
ገደሉ ተንዶ ተይሏል በገመድ
አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ፡፡
እኔስ እበላለሁ የዘመድ አደራ
ዓይን ዓይኑን እያየሁ ከጅመሬው ጋራ፡፡
የጅመሬው ጎፍላ ወርዷል በደረቱ
ጥርሱ ይርገፍና ከነውቅራቱ
ዓይኑ ይርገፍና ብረቱ ብረቱ
ወዳጁ ነኝ እንጂ አይደለሁ ጠላቱ፡፡
ዝናብ ጥሎ ላይጥል እያጉረመረመ
ከምወደው ልጅ ጋር ለይቶኝ ከረመ፡፡
ሸኝቼው ነበር በነጭ ፈረስ
እገልዬ አበሉ በደህና ቢመለስ፡፡

4. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
የውሃ ላይ ቧቧ የውሃ ላይ ቧቧ
እገሊትዬ እገሌ እኔስ ሆዴ ባባ፡፡
አባቷን እሠሩት እላይኛው ማገር
እናቷን እሠሯት እታችኛው ማገር
እሜቴን /እገሌን/ ሰደዷት ከማታውቀው ሀገር፡፡
እሷስ ሄደች ሄደች ጎራውን ጨርሳ
ብቅልና ጌሾ በሆዷ ጠንስሳ
እንዳይበጠበጥ ብቅሉን አሳንሳ፡፡
ውሃ ላይ ሰርዶ ስፍራ የተመቸው
እንትናዬ እንትና የማትሰለቸው፡፡
የከረረች ሎሚ የከረረች ሎሚ
እንትናዬ እንትና በደህና ክረሚ፡፡
እንትናዬ እንትና እቴ የበታቹ
ከጆሮዬ ላርግሽ እንደ ጉትቻዬ
የጆሮ ጉትቻ ቢያወልቁት ይወልቃል

የእንትናዬ ፍቅር በስንት ዓመት ያልቃል፡፡
እገልዬ እገሌ እቴ አብረን እቴ አብረን
ሞት እንኳን ቢመጣ አብረን ተነባብረን፡፡
ዋለለ ዋለለ ዋለለ ባላገር
አልወጣም ወይ ሸጉ ከሄደበት ሀገር፡፡
የሄድክበት መንገድ አፈሩ መላሙ
ያረፍክበት ጥላ ዛፉ መለምለሙ
አፋፉ ዘልቂ ልበልህ ዓይናሙ፡፡
እናት አትልም ወይ ልጄ ገና ናት
አባት አይልም ወይ ልጄ ገና ናት
ቅዳሜ ለምኖ እሁድ ሲወስዳት፡፡
ከእንግዲህ የሰው ቤት ተጠንቅቆ ነው
ባጡም ግድግዳውም ተናጋሪ ነው፡፡
የኩባያ ወተት የለውም አረፋ
ካንተ ከመለየት ህይወቴ በጠፋ፡፡
ካላጉረመረመ አይጥልም ዝናቡ
አንዳንድ ቀን እንኳን ብቅ በል ዓይናሙ፡፡
አንዳንድ ቀን እንኳን ብቅ አትልም ወይ
የሰው ልጅ በናፍቆት ትገድላለህ ወይ፡፡
የሰው ልጅ በናፍቆት ምን ብዬ እገድላለሁ
ሰኞ ለማስገኞ እዘልቅላታለሁ፡፡
ሰኞ ለማስገኞ ለእኔ ምኔ ነው
ይምጣ እሁድ ቅዳሜ የማጫውተው፡፡
አጫውተዋለሁ ደርቤ ደርቤ
ቁመቴ እንኳን ቢያጥር የኮራ ነው ልቤ
ኧረ ልቤ ልቤ ልቤ ምን ትላለህ
ካለው ልመድ እንጂ ከሄደው ምን አለህ፡፡
5. በለው በለው ኧረ በለው በለው
እኔስ እሄዳለሁ ጋራ ጋራውን
አገኘሁ እንደሆን የወደድኩትን፡፡
ትሄዳለህ አሉ በረጅም ጎዳና
ለእግርህ ጫማ ልሁን ለራስህ ዳመና፡፡
ለግርህ ጫማ እንዳልሆን እሾህ ይወጋኛል፣
ለራስህ ዳመና መሆን ይሻለኛል፡፡
ከራስህ ላይ አርገኝ ከሚዶህ በላይ፣
ካርቲው ካሽኩቲው እበልጣለሁ ወይ፡፡
የልጅ መንገደኛ አይችልም ጸሐይ
ሸጋው ጥላ ይገፍ ልከተልህ ወይ፡፡
የከንፈር ወዳጁን የልጅነቱን
ሳልሰናበተው ሄድኩኝ ድንገቴን

ሳልሰናበተው ሳይነግረኝ ቁርጡን
ወይ እንዲመነኩስ ወይ እንዲመንን፡፡
እመነኩሳለሁ እመንናለሁ ስል
አገኘሁ ጠይም ልጅ አንተን የሚመስል፡፡
ከሳይንት ወዲያ ስሙ ነው ቆተት
አይመነጠርም ሎሚ ቢዳንት፡፡
አይገደገድም ያንበሳ ቁርበት
ጨዋታው ቀርቶብኝ ዓይኑን ባየሁት፡፡
አድሩሱን ከደሴ ቡና ከሲዳሞ
ያለያየን ጌታ ያገናኘን ደግሞ፡፡
ምን አላህ ሻተብን ይሄን መለያየት
ግማሹን በመሄድ ግማሹን በመሞት፡፡
የሚጠፋ ባትሪ ከልቤ ተክለሽ
ምን ጨለማ ቢሆን ትታይኛለሽ፡፡
በረጅም ምንሽር ይታደናል ዝሆን
ዓይኔን ልላክልሽ ምስጢር ታውቂ እንደሆን፡፡
ከእንግዲህ ላልበላ ቀይ ሎሚ መልጩ
መለየትህን ያህል አደጋ አስቀምጩ፡፡
ይሄ ወዳጅ ማለት ምን ዕድል አነሰው
አርሞ ኮትኩቶ አሳድጎ ለሰው፡፡
ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ
ካለው ልመድ እንጂ ከሄደው ምን አለህ፡፡
ሐምሌና ነሐሴ እንደ ወዲያኛው
ልቤን ክፍት ክፍት አለብኝ ምነው፡፡
የምንጃር ነጭ ጤፍ የጀግኖቹ ምሳ
የት አገኛሻለሁ ብወድቅ ብነሳ፡፡
ያንን ማዶ ጎራ አላህ ይናደው
የሸግዬን አገር ጎራ ጋረደው፡፡

6. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

እልክልሃለሁ ሁለት ወረቀት
አንዱን ለሠላምታ አንዱን ለናፍቆት፡፡
እኔ በቁመናው ቤት አልሠራበትም
አሁን ተነስቼ እሄዳለሁ የትም፡፡
ሸዋ ነው ሸዋ ነው ሸዋ ነው በረሃ
መጥቼ እንዳላይህ አቅም የለኝ ድሃ፡፡
አቅም የለኝ ድሃ አቅም የለኝ ድሀር
የሰው ፍቅር ይገፍ ሸግዬ እንዴት ልሁን፡፡
ፍቅርህ ቶሎ ደራሽ ጥራጊ የሌለው

አትሂድ ዓይናሙ እኔ መሞቴ ነው፡፡
እንጀራው ተጋግሮ እሰስኪለሰልስ
ወጡ ይሠራና እስኪ ይተንፍስ፡፡
እንጫወት ሸጉ እስክዚያው ድረስ፡፡
ያገዳ ማገዶ ያገዳ ማገዶ
ልቤ ተሻገረ ከዓባይ ወዲያ ማዶ፡፡
ከዓባይ ወዲያ ማዶ ዓባይ አለ ወይ
ሞትና መለየት አንድ አይደለም ወይ
ሞትና መለየት ምን አንድ አደረገው
ሞት አይሻልም ወይ ቁርጡ የታወቀው፡፡
አገራችን ቆላ ማማችን እንኮይ
ሸጉ በሰው ነገር ተቀየምከኝ ወይ፡፡
ሸጌ በሰው ነገር ከተቀየምከኝ
ገና ሳንጀምረው አይሆንም ባልከኝ፡፡
ገና ሳንጀምረው ሳንደረድረው
እንደ እኔ እና እንደ አንተ የሆነ ማን ነው፡፡
እንደ እኔ እና እንደ አንተ የሆነም አላየሁ
እንደ አደረ ሬሳ በእንባ ተለያየሁ፡፡
መሄዱን ይሄዳል የሴትዮዋ ልጅ
ሳይሰናበተኝ ብዬ አማሁት እንጂ፡፡
ሳይሰናበተኝ ሳይነግረኝ ብልሃቱን
እንደ ልጃገረድ እንደ ደፋ አንገቱን፡፡
አይዞህ ያገሬ ልጅ አንገትክን አትድፋ
ዓባይ እንኳን ጎድሏል እንዲያ ሲደነፋ፡፡
ዓባይም ጎደለ ጭረቻውም ታዬ
አይገናኝም ወይ ድንገት የተለየ፡፡
ተለየች ይሉኛል ወድጄ አልተለየሁ
የፍቅር ምርኮኛው ዙሬ ዙሬ እያየሁ፡፡
የዳገት ዝንጀሮ አይበላም ሬት
ልቅም እንደ ስንዴ ግፋ እንደ ወተት
እንደናት እንዳባት እንደ ወንድም ሞት
እንዲህ መስሎ ታየኝ ካንተ መለየት፡፡
7. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ዋርካዬ ያየና ዋርካዬ ያየና
ፍቅር ምን ያደርጋል መለየት አለና፡፡
ኧረ ፍቅር ፍቅር ፍቅር አሊባሶ
መጀመሪያው ማር ማር መጨረሻው ኮሶ፡፡
ይመራል ይላሉ ኮሶ መጠጣት
የሚመርስ ባዩ ወዶ መለየት፡፡
መለየት መለየት ይለይ አባቱና

ምጣዱ ነው ብዬ ሌማቱን ጣድኩና፡፡
እባክህ ሌማቱ አትንደድብኝ
የልጅ መንገደኛ ጦም አዳሪ ነኝ፡፡
የልጅ መንገደኛ ስንቁ የተቦካ
አንጫወትም ወይ እስኪጋገር ‘ኳ፡፡
እንጀራው ተጋግሮ እስኪለሰልስ
ወጡ ተቀቅሎ እስኪተነፍስ፡፡

8. ያገሬ ልጅ ና ና የወንዜ ልጅ ና ና

ጫካ ገብቻለሁ አሳየኝ ጎዳና፡፡
ተው አንተ ጎዳና ተው አንተ መንገድ
አሁን ሰው አሁን ሰው አሁን ሰው ውለድ፡፡
አሁን ሰው አሁን ሰው መውለዴንም እንጃ
እንዳው ጎዳና ነኝ የከፋው መሄጃ፡፡
ጨረቃ ቢወጣ የነጋ መስሎኝ
ካውላላው ሜዳ ላይ ጅብ አቆራርጦኝ
ኧረ ጅቡ ጅቡ አታቆራርጠኝ
ካገሬ ወጥቼ እሰው አገር ነኝ፡፡
አወይ የሰው አገር አወይ የሰው ቦታ
ተከለከለ አሉ ሳቅና ጫወታ፡፡
ሳቅም ቢከለከል ጥርስም ቢከለከል
ሸጌን አይቼው መጣሁ አረዳው መካከል፡፡
አረዳም ጉድ አለ እኔም ጉድ አልፈራ
በቅሎም አረገዘች ሸንበቆም አፈራ፡፡
እሳቱን አንድዱት በሰፊው እምድጃ
ፈረሴን ጫኑልኝ ባዲሱ ኮርቻ
ሀረርጌ እወርዳለሁ መመለሴን እንጃ፡፡
መመለሱን እንኳ ቶሎ እመለሳለሁ
የዝንጆሮ መሬት ስንዴ ዘርቻለሁ፡፡
የስንዴ ቡቃያ የሸንብራ ለምለም
ሸጌ ደህና ሰንብት ሰው እንዳይሆን የለም፡፡
የሹም አሽከር ሆኜ ወግዲ ልመራ
ሸጋው ከዓይናሙ ልጅ ስም አይጠሩ ጋራ፡፡
አንተ ዓባይ አንተ ዓባይ የተንጋለልክው
አታሻግርም ወይ የናፈቀ ሰው፡፡
እንኳን አንቺንና የናፈቅሺውን
አሻግረዋለሁ መንገደኛውን፡፡
አንተ መንገደኛ የምትገሰግሰው
ልቤ ተከተለህ ባለንጋ መልሰው፡፡

ትንሽ የኩል ቀለም ትላንት አግኝቻት
የድስት ውሃ አይፈላም ያለ መግላሊት
ጨዋታው ቀርቶብኝ ዓይኑን ባየሁት
አይቸው አይቸው አይቸው እንደመስተዋት
ልሰንብት አልልም ዕለቱን ልሙት
ለአፈር አይደለም ወይ የተሠራሁት፡፡
እቴ ባልንጀራ አንለይም ያልሺው
አሁን ከምን ጊዜው ቃልሽን በላሺው፡፡
እናቴና አባቴ እኔስ ሄድኩላችሁ
ያ ቁራሽ እንጀራ በሬ ይግዛላችሁ፡፡
ያ ቁራሽ እንጀራ የገዛውን በሬ
እኔ እንኳን ባልመጣ እሰማለሁ ወሬ፡፡
የእኔ አፀደ ካሳ ወዳጄን አደራ
የእኔ ዓለምነሽ ታዬ ወዳጄን አደራ
እኔም እመጣለሁ ሳምንትም አልሞላ፡፡
እንጨት ከማሰሪያሽ ከመሰብሰቢያሽ
ኩበት ከመልቀሚያሽ ከመከረቻሽ
ከምንጩ ላይ ወርዶ ውሃ ከመቅጃሽ
ከወፍ መጠበቂያ ወጥቶ ከማማሽ
ና መለስ በል ብለን አጫወትንልሽ፡፡

6.13 ፍቅርን አለመጨረስን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እሄዳለሁ ደሴ አልፋለሁ ለጋምቦ
ፍቅር አዘንብሎ በእንሥራ በገምቦ፡፡
በእንሥራ በገንቦ በትንሽ ኮሪት
ታልጠጣለት መጣሁ እኔማ ልጂት፡፡
አንድ ቁና ሎሚ አይሆንም እራት
ወዳጄ ድኖልኝ ወንድሜ ይሙት፡፡
ወንድም ለምን ይሙት አርሶ የሚያበላ
ወዳጅ ይሙት እንጅ ወዶ የሚጠላ፡፡

አፋፍ ላፋፍ ስሄድ እንደ ሸረሪት

ሸማዬን ወሰዱት በአሥር መደሃኒት፡፡
ካሥሩ መድሃኒት አንዱን አውቀዋለሁ፡፡
ሸማዬን በመላ እመልሰዋለሁ፡፡
ሸማዬን በመላ ስትመልሺው
በጥርስሽ ሳቅ ብለሽ ባይንሽ ጥቀሺው፡፡
እኔስ እሄዳለሁ ከደመናው በላይ
የሞተን አልቀብር የታመመን አላይ፡፡

የሞተን ቀብሬ የታመመ አይቼ
አገሬ እገባለሁ አዋጅ አሰምቼ፡፡
አዋጅ ተሰማ አሉ ትላንትና ሐሙስ
ነጋዴም ይነግድ ገበሬውም ይረስ፡፡
ጎበዝና ቆንጆ ፍቅሩን ይጨርስ፡፡
ጎበዝና ቆንጆ ገና ነው አሳሩ
ውሃው እየሞላ እያደገ ሳሩ፡፡

2. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ቁልቋል ደመ ብዙ ምነው ቅጠል የለው
ጫቀታ የሚሉ አገር ያቀናብኝ ማን ነው፡፡
አዲሱ ፍቅራችን ተቋጨ እንደ ሸማ
አካለ አካለ አካለ መንማና
ሸብ አድርገህ ታጠቀው ይበጠሳልና፡፡
ሸብ እንደ ጎራዴ ሸብ እንደ ጥይት
አይገባበት የለው ፍቅርና ሞት፡፡
ያልሞተበት የለም ያልጎተተ ሬሳ
ጨዋታ ነው እንጂ ሁሉን የሚያስረሳ፡፡
ቤትህና ቤቴ ማዶ ለማዶ ነው፣
ውሀ ማጠጫችን ወንዛችን አንድ ነው፣
አልተገናኘንም ፍቅራችን ገና ነው፡፡

6.14የከንፈር ወዳጅ መቀማማትን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ልጃገረድ ሆኖ አይዋስም ወንፊት
ወዳጄን አትንኪ ነገርኩሽ በሰው ፊት፡፡

ነግሬሽ ነግሬሽ መጨረሻው ጠብ ነው

ልብ ይሰማል እንጂ ጆሮማ ቅጥል ነው፡፡

አታሞውን ምቺው ከፍ ዝቅ አድርገሽ

እነማን ነበሩ ታሰኚናለሽ፡፡

እኛ ባገራችን አንድ ሰው ላንድ ነው

ይሄ ድርብርቡ ቡትቴው ምንድን ነው፡፡

...ሙያ በልብ ነው፡፡

የወዳጄን ወዳጅ ትላንት አየኋት

ከባህር የወጣች ትመስላለች ጃርት፡፡

አንች የኔን ወዳጅ ወየት ዐውቀሽበት

እስማለሁ ብለሽ የቀረሽሽበት፡፡

እቱ ባልንጀራ የደባይ እርሻ ነሽ

የባልንጀራዬን አትይም ውሻ ነሽ፡፡

ውሻ ነሽ ውሻ ነሽ ውሻ ነሽ ጦልጧላ

ከባልንጀራዬ ከቱም አልጣላ፡፡

የነጭ ጤፍ ወፍጮ ይላል እሽም እሽም

ይቆልልሻል እንጂ እኔ አልተውልሺም፡፡

ይቆጭሻል እንጂ ያሸሻል ያሸሻል

የወዳጅ ጉልማ ማን አባሽ ሰጥቶሻል፡፡

እንደ ሰፌድ ቆሎ ካንቀረቀቡሽ

ውሰጂው ሽግዬን ከለመደልሽ

መቼም የሰው ወዳጅ ተበዳሪ ነሽ

በሰኔ አረብራቦ ትመለሻለሽ፡፡

ሰኔና ግንቦቱ የሚሉት ወራት

እንኳን ከባልንጀራ ይለያል ከእናት፡፡

6.15 የከንፈር ወዳጅን ወረተኛነት በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

አሻግሬ ባየው ጎራው ከለከለኝ

ዓይንህ ጥሩ መጣ ተልኳል መሰለኝ፡፡

ወዳጄ ወዳጄ ያምናው ያምናው

ይሄስ የዘንድሮ ወረተኛ ነው፡፡

አንተ ወረተኛ ወረት አይታክትህ

እስኪ መድረሻህን ቁሜ ልመልከትህ፡፡

የዘበናችን ሰው ኮከቡ ዓይነ ጥላ

የወደዱት እንደሁ ፍቅሩ ወር አይሞላ።።

አጋም ፍሬው መልካም እሾሁ መርዘኛ

እንዴት ነህ በሉልኝ ያንን ወረተኛ።።

ያንን ወረተኛ ወረት አይታክተው

እስኪ መድረሻውን ቁሜ ልመልከተው።።

የደሴ ቆርቆሮ እባብ የላሰው

ምን ያዋልልሃል እርጋ ባንድ ሰው።።

ተው እርጋ ተው እርጋ እርጋ ለመሬቱ

ለሌሊት ጨረቃ ለቀን ጀንበሪቱ።።

ጀንበሪቱ ገባች ተወረወረች

አዳራሹን አልፋ ከእልፍኙ ገባች።።

እኔ ከአዳራሹ ከእልፍኙ ምን አለኝ

ይምጣልኝ ሸግዬ ከእሱ ጉዳይ አለኝ።።

ንገረኝ እውነቱን በግልጥ አማርኛ
የእኔ መሆን ከቻልክ የእውነት ፍቅረኛ።።

6.16 የጠፋ ፍቅረኛን ፍለጋ በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው

አንቺ የቆላ ፍየል ቅጠል መልማይ
ጠይም ዘለግ ያለ አላየሽም ወይ።።
ጠይም ዘለግ ያለ እኔ ወየት አይቼ
ቅጠል መቦጥቦጤን መባከኔን ትቼ
ጌቶች መጡ ቢሉኝ ምንትዋብ ወርጂ።።
የምንትዋብ ውሃ ውስጡ ቦረቦር
ጠዋት አይቼው ማታ ይመስለኛል ወር።።
አንተ አባይ አንተ አባይ የተንጋለልከው
አታሻግርም ወይ የናፈቀ ሰው።።
እንኳን አንቺንና የናፈቅሺውን
አሻግረዋለሁ መንገደኛውን።።
አንተ መንገደኛ የምትገሰግሰው
ልቤ ተከተለህ ባለንጋ መልሰው።።

የመኪናው መንገድ መቶ ከዘጠና
በየትኛው መንገድ ተላልፈን ይሆና፡፡
4. አላውቀውም ነበር የጨለማ ጉዞ
ይመራኝ ጀመር ፍቅር ዘንጉን ይዞ፡፡
የበርበሬ ዱቄት አይሆነም ጥቅጥቆ
ካለህበት ሀገር ያምጣልኝ መንጥቆ፡፡
ያለ ቆዳ ጫማ አያምርም ቦላሌ
መሄድ እንዳነተ ነው መከተል እንደ እኔ፡፡

6.17. ፍቅር ላይ እንከን መፈጠርን በተመለከተ የተዜሙ ቃል ግጥሞች

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
ፍቅርህና ፍቅሬ በጋን ተጠንስሶ
ሳይጠጣ ቀረ ስባራው አፍስሶ፡፡
እቱ ሄደሽ ሄደሽ እበሩ ስትደርሽ
ቆንጆዎቹ እንጨት ሄዱ ብለሽ ተመለሽ፡፡
ቆንጆዎቹ አንጨት ሄዱ ብዬ ብመለስ
ይቆጡ የለም ወይ የሸዋው ንጉሥ፡፡
ኧረ ሸዋ ሸዋ ሸዋ ጥቁር መሬት
የቦረና ኑሮ መረረኝ እንደ ሬት፡፡
መረረኝ እንደ ሬት ፈጀኝ እንደ ሳማ
የሚሆን የማይሆን ጆሮዬ እየሰማ፡፡
አባይ እወርዳለሁ ተሸክሜ ሳር
ባንተ አየሁ መከራ ባንተ አየሁ አሳር፡፡
እወጣለሁ ደሴ አድራለሁ ከተማ
የተናገሩትን ያሉትን ልሰማ፡፡
የሞሰቤን ዳገት ዝንጀሮ አይወጣውም
ሰው ከተዋደደ ምቀኛ አያጣውም፡፡
ምቀኛ ምቀኛ ይሂድ በጅማቱ
ያላበደ የለም ሰው በልጅነቱ፡፡
የሰማይ ስባሪ ከማን ቤት ይገኛል
የእኛ መገናኛ ምናብ ይመስለኛል፡፡
አሻግሮ ያየኛል አሻግሮ ያየኛል
ዓይኑ ይፍሰስና ምን አድርጊ ይለኛል፡፡
ዓይኑ ይፍሰስና ብረቱ ብረቱ
ጥርሱ ይርገፍና ከነውቅራቱ
ወዳጁ ነኝ እንጂ አይደለሁ ጠላቱ፡፡
ውሃ ቦይ ለቦይ ውሃ ቦይ ለቦይ
ያሳደጉት ውሻ ይናከሳል ወይ፡፡
ያሳደጉት ውሻ ወትሮም ይናከሳል

አመሉ ነው እንጂ መልኩ ከማን ያንሳል።
የጣት ቀለበቱ አትነቃነቂ
ሰው ነገረኛ ነው ሀገር አስለቃቂ።
ዋለለ ዋለለ ዋለለ ባላገር
አይመጣም ወይ ሽጋው ከሄደበት ሀገር።
አይደመደምም በርበሬ በጎታ
አይጠነሰስም ጠላ በገበታ
ተደጋጋፊ ነው ለሚና ጫቀታ።
ለሚና ጫቀታ የከብት ሀገር ነው
የሚያቆራርጠው የሰው ነገር ነው።
አንተም የሰው ነገር የሰማህ እንደሆን
እንኳን ወዳጅና ጎረቤትም አንሆን።
የጎረቤት ወዳጅ የጓሮ በርበሬ
ዓመት ይለቀማል ሳይሰማ ወሬ።
ዓመት ሁለት ዓመት ይለቀም የነበር
ባንደዜ ተሰማ የያዝነው ነገር።

1. አያ በለው በለው ኧረ በለው በለው
እቴ ባልንጀሪት ልንገርሽ ስሞታ
የሸግዬን ነገር ስቋጥር ስፈታ።
የሸግዬን ነገር አትቋጥሪ አትፍቺው
ጫር ጫር አድርገሽ አፈሩን አልብሺው።
ጫር ጫር አድርጌ አፈሩን ባለብሰው
ያወጣው የለም ወይ የዘመኑ ሰው።
አፋፍ ለአፋፍ ስሄድ እንደ ሸረሪት
ሸግዬን ወሰዱት በአሥር መድኒት።
ካሥሩ መድሃኒት አንዱን አውቀዋለሁ
ሸግዬን በመላ አስመልሰዋለሁ።
የሰንበሌጥ ጉቶ ወጋኝ ተረከዜን
ሁሉም አውቆብኛል ባንቺ መተከዜን።
የደሴ ባህርዛፍ እባብ አይወጣውም
የተዋደደ ሰው እንከን አያጣውም።

3. ሽጌ ለወዳጁ ሎሚ ይዟል በእጁ።
አንተ ወዲያ ማዶ ተይዘህ በሳጥን
እኔ ወዲህ ማዶ ተይገፎ በሳጥን
ብሠራ አያምርብኝ ብሄድ አላፈጥን።
እሄዳለሁ የትም አድራለሁ ከተማ
የተናገሩትን ያሉትን ልሰማ።
የተናገሩትን ያሉትን ሰምቼ
አገሬ እገባለሁ አዋጅ አሰምቼ።
አገራችን ቆላ ማማችን እንኮይ

የሰው ነገር ሰምተህ ተቀየምከኝ ወይ፡፡
የሰው ነገር ሰምተህ ከተቀየምከኝ
ገና ሳንጀምረው አይሆንም ባልከኝ፡፡
ገና ሳንጀምረው የሆነም አላየሁ፡፡
እንደ አደረ ሬሳ በእንባ ተለያየሁ፡፡
አጭር ሰው ቢኮራ የማይረዝመውን
ጥቁር ሰው ቢታጠብ የማይቀላውን
አሸዋ ፍጪ አለኝ የማልፈጨውን
ሸግዬን ተይ አሉኝ የማልተወውን፡፡
አሸዋ ቢፈጩት አይልም አይከረታ
የዓባይ ጥቁር እንጨት መንትያው ተልጧል
ዛሬስ ያገሬ ልጅ ባህሪው ተለውጧል፡፡
ባህሪው ተለውጧል ቂም ይዟል በሆዱ
አገሩ ርቆበት እየገባ ሆዱ፡፡
እቴ ደህና ሰንብቺ ሳይለኝ መሄዱ፡፡
አንቺስ አታለልሺኝ አንቺስ አታለልሺኝ
ሰው የጎረቤቱን አይበላም እያልሺኝ፡፡
ውሃ እንኳን ይኖራል አረንጓዴ ለብሶ
ምነው ታምተን ኖሮ የልባችን ደርሶ፡፡
የወፍ ሥጋ በላሁ ቢጥመኝ መረቁ
መታማት አይቀርም ምን ቢጠነቀቁ፡፡
ሁሉን ተጠግቼ ሁሉን አይቻለሁ
አንቺን የመሰለ ታማኝ አጥቻለሁ፡፡
እምነት ለመቼውም ጥሩ ነገር ነበር፤
የኔ ብቻ ሳይሆን ፍቅር ያንችም ነበር፡፡

4. ሸጌ ለወዳጁ ሎሚ ይዟል በእጁ፡፡

እቴ ባልንጀሬ ጥቁር ማርዳሽን
አብረን አንውልም ወይ እንቁጣጣሽን፡፡
አብረን እንውላለን ብየሽማ ነበር
ያገር ሽማግሌ ምቀኛ ባልነበር፡፡
ያገር ሽማግሌ ቴንሳህን ያጥፋው
ልጃችን ገና ናት አይልም ወይ ሰው፡፡
መረረኝ እንደ ሬት ፈጀኝ እንደሳማ
ክፉ ክፉ ነገር ጆሮዬ እየሰማ፡፡
ቆይ አንቺ ጆሮዬ ነገ እቆርጥሻለሁ
ክፉ ክፉ ነገር ሰምቼብሻለሁ፡፡
አይጠነሰስም ጠላ በገበታ
ተደጋጋፊ ነው ለሚና ጫቀታ፡፡

ለሚና ጫቀታ የልጁ አገር ነው
የሚቆራርጠው የሰው ነገር ነው።።
አንተም የሰው ነገር የሰማህ እንደሆን
እንኳን ወዳጅና ጎረቤትም አንሆን።።
የጎረቤት ወዳጅ የጓሮ በርበሬ
ዓመት ይለቀማል ሳይሰማ ወሬ።።
5. ሸጌ ለወዳጁ ሎሚ ይሏል በእጁ።።
የፏፏቴ ውሃ ፈረስ የረገጠው
ሸግዬ በኔ ሞት ጥርስህን ግለጠው።።
ሸግዬ በኔ ሞት እኔ አፈር ስሆን
አንደዜ ሳቅና ልየው ጥርስህን
አንደዜ ሳቅና በሁለተኛው
ይበቃል ሸግዬ ሰው ምቀኛ ነው።።
ምቀኛ ላመሉ አፉን ያላምጣል
አበጀሁ ደግ አረኩ ቢሉት ምን ያመጣል።።
የደሴ ቆርቆሮ ዝናብ አያፈስም
እኔ ያንተ ወዳጅ ግንብ ነኝ አልፈርስም
ባረባባ ወሬ ሆዴ አይደፈርስም።።
ያቡጀዲ ሸማ የለውም እራፊ
ዓለም ዘወርዋራ ዓለም ቀን አላፊ።።
ዓለም ዘወርዋራ ቀንም አላፊ ነው
ማረኝ ያገሬ ልጅ ልጅነቴ ነው።።
በፍቅራችን መሃል አይግባ ምቀኛ
ተራርቆ ቀርቷል ስንቱ በወሬኛ።።

አሁን ለምንድን ነው የተከዳዳነው

እኛን ያካዳዳን ምቀኛ ብቻ ነው።።

እንደ ሴኮ ሰዓት በዜሮ ተሞልተህ

እንዳንቆራረጥ የሰው ወሬ ሰምተህ።።

ፍየል በቁልቁለት ይመስላል ሰርገኛ

እኛም አንጣላ ደሞ በምቀኛ።።
መካካድ ባይመጣ ቅናት ባይፈጠር
የምስጢር ጓደኛ አንድ ይበቃ ነበር።።
የሰማይ ላይ ኮከብ ብቆጥረው ሠላሳ
ምኑን ቅጠል በላሁ አንተን የሚያስረሳ።።

7 የውቂያ ቃላዊ ግጥም

7.1 ሙገሳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

አያ በሬ ሆዬ አያ በሬ ሆይ አዝማች

1. በርዬ እንዙር በርዬ እንዙር
   የገና ጀንበር ሳይወረወር፡፡

2. አድርገው ድቅቅ አድርገው ገለባ

   ቤታችን ሩቅ ነው በጊዜ እንዲንገባ፡፡

3. በርዬ እሸምድ ጎናቱ እሸምድ

   እናድርገው አመድ
   ያውም በጧቱ ሳይረፋፍድ፡፡

4. በሬ ሆይ በሬ ሆይ በሬ ሆይ

   በርዬ አላንተማ በርዬ አላንተማ
   አይሠራ ማማ አይበጅ አውድማ፡፡

5. የበሬን ገለታ ወሰደው ፈረሱ
   ከኋላው ተነስቶ እፊት በመድረሱ፡፡
   የበርዬን ሞት ቢሰማ ሳይንት
   ሲለቀስ አደረ በአርባ ነጋሪት
   በሺህ መኳንንት፡፡

6. አያ ጎኔ ሆይ አያ በሬ ሆይ

   ያልገዛ ሲነዳህ እምቢ አትልም ወይ፡፡
   ያልገዛ ቢነዳኝ እኔ ምን ተዳዬ
   ካበላኝ ካጠጣኝ ሁሉም ነው ጌታዬ፡፡

7. በርዬ እሹሩሩ ጎንዬ እሹሩሩ

   ጠላትህ ይረሩ
   እንደ አብሽ ቅጠሉ እንደ ጎመን ዘሩ፡፡
   የበርዬን ሞት ቢሰማ ጎንደር
   ሲለቀስ አደረ በጋሻ በጦር፡፡
   ኧረ በሬ ደጉ ኧረ በሬ ደጉ
   እንጀራ አይበላም ካላደገደጉ፡፡

8. እሹሩሩ በርዬ እሹሩሩ
   ብላ ከዳር ዳሩ ጠጣ ከባህሩ፡፡
   በሬዬ እንዳንተ እሚዞር የሚሸከረከር
   እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር፡፡

አሁን የት አለና እንደ በሬ ወንድ
ሞፈር ቀንበር ይዞ መሬትን የሚቀድ፡፡
በርዬ ባንተ ጫንቃ በርዬ ባንተ ጫንቃ

መኪንንቱ ሁሉ መሰለ ጨረቃ
ጋለሞታው ሁሉ መሰለ ጨረቃ፡፡
በሬ ባንተ ላይ
ይመሰላል ጸሐይ፡፡
የበሬን ገለታ እንጫወት ማታ
በሰፊ ገበታ በዋንጫ ጋጋታ፡፡

9. እሹሩሩ በርዬ እሹሩሩ

አንተ በሠራኸው ይኖራል ሀገሩ፡፡
እኔና በሬዬ ባቀናነው ቤት
እምድጃ ቁጭ ብላ ታፈጣለች ሴት፡፡
በርዬ እሹሩሩ በርዬ እሹሩሩ
ያላንተም አይሞላ በየትም ቢዞሩ፡፡

10. በርዬ እሹሩሩ

በሬ ወዳጄ ማሩ፡፡
የበሬው ንጉሥ
እየው ሲቀልስ
እየው ሲመልስ፡፡
በርዬ እሸምድ ጎናቱ እሸምድ
አድርገው አመድ የሚቅመደመድ
እናርገው ገለባ
እጎሞ እሚገባ፡፡

11. ሆ በሬ ሆ በሬ ጅራተ ጉንጉኔ
ቀንደ ቀጫጭኔ፡፡
ኧረ በሬ ደጉ ኧረ በሬ ደጉ
ላንተ ያደግድጉ ለባለ ማዕረጉ፡፡
በሬዬ ያለ አንተማ ጎንዬ ያለ አንተማ
ዓይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ፡፡

7.2 መታተርን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. በሬዬ እንሂድ በሬዬ እንሂድ
ዛሬም እንሂድ ነገም እንሂድ
ካልጠገበ ሆድ ካልጫነ ዘመድ፡፡
የበሬው ንጉሥ ይሄው ሲቀልስ
የበሬው አበያ ይውላል ገበያ፡፡

2 ሆ በሬ ሆ በሬ ሆ በሬዬ እንዙር

ወታደር መስለን ይዘን ጋሻ ጦር ።።
በርዬ ዙር ዙር አብረን እንዙር
እንደ ጨረቃ እንደ ጀንበር።።
የበራን ገለታ አህያ ቀማችው
እሷው ተበራይታ እሷው ተጫነችው።።

3. በርዬ ዙርልኝ ጎናቱ ዙርልኝ
አሟሪም የለኝ
በርባሪም የለኝ።።
እኔና አያ በራ እኔና ሶረን
እንብላ ዞረን አውራ እንዳይበላን
ጋሻ ጦር ይዘን።።
ኧረ በራው ቀልስ ኧረ በራው ግባ
በራ ካልገባበት አይደቅም ገለባ።።
ኧረ በራ ቀልስ ኧረ በራ ቀልስ
ገለባውን በጎሞ ምርቱ በጎተራ እንዲፈስ።።

8. የእርሻ ቃላዊ ግጥም

8.1 ምክር አዘል ትችትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. በጎምላላ በራ ወርደው ታላረሱ
ገንዘብ አይገኝም ኪስን ቢዳብሱ።።
ማረስ ነው እንጂ ከሌ አሸርጦ
ማረስ ነው እንጂ ቡትቲ ለብሶ
ሐምሌ መጣልህ ጨለማ ለብሶ።።
ከሐምሌም ሐምሌ አለ መስከረም
ቢንጦለጦሉ የሚያቀምስ የለም።።

2. ጎበዝ እርሻ እረሱ ከእርሻ አትመለሱ
ቡና እንኳን ሲፈላ ይቸግራል ቁርሱ።።
በራውን ግረፈው ደሙ እስኪንጠረገገር
ገበያ ላይ ወጥቶ ቁና ከመሰንዘር
ብጣሪ ዘንጋዳ በጤፍ ከመበደር።።
ማረስ ነው እንጂ ዲቡን አፍርሶ
ሐምሌ ይመጣል ጉም ተንተርሶ።።

3. ቅዳሜ ቆጥቁጠህ እሁድ ጥመድ እርሻ
ከከበርቱ በራፍ እንዳይበላህ ውሻ።።
ማረስ ነው እንጂ እርፉ እስኪለመጥ
ገበያ ወጥቶ ጎማ ከመምረጥ።።
በሐምሌም እንዳያርስ ዝናብ እየፈራ
በበጋም እንዳያርስ ፀሐይ እየፈራ
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ።።
እምቢ አለ ልጁ አልባበል ብሎ
ከራብ የበለጠ ምን ጅብ አለ ብሎ።።

ማረስ ነው እንጂ በቀይ በጥቁር
ሐምሌ ይመጣል የሚያደናግር።።

4. ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ
ረሃብ ክፉ ነው ይገድላል አንቆ።።
በጥቋቁር በሬ ጠምደው ካላረሱ
አበዳሪ ቢገኝ ይቸግራል መልሱ።።
ማረስ ነው እንጂ እርፍ ነቅንቆ
ረሃብ ክፉ ነው ይገድላል አንቆ።።

5. ማረስ ነው እንጂ አሻ ጎድጓዳ
በሬ እየሸጡ ምንድን ነው ጥጃ።።
ማረስ ነው እንጂ ሞፈሩ እስኪለመጥ
አጋሮ ወርዶ ቆጮ ከማላመጥ።።
እጨፉ ጎተራ ገፍትረው ካልጣሏት
ሴት አትቀመጥም ባላባት ነኝ ቢሏት።።
ማረስ ነው እንጂ አሻ ጎድጓዳ
በሬውን ሸጦ ምንድን ነው ጅዳ።።

6. ያላረሰ ጎበዝ እርፍ ያልነቀነቀ
ስልቻውን ይዞ በቃርሚ ዘለቀ።።
ማረስ ደግ ነበር መነቃቅሎ ሰርዶ
ሰውነት ያከሳል መቀላወጥ ለምዶ።።
አገር ጥሎ መሄድ ምን ያደርግልሃል
ጠንክሮ ማረስ ነው ላንተም ይጠቅመሃል።።

7. በሮቹን ንዳቸው አረንዛው መሬት
የሰው ቤት እንጀራ ይላል እሬት እሬት።።
ምነው በቅዳሜ ምነው በእሁድ ቢያርሱ
ከባለፀጋ ቤት ከሚመላለሱ
ከሀብታም ቀዬ እንዳያጎነብሱ።።
አላየሽውም ወይ የጨፉን ተራ
አላየሽውም ወይ የምስሩን ተራ
እንደ ክረምት አግቢ ሺልንጉ ሲፈላ።።

8. ማረስ ነው እንጂ እርፉን አርቆ
ማፈር ምንድን ነው ገብስ ነዶ ሰርቆ።።
ማረስ ነው እንጂ ቁረንጮ ታጥቆ
የሰው ቤት እንጀራ አይገኝ ወድቆ።።
ምንኛ ደግ ነው መንገድ ዳር ማረስ
ዓይን እንኳን ይጠግባል ሽጋ ሲመላለስ።።
እነ ጣቱ ለምለም እነ ገላው ለምለም
ከቤት ውስጥ ሲገባ የሚቀመስ የለም።።
እረሰው ዳገቱን አስመስለው ሜዳ
ቦላሌ መታጠቅ አይሸኝም እንግዳ።።

ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ
ረሃብ ክፉ ነው ይገድላል አንቆ፡፡
እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ማደር ነበር
ፈረስ የናቀውን ጓያ በአራጣ ከመበደር፡፡

9. በደጋግ በሬ ላይ ላይ ብሎበት
ጤፉን በጎታው ታልከተቱበት
ከየት ታመጣለች ሴትን ቢቆጧት፡፡
በጥቂቁር በሮች ካላደፋረሰው
እህል አፈር አይሆን ከመሬት አያፍሰው፡፡

10. እርሻ ማረስ ነው መቅን ለይቶ
ይመጣል ሐምሌ ነሐሴን ተክቶ፡፡
ደሞም አለ ለጥቆ መስከረም
ቢሉ ጡል ጡል የሚያቀምስ የለም፡፡

11. ከጤፉ ጎተራ ዝገኝ ካላሏት
ከስንዴው ጎተራ ዝገኝ ካላሏት
ከገብሱ ጎተራ ዝገኝ ካላሏት
ከየት ታመጣለች ሚስትን ቢያኮርፏት፡፡
ቀይ የወደደና ፈረፈር ያረሰ
ምንጊዜም ይኖራል እንደተወረሰ፡፡

8.2. ጠንክሮ መሥራትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ማረስ ነው እንጂ ቆላ ተደጋ
ሞፈሩ እስኪቀጭ እርፉ እስቲላጋ፡፡
በሮቹ ጥቁር ሰውዬው መጫ
ማን ይለቀዋል እርፉ ቢንጫጫ፡፡
ማረስ ነው እንጂ ሸክኬም ቢሆን
አንድ ቁና እህል አንድ ሺህ ብር ሲሆን፡፡
ሰውዬው ጥቁር በሮቹ ጥቁር
ሰርዶ አራጋፊ እንደ ነፍሰ ጡር፡፡
ማረስ ነው እንጂ እድቡ ድረስ
የመጣ እንግዳ ጠግቦ እንዲመለስ፡፡
ማረስ ነው እንጂ ጎራ ለጎራ
የበሬው ትንፋሽ ሰው እስቲጣራ፡፡

2. እኔስ አርሳለሁ አልመረርም
ችጋር በወንጭፍ አይባረርም፡፡
ካረሱ ያርሳሉ በቀጭን ሞፈር
የሰው ቤት እንጀራ ይላል አፈር አፈር፡፡
ማረስ ነው እንጂ እዲቡ ድረስ
ምራር መርገጡ እስኪበጣጠስ፡፡
ወይፈኑን ተውና በሬውን ጥመደው
ላንተም ይሻልሃል ሁሉን የለመደው፡፡

3. በሬውን ተውና በለው በደንጎራ
አላየኸውም ወይ የማሽላን ተራ
እንደ ክረምት አግቢ ባውንዱ ሲፈላ፡፡
ገና ለገና ለሚመጣው ቀን
አልወጣልኝም የእርሻው ሰቀቀን፡፡
አሁን መቺ ይገኛል እንደ በሬ ወንድ
ሞፈር ቀንበር ይዞ መሬት የሚንድ፡፡
ከወራቱ ሁሉ ሚያዝያን እወዳለሁ
በሬና ገበሬ ተጠምዶ አየዋለሁ፡፡
4. ታታሪ አርሶ አደር ጥሩ ምርት ያለው
ጎልጉሎ ይዘራል ምንም ቢደክመው፡፡
በሬዬ ቀና በል ከጥጉ ድረስ
አርሶ የበላ ሰው አለው ደስ ደስ፡፡
በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ
ያደግንብሽ እንዴት ነሽ እርሻ፡፡
ቁመቱ ቢያጥር መልኩ ቢከፋ
ከቀንበሩ ሥር አለው ማሪፋ፡፡
ወርደህ ተጋፈጠው ሽበታውን ደሬ
እዚያው ታገኛለህ ወይፈን እና በሬ፡፡
5. ሆ ይላል ገበሬ ሆ ይላል ገበሬ
ድብ እያፈረሰ በአሻልማው በሬ፡፡
የሎሚ ጌታ አይልም ደርሶ
የኩሌ ጌታ አይልም ደርሶ
ይነዳል እንጂ አቢራ ለብሶ፡፡
አራሽና አራሽ ይፎካከራል
የበሬው ጫንቃ ይመሰክራል፡፡
6. የዳለች ጌታ የበርኖስ ጌታ
እግርጌ ጠምዶ ከራስጌ ፈታ፡፡
አቶ እገልዬ የልጅ ወጌሻ
ሞፈር አራቂ በዳገት እርሻ፡፡
ጠንካራ ገበሬ ያርሳል በጠራራ
መሸታ ቤት ገብቶ አይፈራም ኪሳራ፡፡
እገሌ አባበሉ ጠንቃቃው ገበሬ
እንደ ጥንግ ይዘላል የጠመደው በሬ፡፡
7. አርሳለሁ ጎራ ለጎራ
ውሽቱን እንደሆን ይናገር ቦራ፡፡
በሬው ቀና በል ከጥጉ ድረስ
አርሶ የበላ አለው የደስ ደስ፡፡
እኔና ሎሚ ገብተናል መሃላ
ቂቂቱ ላይጎል እሱም ላይሳሳ፡፡

አርሶ በበላ በበሬ ጫንቃ
ይመቀኘዋል ማንም ጨምላቃ።
በቀጭን ሞፈር በሹል ማረሻ
ካረባባ ሹመት ይሻላል እርሻ።
እኔና ኩሌ የምንመኘው
ጎድጓዳ ማሳ ክምር ያዋኘው።

8. ሆ ይላል ገበሬ

ሆ ይላል ገበሬ
ዲብ እያፈረሰ ባሻልማ በሬ።
በርዬ በርዬ አንተን የቻለ ሰው
ቶሎ ቶሎ ብለህ አንጀቴን አርሰው
እረኛህ ያለቅሳል ምሳ እያነሰው።
ዝሩ ምስር በየገደሉ ሥር
በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር።

8.3. **ውዳሴን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች**

1. በጎምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ቆርቆሮ ቤት ሠራ ሰማይ የሚመስል።
ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳንራ መስከረም ዘለቀ።
በትላልቅ በሬ ሂድ ብሎ ሂድ ብሎ
ምርቱን ይዞ ገባ ገለባውን ጥሎ።
ማረሻው ሀዲድ ሞፈሩ ወይራ
ሰርዶ አራጋፊ እንደ ጨንገራ።
የወይኖ ጌታ የስመ ጥሩ
የጫሉ ጌታ የስመ ጥሩ
የጀንበር ጌታ የስመ ጥሩ
መብረቅ ያረሰው ይመስላል ፈሩ።

2. አሁን አያችሁ ወይ የማረሻን ለዛ
ወገንን አጥግቦ ከንፈር የሚያወዛ።
አሁን ማን ያውቀዋል የገበሬን ለዛ
እህል ካልቀመሱ ከንፈርም አይወዛ።
ማረስ ነው እንጂ በቀኝ በግራ
አልመቀኝም በሰው ጎተራ
ግንፍል ግንፍል አለ ጎተራው ሊያግበው
በዳለቻ በሬ እያርገበገበው።

3. በመጋላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
በሾለ ማረሻ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ቆርቆሮ ቤት ሠራ ሰማይ የሚመስል።
ቀጭን ገበሬ አካለ ጠውላጋ
ወፍጮው ሳያቆም መስከረም ነጋ።

ሐምሌ ግም ሲል ሰኔ ሲያገሳ
አደባላቂ ጎድጓዳ ማሳ፡፡
የእርሻው መድሃኒት የእርሻው ደብተራ
ማን ተወዳድሮ ከኩሌ ጋራ፡፡
ብርገግ የመታው ይመስላል ፈሩ፡፡
4. የበሮቹ ቁስ የእርሻው መምህር
አቆላላፊ ክምር በክምር፡፡
ሚያዚያ ግም ሲል ግንቦት ሲያገሳ
አከናናቢ ኩዳዱን ማሳ፡፡
በረጅም ዋንጫ ቢጠጣ ጠላ
አርሶ ነው እንጂ ደጋና ቆላ፡፡
5. በቀይ ሶረን በሬ ላይ ብሎ ላይ ብሎ
ቆርቆሮ ቤት ሠራ ሳሩን ወዲያ ብሎ፡፡
ሐምሌ ነሀሴ ያልተራበ ሰው
ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡
የበሬው ጌታ የእግረ ድንበሉ
ገና ሲራመድ ይለያል ፈሩ፡፡
አዬ ጉዴ ኪሊም አረጀ
ሸማኔ አይደለሁ አልሠራው በእጄ፡፡
በቀጭን ሞፈር ምድር ሰንጣቂ
በሰፊው አውድማ ምርት አስጨናቂ፡፡

6. ሐምሌና ነሐሴ ያልተራበ ሰው
ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡

ሚያዝያ ግም ሲል ግንቦት ሲያገሳ
አከናናቢ ጎድጓዳ ማሳ፡፡
አረንዛ ውጦኝ እስከ ጉልበቱ
አስተራረሱ አገር ያወቀው
እሱ ሳቅ እንጂ ችግር አያውቀው፡፡
አርሶ አደር ነህ አሉኝ መሬትን አራሽ
የሕዝብ መጋቢ የወገን ደራሽ፡፡

9. የሙሾ ቃላዊ ግጥም -

9.1. ሞት ያስከተለውን ጉዳት በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ትላንትና ማታ የወረደው ናዳ

የሞተውን እንጂ ማንንም አልጎዳ፡፡
እገሌን ነው እንጂ ሌላ ሰው መች ጎዳ፡፡
ከእንግዲህ አልበላም ቀይ ሎሚ ልጩ

መለየትን ያህል አደጋ አስቀምጬ
ምን ይሻላል ብዬ ልቤን ልጠይቀው
አለኝ ወንድም ወንድም እንዳይገኝ ሲያውቀው፡፡
2. እገልዬ አበሉ ጣቱ በሰበሰ
ያበላን ነበር እያግበሰበሰ፡፡
ዋ ምን አገኘህ ትላንትና ማታ ብርጭቆ ነበረ
አሁን ከምን ጊዜው ወርቆ ተሰበረ፡፡
ሩቅ ነው ይላሉ ሸዋ በጌምድር
ሩቅስ ባያችሁ የጓሮ ቀብር፡፡
ያ የማን ነው ኩታ ታጥቦ የተሰጣው
ባለ ጥምጣም ጎበዝ ባለቤቱን ያጣው፡፡

3. ወንድሙ ሞቶበት ወንድም የሌለው ሰው

ክንፉን ከተመታ አሞራስ ምን አለው፡፡
እባክህ ፈጣሪ አትቁረጥበት
ተለይቶ ሄደ ቀረ ጎረቤት፡፡
የእናቴን ኩታ መንገድ ላይ ጣሉት
እሷ የሞተች ዕለት እንዴት ሊያደርጉት፡፡
አባት ይሞትና አጎትን ማመን
እናት ትሞትና አክስትን ማመን
ከሰማይ አሞራ ሥጋ መለመን፡፡
የዘመዶቼ ቤት ግድግዳው ምን አለኝ
ሳጣቸው ነው እንጂ እኔን የቸገረኝ፡፡
4. አዬ ጉድ ዋይ ዋይ አዬ ጉድ ዋይ ዋይ
አፈሩ በላህ ወይ
መወለድ መጫወት መሳቅ ጥሩ ነበር
የሦስት ሜትር ፍልፍል መቃብር ባልነበር፡፡
እኔስ አሳዘነኝ ጎጆው አለቀሰ
ምሰሶው ተነቅሎ መደቡ ፈረሰ፡፡
ሰንጋው አኮረፈ ባለቤቱ ናፍቆት
ያለ እሱ መለጎም ግራ እየሆነበት፡፡
ምን ያደርጋል ሰንጋ ምን ያደርጋል ዝናር
እንዲህ እርግፍ አድርገው ለሚሄዱት ነገር፡፡
ጎረቤቱ ሲሞት ያልቅስ ጎረቤቱ
የጮማው የቅቤው ሲዘጋበት ቤቱ፡፡
ልጅ አደራ ማለት ምን አማርኛ ነው
ልጅን ያለ እናቱ የሚችለው ማን ነው፡፡
ይሄ የማን ነው ጨርቅ እዚህ የተሰጣው
የእገልዬ አበሉ ባለቤቱን ያጣው፡፡

ኧረ መሃን መሃን መሃን አንድነቷ
ከመቃብር በፊት ይቆለፋል ቤቷ።።

5. ዋ ምን አገኘህ ዋ ምን አገኘህ

እንኳን ደህና ጎበዝ አውራጃ የሚያጨው
ጎመን ያሳዝናል በረዶ ለቀጨው።።
ወንበሩን አልጋሽን ፎቶሽን እያየሁ
አበባ እህት ዓለም እንዴት እችላለሁ።።
አንድ እሷ ነበረች እህቱ የምላት
ከእንግዲህ አረፍኩት እሷንም አጣኋት።።
ከለምለም ሳር መሃል አንድ እሷ ነበረች
ሽታ መዓዛዋ መድሃኒት የሆነች።።
ዛሬ ብትቀበር መዓዛዋ ጠፋ
ከቤት ውስጥ ሲያጣት ቤተሰብ ተከፋ።።
አታልቅሱ ይላል ቄስና ቃልቻ
ትልቁ ሰው ሞቶ ቀረ ውሪ ብቻ።።
በሮቹ ጥቋቁር እርሻው አፋፍ ላይ
ተው ተው እንኳን የሚል ሰው መጥፋቱ ነው ወይ።።
በል ቻለው ይለኛል ቋሚ ዘመናይ
ሰማይ ተደፍቶብኝ እንዳው እስተእንባዬ።።
እናት የሌለው ልጅ ጆሮ የሌለው እንሥራ
አይመሰገንም ቢሠራ ቢሠራ።።

6. የእገልዬ በቅሎ ወረደች ኮምቦልሻ
ጌታዋ ሞቶባት ሌላ ጌታ ልትሻ።።
የኛማ ዘመዶች አሉ ጎደል ጎደል
ግማሹ በውሃ ግማሹ በገደል።።
ልጅ ልጅ ብለሽ ብትርገበገቢ
የዘን እንጀራ እንጂ ልጅ አትረጠቢ።።
እውነት ተለየ ወይ እንዲህ በድንገት
የበታተነውን ሐሳቡን ሳይከት።።
እንግዲህ ከዘመድ ማን ያስተዋውቀን
በቃ ተከተተ እኛም ተራራቅን።።
ቤታችን ቀዝቅዞ በረዶ መታው
አንተ ነበርክ እኮ በጨዋታ በቀልድ የምታሞቀው።።
ቤተሰብ ሰብሳቢ ዘመድን አክባሪ
አለኝታ ጓዳችን የሁላችን መሪ።።
ማረፉንስ ይረፍ ከእንግዲህ ይብቃው
ዘመድ አዝማዱንስ ማን ይሰብስበው።።
ትልቁ ሰው ሄደ ዘመድ ናፋቂው

ተመለስ የሚለው ከእንግዲህ ማነው።
ለዘመድ አዝማዱ አልታላከም ወይ
አንድ የቀይ ዳማ አርፎ የለም ወይ።
አራሹ ገበሬ አምራቹ ገበሬ
ያ ሙሉዓለም ዘውዴ የት ውሎ ነው ዛሬ።

9.2 ወቀሳን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. የቦረና መሬት ሆዳሙ ሆዳሙ

ጎበዙን ብላና ይውጣልህ ራቡ።
ምን ይከፋል ቀኑ ምን ይከፋል ቀኑ
ጉድጓዱ ሲቆፈር ሲሰፋ ከፈኑ።
ሲያመርትም ሲለብስም የሚያመርትበት
መጥቶ ወሰደው አባ ጨካኝ ሞት።
ወንድም የሌለው ሰው አያድግም መስሏቸው
አባት የሌለው ሰው አያድግም መስሏቸው
እያደገ ሄደ እየበለጣቸው።
ቤቷን ሠርታ ነበር በሸንበቆ ማገር
አፈራርሳው ሄደች አወይ የሰው ነገር።

1. አዬ ጉዴ ሆይ ከወንዝ ወዲያ ማዶ አልቃሽ አምጥታችሁ
እያለቃቀሰ ይሄው ጨረሳችሁ።
አገሬ ቦረና ምንድን ነው ነገሩ
እንደ ሽንብራ እሸት መረጠው ከሥሩ።
አልቃሽ ይሳደባል የተረገመ ሰው
ከመሃሉ ገብቶ እንደ እኔ ይቅመሰው።
አንተ መላዕከ ሞት ና ቶሎ ሲመሽ
በጧት እየመጣህ ደጅ አታበላሽ።
አጥሩ ምን ይለኛል፤ በሩ ምን ይለኛል
ያጎረሰኝ ይመስል ጨርቁን ይይዘኛል።
ምን ላይሞላ ጉድጓድ ላይጠግብ መሬት
ስንቱን ጀግና ጎበዝ ወሰደው በጧት።
አንተ ሞት የሚሉህ ዋ ይብላኝልህ
ትንሹን ትልቁን ትወስደዋለህ።
ሲሠራው ዋለና ሲያንጸው ሲያንጸው
እንደ መፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው።
ከሰው ምቀኛ ፈጣሪ ይብሳል
ወርዶ ላይገባበት የሰው ቤት ያፈርሳል።

9.3 ተስፋ መቁረጥን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. የወደቀ ዛፍ እሾህ አያጣም
የዛሬን አልቅሼ ከእንግዲህ አልመጣም።

የጎጃም እንግዳ ባለህበት እርጋ
የጎንደር እንግዳ ባለህበት እርጋ
የከልዬስ ደጃፍ በድንጋይ ተዘጋ።
እስኪ ልነሳና ልበል ዋኔ ዋኔ
ከሰው ውሪ ቀረ ከእህልም ሰለሌ።

2. አዬ ጉድ ዋ ሆዬ አየ ጉድ ዋ ሆይ
ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
በቤታችን ነዋሪ መጥፋቱ ነው ወይ።
አሁን ምን ያደርጋል እኔ ባበጃጅሽ
መሰንበቱ ነበር ላንች የሚበጅሽ።
የአሁኑ በጋ አልፎ የሚመጣው በጋ
በሬህ ከሰው ቀንበር ሚስትህ ከሰው አልጋ።
አንተ አለኸኝ ብዬ ስመካ ስመካ
አይ የሰው ነገር ሞተህ ነው ወይ ለካ።
እንዲህ ወደ ጎጃም አዋጅ ተነገረ
እንዲህ ወደ ሳይንት አዋጅ ተነገረ
እገልዬ እገሌ እንደወጣ ቀረ።
ምን ያደርግልሃል እኔ ባበጃጅህ
መሰንበቱ ነበር ላንተ የሚበጅህ።

3. ዋ ምን አገኘህ ዋ ምን አገኘህ
አገልዬ አበሉ ሞፈርክን በረደው
አትመለስ እንደሁ ፈልጠን እንማግደው።
ምን ያደርጋል ሰንጋ ምን ያደርጋል ዝናር
እንዲህ እርግፍ አድርገው ለሚሄዱት ነገር።
እንዲህ በስተሸዋ ዳመና ዘለቀ
እንዲህ በስተጃማ ዳመና ዘለቀ
ዘር ያላችሁ ዝሩ የእኛስ ዘር አለቀ።
ኩቱንም ሽጡለት ላንድ ጭብጥ ጓያ
ሸሚዙን ተውለት የአንገቱን ማሳያ።
ጃኬቱንም ጣሉት አትስጡ ለወራሽ
ቀርቀሃውን ጣሉት አትስጡት ለወራሽ
ከመንገድ ላይ ጣሉት እንደ እሱው ይበላሽ።
ተስፋ አድርን ነበር መልሰን ልናይህ
ቀኑ ጨለመና እንደ ተኛህ ቀረህ።

9.4 ጀግንነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ሽጡት ለቃጤ እህል ጓያ
ምንሽሩንም ሽጡት ለቃጤ እህል ጓያ
ሱሪው እንዳይሸጥ ያባቱ ምስያ።
ሞት የሚሉት መጣ እየገሰገሰ

ጀግና እንደ ብርሌ እያፈራረሰ፡፡
ሜዳውን ዳገቱን የሚያፈራርሰው
ሙቶ ተቀበረ መገን ጎበዙ ሰው፡፡

ጠመንጃው አርግዛ ቁማለች ከፊቱ

ቀኑ ከደረሰ የለው የሰው ብርቱ፡፡
2. የሰኔው ገበሬ የሐምሌው ጎልጓይ
ጅራፉን ጠቅልሎ መሄዱ ነው ወይ፡፡
የሽመሉ ዳኛ የክላሹ ዳኛ
ከእንግዲህ አረፈ ጥቅልል ብሎ ተኛ፡፡
የእገልዬ ጠመንጃ ጎጃም ተሻገረ
ባለቤቱን አጥቶ እያንጎራጎረ፡፡
አዬ ጉድ እገሌ ገበሬው አራሹ
አሁን ከምን ጊዜው ተሰቀለ መንሹ፡፡
የት አለ ጉብዝናው የት አለ ጀግንነቱ
ለክር አይደለም ወይ የተሠራው ጣቱ፡፡
የዛን ጀግና ቀብር ሰፋ አድርጋችሁ ማሱ
አይበቃውምና ለእልኩና ለእሱ፡፡
እራቱን አልበላም ለምን ትላላችሁ
ምሳውን አልበላም ለምን ትላላችሁ፡፡
ምነው በልቷል እንጂ ምነው ግጥም አድርጎ

9.5 የቤተሰብ ዓባላትን ሞት በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. አባት ይሞትና አዘን ይታዘናል
እናት ትሞትና አዘን ይታዘናል
ተሁሉ ተሁሉ የልጅ ሞት ይበልጣል
ያለ ካራ መትሮ ያለ እሳት ይጠብሳል፡፡
ጋቢ ያለኝ እንደሁ እገዛለታለሁ
ሱሪ ያለኝ እንደሁ እገዛለታለሁ
እናት ያለኝ እንደሁ ከየት አመጣለሁ፡፡
እናት ያልሞታችሁ
አባት ያልሞታችሁ
ወንድም ያልሞታችሁ
እህት ያልሞታችሁ
ወጣ ወጣ በሉ እንዳልጮህባችሁ፡፡
እናት የሌላችሁ አባት የሌላችሁ እንሂድ ምናኔ
እናት የሚሠራ አባት የሚሠራ ብናገኝ ሸማኔ፡፡
እኔማ ልጆቼን ከአፈሩ ድሬያቼው
ይመጡልኝ ይሆን ምላሽ ብጠራቸው፡፡
እንጆራ ያለኝ እንደሁ እንጆራ እሰጣለሁ

ውሃም ያለኝ እንደሁ ውሃም እሰጣለሁ
እናት ያለኝ እንደሁ ከየት አመጣለሁ፡፡
እናት እናት ቢሉ እንደ ወፍ ቢበሩ
እናት አትገኝም በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፡፡

2. አባት የሚሠራ ባገኘሁ ሸማኔ
ድርና ማግ ሆኜ ባቀለምኩኝ እኔ፡፡
ከሁሉም ከሁሉም የእናት ሞት ይብሳል
ያለ ካራ መትሮ ያለ እሳት ይጠብሳል፡፡
ጡታ እየፈሰሰ መሬት እየራሰ
አደረ አሉ ልጁ የሰው ገላ እየላሰ፡፡
ግልገል በቅሎ ገዛሁ ከእናቱ ነጥዬ
አባት በቅሎ እንግዲህ አይገኝም ብዬ፡፡
ልጆቼን አደራ ምን አማርኛ ነው
ልጁን ካለ እናቱ የሚያውቅበት ማን ነው፡፡
አባት የሌለው ልጅ አይበላም ጥንቅሽ
ከብት ካልገባበት ካልሆነ ርካሽ፡፡
ትንሹ ልጅህ መሞትህን አያውቅም
ትመጣለህ ብሎ በራፉን አይለቅም፡፡
አባት የሌለው ልጅ ከበራፍ ያመሻል
እናቲቱ አስገቢው ጅብ ይበላብሻል፡፡

3. ደህና ሁን አባባ መሬቱ ይቅለልህ
አምላክ በምህረቱ በቀኙ ያኑርህ፡፡
አባታችን ማረን እባክህ ተመለስ
መጪው ክረምት ነው ቤታችን አይፍረስ፡፡
አባት የሞተ እንደሁ አበባው ይረግፋል
ከሁሉም ከሁሉም የእናት ሞት ይብሳል
ወንድም የሞተ እንደሁ ጠላት ይደነፋል
እህት ሞተች እንደሁ ያዋዩት ይጠፋል፡፡
እከልዬ አቦሉ ልጆችሽ ተንጫጩ
እነዚያ ጥርሶችሽ አፈር ሲጎነጩ፡፡
እህትም ነበረው ወንድምም ነበረው
የሞት ባላንጋራ ገብቶ በረበረው፡፡.

9.6 ጭካኔን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. እኔን ባደረገኝ የምስጥ አውራውን
ይህን መሳይ አንገት የሚበላውን፡፡
ከመሣሪያሽ ሁሉ ምጣድሽ ይድረስኝ
ተርቤ ስመጣ አንጉቶ እሚያጎርሰኝ፡፡
ሊያሳድጉህ አይደለም ቢያከባብሩህ
ሊቀብሩህ ነው እኮ አፈር ሊያለብሱህ፡፡

የዛሬውን ለቅሶ ችላ ብሏል ሴቱ
አኑሯል መሰለኝ ሽጋ በየቤቱ፡፡
ዓይን አላይም አትበል እግር ካደረሰ
ያቺን ልጅ ቀበሯት ጡት እየፈሰሰ፡፡
1. ምነው በቀረብኝ ከእናንተ መወለድ
እድሜያቸው አጭር ነው እንደ ጓሳ ገመድ፡፡
ኧረ እባክሽ ተይኝ
ያንቺስ ተቀበሩ የእኔን ጅብ በላብኝ፡፡
እኒያ ሽማግሎች አማሩ ደመቁ
የእኛ ቤተሰቦች እንዳሉ ጠይቁ፡፡
አባት ይሞትና የሰው አባት ቢያዩ
እናት ትሞትና የሰው እናት ቢያዩ
ሞሰብ መቼ ይገጥማል ያለ ወስከባዩ፡፡
ደግ እናት ያልሞተው አሁን የት አለና
ደግ አባት ያልሞተው አሁን የት አለና
ደግ እህት ያልሞተው አሁን የት አለና
ደግ ወንድም ያልሞተው አሁን የት አለና
እንዳው ይፈጠራል አንጀተ ደንዳና፡፡
ዘንከትከት መለሎ መልከ መልካሙን
ከረቸሙት አሉ አሠሩት እጁን፡፡
ዓይኗ የሚመስለው የንጋት ጨረቃ
እግሯ የሚመስለው የውርማ ጨፈቃ
ቀባሪ ጨካኝ ነው መረገባት ጭቃ፡፡

10. የቀረርቶ ቃላዊ ግጥሞች

10.1 ታታሪ አለመሆንን በተመለከተ የቀረቡ ሂስ አዘል የቃል ግጥሞች

1. ዘንድሮ ገልበቱን አይጥ ተንፍሳበት
ብደክም ብለፋ ምስጋናም የለበት፡፡
2. አረስን አረስን ያሉት የታለ ማረሳቸው
እመንገድ ተገኙ እስተ አህዮቻቸው፡፡
2. አጭር ነን ቀጭን ነን ዋጋም አናወጣ
ጠምዳችሁ ልቀቁን ከአፈርም አንወጣ፡፡
3. እርሻ እረሱ ጎበዝ እርሻ እረሱ ከእርሻ አትመለሱ
ቡና እንኳን ቢፈላ ይቸግራል ቁርሱ፡፡
4. ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ማደር ነበር
የነቀዘ ጓያ በጤፍ ከመበደር፡፡
5. እንጆራ አለ ብለን የወረድንበት
ከሾተል ይብሳል የድናጋዩ ስለት፡፡

10.2. ፈሪን የሚተቹ ቃላዊ ግጥሞች

1. ሁል ጊዜ መጠቃት እንደ መከነች ጊደር
   ሰው ገድሎ ዱር መግባት ነውር ይመስል።
2. ወይ እነሱ አይመጡ ወይ እኛ አንሻገር
   መልካው ጦም አደረ የሁለት ፈሪ አገር።
3. የወንድሙን በደል ወንድሙ ካልከፋው
   ከደጃፍ እሰረው ደሙ እንዲከረፋው።
4. ኧረ ለምንድን ነው ንጉሴ ማቶንቶኑ
   ይበጠስ ይመስል ቅጠል ያለ ቀኑ።
5. የወንድሙ ደም ለወንድሙ ካልከረፋው
   ከደጁ ዘርጋለት ደሙ እንዲከረፋው።
6. ባልዮው በሬ አርዶ ሚስቱ እየመተረች እያለችው ብላ
   ወኔው ቀዝቃዛ ነው እንደ ዋርካ ጥላ
   ወኔው ቀዝቃዛ ነው እንደ ማታ ጥላ።
7. ግፋ በለው ኧረ ግፋ በለው ይገፋል በግዱ
   ያገሩ ገመገም ሲጠፋው መንገዱ።
8. አየ ጉድ አየ ጉድ ጉድ አይታክተው
   ጋሻ ነው ብሎ ሞክዱን መከተው።
9. አባቱ በሬ አርዶ እህቱ እየመተረች እያለችው ብላ
   ወኔው ቀዝቃዛ ነው እንደ ዋርካ ጥላ።
10. ተንኮለኛ ዶሮ ቀፍቅፋ ቀፍቅፋ
    ጨርሶ ሴት ሆነ ኩሉ የሚል ጠፋ።
11. ዝም ብለው አንገቴን ብደፋ
    መነኩሴ አደረገኝ ያውም ቆብ የደፋ።
12. ከላይ ቢረገጡት ከታይ ደፈረሰ
    አንድ ቂጣም አለ ቀኑ የደረሰ።
13. ፈሪ ይብላኝልህ ዛርጢ ይብላኝልህ
    እጦሩም ሳትገባ ሞቱም ላይቀርልህ።
14. አንበሳው ማደሪያ ዝንጆሮ ሸንቶበት
    ሲባንን አደረ በህልሙ እየመጣበት።
15. ይሮጣል እንጂ ፈሪ አይዋጋም
    እንደምን ነው በሽሎ የታጠረው ባጋም።
16. ሃምሳ ስልሳ ወልዳ ዶሮ ጋት የላትም
    ለዛርጢ መድሃኒት አልተገኘለትም።
17. እዩት እዚያ ማዶ አሞራ ዶልቷል
    ገዳይ ጠፍቶ ነው እንጂ ሚች ሞልቷል ሚች ሞልቷል።
18. አባት ጋሻ ገዝቶ ልጁ የፈራ እንደሆን
    የኮሲ ባቄላ እንጆለሌ መሆን።
19. ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልተባለ አጅሬ
    ከዳገት ስደደው ሣር ይብላ እንደ በሬ።
20. ኧረ ፈሪ ብልጡ ኧረ ፈሪ ብልጡ

ሲሸሽ የሚያይበት ዓይን አለው በቂጡ፡፡
21. ኧረ ምን ቢሆን ነው ጎበዝ ምን ቢሆን ነው
ፈሪና ዝንጆሮ አካሄዱ የሚያምረው፡፡

10.3. ጀግንነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ተወው ልቤ ደርሶ መደንገጡን
ሞት አይቀርም ብዬ ነግሬህ እርግጡን፡፡
2. ዓባይን አረሱት ዘቅዝቀው ቦይ ለቦይ
አባትዮው ቢሞት ልጆዮው የለም ወይ፡፡
3. ኧረ ተው አንተ ሰው ወይ አንተ ተመለስ ወይ እኔ ልመለስ
የሁለታችን ቤት በአንድ ላይ ከሚፈርስ፡፡
4. እባክህ ወንድሜ ጠላትህን ገልምጠው
እሱ እየረገጠህ አትለማመጠው፡፡
5. ሳሩን በልቶ ውሃውን ጠጥቶ የተኛውን በሬ
ነካክተው ነካክተው አደረጉት አውሬ፡፡
6. አባይ ዳሩ ዳሩ አብቅሏል ለጉዝጓዝ
እኛም እንደርሳለን ሰው ገድሎ ለመጓዝ፡፡
7. እንዲህ ተጉመትምቼ እንደ ትግሬ ገረድ
አምጡልኝ ቆሌዬን ሃሳቤን ልዋረድ፡፡
8. ጫቀታ ሀገራችን ቦረና ሀገራችን
እንኳንስ ጥይቱ ይሰብራል ጓያችን፡፡
9. ብለነው ብለነው ካልሆነ ነገሩ
የወንድና የብር የትም ነው አገሩ፡፡
10. አንጣቆ ነው ሜታ ለጠብ አይመችም
አሻግረው ያዩታል ላሞቹም ጥጆቹም፡፡
11. ቦረናና ነብር ሁለቱ አንድ ናቸው
ከሰው ላይ አይደርሱም ካልደረሱባቸው፡፡
12. ጦር አይመጣም ሲሉ ይመጣል ድንገት
ደህና ደህና አሸክር መርጠው ካልቆዩት፡፡
13. ጥቂት እንዳንመስለው ለባላጋራችን
ተከዜ ብቅ ይላል አያሌው ጦራችን፡፡
14. ኧረ ተወኝ ልቤ ደርሶ መደንገጡን
ሞት አይቀርም ብዬ ነግሬህ እርግጡን፡፡
15. አባይ ሞልቶ ጣና ሞልቶ እሳት ይዞረዋል
ሲጠፋ ነው እንጂ መች ይሻገረዋል፡፡
16. ብቅል ሳይበቅል ጌሾ ሳንከተክት ሳንሰነዳዳ
ወይ ዛሬ ወይ ነገ ይመጣል እንግዳ፡፡
17. ሞፈሩንም ቀንበሩንም ሰጠሁት ለሌላ
ባገሩ ለሚኖር አርሶ ለሚበላ፡፡
18. ይቅር ምናባቱ የአንድ ዓመት አዝመራ
ቤት ስለሌለው ነው አንበሳ የማይፈራ፡፡

19. ኧረ ተው አንተ ሰው አትለፍ በደጇ
እንደ ኩበት እሳት ትጠፋለህ በእጇ፡፡
እንደ ገለባ እሳት ትጠፋለህ በእጇ፡፡
20. እናንተ ዝም በሉ የእዛ ቤት ሰው ያውጋ
ካንበሳ ጉሮሮ ማን ያወጣል ሥጋ፡፡
21. እደግ እደግ ብለን ያሳደግነው ቀጋ
ዘንበል ዘንበል አለ እኛኑ ሊዋጋ፡፡
22. ከታች ከበረሃው ወይፈን ካላረዱ
ከላይ ከጓሳው ላይ ወይፈን ካላረዱ፡፡
መቼ ያስታውቃል ወንድ መወለዱ፡፡
23. እልም ነው ጭልጥ ነው ውሃ አይላመጥም
ሆኖ ላይሆን ነገር አልልመጠመጥም፡፡
24. አሞኛል አሞኛል ህመሜን አላውቅም
ካልተገማመተ ወንድን ወንድ አይንቅም፡፡
25. አባይ ሞልቶ ጣና ሞልቶ ግንድ ያገላብጣል
ጠላትን ሳይገድሉ ምን ያቀማምጣል፡፡
26. አንበሳ ተኝቶ ጦጣ ዘለለችው
አውቆ ቢያሳልፋት ፈርቶኝ ነው አለችው፡፡
27. አገራችን ሜታ መልሶ አገራችን
ጓያችን ይሰብራል እንኳን ጥይታችን፡፡
28. አሙን አሉ አሙን ተዋቸው ይሙን
ቢፈሩን ነውና ቢጠረጥሩን፡፡
29. ሜታ ወርደ ጠባብ መንገዱ ረጅም ነው
ከተጣሉ ወዲያ እርቁ ለምንድን ነው፡፡
30. አትውረዱ ሜታ በርበሬ ብላችሁ
መሰንበት ይሻላል አልጫ በልታችሁ፡፡
31. አባይ ሞልቶ ጣና ሞልቶ ድብድቡን ሲያለብሰው
ምን ጥልቅ አደረገው ዋኝቶ የማይወጣ ሰው፡፡
32. እኛ አልነበርንም ወይ የወንበዴ አለቃ
እኛ አልነበርንም ወይ የሌቦች አለቃ
ዛሬ ታማኝ ሆን ለአደራ የምንበቃ፡፡
33. ነብር ዓይኑን ታሞ ላም ተራመደችው
ዐውቆ ዝም ቢላት ንጉሴ ነው አለችው፡፡
34. ሐምሌንም ዘንቦ ነሀሴንም ዘንቦ መስከረምን ፀሐይ
ልብ እንደ ጎራዴ ተመዝዞ አይታይ፡፡
35. እም አለ ንቡ ቀፎው ተጨነቀ
ማር ብቻ ነው ይላል መርዙን ያላወቀ፡፡
36. ከእንግዲህ ጎጆዬ ቅረብኝ ቅረብኝ
ጠላት በደጇ ላይ ተንጎባለለብኝ፡፡
37. ነብር ዝንጉርጉሩ ነብር ዝንጉርጉሩ

ጅራቱን ሲይዙት ይርቃል ወገቡ፡፡
38. ሾላ ሞኙ ዋርካ ሞኙ ሳያብብ ያፈራል
አንዱን ካልገደሉት አንዱ መች ይፈራል፡፡
39. በትሬም ቀጭን ናት እኔም ቀጭን ነኝ
እስኪ ጠጋ ብለህ ጎኔን ሰልለኝ፡፡
40. ጠላቴ ተቀመጥ ዘመዴ መስለህ
አውድማ አበጅቼ እስካበራይህ፡፡
41. አባቱ ነበር ሰው አስታራቂ
ልጁ ደረሰ ክላሽ ነቅናቂ፡፡
42. አሞኛል ዘንድሮ ጤና እማይደለሁኝ
ከሚገጥመኝ ጋር ካልተገናኘሁኝ፡፡
43. በለው በለኝና ወርጄ ልበለው
እኔ ምን ጓዝ አለኝ የማንጠለጥለው፡፡
44. እንደምን ነው ልመስክ የበሩ ግድም
እንኳን ገድለውበት ይሸታል ደም ደም፡፡
45. ታሞ ታሞ በሽታው ሲጠና
በለው በምንሽር መድሃኒት ነውና፡፡
46. ጋማውን ጅራቱን ቢጎነዳድሉት
መቅበጥበጡ አይቀርም ኮርቻ ሲጭኑት፡፡
47. እንዲህ ዳምኖ ዳምኖ የዘነበ እንደሆን
እንዴት ያሉ በሮች ይጠመዱ ይሆን፡፡
48. በሬው ጥጃ ወልዶ ተኝቶ ይልሳል
አሞት ያለው ጎበዝ ደሙን ይመልሳል፡፡
49. እነ እገሌ መንደር ከመሸ ማን ደርሶ
ሠላሳ ጎራሹ ሙሉ በሙሉ ጎርሶ፡፡
50. መሄድ መሄድ አለኝ መንከልከል መንከልከል
አፌ ባይናገር ሆዴ ይሂል ተንኮል፡፡
51. አይዞሽ ምንሽሬ አልሰጥሽም ለሰው
አምስቱን ስድስቱን አፈር ሳላለብሰው፡፡
52. ረጅም ምንሽር ተኩሱም ረጅም ነው
ከተጣሉ ወዲያ እርቁ ለምንድን ነው፡፡
53. ከአለት ወዲያ ማዶ ነጭ ላም ቁማለች
ያም ለእኔ ያም ለእኔ ያም ለእኔ ይላታል
ጉልበቱን ያመነ ሂዶ ያመጣታል፡፡
54. የሹም ከወንዙ ዳር የተኛውን በሬ
ጭላጋ ከበሩ ዓባይ ከወረቡ የተኛውን በሬ
ነካክተው ነካክተው አደረጉት አውሬ፡፡
ነካክተው ነካክተው ሲያሳጡት መድረሻ
ዙሮ ይናከሳል ያሳደጉት ውሻ፡፡
55. አጨደው ከመረው ወቃው በጎራዴ

እኔስ ደስ ይለኛል ሜታ መወለዴ።።
56. እስከ ዛሬ ድረስ ድስ የበላ በሬ
ቀንበሩ ወረደ ሊጠመድ ነው ዛሬ።።
57. አባይ ወዲያ ማዶ ተሻግራ ላማችን
እናመጣታለን ታለ ጉልበታችን።።
58. የሰማይ ልቡ ያጋም ጨፈቃ የነብር ጫንቃ
የተናገረው አንዱ የሚበቃ።።
59. አብሽ ቢዘሩት አብሽ ነው ሽታው
አያስታውቅም የሰው በሽታው።።
60. ኧረግ እርቁን ትተው ጠቡን ከወደዱ
ንዲቸው በሮቹን መንገዱን ይልመዱ።።
61. የዛ የሰው ልጅ የዛ የአጣቆ
የምንመኘው ሰው በጥልቆ።።
62. ባቄላ ምርቱ እንጅ አያምርም ክምሩ
ይምጣ የሜታ ልጅ ከነምንሽሩ።።
63. በሺህ በሁለት ሺህ ይገዛል ጠብመንጃ
በለው በለው አለኝ የነካኝን እንጃ።።
64. እጥፍ እጥፍ ያለው እንደ ኩታ ልብስ
አተካኮሱ አንጅት የሚያርስ።።
65. እምቢ ብሎ እንደሁ ልቡ እየጎደራ
እሱን በምንሸር በሬውን በካራ።።
66. ጥይት ወለወለ ሰጠኝ ለጠሃይ
የበረሃው ጓዴ የአሞራው ሲሳይ።።
67. የሰማይ አሞራ ልጠይቅሽ ወሬ
አባቴ መሬት ላይ ተጠምዷል ወይ በሬ።።
68. በሽሎ ተጭረቻው ብረት ምጣድ ጠፍቶ
ያ ጎበዝ አበላኝ በምንሸር ቆልቶ።።
69. በሽሎ ተሜዳው ላይ ትንሽ አውድማ አለች
የደም አግማስ ለምዳ ትቅለበለባለች።።
70.አሉ በሮች ያውም የገነኑ
ገጥመው ባየናቸው መቼም ሳር አልበሉ።።
71. የፍየል ቅረኔ ቅጠል በልታ በልታ ልቧ ቢሞላባት
ጠብ እንዴት ነው ብላ ነብሩን ጠየቀችው
እሱስ ይበላሻል ይቆረጣጥምሻል
ከጉሬው ከወጣ መቼ ይፈራሻል።።
ነብሩ ዝንጉርጉሩ ነብሩ ዝንጉርጉሩ
ከጉሬው ሳይወጣ የሚበላው ሙክት እየሮጠ መጣ።።
72. ሻዕቢያም ብላ ነበር ደሴ ነው ድንበሬ
እምቢ አለ አሉ ወሎ ተጠምዶ እንደ በሬ።።
73. ገበረ አሉ ወሎም ገበረ አሉ ያየናም ገበረ

እምቢ አለ አሉ ሜታ እያንገራገረ፡፡
74. ያየናም ገበረ ቅቤ በገበታ
ወሎም ገበረ አሉ ቅቤ በገበታ
75. አጭር ናቸው ብለው በእኛ ላይ መጡብን
ማን በነገራቸው ዐመል እንዳለብን፡፡
ኧርንጉርጉሩ ነብር ኧርንጉርጉሩ ጅራቱን ሲይዙት ወገቡ ይርቃል
አሚር ያለው ጀግና በእጁ ይታረቃል፡፡
76. የበሬውን ቀለብ ወይፈኑ በላው
አንድ ቀን ተጠምዶ ፈሩን ሳያየው፡፡
77. ኧረ ተወኝ ተወኝ ተወኝ ግድ የለህም
የእኔ ጎጆ ፈርሶ አንተም ቤት የለህም፡፡
78. ጎጃም በሬ አረደ እኛም ጥጃ እንረድ
ለሥጋው አይደለም እጃችን ደም ይልመድ፡፡
79. ይሄ የእኔ ሱሪ ስሮጥ አያስሮጥም ስቀመጥ ጠበበኝ
ቀድጀ ቀድጀ ልጣለው መሰለኝ፡፡
80. የአባቱ ጠላቶች ለእኔ ዘመድ ናቸው
አውድማ ለቅልቁ እስካበራያቸው፡፡
81. በምንሽር ተልሞ በጓንዴ ነው ማረስ
አረም አያበቅልም እስከ ወዲያው ድረስ፡፡
82. በሬው ስንዴ ዳለች ሣሩ ጎቻ ለምለም
ይሞክራሉ እንጂ የሚበልጠን የለም፡፡
83. ድሃ የድሃ ልጅ ድሃ የወለደው
በገዛ እጁ ክቦ በገዛ እጁ ናደው፡፡
84. ከጫካ እየበላሁ እኖራለሁ እንጂ
ማን ነው የሚነካው የጎበዙን ደጅ፡፡
85. አስከትለኝ ጎበዝ አስከትለኝ ልጅ ነው አትበልና
ግንድ የሚያቀጣጥል ጭራሮ ነውና፡፡
86. ገና ልጅ ነው አበባ ነው ብለው ቢጨፈጭፉት
ያስቸግር የለም ወይ የጎመራ ዕለት፡፡
87. ሁል ጊዜ ቀረርቶ ሁል ጊዜ ፉከራ አገር ያሰለቻል
ወይም ገድሎ መሄድ ወይም ሰምቶ መቻል፡፡
88. የበረሃው ንዳድ የቆየው በሽታ ህመሙ እንደምን ነው
እያንዘፈዘፈ እየቀዘፈው ነው፡፡
89. ንክች እስኪ ርስቱን ንክች እስኪ ሚስቱን
ያን ጊዜ ነው ማየት ወንድ ወንድነቱን፡፡
90. ቢመቸኝ ነው እንጂ መስክ ላይ መኖሬ
ከመረረኝማ የትም ነው ሀገሬ፡፡
91. አቆጠቆጠ አሉ ያምናው ምንጥራችን
ዘንድሮም እንበለው እንደልማዳችን፡፡
92. ያ በሬ እምቢ ብሎ አጥር ጥሶ ወጥቶ

እንደ ወጣ ቀረ መልሶ መግቢያ አጥቶ፡፡
93. ቆርጠህ ቆርጠህ ጣለው እንደ ጉል አገዳ
ወዶ የማይጠቅም ጠልቶስ ምን ሊጎዳ፡፡
94. . አውድማው ይለቅለቅ በሮቹም አይራቁ
መቼም አልጠበቀም ውሽልሽል ነው እርቁ፡፡
95. ነብር በቁልቁለት ሲሄድ መላጋ ነው
ከጉሬው ከገባ የሚነካው ማን ነው፡፡
96. ወንድነት አይጠቅም ሴትነት አይጎዳ
መገኘት ነው እንጂ ከጎበዞች ጓዳ፡፡
97. እምቢኝ አሻፈረኝ መጣብኝ አመሌ
እንዴት ሊኮን ነው ልጓዝ ነው አገሬ፡፡

10.4 ነገረኛነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. አያችሁለት ወይ ይሄን ጠብ መፈለግ ይሄን ጠብ መውደድ
አባይ በጣና ላይ ይፈልጋል መንገድ፡፡
2. ቤቱ በረሃ ነው ጫካ ነው አገሬ
ከደጁ ማን ደርሶ ምንስ ተናግሬ፡፡
3. አሳረኛ ጊደር አሳር የገተተች
አምናም ወልዳ ነበር ዘንድሮም አጋተች፡፡
4. ነካካቸው ነካካቸው አትስጣቸው ጤና
ምን ጊዜም ደህና ሰው አልተባልንምና፡፡
5. አሞኛል አሞኛል ትከሻዬን ብቻ
የተሸከምኩበት የነገር ስልቻ፡፡
6. ተንኮለኛ ጊደር ከሰው በረት ገብታ
ነገሯን አመጣች ጎትታ ጎትታ፡፡
7. ሸውከኛን ወሬኛን ጅብ በላው አህያ መስሎት
ነገር ተሸክሞ ሲዞር አግኝቶት፡፡
8. ደሜ ፈልቶ ፈልቶ መልሼ ጠጣሁት
ካለ እኔ ወንድ የለም ሲል እየሰማሁት፡፡
9. ኧረ ጎራው ፈርሶ ጎራው ሲደለደል
አስቀድሞ ነበር ነገረኛን መግደል፡፡
10. አይጥ ብቅል በልታ እሷው ሰክራ እሷው በልታ
ያዙኝ ጋብዙኝ አለች ገዳይዋን ልትመታ፡፡
11. በሸሎ ታረሰ አሉ በጥቋቁር በሬ
ማሽላ ቢዘሩት ሆነ አሉ በርበሬ፡፡
12. አማን ነው ወይ ሀገሬ አማን ነው ወይ
ነገር የሚመጣ ከእነሱ አይደለም ወይ፡፡
13. አሳረኛ ገደል በሬ ያሳልፋል ዝንጀሮ ይጠልፋል
ጅል ያመጣው ነገር ለብዙ ይተርፋል፡

10.5 ቁጭትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. እኝኝ ይላል ብጉንጅ የያዘው ሰው

እኝኝስ የሚለው ነገር የገባው ሰው።
2. በድንጋይ ቢመታኝ መታሁት በኩበት
እንዳው አለ ጊዜ እንዳው አለ ወራት
ምን ያደርጋል ጉልበት።
3. ሴት በቅሎ ገዛሁ ከእናቷ ነጥዬ
ወንድ በቅሎ ከእንግዲህ አይገኝም ብዬ።
4. አባይ ሞልቶ ጣና ሞልቶ በደረቁ ላጨኝ
መላጨቱ ሳይሆን መደፈሩ ቆጨኝ።
5. አቃጠሉት አሉ ሸተተኝ አገሬ
አጠፋው ነበረ ወይ አለመኖሬ።
6. አባይ ታረሰ አሉ በጥቋቁር በሮች በጅራተ ፈንዛ
ምነው በእኛ ጊዜ ጠላታችን በዛ።
7. አወላውሌ እያወላወለ
ጠላቱን ሰደደው ነገ ዛሬ እያለ።

8. የላሚቷን ጥጃ ነብር በልቶባት

እንቧ እንቧ ትላለች እየነደዳት።
9. ዝዜን ጠቅለል ጠቅለል ከብቴን ነዳ ነዳ
እኔ እንኳን በቀድሬ ጠላቴን ልጎዳ።
10. ኧረ አገሬ ወሎ ሸንበቆው ማማሩ
ቆርጠው ቆርጠው ጣሉት ለማገር እያሉ።
11. አየር ላይ ነው ቤቱ ሰማይ ነው ወይ ቤቱ
የእኛ ጎጆ ፈርሶ የእሱ መሠራቱ።

1.2 ከነማን ተውዷል ከእነማን ተጋብቷል ብለው ሳይጠይቁ
ወርደው ደበደቡት እነ ልክ አያውቁ።
13. አትንኳቸው ሄደ ሄደ አትበሏቸው
እልህና ንዴት ቁጭት አለባቸው።
14. ወለቃ በረሃን ዝንብ ወረረው
የዓባይን በረሃ ዝንብ ወረረው
በሳንጃ የሚወጋ ዳኛ እንዳልነበረው።

10.6 ምክርን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ሰማይ ሲደማምን በሬ የሌለው ሰው
ረብሻ ሲነሳ ወንድም የሌለው ሰው
አይሄድም ወይ ዱብቲ ምን አልከሰከሰው።

2. አይቶ ነው ተችቶ ነው መውረድ
እያዩ ነው ቁልቁለቱን መውረድ
ይቸግር የለም ወይ ሬሳ መራመድ።።
3. ቢመታህ ዝም በለው ቢሰድብህ ዝም በለው
የእሱን መንከራተት ላንተ ሊያጋባ ነው።።
4. በቆሎ ቢዘሩ ጦጣው ዘነጠለው
ማሽላ ቢዘሩ ወፉ ጠረጠረው
እስኪ ተልባ ዝሩ የሸርታታ ቀን ነው።።
5. ጎበዝ ልንገራችሁ ጎበዝ እርሻ እረሱ
ካልሆነም መንኩሱ
እየወለዳችሁ ልጅ አታስለቅሱ።።
6. አገራችን ታሞ ተኝቶ ባልጋ ላይ
ወደ የት እንሄዳለን ሞት ሸረቱን ሳናይ።።
7.ያንበሳው ለማዳ ይውላል ከላም
ይህ አንጉል ኑሮ ያደርጋል ገራም።።
8. መሄድማ ቆቅም ትሄዳለች ተራራውን ዙራ
ምድር ስትጭር ነው ያጠቃት አሞራ።።
9. ገዴ ዙራ ዙራ እንቁላሏ ላይ
ቀን ያሳለፈ ሰው ሞኝ ይባላል ወይ።።
10. አትንኩት ያን በሬ እዛው ይቀመጥ
አያል ሰው ይፈጃል ሲገለባበጥ።።
11. በሬው እሱው አርሶ እሱው አበራየ
ከሰው ላይ አይደርስም ፖሊስ ጣቢያን ያየ።።
12. ዝናብ ሲዘናንብ በሬ የሌለው ሰው
አምባንሮ ሲኖር ወንድም የሌለው ሰው
አይሄድም ወይ ጎጆብ ምን አልከሰከሰው።።
13. ቢልክም ዝም በለው በስልክም ዝም በለው
የሱን መንገላታት ለእኛ ሊያጋባ ነው።።
14. ረጅም ዛፍ አይቶ ይሰቀላል ቀፎ
አውርድና ጣለው በረጅም ወጨፎ።።
15. አስረው ደበደቡት ያንበሳውን ጥጃ
ዛሬስ ደስ አላቸው የኋላውን እንጃ።።
16. ለምን በለው በለው ለምን ጣለው ጣለው
ይቸግር የለም ወይ ደም መላሽ እንዳለው።።
17. በሬው ሳበው ሳበው እንውጣው ገደሉን
የሰው ልጅ አይረባም ከረሳው በደሉን።።
18. ጦር ይምጣ ጦር ይምጣ ለምን ትላላችሁ
ጀግና ብርሌ ነው ታሰብራላችሁ።።
19. ተይ ስልሽ ስቆጣሽ ቧልታ እየመሰለሽ
ትግሬ ውሸማ እንጂ ባል አይሆንም ስልሽ።።

ለምን ታለቅሳለህ ወንዱ ልጅ እንደ ሴት ሁል ጊዜ ሁል ጊዜ
ወንዙን ሸገር በለው አለው የሰው ጊዜ።።
20. ዓባይ ሞልቶ ጣና ሞልቶ ይታያል ክርሰሱ
በፍቅርም ጠብ አለ እስኪ ዋና አትርሱ።።
ሸንብራዬ አፈራች እንግዲህ ልጠርጥር
ጅል እዳ ይገባል በጠገበ ቁጥር።።

21. አትንኩት ሲሏቸው እየነካኩት

የተኛውን በሬ ጎሽ አደረጉት።።
22. ምን ያስለቅሰሃል ሴት ይመስል ወንዱ
ውሃው ሞልቶ እንደሆን ተሻገር በግንዱ።።
23. በሉ እንበልና እንግባ ሀገራችን
እንደወጡ ቀሩ አይበል ጠላታችን።።
24. ወርደህ ተጋጠመው ሸበታሙን ደሬ
ከዚያው ታገኛለህ ወይፈንና በሬ።።

10.7 መከፋትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. እኛን ስለከፋን ብናንጎራጉር
እነዚህ ጥጋበኞች እንባል ጀመር።።
2. አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነው ወይ
ይህም ሠርቶ መብላት ጤና ላይሆን ነው ወይ።።
3. እኔስ መሄዴ ነው፤ እኔስ መጓዜ ነው፤ እዚች ግድም አልገኝ
እንደ እኔ የከፋው መንገደኛ ባገኝ።።
4. ዝንጆሮ ሆይ ሲሉት ይገባል ከገደል
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል።።
5. ቀበቶዬን ላጥብቅ ቁርጥ ነው ዘንድሮ
መሄድ ይሻለኛል ከማይረባ ኑሮ።።
6. ፍቀድልኝ ልምጣ ጫካውና ዱሩ
ወዳጅ ዘመዶቼ በእኔ ላይ ካሴሩ።።
7. አሞራው ተከፍቶ ዋ ሲል ሰማሁት
እንዳሻው እንዳይበር ጊዜው ከፍቶበት።።
8. ኧረ ተው አንተ ሰው ስሸሽ አታባርረኝ
ለአንተም ግፉ በዛ እኔንም መረረኝ።።
9. ንቡ ሄደ የወለደው ያውም የከበደው ከማር ቤቱ ከወለላ ቤቱ
እየኮረኮሩት እያረረ አንጀቱ።።
10. ቀበቶዬ አልቆብኝ ታጥቄ በልጥ
እኔ አልሆነልኝም ሥፍራ ልለውጥ።።
11. በሬውን አረዱት ከቀንበሩ ላይ
ላሚቱን አረዷት ከእንቦሳዋ ላይ

ሞፈሩን ፈለጡት ለሥጋ መጥበሻ
የእኛን ቤት ጉድ ያየ እስከ መጨረሻ።።
12. ላሚቱ እሳት ወልዳ አትልሰው ፈጃት
ያረባባ ነገር ያደርጋል እመጫት።።
13. አንድ ዓይና በሬና ከሰው ቤት ያለ ሰው
አይመሰገንም ጉልበቱን ጨረሰው።።
14. አንድ ወይፈን ነበረኝ እንደ እኔ የከፋው
የሆዴን ሳዋየው የጉንጩን ሳር ተፋው።።
15. ወይ ግደለኝ ወይ ሰው አስገድለኝ
በየደረስክበት ጉራህም ገደለኝ።።
16. አበድረኝ ቢሉት አባት ይሰለቻል
ወይ ለቆ መሄድ ወይ ራስን መቻል።።
17. በጥዋት ተነስቼ በሮቹን ጠምጄ ጅራፉን ሳነሳ
ለካስ መሬት የለም ኧረግ እናንተ ሆዬ።።
18. ነፋኝ ቀበተተኝ እስከ አንገቴ ድረስ
እንዳትገድለኝ ጀሊል የልቤን ሳላደርስ።።
19. አርግጥለሁና ደምና መግል
እንዳትገለኝ ጌታ ሳልገላገል።።
20. ገዴ ዙራ ዙራ እንቁላሏ ላይ
ቀን ያሳለፈ ሰው ጅል ሊባል ነው ወይ።።
21. የተጣደ ምጣድ ከኋላዬ ኑሮ
ለካ ጠላት ብቻ ሁኖለሁ ዘንድሮ።።
አርሰን እንዳንበላ የፊት ሰው ይዟታል
ሂደን እንዳንሠራ መንገዱ ተዘግቷል
እንዲንሞት ነው ወይ የተፈረደብን።።
22. በሬው ጥጃ ወልዶ ተኝቶ ይልሳል
ቢቸግር ነው እንጂ በደል መች ይረሳል።።
23. ብችለው ብችለው አንገቴ ደረሰ
እክ ብለው ወጣ ደም እየጎረሰ።።
የባህር ዳር ዳሩ ቁጠማው ለምለም
የጭቁኖች ደም ነው ዝናብ ጥሎ አይደለም።።
24. አገራችን ታሞ ባልጋ ላይ ተኝቷል
ሞት ሽረቱን ሳናይ ትተነው መጥተናል።።
25. ኧረ ጉድ አርግዤ ኧረ ጉድ ኧረ ጉድ
ባምጠው ባምጠው የማይወለድ።።
26. መራራው ቦረኔ ይሄዳል ርቆ
አዝመራውን ለከብት ሚስቱን ለሰው ለቆ።።
እንጀራ አለው ብለው አይነግሩም ለድሃ
ተሻግሮት ይሄዳል አርባ አራቱን ውሃ።።
27. ኧረ ድመቲቱን አይጢቱ በላቻት

እም ብላ ቀረች ቦታው ባይመቻት።።

28. ውሻና ዝንጆሮ ባንድ ላይ አደሩ
ቢቸግር ነው እንጂ ጓድም አልነበሩ።።

29. ሰማይ ሲደማምን ይወረዛል ገደል
ይዘገያል እንጂ አይረሳም በደል።።

30. ቆስቁሱበት ካልጋመ አይጋግርም
ወንድ ልጅ ካልከፋው ወንዝ አይሻገርም፡

31. እኔው ተበድዬ እኔው ካሳ ክሼ
እኔስ ማፍረሴ ነው መልሼ ከልሼ።።

32. ቀጣጠነ ሊጡ በጠባቡ አቡክቼው
እኔስ መሄዴ ነው ሁሉንም ታትቸው።።

33. አጎንብሼ ልሂድ እንደ ነሰረው ሰው
ጊዜ ያመጣውን ጊዜ እስኪመልሰው።።

34. ልኑር ብሎ ልደር ብሎ ከሰው
የነብርን ጉረሮ ፍየል ገብቶ ላሰው
ያንበሳን ጎፈሬ ጊደር ተንተራሰው
ይሄ ጊዜ ታሚል ጊዜውን መልሰው።።

35. ምን በልቼ ምን ጠጥቼ ልደልለው ሆዴን
ዛሬ ቢቀር ነገ አልተወው መሄዴን።።

36. የአምናን ቀን ታዘብኩት ዘንድሮን ጠላሁት ክርሞንም አልወድም
ሰው አንድ ጊዜ እንጂ ሁሌ አይሸወድም።።

37. ዓባይ ታረሰ አሉ በጥቂቁር በሬ
ማሽላ ቢዘሩት ሆነ አሉ በርበሬ።።

38. ምን አለ ድኩላው ቅጠለ በላው
ቅጠል በልቶ በልቶ ዱሩ ለተኛው

39. ዘንድሮ ጉልበቴ ምንኛ ዋለልኝ
አንገቴን ብደፋ ራሴን ቻለልኝ።።

40. አገሬ ወግዲ እረ እንደምን ነሽ
ክፉንም ደጉንም ያሳለፍኩብሽ።።

10.8 ያጋጠመ እክልን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ወዲያ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ተጣራ ወዲህ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ወይ አለው
ባናውቀው ነው እንጂ መዘዙ የእኛው ነው።።

2. አሞኛል ዘንድሮ ታመሙ እናንተም
ያንድ ሰው በሽታ ይበቃል ለሁሉም።።

3. በሮቹ ጥቂቁር ጅራታቸው ፈንዛ
አርሰን እንዳንበላ ጠላታችን በዛ።።

4. በሮቹን በሏቸው አቃኗቸው ይብሉ
አሳር አይደለም ወይ የምናየው ሁሉ።።

5. አገር ሞልቶ ቦታ ሞልቶ
እንዴት ሰው ይኖራል በቅርጫት ተደፍቶ፡፡

6. አምጡልኝ በሮቼን አርጂ ልብላቸው
ጉልበቴ ሳይደክም ሌባም ሳይነዳቸው፡፡
እንጀራ አለ ብለን የወረድንበት
ከሾተል ይብሳል የድናጋዩ ስለት፡፡
7. አቃጠሉት አሉ ዓባይ በረሃውን
አቃጠሉት አሉ ወለቃ ደኑን
አቃጠሉት አሉ የሹም በረሃውን
ከማይረባ ጎጆ የሚሻለውን፡፡
8. ነብር መንታ ወልዶ ላም ተራመደችው
ዐውቆ ዝም ቢላት ሞኝ አደረገችው፡፡
9. አንቺ ቡሬ ጊደር ቅቤሽ መና ቀረ
ቀድሞ አልተገፋ ወይ ቀድሞ አልተነጠረ፡፡
10 አልቀትና መጋኛ ያለበት መንደር
ጀግናም አይወጣበት ኮርማም አይዳብር፡፡

11. እንባጮ አድባር ሆኖ ዋርካዎች ተቆርጠው

ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆነው፡፡
ሁሉም አለሁ ሆነ አለመጠኑ
እኛም አውሬ እንሁን እናንተም አድኑ፡፡
12. የዘመኑ ተዓምር ሲሰሙት ያፈዛል
ውሃው ቁጭ ብሎ ድንጋዩ ይንዛል፡፡

10.9 ረዳት /ወገንን በተመለከተ

1. ወንድም የሌለው ሰው የሌለው አባሪ
እቆጡ ላይ ቀረ የዱላው ስባሪ፡፡
2. ሽንብራ ነው ወንድም ሽንብራ ነው
ሲሄድም ተጠርጥሮ ሲኖርም ጥላ ነው፡፡
3. ገዴ ዙራ ዙራ ከምድቧ ላይ
የሙሽራው ወንድም የሚል የለም ወይ፡፡
4. ቁጥቋጦ ቆጥቁጬ ቀርታኛለች ከሴ
እገልዬ አበሉ ተነስ በሥላሴ፡፡
5. ኧረ ተይ እናቴ ውለጅልኝ ወንድም
አገር ሴረኛ ነው አንድ ሰው አይወድም፡፡
6. ወንድም ያለውና የውሃ ዳር ዛፍ
አምሮበት ይኖራል አበባው ሳይረግፍ፡፡
7. ካምሳ ከሰላሳ ከሺህ ቢወለዱ
መጠቃት አይቀርም ብቻ ከወረዱ፡፡
8. ጅራተ ከባድ በሬ ዝናብ አይከለክልም

ሆሳ ባልንጀራ ከጭንቅ አያድንም፡፡

9. ሁለት ወንድማማች ወረዱ በእንብሱ
ወንድም የሌለው ሰው ገድለው ሊመለሱ፡፡

10. ሸንበቆ ቢረዝም ከጫፉ አያፈራ
ደግ ወንድም ያለው ሰው ሲናገር አይፈራ፡፡

11. አሞራው በሰማይ ይላል ወዬ ወዬ

ወንድም የሌለውን ሲገድሉት እያዬ፡፡

41. ተው በሉት ያን በሬ ድቡን አያፍርሰው
ይቀበርበታል ወንድም የሌለው ሰው፡፡

42. ኧረ ምን ያለው ነው ምን ያለው ተላላ
ወንድሙን ሰው ገድሎት አርሶ የሚበላ፡፡

43. ሲይዙት ቀላል ነው ወንድምና ብር
ሲጠፋ ነው እንጂ የሚያደናግር፡፡

11. የፉከራ ግጥም

11.1 ታታሪነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. በቀይ በሬ ገራንጉር አራሽ
በነጭ አህያ ማኛ አመላላሽ፡፡

2. አባቱ ነበር ጥይት መንዛሪ
ልጁ ደረሰ ዘንጋዳ ዘሪ፡፡

3. የበሮቹ ቁስ የእርሻው ደብተራ
አይመቀኝም የሰው ጎተራ፡፡

4. የመጋል ጌታ የውንሽፍሩ
የደበቅ ጌታ የውንሽፍሩ
ማዕበል የመታው ይመስላል ፈሩ፡፡

5. የእንትናዬ ልጅ የእንትና ውሻ
ከሥር ከሥሩ ያደገው በእርሻ፡፡

6. አባቱ ነበር ነጭ ጤፍ ዘሪ
ልጁ ደረሰ ሰርዶ መንዛሪ፡፡

7. ቲም ቲም ተደርጎ ይነፋል ወንፊት
አደርጋለሁ ባይ ገና ወደፊት
ገና ወደ ፊት ለሚመጣው ቀን
አልወጣለትም የእርሻው ሰቀቀን፡፡

8. ከፍ ከፍ ያለ ትልም ተላሚ
በጫላ በሬ ንሽ አባራሪ።
9. ማረስ ነው እንጂ ድሪቶ ለብሶ
መጣል ሐምሌ ጨለማ ለብሶ።
ደግሞ ከሐምሌ አለ መስከረም
ቢንጦለጦሉት የሚያቀምስ የለም።
10. ማረስ ነው እንጂ ሾከኬ መሬት
ገበያ ወጥቶ ሳህን ከመምረጥ።
11. ሰርዶ አራጋፊ እንደ ጨንራ
ሞፈሩ ወይራ ገበሬው መጫ
ማን ይለቀዋል እርፉ ቢንጫጫ።

11.2. ጀግንነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. ያርሳል በበጋ ያርማል በጉም
እሰው ጐተራ ጨርቅ አይዘረጋም።
2. ማረስ ነው እንጅ ከጋራ ጋራ
የበሬው ትንፋሽ ሰው እስኪጠራ።
3. የማረግ ጌታ አይልም ደርሶ
የሶረን ጌታ አይልም ደርሶ
በሬ ሲነዳ ድብ አንተርሶ።
4. ድብና ድቡን አደባላቂ
በቀጭን ሞፈር ምድር ሰንጣቂ
በሰፊ አውድማ ምርት አስጨናቂ።
5. ማረስ ነው እንጅ ዋጫ መንጥሮ
ቀይ ሴት በማየት አይሆንም ኑሮ።
6. ማረስ ነው እንጅ እድቡ ድረስ
ምራር መርገጥ ነው እስኪበጣጠስ።
7. የሶረን ጌታ የተራማጁ
የጅራፉ እንጨት የሚያምረው በእጁ።
8. በሮቹ ጥቁር ማረሻው ጥቁር
ሰርዶ አስጨናቂ እንደ ነፍሰ ጡር።

9. አራሽ ገበሬ እርፍ እስኪናጋ
ወፍጮውም ሳይቆም መስከረም ነጋ።
10. በጀገሎ ብሎ በቦሩ መላሽ
በቡላ አህያ ምርት አመላላሽ።
11. የእርሻው መድሃኒት የእርሻው ወንበዴ፤
እርፍ የሚያምርበት እንደ ጐራዴ
12. እስኪ እንመለስ ወደ እርሻ ቦታ
የአቶ እገሌ ልጅ የሽልም ጌታ
ያጨናነቀው ምርቱን በጎታ።

13. ሰኔ ግም ሲል ሐምሌ ሲያጓጓ
የሚጠመደው ከሽልም ጋራ።

14. የእርሻው ሰቀቀን የእርሻው ደብተራ
አሻግሮ አያይም የሰው ጎተራ።

15. ገዳይ በሀምሌ ዘንቦ ሲያባራ፤

አረም አራሚ ከሚስቱ ጋራ።

11.3 ጀግንነትን በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች

1. እክትት ጣቴን ደም ነካኝ
ዘወረዋራ ነው እንደ ባጥ ማገር
2. አሁን ማን ያውቃል የሆዱን ነገር።

እጥፍጥፍ ያለው እንደ መጫኛ

ካባቱ በቀር የለውም ዳኛ።
3. የለበሰው ልብስ የኮሰኮሰው
አሳር በሆዱ የጠነሰሰው።
4. ትከሻው ሰፊ እንደ ጨረቃ
የተረገጠው መሬቱ ነቃ
የተናገረው አንዱ የሚበቃ።

5. እክትት ትላለች ገደ

አሻግሮ ተኳሽ በረጅም ጓንዴ፡፡

6. ጎጃም ሠላሳ በጌምድር ሃምሳ

የያዘው ሽመል አለው ነቀርሳ፡፡

7. አጭር ቁመቱ

ጠባብ ደረቱ

ክትት ያለ አሞቱ

ትዕቢት ጉልበቱ

አልተገናኘም ከመድሃኒቱ፡፡

8. የያዘው ቆሌ ይወጠውጣል

እንደ ሀዘንተኛ ፊት ያስሚጥጣል፡፡

9. የለበሰው ጨርቅ የኮሰኮሰው

አሳር በሆዱ የጠነሰሰው፡፡

10. የሜቶች ዘር የሜቶች ቅልብ

በሰፋ ቆሌ የሚያቅለበልብ፡፡

11. አጭር ቁመቱ ወኔው ተራራ

የሚጋጠመው ከእነዚያ ጋራ፡፡

የሚጋጠመው ከወፍራም ጋራ፡፡

ምቀኛው ብዙ ከሳር ከቅጠል

አንዱን ሲበጥስ አንዱን ሲያቃጥል፡፡

12. አካለ ቀጭን ልበ ወጫቃ

የሚረጋግጥ ሰው እንደ ጭቃ፡፡

13. እክትት እጀን ደም ነካኝ

የቦረኖች ዘር የነአባ ጨካኝ፡፡

14 አብሽ ተዘርቶ አብሽ ነው ሽታው

አያስታውቅም የሰው በሽታው፡፡

15. የቦረኖች ዘር የወዲያኞቹ

መሸጋገሪያው መንገዱ ምቹ።።

16. እንኳን እናቱ የወለደችው

ጓደኛው ቀናች የወደደችው።።

17. እንኳን እንትና አይዞህ እያለኝ

እንዳውም ልጁ ጥጋበኛ ነኝ።።

18. እክትት እኔን ምን ነካኝ

በገዛ ቤቴ የሚያበሳጫኝ።።

እንደ ኮርማ በሬ የሚጀንነኝ።።

19. እጥፍጥፍ ያለው እንደ ጠብመንጃ

ያመለጠ እንደሁ መያዙንም እንጃ።።

20. የጎበዙ ልጅ የጎበዝ ወንድም

ሱሪ አስወጥቶ የሚያስገለድም።።

21. በዛ ቁልቁለት በዛ ደፋታ

ቆላ ተኩሶ ደጋ የሚመታ።።

22. ዘራፍ ተነስቶ ዘራፍ ሲታጠቅ

ወኔው አይራራ ልቡ አይጨነቅ።።

23. አሻግሮ እያየ ያንን ማዶ ጎራ

ልቡ አይደነግጥ ወኔው አይራራ።።

24. ዘራፍ አካኪ ዘራፍ

እምቢ እምቢ እምቢ እንጃ

ቀማ ቀማ አለኝ የሰው ጠብመንጃ።።

25. ዘራፍ ያቶ እገሌ ልጅ ትላንት የሞተው

ስሙ እንደ ድንጋይ የተጎለተው።።

26. በዛ ቁልቁለት በዛ ሸርታታ

ባንድ እጁ ቆመጥ ባንድ እጁ ቃታ።።

27. አልሞ ተኳሽ አነጣጣሪ

የቦረኖች ዘር ያሰኛል እሪ።።

28. በለው በለውና አገር ይዋሰው

በስንቱ ቂጣም ይጨነቃል ሰው።።

29. የደኑ በሬ የደኑ ሽታ

ራስ ይመታል እንደ በሽታ።።

30. እንጠጣው እንጂ ጠላውን በተዝካር
የምንሠራውን አንድ አምላክ ያውቃል።።

31. እዛም ቁጭ እዛም ጉልት
እንደ አራስ ነብር እንደ እመጫት።።

32. ወሎ ተወልዶ ወሎ ያደገው
ጎጃም ተወልዶ ጎጃም ያደገው
ጎንደር ተወልዶ ጎንደር ያደገው
እንደ አራስ ነብር ደም የለመደው።።

33. ትዕቢተኛ ሰው ትዕቢት ያነቀው
ወንዱን እንደ ሴት የሚያስጨንቀው
መቼ ይመለሳል ሳይደበላልቀው።።

34. እገልዬ እገሌ አይዞህ እያለው
እንዳውም ልጁ ትዕቢተኛ ነው።።

35. አላቅሙ ታጋይ አለ እኩያቱ
አዙሮ ደፊ በጭንቅላቱ።።

36. ይምጡ ይጠራቀሙ
ለሁላችንም እንዳጣቅሙ።።

37. ይሄዳል ጊዜ ከመሸ
በሰፋ ዱላ እየመነሸ።።

38. የያዘው ሰፋ እጁን የሞቀው
መች ይመለሳል ሳይደባልቀው።።

39. የክፉ ሰው ዘር የክፉ ብቅል
ፍርሃት በሆዱ የማይቀላቅል፡

40. አስታጥቁኝና አንገቱ ድረስ
ግንባር ግንባሩን ብየው ልመለስ።።

41. ብቻውን በቃይ እንደ ክትክታ
የሚዘነጠል የለውም መንታ።።

42. እንኳን አባቱ አይዞህ እያለው
እንኳን ወንድሙ አይዞህ እያለው

እንዳውም ልጁ ቀበጥባጣ ነው።።

43. የእገልዬ ልጅ ብለሽ ጠይቂ
ከቂጣሙ ጋር ሳትደበልቂ።።

44. እገሌ ብላ የወለደችው
አሞቱን ገልጣ በምን አየችው።።

45. የዓይናሜ ወዳጅ የቀይ ሳዱላ
ወንዝ አሻጋሪ በሰፋ ዱላ።።

46. መልከ ጥፍፉ ዝንጆሮ መሳይ
ሳቅ ሳቅ የሚለው አምባንሮ ሲያይ።።

47. የቀን አንበሳ የሌሊት ዘንዶ
የሚሸጋገር ገድሎ ተራምዶ።።

48. ልቡን ያመነ የማይጠራጠር
ሳይገድል አይመጣም በወጣ ቁጥር።።

49. ልጁ ትንሽ ነው ጠጠር የሚያክል
ሰንጥቆት መጣ መሃል ለመሃል።።

50. የደጋው ሳማ የቆላው ምች
ጀግና ሲጨነቅ የሚለው ከች።።

51. አይወረወር የእሳት አሎሎ
አይቆረጠም የድንጋይ ቆሎ
ያጅሬ ልቡ አይገኝ ቶሎ።።

52. የቅርጫት ሥጋ ዝንብ የወረረው
እምቢ አለኝ ልቤን ክልብሽ እያለው።።

53. እዚሁ ገድሎ እዚሁ ኗሪ
እንደ አንድ ጌታ እንደ አንድ ፈጣሪ።።

54. አሻግሮ እያየ ያንን ማዶ ጎራ
የተሸፈነው ልቡ በሞራ።።

55. ይሸሻል ተብሎ አይጠረጠር
ካሳቻ ቦታ ወርዶ የሚታጠር።።

56. ተው ትሞታለህ ሲለው አባቱ
ተው ትሞታለህ ስትለው እናቱ

አዙሮ ደፊ በጭንቅላቱ፡፡

57. ጎበዝ የጎበዝ ወንድም
እንበለው እንጂ መሸሽ አይወድም፡፡

58. እጥፍጥፍ ያለው እንደ ኩታ ልብስ
አተኳኮሱ አንጀት የሚያርስ፡፡

59. እስኪ ዝም በሉ አትንጫጩብኝ
የአቶ እገሌ ልጅ አመል አለብኝ፡፡

60. አመለ ውሻ መልኩ ምናምን
ከጠራው ሜዳ ውሃ የሚያስለምን፡፡

61. ያቶ እገሌ ልጅ ማለት ይሄ ነው
እንደ ኮርማ በሬ የተጀነነው፡፡

62. ወይፈኑ ወይፈኑ
የወይፈን ኩሩ
ያልተፈተሸ ያልታየ አመሉ፡፡

63. ሲከፋው ኗሪ የደላው መሳይ
ሳቅ ሳቅ የሚለው አምባንሮ ሲያይ፡፡

64. እገሌ ብለው ሲጣሩ
አለ ነው እንጂ የለም አትበሉ፡፡

65. እገሌ የሚሉት ይሄ ነው ለካ
ከትለሙ ጋር የተለካካ፡፡

66. እገሌ የሚሉት ገና አሁን መጣ
እንደ አራስ ነብር እየተቆጣ፡፡

67.በወዲያ ማዶ መንዝ ያማረው
ያገሩ ነገር እየቸገረው፡፡

68. መተኮስና መግደል ለብቻ
አርጎ አስቀራቸው ለመዛበቻ፡፡

69. የእገሌ ወንድም የእገሌ ታናሽ
ከመሃል ገብቶ በትለም አማሽ፡፡

70. የዛ የሰው ዘር የዛ ያንጣቆ
ደርሶ ይመኛል ሰው በጥልቆ፡፡

71. የያዘው ቆሌ በእጁ የሚደምቀው
መቼ ይመለሳል ሳይደባልቀው፡፡
72.ያሳረኛ ልጅ ያሳር ምሰሶ
ለወደደው ማር ለጠላው ኮሶ፡፡
73. ትዕቢተኛው ትዕቢት ያነቀው
ወኔው ባንገቱ የተናነቀው፡፡
74. ደጋ ተኩሶ ቆላ የሚመታ
እርሳሱ ጥቁር ባሩዱ መንታ፡፡
75. አገሩ ቆላ ውስጡ ጉራንጉር
በቀጭን ቆሌ የሚያደናግር፡፡
76. የጎበዞች ዘር የነብሰ በላ
አጥንቱን ለጸሐይ ደሙን ለአሞራ፡፡
77. ተመልከት ብሎ የሚተኩሰው
መሃል አገዳ የሚበጥሰው፡፡
78. ድኩላ ገዳይ ቀንዱ የዞረ
ነፍጠኛን ሁሉ ያደናገረ፡፡
79. ገዳይ ነፍጠኛ ከቤቱ በታች
አማቱ እያየች ሚስቱ እያወካች፡፡

12. የሆታ ቃላዊ ግጥሞች

12.1ትችትን በተመለከተ

1. ቆሌ ካማረው
ና በለው
ና በለው፡፡
የፈሳሜው ልጅ የፈራ ጊዜ
የሚስቱን ወዳጅ አደረገው ሚዜ፡፡
ለሴቶቹ /ለቆንጆዎቹ/ ይመስል አግድመት ቢሮጡ
ያንዳልጥ የለም ወይ ሳሩ ሰንበሌጡ፡፡
አንድ አልፎ አንድ አልፎ ይበሳል ቀንበር
የዱላው ለታ የት ሂደህ ነበር፡፡

ትመታ እንደሆን ምታ በእግርህ

እሾህም የለው የሚወጋህ፡፡

የሸግዬን ከንፈር ወልምጠህ ወልምጠህ፡፡

ወደየት ትሸሻለህ ደረትክን ገልብጠህ፡፡

2. አበባ መውዜር አበባ

ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ዋሾ

ሲሸሽ አየሁት ጌሾ ለጌሾ፡፡

ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ላዛ

ሲሸሽ አየሁት ታዛ ለታዛ፡፡

3. የለመደው መንሽ የለመደው

ሲሸሽ ይውልና እንደ ቀንዳም በሬ

እቤቱ ሲገባ ያበጃል ወሬ፡፡

12.2 ምርጫን በተመለከተ

1. ወይ ዞማ ዓለም ዓለም

ቆንጆ- ሳዶላ ሙቺ ሙቺ አፈሩ ይብላሽ

ትመርጫለሽ አሉ ቂሎና ጥንቅሽ፡፡

መለል ያለች ሎሚ መዋጮ የሌላት

ሐብታም በገንዘቡ ድሃ በዓይኑ በላት፡፡

2. ዞሜዋ ዞሜዋ ኧረ እንደምን አለሽ

አህም ህም ወይዞማ ዓለም ዓለም

ዞሜዋ ዞሜዋ ያገሬን ልጅ ትቺ የሰው አገር ሳድን

እንደከሳሁ ቀረሁ ጎኔ ሳይደነድን፡፡

ሽጌ ሙቺ ሙቺ ንዳድ ይግደልሽ

አትመርጪም አሉ ጭራና ጥንቅሽ፡፡

12.3 ጀግንነትን በተመለከተ

1. ድብክብክ ያለች ናት እንደ ጤፍ እብቅ

ፈረሱ ዳለች ጭራው ገብስማ

በለው በቡጢ ጨኸቱ እንዳይሰማ፡፡

ተባባሉና ውረድ እንውረድ

አቆላለፈው እንደ በግ ቀንድ፡፡

አሸኮበኮበ ሰንጋው እንደ ርኩም

አንተ ሰውዬ በአንተ አልደረስኩም፡፡

2. እምቢ አለ እምቢ አለ

እያጋመረ እያጋመረ፡፡

መች ተዋጋና

ያሻዋል ገና ያሻዋል ገና፡፡

ተልባ ሲቆሉት ይላል ሲጢጢ

ማሬው ጊንጥ አምባ አመለ ቅብጢ፡፡

ያሻዋል ገና

ረጅም ገደል አይወጣም ዘንዶ

ማሬው ጊጥ አምባ አለው በረዶ፡፡

እያት ሽመሌን ተመልከታት

ደምን እንደ ውሃ የማጠጣት‹‹

3. ያሆው ያሆው

ሰፋው ዘመተ

እያመረተ፡፡

እምቢ አለ እምቢ አለ

እያጋመረ፡፡

ያሆ ያሆ ቆሌ ላመረው

ና በለው ና በለው፡፡

አንድ አልፎ አንድ አልፎ ይበሳል ቀንበር

የዱላው ለታ የት ሂደህ ነበር፡፡

4. ነይ ዞሜ ነይ ዞሜ ነይ ዞሜ ባያሌው

ህም ህም ወይ ዞማ ዓለም ዓለም

ወይ ዞሜ ዓይነ ኩሌ በተራዘም ቆሌ አድርገው ገልል ገለል

መችም ሞት አይቀርም በጀርባ መንጋለል፡፡

5. አበባ መውዜር አበባ

እኔ እናቱ ነኝ ወይ ሲሸሸ የምወደው

በተራዘም ቆሌ ሳላንጎራድደው፡፡

አትለውም ወይ ባበደው ሰፋ

እንደወለደች እናቱ ትልፋ።

አረንዛው ለሚ የወረደበት

መሬቱ ጎድጉዶ ውሃ ሞላበት።

ዳለቻው ፈረስ ጭራው ገብስማ

በለው በጉሽም ድምጹ እንዳይሰማ።

6. ያሆ ያሆ

ያሆ ያሆ

ቆሌው ካለልኝ

እምቧ በይልኝ።

ያሆየመራጅ ወባ

አለው አበባ።

አንቺ ዓለም የማይል የለም።

አንቺ ዓለም ወባ

አለው አበባ።

በለው ጎበዝ በል ድንብል ድንብል

አይፈራም ሽመል።

ወይ ጎበዝ አይዞህ ጋሞቼ በሙናው ወባ

አለው አበባ።

ሰፋው ታማረው

ና በለው።

7. ዞሜ ነይ ዞሜ ነይ ዞሜ ነይ ዙር በዙር

ዞሜ ዙር በዙር

የአፋፍ ላይ ደደሆ ነፋስ የመለሳት

የቆሌው ወላፈን ይነዳል እንደ እሳት።

12.4 ፍቅርን በተመለከተ

1. ያሆ ያሆ

የለመደው ዘብ የለመደው

ሰማይ ለሰማይ ይሄዳል ገዴ

የለመደው መንሽ የለመደው

በአንገቱ ላድርግሽ እንደ ግማዴ።

የለመደው መንሽ የለመደው

ዘብ የለመደው

የድንጋይ ሥር ውሃ ይጠጣል በእፍኝ

ምነው ባላየሁሽ በቀረሽብኝ፡፡

2. ያሆ ያሆ

እምቢ አለ እምቢ አለ

እያጋመረ

ብሻው ደራ ልሂድ ብሻው መርሃቢቱ

መች እሰድሻለሁ ሳይሰማ ሞቱ፡፡

3. ያሆ ያሆ

የመራጅ ወባ

አለው አበባ፡፡

መች እንዲህ ነበር ቆንጆ መሳሙ

እንደ ቁጤማ እየዘመሙ፡፡

4. ጎበዝዬ ተው ጎበዝዋ ያሆው ያሆው

መች ተዋጋና

ያሻዋል ገና፡፡

ለእኔ ብለሺ

ነይ ኩብለሺ፡፡ ነይ ኩብለሺ፡፡

ዞሜ ነይ ዞሜ ነይ ዞሜ ነይ ዙር በዙር

አፋፍ ላይ ሲዘልቁ ይታያል ገደሉ

አሁን ምናለበት በአንቺ ቢጋደሉ፡፡

አባሪ ሦስት፡- ቃለ መጠይቅ

አጭር መግለጫ

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው በመገኘትዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ «የወሎ ቦረና ማኅበረሰብ ቃል ግጥሞች ዐውዳዊ ትንተና»በሚል ርእስ ለ3ኛ ዲግሪ ማሟያነት ለሚካሄደው ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች ባሉ አርሶ አደር ማኅበረሰቦች ዘንድ በሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ ለጥናቱ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ መረጃዎቹም ለትምህርት ዓላማ ብቻ የሚያገለግሉ እንጂ ከዚህ ውጭ ለሌላ ጉዳይ የማይውሉ መሆናቸውን በሐቅ እየገለጽኩ በእውነት ላይ የተመሰረቱ መረጃዎችን እንዲሰጡኝ በታላቅ አክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ሀ. የመረጃ ሰጪዎች አጭር ግለ ታሪክ

የመረጃ ሰጪ ስም ———————— ዕድሜ ————————ፆታ ———

ወረዳ ———————— ቀበሌ ----------

ለ. ለመረጃ ሰጪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. በቅድሚያ ስለ ህይወት ታሪክዎ ይንገሩኝ፡፡
2. የወረዳው ስም ለምን ቦረና፣ ወግዲ፣ ከለላ ተባለ?
3. የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ምን ይመስላል? ቆላ፣ ወይና ደጋ፣ ደጋ፣ ወይስ ሁሉም?
4. በወረዳዎ የሚገኙ የሰብል ዓይነቶችን፣ የቤትና የዱር እንስሳትን፣ ወንዞችን፣ ደንን፣ የህዝቡን የመተዳደሪያ ሁኔታ፣ ወዘተ. በዝርዝር ቢገልጹልኝ?
5. የወረዳውን አጠቃላይ ማኅበረ ባህላዊ ዳራ በተመለከተ የህዝቡን ብዛት፣ የሚነገረውን ቋንቋ፣ ሃይማኖትን፣ የጋብቻን እና የለቅሶን ሁኔታ፣ ወዘተ. ቢያብራሩልኝ?
6. አርሶ አደሮቹ በሃይማኖትም ሆነ በሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው?
7. ቃል ግጥሞቹ መቼ መቼ ነው የሚቀርቡት? በጋብቻ፣ በለቅሶ፣ በወቅታዊ ሁኔታ፣ በሥራ፣ በበዓላት፣ ወዘተ.
8. ለምንድን ነው ቃላዊ ግጥሞቹ የሚቀርቡት?
9. የት ነው ቃላዊ ግጥሞቹ የሚቀርቡት?

10. ማን ነው ቃላዊ ግጥሞቹን የሚያቀነቅነው (የሚያዜመው)?
11. ቃላዊ ግጥሞቹ በሚቀነቀኑበት ወቅት ታዳሚዎቹ ምን ዓይነት ቁሳቁሶችን ነው በአጃቢነት የሚጠቀሙት (የሚይዙት)?
12. ቃላዊ ግጥሞቹ በሚቀርቡበት ወቅት ምን ዓይነት ተግባራት ወይም ድርጊቶችና የአካል እንቅስቃሴዎች ይከወናሉ?
13. እስኪ እርስዎ የሚያውቋቸውን የቃል ግጥሞች ይንገሩኝ?
14. አሁን ያዜሙት ቃል ግጥም የራስዎ ነው ወይስ ከሌላ ሰው ሰምታችሁ ያጠናችሁት ነው?
15. በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ የሚዜሙት ቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ?
16. በእነዚህ ወቅቶች የምታዜሚቸው ግጥሞች ከሥራዎቹ ጋር ብቻ የተገናኙ ናቸው ወይስ ከሌላ ነገር ጋር?
17. በተለያዩ የሥራ ወቅቶችም ሆነ በሌሎች የምታዜሚቸው ቃል ግጥሞች ምን ምን ጥቅም አላቸው ይላሉ? ለሥራውም ሆነ ለእርስዎ?
18. የአርሶ አደሮችን ስም፣ ታታሪነት፣ ስንፍና፣ ባህርይ፣ የትውልድ ቦታ፣ ወዘተ. በማንሳት ቃላዊ ግጥሞችን ታዜማላችሁ? የእነዚህ ዓይነት ቃላዊ ግጥሞች ጠቀሜታ ምንድን ነው?
19. ማዳበሪያን፣ ኮምፖስትን (ብስባሽን)፣ አፈርን እና ውሃ ጥበቃን (እርከን ሥራን) እና ጸረ አረምን፣ ወዘተ. በተመለከተ በጥቅማቸውም ሆነ በጉዳታቸው ላይ የተነገሩ ቃል ግጥሞች ካሉ ይንገሩኝ?

    ሀ. ማዳበሪያን፣ ለ. ኮምፖስትን (ብስባሽን)፣

    ሐ. አፈርና ውሃ ጥበቃን (እርከን ሥራን) መ. ጸረ አረምን

    ሠ. ሌሎችንም
20. በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች ተበቺሳ ወይም ለፍጆሌ የሚባል ጨዋታ እንዳለ ሰምቻለሁ። ተበቺሳ ማለት ምን ማለት ነው? ለፍጆሌስ?
21. በእነዚህ ወቅቶች ወይም አጋጣሚዎች የሚዜሙትን ቃላዊ ግጥሞች (ዘፈኖችን) ቢነግሩኝ?
22. ልጃገረዶች ለየብቻ የምታዜሙት ቃል ግጥም በቡድን ሆናችሁ (እዋ አበባዬ እዋ አበባ) ከምትዘፍኑት ይለያል? ልዩነት ካለው ልዩነቱ ምንድን ነው?

23. በቦረና፣ በወግዲና በከለላ ወረዳዎች የከንፈር ወዳጅ እንዳለ ሰምቻለሁ። የከንፈር ወዳጅ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይከወናል?
24. የከንፈር ወዳጅ በቃላዊ ግጥም እንዴት ይገለጻል? መልክ፣ ቁመት፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ወዘተ. በቃል ግጥሞቹ ይቀነቀናሉ?
25. በሰርግ ዕለት የሚቀርቡትን ዘፈኖች ብትነግሩኝ?
26. በዕለት ሞትም ሆነ በመርዶ ወቅት ባሉ የለቅሶ ሥርዓቶች በሙሾ የሚደረደሩትን ቃላዊ ግጥሞች ቢነግሩኝ።
27. ለምን ዓላማና ምክንያት ነው ለውጥ የተደረገው? ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው ለውጡ የተከሠተው? በለውጡ አማካይነት የተገኙ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉ ወይ? ማኅበረሰቡ ለውጡን በአዎንታዊ ወይስ በአሉታዊ ነው የተመለከተው?

አባሪ አራት፡- ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች



ከፎቶግራፍና ከቪዲዮ ካሜራ ባለሙያ ጋር ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጉዞ ላይ እያለሁ፡፡



በ23/05/2012 ዓ.ም ከአቶ ሙሐመድ እንድሬ ጋር የተካሄደ ቃለመጠይቅ



በ21/05/2012 ዓ.ም በቀጥተኛ ተሳትፎ የበራይ ተግባር ሳከናውን



በ21/05/2012 ዓ.ም በቀጥተኛ ተሳትፎ የበራይ ተግባር እየተካሄደ ባለበት እለት ምሳ በጋራ በመመገብ ላይ እያለን



በ22/05/2012 ዓ.ም የተመረተው ጤፍ እየተሰፈረ ወደቤት ከመግባቱ በፊት በዐውድማ ላይ በጋራ አጉማስ በመመገብ ላይ እያለን



በ20/05/2012 ዓ.ም ከ፱ አለቃ አድማሱ ከበደ ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ



በ22/05/2012 ዓ.ም ከአቶ አብዱ ሙሐመድ ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ



በ20/05/2012 ዓ.ም ከወይዘሮ ከረን ሐሰን ጋር የተካሄደ ቃለመጠይቅ



በ22/05/2012 ዓ.ም ከአቶ ይማም አብዱ ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ